# የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡

## የንግድ ፡ ሕግ ።

## አንደኛ ፡ መጽሐፍ ። ገጽ ፡

## ስለ ፡ ነጋዴዎችና ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ መደብሮች ።

### አንቀጽ ፡ ፩ ።

### በነጋዴዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።


ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ የንግድ ፡ ሥራ ፡ በሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የሚፈጸም ፡ ሕግ ። . . ፩
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ነጋዴ ፡ ናቸው ፡ የሚባሉ ፡ ሰዎች ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፪
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ የንግድ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ችሎታ ፡ ስለሌላቸው ፡ ሰዎች ። . . . ፬
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ የተጋቡ ፡ ሰዎች ፡ ስለሚያደርጉት ፡ የንግድ ፡ ሥራ ። . . . . . . . . ፮
ምዕራፍ ፡ ፭ ፤ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ መብት ። . . . . . . . . . . . . . . ፯


### አንቀጽ ፡ ፪ ።

### የንግድ ፡ ረዳቶችና ፡ ወኪሎች ።


ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ንግድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፰
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፱
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ንግድ ፡ ተላላኪዎችና ፡ እንደራሴዎች ። . . . . . . . . . . . . . ፲
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ ስለ ፡ ንግድ ፡ ወኪሎች ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፪
ምዕራፍ ፡ ፭ ፤ ስለ ፡ ደላሎች ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፫
ምዕራፍ ፡ ፮ ፤ ስለ ፡ ባለኮሚሲዮኖች ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፬


### አንቀጽ ፡ ፫ ።

### ስለ ፡ ሒሳብ ።


ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ሒሳብ ፡ መያዝ ፡ ግዴታ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ። . . . . . . . . . . . . . . ፲፭
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ መያዝ ፡ ስለሚገባቸው ፡ መዛግብቶችና ፡ ሰነዶች ። . . . . . . . . . . ፲፮
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ የሒሳብ ፡ መዝገቦቹን ፡ ማስረጃ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። . . . . . . . . . . ፲፰
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ የሒሳብ ፡ አያያዝ ፡ ደንቦች ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፱


### አንቀጽ ፡ ፬ ።

### ስለ ፡ ንግድ ፡ መዝገብ ።


ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ንግድ ፡ መዝገብ ፡ አቋቋም ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፳፫
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ስለሚገቡ ፡ ጉዳዮች ። . . . . . . . . . . . . . . ፳፭
ክፍል ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፳፮

ገጽ ፡

ክፍል ፡ ፪ ፤ በመዝገብ ፡ ስለ ፡ መግባት ። ................ ፳፯
ክፍል ፡ ፫ ፤ የተመዘገበውን ፡ በመለዋወጥ ፡ ወይም ፡ በተጨ
ማሪ ፡ ስለሚደረግ ፡ የመመዝገብ ፡ ሥራ ። ............ ፳፱
ክፍል ፡ ፬ ፤ ከመዝገብ ፡ ስለ ፡ መሰረዝ ። ................ ፴፩
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ቅጣት ። ........................................ ፴፩
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ወንጀል ፡ ቅጣት ። ...................... ፴፩
ክፍል ፡ ፪ ፤ ፍትሐ ፡ ብሔራዊ ፡ ማስገደጃ ፡ (ቅጣት) ። ...... ፴፪
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ ፍጻሜ ፡ ድንጋጌዎች ። .............................. ፴፫

## አንቀጽ ፡ ፭ ።

## ስለ ፡ ንግድ ፡ መደብር ፡ (መድበል) ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። .......................... ፴፬
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ የንግድ ፡ መደብር ፡ የተቋቋመባቸው ፡ ነገሮች ። ............ ፴፭
ክፍል ፡ ፩ ፤ በንግድ ፡ መደብር ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኙ ፡ ነገሮች ። ፴፭
ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ደንበኛ ፡ ገበያተኛና ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ
ውድድር ። .................................. ፴፯
ክፍል ፡ ፫ ፤ ነጋዴ ፡ ስለሚነግድበት ፡ ስም ። ............ ፴፯
ክፍል ፡ ፬ ፤ የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሰሌዳ ። ................ ፴፰
ክፍል ፡ ፭ ፤ ስለ ፡ ኪራይ ፡ ውል ፡ መብት ። .............. ፴፱
ክፍል ፡ ፮ ፤ የኢንዱስትሪ ፤ የድርሰት ፤ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ የባለቤ
ትነት ፡ (ባለሀብትነት) ፡ መብቶች ፡ መጠበቂያ ። ... ፵
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ የንግድ ፡ መደብር ፡ (የንግድ ፡ መድበል)፡ ሽያጭ ። .......... ፵፩
ክፍል ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። ........................ ፵፩
ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ሽያጭ ፡ ጽሑፍ ፡ ሥርዐት ። ... ... ... .. ፵፩
ክፍል ፡ ፫ ፤ የሻጭ ፡ ግዴታዎች ። ............................ ፵፪
ክፍል ፡ ፬ ፤ የገዢው ፡ ግዴታዎች ። ........................ ፵፬
ክፍል ፡ ፭ ፤ ሽያጮቹን ፡ በማስታወቂያ ፡ ስለ ፡ ማስወጣትና ፡
ከሻጩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ያሏቸው ፡ መብቶች ። ፵፭
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ የንግዱን ፡ መደብር ፡ በዋስትና ፡ መያዣ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ። ፵፯
ክፍል ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። ........................ ፵፯
ክፍል ፡ ፪ ፤ ሻጩ ፡ በንግድ ፡ መደብር ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ ከሕግ ።
የሆነ ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ መብትና ፡ ውሉ ፡ እንዲ
ፈርስ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ። ........................ ፵፯
ክፍል ፡ ፫ ፤ በንግድ ፡ መደብር ፡ ላይ ፡ ስለሚደረገው ፡ የውል ፡
የዋስትና ፡ መያዣ ። ................................ ፵፱

ገጽ ፡

ክፍል ፡ ፱ ፡ በንግድ ፡ መደብር ፡ ላይ ፡ የሚደረጉትን ፡ የዋስትና፡ መያዣዎችን፡ ስለ፡ማስመዝገብ ። ......... ፵፱

ክፍል ፡ ፲ ፡ የዋስትና ፡ መያዣው ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ዎች ፡ በንግድ ፡ መደብሩ ፡ ላይ ፡ ያሏቸው ፡ መብቶች ። ፶፩

ምዕራፍ ፡ ፭ ፡ የንግድ ፡ መደብርን ፡ ስለ ፡ ማከራየት ። .................... ፶፫

ምዕራፍ ፡ ፮ ፡ የማኅበረተኛነት ፡ ድርሻ ፡ መዋጮ ፡ አድርጎ ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ መደብርን ፡ ለማኅበር ፡ ስለ ፡ ማግባት ። ................ ፶፮

ሁለተኛ ፡ መጽሐፍ ።

ስለ ፡ ንግድ ፡ ማኅበሮች ።

አንቀጽ ፡ ፩ ።

ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። ..................... ፶፯

አንቀጽ ፡ ፪ ።

ስለ ፡ ተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ............................... ፷፩

ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ስለ ፡ መዋጮ ። ............................... ፷፩

ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ የማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ። ..................... ፷፪

ምዕራፍ ፡ ፬ ፡ የማኅበረተኞች ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ። ............... ፷፬

ምዕራፍ ፡ ፭ ፡ ማኅበሩ ፡ ከሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጋራ ፡ ስላለው ፡ ግንኙነት ። ፷፯

ምዕራፍ ፡ ፮ ፡ ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ መፍረስና ፡ የሒሳብ ፡ መጣራት ። ............. ፷፰

አንቀጽ ፡ ፫ ።

የእሽሙር ፡ ማኅበር ። ..................... ፸፩

አንቀጽ ፡ ፬ ።

የኅብረት ፡ ሽርክና ፡ ማኅበር ። ................ ፸፫

አንቀጽ ፡ ፭ ።

ሁለት ፡ ዐይነት ፡ አላፊነት ፡ ያለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ። (ኮማንዲት) ፡ ፸፯

አንቀጽ ፡ ፮ ።

የአክሲዮን ፡ ማኅበር ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። ............................ ፹

ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ የማኅበሩ ፡ አቋቋም ። ................................ ፹፪

ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ስለ፡አክሲዮኖችና፡ስለ፡ባለአክሲዮኖች፡መብትና፡ግዴታዎች። ፹፯

ገጽ ፡

ምዕራፍ ፡ ፱ ፤ ስለ ፡ አስተዳዳሪዎች ፤ ሒሳብ ፡ አጣሪዎችና ፡ የባለ ፡ አክሲዮኖች ፡ ጉባኤ ። ........ ፺፭
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ። ........ ፺፭
ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ተቈጣጣሪዎች ። ........ ፻፩
ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ጉባኤ ። ........ ፻፲
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ፤ አጠቃላይ ፡ ድንጋጌዎች ። ........ ፻፲
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ፤ ደንበኛ ፡ ጉባኤ ። ........ ፻፲፰
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ድንገተኛ ፡ ጉባኤዎች ። ........ ፻፳
ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፬ ፤ ልዩ ፡ ጉባኤዎች ። ........ ፻፳፩
ምዕራፍ ፡ ፲ ፤ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ። ........ ፻፳፩
ምዕራፍ ፡ ፲፩ ፤ የማኅበር ፡ ሒሳቦች ። ........ ፻፳፰
ምዕራፍ ፡ ፲፪ ፤ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍና ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረገው ፡ መለዋወጥ ። ........ ፻፴፫
ምዕራፍ ፡ ፲፫ ፤ ስለ ፡ ማኅበር ፡ መፍረስና ፡ ስለ ፡ ሒሳብ ፡ ማጣራት ። ........ ፻፵፪

አንቀጽ ፡ ፯ ።

የተወሰነ ፡ ኣላፊነት ፡ ስላላቸው ፡ የግል ፡ ማኅበሮች ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎችና ፡ የማኅበሩ ፡ አቋቋም ። ........ ፻፵፯
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ አክሲዮኖች ። ........ ፻፶
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ የማኅበሩ ፡ አደረጃጀት ። ........ ፻፶፩
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ የማኅበሩ ፡ ሒሳቦች ። ........ ፻፶፭
ምዕራፍ ፡ ፭ ፤ የማኅበሩ ፡ መፍረስ ። ........ ፻፶፰

አንቀጽ ፡ ፰ ።

የማኅበሮች ፡ መለዋወጥና ፡ መቀላቀል ። ........ ፻፶፱

አንቀጽ ፡ ፱ ።

በውጭ ፡ አገር ፡ የተቋቋሙ ፡ ወይም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የሚሠሩ ፡ ማኅበሮች ፡ ፻፷

ሦስተኛ ፡ መጽሐፍ ።

ስለ ፡ ማጓጓዝ ፡ (ማመላለስ) ፡ ሥራና ፡ ስለ ፡ ኢንሹራንስ ።

አንቀጽ ፡ ፩ ።

በየብስ ፡ ስለሚደረግ ፡ የማጓጓዝ ፡ ሥራ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። ........ ፻፷፪
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ የማጓጓዝ ፡ (የማመላለሻ) ፡ ሰነድ ። ........ ፻፷፫
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ መንገደኞች ፡ ቲኬት ። ........ ፻፷፫
ክፍል ፡ ፪ ፤ የጓዝ ፡ ቲኬት ። ........ ፻፷፫
ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ዕቃዎች ፡ የማጓጓዣ ፡ ሰነድ ። ........ ፻፷፬

ገጽ ፡

ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ መጓጓዝ ፡ በሚደረገው ፡ ውል ፡ የተዋዋዮቹ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ። ........ ፪፷፮
ክፍል ፡ ፩ ፤ ዕቃዎቹን ፡ የላከውና ፡ የተቀባይ ፡ ሰው ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ። ........ ፪፷፮
ክፍል ፡ ፪፤ ስለ ፡ ዕቃዎችና፡ ስለ፡ ተመዘገቡ፡ ጓዞች ፡ የአጓጓዥ ፡ ግዴታዎች ። ........ ፪፷፯
ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ሰው ፡ ማጓጓዝ ፡ ውል ፡ የተዋዋዮቹ ፡ ግዴታዎች ። ........ ፪፷፰
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ የአጓዥ ፡ አላፊነት ። ........ ፪፷፰
ምዕራፍ ፡ ፭ ፤ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ መክሰስ ። ........ ፪፸

## አንቀጽ ፡ ፪ ።

## የአየር ፡ ጕዞ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌ ። ........ ፪፸፩
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ማጓጓዣ ፡ ሰነዶች ። ........ ፪፸፪
ክፍል ፡ ፩ ፤ የመንገደኛ ፡ ቲኬት ። ........ ፪፸፪
ክፍል ፡ ፪ ፤ የጓዝ ፡ ቲኬት ። ........ ፪፸፫
ክፍል ፡ ፫ ፤ የአየር ፡ ማጓዣ ፡ ሰነድ ። ........ ፪፸፫
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ የላኪና ፡ የተቀባይ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ። ........ ፪፸፮
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ የአጓዥ ፡ ኀላፊነት ። ........ ፪፸፰
ምዕራፍ ፡ ፭ ፤ ባንዳንድ ፡ ዐይነት ፡ መጓጓዣዎች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑ ፡ ድንጋጌዎች ። ........ ፪፹፪

## አንቀጽ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ኢንሹራንስ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ውሳኔዎች ። ........ ፪፹፩
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ለሆኑ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ማኅበሮች ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑ ፡ ድንጋጌዎች ። ........ ፪፹፬
ክፍል ፡ ፩ ፤ የኢንሹራንስ ፡ ፖሊሲ ፡ ውል ። ........ ፪፹፬
ክፍል ፡ ፪ ፤ የተዋዋዮቹ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ። ........ ፪፹፮
ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ይርጋ ። ........ ፪፺
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ኢንሹራንስ ። ........ ፪፺
ክፍል ፡ ፩ ፤ የዕቃዎች ፡ ኢንሹራንስ ። ........ ፪፺
ክፍል ፡ ፪ ፤ የኀላፊነት ፡ ኢንሹራንስ ። ........ ፪፺፫

ገጽ ፡

ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ የሰዎች ፡ ኢንሹራንስ ። ........ ፪፻፺፩
ክፍል ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። ........ ፪፻፺፩
ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ሕይወት ፡ ኢንሹራንስ ። ........ ፪፻፺፩
ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ አካል ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሕመም ፡ የሚደረግ ፡ ኢንሹራንስ ። ........ ፪፻፺፱

አንቀጽ ፡ ፬ ።

ስለ ፡ ውርርዶችና ፡ ስለ ፡ ኪሣራ ፡ ጨዋታ ። ፪፻፺፱

አራተኛ ፡ መጽሐፍ ።

የሚተላለፉ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶችና ፡ የባንክ ፡ ሥራዎች ፡ ሕግ ።

አንቀጽ ፡ ፩ ።

ጠቅላላ ፡ ውሳኔዎች ። ........ ፫፻

አንቀጽ ፡ ፪ ።

የንግድ ፡ ወረቀቶች ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ጠቅላላ ፡ ውሳኔዎች ። ........ ፫፻፫
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ሐዋላ፡ ወረቀቶች ። ........ ፫፻፭
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ አጻጻፍና ፡ ፎርም ። ........ ፫፻፭
ክፍል ፡ ፪ ፤ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ። ........ ፫፻፮
ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ እሺታ ። ........ ፫፻፲፩
ክፍል ፡ ፬ ፤ ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ማለት ፡ (አባል) ። ፫፻፲፬
ክፍል ፡ ፭ ፤ ለመክፈል ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ። ........ ፫፻፲፭
ክፍል ፡ ፮ ፤ ስለ ፡ አከፋፈል ። ........ ፫፻፲፯
ክፍል ፡ ፯ ፤ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ እሺ ፡ ባልተባለና ፡ ባልተ ክፈለ ፡ ጊዜ ፡ አቤቱታዎችን ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ። ፫፻፲፰
ክፍል ፡ ፰ ፤ ስለመክፈል ፡ ጣልቃ ፡ ስለ ፡ መግባት ። ........ ፫፻፳፰
ክፍል ፡ ፱ ፤ ተባዝቶ ፡ ስለ ፡ ተጻፈና ፡ ስለ ፡ ግልባጮች ። ፫፻፴
ክፍል ፡ ፲ ፤ ስለ ፡ መለዋወጥ ። ........ ፫፻፴፪
ክፍል ፡ ፲፩ ፤ ስለ ፡ ይርጋ ። ........ ፫፻፴፪
ክፍል ፡ ፲፪ ፤ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። ........ ፫፻፴፫
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ የተስፋ ፡ (ለመክፈል ፡ ቃል ፡ የሚሰጥበት ፡) ወረቀት ። ፫፻፴፬
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ ስለ ፡ ቼክ ። ........ ፫፻፴፮
ክፍል ፡ ፩ ፤ ስለ ፡ ቼክ ፡ አጻጻፍና ፡ ሥርዐት ፡ (ፎርም ። ፫፻፴፮
ክፍል ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ማስተላለፍ ። ........ ፫፻፴፱

ገጽ ፤

ክፍል ፡ ፫ ፤ ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ስለ ፡ ማለት ፡ (አባል) ። ፪፻፹፪
ክፍል ፡ ፬ ፤ ቼኩን ፡ ስለ ፡ ማቅረብና ፡ ስለ ፡ መክፈል ። ፪፻፹፪
ክፍል ፡ ፭ ፤ የስርዝ ፡ ምልክት ፡ ያለበት ፡ ቼክና ፡ ከሒሳብ ፡
ውስጥ ፡ የሚገባ ፡ ቼክ ። ...................... ፪፻፹፬
ክፍል ፡ ፮ ፤ ሳይከፈል ፡ በመቅረቱ ፡ አቤቱታ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ፡ ፪፻፹፮
ክፍል ፡ ፯ ፤ አንዱን ፡ ቼክ ፡ አባዝቶ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ። ....... ፪፻፺
ክፍል ፡ ፰ ፤ ስለ ፡ መለዋወጥ ። ...................... ፪፻፺
ክፍል ፡ ፱ ፤ ስለ ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ። ...................... ፪፻፺፩
ክፍል ፡ ፲ ፤ ጠቅላላ ፡ ውሳኔዎች ። ...................... ፪፻፺፩
ምዕራፍ ፡ ፭ ፤ የመንገድ ፡ ቼክ ። ...................... ፪፻፺፪
ምዕራፍ ፡ ፮ ፤ የመክፈል ፡ እንቢታን ፡ ስለማስታወቅ ። ...................... ፪፻፺፫

## አንቀጽ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ባንክ ፡ ሥራዎች ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ለባንክ ፡ የሚሰጡ ፡ አደራዎች ። ...................... ፪፻፺፬
ክፍል ፡ ፩ ፤ ገንዘብ ፡ በአደራ ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥ ። ...................... ፪፻፺፬
ክፍል ፡ ፪ ፤ በባንክ ፡ ሒሳብን ፡ ስለ ፡ ማዘዋወር ። ...................... ፪፻፺፮
ክፍል ፡ ፫ ፤ ሰነዶችን ፡ በአደራ ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥ ። ...................... ፪፻፺፰
ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ስለ ፡ ነገዝና ፡ ኪራይ ። ...................... ፪፻፺፱
ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ውል ። ...................... ፫፻
ክፍል ፡ ፩ ፤ ትርጓሜ ፤ የተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ሁኔታዎችና ፡
የሚቈይበት ፡ ጊዜ ። ...................... ፫፻
ክፍል ፡ ፪ ፤ የተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ውጤቶች ። ...................... ፫፻፪
ክፍል ፡ ፫ ፤ በተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ በቅናሽ ፡ የገቡት ፡ የንግድ ፡
ሰነዶች ፡ ገቢ ፡ በተደረጉ ፡ ጊዜ ፡ የሰጪው ፡ መክሠር ፡
የሚያስገኘው ፡ ውጤት ። ...................... ፫፻፬
ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ ስለ ፡ ቅናሽ ። ...................... ፫፻፭
ምዕራፍ ፡ ፭ ፤ ብድር ፡ ስለሚያሰጡ ፡ ግንኙነቶች ፡ (ክሬዲ) ...................... ፫፻፯
ክፍል ፡ ፩ ፤ የብድር ፡ መከፈት ፡ ...................... ፫፻፯
ክፍል ፡ ፪ ፤ ሰነድ ፡ አሲዞ ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መበደር ። ....... ፫፻፯
ክፍል ፡ ፫ ፤ ስለ ፡ ሰነዶቹ ፡ መያዣነት ። ...................... ፫፻፰
ክፍል ፡ ፬ ፤ በሰነድ ፡ ስለሚሰጡ ፡ ብድሮች ። (ክሬዲ) ፡ ፫፻፱

ገጽ ፡

አምስተኛ ፡ መጽሐፍ ።

የኪሣራና ፡ የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ።

አንቀጽ ፡ ፩ ።

ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። ........ ፪፻፷፱

አንቀጽ ፡ ፪ ።

ስለ ፡ መክሠር ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ስለ ፡ መክሠር ፡ የሚሰጡ ፡ ፍርዶች ። ........ ፪፻፸፫
ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ የመክሠርን ፡ ሥራ ፡ የሚያስፈጽሙ ፡ ሰዎች ። ........ ፪፻፸፯
ክፍል ፡ ፩ ፡ ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ። ........ ፪፻፸፯
ክፍል ፡ ፪ ፡ የመክሠር ፡ መርማሪ ፡ ዳኛ ። ........ ፪፻፸፰
ክፍል ፡ ፫ ፡ የከሠረው ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎች ። ........ ፪፻፸፱
ክፍል ፡ ፬ ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ኮሚቴ ። ........ ፪፻፹፪
ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ የአጠባበቅ ፡ ሥራዎች ። ........ ፪፻፹፫
ክፍል ፡ ፩ ፡ የአጠባበቅ ፡ ውሳኔዎች ። ........ ፪፻፹፫
ክፍል ፡ ፪ ፡ ስለ ፡ ማሸግ ። ........ ፪፻፹፬
ክፍል ፡ ፫ ፡ የዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ። ........ ፪፻፹፮
ምዕራፍ ፡ ፬ ፡ መክሠርን ፡ የሚያስታውቅ ፡ ፍርድ ፡ የሚያስከትላቸው ፡ ውጤቶች ። ........ ፪፻፹፯
ክፍል ፡ ፩ ፡ በባለዕዳው ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ውጤቶች ። ........ ፪፻፹፯
ክፍል ፡ ፪ ፡ የባለዕዳውን ፡ ንብረቶች ፡ ስለ ፡ ማስተዳደር ። ........ ፪፻፺
ምዕራፍ ፡ ፭ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ ሰነዶችን ፡ ስለ ፡ መመርመር ። ........ ፪፻፺፫
ክፍል ፡ ፩ ፡ ስለ ፡ ምርመራው ፡ አሠራር ። ........ ፪፻፺፫
ክፍል ፡ ፪ ፡ ስለ ፡ ጋራ ፡ ተገዳጆችና ፡ ስለ ፡ ዋሶች ። ........ ፪፻፺፯
ክፍል ፡ ፫ ፡ ከንግድ ፡ መደብር ፡ ውስጥ ፡ ባልሆን ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የመያዣ ፡ ዋስትናዎች ፡ ያሏቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መብት ። ........ ፪፻፺፰
ክፍል ፡ ፬ ፡ በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ የመያዣና ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ። ........ ፪፻፺፱
ክፍል ፡ ፭ ፡ በንግዱ ፡ መደብር ፡ ላይ ፡ መያዣ ፡ ያላቸው ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መብት ። ........ ፫፻
ክፍል ፡ ፮ ፡ በመፋለም ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ። ........ ፫፻፩
ምዕራፍ ፡ ፮ ፡ ስለ ፡ ኪሣራው ፡ አሠራር ፡ የሚደረግ ፡ ዘዴ ። ........ ፫፻፫
ክፍል ፡ ፩ ፡ ስምምነት ። ........ ፫፻፫

ገጽ ፡


ክፍል ፡ ፪ ፤ በግዴታ ፡ የሚሆን ፡ የኅብረት ፡ ማጣራት ። ........ ፫፻፲

ምዕራፍ ፡ ፯ ፤ የመክሠሩ ፡ ሥራ ፡ መዘጋት ። ........................ ፫፻፲፫

አንቀጽ ፡ ፫ ።

የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ። ..................፫፻፲፭

አንቀጽ ፡ ፬ ።

ስለ ፡ ማኅበሮች ፡ መክሠርና ፡ የመጠበቂያ ፡ ስምምነቶች ፡ የሚጸኑ ፡

ልዩ ፡ ውሳኔዎች ። ................ ፫፻፳፭

አንቀጽ ፡ ፭ ።

አጭር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ። ................ ፫፻፳፱

ስድስተኛ ፡ መጽሐፍ ።

መሸጋገሪያ ፡ ሕግ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ። ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ። .............................. ፫፻፴

ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ነጋዴዎች ፤ ንግዶችና ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ። ............. ፫፻፴፩

ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ የገንዘብ ፡ ሰነዶችና ፡ የባንክ ፡ ሥራዎች ። .............. ፫፻፴፪

ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ ኪሣራ ። ........................................ ፫፻፴፫

| | |
|---|---|
| ዐሥራ ዘጠነኛ ዓመት<br>ቁጥር ፫ ።<br>19th Year No. 3 | አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳፯ ቀን<br>፲፱፻፶፪ ዓ. ም.<br>Addis Ababa 5th May 1960 |


የ ኢ ት ዮ ጵ ያ ን ጉ ሠ ነ ገ ሥ ት መ ን ግ ሥ ት

# ነጋሪት ጋዜጣ ።

በ ተ ለ ይ የ ወ ጣ

# NEGARIT GAZETA

*Gazette Extraordinary*

| | | |
|---|---|---|
| ዋጋ | በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በጽሕፈት ሚኒስቴር ተጠባባቂነት የቆመ ። | ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይታተማል ።<br>የፖስታ ሣጥን ቊ. 137 |


## በአዋጅ ቁጥር ፻፷፮/፲፱፻፶፪ ዓ. ም. የወጣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የንግድ ሕግ ።

## COMMERCIAL CODE OF THE EMPIRE OF ETHIOPIA

## PROCLAMATION No. 166 OF 1960

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡
በሠላሳ ፡ አንደኛው ፡ ዓመተ ፡ መንግሥት ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡
ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ታተመ ።

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

# መቅድም ።

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ የምንገኝበት ፡ ዘመናዊ ፡ ዓለም ፡ ማንኛው ም ፡ ሕዝብ ፡ ለንግዱ ፡ ሥራ ፡ አቋምና ፡ ዋስትና ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ ነገሮች ፡ የሚረጋ ጡበት ፡ ጽኑ ፡ የሕግ ፡ መሠረት ፡ ከሌለው ፡ ንግዱንና ፡ ኤኮኖሚውን ፡ የማስፋፋት ፡ ተ ስፋ ፡ ሊኖረው ፡ አይ ችልም ። በዘመነ ፡ መንግሥታችን ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ያወጣናቸው ፡ የኪዛራና ፡ የን ግድ ፡ ማኅበር ፡ ሕጎች ፡ በቀድሞው ፡ ጊዜ ፡ ለንግድና ፡ ለእንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡ ሲያገለ ግሉ ፡ ከቈዩ ፡ በኋላ ፡ ዛሬ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለደረሰችበት ፡ የንግድ ፡ መሻሻል ፡ ደረጃ ፡ በቂ ፡ አልሆኑም ፤ ንግድ ፡ በመስፋፋቱና ፡ የኢትዮጵያና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ኩባንያዎችም ፡ መቋቋምና ፡ መመዝገባቸው ፡ እንደመብዛቱ ፡ መጠን ፡ ባለፉት ፡ ጥቂት ፡ ዘመናትም ፡ ውስጥ ፡ የንግድ ፡ ሥራዎች ፡ የሚፈጸሙበት ፡ ዘዴ ፡ አስቸጋሪ ፡ እየሆነ ፡ ሄዱዋል ።

የንግድን ፡ ድርጅቶች ፡ አቋምና ፡ ተግባር ፡ የሚደነግግ ፡ ዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ ማው ጣት ፡ ንግድን ፡ በበለጠ ፡ ለማሳደግ ፡ የሚረዳ ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ እኛ ፡ ያቋቋም ነው ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ጉባኤያችን ፡ ለዛሬው ፡ ጊዜ ፡ የሚያገለግልና ፡ ለወደፊትም ፡ ለዚሁ ፡ ሕግ ፡ መሻሻል ፡ ጠንካራ ፡ መሠረት ፡ የሚሆነውን ፡ ዘመናዊ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ አድርገን ፡ የንግድ ፡ ሕጎቻችን ፡ በአንድነት ፡ ተጠቃለው ፡ እንዲስፋፉ ፡ ስናደርግ ፤ ንግድ ፡ በጠቅላላውና ፡ በተለይም ፡ በሰውና ፡ በዕቃ ፡ ማጓጓዣ ፡ ረገድ ፡ ያለው ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ባለፉት ፡ ዐሥር ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ እጅግ ፡ ስለተስፋፋ ፡ ይህ ፡

የንግድ ፡ መቈጣጠሪያ ፡ ሕግ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ አዘናል ። እንዲሁም፡ የውጭና ፡ የውስጥ ፡ ንግዳችን ፡ በብለጠ ፡ የተስፋፋ ፡ መሆኑን ፡ በመመልከት ፡ የገንዘብ፡ ሰነዶችና ፡ የባንክ ፡ ሥራዎች ፡ ሕግ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ ማድ ረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ አግኝተነዋል ።

ይህ ፡ ዛሬ ፡ የምናውጀው ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ እነዚህን ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ፡ የያዘና ፡ በኢትዮጵያ ፡ የጥንት ፡ ሕጎችና ፡ ልማዶች ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሆኖ ፡ የሌሎ ችን ፡ ታላላቅ ፡ የንግድ ፡ አገሮች ፡ ሕግ ፡ በመጠቀስ ፡ ተስፋፍቷል ። ይህ ፡ ሕግ ፡ የተወ ደደውን ፡ ሕዝባችንን ፡ ተስፋ ፡ የሚያሟላና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኤኮኖሚ ፡ በቀላሉና፡ በሚ ገባ ፡ ሁኔታ ፡ ለማሻሻል ፡ እንደሚረዳ ፡ እናምናለን ። ፓርላሜንታችን ፡ በዝርዝር ፡ የተ መለከቱትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ በጥንቃቄና ፡ በትዕግሥት ፡ አጥንቶ ፡ ያጸደቀው፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ለአገራችን ፡ ፍላጎትና ፡ ከሌላ ፡ አገሮች ፡ መጥተው ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታ ችን ፡ የንግድ ፡ ጥቅም ፡ ተካፋይ ፡ ለሆኑት ፡ ሰዎችና ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶችም ፡ ተስማሚ፡ ሆኖ ፡ አግኝተነዋል ።

እኛም ፡ ሕጎቻችንን ፡ በማውጣት ፡ የፈጸምነው ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ ሁሉን ፡ በሚ ችል ፡ እግዚአብሔር ፡ አሠሪነት ፡ መሆኑንና ፡ የዚህም ፡ ሥራ ፡ ፍሬ ፡ ለማንኛውም ፡ አገር ፡ እድገትና ፡ ኑሮ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ኢንተርናሰዮናል ፡ ፍትሕ ፡ አጕልቶ ፡ እንደሚያሳይ ፡ እናምናለን ።

በነገሥን ፡ በሠላሳ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ ዛሬ ፡ ሚያዝያ ፡ ሐያ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ዐሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ሁለት ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ተጻፈ ።

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
ንጉሠ ፡ ነገሥት ።

ቍጥር ፡ ፩፻፷፮/ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡

የ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የንግድ ፡ ሕግ ።

# ዐ ዋ ጅ ፡፡

ሞዓ ፡ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡

ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛታችን ፡ በንግድ ፡ ረገድ ፡ በተደረገው ፡ እርምጃ ፡ አዲስ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ማወጅ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ አገኘነው ፤

በእኛ ፡ መሪነት ፡ ይህ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ እንዲዘጋጅ ፡ አድርገን ፡ የሕግ ፡ መወሰኛና ፡ የሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤቶቻችን ፡ ስለተቀበሉት ፤

በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችን ፡ በ፴፬ኛውና ፡ በ፹፰ኛው ፡ አንቀጽ ፡ የተጻፈውን ፡ ተመልክተን ፡ የሕግ ፡ መወሰኛና ፡ የሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤቶቻችን ፡ የመከሩበትን ፡ አይተን ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ አውጀናል ።

፩ ፤ ይህ ፡ ሕግ ፡ « የ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ » ተብሎ ፡ ሊጠቀስ ፡ ይቻላል ።

፪ ፤ ልዩ ፡ መጽሐፍ ፡ ሆኖ ፡ በተለይ ፡ በወጣው ፡ በቍጥር ፡ ፫/፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ የታተመው ፡ ይህ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ከመስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

፫ ፤ በሐምሌ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለ ፡ ኪሣራና ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ ማኅበር ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ከመስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ በዚህ ፡ ተሽሮአል ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡

ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ አክሊሉ ፡ ሀብተ ፡ ወልድ ።

ምክትል ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትርና ፡ የጽሕፈት ፡ ሚኒስትር ።

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የንግድ ፡ ሕግ ።

# አንደኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ስለ ፡ ነጋዴዎችና ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ መደብሮች ።

## አንቀጽ ፡ ፩ ።

## በነጋዴዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### የንግድ ፡ ሥራ ፡ በሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የሚፈጸም ፡ ሕግ ።

**ቍ ፡ ፩ ።  ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አፈጻጸም ፡ ወሰን ።**

በዚህ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ ሌላ ፡ ውሳኔ ፡ የተሰጠው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎችና ፡ ማኅበሮች ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንባቸውና ፡ በሥራቸውም ፡ ላይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ይጸናባቸዋል ።

**ቍ ፡ ፪ ።  ስለ ፡ ባሕር ፡ ሕግ ፡ አፈጻጸም ፡ ወሰን ።**

የንግድ ፡ ሥራቸው ፡ ከባሕር ፡ ንግድ ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎችና ፡ ማኅበሮች ፡ በባሕር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተገቢ ፡ የሆኑት ፡ ልዩ ፡ ውሳኔዎች ፡ ይጸኑባቸዋል ።

**ቍ ፡ ፫ ።  ስለ ፡ ሰዎችና ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ።**

በሰዎች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ናቸው ፡ ተብሎ ፡ በግልጽ ፡ የተወሰነ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ነጋዴ ፡ በሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የሚፈጸሙት ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ውሳኔዎች ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮችም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ። ይኸውም ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ ይልቁንም ፡ በሁለተኛው ፡ መጽሐፍና ፡ በአምስተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ በአንቀጽ ፡ ፭ ፡ በተለይ ፡ ለንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ፡ የተሠሩት ፡ ልዩ ፡ ውሳኔዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፬ ።  በመንግሥት ፡ ሕግ፡መሠረት፡የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፤**

(፩) በመንግሥት ፡ ሕግ ፡ የተቋቋሙ ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ማኅበሮች ፤ የአስተዳደር፡ክፍሎች ፤ የሃይማኖት ፡ ማኅበሮች ፤ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ፤ በቍጥር ፡ አምስት ፡ የተመለከተውን ፡ ሥራ ፡

ቢሠሩም ፡ እንኳ ፡ በሕግ ፡ ተገልጾ ፡ የተወሰነ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በነጋዴዎች ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ መሆን ፡ የለባቸውም ።

(፪) የ፩ደኛው ፡ ንኡስ፡ቍጥር፡ ውሳኔ ፡ በመንግሥት ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተቋቋሙ ፡ ድርጅቶች ፡ ተካፋይ ፡ ለሆኑበት ፡ ሥራ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ነጋዴ ፡ ናቸው ፡ የሚባሉ ፡ ሰዎች ።

### ቍ ፡ ፭ ። ነጋዴዎች ፡ የሚባሉ ፡ ሰዎች ።

የሞያ ፡ ሥራቸው ፡ አድርገው ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተቈጠሩትን ፡ ሥራዎች ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ነጋዴዎች ፡ ናቸው ።

(፩) በቀድሞ ፡ ሁኔታቸው ፡ እንዳሉ ፡ ወይም ፡ ለዋውጦ ፡ ወይም ፡ አሻሽሎ ፡ መልሶ ፡ ለመሸጥ ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ወይም ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ የሚገዙ ፤

(፪) ለማከራየት ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ንብረቶችን ፡ የሚገዙ ፤

(፫) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ዕቃ ፡ ማከማቻ ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በቍጥር ፡ ፪ሺ፻፺፮ ፡ እንደተመለከተው ፡ ያለ ፡ የዕቃ ፡ ማከማቻ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፤

(፬) ማዕድን ፡ ማውጣትና ፡ የዘይት ፡ (የነዳጅ) ፡ ማዕድን ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፤

(፭) የእጅ ፡ ሥራ ፡ ጥበበኛ ፡ ከሚሠራው ፡ መጠን ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ አሠራር ፡ የሕንጻ ፡ ድንጋይ ፡ የሚያወጡ ፡ (የሚፈልጡ) ፤

(፮) የጨው ፡ ማዕድንን ፡ የሚያወጡ ፤

(፯) ግዙፍነት ፡ ያላቸው ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ዕቃዎችን ፡ ይልቁንም ፡ እንደ ፡ ምግብ ፡ ዕቃዎች ፡ ያሉትን፡ያልተሠሩ ፡ (ጥሬ ፡ ) ወይም ፡ በግማሽ ፡ የተሠሩ ፡ ዕቃዎችን ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ጥበበኛ ፡ ከሚሠራው ፡ መጠን ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ አሠራር ፡ ለዋውጠው ፡ የሚሠሩና ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ የሚያውሉ ፤

(፰) የእጅ ፡ ሥራ፡ ጥበበኛ ፡ ከሚሠራው ፡ መጠን ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ አሠራር ፡ ቤት ፡ መሥራት ፤ ማደስ ፤ መጠገን ፤ (መጠበቅ)፤ ማጽዳት ፤ ተንቀሳቃሽ ፡ ወይም ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ የሚቀልሙ ፤ ወይም ፡ ቀለም ፡ የሚቀቡ ፤

(፱) የእጅ ፡ ሥራ ፡ ጥበበኛ፡ ከሚሠራው ፡ መጠን፡በላይ ፡ በሆነ ፡ አሠራር ፡ በሌላ ፡ ሰው፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ ላይ፡ የመደልደል ፤ የመደደቅ ፤ ለረግረግ፡ ውሃ ፡ መውረጃ ፡ ቦዮች ፡ የመሠንጠቅ ፡ ሥራዎችን ፡ የሚሠሩ ፤

(፲) የእጅ ፡ ሥራ፡ ጥበበኛ፡ ከሚሠራው፡ መጠን ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ አሠራር ፡ ዕቃዎችን ፤ ወይም ፡ ሰዎችን ፡ ማናቸውንም ፡ ዐይነት ፡ የማጓጓዝ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፤

(፲፩) የማተሚያ ፡ ቤት፡(የማተም)፡ሥራዎች ፡ ወይም ፡ የመቅረጽና ፡ ከፎቶግራፍ ፡ ወይም ፡ ከሲኒማቶግራፊ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸውን ፡ ሥራዎች ፡ የሚሠሩ ፤

BACK



(፲፪) ውሃ ፡ በቦይ ፤ በአሸንዳ ፤ እያመጡ ፡ የማከፋፈልና ፡ የማቀበልን ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፤

(፲፫) ኤሌክትሪክ ፤ ጋዝ ፤ ታፍኖ ፡ የተያዘ ፡ ነፋስ ፤ የማሞቂያና ፡ የማቀዝቀዣ ፡ ሥራ ፤ የሚሠሩ ፤ የሚያከፋፍሉ ፤ የሚሸጡ ፤

(፲፬) ለሕዝብ ፡ ትርኢይት ፡ አቋቁመው ፡ የሚሠሩ ፤ ወይም ፡ የራዲዮ ፤ ወይም ፡ የቴሌቪዚዮን ፡ ጣቢያ ፡ የሚያቋቁሙና ፡ የሚሠሩ ፤

(፲፭) የሆቴል ፤ የምግብ ፡ ቤት ፤ (ሬስቶራን) ፡ የቡና ፡ ቤት ፤ የመጠጥ ፡ ቤት ፤ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ መታጠቢያ ፡ (መዋኛ)፡ ቦታ ፡ የሚያቋቁሙና ፡ የእጅ ፡ ሥራ፡ ጥበበኛ ፡ ከሚሠራው ፡ መጠን ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ አሠራር ፡ የጠጕር ፡ ማስተካከል ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፤

(፲፮) በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ በተለይም ፡ በማተም ፤ በመቅረጽ ፤ በፎቶግራፍ ፤ ወይም ፡ ቃልን ፡ በመመዝገብ ፤ አትሞ ፡ የማውጣት ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፤

(፲፯) መረጃ ፡ ወይም ፡ ወሬ ፡ የማስተላለፍ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፤

(፲፰) የጕዞ ፡ ወይም ፡ የጋዜጣ ፡ ወኪልነት ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፤

(፲፱) የደላላነት ፡ ወይም ፡ የኮሚሲዮን ፤ የምንዛሪ ፡ ወይም ፡ በንግድ ፡ ወኪልነት ፡ የሚሠሩ ፤

(፳) የባንክና ፡ የገንዘብ ፡ መመንዘር ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ።

(፳፩) የኢንሹራንስ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፤

## ቍ ፡ ፯ ። የእርሻና ፡ የደን ፡ ማልማት ፡ ሥራዎች ።

(፩) የእርሻ ፡ ወይም ፡ የደን ፡ ማልማት ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፤ ወይም ፡ ከብት ፡ የሚያረቡ ፤ ወይም ፡ የግጦሽ፡ ሣር ፡ የሚያሳድጉ ፤ ከሚሠሩበት፡ወይም ፡ ከሚያዙበት ፡ መሬት ፡ የአገኙትን ፡ ሰብል ፡ ቢሸጡ ፤ ወይም፡በሚሠሩበት ፡ ወይም ፡ በሚያዙበት ፡ መሬት ፡ ባገኙት ፡ እላባ ፡ እየቀለቡ ፡ ያረቡአቸውን ፡ ከብቶችና ፡ ርቢዎቻቸውን ፡ ቢሸጡ ፡ ነጋዴዎች ፡ አይባሉም ።

(፪) የመሬት ፡ ማልማቱ ፤ የከብት ፡ ማርባቱ ፡ ሥራ ፤ በግል ፡ በአንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ በእርሻ ፡ ኅብረቶች ፡ ወይም ፡ በገበሬዎች ፡ ማኅበር ፡ ቢሠራም ፡ ነጋዴዎች ፡ አይባሉም ።

(፫) ከሚሠሩበት ፡ ወይም ፡ ከሚያዙበት ፡ መሬት ፡ ያበቀሉትን ፡ ችግኝ ፡ የሚሸጡ ፡ ችግኝ ፡ አብቃዮች ፡ ነጋዴዎች ፡ አይባሉም ።

## ቍ ፡ ፰ ። ከእርሻ ፡ ሥራ ፡ የተገኙትን ፡ ሰብሎች ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ።

(፩) በቍጥር ፡ ፯ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) ፡ የሠረት ፡ ገበሬዎች ፤ በደን ፡ ሥራ ፡ የሚጠቀሙ ፡ ሰዎች ፤ አርቢዎች ፤ ወይም ፡ የከብት ፡ መንጋ ፡ ጠባቂዎች ፤ የሥራቸውን ፡ የዘወትር ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ከሚያለሙት ፡ ወይም ፡ ከሚያዙበት ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያገኙትን ፡ ሰብል ፡ ወይም፡ ከዚህ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡

BACK



በሚያገኙት፡ ሰብል ፡ የቀለቧቸውን ፡ ወይም ፡ ያረቧቸውን ፡ እንስሳዎች ፡ ለዋውጠው ፡ ቢሸጡ ፡ ነጋዴ ፡ አያሰኛቸውም ።

(፪) ሰብልን ፡ የመለዋወጥ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩት ፡ በግል ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ የእርሻ ፡ ኅብረቶች ፡ ወይም ፡ ማኅበሮች ፡ ቢሆኑም ፡ ነጋዴ ፡ አያሰኛቸውም ።

**ቍ ፡ ፰ ። ስለ ፡ ዓሣ ፡ አጥማጆችና ፡ ስለ ፡ ዓሣ ፤ ሼል ፡ ፈሽና ፡ ሼል ፡ አርቢዎች ።**

ዓሣ ፡ አጥማጆችና ፡ ዓሣ ፤ ሼል ፡ ፈሽና ፡ ሼል ፡ አርቢዎች ፡ አጥምደው ፡ የያዙዋቸውን፡ ወይም፡ ያረቡዋቸውን ፡ ዓሣዎች ፤ ሼል ፡ ፈሽና ፡ ሼሎች ፡ ቢሸጡ፡ ነጋዴ፡ አያሰኛቸውም ።

**ቍ ፡ ፱ ። የእጅ ፡ ሥራ ፡ ጥበበኞች ።**

(፩) ስለ ፡ ነጋዴዎች ፡ የተደነገገው ፡ ማናቸውም ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ በእጅ ፡ ሥራ ፡ ጥበበኞች ፡ ላይ ፡ የሚፈጸም ፡ አይደለም ።

(፪) የእጅ ፡ ሥራ ፡ ጥበበኞች ፡ ማለት ፡ በቤተ ፡ ሰባቸው ፡ እየተረዱ ፡ ከሦስት ፡ ተቀጣሪ ፡ ሠራተኞች ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ ለማጅ ፡ ሠራተኞች ፡ በላይ ፡ ሳይኖራቸው ፡ ለሥራቸው ፡ የሚሆን ፡ ዕቃ ፡ አከማችተው ፡ ሳይሆን ፤ ሥራቸውን ፡ ለማካሄድ ፡ የሚያበቃቸውን ፡ ዕቃ ፡ ብቻ ፡ የሚገዙና ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ሥራ ፡ እያከናወኑ ፡ በእጅ ፡ ሥራቸው ፡ ብቻ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

(፫) የእጅ ፡ ሥራ ፡ ጥበበኞች ፡ በመኪና ፡ ሊሠሩ ፡ ይችላሉ ።

(፬) የእጅ ፡ ጥበበኞችን ፡ ሥራ ፡ የሚመለከት ፡ ልዩ ፡ ሕግ ፡ ሊደነገግ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፲ ። ስለ ፡ ንግድ ፡ ማኅበሮች ።**

(፩) በመመሥረታቸው ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በተግባር ፡ ማናቸውንም ፡ በዚሁ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፭ ፡ የተገለጹትን ፡ ሥራዎች ፡ የሚሠሩ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ዐይነተኛ ፡ የንግድ ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ማኅበሮች ፡ ናቸው ።

(፪) ባለአክሲዮን ፡ ማኅበሮችና ፡ ኀላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበሮች ፡ ዓላማቸው ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆን ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## የንግድ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ችሎታ ፡ ስለሌላቸው ፡ ሰዎች ።

**ቍ ፡ ፲፩ ። ችሎታ ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ።**

(፩) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ማንኛውንም ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ሊሠሩ፡አይፈቀድላቸውም ።

BACK



(፪) በቍጥር ፡ ፲፬ ፡ እና ፡ ፲፭ ፡ የተነገረው ፡ ውሳኔ ፡ የሚሠራበት ፡ መሆኑ ፡ እንደ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ እነዚህ ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ የንድግ ፡ ሥራ ፡ ቢሠሩ ፤ የነጋዴነትን ፡ ስም ፡ አያገኙም ፤ የሠሩትም ፡ ሥራ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ፍርስ ፡ እንዲሆን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይቻላል ።

## ቍ ፡ ፲፪ ። ስለ ፡ ሞግዚት ።

በፍትሐ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ፡ ሰዎች ፡ ችሎታ፡ በተባለው ፡ አንቀጽ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፺፰ ፡ ለተገለጹት ፡ ጕዳዮች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሞግዚት ፡ የሆኑት ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሰ ፡ ሰው ፡ ስምና ፡ ስለርሱ ፡ ሆነው ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ሊሠሩ ፡ አይ ችሉም ። ይኸው ፡ ውሳኔ ፡ ለተከለከለ ፡ ሰው ፡ ሞግዚትም ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

## ቍ ፡ ፲፫ ። በሞግዚት ፡ ከመተዳደር ፡ ስለ ፡ ወጣ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ስላላደረሰ ፡ ልጅ ።

(፩) የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ ችሎታ ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በቍ ጥር ፡ ፫፻፴፫ ፡ የተጻፈው ፡ ቢኖርም ፡ እንኳን ፤ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ በጽሑፍ ፡ ሥልጣን ፡ ካልተሰጠው ፡ በቀር ፡ በሞግዚት ፡ ውስጥ ፡ ከመተ ዳደር ፡ ነፃ ፡ የወጣ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ አይ ችልም ።

(፪) በሞግዚት ፡ ውስጥ ፡ ከመተዳደር ፡ ነጻ ፡ የወጣ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ እንዳደረሰ ፡ የሚቈጠረው ፤ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) መሠረት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ምክር ፡ ጉባኤ ፡ በጽሑፍ ፡ ይህን ፡ ሥልጣን ፡ (ፈቃድ) ፡ የሰጠው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፲፬ ። አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ መሆኑ ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ የሚያስ ከትለው ፡ ውጤት ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ ችሎታ ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፲፰ ፡ የተወሰነው ፡ ቢኖርም ፡ እንኳን ፤ አንድ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ልጅ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ እንዳደረሰ ፡ አድርጎ ፡ ራሱን ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ አስገብቶ ፡ ከተገኘ ፤ በዚህም ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፻፹፩ ፡ በተጻፈው ፡ መሠ ረት ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ መሆኑን ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖ ችን ፡ መከራከሪያ ፡ ሊያደርግባቸው ፡ አይችልም ።

## ቍ ፡ ፲፭ ። የተከለከለ ፡ መሆንን ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፻፹፩ ፡ መሠረት ፡ በፍርድ ፡ የተከለከለ ፡ ሰው ፡ መሆኑ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ካልገባ ፡ በቀር ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

## ምዕራፍ ፬ ።

## የተጋቡ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ሚያደርጉት ፡ የንግድ ፡ ሥራ ።

**ቍ ፡ ፲፮ ። ያገቡ ፡ ሰዎች ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ስላላቸው ፡ መብት ።**

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሥጋና ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፵፮ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ካልተቃወመ ፡ በቀር ፡ ያላገባ ፡ ሰው ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ እንደሚቻለው ፡ ሁሉ ፡ ያገባም ፡ ሰው ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፯ ። መቃወሚያውን ፡ ስለማስታወቅ ።**

(፩) በባልና ፡ ሚስት ፡ መካከል ፡ በቍጥር ፡ ፲፮ ፡ መሠረት ፡ የሚደረገው ፡ መቃወሚያ ፡ ለሚነግደው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ እንዲደርሰው ፡ ለማድረግ ፡ በማናቸውም ፡ መንገድ ፡ ማስታወቅ ፡ ይቻላል ።

(፪) እንደዚህ ፡ ያለው ፡ መቃወም ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ካልገባ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፯፹፩ ፡ መሠረት ፡ ሦስተኛ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፲፰ ። መቃወሚያውን ፡ ስለ ፡ ማንሣት ።**

(፩) የሚነግደው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ መቃወሚያውን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ጥቅም ፡ የማያጸድቀው ፡ መስሎ ፡ የታየው ፡ እንደሆን ፡ መቃወሚያው ፡ እንዲነሣለት ፡ ጕዳዩን ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ መቃወሙ ፡ እንዲቀር ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፤ ይህንኑ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ እንዲገባ ፡ ማድረግ ፡ ይገባል ።

**ቍ ፡ ፲፱ ። የሚነግደው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ስለ ፡ ተዋዋለው ፡ ዕዳ ።**

የሚነግደው ፡ ባል፡ወይም ፡ ሚስት ፡ የተዋዋለው ፡ ዕዳ ፡ ስለ ፡ ሥጋና ፡ ጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ በሚለው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፶፱፡መሠረት ፡ እንደ ፡ ባልና፡ሚስት ፡ ዕዳ ፡ ስለሚቈጠር ፡ ከያንዳንዱ ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ የግል ፡ ንብረትና ፡ የጋራ ፡ ንብረት ፡ እንዲከፈል ፡ ሊጠየቅ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፳ ። መቃወሚያው ፡ ስለሚሰጠው ፡ ውጤት ።**

በቍጥር ፡ ፲፮ ፡ መሠረት፡ ባል፡ ወይም፡ ሚስት ፡ ያቀረበው ፡ መቃወሚያ ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ከገባ ፡ የሚነግደውን ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ዕዳ ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚቻለው ፡ ከዚሁ ፡ ሰው ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፩ ። ባልና ፡ ሚስት ፡ ተባብረው ፡ ስለሚሠሩት ፡ ሥራ ።

አንዱ ፡ ለሌላው ፡ ሠራተኛ ፡ መሆኑ ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበበት ፡ በቀር ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ በአንድነት ፡ በሚነግዱበት ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱም ፡ ነጋዴዎች ፡ ናቸው ፡ ተብ ለው ፡ ይቈጠራሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## የንግድ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ መብት ።

ቍ ፡ ፲፪ ። የንግድ ፡ ሥራ ፡ የመሥራት ፡ ነጻነት ።

በሕግ ፡ ተለይተው ፡ የተከለከሉ ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ መወዳደር ፡ እንዳ ይደረግ ፡ የተደረጉ ፡ የስምምነት ፡ ውሎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ ማንኛ ውም ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ በወጡት ፡ ሕጋዊ ፡ ድንጋ ጌዎች ፡ ያሉበትን ፡ ግዴታዎችን ፡ እየፈጸመ ፡ የመረጠውን ፡ ማንኛውንም ፡ የን ግድ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፲፫ ። በሕግ ፡ ስለ ፡ ተከለከሉ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ተወሰኑ ፡ ነገሮች ።

(፩) የአንዳንድ ፡ ሰዎችን ፡ የመነገድ ፡ መብትን ፡ ይልቁንም ፡ መነገድን ፡ በመከ ልከል ፡ ወይም ፡ ከያዙት ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ የማይስማማ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በመወሰን ፡ በተለይ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ እንዳይሠሩ ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ የተለዩ ፡ የንግድ ፡ ሥራዎችን ፡ እንዳይሠሩ ፡ በሕግ ፡ ለመከልከል ፡ ይቻላል ።

(፪) እንደዚሁም ፡ አንዳንድ ፡ ንግዶችን ፡ ለመነገድ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ልዩ ፡ ሁኔ ታዎች ፡ (ግዴታዎች)፡ እንደ ፡ ዕድሜ ፤ እንደ ዲፕሎም ፤ እንደ ፡ ዋስ ፤ እንደ ፡ ዜግ ነት ፤ ወይም ፡ እንደ ፡ ልዩ ፡ ፈቃድ ፡ መቀበልን ፡ እንደዚሁ ፡ ያሉትን ፡ በሕግ ፡ ሊወሰን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፬ ። በሕግ ፡ የተከለከለውን ፡ ስለሚተላለፉ ፡ ሰዎች ፡ ቅጣት ።

(፩) በሕግ ፡ የተከለከሉትን ፡ ወይም ፡ ከያዙት ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ የማይስማማ ፡ በመሆኑ ፡ የተከለከለ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑትን ፡ ልዩ ፡ ግዴታዎች ፡ (ሁኔ ታዎች) ፡ ሳይሞሉ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ የተገኙ ፡ ሰዎች ፡ በሕግ ፡ እንደ ፡ ተወሰነው ፡ በወንጀል ፡ ይቀጣሉ ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ ነጋዴዎች ፡ ሆነው ፡ የሠሩትን ፡ ሥራ ፡ የማይጸና ፡ ለማድረግ ፤ ሕግ ፡ ሳይፈቅድ ፡ የሠራሁት ፡ ነውና ፡ አይጸናብኝም ፡ ብለው ፡ መከራከሪያ ፡ ሊያደርጉት ፡ አይችሉም ። ነጋዴ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ላሉበት ፡ ግዴታዎች ፡ ሁሉ ፡ ተገዳጅ ፡ ይሆናል ፡ ስለ ፡ ሆነም ፡ በነጋዴነት ፡ ስም ፡ ከሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጋራ ፡ መከራከር ፡ አይችልም ።

BACK



ቊ ፡ ፲፭ ። ስለ ፡ ማኅበሮች ።

(፩) የገንዘብ ፡ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ ያልተቋቋሙ ፡ ማኅበሮች ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ሊሠሩ ፡ አይችሉም ።

(፪) በንኡስ ፡ ቊጥር (፩) የተወሰነውን ፡ ተላልፈው ፡ ሲገኙ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ተሰጣቸው ፡ ማኅበሮች ፡ (ድርጅቶች) ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በቊጥር ፡ ፬፻፸፩ ፡ በተጻፈው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመፍረድ ፡ ይቻላል ።

ቊ ፡ ፲፮ ። ስለ ፡ ንግድ ፡ ማኅበሮች ።

የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ እንዲሠሩ ፡ ያልተፈቀደላቸውን ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ሥራዎችን ፡ ለመሥራት ፡ በሕግ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ሕጋዊ ፡ ግዴታዎች ፡ ሳይፈጽሙና ፡ ሳይሞሉ ፡ ለመሥራት ፡ አይፈቀድላቸውም ።

ቊ ፡ ፲፯ ። በመንግሥት ፡ ሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ማኅበሮች ፡ (ድርጅቶች ።)

የአዲሚኒስትራሲዮን ፡ ወይም ፡ የሃይማኖት ፡ ድርጅቶች ፤ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ የሥራ ፡ ድርጅቶች ፤ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የሚችሉበት ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ፡ ውጤት ፡ ተዘርዝሮ ፡ በልዩ ፡ ሕግ ፡ ይወሰናል ።

## አንቀጽ ፡ ፪ ።

## የንግድ ፡ ረዳቶችና ፡ ወኪሎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ንግድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ።

ቊ ፡ ፲፰ ። ትርጓሜ ።

(፩) የንግድ ፡ ሠራተኞች ፡ ማለት ፡ በሥራ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ለአንድ ፡ ነጋዴ ፡ ሥራ ፡ የጉልበት ፡ ሥራ ፡ ያልሆነ ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ሻጭ ፤ ጸሓፊ ፤ የሒሳብ ፡ ሠራተኛ ፤ ተጠባባቂ ፤ መርማሪ ፤ ወይም ፡ አስተዳዳሪ ፡ በመሆን ፡ ከነጋዴው ፡ ጋራ ፡ ተባብረው ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

(፪) የነጋዴው ፡ ሠራተኞች ፡ ነጋዴዎች ፡ አይባሉም ።

ቊ ፡ ፲፱ ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

የዚህ ፡ ሕግ ፡ ውሳኔዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ የንግድ ፡ ሠራተኞች ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ በሚለው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ይተዳደራሉ ።

ቊ ፡ ፳ ። የግል ፡ ንግድ ፡ ማቋቋምን ፡ ስለ ፡ መከልከል ።

(፩) አንድ ፡ የንግድ ፡ ሠራተኛ ፡ ስለ ፡ ራሱም ፡ ሆነ ፡ ስለሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ሆኖ ፡ እሱን ፡ የቀጠረው ፡ ነጋዴ ፡ ከሚሠራው ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይ ፡

BACK



የሆነ ፡ ሌላ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ አይፈቀድለትም ፤ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሠራተኛ ፡ ይህን ፡ የተከለከለውን ፡ ጥሶ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ቀጣሪው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በቍጥር ፡ ፪ሺ፭፻፺፩ ፡ መሠረት ፡ ኪሣራ ፡ ለማግኘት ፡ ይችላል ፤ የሥራውንም ፡ ውል ፡ ለመሠረዝ ፡ ወይም ፡ ውሉን ፡ አሳድስም ፡ ለማለት ፡ የሚያበቃ ፡ ምክንያት ፡ ነው ።

(፪) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በቍጥር ፡ ፪ሺ፭፻፺፱ ፤ ፪ሺ፭፻፺ ፡ እና ፡ ፪ሺ፭፻፺፪ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለንግድ ፡ ሥራ ፡ የተቀጠረው ፡ ሠራተኛ ፡ የውሉ ፡ ዘመን ፡ ከአለቀ ፡ በኋላ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሚሆን ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ አይሠራም ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ሥራ ፡ በተቀጠረበት ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ማግባት ፡ አይቻልም ።

### ቍ ፡ ፴፩ ። ውክልና ።

(፩) የንግድ ፡ ሠራተኞች ፡ በግልጽ ፡ ወይም ፡ በዝምታ ፡ መሠረት ፡ ወኪል ፡ ሊሆኑ ፡ ይቻላል ።

(፪) የወኪልነቱን ፡ ሥልጣን ፡ መሻር ፡ የሠራተኛውን ፡ ውል ፡ መሠረዝን ፡ ሊያስከትል ፡ አይችልም ።

### ቍ ፡ ፴፪ ። ዕቃ ፡ ለመሸጥ ፡ ኀላፊ ፡ የሆነ ፡ ሠራተኛ ፡ ስላለው ፡ ሥልጣን ።

(፩) አንድ ፡ ሱቅ ፡ ውስጥ ፡ ዕቃ ፡ ለመሸጥ ፡ ኀላፊነት ፡ የተሰጠው ፡ ሠራተኛ ፡ ዕቃዎችን ፡ ለመሸጥና ፡ በዚሁ ፡ ሱቅ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ዕቃዎች ፡ ለመቀበል ፡ ውክልና ፡ እንዳለው ፡ ሁኖ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ለልዩ ፡ ሒሳብ ፡ እንዲከፈል ፡ የተደረገ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የተሸጡትን ፡ የሸቀጦች ፡ ዋጋ ፡ ለኔ ፡ ክፈሉ ፡ ማለት ፡ ይችላል ።

(፫) ነጋዴው ፡ የፈረመበትን ፡ ደረሰኝ ፡ ካላቀረበ ፡ ወይም ፡ በተለይ ፡ ሥልጣን ፡ ካልተሰጠው ፡ በቀር ፡ ሠራተኛው ፡ ከሱቁ ፡ ውጭ ፡ የዕቃ ፡ ሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ እንዲከፈለው ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ።

### ቍ ፡ ፴፫ ። ትርጓሜ ።

(፩) ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ማለት ፡ በነጋዴው ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ በውክልና ፡ እንዲፈርም ፡ ሥራውንም ፡ እንዲያካሂድ ፡ በግልጽ ፡ ወይም ፡ በዝምታ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ነው ።

(፪) ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ነጋዴ ፡ አይደለም ።

**ቍ ፡ ፴፩ ። በመዝገብ ፡ በማግባት ፤ ስለ ፡ ማስታወቅ ።**

(፩) ነጋዴው ፤ ሥልጣን ፡ ያለውን ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁን ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ እንዲገባ ፡ ማድረግ ፡ ይገባዋል ።

(፪) ነጋዴው ፤ ሥልጣን ፡ የሰጠውን ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) መሠረት ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ሳያስገባ ፡ ቢቀርም ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፡ ወዲያው ፡ ሥራውን ፡ ለማከናወን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፴፪ ። ስለ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ሥልጣን ።**

(፩) ከሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጋራ ፡ በሚያገናኙት ፡ ጕዳዮች ፡ ሁሉ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ከነጋዴው ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ ነክነት ፡ ያላቸውን ፡ ማናቸውንም ፡ ግዴታዎች፡ለመፈረምና ፡ የሚተላለፉ ፡ የንግድ፡ሰነዶችን ፡ (ኔጎሽያብል፡ ኢንስትሩመንት)፡ ጭምር፡ ለመፈረም ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ በግልጽ ፡ ሥልጣን ፡ ካልተሰጠው ፡ በቀር ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ መያዣ ፡ ማድረግ ፡ ወይም ፡ መሸጥ ፤ መለወጥ ፤ ወይም ፡ የንግዱን ፡ መደብር፡መሸጥ ፤ ማከራየት ፤ ወይም ፡ ለዕዳ ፡ ማስያዝ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፴፫ ። ሥልጣን ፡ መቀነስ ።**

(፩) የሥራ፡አስኪያጅነት ፡ ሥልጣን ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ቅርንጫፍን ፡ ሥራ ፡ ለማስኬድ ፡ ብቻ ፡ ሥልጣን ፡ በመስጠት ፡ ሥልጣኑን ፡ የተወሰነ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ፤ ስለሆነም ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ የሥልጣን ፡ መቀነስ ፡ ማስታወቂያ ፡ በንግድ፡መዝገብ፡ ካልተመዘገበ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፴፩፡ መሠረት ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆንባቸው ፡ አይችልም ።

(፪) ሌላው ፡ ዐይነት ፡ የሥልጣን ፡ መቀነስ ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆንባቸው ፡ አይችልም ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ንግድ ፡ ተላላኪዎችና ፡ እንደራሴዎች ።

**ቍ ፡ ፴፬ ። ስለ ፡ ንግድ ፡ ተላላኪዎች ።**

(፩) የንግድ ፡ ተላላኪዎች ፡ ማለት ፡ መኖሪያቸው ፡ የንግዱ ፡ መደብር ፡ ዋናው ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ ባለበት ፡ የሆነና ፡ በተዋዋሉት ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ከነጋዴው ፡ ጋራ ፡ የሚሠሩ ፤ ነጋዴው ፡ እያዘዛቸው ፡ የነጋዴው ፡ ደንበኞች ፡ በሚገኙበት ፡ ቦታ ፡ እየዞሩ ፡ በነጋዴው ፡ ስምና ፡ ምትክ ፡ ሆነው ፡ ዕቃ ፡ የሚያቀርቡ ፡ ወይም፡ አገልግሎት ፡ የሚሰጡ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

(፪) ሌላ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ ተላላኪዎች ፡ የተዋዋሏቸው ፡

BACK



ውሎች ፡ ነጋዴው ፡ እንዲያጸድቃቸው ፡ ለእርሱ ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ።

(፫) የንግድ ፡ ተላላኪዎች ፡ ነጋዴዎች ፡ አይደሉም ።

**ቍ ፡ ፴፰ ። ስለ ፡ ንግድ ፡ እንደራሴ ።**

(፩) የንግድ ፡ እንደራሴዎች ፡ ማለት ፡ መኖሪያቸው ፡ የወካዩ ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ባለበት ፡ ስፍራ ፡ ያልሆነና ፡ ከነጋዴው ፡ ጋራ ፡ በተዋዋሉት ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ነጋዴው ፡ እንዲሠሩ ፡ እያዘዛቸው ፡ በተወሰኑ ፡ ቦታዎች ፡ ብቻ ፡ የነጋዴው ፡ ደንበኞችን ፡ እየጐበኙ ፡ በነጋዴው ፡ ስምና ፡ ምትክ ፡ ሆነው ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ አገልግሎት ፡ የሚሰጡ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

(፪) ሌላ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ እንደራሴዎች ፡ የተዋዋሏቸው ፡ ውሎች ፡ ነጋዴው ፡ እንዲያጸድቃቸው ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ ነጋዴው ፡ የሚገደድባቸው ፡ ይሆናሉ ።

(፫) የንግድ ፡ እንደራሴዎች ፡ ነጋዴዎች ፡ አይደሉም ።

**ቍ ፡ ፴፱ ። ስለ ፡ ግል ፡ ንግድ ።**

(፩) በሥራ ፡ ውላቸው ፡ ውስጥ ፡ ስምምነት ፡ ካላደረጉ ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ ተላላኪዎችና ፡ የንግድ ፡ እንደራሴዎች ፡ ለራሳቸው ፡ የግል ፡ ንግድ ፡ ሊነግዱ ፡ አይችሉም ። የግል ፡ ንግድ ፡ ሲነግዱ ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡ በቍጥር ፡ ፵፪ ፡ እና ፡ ፵፫ ፡ የተነገረውን ፡ የኪሣራ ፡ መክፈል ፡ መብታቸውን ፡ ያጣሉ ።

(፪) የንግድ ፡ ተላላኪዎችና ፡ እንደራሴዎች ፡ የግል ፡ ንግድ ፡ እንዲነግዱ ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጣቸው ፡ ጊዜ ፡ በቍጥር ፡ ፴ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) የተጻፈው ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፵ ። ስለሌሎች ፡ ነጋዴዎች ፡ ተተክቶ ፡ ስለ ፡ መሥራት ።**

(፩) ሌላ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ ተላላኪዎችና ፡ እንደራሴዎች ፡ በውል ፡ ግዴታ ፡ ለገቡለት ፡ ነጋዴ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፤ ስለሌሎች ፡ ነጋዴዎች ፡ ተተክተው ፡ መሥራት ፡ አይችሉም ። ለሌሎቹ ፡ ነጋዴዎች ፡ ተተክተው ፡ ሲሠሩ ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡ በቍጥር ፡ ፵፪ ፡ እና ፡ ፵፫ ፡ የተነገረውን ፡ የካሣ ፡ መክፈል ፡ መብታቸውን ፡ ያጣሉ ።

(፪) በምንም ፡ አኳኋን ፡ ቢሆን ፡ ግዴታ ፡ የገቡለት ፡ ነጋዴ ፡ ከሚሸጠው ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ ከሚሰጠው ፡ አገልግሎት ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ ዕቃ ፡ ለመሸጥ ፡ ወይም ፡ አገልግሎት ፡ ለመስጠት ፡ ለሌላ ፡ ነጋዴ ፡ ተተክቶ ፡ ለመሥራት ፡ አይፈቀድላቸውም ።

**ቍ ፡ ፵፩ ። ስለ ፡ አበል ።**

(፩) የንግድ ፡ ተላላኪዎችና ፡ የንግድ ፡ እንደራሴዎች ፡ የሚከፈላቸው ፡ በደመወዝ ፡ ወይም ፡ በኮሚሲዮን ፡ ወይም ፡ ሁለቱንም ፡ በማጣመር ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

(፪) አበላቸው ፡ በሥራ ፡ ውላቸው ፡ መሠረት ፡ በውል ፡ የተወሰነ ፡ ካልሆነ ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ።

ቍ ፡ ፴፪ ። ውል ፡ እንዳይቀጥል ፡ በተሠረዘ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚያገኙት ፡ ካሣ ።

የንግድ ፡ ተላላኪዎችና ፡ የንግድ ፡ እንደራሴዎች ፡ ውላቸው ፡ ሳልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነጋዴው ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ውሉታውን ፡ በሠረዘ ፡ ጊዜ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪ሺ፭፻፳፫ ፡ በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ በርትዕ ፡ የሚገባ ፡ ካሣ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አላቸው ።

ቍ ፡ ፴፫ ። ባቀረቡዋቸው ፡ ደንበኞች ፡ መሠረት ፡ ታስቦ ፡ ስለሚከፈላቸው ፡ ካሣ ።

ማናቸውም ፡ የንግድ ፡ ተላላኪዎች ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ወኪሎች ፡ አንዳች ፡ ጥፋት ፡ ሳያደርጉ ፡ ላልተወሰነ ፡ ዘመን ፡ የተዋዋሉትን ፡ ውል ፡ ነጋዴው ፡ የሠረዘው ፡ ወይም ፡ ለተወሰነ ፡ ዘመን ፡ የተዋዋሉትን ፡ ውል ፡ ነጋዴው ፡ ሳያድስላቸው ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባቀረቡዋቸው ፡ ደንበኞች ፤ ወይም ፡ ባስገኙት ፡ ወይም ፤ ባስፋፉት ፡ ገበያ ፤ ወይም ፡ ባስገኙት ፡ ወይም ፡ በተገኘው ፡ ጥቅም ፡ ልክ ፡ ካሣ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አላቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## ስለ፡ንግድ ፡ ወኪሎች ።

ቍ ፡ ፴፬ ። ትርጓሜ ።

(፩) አንድ ፡ የንግድ ፡ ወኪል ፡ ማለት ፡ ከነጋዴው ፡ ጋራ ፡ እንዲሠራ ፡ በውል ፡ የተቀጠረ ፡ ሳይሆን ፤ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ በተወሰነ ፡ ስፍራ ፡ ሁኖ ፡ ሁል ጊዜ ፡ የነጋዴው ፡ እንደራሴ ፡ ሊሆን ፡ በነጋዴው ፡ ስምና ፡ ምትክ ፡ እንዲሠራ ፡ ወይም ፡ ውል ፡ እንዲዋዋል ፡ ውክልና ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ነው ።

(፪) በውክልናው ፡ ስምምነት ፡ ውስጥ ፡ ሌላ ፡ ስምምነት ፡ ካላደረጉ ፡ በቀር ፡ የነጋዴው ፡ ማጽደቅ ፡ ሳያሻ ፡ የንግድ ፡ ወኪሉ ፡ ውሎች ፡ ለመዋዋል ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) የንግድ ፡ ወኪል ፡ የውክልና ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡ የደላላነትም ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ይችላል ፤ ለሁሉም ፡ ቢሆን ፡ ነጋዴ ፡ ይባላል ።

ቍ ፡ ፴፭ ፤ የንግድ ፡ ወኪል ፡ ብቸኛ ፡ ወኪል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

በውክልናው ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ሌላ ፡ ስምምነት ፡ ካላደረጉ ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ወኪል ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ በተገለጸው ፡ ስፍራ ፡ የወካዩ ፡ ብቸኛ ፡ ወኪል ፡ ነው ።

BACK



**ቍ ፡ ፵፯ ። የንግድ ፡ ወኪል ፡ ግዴታዎች ።**

(፩) የንግድ ፡ ወኪል ፡ መልካም ፡ ነጋዴ ፡ የሚያደርገውን ፡ ጥንቃቄ ፡ ሁሉ ፡ በማድረግ ፡ የወካዩን ፡ ጥቅም ፡ በትጋት ፡ መጠበቅ ፡ ይገባዋል ።

(፪) ከዚህ ፡ የሚከተሉትንም ፡ ይፈጽማል ።

(ሀ) የወካዩን ፡ ትእዛዞች ፡ ሁሉ ፡ ይፈጽማል ።

(ለ) የተዋዋላቸውን ፡ ውሎች ፡ ወይም ፡ ሊዋዋል ፡ የተነጋገረባቸውን ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ ለወካዩ ፡ ያስታውቃል ።

(ሐ) ስለ ፡ ሥራው ፡ በየጊዜው ፡ ራፖር ፡ ያደርግለታል ፤ እንዲሁም ፡ በሚሠራ በት ፡ ስፍራ ፡ ስላለው ፡ የገበያ ፡ ሁኔታ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑትን ፡ መረጃዎች ፡ ሁሉ ፡ ያስታውቀዋል ።

(፫) የውክልናው ፡ ውል ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላም ፡ ቢሆን ፡ የንግድ ፡ ወኪል ፡ ወካዩ ፡ የገለጸለትን ፡ የንግድ ፡ ምስጢር ፡ ወይም ፡ ወኪል ፡ ሆኖ ፡ ሲሠራ ፡ ያወቀቸውን ፡ የንግድ ፡ ምስጢሮች ፡ ማውጣት ፡ ወይም ፡ ሊጠቀምባቸው ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፵፰ ። የግል ፡ ንግድ ፡ ማቋቋም ፡ ክልክል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) አንድ ፡ የንግድ ፡ ወኪል ፡ ወካዩ ፡ ከሚሠራቸው ፡ ንግዶች ፡ ጋራ ፡ የማይመሳሰሉትን ፡ ማናቸውንም ፡ የግል ፡ ንግድ ፡ ሊነግድ ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ወካዩ ፡ ከሚሠራው ፡ ንግድ ፡ ጋራ ፡ የሚመሳሰል ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ አይችልም ። ወኪሉ ፡ ይህን ፡ ክልከላ ፡ በጣሰ ፡ ጊዜ ፡ የውክልናው ፡ ስምምነት ፡ እንዲሠረዝ ፡ ይደረጋል ፤ ኪሣራም ፡ እንዲከፍል ፡ ይጠየቃል ።

(፪) በውክልናው ፡ ውል ፡ ሌላ ፡ ስምምነት ፡ ካላደረጉ ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ወኪል ፡ በተወከለበት ፡ ስፍራ ፡ ሆኖ ፡ የሌሎች ፡ ነጋዴዎች ፡ ወኪል ፡ መሆን ፡ አይችልም ።

(፫) በምንም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ወኪል ፤ ወኪል ፡ በሆነበት ፡ ስፍራ ፡ ወካዩ ፡ ከሚሠራባቸው ፡ የንግድ ፡ ሥራዎች ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆኑ ፡ የንግድ ፡ ሥራዎች ፡ ለሚሠሩ ፡ ነጋዴዎች ፡ ወኪል ፡ ሆኖ ፡ መሥራት ፡ ፈጽሞ ፡ አይፈቀድለትም ፤ ይህን ፡ ክልከላ ፡ ጥሶ ፡ የተገኘ ፡ የንግድ ፡ ወኪል ፡ ውሉ ፡ ተሠርዞ ፡ ኪሣራም ፡ እንዲከፍል ፡ ይደረጋል ።

**ቍ ፡ ፵፱ ። የወካዩ ፡ ግዴታዎች ።**

ወካዩ ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ የወኪሉ ፡ ሥራ ፡ የተቃና ፡ እንዲሆንለት ፡ የሚቻለውን ፡ ሁሉ ፡ ያደርግለታል ፡ መረጃዎችና ፡ የዕቃ ፡ ዐይነቶች ፡ እንዲደርሱት ፡ ያደርጋል ።

ቍ ፡ ፵፱ ። ወጪዎችን ፡ ስለ ፡ መክፈል ።

ሌላ ፡ ስምምነት ፡ ካላደረጉ ፡ በቀር ፡ በወኪልነት ፡ ለሚመራው ፡ ሥራ ፡ የተደረጉትን ፡ መደበኛ ፡ ወጪዎችና ፡ ለአንዳንድ ፡ ጉዳይ ፡ የተደረገውን ፡ ወጪ ፡ ወኪሉ ፡ ይከፈሉኝ ፡ ብሎ ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ የለውም ። ነገር ፡ ግን ፡ ወኪል ፡ አድራጊው ፡ ላሠራቸው ፡ ሥራዎች ፡ ወኪሉ ፡ የከፈላቸውን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲሁም ፡ በወኪል ፡ አድራጊው ፡ ትእዛዝ ፡ ያወጣቸውን ፡ ልዩ ፡ ወጪዎች ፡ ወኪል ፡ አድራጊው ፡ ለወኪሉ ፡ ሊከፍለው ፡ ይገባል ።

ቍ ፡ ፶ ። ስለ፡ አበል ።

(፩) አንድ ፡ የንግድ ፡ ወኪል ፡ በእርሱ ፡ አማካይነት ፡ ለተነጋገራቸው ፡ ወይም ፡ ለፈጸማቸው ፡ ሥራዎች ፡ ( ንግዶች ፡ ) ሁሉ ፡ አበል ፡ ሊከፈለው ፡ ይገባል ። ደግሞም ፡ ሌላ ፡ ውሳኔ ፡ ከሌለ፡በቀር ፡ እርሱ ፡ በተወከለበት ፡ ቦታ ፡ ወካዩ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ የወካዩ ፡ ሌላ ፡ ወኪል ፡ ቢሆን ፡ ለፈጸሙዋቸው ፡ ሥራዎች ፡ አበል ፡ ሊቀበል ፡ ይገባዋል ።

(፪) የንግዱ ፡ ወኪል ፡ ለተዋዋላቸውና ፡ ለጨረሳቸው ፡ ውሎች ፡ ወኪል ፡ አድራጊው ፡ በአደረገው ፡ ነገር ፡ ምክንያት ፡ ፍጻሜ ፡ ያላገኙ ፡ ቢሆኑም ፡ አበሉ ፡ ለወኪሉ ፡ ሊከፈለው ፡ ይገባል ።

(፫) የአበሉ ፡ ልክ ፡ በውክልናው ፡ ውላቸው ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ። ውል ፡ ባይኖር ፡ ግን ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ ይቈረጣል ።

ቍ ፡ ፶፩ ። ወኪሉ ፡ ሥራውን ፡ ራሱ ፡ መፈጸም ፡ የሚገባው ፡ ስለ፡መሆኑ ።

የውክልና ፡ ውል ፡ የሚደረገው ፡ የሰውዬውን ፡ ችሎታ ፡ በመገንዘብና ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ወኪል ፡ የውክልናውን ፡ ውል ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ማሳለፍ ፡ ወይም ፡ በእርሱ ፡ ምትክ ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ መተካት ፡ አይፈቀድለትም ።

ቍ ፡ ፶፪ ። ስለ ፡ ውክልና ፡ ውል ፡ ፍጻሜ ።

(፩) የንግድ ፡ ውክልና ፡ ውል ፡ የሚፈጸመው ፤

(ሀ) ተስማምተው ፡ የወሰኑት ፡ የውል ፡ ዘመን ፡ ሲኖር ፤ የውሉ ፡ ዘመን ፡ ሲደርስ ፡ ( ሲያልቅ ) ፤

(ለ) ለነጋዴው፡ ወኪል፡የሆነ፡ ሰው፡ ሲሞት ፤ ችሎታ፡ ሲያጣ ፤ ወይም፡ ሲከሥር ፤

(ሐ) ወኪል፡ ሆኖ ፡ ይሠራ ፡ የነበረው ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ሲፈርስ ፡ ነው ።

(፪) የውክልናው ፡ ውለታ ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ሲሆን ፡ ከሁለቱ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ በቃኝ ፡ ብሎ ፡ ሲያስታውቅ ፡ ውሉ ፡ፍጻሜ ፡ ሊያገኝ ፡ ይችላል ፤ ውክልናውን ፡ ለማፍረስ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ካለ ፡ የመሰናበቻ ፡ ጊዜ ፡ መስጠት ፡ አያስፈልግም ።

(፫) ለመሰናበቻ ፡ የሚሰጠው ፡ ጊዜ ፡ በውክልናው ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ፤ ወይም ፡ ይህ ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ። በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ሲሆን ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ የማያንስና ፡ ከመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ሲሆን ፡ ከሁለት ፡ ወር ፡ የማያንስ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፺፫ ።  ውልን ፡ በመሠረዝ ፡ ስለሚከፈል ፡ ካሣ ።**

ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የተስማሙበትን ፡ የውክልና ፡ ውል ፡ ወካዩ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሳያገኝ ፡ የሠረዘው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወኪሉ ፡ በወካዩ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ያገለገለበት ፡ ጊዜ ፤ ያቀረባቸው ፡ ደንበኞች ፤ ወይም ፡ ያዘጋጀው ፡ ወይም ፡ ያስፋፋው ፡ ገበያና ፡ ሌሎችም ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ የሰጣቸው ፡ ፍሬዎች ፡ ታስበው ፤ በርትዕ ፡ የሚገባ ፡ ካሣ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፺፬ ።  ውለታው ፡ ሲያልቅ ፡ በመካሄድ ፡ ላይ ፡ ስላሉ ፡ ሥራዎች ።**

(፩) አንድ ፡ የውክልና ፡ ስምምነት ፡ በሚያልቅበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በውክልና ፡ ሲሠራ ፡ የቈየው ፡ ወኪል ፡ ወይም ፡ ወራሹ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ የውሉ ፡ ጊዜ ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ ለተነጋገራቸው ፡ ወይም ፡ ለጨረሳቸው ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ አበል ፡ ሊቀበል ፡ ይገባል ።

(፪) የውሉ ፡ ጊዜ ፡ ሲያልቅ ፡ ማናቸውንም ፡ አበሎችና ፡ የሚከፈሉ ፡ ወጪዎች ፡ ወካዩ ፡ ወዲያውኑ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፺፭ ። የውሉ ፡ ጊዜ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ የንግድ ፡ ውድድር ፡ እንዳይደረግ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ የውል ፡ ቃል ።**

(፩) የውሉ ፡ ጊዜ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ የንግድ ፡ ወኪሉ ፡ ወካዩ ፡ ከሚሠራው ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ እንዳይሠራ ፡ ወይም ፡ ከወካዩ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ ንግድ ፡ ለሚነግድ ፡ ነጋዴ ፡ ወኪል ፡ ወይም ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ እንዳይሠራ ፡ በውክልናው ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ስምምነት ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) ከዚህ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ውል ፡ ቢኖርም ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ የበለጠ ፡ የመነገድ ፡ ውድድር ፡ ክልከላ ፡ አይጸናም ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

## ስለ ፡ ደላሎች ።

**ቍ ፡ ፺፮ ።  ትርጓሜ ።**

(፩) ደላሎች ፡ ማለት ፡ ውል ፡ የሚዋዋሉ ፡ ሰዎችን ፡ ይልቁንም ፡ እንደ ፡ ሺያጭ ፤ ኪራይ ፤ ኢንሹራንስ ፤ የማመሳለሻ ፡ ውል ፤ እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ ውሎች ፡ የሚዋ

ዋሉ ፡ ሰዎችን ፡ ፈልገው ፡ የሚያገናኙና ፡ የሚያዋውሉ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ የሞያ ፡ ተግባራቸው ፡ አድርገው ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ይሆንኑ ፡ የደላልነት ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ነው ።

(፪) ደላሎች ፡ አስማሚ ፡ ሆነው ፡ የሚያስፈጽሟቸው ፡ ውሎች ፡ ዐይነትና ፡ ግብ ፡ ወይም ፡ የሚያገናኙዋቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁኔታ ፡ ሳይታይ ፡ ነጋዴዎች ፡ ይባላሉ ።

**ቍ ፡ ፶፯ ። ለተዋዋዮች ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።**

(፩) በልማድ ፡ የታወቀ ፡ ካልሆነ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ስምምነት ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ ተዋዋዮቹ ፡ በጕዳዩ ፡ ውል ፡ ለማድረግ ፡ የተስማሙ ፡ እንደሆነ ፡ ውሉ ፡ የሚደረግበትን ፡ ሁኔታ ፡ ለተዋዋዮች ፡ ሁሉ ፡ ወዲያውኑ ፡ ደላላው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) በልማድ ፡ የታወቀ ፡ ካልሆነ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ የተዘጋጀውን ፡ ውል ፡ ባለጕዳዮቹ ፡ ካላጸደቁት ፡ ፍጹም ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ፶፰ ። ስለ ፡ ደላላው ፡ ኀላፊነት ።**

ደላላው ፡ በሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ለሚያደርገው ፡ ጉዳት ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል።

**ቍ ፡ ፶፱ ። ስለ ፡ ደላላው ፡ አበል ።**

(፩) ደላላው ፡ አስማሚ ፡ ሆኖ ፡ ውሉን ፡ ካስጨረሰ ፡ የውሉ ፡ ግዴታ ፡ ቢፈጸምም ፡ ባይፈጸምም ፡ የእርሱ ፡ አበል ፡ ሊከፈለው ፡ ይገባል ።

(፪) በልማድ ፡ የታወቀ ፡ ካልሆነ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ስምምነት ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ አበሉን ፡ የሚከፍለው ፡ የደላላውን ፡ ሥራ ፡ የጠየቀው ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፫) አበሉ ፡ በስምምነቱ ፡ ውስጥ ፡ ይወሰናል ፡ ወይም ፡ ባልተወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ ይቈረጣል ፤ የተስማሙበት ፡ አበል ፡ ከባድ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ ወይም ፡ ደላላው ፡ ከሰጠው ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ ተመዛዛኝ ፡ አለመሆኑ ፡ ሲታየው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለመቀነስ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

## ስለ ፡ ባለኮሚሲዮኖች ።

**ቍ ፡ ፷ ። ትርጓሜ ።**

(፩) ባለኮሚሲዮኖች ፡ ማለት ፡ ራሳቸውን ፡ የቻሉ ፡ ተግባረኞች ፡ ሆነው ፡ አበል ፡ ለማግኘት ፡ ባለኮሚሲዮን ፡ ስለ ፡ አደረጋቸው ፡ ሰው ፡ በራሳቸው ፡ ስም ፡ ሸቀጦችን ፡ ወይም ፡ የሚንቀሳቀሱትን ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ ማንኛቸውንም ፡ እነዚሁን ፡ የመሳሰሉ ፡ ዕቃዎችን ፡ ለመግዛት ፡ ወይም ፡ ለመሸጥ ፤ የዚሁ ፡ ዐይነት ፡

ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ወይም ፡ ማጓጓዣ ፡ ውል ፡ ለመዋዋል ፡ ግዴታ ፡ የሚገቡ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ናቸው ።

(፪) ባለኰሚሲዮኖች ፡ የሚዋዋሏቸው ፡ ወገኖችና ፡ የውሉቹ ፡ ዐይነትና ፡ ግብ ፡ እግምት ፡ ሳይገባ ፡ ነጋዴዎች ፡ ይባላሉ ።

<u>ቍ ፡ ፳፩ ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለመሆኑ ።</u>

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ግዴታዎች ፡ በሚለው ፡ መጽሐፍ ፡ በቍጥር ፡ ፪ሺ፪፻፷፩ ፡ እስከ ፡ ፪ሺ፪፻፺፪ ፡ የተጻፈው ፡ ሕግ ፡ በኰሚሲዮን ፡ ውል ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

<u>ቍ ፡ ፳፪ ። ስለ ፡ አክሲዮን ፡ ደላሎች ።</u>

(፩) በአክሲዮን ፡ ገበያ ፡ የሚሠሩ ፡ ደላላዎች ፡ ባለኰሚሲዮን ፡ ናቸው ።
(፪) ልዩ ፡ ሕግ ፡ የተሠራላቸው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የአክሲዮን ፡ ደላሎች ፡ በባለኰሚሲዮን ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ይተዳደራሉ ።

## አንቀጽ ፡ ፫ ።

## <u>ስለ ፡ ሒሳብ ።</u>

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### <u>ሒሳብ ፡ መያዝ ፡ ግዴታ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።</u>

<u>ቍ ፡ ፳፫ ። ነጋዴዎችና ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ።</u>

(፩) ማንኛውም ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ ነጋዴ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ እንደሚሠራው ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ስፋትና ፡ ዐይነት ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ልምድና ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ የሚያስፈልግ ፡ የሒሳብ ፡ መዝገቦችና ፡ ሰነዶች ፡ ሊኖሩት ፡ ይገባል ።
(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከቍጥር ፡ ፳፰ ፡ እስከ ፡ ፸ ፡ የተጻፉትን ፡ መፈጸም ፡ ይገባቸዋል ።

<u>ቍ ፡ ፳፬ ። ትንንሾች ፡ ቸርቻሪ ፡ ነጋዴዎች ።</u>

በሚወሰነው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ትንንሽ ፡ ቸርቻሪ ፡ የሆኑ ፡ ነጋዴዎች ፡ የሒሳብ ፡ መዝገብ ፡ ከመያዝ ፡ ነጻ ፡ ናቸው ።

<u>ቍ ፡ ፳፭ ። የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ልዩ ፡ ደንቦች ።</u>

ስለንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በሁለተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ የተነገሩት ፡ ልዩ ፡ ደንቦች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## መያዝ ፡ ስለሚገባቸው ፡ መዛግብቶችና ፡ ሰነዶች ።

**ቍ ፡ ፷፫ ። ንግዶችን ፡ ስለ ፡ መመዝገብ ።**

(፩) እያንዳንዱ ፡ ነጋዴ ፡ ስለሚነግደው ፡ ንግድ ፡ ዐይነትና ፡ ስላነጋገዱም ፡ ሁኔታ ፡ እስተያየት ፡ ሳያደርግ ፡ ዕለት ፡ በዕለት ፡ ንግዱን ፡ የሚመዘግብበት ፡ የሒሳብ ፡ መዝገብ ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ።

(፪) ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ በወር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የእንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ንግድ ፡ ሒሳብ ፡ ማመዛዘንና ፡ እነዚህን ፡ ንግዶች ፡ ዕለት ፡ በዕለት ፡ ለመቈጣጠር ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ሰነዶች ፡ ጠብቆ ፡ ማቈየት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፷፬ ። የዕቃ ፡ መዝገብና ፡ (እንቫንቴርና) ፤ የሒሳብ ፡ ማመዛዘኛ ፡ (ቢላን) ።**

(፩) ማንኛውም ፡ ነጋዴ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ሲጀምር ፡ የዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብና ፡ የሒሳብ ፡ ማመዛዘኛ ፡ ማዘጋጀት ፡ አለበት ።

(፪) እንደዚሁም ፡ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ በያንዳንዱ ፡ የባጀት ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ የሥራውን ፡ የዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ያለውን ፡ ሀብትና ፡ ያለበትን ፡ ዕዳ ፡ የመጨረሻ ፡ ሒሳብ ፡ ማመዛዘኛ ፡ ቢላን ፡ እና ፡ የትርፍና ፡ ኪሣራ ፡ ሒሳብ ፡ ማዘጋጀት ፡ አለበት ፤ ቢላኑና ፡ የትርፍና ፡ የኪሣራው ፡ ሒሳብ ፡ በደንበኛ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፷፭ ። ስለ ፡ መዛግብቶች ፡ አያያዝ ።**

(፩) በቍጥር ፡ ፷፫ ፡ እና ፡ ፷፬ ፡ መሠረት ፡ መያዝ ፡ የሚገባቸው ፡ መዝገቦች ፡ የቅደም ፡ ተከተል ፡ ሥርዐት ፡ በመጠበቅ ፡ እንዲሠራባቸውና ፡ አንዳችም ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ ሳይተውባቸው ፡ ወይም ፡ አንዳችም ፡ መለዋወጥ ፡ ሳይደረግባቸው ፡ እንዲጠበቁ ፡ ይገባል ።

(፪) በደንቦች ፡ መሠረት ፡ ሥልጣን ፡ ከተሰጣቸው ፡ ሹሞች ፡ አንዱ ፡ ለነዚህ ፡ መዛግብት ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ እየተሰጣቸው ፡ አጭር ፡ የፊርማ ፡ ምልክት ፡ ያደርግባቸዋል ፤ የመዛግብቶቹን ፡ ገጽ ፡ ብዛት ፡ በያንዳንዱ ፡ መዝገብ ፡ መጨረሻ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ባለሥልጣኑ ፡ ዘርዝሮ ፡ ይጽፋል ።

**ቍ ፡ ፷፮ ። የንግድ ፡ መዛግብቶችን ፡ ጠብቆ ፡ ስለ ፡ ማኖር ።**

ማናቸውንም ፡ መዝገቦችና ፡ የሒሳብ ፡ ሰነዶች ፡ የመጨረሻው ፡ ጽሕፈት ፡ ከተጻፈባቸው ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ወይም ፡ ሰነዶቹ ፡ ከተጻፉበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ወደፊት ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ጠብቆ ፡ ማኖር ፡ ይገባል ።

**ቍ ፡ ፷፯ ። ስለ ፡ ገቢና ፡ ወጪ ፡ ደብዳቤዎች ።**

የገቡት ፡ ደብዳቤዎች ፤ መልእክቶችና ፡ ቴሌግራሞች ፤ ዋናው ፡ ደብዳቤና ፡ የተ

ላኩትም ፡ ደብዳቤዎች ፤ መልእክቶች ፡ ወይም ፡ ቴሌግራሞች ፡ ግልባጭ ፡ በፋይል ፡ አግብቶ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ጠብቆ ፡ ማኖር ፡ ይገባል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## የሒሳብ ፡ መዝገቦቹን ፡ ማስረጃ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

### ቍ ፡ ፹፩ ። መዝገቦች ፡ ለባለመዝገቡ ፡ ማስረጃ ፡ ስለ ፡ መሆናቸው ።

ዳኛው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪ሺ፲፮ ፡ የተመለከተውን ፡ መከተል ፡ ግዴታ ፡ ሳይሆንበት ፡ ክርክር ፡ የተነሣው ፡ በነጋዴዎችና ፡ ወይም ፡ በንግዱ ፡ ማኅበሮች ፡ መካከል ፡ ስለ ፡ ንግዳቸው ፡ ጕዳይ ፡ ሲሆን ፡ ስለመዝገቦች ፡ አያያዝ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፉት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ የተሠሩ ፡ መዝገቦች ፡ ከሆኑ ፡ የንግድ ፡ መዝገቦችን ፡ ለባለመዝገቡም ፡ ቢሆን ፡ ማስረጃ፡ አድርጎ ፡ ሊቀበላቸው ፡ ይችላል ።

### ቍ ፡ ፹፪ ። መዝገቦች ፡ በባለመዝገቡ ፡ ላይ ፡ ማስረጃ ፡ ስለመሆናቸው ።

(፩) የንግድ ፡ መዝገቦች ፡ ለባለመዝገቡ ፡ ወይም ፡ በባለመዝገቡ ፡ ላይ ፡ አስረጅ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ስለሆነም ፡ በመዝገቡ ፡ ለመጠቀም ፡ የሚፈልገው ፡ እሱ ፡ ለሚለው ፡ ቃል ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆኑትን ፡ ቃሎች ፡ ከፍሎ ፡ ለማስቀረት ፡ አይችልም ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## የሒሳብ ፡ አያያዝ ፡ ደንቦች ።

### ቍ ፡ ፹፫ ። የዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አፈጻጸም ፡ ወሰን ።

(፩) ነጋዴዎች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎችና ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ በሚወሰነው ፡ ደንብ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በተመለከቱት ፡ ቍጥሮች ፡ የሒሳብ ፡ አያያዝ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ መሥራት ፡ አለባቸው ።

(፪) በአንዳንድ ፡ ዐይነት ፡ ነጋዴዎችና ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ፡ የተለዩ ፡ ደንቦች ፡ ሊወሰንላቸው ፡ ይችላል ፤ እንዚሁም ፡ ደንቦች ፡ በንግድ ፡ ሥራው ፡ ዐይነትና ፡ ከፍተኝነት ፡ መጠን ፡ በያይነቱ ፡ ለመሆን ፡ ይችላሉ ።

### ቍ ፡ ፹፬ ። ነጋዴው ፡ በሒሳብ ፡ ማመዛዘኛ ፡ ስላለው ፡ ሒሳብ ፡ (አክቲፍ) ።

(፩) ነጋዴው ፡ በሒሳብ ፡ ማመዛዘኛ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ሒሳብ ፡ ክፍል ፡ በጠቅላላ ፡ ገቢ ፡ የሒሳብ ፡ ቀሪዎችና ፡ ባለበትም ፡ ሒሳብ ፡ ክፍል ፡ በጠቅላላ ፡ ወጪ ፡ የሒሳብ ፡ ቀሪዎች ፡ ማሳየት ፡ አለበት ።

(፪) ባለው ፡ ሒሳብ ፡ ክፍል ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተርታ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ አድ ርጎ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(ሀ) የመመሥረቻ ፡ ወጪዎችን ፤
(ለ) የማይንቀሳቀሱ ፡ ቋሚ ፡ የሆኑትን ፡ ንብረቶች ፤
(ሐ) ንግዱ ፡ የሚከናወንባቸው ፡ የጥቅም ፡ ማስገኛ ፡ ሀብቶች ፤
(መ) በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የሚገኙ ፡ ወይም ፡ ተቀማጭ ፡ የሆኑ ፡ ሀብቶችን ፤
(ሠ) ውጤቶችን ፡ (ከኪሣራና ፡ ትርፍ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ነጋዴው ፡ ያለውን ፡ ገቢ ፡ ሒሳብ) ።

__ቍ ፡ ፸፭ ። ነጋዴው ፡ በሒሳብ ፡ ማመዛዘኛ ፡ ስላለበት ፡ ሒሳብ ፡ (ፖሲፍ) ።__

ባለበት ፡ ሒሳብ ፡ ክፍል ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተርታ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ አድ ርጎ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፩) ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ (ካፒታል) ፡ እና ፡ ስለ ፡ መጠባበቂያ ፡ ተቀማጭ ፡ የሆኑትን ፡ ገንዘቦች ፤

(፪) እንደገና ፡ የዞረውን ፡ የንግድ ፡ ትርፍ ፡ ድምርና ፡ ስለ ፡ ማደሻ ፡ ተቀማጭ ፡ የሆኑትን ፡ ገንዘቦች ፤

(፫) ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ሥንቅና ፡ ስለ ፡ ረዥም ፡ ጊዜ ፡ ዕዳዎች ፡ መጠባበቂያ ፡ የሆኑ ፡ ገንዘቦችንና ፡ ያለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ጡረታ ፡ የተቀመጠውን ፡ ገንዘብ ፤

(፬) ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ የሆኑትን ፡ ዕዳዎች ፤

(፭) ውጤቶችን ፡ (ከኪሣራና ፡ ትርፍ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ነጋዴው ፡ ያለበትን ፡ ወጪ ፡ ሒሳብ) ።

__ቍ ፡ ፸፮ ። አሳቂ ፡ ለሚሆን ፡ ነገር ፡ የዋጋ ፡ መተኪያ ፡ ገንዘቦች ፡ የውጭ ፡ መጠባበ ቂያ ፡ ገንዘቦች ፤ የማስተካከያ ፡ ሒሳቦች ።__

(፩) አሳቂ ፡ ለሆነ ፡ ነገር ፡ የዋጋ ፡ መተኪያ ፡ ገንዘቦችና ፡ መጠባበቂያ ፡ ገን ዘቦች ፡ በነጋዴው ፡ ሒሳብ ፡ ማመዛዘኛ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ የሒሳብ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ መመዝገብ ፡ አለባቸው ።

(፪) የማስተካከያ ፡ ሒሳቦች ፡ በነጋዴው ፡ ሒሳብ ፡ ማመዛዘኛ ፡ ባለው ፡ ወይም ፡ ባለበት ፡ ሒሳብ ፡ እነሱን ፡ በሚመለከት ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ መመዝገብ ፡ አለ ባቸው ።

__ቍ ፡ ፸፯ ። የመመሥረቻው ፡ ወጪዎች ።__

የመመሥረቻ ፡ ወጪዎች ፡ ማለት ፡ ሥራው ፡ የሚከናወንበት ፡ የጥቅም ፡ ማስ ገኛ ፡ ቤቱ ፡ በተቋቋመ ፡ ጊዜ ፡ የሆነው ፡ ወጪ ፡ ወይም ፡ የጥቅም ፡ ማስገኛ ፡ የሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ መሣሪያዎችን ፡ ለመግዛት ፡ ወጪ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

BACK



**ቍ ፡ ፻፹፰ ። የማይንቀሳቀሱ ፡ ቋሚዎች ፡ የሆኑት ፡ ሀብቶች ።**

(፩) የማይንቀሳቀሱ ፡ ቋሚዎች ፡ ሀብቶች ፡ ማለት ፡ ለሥራ ፡ የሚያገለግሉ ፡ የጥቅም ፡ ማስገኛ ፡ ወይም ፡ ለሥራ ፡ ከማያገለግሉ ፡ ከጥቅም ፡ ማስገኛ ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አላቂ ፡ ነገር ፡ ዋጋቸው ፡ በሙሉ ፡ የተተካ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ቋሚዎች ፡ ሀብቶች ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አላቂ ፡ ነገር ፡ ዋጋቸው ፡ በመተካት ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ቋሚዎች ፡ የሆኑ ፡ ሁሉ ፡ ሀብቶች ፡ ናቸው ።

(፪) በሥራ ፡ የሚያገለግሉ ፡ የጥቅም ፡ ማስገኛ ፡ ቋሚዎች ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ሀብቶች ፡ ማለት ፡ ንግድ ፡ ቤቱ ፡ ለመሸጥ ፡ ወይም ፡ ለመለወጥ ፡ ሳይሆን ፡ ቋሚ ፡ መሣሪያ ፡ እንዲሆኑለት ፡ የገዛቸው ፡ ወይም ፡ የሠራቸው ፡ ንብረቶች ፡ ሁሉ ፡ ናቸው ።

(፫) በሥራ ፡ የማያገለግሉ ፡ ከጥቅም ፡ ማስገኛ ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ ቋሚዎች ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ሀብቶች ፡ ማለት ፡ የሥራ ፡ መሣሪያዎች ፡ ያልሆኑ ፡ ንግድ ፡ ቤቱ ፡ ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ የተሠሩ ፡ ወይም ፡ የተገዙ ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ የሆኑ ፡ ንብረቶች ፡ ሁሉ ፡ ናቸው ።

(፬) ስለ ፡ አላቂ ፡ ነገር ፡ ዋጋቸው ፡ በሙሉ ፡ የተተካ ፡ ቋሚዎች ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ሀብቶች ፡ ማለት ፡ ዋጋቸው ፡ ትክክል ፡ በሆኑ ፡ ድርሻዎች ፡ ተተክቶ ፡ ያለቀላቸውና ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ቋሚዎች ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ የሆኑት ፡ ሀብቶች ፡ ናቸው ።

(፭) ስለ ፡ አላቂ ፡ ነገር ፡ ዋጋቸው ፡ በመተካት ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ቋሚዎች ፡ የሆኑት ፡ ሀብቶች ፡ ማለት ፡ ያመቱ ፡ ሒሳብ ፡ በመዘጊያው ፡ ዋጋቸው ፡ በሙሉ ፡ ያልተቀነሱ ፡ ሆነው ፡ የሚገኙ ፡ ሀብቶች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፻፹፱ ። ያልተሸጡ ፡ ዕቃዎች ፡ የጥቅም ፡ ማስገኛ ፡ ሀብቶች ።**

ያልተሸጡ ፡ ዕቃዎች ፡ የጥቅም ፡ ማስገኛ ፡ ሀብቶች ፡ ማለት ፡ ሸቀጦች ፡ ዕቃዎች ፡ የተከማቹ ፡ ዕቃዎች ፡ በገሚስ ፡ በሙሉ ፡ የተሠሩ ፡ ዕቃዎች ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ ዕቃዎችና ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ መጠቅለያዎች ፡ የሆኑት ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፻፺ ። ዋና ፡ ገንዘብና ፡ (ካፒታልና) ፡ የመጠባበቂያ ፡ ገንዘቦች ።**

(፩) ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ከባለቤቱ ፡ ወይም ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ በየድርሻቸው ፡ በገንዘብ ፡ ወይም ፡ በዐይነት ፡ ለጥቅም ፡ ማስገኛ ፡ የንግድ ፡ ቤቱ ፡ የተሰጠው ፡ መሠረታዊ ፡ ሀብቱ ፡ ነው ።

(፪) በንግድ ፡ ቤቱ ፡ እጅ ፡ ከዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ሳይቀላቀል ፡ ተቀማጭ ፡ የሆነ ፡ ትርፍ ፡ ሁሉ ፡ የመጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፡ ይባላል ።

**ቍ ፡ ፻፺፩ ። የዞረ ፡ ድምር ።**

የዞረ ፡ ድምር ፡ ማለት ፡ ባለፉት ፡ የሥራ ፡ ዘመኖች ፡ የተገኙት ፡ ሳይከፋፈሉ ፡ የቀሩት ፡ ትርፎች ፡ ወይም ፡ በመጠባበቂያ ፡ ሒሳብ ፡ ተቀማጭ ፡ ያልሆ

BACK



ኑና ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ኪሣራዎች ፡ ማስተካከያ ፡ ከትርፉ ፡ ገንዘብ ፡ ያልተነሣላቸው ፡ ሒሳቦች ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፹፪ ። ስለ ፡ አላቂ ፡ ነገር ፡ የዋጋ ፡ መተኪያና ፡ የገንዘብ ፡ ሥንቅ ፡ (መጠባበቂያ) ፡ ገንዘቦች ።

(፩) ስለ ፡ አላቂ ፡ ነገር ፡ የዋጋ ፡ መተኪያ ፡ ገንዘቦች ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ቋሚ ዎች ፡ በሆኑት ፡ ላይ ፡ ለሚደርስባቸው ፡ የዋጋ ፡ ጕድለትና ፡ በጊዜም ፡ ብዛት ፡ ዋጋ ቸው ፡ እየተቀነሰ ፡ ስለ ፡ መሄዱ ፡ ለዚሁም ፡ የሒሳብ ፡ መጠንቀቂያ ፡ መለኪያ ፡ ማለት ፡ ነው ።

(፪) የአደጋ ፡ ኪሣራ ፡ የገንዘብ ፡ ሥንቅ ፡ (መተኪያ) ፡ ገንዘቦች ፡ ማለት ፡ የሚገጥመውን ፡ አደጋ ፡ ማለት ፡ እጕልቶ ፡ የሚታወቁትን ፡ አደጋዎች ፡ እኒሁም ፡ በየዓመቱ ፡ የሒ ሳብ ፡ መዝጊያ ፡ ጊዜ ፡ ሊገነዘቧቸው ፡ የሚቻሉትን ፡ አደጋዎች ፡ ኪሣራ ፡ ለመሸፈን ፡ የሚያገለግሉ ፡ ናቸው ።

(፫) ስለ ፡ ዋጋ ፡ ጕድለት ፡ መተኪያ ፡ ገንዘቦች ፡ የተባሉት ፡ ነጋዴው ፡ ባለው ፡ ሒሳብ ፡ በተመለከቱት ፡ ንብረቶች ፡ ስለሚደርስባቸው ፡ የዋጋ ፡ ጕድለት ፡ መተኪያ ፡ የሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፹፫ ። የማስተካከያ ፡ ሒሳቦች ።

የማስተካከያ ፡ ሒሳቦች ፡ ማለት ፡ በተራ ፡ ሒሳቦች ፡ ውስጥ ፡ ሳይመለከቱ ፡ የቃ ለፉትን ፡ ወይም ፡ ተፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ገንዘቦች ፡ የሚያስተካክሉና ፡ በእርግጥ ፡ ራሱን ፡ የሚመለከተውን ፡ ዕዳና ፡ ተፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ በተወሰነ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ለማስተሳሰር ፡ ለዚሁ ፡ ብቻ ፡ የሆኑ ፡ ዕዳዎችንና ፡ ገን ዘቦችን ፡ የሚተኩ ፡ ሒሳቦች ፡ ማለት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፹፬ ። ስለ ፡ አገማመት ።

(፩) የማይንቀሳቀሱ ፡ ቋሚዎች ፡ ሀብቶች ፡ የሆኑት ፡ በሒሳብ ፡ ማመዛዘኛ ፡ ውስጥ ፡ በመሠረታዊ ፡ ዋጋቸው ፡ ይመዘገባሉ ፤ ወይም ፡ እንደገና ፡ ተገምተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደገና ፡ በተገመቱበት ፡ ዋጋቸው ፡ ይመዘገባሉ ።

(፪) በተቈጠሩበት ፡ ቀን ፡ ያሉት ፡ ሸቀጦች ፤ ዕቃዎች ፤ የዕቃ ፡ መጠቅለያዎ ችና ፡ የተከማቹ ፡ ዕቃዎች ፡ የሚገመቱት ፡ በሚያወጡት ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ነው ።

(፫) ተንቀሳቃሽ ፡ ያልሆኑት ፡ ንብረቶች ፡ በሒሳብ ፡ ማመዛዘኛ ፡ ሒሳብ ፡ ክፍል ፡ በተገዙበት ፡ ዋጋ ፡ ይመዘገባሉ ።

(፬) ቅንጣቢዎቹ ፤ (ከፋብሪካ ፡ ሥራ ፡ የሚቀሩ ፡ ልቅምቃሚና ፡ ጥራጊዎቹ) ፡ በሒ ሳብ ፡ ማጣሪያው ፡ ቀን ፡ ባለው ፡ ገበያ ፡ ዋጋ ፡ ይገመታሉ ፤ ወይም ፡ የገበያ ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ያልኖረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያወጣሉ ፡ ተብሎና ፡ በሚሰጣቸው ፡ ዋጋ ፡ ይገመታሉ ።

(፭) በሒሳብ ፡ ማመዛዘኛ ፡ ሒሳብ ፡ ክፍል ፡ ተሠርቶ ፡ ያለቀላቸው ፡ ዕቃዎ

ችና ፡ በመሠራት ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ ዕቃዎች ፡ በሒሳብ ፡ ማጣሪያው ፡ ቀን ፡ ባለው ፡ ዋጋቸው ፡ ይመዘገባሉ ።

ቍ ፡ ፹፭ ። ስለ ፡ ዋጋ ፡ ጕድለት ፡ መተኪያ ፡ ገንዘቦች ።

ዕቃው ፡ በተቈጠረበት ፡ ቀን ፡ ተከማችተው ፡ የሚገኙት ፡ ሸቀጦች ፤ በገሚስ ፡ የተሠሩት ፡ ዕቃዎች ፤ በሙሉ ፡ የተሠሩ ፡ ዕቃዎች ፤ የዕቃ ፡ መጠቅለያዎች ፤ እርግጠኛ፡ ዋጋቸው፡ ከወጣበት ፡ ዋጋ ፡ በታች ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ነጋዴው ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበሩ ፡ ስለ ፡ ዋጋ ፡ ጕድለት ፡ መተኪያ ፡ የሚሆን ፡ ገንዘቦች ፡ ማደራጀት ፡ አለባቸው ።

እንቀጽ ፡ ፪ ።

ስለ ፡ ንግድ ፡ መዝገብ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

ስለ ፡ ንግድ ፡ መዝገብ ፡ አቋቋም ።

ቍ ፡ ፹፮ ። በየአገሩ ፡ የሚቋቋሙ ፡ የንግድ ፡ መዝገቦችና ፡ ጠቅላይ ፡ የንግድ ፡ መዝገብ ።

(፩) የየአገሩ ፡ የንግድ ፡ መዝገብ ፡ እያንዳንዱ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ይቋቋማል ።

(፪) ጠቅላይ ፡ የንግድ ፡ መዝገብ ፡ ከንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ ዘንድ ፡ ይቋቋማል ።

ቍ ፡ ፹፯ ። የንግድ ፡ ኦፊሲየል ፡ ጋዜጣ ።

(፩) ማናቸውም ፡ ዋና ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ሆነው ፡ የተመዘገቡ ፡ ወይም ፡ ከመዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የተለወጡ ፡ ወይም ፡ የተፋቁ ፡ ወደ ፡ ጠቅላይ ፡ የንግድ ፡ መዝገብ ፡ ሲላኩ ፡ ያለአንዳች ፡ መዘግየት ፡ በንግድ ፡ ኦፊሲየል ፡ ጋዜጣ ፡ ታትመው ፡ ይወጣሉ ።

(፪) ስለ ፡ አንዳንድ ፡ ጕዳዮች ፡ ባጭሩ ፡ የተዋጡ ፡ የመዝገብ ፡ ቅጂዎችን ፡ ብቻ ፡ በጋዜጣ ፡ ለማውጣት ፡ በደንቦች ፡ ሊፈቀድ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፹፰ ። ስለ ፡ ማስታወቅ ።

(፩) ነጋዴዎች፡ የሆኑ፡ ሰዎች፡ በንግድ፡ መዝገብ፡ የማስገባትን፡ ነገር፡ የሚፈጽሙት፡ ለየአገሩ ፡ የንግድ ፡ መዝገብ ፡ ኀላፊ ፡ ለሆኑ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ መግለጫቸውን ፡ (ዲክላራሲዮን) ፡ አቅርበው ፡ በማስመዝገብ ፡ ነው ፤ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ የተመዘገበው ፡ ከተመዘገበበት ፡ ዕለት ፡ ቀጥሎ ፡ ካለው ፡ የሥራ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

(፪) የንግድ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ማኅበሮች ፡ የሥራቸውን ፡ መግለጫ ፡ (ዲክላራሲ

ዮን) ፡ ሰጥተው ፡ የሚያስመዘግቡበት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በሁለተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተሠርቶላቸዋል ።

ቍ ፡ ፹፱ ። ለአገሩ ፡ ክፍል ፡ የንግድ ፡ መዝገቦች ፡ አጠባበቅ ።

የአገሩ ፡ ክፍል ፡ የንግድ ፡ መዝገቦች ፡ በያንዳንዱ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ በሚሾመው ፡ ሰው ፡ ያዥነት ፡ ይጠበቃሉ ።

ቍ ፡ ፺ ። ጠቅላይ ፡ መዝገብ ።

(፩) ጠቅላይ፡ መዝገብ ፡ የሚቀመጠው ፡ የንግድ ፡ ጠቅላይ ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት፡ ቤት ፡ በሚባለው ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ በንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ በልዩ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

(፪) ይህም ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሊሠራው ፡ የሚገባው ፤

(ሀ) በየስፍራው ፡ ባሉት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መዝገቦች ፡ የተጻፉትን ፡ የየአንዳንዱን ፡ የተመዘገበውን ፡ ሰው ፡ የሚመለከቱ ፡ አስረጂዎች ፡ በሙሉ ፡ ሰብስቦ ፡ መመዝገብ ፤

(ለ) ስለ ፡ ንግድ ፡ መዝገቦች ፡ የወጡት ፡ ሕጎች ፡ በትክክል ፡ እንዲፈጸሙ ፡ መጠባበቅ ፤

(ሐ) በቍጥር ፡ ፹፯ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በንግድ ፡ አፊሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ሁሉ ፡ እንዲወጡ ፡ ማድረግ ።

(መ) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በ፪ተኛው ፡ መጽሐፍ ፤ የተነገሩትን ፡ ማኅበሮች ፡ የሚመለከቱ ፡ ጽሑፎች ፤ ሰነዶች ፤ ማስታወቂያዎች ፡ መቀበልና ፡ ጠብቆ ፡ ማስቀመጥ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፺፩ ። ስለ ፡ ኀላፊነት ።

የንግድ ፡ መዛግብቶች ፡ ኀላፊ ፡ የሆኑ ፡ ሠራተኞች ፡ ራሳቸው ፡ ወይም ፡ እነሱ ፡ የቀጠሩዋቸው ፡ ሠራተኞች ፡ በአደረጉት ፡ ጥፋት ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፺፪ ። የተመዘገበ ፡ ለመሆኑ ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የተወሰነውን ፡ ገንዘብ ፡ ከፍሎ ፡ በየአገሩ ፡ ንግድ ፡ መዝገብ ፡ ወይም ፡ በጠቅላይ ፡ መዝገብ ፡ የገባውን ፡ ቃል ፡ ግልባጭ ፡ ወይም ፡ ከመዝገቡ ፡ በአጭር ፡ የተውጣጣ ፡ ቃል ፡ እንዲሰጠው ፡ ወይም ፡ የሚጠይቀው ፡ ጉዳይ ፡ ያልተመዘገበ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አለመመዝገቡን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ እንዲሰጠው ፡ የአገሩ ፡ መዝገብ ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ የጠቅላይ ፡ መዝገብ ፡ ሠራተኛ ፡ የሆነውን ፡ ባለሥልጣን ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

BACK



**ቍ ፡ ፺፫ ። በነጋዴው ፡ ወረቀቶች ፡ ላይ ፡ መግባት ፡ ስለሚያስፈልጉ ፡ ነገሮች ።**

ማንኛዎቹም ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ የተመዘገቡ ፡ ነጋዴዎች ፡ ሁሉ ፡ በሚሠሩባቸው ፡ ወረቀቶች ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ የተመዘገቡበትን ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛትና ፡ የመዝገብ ፡ ቍጥራቸውን ፡ መግለጽ ፡ አለባቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ስለሚገቡ ፡ ጉዳዮች ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፺፬ ። በመዝገብ ፡ ስለሚገቡ ።**

ማንኛቸውም ፡ ዋና ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ወይም ፡ ማሟያ ፡ ሆነው ፡ የሚመዘገቡ ፡ ማንኛቸውም ፡ የተደረጉ ፡ መለዋወጦች ፡ ወይም ፡ የተሰረዙ ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ መግባት ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፺፭ ። በመዝገብ ፡ የማግባቱ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።**

(፩) በመዝገብ ፡ ማግባት ፡ የሚቻለው ፡ የሚያስመዘግበው ፡ ሰው ፡ በጽሑፍ ፡ መግለጫውን ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(፪) ከመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ የሚሰረዝ ፡ ነገር ፡ ሲኖር ፡ በቍጥር ፡ ፻፲፬ ፡ በተመለከተው ፡ ሥልጣን ፡ ሲታዘዝ ፡ ሊሰረዝ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፺፮ ። ስለ ፡ መግለጫው ፡ አሠራር ፡ (ፎርም) ።**

(፩) በቍጥር ፡ ፺፭ ፡ (፩) መሠረት ፡ የሚቀርበው ፡ መግለጫ ፡ በጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ በሦስት ፡ ግልባጮች ፡ ተሠርቶ ፡ አስመዝጋቢው ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ እንደራሴው ፡ ፈርሞበት ፡ የየአገሩ ፡ መዝገብ ፡ ሥራ ፡ ኀላፊ ፡ ለሆነው ፡ ሠራተኛ ፡ ይቀርባል ።

(፪) በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አስፈላጊዎቹ ፡ ሰነዶች ፡ ሁሉ ፡ (ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ) ፡ ከማመልከቻው ፡ ጋራ ፡ አባሪ ፡ ሆነው ፡ ይቀርባሉ ።

(፫) በመዝገብ ፡ የሚገባው ፡ ነገር ፡ ማስመዝገብ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነበት ፡ እንሥቶ ፡ በሁለት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መግለጫው ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፺፯ ። የመግለጫውን ፡ ቃል ፡ ትክክለኛነት ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ።**

(፩) ለመመዝገብ ፡ የሚያመለክተው ፡ ሰው ፡ የሚያቀርበውን ፡ የማመልከቻ ፡ ቃል ፡ ትክክለኛነት ፡ የመዝገቡ ፡ ሥራ ፡ ኀላፊ ፡ ሠራተኛ ፡ ማጣራት ፡ አለበት ፤ አንድ ፡

ሰውም ፡ በነጋዴነት ፡ ሊመዘገብ ፡ ሲል ፡ በአመለከተ ፡ ጊዜ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ በተለይም ፡ የሚመዘገብበትን ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ሕጉ ፡ የሚያዛቸውን ፡ ሁኔታዎች ፡ (ግዴታዎች) ፡ ሁሉ ፡ መፈጸምና ፡ አለመፈጸሙን ፡ አጥብቆ ፡ ማረጋገጥ ፡ ኃላፊ ፡ የሆነው ፡ ሠራተኛ ፡ ተግባር ፡ ነው ።

(፪) ሠራተኛው ፡ ማናቸውም ፡ በሕግ ፡ የታዘዙት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ በመግለጫው ፡ ውስጥ ፡ መጻፋቸውን ፡ እንዲሁም ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃዎችን ፡ ሁሉ ፡ በመግለጫው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውም ፡ ቃል ፡ ከነዚህ ፡ ማስረጃዎች ፡ ጋራ ፡ የሚስማማ ፡ መሆኑን ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ።

(፫) ኃላፊ ፡ የሆነው ፡ ሠራተኛ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ተጨማሪ ፡ አስረጂ ፡ ጽሑፎች፡ እንዲያቀርብ፡ የጐደለውንም፡ ጽሑፍ ፡ እንዲሞላ ፡ ሊጠይቀው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፺፰ ። በሚቀርበው ፡ መግለጫ ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸመው ።

(፩) መግለጫው ፡ በትክክል ፡ የተሞላ ፡ ሆኖ ፡ ያገኘው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኃላፊ ፡ የሆነው ፡ ሠራተኛ ፡ መግለጫውን ፡ በመዝገብ ፡ አግብቶ ፡ መግለጫው ፡ የቀረበበትን ፤ ተመዝግቦ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ የተመዘገበበትን ፡ ቀንና ፡ የመዝገቡን ፡ ቍጥር፡ ከጻፈበት ፡ በኋላ ፡ እንዱን ፡ ግልባጭ ፡ ለአመልካቹ ፡ ይሰጠዋል ።

(፪) አስመዝጋቢው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የንግዱ ፡ ማኅበር ፡ እንደ ፡ መሆናቸው ፡ መጠን ፡ እየታየ ፡ በሁለት ፡ የተለያዩ ፡ ቍጥሮች ፡ ይሠራል ።

(፫) ኃላፊ ፡ የሆነው፡ ሠራተኛ፡ የማመልከቻውን ፡ ግልባጭ ፡ አስቀርቶ ፡ በዶሴዉ ፡ ማስቀመጥ ፡ አለበት ።

(፬) ሦስተኛውን ፡ ግልባጭ ፡ ወደ ፡ ጠቅላይ ፡ የንግድ ፡ መዝገብ ፡ ክፍል ፡ ያስተላልፋል ።

ቍ ፡ ፺፱ ። በሠራተኛውና ፡ ባመልካቹ ፡ መካከል ፡ ስለሚነሣ ፡ ክርክር ።

በአመልካቹና ፡ በመዝገቡ ፡ ኃላፊ ፡ ሠራተኛ ፡ መካከል ፡ የሚነሣውን ፡ ማንኛውንም ፡ ክርክር ፡ የንግድ ፡ ሚኒስትር ፡ ይወስነዋል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## በመዝገብ ፡ ስለ ፡ መግባት ።

ቍ ፡ ፩ ። በመዝገብ ፡ መግባት ፡ ያለባቸው ፡ ሰዎች ።

(፩) በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ ማንኛውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወይም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ በመዝገብ ፡ መግባት ፡ አለበት ።

(፪) የንኡስ፡ ቍጥር፡ (፩)፡ ውሳኔ፡በተለይ፡ በሚከተሉት፡ ሰዎች፡ ላይ፡ ይፈጸማል ።

BACK



(ሀ) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ ነጋዴ ፡ በሆነ ፡ በማንኛውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወይም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ላይ ፤

(ለ) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፲ ፡ መሠረት ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበር ፡ በሆነ ፡ በማንኛውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወይም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፤

(ሐ) በማንኛዎችም ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ በሚሠሩ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ድርጅቶችና ፡ በማንኛዎችም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ የንግድ ፡ እንደ ራሴዎችና ፡ ወኪሎች ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ማኅበሮች ፡ ወይም ፡ ድርጅ ቶች ፡ ላይ ።

(፫) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፪)(ሐ) ለተጻፉት ፡ ድርጅቶች ፡ የሚፈጸም ፡ ልዩ ፡ ደንብ ፡ እንዲወጣ ፡ ይደረጋል ።

ቍ ፡ ፻፩ ። በመዝገብ ፡ ለመግባት ፡ ማመልከቻ ፡ ማቅረብ ፡ ያለባቸው ፡ ሰዎች ።

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ በወኪሉ ፡ አማካይነት ፡ በነጋዴነት ፡ መዝግ ቡኝ ፡ ሲል ፡ ማመልከቻ ፡ ካላቀረበ ፡ በስተቀር ፡ በነጋዴነት ፡ ሊመዘገብ ፡ አይ ችልም ።

(፪) ነጋዴው ፡ ንግዱን ፡ በጀመረ ፡ በሁለት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ማመልከቻውን ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፫) ማመልከቻውን ፡ ወኪሉ ፡ በሚያቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ ሲሆን ፡ የወኪልነቱ ፡ ሥልጣን ፡ ከማመልከቻው ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ መያያዝ ፡ ይገባዋል ።

ቍ ፡ ፻፪ ። ቀድሞ ፡ የተመዘገበውን ፡ ነጋዴ ፡ ስለ ፡ መሰረዝ ።

አንድ ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ (መደበኛ ፡ ንብረት) ፡ የገዛ ፡ ወይም ፡ የተከራየ ፡ የቀ ድሞው ፡ ነጋዴ ፡ መዝገብ ፡ ከመዝገቡ ፡ እስከ ፡ ተሰረዘ ፡ ድረስ ፡ ገዥው ፡ ወይም ፡ ተከራዩ ፡ በመዝገብ ፡ ሊገባ ፡ አይችልም ።

ቍጥር ፡ ፻፫ ። ስለ ፡ መመዝገቢያ ፡ ስፍራ ።

(፩) የመመዝገቢያ ፡ ማመልከቻ ፡ የሚቀርበው ፡ ተመዝጋቢው ፡ ሰው ፡ የንግዱን ፡ ሥራ ፡ በሚሠራበት ፡ ስፍራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ካለው ፡ የንግድ ፡ መዝገብ ፡ ነው ። አመልካቹም ፡ ብዙ ፡ ንግዶች ፡ የሚነግድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዋናው ፡ የንግዱ ፡ ቦታ ፡ በተቋቋመበት ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የንግድ ፡ መዝገብ ፡ ማመልከቻውን ፡ ያቀርባል ።

(፪) የንግዱም ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ነጋዴው ፡ የንግዱ ፡ ዋና ፡ ቅርንጫፍ ፡ ወይም ፡ ወኪል ፡ ባለበት ፡ ስፍራ ፡ ባለው ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ለተቋቋመው ፡ የንግድ ፡ መዝገብ ፡ ማመልከቻውን ፡ ያቀርባል ።

BACK



ቍ ፡ ፲፬ ። በአጭር ፡ ስለሚደረግ ፡ መመዝገብ ።

(፩) ማንም ፡ ነጋዴ ፡ ቢሆን ፡ በዋናነት ፡ በብዙ ፡ የአገር ፡ ክፍል ፡ የንግድ ፡ መዝገቦች ፡ ለመመዝገብ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ከአንድ ፡ የበለጠ ፡ መዝገብ ፡ ቍጥር ፡ ሊሰጠው ፡ አይቻልም ።

(፪) በዋናነት ፡ ከተመዘገበበት ፡ ቦታ ፡ በስተቀር ፡ በብዙ ፡ ስፍራዎች ፡ የሚነግድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ የሚገኙ ፡ የቅርንጫፍ ፡ ወይም ፡ የወኪል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ያሉት ፡ ነጋዴ ፡ መጀመሪያ ፡ የተመዘገበበት ፡ ዋናው ፡ መዝገብ ፡ እየተጠቀሰ ፡ በአጭር ፡ ቃል ፡ በየቦታዎቹ ፡ እንዲመዘገብለት ፡ ይጠይቃል ።

ቍ ፡ ፲፭ ። ነጋዴው ፡ መጀመሪያ ፡ በዋና ፡ መዝገብ ፡ ሲያስገባ ፡ ማጻፍ ፡ ስለሚገባው ፡ ነገር ።

አንድ ፡ ነጋዴ ፡ መጀመሪያ ፡ ዋና ፡ መዝገብ ፡ ለማስገባት ፡ ማመልከቻ ፡ ሲያቀርብ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተሉትን ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

(ሀ) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስሙን ፤

(ለ) የተወለደበትን ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፤

(ሐ) ዜግነቱን ፤

(መ) የግል ፡ አድራሻውን ፤

(ሠ) አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ የቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ጉባኤ ፡ የፈቀደበትን ፡ የጽሑፍ ፡ ቀን ፤

(ረ) ያገባ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የተጋባበትን ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፤ እንዲሁም ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ መኖርና ፡ አለመኖሩን ፤ የጋብቻ ፡ ውል ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ የተቀመጠበትን ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ሰው ፡ ስም ፤

(ሰ) የንግዱን ፡ ዓላማ ፤

(ሸ) ንግዱን ፡ እርሱ ፡ ያቋቋመው ፡ ወይም ፡ የገዛው ፡ ወይም ፡ የተከራየው ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ማመልከት ፤ ከቀድሞ ፡ ነጋዴ ፡ የተከራየው ፡ ሲሆን ፡ የቀድሞውን ፡ ነጋዴ ፡ ስምና ፡ ለመመዝገቡ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ መረጃዎች ፤

(ቀ) የንግዱን ፡ ስም ፤

(በ) የሚነግድበት ፡ የተለየ ፡ የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሰሌዳ ፤

(ተ) የንግዱ ፡ መደብር ፡ የሚገኝበትን ፡ አድራሻ ፤

(ቸ) ነጋዴው ፡ በተመዘገበበት ፡ ስፍራ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ቦታዎች ፡ የሚሠራቸው ፡ ሌሎች ፡ የንግድ ፡ መደብሮች ፤ ቅርንጫፎች ፡ ወይም ፡

BACK



ውክልናዎች ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚገኙበትን ፡ አድራሻ ፤

(ኀ) የሥራ ፡ አስኪያጂዎች ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሥልጣናቸውም ፤ ቅርንጫፉን ፡ በማስተዳደር ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ መሆኑን ፤

(ነ) ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለመነገድ ፡ የንግድ ፡ ፈቃድ ፡ የተሰጠበትን ፡ ቀን ።

**ቍ ፡ ፺፯ ። የሚመዘገበው ፡ በአጭር ፡ ቃል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሊጻፍ ፡ የሚገባው ።**

በአጭር ፡ ቃል ፡ ለመመዝገብ ፡ ማመልከቻ ፡ የሚያቀርብ ፡ ነጋዴ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተሉትን ፡ መግለጽ ፡ ይገባዋል ።

(ሀ) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስሙን ፤

(ለ) ዜግነቱን ፤

(ሐ) የግል ፡ አድራሻውን ፤

(መ) የንግዱን ፡ መደብር ፤ የቅርንጫፉን ፡ ወይም ፡ የውክልናውን ፡ ስም ፤

(ሠ) የንግዱ ፡ መደብር ፡ ቅርንጫፉ ፤ ወይም ፡ ውክልናው ፡ የሚገኝበትን ፡ አድራሻ ፤

(ረ) የንግዱን ፡ ዓላማ ፤

(ሰ) የሥራ ፡ አስኪያጁን ፡ ስምና ፡ ሥልጣኑም ፡ ቅርንጫፉን ፡ በማስተዳደር ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፤

(ሸ) እንዲነግድ ፡ ፈቃድ ፡ የተሰጠበትን ፡ ቀን ፤ ቢኖር ፡

(ቀ) በዋናነት ፡ የተመዘገበበትን ፡ ቦታና ፡ የመዝገቡን ፡ ቍጥር ።

**ቍ ፡ ፺፰ ። የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ።**

ስለ ፡ ንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ፡ መመዝገብ ፡ ጒዳይ ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ የሁለተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ተገቢ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## የተመዘገበውን ፡ በመለዋወጥ ፡ ወይም ፡ በተጨማሪ ፡ ስለሚደረግ ፡ የመመዝገብ ፡ ሥራ ።

**ቍ ፡ ፺፱ ። የተመዘገበውን ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።**

(፩) ማንኛውም ፡ የተመዘገበ ፡ ነጋዴ ፡ በመዝገብ ፡ ሲገባ ፡ የተጻፈውን ፡ የሚለውጥ ፡ አንድ ፡ ሁኔታ ፡ (ወይም ፡ አድራጎት) ፡ ከደረሰበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ከመዝገቡ ፡ የገባው ፡ ቃል ፡ እንዲለወጥለት ፡ ማመልከት ፡ ይገባዋል ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) መሠረት ፡ የሚቀርበውን ፡ ማመልከቻ ፡ ማንኛውም ፡ ሕጋዊ ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ማመልከት ፡ ይችላል ።

BACK



(፫) በተለየም፡ ሥራ፡ አስኪያጁን ፡ ሲሾር ፡ የተመዘገበው ፡ እንዲለወጥ ፡ ማድ ረግ ፡ ይገባዋል ።

ቍ ፡ ፻፱ ። ስለ ፡ ሰዎች ፡ በተጨማሪ ፡ ስለ ፡ ማስመዝገብ ።

(፩) ማንኛውም ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ የተመዘገበ ፡ ነጋዴ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ የሚ ከተሉት ፡ በተጨማሪ ፡ እንዲመዘገቡለት ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

(ሀ) ጋብቻውን ፡ ያገባበት ፡ ቦታና ፡ ቀን ፡ እንዲሁም ፡ ጋብቻው ፡ የተፈጸመበ ትን ፡ ስፍራ ፡ የተፈራረሙት ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ እንዳለ ፡ የተፈራረሙበትን ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ውሉ ፡ የተቀመጠበትን ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ሰው ፡ ስም

(ለ) የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ የወሰነውን ፡ ውሳኔ ፤

(ሐ) ፍርድ ፡ ቤት ፤ ነጋዴው ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በፍርድ ፡ የተ ከለከለ ፡ መሆኑን ፡ የወሰነበት ፤

(መ) ሚስት ፡ ወይም ፡ ባል ፡ ተቃውመው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ንግዱ ፡ ሥራ ፡ ያቀረቡትን ፡ መቃወም ፤

(ሠ) በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፲፰ ፡ መሠረት ፡ መቃወሚያውን ፡ ማስቀረት ፤

(ረ) አዲስ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ መሾሙን ፤

(ሰ) አዲስ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ወይም ፡ ውክልና ፡ መክፈቱን ፤ እንደዚህ ፡ ያለውም ፡ አዲስ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ወይም ፡ ውክልና ፡ በተከፈተ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ወይም ፡ ውክልና ፡ ባለበት ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በአጭር ፡ ቃል ፡ ለመመዝገብ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) መሠረት ፡ የሚቀርበውን ፡ ማመልከቻ ፡ ማንኛውም ፡ ሕጋዊ ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ማመልከት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፻፲ ። ስለ ፡ ንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ በተጨማሪ ፡ ስለሚመዘገቡ ፡ ጉዳዮች ።

ስለ፡ ንግድ ፡ ሥራ፡ ማኅበሮችን ፡ በተጨማሪ ፡ መመዝገብ ፡ ጉዳይ ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ የሁለተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ተገቢ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፻፲፩ ። ስለ ፡ መክሠር ፡ የሚሰጥ ፡ ፍርድ ።

ስለ ፡ መክሠር ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ የሚፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በአምስተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ በተነገረው ፡ ተገቢ ፡ ድንጋጌ ፡ መሠ ረት ፡ በተጨማሪነት ፡ ማስመዝገብ ፡ ይገባል ።

BACK



ክፍል ፡ ፬ ።

ከመዝገብ ፡ ስለ ፡ መሰረዝ ።

ቍ ፡ ፻፲፪ ። መነገድን ፡ መተው ።

ማንኛውም ፡ የተመዘገበ ፡ ነጋዴ ፡ የተመዘገበውን ፡ የንግድ ፡ ሥራውን ፡ በማና ቸውም ፡ ምክንያት ፡ በተወ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ የንግዱን ፡ መደብር ፡ በአከራየ ፡ ጊዜ ፡ በሁለት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ከመዝገቡ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ማመልከቻ ፡ ማቅረብ ፡ ይገባዋል ።

ቍ ፡ ፻፲፫ ። የነጋዴው ፡ መሞት ።

(፩) ነጋዴው ፡ በሞተ ፡ በሁለት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ የሟቹ ፡ ወራሾች ፡ መዝገቡ ፡ እን ዲሰረዝላቸው ፡ ማመልከቻ ፡ ማቅረብ ፡ አለባቸው ።
(፪) ወራሾቹም ፡ ሳይካፈሉ ፡ በጋራ ፡ ባለቤትነት ፡ ንግዱን ፡ የሚቀጥሉ ፡ ሲሆኑ ፡ አዲስ ፡ መዝገብ ፡ እንዲመዘገብላቸው ፡ ማመልከት ፡ አለባቸው ።
(፫) የጋራ ፡ ባለቤትነቱ ፡ ሲቀርና ፡ ሲካፈሉ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) መሠረት ፡ የተመዘገበው ፡ እንዲሰረዝለትና ፡ ንግዱ ፡ የተላለፈለት ፡ ሰው ፡ አዲስ፡ መዝገብ ፡ እንዲመዘገብለት ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፲፬ ። መዝገቦችን ፡ በሥልጣን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ማሰረዝ ።

(፩) ነጋዴው ፡ ሥራውን ፡ ያቆመ ፡ ወይም ፡ ነጋዴው ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ የተመዘገበውን ፡ ንግድ ፡ ለመነገድ ፡ ያልቻለ ፡ ለመሆኑ ፡ የተወሰነበት ፡ መሆኑን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ የንግድ ፡ ሚኒስትር ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ ነጋዴው ፡ የተመ ዘገበበት ፡ እንዲሰረዝ ፡ ያዛል ።
(፪) መዝገቡ ፡ እንዲሰረዝ ፡ የንግድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ያዘዘው ፡ ትእዛዝ ፡ ለባለጕዳዩ፡ ነጋዴ ፡ እና ፡ የሚሰረዘውን ፡ መዝገብ ፡ ለሚሠራው ፡ ሠራተኛ ፡ እንዲደርር ሰው ፡ መደረግ ፡ አለበት ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ስለ ፡ ቅጣት ።

ክፍል ፡ ፩ ።

ስለ ፡ ወንጀል ፡ ቅጣት ።

ቍ ፡ ፻፲፭ ። ሳይመዘገቡ ፡ ስለ ፡ መቅረት ።

ማንም ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ሳይመዘገብ ፡ ወይም ፡ ሊመዘ ገብ ፡ የሚገባውን ፡ ሳያስመዘግብ ፡ የቀረ ፡ ሰው ፡ አጥፊ ፡ ሆኖ ፡ ተከሰ ፡

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፺፰ ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ።

ቍ ፡ ፻፲፮ ። ሆን ፡ ብሎ ፡ ትክክል ፡ ያልሆነ ፡ መግለጫ ፡ መስጠት ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ስለሚመዘገበው ፡ ጕዳይ ፡ ሐሰት ፡ የሆነ ፡ መግለጫ ፡ የሰጠ ፡ ሰው ፡ አጥፊ ፡ ሆኖ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፺፯ ፡ መሠረት ፡ ይቀጣል ።

ክፍል ፡ ፪ ።

ፍትሐ ፡ ብሔራዊ ፡ ማስገደጃ ፡ (ቅጣት) ።

ቍ ፡ ፻፲፯ ። መዝገብ ፡ መግባት ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

(፩) ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበበት ፡ በስተቀር ፡ ማንኛውም ፡ በመዝገብ ፡ የገባ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ነጋዴ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ።

(፪) ማንኛውም ፡ የተመዘገበ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ነጋዴ ፡ ላለመሆኑ ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ አይፈቀድለትም ፤ ነጋዴነት ፡ የሚያስከትለውንም ፡ ኀላፊነት ፡ ሁሉ ፡ ይቀበላል ።

ቍ ፡ ፻፲፰ ። በመዝገብ ፡ ሳይገቡ ፡ መቅረት ፡ ስለሚሰጠው ፡ ውጤት ።

(፩) ማንኛውም ፡ ነጋዴ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ መመዝገብ ፡ የሚገባ ፡ ሆኖ ፡ ሳይመዘገብ ፡ የቀረ ፤ እንደ ፡ ነጋዴ ፡ ተቈጥሮ ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ፤ እንጂ ፤ ነጋዴ ፡ አይደለሁም ፡ ብሎ ፡ ከሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጋራ ፡ ሊከራከር ፡ አይችልም ።

(፪) ስለዚህ ፡ ጕዳይ ፡ የተሠሩት ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ሁለተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ተገቢ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ፡ ይፈጸማሉ ።

ቍ ፡ ፻፲፱ ። መዝገቦችን ፡ ሳያሰርዙ ፡ መቅረት ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

ማንኛውም ፡ የንግዱን ፡ መደብር ፡ የሚያስተላልፍ ፡ ወይም ፡ የሚያከራይ ፡ ሰው ፡ የተመዘገበበትን ፡ እስከ ፡ አሰረዘ ፡ ድረስ ፡ የተላለፈለት ፡ ወይም ፡ የተከራየው ፡ ሰው ፡ ለሚደርስበት ፡ ዕዳ ፡ በመላው ፡ ሳይከፋፈል ፡ በአንድነት ፡ አላፊነት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፻፳ ። በመዝገብ ፡ የገባ ፡ ቃል ፡ ስለሚሰጠው ፡ ውጤት ።

(፩) ማንኛውም ፡ በመዝገብ ፡ ቃሉን ፡ ያስመዘገበ ፡ ሰው ፡ የተመዘገበው ፡ ጕዳይ ፡ ይለወጥልኝ ፡ ሲል ፡ ማመልከቻ ፡ አቅርቦ ፡ ለመለወጫ ፡ ያቀረበውን ፡ ቃል ፡ ያስመዘገበ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ መዝገቡ ፡ ትክክል ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ አይፈቀድለትም ።

(፪) ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በንግዱ ፡ መዝገብ ፡ በትክክል ፡ የገባውን ፡

ጕዳይ ፡ አላወቅንም ፡ ነበር ፡ ብለው ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ አይፈቀድላቸውም ።

**ቍ ፡ ፻፴፭ ። ነጋዴ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ የሚመለከቱ ፡ ጕዳዮች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ ስላለመሆናቸው ።**

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉት ፤ ነጋዴ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ የሚመለከቱ ፡ ጕዳዮች ፤

(ሀ) የነጋዴው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያለማድረስ ፤

(ለ) የነጋዴው ፡ ማግባት ፤

(ሐ) የነጋዴው ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፤

(መ) የነጋዴው ፡ መፋታት ፡ የተወሰነበትን ፤

(ሠ) ነጋዴው ፡ በፍርድ ፡ የተከለከለ ፡ መሆኑን ፡ የሚወስነው ፡ ፍርድ ፤

(ረ) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ፡ መሠረት ፡ የቀረበው ፡ መቃወሚያ ፤

(ሰ) የሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ሥልጣን ፡ የቅርንጫፉን ፡ ወይም ፡ የውክልናውን ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ በማካሄድ ፡ የተወሰነ ፡ መሆኑ ፤

(ሸ) ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ከሥራ ፡ መሰናበት ፤ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ከገባው ፡ ቃል ፡ ውስጥ ፡ የሌሉ ፡ ከሆነ ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ያላቸውን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፻፴፮ ። የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ጕዳዮች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ ስላለመሆናቸው ።**

በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ከገባው ፡ ቃል ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮችን ፡ የሚመለከቱ ፡ የሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መብቶች ፡ መቃወሚያ ፡ ለመሆን ፡ የማይችሉት ፡ ጕዳዮች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በሁለተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ተነግረዋል ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## ፍጻሜ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፻፴፯ ። ደንቦች ።**

የዚህን ፡ አንቀጽ ፡ አፈጻጸም ፡ የሚመራ ፡ በተለይም ፤

(ሀ) በቍጥር ፡ ፯ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፪) (ሐ) ለተገለጹት ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ የሚሆን ፡ ልዩ ፡ ደንብ ፤

(ለ) ለየአገሩ ፡ መዝገቦችና ፡ ለጠቅላይ ፡ መዝገብ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፤

(ሐ) ለመዝገብ ፡ ቍጥር ፡ አሰጣጥ ፡ የሚሆን ፡ ደንብ ፤

(መ) መቅረብ ፡ ስለሚገባቸው ፡ አስረጂ ፡ ጽሑፎች ፤

BACK



(ሠ) ለማመልከቻ ፡ (ለዴክላራሲዮን) ፡ የሚሆን ፡ ፎርም ፤

(ረ) ለመመዝገቢያ ፡ ስለሚከፈለው ፡ ገንዘብና ፡ የመዝገብ ፡ ግልባጭ ፡ ወይም፡ ከመዝገብ ፡ በአጭር ፡ የተውጣጣ ፡ ቃል ፡ ለመቀበል ፡ ስለሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፤

(ሰ) የንግድ ፡ ኦፌሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ የሚታተምበትን ፡ አኳኋን ፤ በውስጡ ፡ ስለ ሚጻፍ ፡ ማስታወቂያና ፡ ለጋዜጣውም ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፤

(ሸ) ለሌላም ፡ ደንብ ፡ ሊወጣለት ፡ ለሚያስፈልግ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፤ የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ ደንቦች ፡ ያወጣል ።

## አንቀጽ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ንግድ ፡ መደብር ፡ (መድበል) ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፻፳፬ ። ትርጓሜ ።**

የንግድ ፡ መደብር ፡ (መድበል) ፡ የሚባለው ፡ አንድ ፡ ግዙፍነት ፡ የሌለው ፡ በዚህ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ በ፭ተኛው ፡ ቍጥር ፡ ለተጠቀሱት ፡ የንግድ ፡ ሥራዎች ፡ ዐይነት ፡ ለሆነው ፡ ላንድ ፡ ሥራ ፡ ማካሄጃ ፡ የተዘጋጁ ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ሁሉ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፻፳፭ ። ነጋዴዎችና ፡ የንግድ ፡ መደብር ።**

(፩) ማናቸውም ፡ ነጋዴ ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ሥራ ፡ ያካሂዳል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ማናቸውም ፡ ነጋዴ ፡ ለብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ሥራዎችም ፡ አከናዋኝ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

(፫) ነጋዴውም ፡ ሥራውን ፡ ለሚያከናውነው ፡ ላንዱ ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ባለ ቤት ፤ በአበሉ፡ ተጠቃሚ፡ ባለ፡ አላባ ፡ ወይም ፡ ተከራይ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ። የንግድ ፡ መደብር ፡ ባለቤት ፡ (ባለሀብት) ፡ አከራይ ፡ ነጋዴ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ፤ በንግዱ ፡ መደብር ፡ የሚነግድ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ነጋዴ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፳፮ ። ስለ ፡ ዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤትና ፡ የቅርንጫፍ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ።**

(፩) አንድ ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ባንድ፡ በዋና ፡ የንግድ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የተወ ሰነ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

BACK



እንዲሁም ፡ ከዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ጋራ ፡ የተያያዙ ፡ የቅርንጫፍ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ የወኪል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ።

(፪) የንግድ ፡ ቤቱ ፡ ዋና ፡ መኖሪያ ፡ ቦታው ፡ አውራ ፡ በሆነው ፡ የንግድ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ነጋዴው ፡ የንግዱን ፡ ሥራ ፡ ከሚያከናወንበት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነው ።

(፫) አውራው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሳይሆን ፡ አንድ ፡ የቅርንጫፍ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ የወኪል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የተሸጠ ፡ ወይም ፡ በኪራይ ፡ የተሰጠ ፡ እንደሆን ፤ የንግድ ፡ መደብር ፡ መሸጥ ፡ ወይም ፡ ማከራየት ፡ ተብሎ ፡ ስለሚቈጠር ፡ የዚሁ ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ዋና ፡ መኖሪያው ፤ የቅርንጫፍ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ወይም ፡ የወኪል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ሥራ ፡ በሚከናወንበት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## የንግድ ፡ መደብር ፡ የተቋቋመባቸው ፡ ነገሮች ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### በንግድ ፡ መደብር ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኙ ፡ ነገሮች ።

**ቍ ፡ ፻፳፯ ። የነጋዴው ፡ ደንበኛ ፡ ገበያተኞችና ፡ ግዙፍነት ፡ የሌላቸው ፡ ነገሮች ።**

(፩) በንግድ ፡ መደብር ፡ ደንበኛ ፡ የሆኑ ፡ ገበያተኞች ፡ ይገኙበታል ።

(፪) በንግድ ፡ መደብር ፡ ሌላም ፡ ግዙፍነት ፡ የሌላቸው ፡ ነገሮች ፡ ሊገኙበት ፡ ይቻላል ፡ በተለይም ፤

(ሀ) የንግድ ፡ ቤቱ ፡ ስም ፤

(ለ) የሚነገድበት ፡ የተለየ ፡ የንግድ ፡ የማስታወቂያ ፡ ሰሌዳ ፤

(ሐ) የንግዱ ፡ ሥራ ፡ የሚከናወንባቸውን ፡ ቤቶች ፡ የማከራየት ፡ መብት ፤

(መ) የኢንዱስትሪ ፤ የድርሰት ፤ የኪነ ፡ ጥበብ ፤ መብቶች ፡ ባለሀብትነት ፡ ሊገኙበት ፡ ይቻላል ።

(ሠ) ይኸውም ፡ እነዚህ ፡ መብቶች ፡ የተሰጡት ፡ ለነጋዴው ፡ ሰው ፡ ሳይሆን ፡ ለንግድ ፡ መደብሩ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፳፰ ። ግዙፍነት ፡ ስላላቸው ፡ ነገሮች ።**

በንግድ ፡ መደብር ፡ ውስጥ ፡ ግዙፍነት ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ መሣሪያዎች ፤ የቤት ፡ ዕቃዎችና ፡ ሸቀጥ ፡ ይገኙበታል ።

**ቍ ፡ ፻፳፱ ። የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብቶችና ፡ ዕዳዎች ።**

(፩) በንግድ ፡ መደብር ፡ ውስጥ ፡ ከቤት ፡ ኪራይ ፡ ውል ፡ መብት ፡ በስተቀር ፡ የነጋዴው ፡ ከሰው ፡ ላይ ፡ የሚጠይቀው ፡ ገንዘብና ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ የሚጠየቅበትም ፡

BACK



ዕዳ ፡ አይገባበትም ።

(፪) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ በተለይም ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በቍጥር ፡ ፪ሺ፶፯ ፡ በዚህ፡ መጽሐፍ፡ በቍጥር ፡ ፻፴፪ ፡ እንዲሁም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፸፬ ፡ ስለ ፡ አሹራንስ ፡ የተነገሩት ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ውሳኔዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ደንበኛ ፡ ገበያተኛና ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ ውድድር ።

### ቍ ፡ ፻፴ ። ስለ ፡ ደንበኛ ፡ ገበያተኛ ፡ ትርጕም ።

ደንበኛ ፡ ገበያተኛ ፡ ማለት ፡ ከንግድ ፡ መደብር ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የተፈጠረ ፡ ዋጋ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ዋጋ ፡ ከነጋዴው ፡ ዕቃ ፡ (ሸቀጥ) ፡ ወይም ፡ አገልግሎት ፡ ከሚፈልጉት፡ ሦስተኛ፡ ወገኖች፡ ጋራ፡ በሚደረገው፡ ግንኙነት፡ ሁሉ፡ የተገኘ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፻፴፩ ። ደንበኛ ፡ ገበያተኛን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ።

በደንበኛ ፡ ገበያተኛ ፡ ላይ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ መጥፎ ፡ የውድድር ፡ ሥራ ፡ እንዳ ይሠራ ፡ የማይገባ ፡ ውድድርን ፡ ለማስቀረት ፡ በሚቀርበው ፡ የክስ ፡ መብትና ፡ በተ ለይም ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ፡ በቍጥር፡ ፴ ፤ ፵ ፤ ፵፯ ፤ ፶፰ ፤ ፻፵፬ ፤ ፻፶፰ ፤ ፻፶፱ ፤ ፻፷፬፤ ፻፷፭፡ የውድድር ፡ ሥራ ፡ የተከለከለ ፡ በሚያደርጉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ወይም ፡ ስም ምንቶች ፡ መሠረት ፡ ይጠበቃል ።

### ቍ ፡ ፻፴፪ ። ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የንግድ ፡ የውድድር ፡ ሥራ ።

በውድድር ፡ ሥራ ፡ ጥፋት ፡ አድርጎ ፡ በሚገኝ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ነጋዴው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ኀላፊነት ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፺፯ ፡ መሠረት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲያገኝ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብበት ፡ ይችላል ።

### ቍ ፡ ፻፴፫ ። የማይገባ ፡ የውድድር ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ የሚያሰኘው ፡ ነገር ።

(፩) በንግድ ፡ ሥራ ፡ ከሐቀኝነት ፡ አደራረግ ፡ ውጭ ፡ የሚሠራው ፡ የውድድር ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ጥፋት ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ።

(፪) የማይገባ ፡ የውድድር ፡ ሥራዎች ፡ ተብለው ፡ የሚቈጠሩትም ፡ በተለይ ፡ የሚ ከተሉት ፡ ናቸው ።

(ሀ) አንድ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሆነው ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ በሚያወጣው ፡ ዕቃ ፡ ለማሳከር ፡ ሲባል ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ የሚሠሩት፡ የውድድር ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ናቸው ።

(ለ) አንድ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሆነው ፡ የንግድ ፡ ቤትን ፡ ለመጕዳት ፡ ሲባል ፡ በንግድ፡ ሥራው ፡ ወይም ፡ በሚያወጣቸው ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ የሚነዙት ፡ ሐሰተኛ ፡ መግለጫዎች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፻፴፬ ። የማይገባ ፡ የውድድር ፡ ሥራ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።**

(፩) በማይገባ ፡ የውድድር ፡ ሥራ ፡ በማድረግ ፡ ክስ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፤

(ሀ) በማይገባ ፡ የተወዳደረው ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍል ፡ ያደርጋል ።

(ለ) ይኸንንም ፡ የማይገባ ፡ የውድድር ፡ ሥራ ፡ ለማስወገድ ፡ አስፈላጊውን ፡ ሁሉ ፡ ያዝለታል ።

(፪) በተለይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፤

(ሀ) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ ኀላፊነት ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ በቍጥር ፡ ፪ሺ፻፳ ፡ በታዘዘው ፡ መሠረት ፡ በማይገባ ፡ በተወዳደረው ፡ ኪሣራ ፤ የከሳሹን ፡ ንግድ ፡ ስም ፡ ለማጥፋት ፡ በሐሰት ፡ የተነዛውን ፡ ነገርና ፡ ወሬ ፡ ስሚት ፡ ለማጥፋት ፡ በማስታወቂያ ፡ እንዲገለጽ ፡ ያዝለታል ።

(ለ) ወይም ፡ በዚያው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪ሺ፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ በማይገባ ፡ የሚወዳደረው ፡ ይህን ፡ ሕጋዊ ፡ ፡ ያልሆነውን ፡ ድርጊት ፡ ሁሉ ፡ ያቆም ፡ ዘንድ ፡ ያዝለታል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ነጋዴ ፡ ስለሚነግድበት ፡ ስም ።

**ቍ ፡ ፻፴፭ ። ትርጓሜ ።**

(፩) ነጋዴ ፡ የሚነግድበት ፡ ስም ፡ የሚባለው ፡ ነጋዴ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የንግድ ፡ መደብሩን ፡ ጥቅም ፡ የሚያስገኝበት ፡ ስምና ፡ የንግድ ፡ መደብሩንም ፡ ዐይነት ፡ ለይቶ ፡ የሚያስረዳ ፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ ንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ስም ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ የሁለተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ተገቢ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፻፴፮ ። ስለ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ፈጠራ ፡ ስም ።**

ነጋዴው ፡ የሚነግድበትን ፡ ስም ፡ የቤተ ፡ ዘመድን ፡ ስም ፡ ከአባቱ ፡ ስም ፡ ጭምር ፡ ወይም ፡ ያለአባቱ ፡ ስም ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ፈጠራ ፡ ስም ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መፈረም ፡ የሚችለው ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስሙ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፴፯ ። ስለ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስም ።**

(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ስሙ ፡ ከአባቱ ፡ ስም ፡ ጭምር ፡ ወይም ፡ ያለአባቱ ፡ ስም ፡ ለመነገድ ፡ አይከለከልም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የዚህ ፡ ስም ፡ ወይም ፡ የአባት ፡ ስም ፡ እያያዘ ፡ በማሳከር ፡ የተነሣ ፡ የሌላውን ፡ ነጋዴ ፡ ጥቅም ፡ የሚጎዳ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ሰዎት ፡ በሚለው ፡ አንቀጽ ፡ የቍጥር ፡ ፵፰ ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፪) በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ጕዳይ ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ ተደርጓል ፡ ተብሎ ፡ ክስ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ዳኛው ፡ ያለአገባብ ፡ ተወዳዳሪው ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍል ፡ ከመፍረዱም ፡ በላይ ፡ የመሳከር ፡ ጕዳይንም ፡ ለማስወገድ ፡ ያለአገባብ ፡ ተወዳ ዳሪውን ፡ በቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ስም ፡ ላይ ፡ የእሱን ፡ ስም ፡ ከአባቱ ፡ ስም ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ሊያስገድደውም ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፻፴፰ ። ፈጠራ ፡ የሆነ ፡ ስም ።**

(፩) ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ንግዱን ፡ ባንድ ፡ ፈጠራ ፡ በሆነ ፡ ስም ፡ መሠረት ፡ ለማ ካሄድ ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህም ፡ ስም ፡ በማሳከር ፡ የተነሣ ፡ የሌላውም ፡ ነጋዴ ፡ ጥቅም ፡ እንዳይጎዳ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ጕዳይ ፡ የማይገባ ፡ ውድድር ፡ ተብሎ ፡ ክስ ፡ በቀበረ ፡ ጊዜ ፡ ዳኛው ፡ ያለአገባብ ፡ ተወዳዳሪው ፡ ለከሳሹ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍለው ፡ ከመፍረ ዱም ፡ በላይ ፡ በዚሁ ፡ በመረጠው ፡ የፈጠራ ፡ ስም ፡ ዳግም ፡ እንዳይሠራበት ፡ ያለአገባብ ፡ ተወዳዳሪውን ፤ ሊከለክለው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፻፴፱ ። የሚነግድበትን ፡ ስም ፡ ለሌላ ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።**

(፩) ነጋዴው ፡ የሚነግድበት ፡ ስም ፡ ለሌላ ፡ እንዲተላለፍ ፡ የሚሆነው ፡ የን ግድ ፡ መደብሩ ፡ አዲስ ፡ የንግዱን ፡ ሥራ ፡ ለሚያካሂደው ፡ ሰው ፡ አብሮ ፡ በተላለፈለት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) ይህም ፡ አዲስ ፡ የንግዱን ፡ ሥራ ፡ የሚያካሂደው ፡ ሰው ፡ በተዛወረለት ፡ የን ግድ፡ ስም፡ መሠረት፡ ለመሥራት፡ የሚችለው፡ የገዛ፡ ራሱን፡ ስም፡ «ተተኪው» ፡ ወይም፡ «ተከራዩ»፡ የሚል፡ ጽሑፍ፡ የማስከተል፡ ግዴታ፡ አለበት ፤ የንግድ፡ ወረ ቀቶችን፡ ለመፈረም፡ ግን፡ የሚችለው፡ በራሱ፡ ቤተ፡ ዘመድ፡ ስሙ ፡ ብቻ ፡ ነው።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## የንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሰሌዳ ።

**ቍ ፡ ፻፵ ። ትርጓሜ ።**

(፩) የማስታወቂያ ፡ ሰሌዳው ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ በሚከናወንባቸው ፡ ስፍራዎች፡ ላይ ፡ የሚውል ፡ ስም ፡ ምልክት ፤ የንግዱንም ፡ መደብ ፡ ዐይነት ፡ ለይቶ ፡ የሚ ያስረዳ ፡ ጽሑፍ ፡ ነው ።

(፪) ነጋዴው ፡ የማስታወቂያ ፡ ሰሌዳ ፡ የሚያደርገው ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፵፩ ። ስለ ፡ ንግድ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሰሌዳ ፡ አመራረጥ ።**

(፩) ነጋዴው ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ የወደደውን ፡ የማስታወቂያ ፡ ሰሌዳውን ፡ ለመም ረጥ ፡ ይችላል ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ ነጋዴው ፡ ይህ ፡ የመረጠው ፡ የንግድ ፡ የማስታወቂያ ፡ ሰሌዳ ፡ ከርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ሌላ ፡ ነጋዴ ፡ ከመረጠው ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝና ፡ ይህም ፡ በመሳከር ፡ ምክ

ንያት ፡ የዚያኑ ፡ ነጋዴ ፡ ጥቅም ፡ የሚጎዳ ፡ በመሆኑ ፡ በማይገባ ፡ የውድድር ፡ ሥራ፡ ሠርተሃል ፡ ተብሎ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍል ፡ ክስ ፡ እንዲቀርብበት ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ፡፡

## ክፍል ፡ ፫ ፡፡

## ስለ ፡ ኪራይ ፡ ውል ፡ መብት ፡፡

**ቍ ፡ ፻፺ ፡፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡፡**

የንግድ ፡ መደብር ፡ የሚከናወንበት፡ ቤት ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ መብት ፤ በዚህ ፡ ክፍል ፡ የተዘረዘሩት ፡ ቍጥሮች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ኪራይ ፡ ውሎች ፡ በተባለው ፡ አንቀጽ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ የሚፈጸሙ ፡ ናቸው ፡፡

**ቍ ፡ ፻፺፩ ፡፡ የሚነገደው ፡ የንግድ ፡ ዐይነት ፡፡**

በቤቱ ፡ ኪራይ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ተከራዩ ፡ የሚሠራው ፡ የንግድ ፡ ዐይነት ፡ ተጠቅሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተከራዩ ፡ በነዚሁ ፡ ቦታዎች ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ንግድ ፡ ሊያከናውንባቸው ፡ አይችልም ፤ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ንግድ ፡ ቢሠራባቸው ፡ ግን ፡ ውሉን ፡ ፍርስ ፡ ያደርገዋል ፡፡

**ቍ ፡ ፻፺፪ ፡፡ አከራዩ ፡ የውድድር ፡ ሥራ ፡ እንዳያደርግ ፡ ስለ ፡ መከልከል ፡፡**

(፩) ለንግድ ፡ አገልግሎት ፡ የሚውል ፡ ቦታ ፡ ባለቤት ፡ ቤቱን ፡ በውል ፡ ካከራየ ፡ ወዲህ ፡ ከቤቱ ፡ በሌላ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ተከራዩ ፡ በሚያካሂደው ፡ የንግድ ፡ ዐይነት ፡ መሰል ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ አይፈቀድለትም ፡፡

(፪) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተከለከለውን ፡ ቢተላለፍ ፡ ግን ፡ ኪሣራ ፡ ከፍሎ ፡ ሱቁም ፡ እንዲዘጋ ፡ ይደረጋል ፡፡

**ቍ ፡ ፻፺፫ ፡፡ የኪራይን ፡ ውል ፡ ለሌላ ፡ ማስተላለፍን ፡ ወይም ፡ የተከራየውን ፡ ለሌላ ፡ ማከራየትን ፡ ስለሚከለክሉ ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡፡**

(፩) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የማይንቀሳቀሱ፡ ንብረቶችን ፡ ስለሚመለከቱ፡ውሎች፡ በሚል፡ አንቀጽ፡ በቍጥር፡ ፪ሺ፱፻፶፮፡ የተወሰነው፡ ቢኖርም ፡ እንኳን ፤ ተከራዩ ፡ የንግድ ፡ መደብሩን ፡ ለገዛው ፡ ሰው ፡ የቤት ፡ ኪራይ ፡ ውሉን ፡ እያስተላልፍም፡ ወይም ፡ የተከራይ ፡ ተከራይ ፡ አድርጎ ፡ አያከራይም ፡ ወይም ፡ የኪራዩን፡ውል ፡ ለማስተላለፍ ፡ ወይም ፡ የተከራዩ ፡ ተከራይ ፡ አድርጎ ፡ ለማከራየት፡የባለቤቱን ፡ ፈቃድ ፡ ያስፈልጋል ፡ የሚሉ ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ ሁሉ ፡ ፍርስና ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸው ፡ ናቸው ፡፡

(፪) እንደዚሁም፥ የተከራዩን ፡ የኪሣራ ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪ ፡ ሆኖ ፡ ለተሾመው፡ሰው፡ (ሰንዲክ)፡ በዚህ ፡ ሕግ፡ በቍጥር ፡ ሺ፰፻፪ ፡ መሠረት ፡ የታወቁለትን ፡ መብቶች፡ የሚቀንሱ ፡ ወይም ፡ የሚሰርዙ ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ ሁሉ ፡ ፍርስ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፻፺፮ ። ስለ ፡ ቤት ፡ ኪራይ ፡ ውል ፡ ማፍረስ ።**

(፩) የንግድ ፡ መደብር ፡ ለዕዳ ፡ ዋስትና ፡ መያዣ ፡ ተሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ቤቱን፡ በውል ፡ አከራዩ ፡ የንግድ ፡ መደብሩን ፡ መያዣ ፡ አድርገው ፡ ገንዘብ ፡ ላበደሩት ፡ ሰዎች ፤ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ የሚከስ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ በስምምነት ፡ ውሉን፡ ለማፍረስ ፡ አሳብ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፤ ወይም ፡ ውሉን ፡ ፍርስ ፡ በሚያደርገው ፡ በውሉ ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ ውሉ ፡ የፈረሰ ፡ መሆኑን ፡ ለይቶ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ፡ ውሉም ፡ ለመፍረስ ፡ የሚችለው ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተደረገ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ነው ።

(፪) ይህ ፡ ማስታወቂያ ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ መደብሩን ፡ መያዣ ፡ አድርገው ፡ ገንዘብ ፡ ባበደሩት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የውሉ ፡ ማፍረስ ፡ መቃወሚያ ፡ አይሆንባቸውም ።

**ቍ ፡ ፻፺፯ ። ስለ ፡ ተከራዩ ፡ መክሠር ።**

(፩) ተከራዩ ፡ በከሠረ ፡ ጊዜ ፡ አለክርክር ፡ በሙሉ ፡ መብት ፡ ውሉ ፡ ፍርስ ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ በኪራይ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈ ፡ ቃል ፡ አይጸናም ።

(፪) ተከራዩ ፡ በከሠረ ፡ ጊዜ ፡ የተከራዩ ፡ የኪሣራ ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪው ፡ መብቶች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በ፭ተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ በቍጥር ፡ ሺ፵ ፡ እና ፡ ሺ፰፻፪ ፡ ተወስነዋል ። የአከራዩ ፡ መብቶችም ፡ በቍጥር ፡ ሺ፰ ፡ እና ፡ ሺ፰፻፩ ፡ ተወስነዋል ።

## ክፍል ፡ ፮ ።

## የኢንዱስትሪ ፤ የድርሰት ፤ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ የባለቤትነት ፡ (ባለሀብትነት) ፡ መብቶች ፡ መጠበቂያ ።

**ቍ ፡ ፻፺፰ ። የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤትነት ፡ (ባለሀብትነት) ፡ መብቶች ፡ መጠበቂያ ።**

(፩) የንግድ ፡ መደብር ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤትነት ፡ መብቶች ፡ የተመዘገበ ፡ የመፈልሰም ፡ መብት ፤ የንግድ ፡ ምልክቶች ፤ ሥዕሎችና ፡ ሞዴሎች ፤ ሊኖረው ፡ ይችላል ።

(፪) የኢንዱስትሪ ፡ ባለቤትነት ፡ መብቶች ፡ በልዩ ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ ይተዳደራሉ ።

**ቍ ፡ ፻፺፱ ። ስለ ፡ ጽሑፍ ፡ ድርሰትና ፡ ጥበባዊ ፡ የአርት ፡ ባለቤትነት ፡ መብቶች ።**

(፩) የንግድ ፡ መደብር ፤ የድርሰት ፡ ወይም ፡ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ አርት - ባለቤትነት፡ መብቶች ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ።

(፪) የድርሰትና፡ የኪነ፡ ጥበብ ፡ ባለቤትነት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ፡ ስለ ፡ ግዴታዎች ፡ በተባለው ፡ በመጀመሪያው ፡ አንቀጽ ፡ በቍጥር ፡ ፩ሺ፮፻፵፯ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ፮፻፸፬ ፡ መሠረት ፡ ይተዳደራል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## የንግድ ፡ መደብር ፡ (የንግድ ፡ መድበል ፡) ሽያጭ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፻፶ ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

በንግድ ፡ መደብር ፡ ሽያጭ ፡ ላይ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪ሺ፪፻፷፮ ፡ እስከ ፡ ፪ሺ፫፻፷፯ ፡ የተመለከቱት ፡ በመሠረቱ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ። ይኸውም ፡ የዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውሳኔዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆኖ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፶፩ ። የሽያጭ ፡ መግለጫ ።**

(፩) በዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ መደብር ፡ ሽያጭ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በሚከተሉት ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(ሀ) በንግድ፡ መደብር፡ ላይ ፡ የሚደረገው ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ሽያጭ፡ ወይም፡ ማስተላለፍ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ውል ፡ በማስመሰልም ፡ የሚደረገው ፡ ሽያጭ ፡ ወይም ፡ ማስተላለፍ ፤

(ለ) የጋራ ፡ ባለሀብቶቹ ፡ ባቀረቡት ፡ ጥያቄ ፡ የሚደረግ ፡ ሐራጅ ፡ ሽያጭ ፤

(ሐ) የጐደለውን ፡ ሞልቶና ፡ እኩል ፡ በኩል ፤ የሚደረግ ፡ ክፍያ ፤ እዲሁም ፡ ይኸው ፡ ሽያጭ ፤ ማስተላለፍ ፡ ወይም ፡ አከፋፈል ፡ የሚመለከተው ፡ የንግድ ፡ መደብርን ፡ ደንበኛ ፡ ገበያተኛው ፡ ወይም ፡ ከዋናው ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ ተለይቶ፡ በቅርንጫፍ ፡ ወይም ፡ በወኪል ፡ መሥሪያ ፡ ቤትም ፡ ሆነ ፤ ዋናው ፡ የንግድ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ደንበኛ ፡ ገበያተኛው ፡ ሳይተላለፍ ፡ የሚመለከቱ ፡ የሆን ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ነው ።

(፪) ከንግድ ፡ መደብር ፡ የተነጣጠሉ ፡ ነገሮች ፡ ሽያጭ ፤ ከደንበኛ ፡ ገበያተኛ ፡ ሽያጭ ፡ በስተቀር ፡ የሆኑት ፡ ነገሮች ፡ በስውር ፡ የንግድ ፡ መደብርን ፡ ወይም ፡ የደንበኛ ፡ ገበያተኛን ፡ መሸጥ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌዎች፡ መሠረት ፡ እንዲፈጸም ፡ አይገደድም ።

### ክፍል ፡ ፪ ።

### ስለ ፡ ሽያጭ ፡ ጽሑፍ ፡ ሥርዐት ።

**ቍ ፡ ፻፶፪ ። ሽያጭ ፡ በጽሑፍ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

የንግድ ፡ መደብር ፡ ሽያጭ ፡ በጽሕፈት ፡ ካልሆነ ፡ ፍርስ ፡ ነው ።

BACK



ቍ ፡ ፪፻፷፫ ። በሽያጩ ፡ ጽሑፍ ፡ ስለሚጠቀሱ ፡ ነገሮች ።

በንግድ ፡ መደብር ፡ ሽያጭ ፡ ውስጥ ፡ መጠቀስ ፡ የሚገባው ፡—

(፩) በመጨረሻ ፡ በሦስት ፡ የሒሳብ ፡ መዝጊያ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፤ ወይም ፡ ሻጭ ፡ ይኸ ንን ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ከመሠረተበት ፡ ወይም ፡ ከገዛበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የዚ ህም ፡ መግዛት ፡ ወይም ፡ መመሥረት ፡ ከከሦስት ፡ የሒሳብ ፡ መዝጊያ ፡ ጊዜ ፡ የማያልፍ ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ያፈራቸውን ፡ ትርፎችና ፡ የንግድ ፡ ሒሳቦቹን ፡ ዝርዝር ፤

(፪) የንግድ ፡ ቤቱ ፡ ሥራ ፡ የሚከናወንበት ፡ በኪራይ ፡ በሆነ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የአከራዩን ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፤ ውሉ ፡ የተጻፈበትና ፡ ወደ ፊት ፡ የሚያልቅበትን ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፤

(፫) የንግድ ፡ ቤቱ ፡ መደብር ፡ ስለ ፡ ዕዳ ፡ በመያዣነት ፡ የተመዘገበበትን ፡ ሁኔ ታዎች ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፷፬ ። ውሉን ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ።

(፩) በቍጥር ፡ ፪፻፷፫ ፡ ውስጥ፡ የተመለከቱት ፡ ነገሮች፡ ጕድለት ፡ ምክንያት ፡ በፍ ርድ ፡ ቤቱ ፡ አስተያየት ፡ ጕዳት ፡ የደረሰበት ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ ገዢው ፡ የሽያጩ ፡ ውል ፡ ፍርስ ፡ እንዲሆንለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) በቍ ፡ ፪፻፷፫ ፡ መሠረት ፡ የተጠቀሱት ፡ ነገሮች ፡ ትክክል፡ሳይሆኑ ፡ በመቅ ረት ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስተያየትም ፡ እነዚሁ ፡ ጥቅሶች ፡ ትክክል ፡ ባለመ ሆን ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ ገዢው ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ወይም ፡ ከዋጋው ፡ እንዲቀነስለት ፡ ለማስደረግ ፡ ይችላል ።

(፫) በነዚሁ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) እና ፡ (፪) የተነገሩት ፡ ጕዳዮች ፡ ሽያጩ ፡ በተ ደረገበት ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ክሱ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## የሻጭ ፡ ግዴታዎች ።

ቍ ፡ ፪፻፷፭ ። የማስረከብ ፡ ግዴታ ።

(፩) ሻጭ ፡ የንግድ ፡ መደብሩን ፡ ለገዢው ፡ ማስረከብ ፡ አለበት ።

(፪) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የንግድ ፡ መደብርን ፡ መሸጥ ፡ ከንግድ ፡ መደብር ፡ ጋራ ፡ የተያያዘውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለገዢው ፡ ማስተላለፍን፡ ይጨምራል ።

(፫) ሻጩ ፡ በተለይም ፡ ደንበኛ ፡ ገበያተኛን ፡ ለገዢው ፡ ለማስተላለፍ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ ማስረጃዎችና ፡ ማስታወቂያዎች ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፫) የኢንዱስትሪን ፤ የድርሰትን ፤ ወይም ፡ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ መብቶችን ፡ ማስተላለፍ ፡ የሚፈጸመው ፡ በተለይ ፡ የሆኑ ፡ ሕጎች ፡ ወይም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በሚ ያዘው ፡ መሠረት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፸፫ ። ስለ ፡ ሒሳብ ፡ መዝገቦች ።**

(፩) ሻጩና ፡ ገዢው ፡ ሽያጩ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ቀን ፡ በሒሳብ ፡ መዝገቦች ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱትን ፡ ሒሳቦች ፡ አጣናቀው ፡ ዘግተውና ፡ ለነዚሁ ፡ የሒሳብ ፡ መዝ ገቦች ፡ አንድ ፡ ዝርዝር ፡ ጽሑፍ ፡ ያዘጋጃሉ ።

(፪) ሻጩ ፡ የሒሳብ ፡ መዝገቦቹን ፤ ማስረጃዎቹን ፤ የተቀበላቸውን ፡ ደብዳቤዎች ፤ የላካቸውን ፡ ደብዳቤዎች ፡ ግልባጭ ፡ ያስቀራል ፤ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ ሻጩ ፡ እነዚሁ ፡ የሒሳብ ፡ መዝገቦች ፤ ማስረጃዎች ፤ የተጻፉባቸውን ፡ ደብዳቤዎች ፤ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ጠብቆ ፡ ማኖርና ፡ ገዢው ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፡ እንዲያያቸው ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፸፬ ። ስለ ፡ ንግድ ፡ የመጻጻፍ ፡ ደብዳቤዎች ።**

ለተሸጠው ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ጕዳይ ፡ ከሽያጩ ፡ በኋላ ፡ ለሻጩ ፡ የሚደርሱ ትን ፡ ጽሑፎች ፡ ሁሉ ፡ ወዲያው ፡ ገዢው ፡ እንዲያወቃቸው ፡ ማድረግ ፡ ይገባዋል ።

**ቍ ፡ ፸፭ ። ሻጩ ፡ እንዳይወዳደር ፡ ስለ ፡ መከልከል ።**

(፩) ሻጩ ፡ ከሽያጩ ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ፭ ፡ ዓመት ፡ በተሸጠው ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ዐይነትና ፡ በተሸጠውም ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ አካባቢ ፡ ለገዢው ፡ ጕዳት ፡ የሚያደርስ ፡ የውድድር ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ አይገባውም ።

(፪) በሽያጩ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ሻጩ ፡ ንግድ ፡ ለመክፈት ፡ የሚከለከልበትን ፡ ቦታና ፡ የተከለከለውንም ፡ የንግድ ፡ ዐይነት ፡ ወስኖ ፡ ለማስፈር ፡ ይቻላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ የውል ፡ ቃል ፡ የሚጸናበት ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ መሆን ፡ አይገባውም ።

**ቍ ፡ ፸፮ ። ከገዥ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ገዥ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ መብት ።**

ሻጩ ፡ የመወዳደር ፡ ሥራ ፡ እንዳይሠራ ፡ ያለበት ፡ ሕጋዊ ፡ ግዴታ ፡ በቍ ፡ ፸፭ ፡ መሠረት ፡ የንግድ ፡ መደብ ፡ መብት ፡ በመሆኑ ፡ ይህም ፡ ለገዢውና ፡ ለወራ ሾቹ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የንግድ ፡ መደብሩን ፡ ከገዥ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ገዢዎች ፡ ለሆኑትም ፡ የሚጸና ፡ ነው ።

BACK



## ክፍል ፡ ፬ ።

## የገዢው ፡ ግዴታዎች ።

### ቍ ፡ ፻፷ ። የዋጋ ፡ መክፈል ፡ ግዴታ ።

ገዢው፡ በሽያጭ፡ ውል፡ በተስማሙበት ፡ መሠረት ዋጋውን ፡ መክፈል ፡ አለበት ። ስለ ፡ ዋጋው ፡ አከፋፈል ፡ የተስማሙበት ፡ ባይኖር ፡ ግን ፡ ዋጋውን ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ይከፍላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳን ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በቍጥር ፡ ፻፷፱ ፡ የተመለከተውን ፡ መጠበቅ ፡ ይገባል ።

### ቍ ፡ ፻፷፩ ። ሽያጩን ፡ የማስታወቅ ፡ ግዴታ ።

ገዢው፡ ከዚህ ፡ በታች፡ ባለው ፡ ቍጥር ፡ ፻፷፩ ፡ እስከ ፡ ፻፷፫ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ሽያጩን ፡ በማስታወቂያ ፡ እንዲወጣ ፡ ማድረግ ፡ ይገባዋል ።

### ቍ ፡ ፻፷፪ ። ስለ ፡ ዋጋው ፡ መታገድ ።

(፩) ከሽያጩ፡ ቀን ፡ አንሥቶ፡ ለመቃወሚያ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ መቃወሚያ፡ ሳይቀርብበት ፡ እስኪያልፍ ፡ ወይም ፡ የተነሣው ፡ መቃወም ፡ በስምምነት፡ወይም ፡ በፍርድ ፡ ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ መብቶች ፡ እስኪወሰንና ፡ ገንዘብ፡ ጠያቂዎቹም ፡ የተወሰነላቸውን ፡ እስኪቀበሉ ፡ ድረስ ፡ የሽያጩ ፡ ገንዘብ ፡ በገዢው ፡ እጅ ፡ ታግዶ ፡ ይቈያል ።

(፪) እስከዚሁ ፡ ድረስ ፡ ማናቸውም ፡ የገንዘብ ፡ መክፈል ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ተፈላጊ ፡ ገንዘብን ፡ መተው ፡ ከሻጩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ፈላጊዎች ፡ በሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ።

(፫) በሽያጩ፡ ውል፡ ውስጥ ፡ ገዢው ፡ የሽያጩን ፡ ገንዘብ ፡ ባንድ ፡ ሦስተኛ ፡ሰው፡ እጅ ፡ እያደራ ፡ ያስቀምጣል ፡ ተብሎ ፡ ለመስማማትም ፡ ይቻላል ። ገዢው ፡ ይኸንን ፡ በመሰለ፡ አደራረግ ፡ ከሻጩ ፡ ነጻ ፡ ቢሆንም ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ስምምነት፡ ተከፍሎና፡ ታግዶ ፡ ለተቀመጠው ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ገዢው ፡ ከሻጩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ፡ ጠያቂዎች ፡ ለሆኑት ፡ ኀላፊነት ፡ የማይቀርለት ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፻፷፫ ። የሻጩ ፡ ዋስትናዎች ።

ሻጩ ፡ ዋጋው ፡ በሙሉ ፡ እስኪከፈለው ፡ ድረስ ፡ ስለ ፡ ገንዘቡ ፡ አከፋፈል ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተመለከቱት ፡ ቍጥሮች ፡ ፻፷፫ ፡ እስከ ፡ ፻፷፯ ፡ በታዘዘው ፡ መሠረት ፡ በተሸጠው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ የመያዣ ፡ መብትና ፡ ውሉ ፡ ይፍረስልኝ ፡ ብሎ ፡ ክስ ፡ የማቅረብ ፡ መብት ፡ አለው ።

BACK



## ክፍል ፡ ፭ ።

## ሽያጮቹን ፡ በማስታወቂያ ፡ ስለ ፡ ማስወጣትና ፡ ከሻጩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ። ጠያቂዎች ፡ ያሏቸው ፡ መብቶች ።

**ቍ ፡ ፻፷፬ ። ሽያጩን ፡ በማስታወቂያ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ።**

(፩) ማናቸውም ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ሽያጭ ፤ የንግዱ ፡ መደብር ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በሚገኝበት ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሕጋዊ ፡ ማስታወቂያዎችን ፡ በሚያትመው ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥና ፡ እንዲሁም ፡ በንግድ ፡ እ፡፡ሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ በገዢው ፡ ትጋት ፡ ታትሞ ፡ እንዲታወቅ ፡ ማድረግ ፡ ይገባል ።

(፪) የተሸጠውም ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ የቅርንጫፍ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ የወኪል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ያሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) መሠረት ፡ ማስታወቂያውም ፡ የሚደረገው ፡ እያንዳንዱ ፡ የቅርንጫፍ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ የወኪል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በሚኖሩበት ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ሕጋዊ ፡ ማስታወቂያዎችን ፡ ለማተም ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ጋዜጣ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፻፷፭ ። በማስታወቂያው ፡ ስለሚጠቀሱ ፡ ነገሮች ።**

በቍጥር ፡ ፻፷፬ ፡ መሠረት ፡ የሚወጡት ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ፍርስ ፡ እንዳይሆኑ ፤

(ሀ) የሻጭንና ፡ የገዢውን ፡ ስሞችና ፡ አድራሻዎች ፤

(ለ) የንግዱን ፡ መደብር ፡ ዐይነትና ፡ አድራሻ ፤

(ሐ) ከንግድ ፡ መደብሩ ፡ ጋራ ፡ የተሸጡ ፡ የቅርንጫፍ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ የወኪል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የሥራቸውን ፡ ዐይነትና ፡ አድራሻቸውን ፤

(መ) የሽያጩን ፡ ዐይነት ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱን ፤

(ሠ) የሽያጩን ፡ ዋጋ ፤

(ረ) የንግድ ፡ መደብሩ ፡ ዋና ፡ መኖሪያው ፡ ባለበት ፡ ስፍራ ፡ መቃወሚያዎችን ፡ ለመቀበል ፡ የመረጠውን ፡ መኖሪያውን ፡ መጥቀስ ፡ ይገባቸዋል ።

**ቍ ፡ ፻፷፮ ። ለማስታወቂያው ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።**

(፩) በቍ ፡ ፻፷፬ ፡ መሠረት ፡ ማስታወቂያዎቹን ፤ ሽያጩ ፡ በተደረገበት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ማውጣት ፡ ይገባል ።

(፪) ዘግይተው ፡ የሚወጡትም ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ይጸናሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መዘግየቱ ፡ ገዢውን ፡ በሻጩ ፡ ወይም ፡ ከሻጩ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በሆኑት ፡ ፊት ፡ ኀላፊነት ፡ ሊያደርስበት ፡ የሚችለው ፡ መዘግየቱ ፤ ለነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰባቸው ፡ መሆኑ ፡ በተረጋገጠ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፳፯ ። የመቃወም ማስታወቂያ ።

(፩) ከወጡት ፡ ማስታወቂያዎች፡ የመጨረሻው ፡ ማስታወቂያ ፡ ከወጣበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ማናቸውም ፡ ከሻጩ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ተፈላጊውም ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈል ፡ የመጠየቂያው ፡ ጊዜ ፡ ያልደረሰ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳን ፡ ለሻጩ ፡ ዋጋው ፡ እንዳይከፈለው ፡ ለማድረግ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻና ፡ ይህንኑም ፡ መቃወሚያ ፡ ለገዢው ፡ ለዚሁ ፡ በመረጠው ፡ መኖሪያው ፡ እንዲደርሰው ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) የመቃወሚያውም፡ ማስታወቂያ፡ የተቃዋሚውን፡ ስም፤ የሚፈልገውን፡ ገንዘብ፡ ብዛትና ፡ ምክንያት ፡ በትክክል ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

(፫) በቍ፡ ፻፳፭፡ መሠረት፡ ማስታወቂያ፡ ሳይወጣ፡ በቀረ፡ ጊዜና፡ ወይም ፡ ማስታወቂያዎቹ፡ በቍ፡ ፻፳፮፡ የተዘረዘሩት፡ ያልገለጹ፡ እንደ፡ ሆነ፤ መቃወሚያ፡ ለማቅረቢያ ፡ የተወሰነውን ፡ ጊዜ፡ መጠበቅ ፡ ሳይሻ፡ መቃወሚያዎቹን፡ ለማቅረብ፡ ይቻላል ።

(፬) መቃወሚያው፡ እስኪወሰን፡ ድረስ፡ ዋጋው ፡ በገዢው ፡ እጅ ፡ ወይም ፡ አደራ፡ አስቀማጭ፡ በሆነው፡ ሦስተኛ፡ ወገን፡ እጅ፡ ታግዶ ፡ እንዲቀመጥ ፡ የተደረገውን፡ ማጥፋት ፡ አይችልም ፤ እንዲሁም ፡ በቍጥር ፡ ፻፳፪ ፡ ድንጋጌዎችም ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፻፳፰ ። መቃወሚያዎችን ፡ ስለ ፡ ማንሣት ።

ሻጩ፡ መቃወሚያዎቹ፡ እንዲነሡ፡ ፍርድ፡ ቤትን፡ ለመጠየቅ፡ ይችላል ፤ ለመጠየቅም፡ የሚችለው፡ እነዚሁ፡ መቃወሚያዎች፡ ሥርዐትን፡ ያልተከተሉ፡ ወይም፡ ቀኑ፡ የተላለፈባቸው፡ የሆኑ፡ ወይም፡ በበቂ ፡ ምክንያት ፡ ያልተደገፉ፡ በሆነ፡ጊዜ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፳፱ ። ስለ ፡ ዋጋው ፡ ማከፋፈል ።

(፩) የንግድ ፡ መደብር ፡ ዋጋ ፡ በንግድ፡ መደብሩ ፡ ላይ ፡ መያዣ ፡ ዋስትና ፡ ባላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በሆኑትና ፡ መቃወሚያ ፡ ያቀረቡት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ፡ በሆኑት ፡ መካከል ፡ በስምምነት ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ እንዲከፋፈል ፡ ይደረጋል ።

(፪) ከዋጋው ፡ ትርፍ ፡ ገንዘብ ፡ ለሻጩ ፡ ይመለስለታል ።

ቍ ፡ ፻፴ ። ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በሐራጅ ፡ ዋጋ ፡ አብልጦ ፡ ስለ ፡ መስጠታቸው ።

(፩) በንግዱ፡ መደብር፡ የመያዣ፡ ዋስትና፡ ያላቸው፡ ገንዘብ፡ ጠያቂዎች፡ የሆኑትና፤ መቃወሚያ፡ ያቀረቡት፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የሆኑት ፤ (ቍጥር ፡ ፻፳፱፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ ) የንግዱ ፡ መደብር ፡ ዋጋ ፡ ለሚፈልጉት፡ ገንዘብ ፡ አከፋፈል ፡ የማይበቃ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እነዚህም ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የንግዱ ፡ መደብር፡ በሐራጅ ፡ ይሸጥ ፡ ዘንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ መጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ የንግዱ ፡ መደብር ፡ በውሉ ፡ በተመለከተው ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡

አንድ ፡ ዐሥረኛው ፡ ተጨምሮበት ፡ በሐራጅ ፡ ይሸጥ ፡ ዘንድ ፡ ያዝዛል ።

(፫) በሐራጅ ፡ አብልጦ ፡ የሚሰጥ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ገዥ ፡ ሳይቀርብ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የንግዱን ፡ መደብ ፡ ዋጋ ፡ አብልጦ ፡ ለሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ በሐራጅ ፡ ይሸጣል ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## የንግዱን ፡ መደብር ፡ በዋስትና ፡ መያዣ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፻፸፩ ። መያዣ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡ ችሎታ ።**

(፩) የንግድ ፡ መደብርን ፡ በዋስትና ፡ መያዣ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) የንግድ፡ መደብርን ፡ በዋስትና ፡ መያዣ ፡ ማድረግ ፡ ከሕግ ፡ ወይም፡ ከውል፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

(፫) በንግድ፡ መደብር ፡ ላይ ፡ የሚደረገው ፡ ማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ከሕግ፡ ወይም፡ በውል ፡ የሆነ ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ መመዝገብ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፻፸፪ ። ከሕግ ፡ የሆኑ ፡ የዋትስና ፡ መያዣዎች ።**

(፩) ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ በንግድ ፡ መደብር ፡ ላይ ፡ ከሕግ ፡ የሆነ ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ አላቸው ።

(ሀ) ዋጋው ፡ ያልተከፈለው ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ሻጭ ፡ የሆነ ፤

(ለ) በነጋዴው ፡ መክሠር ፡ በወል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፤

(፪) በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) ፡ (ለ) የተመለከተው ፡ ከሕግ ፡ የሆነ ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ ላይ ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ የአምስተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ተገቢ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

### ክፍል ፡ ፪ ።

### ሻጩ ፡ በንግድ ፡ መደብር ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ ከሕግ ፡ የሆነ ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ መብትና ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ።

**ቍ ፡ ፻፸፫ ። ከሕግ ፡ የሆነ ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ።**

(፩) የንግድ ፡ መደብር ፡ ዋጋ ፡ ያልተከፈለው ፡ ሻጭ ፡ በተሸጠው ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ዋጋው ፡ አከፋፈል ፡ ወይም ፡ ከዋጋው ፡ ላይ ፡ ስለሚቀረው ፡ ገንዘብ ፡ አከፋፈል ፡ ከሕግ ፡ የሆነ ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) መሠረት ፡ ከሕግ ፡ የሆነ ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ ለሻጩ ፡ የሚጸናው ፡ ሺያጩ ፡ በጽሑፍ ፡ ተደርጎ ፡ በተፈጸመበት ፡ ወራት ፡ ውስጥ ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ዋስትናዎች ፡ በሚጻፉበት ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ከሕግ ፡ የሆነ ፡ የዋስትና ፡ መያዣነቱ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ እንዲመዘገብ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፹፩ ። ውል ፡ እንዲፈርስ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ።</u>

እንደዚሁም ፡ ዋጋው ፡ ያልተከፈለው ፡ ሻጭ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ። ሻጩም ፡ በዚህ ፡ መብት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ ሊከራከርበት ፡ የሚችለው ፡ ከሕግ ፡ የሆነ ፡ የዋስትናው ፡ መያዣ ፡ በሕግ ፡ በሚጸና ፡ አኳኋን ፡ ተመዝግቦና ፡ በመዝገቡም ፡ ውስጥ ፡ ውሉን ፡ የማፍረስ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ በተለይ ፡ ተጠብቆለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፹፪ ። ከሕግ ፡ የሆነ ፡ የዋስትና ፡ መያዣውን ፡ ስለ ፡ ማስመዝገብ ።</u>

(፩) የሻጩ ፡ ከሕግ ፡ የሆነ ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ በተመዘገበ ፡ ጊዜ ፡ መጻፍ ፡ የሚገባውም ፤

(ሀ) የሻጩና ፡ የገዢው ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፤

(ለ) የሺያጩ ፡ አፈጻጸም ፡ ዐይነትና ፡ የተጻፈበት ፡ ቀንና ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ የሺያጩ ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፤

(ሐ) ከዋጋው ፡ የተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፤

(መ) ቀሪው ፡ ገንዘብ ፡ የሚከፈልበት ፡ አኳኋንና ፡ የወለዱ ፡ ልክ ፤

(ሠ) ዋጋው ፡ ሳይከፈል ፡ ቢቀር ፡ በቍ ፡ ፪፻፹፩ ፡ መሠረት ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ መሆኑን ፤

(ረ) የንግድ ፡ መደብሩ ፡ የሥራው ፡ ዐይነትና ፡ አድራሻው ፤

(ሰ) ስለ ፡ ዋስትና ፡ መያዣ ፡ የሆኑትን ፡ የመደብሩ ፡ ንብረቶች ፡ ዝርዝር ።

(ቀ) ያለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከንግድ ፡ መደብሩ ፡ ጋራ ፡ በዋስትና ፡ መያዣ ፡ የሆኑትን ፡ የቅርንጫፍ ፡ ወይም ፡ የወኪል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ አድራሻ ፡ ነው ።

(፪) ከሕግ ፡ የሆነ ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ መብት ፡ የሚፈጸመው ፡ ከመደብሩ ፡ ንብረቶች ፡ ተጠቅሰው ፡ በተመዘገቡ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፹፫ ። ውል ፡ ማፍረስን ፡ ለመጠየቅ ፡ ስለሚቀርበው ፡ ክስ ።</u>

(፩) የሺያጩ ፡ ዋጋ ፡ ሳይከፈል ፡ በመቅረቱ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ የሚጠይቅ ፡ ሻጭ ፡ ከዋጋው ፡ የቀረው ፡ ገንዘብ ፡ ምን ፡ ያህልም ፡ ቢሆን ፡ ከሺያጩ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ካልተመለከቱት ፡ አዳዲስ ፡ ከተጨመሩት ፡ ንብረቶች ፡ በስተቀር ፡ ክስ ፡ በጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ ያገኘውን ፡ የመደብሩን ፡ ንብረት ፡ መላውን ፡ መልሶ ፡ መውሰድ ፡ አለበት ። (ቍ ፡ ፪፻፹፩) ።

(፪) በሻጪና ፡ በገዥ ፡ መካከል ፡ በሚደረገው ፡ ውሳኔ ፡ የተሸጡትን ፡ ንብረቶች ፡ ዋጋ ፡ ከፍ ፡ ወይም ፡ ዝቅ ፡ ማለት ፡ ግምት ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ አለበት ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## በንግድ ፡ መደብር ፡ ላይ ፡ ስለሚደረገው ፡ የውል ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ።

### ቍ ፡ ፻፸፯ ። በውል ፡ የተደረገ ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ ሁኔታዎች ።

(፩) ማናቸውም፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ፡ መሠረት ፡ ችሎታ ፡ ያለውና ፡ የአንድ ፡ ንግድ ፡ መደብር ፡ ባለቤት ፡ (ባለሀብት ፡) የሆነ ፡ ሰው ፡ ንግዱን ፡ ራሱ ፡ ባያካሂደውም ፡ እንኳ ፡ የንግድ ፡ መደብሩን ፡ በውል ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ።

(፪) ይኸም ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ ውል ፡ በጽሑፍ ፡ መደረግና ፡ ውሉም ፡ በተጻፈበት ፡ በአንድ፡ወር ፡ ውስጥ ፡ የንግድ ፡ መደብሮች ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ በሚመዘገቡበት ፡ መዝገብ ፡ መመዝገብ ፡ አለበት ።

### ቍ ፡ ፻፸፰ ። ስለ ፡ ማስመዝገብ ።

(፩) የውል ፡ የዋስትና ፡ መያዣ፡ ሲመዘገብ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ መጻፍ ፡ የሚገባው፤

(ሀ) የዋስትና ፡ መያዣ ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂና ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ የሰጠው ፡ ባለ ፡ ዕዳ ፤ ስምና ፡ አድራሻው ፤

(ለ) በውል ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ የተሰጠበት፡ ዐይነትና ፡ የተጻፈበት ፡ ጊዜው ፤

(ሐ) በዋስትናው ፡ መያዣ ፡ መሠረት ፡ የተፈላጊው ፡ ገንዘብ ፡ ልክና ፡ ያከፋፈሉም ፡ ሁኔታዎች ፤ የወለዱ ፡ ብዛት ፤

(መ) የንግዱ ፡ መደብር ፡ የሥራው ፡ ዐይነትና ፡ አድራሻው ፤

(ሠ) በዋስትና ፡ ስለ፡ መያዣ ፡ የተሰጡት ፡ የመደብሩ ፡ ንብረቶች ፡ ዝርዝር ፤

(ረ) ያለም፡ እንደ፡ ሆነ፡ ከንግዱ፡ መደብር ፡ ጋራ ፡ በዋስትና ፡ መያዣ ፡ የሆኑት ፡ የቅርንጫፍ ፡ ወይም ፡ የወኪል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶቹ ፡ አድራሻ ፡ ነው ።

(፪) በውል፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ የሚጸናው ፡ በተለይ ፡ ከመደብሩ ፡ ንብረቶች ፡ ተጠቅሶ ፡ በተመዘገቡት ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

## በንግድ ፡ መደብር ፡ ላይ ፡ የሚደረጉትን ፡ የዋስትና ፡ መያዣዎችን ፡ ስለ ፡ ማስመዝገብ ።

### ቍ ፡ ፻፸፱ ። የማስመዝገቢያው ፡ ቦታ ።

(፩) በንግድ ፡ መደብር፡ ላይ ፡ የሚደረገውን ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ ለማስመዝገብ፡ መጠየቅ ፡ የሚገባው ፡ በያንዳንዱ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ማስ

መዝገቢያ ፡ መዝገብ ፡ ሥራ ፡ እንዲያካሂድ ፡ የንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የሾመውን ፡ ሠራተኛ ፡ ነው ።

(፪) የዋስትና ፡ መያዣው ፡ በንግድ ፡ መደብር ፡ ዋና ፡ መኖሪያው ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ መመዝገብ ፡ አለበት ።

(፫) ከጠቅላይ፡ ግዛቱ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ የቅርንጫፍ ፡ ወይም ፡ የወኪል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ያሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቅርንጫፍ ፡ ወይም፡የወኪል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ሥራ ፡ በሚካሂድበት ፡ ቦታ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የዋስትናው ፡ መያዣ ፡ መመዝገብ ፡ ይገባዋል ።

ቍ ፡ ፻፵፬ ። የንግድ ፡ መደብሩን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ ስለ፡ ማዛወር ።

(፩) ባለዕዳ ፡ የሆነው ፡ የንግድ ፡ መደብሩን ፡ ለማዛወር ፡ ሲፈለግ ፡ የሚፈለግበትን ፡ ገንዘብ ፡ ወዲያውኑ ፡ እንዲከፍል ፡ ከመደረግ ፡ ይድን ፡ ዘንድ ፡ የንግድ ፡ መደብሩን ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ አድርገው ፡ ላስመዘገቡት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች፡ ማስታወቅና ፡ ከማዛወሩም ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ወር ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ።

(፪) በመደብሩ፡ የዋስትና ፡ መያዣነት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆኑትም ፡ በቦታው ፡ መዛዋር ፡ የመደብሩ ፡ ዋጋ ፡ ይቀነሳል ፡ ብለው ፡ የሚገምቱ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ በቍጥር ፡ ፻፵፫ ፤ መሠረት ፡ የሚገባቸውን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

(፫) ገንዘብ፡ ጠያቂዎቹ፡ ማዛወሩን ፡ የሚፈቅዱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መደብሩ ፡ የሚዛወረው ፡ ከጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ ሲሆን ፡ ይኸንኑ ፡ በማስመዝገቢያው ፡ መዝገብ ፡ እንዲስተካከል ፡ ጠይቀው ፡ ማስተካከል ፡ አለባቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መደብሩ ፡ ከጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ቦታ ፡ የሚዛወር ፡ ከሆነ ፡ መደብሩ ፡ አዲስ ፡ ዋና ፡ መኖሪያ ፡ ባደረገበት ፡ ቦታ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ባለው ፡ መዝገብ ፡ አዲስ ፡ ማስመዝገብ ፡ አለባቸው ።

(፬) በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ በኡንሱ ፡ ቍጥር ፡ (፫) ፡ መሠረት ፡ በመዝገቡ ፡ የተደረገው ፡ ማስተካከል ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ እንዲመዘገብ ፡ የተደረገው ፡ ሁሉ ፡ በመጀመሪያ ፡ ከመተዘገቡበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፻፵፭ ። ስለ ፡ ዋናውና ፡ ስለ ፡ ወለዱ ።

የመያዣው ፡ መመዝገብ፡ ከዋናው፡ ገንዘብ ፡ ጋራ ፡ የሁለት ፡ ዓመትን ፡ የወለድ ፡ ዋስትና ፡ ያጸናል ።

ቍ ፡ ፻፵፮ ። መመዝገቡ ፡ ጸንቶ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ።

የዋስትና፡ መያዣነት፡ ከተመዘገበበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ የጸና ፡ ይሆናል ። በዚሁ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሳይታደስ ፡ ቢቀር ፡ ግን ፡ ወደፊት ፡ ጽናት ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፻፹፫ ። ስለ ፡ መሰረዝ ።**

የተመዘገበው፡ የዋስትና፡ መያዣ ፡ ጥቅም፡ ባላቸው ፡ በባለጕዳዮቹ ፡ በተጻፈ ፡ ስምምነት ፡ ይሰረዛል ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተፈረደው ፡ መጨረሻ ፡ በሆነ ፡ ፍርድ ፡ መሠረት ፡ የሚሰረዝ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፻፹፬ ። የመዝገቡን ፡ ግልባጭና ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ስለ ፡ መስጠት ።**

ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የተወሰነውን ፡ ክፍሎ ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ መዝገቦች ፡ ከሚይዙ ፡ የመንግሥት፡ሠራተኞች ፡ በዋስትና ፡ መያዣ፡ የተመዘገበበትን፡ በአጭር ፡ የተውጣጣውን ፡ ግልባጭ፡ ወይም ፡ በመደብሩ ፡ ባለ ቤት ፡ ስም ፡ የተመዘገበ ፡ ነገር ፡ ያለመኖሩን ፡ የሚመሰክር ፡ አንድ ፡ የምስክር፡ ወረቀት ፡ ጠይቆ ፡ ለመቀበል ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፻፹፭ ። ስለ ፡ ኀላፊነት ።**

የንግድ ፡ መደብር፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ የሚመዘገብባቸውን፡ መዝገቦች ፡ የሚ ይዙ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በመዝገባቸው ፡ ውስጥ ፡ በደንብ ፡ እንዲመ ዘግቡ ፤ የተጠየቁትን ፡ በመዘንጋት ፡ ለሚያደርጉት ፡ ስሕተትና ፡ እንዲሁም፡ በቍጥር ፡ ፻፹፬ ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ዋስትና ፡ መያዣ ፡ በሚሰጡት ፡ ግልባጭ ፡ ወይም ፡ በምስክር፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ለዘነጉትና ፡ ላደረጉትም ፡ ስሕተት ፡ ሁሉ ፡ ራሳቸው ፡ ኀላፊዎች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፻፹፮ ። ደንቦች ፤**

(፩) ከዚህ ፡ በታች ፡ የተመለከቱት ፤

(ሀ) ስለ፡ ንግድ፡ መደብር፡ የዋስትና፡ መያዣነት ፡ ለሚመዘገቡት ፡ መዝገቦች ፡ አያያዝና ፡ አፈጻጸም ፤

(ለ) ስለ ፡ ማስመዝገቢያ፡ ለማሰረዝ ፡ ወይም ፡ ሊከተሉት ፡ የሚገባ ፡ ሥርዐት ፤ በደንብ ፡ ይወሰናሉ ።

(፪) ስለ ፡ ማስመዝገቢያ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፤ በአጭር ፡ ለተውጣጣውና ፡ የምስክር ፡ ወረቀቶች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍ ፤ ፻፹፬ ፡ መሠረት ፡ ሲሰጡ ፡ የሚከፈ ልባቸው ፡ ዋጋ ፡ በሕግ ፡ ይወሰናል ።

## ክፍል ።

## የዋስትና ፡ መያዣ ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በንግድ ፡ መደብሩ ፡ ላይ ፡ ያሏቸው ፡ መብቶች ።

**ቍ ፡ ፻፹፯ ። ስለ ፡ ንግድ ፡ መደብር ፡ መሸጥና ፡ ማከራየት ።**

(፩) ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ውል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ባለዕዳው ፡ የንግዱን ፡ መደብር ፡ ለመሸጥ ፡ ወይም ፡ ለማከራየት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ የንግዱን ፡ መደብር ፡ ቢሸጥ ፡ ወይም ፡ ቢያከራይ ፡ በዋስትና ፡ መያዣው ፡ መሠረት ፡ የሚፈለግበትን ፡ ገንዘብ ፡ በፍጥነት ፡ እንዲከፈል ፡ ያስደርገዋል ፡ የሚል ፡ ውል ፡ ለመዋዋል ፡ ይቻላል ። ይህም ፡ ውሉ ፡ በሚመዘገብበት ፡ ጊዜ ፡ በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ እንዲጠቀስ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

ቁ ፡ ፪፻፫ ። ስለ ፡ ዋስትናው ፡ መጕደል ።

ባለዕዳ ፡ የሆነው ፡ የንግዱን ፡ መደብር ፡ ዋጋ ፡ ቢያጐድል ፡ ወይም ፡ ለመጕደል ፡ የሚያሠጋው ፡ ቢሆን ፡ በተለይም ፡ የንግዱን ፡ መደብር ፡ ቦታ ፡ በመለወጥ ፡ ምክንያት ፤ የመደብሩ ፡ ሥራ ፡ የሚከናወንባቸው ፡ ቤቶች ፡ ኪራይ ፡ ባለመከፈሉ ፡ የሸቀጦቹ ፡ ብዛት ፡ እየተጓደለ ፡ በመሄዱ ፤ ገንዘብ ፡ ፈላጊው ፡ አዲስ ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ። ይህም ፡ ባይሆን ፡ ከባለዕዳው ፡ ላይ ፡ የሚፈልገው ፡ ገንዘብ ፡ በፍጥነት ፡ እንዲከፈለው ፡ በፍርድ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቁ ፡ ፪፻፬ ። ስለ ፡ ማስያዝ ፡ መብት ።

(፩) የዋስትና ፡ መያዣ ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የሚፈልገው ፡ ገንዘብ ፡ መክፈያው ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ይኸንኑ ፡ ለማስከፈል ፡ ለባለዕዳው ፡ አስታውቆና ፡ ሳይከፈለውም ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ የንግዱን ፡ መደብር ፡ ለማስያዝና ፡ በሐራጅም ፡ እንዲሸጥ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።
(፪) የዋስትና ፡ መያዣ ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የሚፈልገው ፡ ገንዘብ ፡ ሳይከፈለው ፡ ቢቀር ፡ የሕጉን ፡ ሥርዐት ፡ ሳይከተል ፡ የንግዱን ፡ መደብር ፡ ለማሲያዝ ፡ ወይም ፡ ሊሸጠው ፡ ይችላል ፡ ተብሎ ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ለመዋዋል ፡ አይቻልም ።

ቁ ፡ ፪፻፭ ። ስለ ፡ መከታተል ፡ መብት ።

(፩) መያዣ ፡ የሆነው ፡ መደብር ፡ በማንም ፡ እጅ ፡ ቢተላለፍ ፡ መያዣነቱ ፡ የሚከተለው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ መያዣው ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ተላልፎም ፡ ቢገኝ ፡ ለማስያዝ ፡ ይችላል ።
(፪) ይኸንንም ፡ የያዘው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ በዋስትና ፡ መያዣነት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ለሆኑት ፡ የሚፈልጉትን ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ ካልከፈላቸው ፡ በስተቀር ፡ መያዣ ፡ የሆነ ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ እንዳይያዝ ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ።

ቁ ፡ ፪፻፮ ። የዋስትና ፡ መያዣ ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ወሰን ።

(፩) በዋስትና ፡ መያዣነት ፡ መሠረት ፡ የንግዱ ፡ መደብር ፡ እንዲያዝ ፡ በታዘዘ ፡ ጊዜ ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የንግዱ ፡ መደብር ፡ በሚገኝበት ፡ ሁኔታ ፡ የንብረቶቹ ፡ ክፍሎች ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ ከፍተኛነት ፡ ያላቸው ፡ ቢሆንም ፡ መያዣው ፡ ይጸናበታል ።

(፪) በዋስትና መያዣነት፣ የሚያዙት፣ ነገሮች ፡ በተመዘገበ ፡ ጊዜ ፡ በተለይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ንብረቶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፻፺፪ ። የቀደምትነት ፡ መብት ።

(፩) ከንግዱ፣ መደብር ፡ ሽያጭ ፡ ላይ ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ፈላጊዎች ፡ የቀዳሚነት ፡ መብቶች ፡ አሏቸው ።

(፪) የዋስትና፣ መያዣ፣ ባላቸው፣ ገንዘብ፣ ጠያቂዎች ፡ በሆኑት ፡ መካከል ፡ ተረኛነቱ ፡ በተመዘገቡበት ፡ ቀን ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ፡ የዋስትና ፡ መያዣነትን ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ያስመዘገቡት ፡ ግን ፡ ተወዳዳሪዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፫) ስለሆነም ፡ የሻጩ ፡ በገዢው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ከሕግ ፡ የሆነው ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፤ ከውል ፡ የሆነ ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ከሆኑት ፡ ቅድሚያነት ፡ ያለው ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፻፺፫ ፡ የዋስትና ፡ መያዣ ፡ ያለው ፡ ከከሠረው ፡ ባለዕዳ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎችን ፡ መቃወም ፡ ስለ ፡ መቻሉ ።

በንግድ ፡ መደብር ፡ ላይ ፡ የተመዘገበ ፡ የዋስትና ፡ መያዣነት ፡ ያላቸው ፤ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በአምስኛው ፡ መጽሐፍ ፡ በተመለከቱት ፡ ተገቢ ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት፣ ከከሠረው፣ ባለዕዳ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁትን ፡ መቃወሚያ ፡ ይሆናል።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

የንግድ ፡ መደብርን ፡ ስለ ፡ ማከራየት ።

ቍ ፡ ፻፺፬ ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) የንግድ ፡ መደብርን ፡ ለማከራየት ፡ ይቻላል ።

(፪) የንግድ፣መደብር፣የኪራይ፣ ውል፣ በፍትሐ፣ ብሔር፣ ሕግ፣ በቍጥር፣ ፪ሺ፰፻፺፮፣ እስከ ፡ ፪ሺ፱፻፸፬ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ፤ ስለሆነም ፡ የዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ በቍጥር፣ ፻፺፩፣ እስከ፣ ፪፻፫፣ የተመለከቱት፣ የተጠበቁ፣ ሆነው፣ ነው ።

ቍ ፡ ፻፺፭ ። ውልን ፡ በግልጽ ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።

(፩) የንግድ፣ መደብር፣ የኪራይ ፡ ውል ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ፡ይሆን፣ ዘንድ፣ በጽሕፈት፣ መሆንና ፤ ከሁለቱ፣ አንደኛው ፡ ወገን ፡ አመልክቶ ፡ የንግዱ ፡ መደብር ፡ መኖሪያ ፡ በሆነው ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ሕጋዊ ፡ ማስታወቂያዎችን ፡ ለማተም ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥና ፡ በንግድ ፡ ኦፊሲዬል ፡ ጋዜጣም ፡ መታተም ፡ አለበት ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍ፣ (፩) መሠረት ፡ የሚወጡትም ፡ ማስታወቂያዎች ፤

(ሀ) የአከራዩንም ፡ የተከራዩንም፣ ስምና ፡ አድራሻ ፤

(ለ) የውሉን ፡ ዐይነትና ፡ የተጻፈበትም ፡ ቀን ፤

(ሐ) የመደብሩ ፡ ጕዳይና ፡ አድራሻ ፤

(መ) የኪራዩንም ፡ ውል ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፤ ዘርዝሮ ፡ ማመልከት ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፯፻፷፯ ። ስለ ፡ ንግድ ፡ መዝገብ ።

በኪራይ ፡ የተሰጠው ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ባለቤት ፡ (ባለሀብት) ፡ ከንግድ ፡ መዝገብ ፡ ስሙን ፡ ማሰረዝ፡ አለበት ። ተከራዩም፡ ስሙን ፡ ማስመዝገብ ፡ አለበት። ይህም ፡ የሚፈጸመው ፡ በዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩ ፡ በተመለከቱት ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፯፻፷፰ ። ስለ ፡ ንግድ ፡ መደብር ፡ አከራይ ፡ ኀላፊነት ።

በቍ፡፯፻፷፮፡ እና፡ ፯፻፷፯፡ በተመለከተው፡መሠረት፡ካልተፈጸመ፡ የንግድ፡መደብር፡ ባለቤት፡ በንግድ ፡ መዝገብ፡ ውስጥ ፡ ስሙን ፡ እስኪያሰርዝ፡ ድረስ ፡ እንዲሁም፡ ተከራዩ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ስሙን ፡ እስኪያስመዘግብ ፡ ድረስና ፡ የኪራዩም፡ ውል ፡ በጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ እስከወጣ ፡ ድረስ፤ ወይም ፡ በጋዜጣ ፡ ማስታወቂያ፡ የማውጣት፡ ጕዳይ ፡ በመጨረሻ ፡ ከተደረገበት፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ተከራዩ ፡ በንግዱ ፡ መደብር ፡ ሥራ ፡ ማከናወን ፡ በሚደርስበት ፡ ዕዳ ፡ ሁሉ ፡ የንግዱ ፡ መደብር ፡ ባለቤት ፡ ከተከራዩ ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ ኀላፊነት ፡ ይኖርበታል ።

ቍ ፡ ፯፻፷፱ ። በንግድ ፡ ወረቀቶች ፡ ላይ ፡ ተከራይ ፡ መሆኑን ፡ ስለ፡ መጥቀስ ።

ተከራዩ፡ ውሉ፡ ወዲያውኑ፡ ፍርስ፡ እንዳይሆንበት፡ በንግዱ ፡ ወረቀቶች፡ ላይ፡ ሁሉ ፡ ተከራይነቱን ፡ «ተከራይ» በሚል ፡ ቃል ፡ እያስከተለ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፯፻፸ ። ስለ ፡ ተከራዩ ፡ ግዴታዎች ።

ተከራዩ፡ የተስማማበትን፡ ኪራይ፡ በትክክል ፡ መክፈል ፤ የንግዱን ፡ መደብር፡ እንደ ፡ መልካም ፡ ነጋዴ ፡ ሆኖ ፡ ጥቅም ፡ ማስገኘት ፤ ሥራውንም ፡ በትክክል ፡ በንግዱ ፡ መደብር ፡ ዐይነት ፡ ማካሄድ ፡ አለበት ፤ ይህ ፡ ካልሆነ ፡ ግን ፡ ውሉ ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ።

ቍ፡ ፯፻፸፩ ። የዋስትና ፡ ገንዘብ ፡ ስለ፡ማስቀመጥ ።

(፩) በውሉ ፡ ከተወሰነው ፡ ኪራይ ፡ በላይ ፡ ተከራዩ ፡ ለአከራዩ ፡ ወይም ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ያሉበትን ፡ ግዴታዎቹን ፡ መፈጸሙን ፡ ለማረጋገጥ ፡ በዋስትና ፡ የተሰጠውን ፡ እንዲያሲይዝ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ስለ ፡ ዋስትና ፡ የተሰጠው ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ቢኖር ፡ እንኳ ፡ የኪራዩ ፡ ጊዜ ፡ ሲፈጸም ፡ እንዳለ ፡ ለተከራዩ ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

ይህም ፡ ተከራዩ ፡ ለአከራዩ ፡ ያሉበትን ፡ ግዴታዎች፡ የፈጸመ ፡ ሲሆንና ፡ እንዲሁም፡ በቍጥር ፡ ፪፻፪ ፡ በ፫ተኛው ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ እንዲያዝ ፡ ያልተደረገ ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻፩ ። ተከራዩ ፡ ሥራው ፡ የግል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

የኪራዩ፡ ውል፡ የተከራዩን፡ ሰውነት ፡ በመገንዘብ ፡ የተደረገ ፡ በመሆኑ ፡ ባለቤቱ ፡ በጽሑፍ ፡ ካልፈቀደለት ፡ በስተቀር ፡ ተከራዩ ፡ ውሉን ፡ አሳልፎ ፡ ለሌላ፡ ሰው ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፪፻፪ ። የኪራዩ ፡ ውል ፡ ጊዜ ፡ መፈጸሙን ፡ በጋዜጣ ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።**

(፩) የኪራዩ፡ ውል፡ ጊዜ፡ መፈጸሙን፡ በቍ ፡ ፻፺፰ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) መሠረት ፡ እንዲታተም ፡ ማድረግ ፡ ይገባል ።

(፪) በንኡስ፡ ቍ ፡ (፩) መሠረት ፡ በሚወጣውም ፡ ማስታወቂያ ፤

(ሀ) የአከራዩና ፡ የተከራዩ ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፤

(ለ) የንግዱ ፡ መደብር ፡ ዐይነትና ፡ አድራሻው ፤

(ሐ) የኪራዩ ፡ ውል ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ጊዜ ፤

(መ) ባስፈለገም ፡ ጊዜ ፡ በቍ ፡ ፪፻ ፡ መሠረት ፡ በዋስትና ፡ የተቀመጠው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፤ መጻፍ ፡ አለበት ።

(፫) በቍጥር ፡ ፪፻፡ መሠረት ፡ በዋስትና ፡ የተያዘው ፡ ገንዘብ ፡ ለተከራዩ ፡ የሚመለስለት ፡ ከመጨረሻው ፡ የማስታወቂያ ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ነው፤ እንደዚህ፡ ካልተደረገ፡ ግን፡ ባለቤቱ፡ ለሦስተኛ፡ ወገኖች፡ አላፊ ፡ ይሆናል።

**ቍ ፡ ፪፻፫ ። ስለ ፡ ተከራዩ ፡ ዕዳዎች ፡ አከፋፈል ፡ አስገዳጅነት ።**

የኪራዩ ፡ ውል ፡ ጊዜ ፡ መፈጸሙ ፤ ተከራዩን ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ለሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ያሉበትን ፡ ዕዳዎች ፡ በፍጥነት ፡ እንዲከፍላቸው ፡ ያስገድደዋል ።

**ቍ ፡ ፪፻፬ ። ስለ ፡ አከራዩ ፡ የንግድ ፡ መወዳደር ፡ ሥራ ፡ ክልከላ ።**

(፩) የንግድ ፡ መደብር፡ባለቤት፡ የሆነ ፤ የኪራዩ ፡ ውል ፡ በሚጸናበት ፡ ጊዜ፡ውስጥ ፡ ተከራዩን ፡ በንግድ ፡ ሊወዳደረው ፡ አይችልም ፤ በተለይም ፡ ተከራዩ ፡ የሚያካሂደውን ፡ የመሰለ ፡ ሥራ ፡ ሌላ ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ በማቋቋም ፡ ወይም ፡ በመግዛት ፡ የመወዳደር ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ አይቻለውም ።

(፪) በንኡስ፡ ቍ ፡ (፩) እንደተመለከተው፡ ባለቤቱ ፡ ያለበትን ፡ ግዴታ ፡ አፍርሶ ፡ ቢገኝ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍልና ፡ እንዲሁም ፡ ያቋቋመው ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ እንዲዘጋ ፡ ይደረጋል ።

**ቍ ፡ ፪፻፭ ። ስለ ፡ ተከራዩ ፡ የንግድ ፡ መፎካከር ፡ ክልከላ ።**

የኪራዩ፡ ውል፡ በተፈጸመ፡ ጊዜ ፡ ተከራዩ ፡ የንግዱ ፡ መደብር ፡ ባለቤት ፡ የሚ

ሠራውን ፡ ሥራ ፡ ዐይነት ፡ በመሥራት ፡ እንዳይወዳደር ፡ በውል ፡ ለመስማማት ፡ ይቻላል ።

(፪) እንደዚህ ፡ ያለውም ፡ ክልከላ ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ ለመብለጥ ፡ አይችልም ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

## የማኅበረተኛነት ፡ ድርሻ ፡ መዋጮ ፡ አድርጎ ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ መደብርን ፡ ለማኅበር ፡ ስለ ፡ ማግባት ።

### ቍ ፡ ፻፶፯ ። የማኅበረተኝነት ፡ ድርሻ ፡ መዋጮን ፡ በግልጽ ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።

ማናቸውም ፡ ስለ ፡ ማኅበርተኛነት ፡ ድርሻ ፡ መዋጮ ፡ ሆኖ ፡ ባንድ ፡ ገና ፡ ለሚቋቋም ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ ቀድሞ ፡ ለነበረው ፡ ማኅበር ፡ የሚቀርብ ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ሁሉ ፡ በቍ ፡ ፻፶፩ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ እንደተመለከተው ፡ ታትሞ ፡ መታወቅ ፡ አለበት ።

### ቍ ፡ ፻፶፰ ። በማስታወቂያዎቹ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚጻፉ ፡ ነገሮች ።

በቍ ፡ ፻፶፯ ፡ መሠረት ፡ በማስታወቂያዎቹ ፡ መጠቀስ ፡ የሚገባቸው ፡ ነገሮች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

(፩) የማኅበረተኝነት ፡ ድርሻ ፡ መዋጮ ፡ አምጪ ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፤

(፪) መዋጮ ፡ የሆነው ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ዐይነትና ፡ አድራሻ ፤

(፫) መዋጮ ፡ የተደረገለት ፡ የማኅበሩ ፡ ስምና ፡ ዐይነቱ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፤

(፬) የማቋቋሚያው ፡ ጽሑፍ ፡ የወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፻፶፱ ። የማኅበረተኝነቱ ፡ ድርሻ ፡ መዋጮ ፡ የሆነውን ፡ ስለ ፡ መቃወም ።

(፩) በቍ ፡ ፻፶፯ ፡ መሠረት ፡ ከታተሙት ፡ ማስታወቂያዎች ፡ የመጨረሻው ፡ ማስታወቂያ ፡ ከወጣበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ በወሩ ፡ ውስጥ ፡ በማኅበረተኝነት ፡ መዋጮ ፡ ከሚሰጠው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆኑ ፡ ሁሉ ፡ ተጠያቂው ፡ ገንዘብ ፡ የመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ያልደረሰም ፡ ቢሆን ፡ ለማኅበሩ ፡ በዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መኖሪያ ፡ በጽሑፍ ፡ አስታውቆና ፡ የቀረበውን ፡ የማኅበረተኛነት ፡ መዋጮ ፡ እንዳይደረግ ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

(፪) በማስታወቂያ ፡ ሳይወጣ ፡ ሲቀር ፡ ወይም ፡ ማስታወቂያው ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ መጠበቅ ፡ ሳያስፈልግ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፱ ። ማኅበረተኞቹ ፡ ማድረግ ፡ ስለሚችሉት ።**

(፩) ማንኛውም ፡ ማኅበረተኛ ፡ የሆነ ፡ በቍ ፡ ፪፻፱ ፡ መሠረት ፡ መቃወሚያው ፡ ከቀረበበት፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ በመቋቋም ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ማኅበር ፡ ፍርስ ፡ እንዲሆን ፡ ወይም ፡ ቀድሞ ፡ ለነበረው ፡ ማኅበር ፡ በማኅበረተኝነት ፡ የቀረበለት ፡ የድርሻ ፡ መዋጮ ፡ ፍርስ ፡ እንዲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) መሠረት ፡ ጥያቄ ፡ ከሌለ ፡ ግን ፡ ተቃዋሚዎቹ ፡ ስለሚጠይቁት ፡ ገንዘብ ፡ ማኅበሩ ፡ ከማኅበረተኝነት ፡ ድርሻ ፡ እምጪው ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ ኀላፊነት ፡ ይኖርበታል ።

# ሁለተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ስለ ፡ ንግድ ፡ ማኅበሮች ።

## አንቀጽ ፡ ፩ ።

## ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፪፻፲ ። የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ትርጓሜ ።**

(፩) የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ማለት ፡ ማንኛውም ፡ በሽርክና ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ የሚቋቋም ፡ ማኅበር ፡ ነው ።

* (፪) ከእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ በተቀር ፡ ማንኛውም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር፡በሕግ ፡ የሰው፡ መብት ፡ እንዳለው ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፩ ። የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ።**

የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውል ፡ ማለት ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ መዋጮ ፡ አዋጥተው ፡ በአንድነትና ፡ በኅብረት ፡ የኤኮኖሚ ፡ ተግባር ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ለመሥራትና ፡ ከሚገኘው ፡ ትርፍም ፡ ሆነ ፡ ከሚመጣው ፡ ዕዳ ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ የሚስማሙበት ፡ ውል ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻፲፪ ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ።**

(፩) በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ስድስት ፡ ዐይነት ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ አሉ ፤

(ሀ) ተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፤

(ለ) የእሽሙር ፡ ማኅበር ፤

(ሐ) የኅብረት ፡ ሽርክና ፡ ማኅበር ፤

BACK



(መ) ሁለት ፡ ዐይነት ፡ ኀላፊነት ፡ ያለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፤

(ሠ) የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፤

(ረ) ኀላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ።

(፪) በኅብረት ፡ ድርጅቶች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ የሚሆኑ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በሕግ ፡ ይወጣሉ ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፲፫ ። ስለ ፡ ንግድ ፡ ማኅበሮች ።</u>

(፩) ከተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ በተቀር ፡ ሌላው ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፭ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) መሠረት ፡ ዐይነተኛ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ድርጅት ፡ ይሆናል ።

(፪) አንድ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበር ፡ በተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ዐይነት ፡ ሆኖ ፡ የተቋቋመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የማኅበሩ ፡ ዐይነት ፡ ያልተገለጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ሥራ ፡ ማኅበር ፡ እንደ ፡ ኅብረት ፡ ሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፲፬ ። ማኅበሩ ፡ የሚቋቋመው ፡ በጽሑፍ ፡ መሆን ፡ የሚገባው ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።</u>

ከእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ በተቀር ፡ የማንኛውም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ የሚቋቋም በት ፡ ውል ፡ በጽሑፍ ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ አይጸናም ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፲፭ ። ፈራሽ ፡ ስለሚሆኑ ፡ ስምምነቶች ።</u>

(፩) ትርፉን ፡ ሁሉ ፡ ለአንደኛው ፡ ማኅበረተኛ ፡ ብቻ ፡ የሚሰጥ ፡ ስምምነት ፡ ፍርስ ፡ ነው ።

(፪) እንደዚሁም ፡ የአንዱን ፡ ወይም ፡ የብዙዎቹን ፡ ማኅበረተኞች ፡ በማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ከሚመጣው ፡ ኪሣራ ፡ እንዳይነካው ፡ የሚያደርግ ፡ ስምምነት ፡ ፍርስ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፲፮ ። ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ እንደራሴነት ።</u>

(፩) ማኅበሩ ፡ ስለ ፡ እንደራሴነት ፡ በተወሰነው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ እንደራሴ ፡ ያደረጋቸው ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ ሆነው ፡ ለሠሩት ፡ ሥራ ፡ ባለመብትና ፡ ባለዕዳ ፡ ይሆናል ።

(፪) ማኅበሩ ፡ በእንደራሴዎች ፡ አማካይነት ፡ መክሰስ ፡ ወይም ፡ መከሰስ ፡ ይችላል።

(፫) ለንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ እንዲደርስ ፡ የተጻፈውን ፡ ማናቸውንም ፡ መጥሪያ ፡ ለማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ እንዲደርስ ፡ ማድረግ ፡ ይገባል ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፲፯ ። ማኅበሩ ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በስምምነት ፡ የሚፈርስበት ፡ ምክንያት ።</u>

ማንኛውም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ የሚፈርሰው ፤

(፩) ማኅበሩ ፡ የተቋቋመበትን ፡ ጕዳይ ፡ በፈጸመ ፡ ወይም ፡ ለመፈጸም ፡ ባልቻለ ፡ ጊዜ ፤

(፪) የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖርበት ፡ ዘመን ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ተስማምተው ፡ የወሰኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(፫) ማኅበረተኞቹ ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲቀጥል ፡ ካልተስማሙ ፡ በቀር ፡ ማኅበሩ ፡ የተቋቋመበት ፡ ዘመን ፡ ሲፈጸም ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፲፰</u> ። በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ የማኅበሩ ፡ መፍረስ ።

(፩) ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ትክክለኞች ፡ ምክንያቶች ፡ ኖረውት ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ አንዱ ፡ ባቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊበይን ፡ ይችላል ።

(፪) በተለይም ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ አንዱ ፡ ተግባሩን ፡ (ግዴታዎቹን) ፡ ከመፈጸም ፡ በብዙ ፡ ያስታጐለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በአካል ፡ ጕድለት ፡ ወይም ፡ በማይድን ፡ ሕመም ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ በማንኛውም ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ የማኅበሩን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በማኅበረተኞቹ ፡ መካከል ፡ ብርቱ ፡ ጭቅጭቅና ፡ አለመስማማት ፡ የተፈጠረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማኅበሩ ፡ መፍረስ ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያቶች ፡ ይሆናሉ ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፲፱</u> ። በማስታወቂያ ፡ ስለ ፡ መግለጽ ።

(፩) ከእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ በተቀር ፡ ሌሎቹን ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ሁሉ ፡ ለሦስተኞች ፡ ወገኖች ፡ እንዲታወቁ ፡ በማስታወቂያ ፡ መግለጽ ፡ ይገባል ።

(፪) እንደዚህ ፡ ያለውም ፡ ማስታወቂያ ፡ የሚደረገው ፤

(ሀ) የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያዎችን ፡ ለማተም ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ጋዜጣ ፡ ማስታወቂያ ፡ በማውጣት ፤

(ለ) በቍ ፡ ፪፻፳፩ ፡ በታዘዘው ፡ መሠረት ፡ የጽሑፉን ፡ ሁለት ፡ ግልባጮች ፡ የንግድ ፡ መዝገብ ፡ ኀላፊ ፡ ከሆነው ፡ ሠራተኛ ፡ ዘንድ ፡ በማስቀመጥ ፤

(ሐ) በንግድ ፡ መዝገብ ፡ በማስመዝገብ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፳</u> ። ማስታወቂያ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ።

በቍጥር ፡ ፪፻፲፱ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ (ሀ) መሠረት ፡ የሚደረገው ፡ ማስታወቂያ ፡ የማኅበሩ ፡ ዋናው ፡ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በተቋቋመበት ፡ ቦታ ፡ ሕጋዊ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለማተም ፡ በተቋቋመበት ፡ ጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ መውጣት ፡ አለበት ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፳፩</u> ። ጽሑፎችን ፡ ለንግድ ፡ መዝገብ ፡ ሠራተኛ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

(፩) በቍጥር ፡ ፪፻፲፱ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ (ለ) መሠረት ፡ መኖር ፡ የሚገባው ፡ ጽሑፍ ፡ የማኅበሩ ፡ ዋናው ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ባለበት ፡ ስፍራ ፡ ከሚገኘው ፡ የንግድ ፡ መዝገብ ፡ ኀላፊ ፡ ከሆነው ፡ ሠራተኛ ፡ ዘንድ ፡ መቀመጥ ፡ አለበት ።

(፪) ማኅበሩ ፡ የተቋቋመበትን ፡ ጽሑፍ ፡ ሁለት ፡ ግልባጮችና ፡ ማና

ቾውንም ፡ ተጨማሪ ፡ ጽሑፎች ፡ የንግድ ፡ መዝገብ ፡ ኀላፊ ፡ ለሆነው፡ሠራተኛ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፫) የንግድ ፡ መዝገብን ፡ ለመጠበቅ ፡ የተሾመው ፡ ሠራተኛ ፡ ከቀረቡት ፡ ጽሑፎች ፡ አንደኛውን ፡ ያስቀርና ፡ ሁለተኛውን ፡ ግልባጭ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፺ ፡ ለተገለጸው ፡ ጠቅላይ ፡ የንግድ ፡ መዝገብ ፡ ክፍል ፡ ያስተላልፈዋል ።

(፬) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የተወሰነውን ፡ ገንዘብ ፡ ከፍሎ ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ በመዝገብ ፡ የገቡት ፡ ጽሑፎች ፡ ግልባጭ ፡ እንዲሰጠው ፡ ከጠቅላይ ፡ መዝገብ ፡ ክፍል ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ከየአገሩ ፡ ክፍል ፡ መዝገብ ፡ ሠራተኛ ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ <u>፰፻፸፪</u> ። <u>በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ስለ ፡ መመዝገብ ።</u>

(፩) በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ለመመዝገብ ፡ የሚቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ በቍጥር ፡ ፰፻፸፩፡ ከተገለጹት ፡ ጽሑፎች ፡ ጋራ ፡ አባሪ ፡ ሆኖ ፡ መሰጠት ፡ አለበት ።

(፪) የዚህ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፺፰ ፡ እስከ ፡ ፺፱ ፡ የተጻፈው ፡ ለዚህ ፡ ጒዳይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ነው ። የመዝገብ ፡ ሠራተኛው ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ የሚቋቋምባቸው ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ መፈጸምና ፡ አለመፈጸማቸውን ፡ ይቈጣጠራል ።

ቍ ፡ <u>፰፻፸፫</u> ። <u>መመዝገብ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።</u>

በመዝገብ፡ ስለ ፡ መግባት ፡ የተደነገጉት ፡ የዚህ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተጠናቀው ፡ እስኪፈጸሙና ፡ መመዝገቡም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፹፯ ፡ መሠረት ፡ ታትሞ ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ መኖሩም ፡ በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ መሆኑም ፡ በሕግ ፡ አይታወቅለትም ።

ቍ ፡ <u>፰፻፸፬</u> ። <u>ስለ ፡ ማሻሻል ።</u>

(፩) ማኅበሩ፡ የተቋቋመበት ፡ ጽሑፍ ፡ የተሻሻለ ፡ (የተለወጠ)፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተለወጠበትን ፡ ጽሑፍ ፡ የንግድ ፡ መዝገብ ፡ ከሚይዝ ፡ ሠራተኛ ፡ ዘንድ ፡ ማስቀመጥ ፡ ይገባል ።

(፪) ታትሞ ፡ ስለ ፡ ወጣና ፡ ስለ ፡ ተመዘገበ ፡ ጒዳይ ፡ የተደረገ ፡ መሻሻል ፡ ሁሉ፡ እንደዚሁ ፡ ታትሞ ፡ መውጣትና ፡ መዝገቡም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ቍ ፡ ፺፰ ፡ መሠረት ፡ መታረም ፡ አለበት ።

ቍ ፡ <u>፰፻፸፭</u> ። <u>ስለ ፡ ቅርንጫፎች ።</u>

(፩) ዋናው ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በተቋቋመበት ፡ ቦታ ፡ ባልሆነ ፡ በሌላ ፡ ስፍራ ፡ የተቋቋሙ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ወይም ፡ የወኪል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ያሉት ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በመዝገብ ፡ ስለ ፡ መግባት ፡ የተደነገገው ፡ ድንጋጌ ፡ ስለ ፡ እያንዳንዱ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ወይም ፡ ወኪል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በያለበት ፡ ስፍራ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

(፪) በንግድ ፡ መዝገብ ፡ የሚደረገው ፡ አመዘጋገብ ፡ በአጭር ፡ ቃል ፡ አመዘጋገብ ፡ ሁኔታ ፡ ሆኖ ፡ ዋናውን ፡ መዝገብ ፡ መጥቀስ ፡ አለበት ።

(፫) ባጭር ፡ ቃል ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ የሚመዘገበው ፡ በዋና ፡ ለመመዝገብ ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ሐተታዎች፡ ሁሉ ፡ እንዲኖሩበትና ፡ ቅርንጫፍ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት፡ የሚገኝበትን ፡ አድራሻና ፡ የማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፪፻፳፮ ። ከመዝገብ ፡ ስለ ፡ መሰረዝ ።

አንድ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር፡ በፈረሰና፡ ሥራው፡ በቆመ ፡ ጊዜ ፡ አጣሪዎቹ ፡ የንግዱ ፡ ማኅበር ፡ ከንግድ ፡ መዝገብ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ያመለክታሉ ፤ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ መሰረዝ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ኦፊሴል ፡ ጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ በሕግ ፡ የተሰጠው ፡ መብቱ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

## አንቀጽ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ተራ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

ቍ ፡ ፪፻፳፯ ። ትርጓሜ ።

የሽርክና፡ ማኅበር ፡ በዚህ፡ አንቀጽ፡ መንፈስ፡ እንደ፡ ተመለከተው ፡ ተራ ፡ የሽርክና፡ ማኅበር፡ ተብሎ፡ የሚጠራው፡ በዚህ፡ ሕግ፡ በሌላ፡ አንቀጽ፡ የተወሰኑት ፡ የሌሎች ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ልዩ ፡ ጠባዮች ፡ የሌሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፳፰ ። ያልተከፋፈለ ፡ ባለቤትነት ።

(፩) አንድ ፡ ንብረት ፡ የብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሆኖ ፡ ያለፈቃዳቸው ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ ያልተከፋፈለ ፡ ሲሆን ፤ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ አይጸኑበትም።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ ክፍያ ፡ ያላደረጉት ፡ ሰዎች ፡ ያልተከፈለውን ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ ንብረቶች ፡ ለማስተዳደር ፡ በመካከላቸው ፡ አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሊያቋቁሙ ፡ ይችላሉ ።

### ምዕራፍ ፡ ፪ ።

### ስለ ፡ መዋጮ ።

ቍ ፡ ፪፻፳፱ ። ዐይነትና ፡ ልክ ።

(፩) እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ መብት ፡ ወይም፡ ሌሎች ፡ ንብረቶች ፡ ወይም ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ መዋጮ ፡ ማግባት ፡ አለበት ።

(፪) መዋጮዎቹንም ፡ ለማኅበሩ ፡ የመጨረሻ ፡ ሀብት ፡ እንዲሆኑ ፡ ወይም ፡ እን ዲጠቀምባቸው ፡ አድርጎ ፡ ለማግባት ፡ ይቻላል ።

(፫) ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ መዋጮዎቹ ፡ በዐይነታቸውና ፡ ብዛታ ቸው ፡ እኩል ፡ እንዲሆኑና ፡ ለማኅበሩ ፡ ዓላማ ፡ የሚስማሙ ፡ እንዲሆኑ ፡ ያስፈ ልጋል ።

ቍ ፡ ፪፻፹ ። ዋስትና ።

(፩) መዋጮ ፡ የተሰጠው ፡ ንብረት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማኅበረተኛው ፡ ያለበት ፡ ዋስ ትና ፡ ስለ ፡ ሻጭ ፡ ግዴታ ፡ በተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይመራል ።

(፪) መዋጮ ፡ የተሰጠው ፡ ንብረት፡እንዲጠቀምበት ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማኅበረ ተኛው ፡ ያለበት ፡ ዋስትና ፡ ስለ ፡ አከራይ ፡ ግዴታ ፡ በተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይመራል ።

(፫) መዋጮ ፡ የተሰጠው፡ የገንዘብ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ማኅበረተኛው ፡ አላፊ ፡ የሚሆነው ፡ ለገንዘቡ ፡ መብት ፡ መኖር፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ባለዕዳው ፡ የዕዳውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ ችሎታ ፡ ለመ ኖሩ ፡ አይደለም ።

ቍ ፡ ፪፻፹፩ ። ለመድረስ ፡ የሚችል ፡ አደጋ ።

(፩) ለማኅበሩ ፡ የተሰጠው ፡ መዋጮ ፡ ንብረት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለመድረስ ፡ የሚች ሉት ፡ አደጋዎች ፡ ስለ ፡ ሽያጭ ፡ በተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ለማኅ በሩ ፡ ይተላለፋሉ ።

(፪) መዋጮ ፡ የተሰጠው ፡ ንብረት ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲጠቀምበት ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለመድረስ ፡ የሚችሉት ፡ አደጋዎች ፡ የሚደርሰው ፡ ኪሣራ ፡ የማኅበረተ ኛው ፡ ዕድል ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፹፪ ። ወለድ ።

ለማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ አገባለሁ ፡ ያለ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ይህን ፡ ገንዘብ ፡ መክፈል ፡ ከሚገባው ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ገንዘቡ ፡ ለሚሰጠው ፡ ወለድ ፡ ባለ ዕዳ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## የማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ።

ቍ ፡ ፪፻፹፫ ። ውሉን ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ።

(፩) የማኅበሩን ፡ ውል ፡ ለመለወጥ ፡ የሚቻለው ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ በሙሉ ፡ የተስ ማሙበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

BACK



(፪) ነገር ፡ ግን ፡ ከውሉ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ በግልጽ ፡ የተለዩ ፡ የውል ፡ ቃሎችን ፡ በማኅበረተኞች ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ለመለወጥ ፡ ይቻላል ፡ ተብሎ ፡ ለመዋዋል ፡ ይፈቀዳል ።

ቍ ፡ ፪፻፷፬ ። የድምፅ ፡ ብልጫ ።

(፩) ሕጉ ፡ ወይም ፡ ውሉ ፡ አንድ ፡ ውሳኔ ፡ የሚደረገው ፡ በማኅበረተኞች ፡ ድምፅ ፡ ብልጫ ፡ እንዲሆን ፡ የሚያዝ ፡ ሲሆን ፡ ይህ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ የሚቈጠረው ፡ በነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ነው ።

(፪) የድምፅ ፡ ብልጫው ፡ የሚታሰበው ፡ ማኅበረተኞች ፡ እያንዳንዱ ፡ ባገቡት ፡ መዋጮ ፡ መጠን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪፻፷፭ ። ልዩ ፡ ተግባሮች ።

ጠቅላላ ፡ ወኪል ፡ ለመሾም ፡ ወይም ፡ በማኅበሩ ፡ ከተለመደው ፡ ሥራ ፡ ውጭ ፡ ሌላ ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ማኅበረተኞች ፡ በሙሉ ፡ እንዲስማሙበት ፡ ያስፈልጋል ።

ቍ ፡ ፪፻፷፮ ። ሥራ ፡ አስኪያጆችን ፡ ስለ ፡ መሾም ።

ውሉ ፡ ወይም ፡ የማኅበሩ ፡ ውሳኔ ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ ለአንዱ ፡ ወይም ፡ ለብዙዎች ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ የማስተዳደርን ፡ መብት ፡ ካልሰጠ ፡ በቀር ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ መብት ፡ ይኖራቸዋል ።

ቍ ፡ ፪፻፷፯ ። ከአንድ ፡ በላይ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ።

(፩) ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የያንዳንዳቸው ፡ ሥልጣን ፡ ሳይወሰን ፡ ወይም ፡ አንዱ ፡ ስለሌሎቹ ፡ መሥራት ፡ አይቻልም ፡ ሳይባል ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ እንዲሆኑ ፡ ተሾመው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በየበኩላቸው ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሁሉ ፡ ሊፈጽሙ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ሌሎቹ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ እያንዳንዱ ፡ ሥራውን ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

(፫) በዚሁም ፡ መቃወም ፤ የተነሣው ፡ ክርክር ፡ በማኅበረተኞቹ ፡ ድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ይቈረጣል ።

ቍ ፡ ፪፻፷፰ ። በአንድነት ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅነት ።

(፩) የማኅበሩን ፡ ሥራ ፡ ማካሄድ ፡ ብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ እንዲያስኬዱ ፡ የተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሳኔ ፡ ሲደረግ ፡ በነዚህ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ሙሉ ፡ ስምምነት ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ለመሥራት ፡ የሚፈቀድለት ፡ ጕዳይ ፡ አስቸኳይ ፡ የሆነና ፡ ለጊዜው ፡ ሌሎቹ ፡ ሊረዱት ፡ የማይችሉ ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፴፱ ። በማኅበሩ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ፡ መሠረት ፡ የተሾመ ፡ የሥራ፡ አስኪያጅ ።

በውሉ፡ውስጥ፡በሚገኝ፡ልዩ፡ ቃል፤ የማኅበሩን፡ ሥራ፡ እንዲያካሂድ፡ የተሾመ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የማታለል፡ ሥራ፡ ካልሠራ፡ በቀር ፤ ሌሎቹ ፡ ማኅበረተኞች፡ ቢቃወሙም፡ ማንኛዎቹንም፡ የሥራ፡ አስኪያጅነት፡ ሥራዎችን ፡ ለመፈጸም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፵ ። በማኅበሩ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ የተሾመውን ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ስለ ፡ መሻር ።

(፩) የማኅበሩ፡ ሥራ፡ አስኪያጅ፡ ለመሆን፡ በቍ፡ ፪፻፴፱፡ መሠረት፡ ላንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የተሰጠውን ፡ ሥልጣን ፡ ያለበቂ ፡ ምክንያት ፡ ሌሎች ፡ ማኅበረተኞች ፡ ሊሽሩ ፡ ወይም ፡ ሊቀንሱ ፡ አይችሉም ።

(፪) በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሲኖር ፡ በማኅበሩ ፡ ውል ፡ ሌላ ፡ ውሳኔ ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ማንኛውም ፡ ማኅበረተኛ ፡ ለመሻር ፡ ይቻላል ።

(፫) በተለይም ፡ እንደ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የሚቈጠረው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ የሆነ፡ ማኅበረተኛ ፡ በተግባሩ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ ጉድለት ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ወይም፡ ሥራውን ፡ በመልካም ፡ ለመምራት ፡ ችሎታ ፡ ያጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፵፩ ። የሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ።

(፩) የሥራ፡ አስኪያጆች፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ስለ ፡ ውክልና ፡ በተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይመራሉ ።

(፪) የሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በውል ፡ ያሉባቸውን ፡ ግዴታዎች ፡ ያልፈጸሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለሌሎቹ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ባንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ አላፊ ፡ ናቸው ።

(፫) ያለጥፋቱ ፡ አላፊነት ፡ የደረሰበት፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ አላፊነትን ፡ በጥፋቱ ፡ ያደረሰበትን ፡ ሰው ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፪፻፵፪ ። ሥልጣን ፡ ያልተሰጠው ፡ ውክልና ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ላንድ ፡ ማኅበር፡ የሥራ ፡ አስኪያጅነት ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ የተሰጠውን ፡ ሥልጣን ፡ የተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሥልጣን ፡ ሳይኖራቸው ፡ በውክልና ፡ የሚያስተዳድሩ ፡ ሰዎችን ፡ የሚመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆኑበታል ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

የማኅበረተኞች ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ።

ቍ ፡ ፪፻፵፫ ። የማኅበረተኞች ፡ ግዴታዎች ።

(፩) እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የራሱን ፡ ጉዳዮች ፡ እንደሚጠብቅ ፡ ዐይነት ፡ እንደ ዚሁ ፡ ለማኅበሩ ፡ ጉዳዮች ፡ በጥንቃቄና ፡ በትጋት ፡ መሥራት ፡ አለበት ።

(፪) በሌሎች ፡ ጉዳዮች ፡ ለማኅበሩ ፡ ያስጣቸውን ፡ ጥቅሞች ፡ ማቻቻያ ፡ ለማድረግ ፡ ሳይችል ፡ በራሱ ፡ ጥፋት ፡ ለሚያደርስባቸው ፡ ጉዳት ፡ ለሌሎቹ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ኀላፊ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፴፩ ። ከሌላ ፡ ሥራ ፡ የመታገድ ፡ ግዴታ ።

ማንኛውም ፡ ማኅበረተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ለግል ፡ ጥቅሙ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ለማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ ግብ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርሱ ፡ ሥራዎችን ፡ ለመሥራት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪፻፴፪ ። ‹የማኅበሩ ፡ ሀብቶች ፡ ስለ ፡ መገልገል ።

(፩) ለማኅበሩ ፡ የተላለፉ፡ ወይም፡ ማኅበሩ ፡ ያገኛቸው ፡ ንብረቶች ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ መብቶችና ፡ ሌሎች ፡ መብቶች ፡ በማኅበሩ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ የማኅበረተኞች ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ናቸው ።

(፪) እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኞች ፡ በልማድ ፡ ለተመደበላቸው ፡ ሥራ ፡ ከሆነ ፡ በማኅበሩ ፡ ሀብቶች ፡ ሊገለገሉባቸው ፡ ይችላሉ ።

(፫) የማኅበሩን ፡ ጥቅም ፡ በሚጎዳ ፡ አኳኋን ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ማኅበረተኞች ፡ እንደ ፡ መብታቸው ፡ እንዳይሠሩበት ፡ በሚያግድ ፡ ዐይነት ፡ ማን ፡ በነዚህ ፡ ሀብቶች ፡ ሊገለገልባቸው ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪፻፴፫ ። አስፈላጊ ፡ ወጪ ።

እያንዳንዱ፡ ማኅበረተኛ፡ የማኅበሩን፡ ንብረት ፡ ለመጠበቅ ፡ ሌሎች ፡ ማኅበረተኞች ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ወጪ ፡ እንዲያደርጉ ፡ ማስገደድ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፴፬ ። ብድር ፡ ወይም ፡ ዕዳ ።

(፩) አንድ፡ ማኅበረተኛ፡ ለማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ያበደረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ካበደረበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ስለዚህ ፡ ገንዘብ ፡ ወለድ ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ከማኅበሩ ፡ ሣጥን ፡ ገንዘብ ፡ የተበደረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ ዕዳ ፡ ከተበደረበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ወለድ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፫) አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝም ፡ ከደንበኛ ፡ ወለድ ፡ በላይ ፡ ለማኅበሩ ፡ ኪሣራም ፡ ይከፍላል ።

ቍ ፡ ፪፻፴፭ ። መዝገቦችንና ፡ ማስረጃዎችን ፡ የመመርመር ፡ መብት ።

በማኅበሩ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ቢኖርም ፡ እንኳን ፡ ማንኛውም ፡ ማኅበረተኛ ፡ ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ጥያቄ ፡ ማቅረብ ፡ የማኅበሩን ፡ መዝገቦችና ፡ ማስረጃዎች ፡ መመልከትና ፡ እንዲሁም ፡ በሒሳቦቹ ፡ አኳኋን ፡ አጭር ፡ ዝርዝር ፡ ማድረግ ፡ ይችላል ።

BACK



ቍ ፡ ፪፻፵፱ ። የሥራ ፡ መግለጫ ።

(፩) ማኅበሩ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ የሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ የኖረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ማኅበረ ተኞቹ ፡ በየዓመቱ ፡ መጨረሻ ፡ የሥራ ፡ አካሄዱን ፡ የሚያስረዳ ፡ የሥራ ፡ መግ ለጫ ፡ እንዲቀርብ ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላሉ ።

(፪) የሥራዎች ፡ መግለጫ ፡ ከዚህ ፡ በበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይቀርባል ፡ ተብሎ ፡ ለመዋዋል ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፪፻፶ ። ከሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ጋራ ፡ መሻረክ ።

(፩) ማንኛውም፡ ማኅበረተኛ፡ ሌሎች ፡ ማኅበረተኞች ፡ ካልፈቀዱ ፡ በቀር ፡ እማኅ በሩ ፡ ውስጥ ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ማስገባት ፡ አይችልም ።

(፪) አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ እማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ድርሻ ፡ ለሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ እንዲጠቀምበት ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ ያስተላለፈ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ ሦስተኛው ፡ ወገን ፡ ማኅበረተኛ ፡ አይሆንም ። ይልቁንም ፡ በቍ ፡ ፪፻፵፰ ፡ የተመለከተውን ፡ መብት ፡ አያገኝም ።

ቍ ፡ ፪፻፶፩ ። የትርፍ ፡ አከፋፈል ።

(፩) ማኅበረተኞቹ ፡ ለማኅበሩ ፡ የሚደርሰውን ፡ ማናቸውንም ፡ ትርፍ ፡ በመካከላ ቸው ፡ መካፈል ፡ አለባቸው ።

(፪) ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው፡ የሥራው ፡ አመራር ፡ መግለጫ ፡ ከጸደቀ ፡ በኋላ ፡ የተገኘው ፡ ትርፍ ፡ ወዲያ ውኑ ፡ እንዲከፈል ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፶፪ ። የትርፍና ፡ የኪሣራ ፡ የአከፋፈሉ ፡ መሠረት ።

(፩) ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ለማኅበሩ ፡ ያገባው ፡ የመዋጮ ፡ ዐይነትና ፡ ዋጋው ፡ ማናቸውም ፡ ቢሆን ፡ ከት ርፎችም ፡ ከኪሣራም ፡ ትክክል ፡ ድርሻ ፡ አለው ።

(፪) ውሉ ፡ የሚመለከተው ፡ የትርፍ ፡ ድርሻ ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ የኪሣራ ፡ ድርሻ ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ የተመለከተው ፡ ውሳኔ ፡ በትርፉም ፡ ሆነ ፡ በኪ ሣራው ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪፻፶፫ ። በሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ስለሚደረግ ፡ አከፋፈል ።

(፩) ማኅበረተኞቹ ፡ ለድርሻቸው ፡ አከፋፈል ፡ በማለት ፡ ከመካከላቸው ፡ አንዱን ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የመረጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ለርትዕ ፡ ተቃራኒ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ካልታየ ፡ በቀር፡ ሊቃወሙት ፡ አይቻልም ።

(፪) ተጎዳሁ፡ የሚለው፡ ወገን፡ ውሳኔውን፡ ካወቀበት፡ ጊዜ፡ ጀምሮ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡

የበለጠ ፡ ጊዜ ፡ አልፎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በበኩሉ ፡ የዚሁን ፡ አፈጻጸም ፡ መጀመሪያ ፡ ያነሣሣው ፡ ራሱ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ማናቸውንም ፡ አቤቱታ ፡ በዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪፻፶፱ ። ሥራውን ፡ መዋጮ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

በቍጥር ፡ ፪፻፶፰ ፡ የተደነገገ ፡ ቢሆንም ፡ በሥራ ፡ ችሎታው ፡ ብቻ ፡ ሸሪክ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፤ የትርፍ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆን ፤ ኪሣራ ፡ ግን ፡ እንዳይነካው ፡ አድርጎ ፡ ውል ፡ ለመዋዋል ፡ የተፈቀደ ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

ማኅበሩ ፡ ከሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጋራ ፡ ስላለው ፡ ግንኙነት ።

ቍ ፡ ፪፻፷ ። ከማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ።

(፩) ከማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ መብታቸውን ፡ ከማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ሊጠይቁ ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንዲሁም ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ለማኅበሩ ፡ በአንድነት ፡ ላይ ከፋፋል ፡ አላፊ ፡ ከሆኑት ፡ ማኅበረተኞች ፡ የግል ፡ ከሆነው ፡ ንብረታቸው ፡ ላይ፡ መብታቸውን ፡ ሊጠይቁ ፡ ይችላሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፤ ከግል ፡ ንብረቱ ፡ እንዲከፍል ፡ የተከሰሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንደ ፡ ተራ ፡ ዋስ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂውን ፡ አስቀድሞ ፡ ከማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ፈልግ ፡ ብሎ ፡ ለመመለስ ፡ ይችላል ።

(፫) አንዱን ፡ ማኅበረተኛ ፡ ወይም ፡ ከነሱ ፡ አንዳንዶቹን ፡ ማኅበረተኞች ፡ ከአንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ ባለዕዳነት፡ ውጪ ፡ የሚያደርግ ፡ ስምምነት፡ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ የሚያውቁት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ባቸው ፡ አይችልም ። ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፤ በማኅበሩ ፡ ስም፡ ሆነው ፡ ይሠሩ ፡ የነበሩ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፤ በአንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ ኀላፊነት ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፪፻፷፩ ። የማኅበረተኞቹ ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ።

(፩) ከማኅበረተኞች ፡ ላይ ፡ በግል ፡ ገንዘብ ፡ የሚፈልጉት፡ ሰዎች፡ ለባለዕዳቸው፡ የሚደርሱትን ፡ ትርፎች ፡ ማሲያዝ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ማኅበሩን ፡ ለማፍረስ ፡ ሒሳብ ፡ በሚያጣራበት ፡ ጊዜ ፡ ለባለዕዳቸው ፡ ለሚደርሰው ፡ ድርሻ ፡ ማረጋገጫ ፡ እንዲሆናቸው ፡ ማናቸውም ፡ የመብት ፡ አጠባበቅ ፡ ጥንቃቄ ፡ እንዲደረግላቸው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

(፫) የባለዕዳቸው ፡ የግል ፡ ንብረት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ለሚፈልጉት ፡ ንብረት ፤ የማይበቃ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለዕዳቸው ፡ በሚደርሰው ፡ ድርሻ ፡ መጠን ፡ ጥያቄ፡ከአቀረቡ፡በሦስት፡ወር፡ውስጥ፡ማኅበሩ፡እንዲከፈለው፡ለመጠየቅ፡ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፪፻፷፯ ። ማቻቻል ።

የማኅበሩ ፡ ባለዕዳ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ከሌላ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የገንዘብ፡ መብት ፡ እንዲቻቻልለት ፡ መቃወሚያ ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

## ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ መፍረስና ፡ የሒሳብ ፡ መጣራት ።

ቍ ፡ ፪፻፷፰ ። ጊዜ ፡ ያልተወሰነለት ፡ ማኅበር ።

(፩) አንድ ፡ ማኅበር ፡ የተቋቋመው ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከማኅበረተኞቹ፡ በአንዱ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ድረስ ፡ ወይም ፡ በውሉታ ፡ ውስጥ ፡ የማፍረስ ፡ መብት፡ ተጠቅሶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ወገን ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ አስቀድሞ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሰጥቶ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ይህን ፡ ማመልከቻ ፡ በማይገባ ፡ ጊዜ ፡ ሳይሆን ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ መሠረት ፡ ማቅረብ ፡ ያስፈልጋል ።

(፫) ማመልከቻ ፡ የቀረበው ፡ በማይገባ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ ሁኔታው ፡ ያልተወሰነ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነና ፡ ለማኅበሩ ፡ ማፍረሻ ፡ ጊዜ ፡ ማግኘት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሲታይ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፷፱ ። ያንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ መውጣት ።

ማኅበረተኞቹ ፡ ከመካከላቸው፡ አንዱ፡ በቍ፡ ፪፻፷፰ ፡ መሠረት ፡ ማኅበሩን ፡ ለማፍረስ ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ለማቆም ፡ የሚችሉት ፡ ጥያቄ ፡ ላቀረበው ፡ ማኅበረተኛ ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ድርሻውን ፡ ከፍለው ፡ ነው ። እንደዚህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ማኅበሩ ፡ በሌሎች ፡ ማኅበረተኞች ፡ መካከል ፡ ሥራውን ፡ ይቀጥላል ።

ቍ ፡ ፪፻፸ ። ሞት ፤ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ ወይም ፡ መክሠር ።

(፩) ማኅበሩ ፡ የሚፈርሰው ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ አንዱ ፡ ሲሞት ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ አስተያየት ፡ ማኅበረተኛ ፡ ለመሆን ፡ ችሎታ ፡ ሲያጣ ፡ ነው ።

(፪) እንደዚሁም ፡ የአንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ መክሠር ፡ በፍርድ ፡ የተገለጸ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ከዚሁ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ባለዕዳው ፡ በቍ ፡ ፪፻፷፮ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፫ ፡ መሠረት ፡ ከማኅበሩ ፡ ያለውን ፡ ድርሻ ፡ እንዲጣራ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፫) ነገር ፡ ግን ፡ የሚቀሩት ፡ ማኅበረተኞች ፡ ወይም ፡ ከሟቹ ፡ ወራሾች ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ ካጣው ፡ ማኅበረተኛ ፡ እንደራሴዎች ፡ ጋራ ፡ ሥራቸው ፡ ይቀጥላል ፡ ብለው ፡ ለመስማማት ፡ ይችላሉ ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፷፩ ። አንዱን ፡ ማኅበረተኛ ፡ ስለ ፡ ማስወጣት ።</u>

ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሲኖር ፡ አንዱን ፡ ማኅበረተኛ ፡ ከማኅበሩ ፡ እንዲወጣ ፡ ለመፍረድ ፡ ይችላል ። አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ማኅበሩ ፡ በቀሩት ፡ ማኅበረተኞች ፡ መካከል ፡ ይቀጥላል ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፷፪ ። የወጣውን ፡ ማኅበረተኛ ፡ መብቶች ፡ ስለ ፡ መክፈል ።</u>

(፩) አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ከማኅበሩ ፡ የወጣ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የቀሩት ፡ ማኅበረተኞች ፡ የማኅበሩን ፡ ሥራ ፡ የቀጠሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ከማኅበሩ ፡ በወጣበት ፡ ቀን ፡ መብቶቹ ፡ ያላቸውን ፡ ዋጋ ፡ በማስብ ፡ መብቶቹን ፡ በገንዘብ ፡ ይከፍሉታል ።

(፪) አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ማኅበሩን ፡ የተወ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ለነበሩትና ፡ በመሠራት ፡ ላይ ፡ ላሉት ፡ ጉዳዮች ፡ ላስገኙት ፡ ትርፎችና ፡ ኪሣራዎች ፡ ተካፋይ ፡ ነው ።

(፫) እንደዚሁም ፡ ማኅበሩን ፡ ከመተው ፡ በፊት ፡ ለሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ማኅበሩ ፡ ለገባው ፡ ግዴታዎች ፡ አላፊ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፷፫ ። ማኅበሩ ፡ ከፈረሰ ፡ በኋላ ፡ የሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ሥልጣን ።</u>

(፩) ማኅበሩ ፡ ሲፈርስ ፡ የሥራ ፡ አስኪያጆቹ ፡ የመጨረሻውን ፡ ሒሳብ ፡ ለማጣራት ፡ አስፈላጊው ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ የነበራቸውን ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ይቈያሉ ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሁኔታው ፡ የሚያስገድደውን ፡ ማኅበሩን ፡ የማፍረስ ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ ያስተዳደር ፡ ተግባር ፡ ብቻ ፡ ይፈጽማሉ ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፷፬ ። የሒሳብ ፡ አጣሪዎች ፡ መሾም ።</u>

(፩) ማኅበሩ ፡ ከፈረሰ ፡ በኋላ ፡ የመጨረሻ ፡ ሒሳብ ፡ የሚጣራው ፡ በማኅበሩ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በማኅበረተኞቹ ፡ ሙሉ ፡ ስምምነት ፡ በተሾመ ፡ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙዎች ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪዎች ፡ ነው ።

(፪) ማኅበረተኞቹ ፡ የማይስማሙ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪዎችን ፡ ይሾማል ።

<u>ቍ ፡ ፪፻፷፭ ። የሒሳብ ፡ አጣሪዎች ፡ ግዴታና ፡ አላፊነት ።</u>

(፩) በውል ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ሌላ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪዎቹ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ያሏቸው ፡ ግዴታዎችና ፡ አላፊነት ፡ አለባቸው ።

(፪) ሒሳብ፡ አጣሪዎቹ፡ ማኅበረተኞች፡ በሙሉ ፡ ተስማምተውበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ በአንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሻሩ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፮ ። የንብረት ፡ መዝገብ ።**

(፩) ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ለሒሳብ ፡ አጣሪዎቹ ፡ የማኅበሩን ፡ ንብረትና ፡ የማኅበሩን ፡ አስረጂ ፡ ጽሑፎች ፡ ሁሉ ፡ ማስረከብና ፡ የመጨረሻ ፡ የሥራ ፡ መግለጫ ፡ እስከ ፡ ሚያረካክቡበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ የሠሩትን ፡ ማስረዳት ፡ አለባቸው ።

(፪) ይህን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪዎቹ ፡ ማኅበሩ ፡ ያለውንና ፡ ያለበትን ፡ ሒሳብ ፡ ዝርዝር ፡ ያዘጋጃሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፯ ። የሒሳብ ፡ አጣሪዎች ፡ ሥልጣን ።**

(፩) ሒሳብ ፡ አጣሪዎቹ ፡ የማኅበሩ ፡ መጨረሻ ፡ ሒሳብ ፡ እንዲጣራ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ተግባሮች ፡ ሁሉ ፡ ይፈጽማሉ ።

(፪) በተለይም ፡ የማኅበሩን ፡ ንብረት ፡ መሸጥ ፤ ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ ሆነው ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ መቅረብ ፡ መገላገልና ፡ ነገርን ፡ በዘመድ ፡ ዳኛ ፡ ለመጨረስ ፡ ሊዋዋሉ ፡ ይችላሉ ።

(፫) ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ ሆነው ፡ አዲስ ፡ ሥራ ፡ ለመጀመር ፡ አይችሉም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ተጀምሮ ፡ የነበረውን ፡ ሥራ ፡ ለመጨረስ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፰ ። ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ስለ ፡ መክፈል ።**

(፩) አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝም ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪዎቹ ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ ሌላ ፡ ገንዘብ ፡ ተቀብለው ፡ ከማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ለሚፈልጉት ፡ ሰዎች ፡ የሚደርሳቸውን ፡ ይከፍላሉ ።

(፪) እንዲሁም፡ ለማኅበረተኞች፡ ከማኅበሩ፡ ላይ፡ የሚፈልጉትን፡ ከፍለው፡ ማኅበሩ፡ ሊጠቀምበት፡ ብቻ ፡ ገቢ ፡ ያደረጉትን ፡ የንብረት፡ መዋጮ ፡ ይመልሱላቸዋል ።

**ቍ ፡ ፪፻፷፱ ። መዋጮውን ፡ ስለ ፡ መመለስ ።**

(፩) ንብረትን ፡ መዋጮ ፡ አድርጎ ፡ ገቢ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ ማኅበሩ ፡ ሲፈርስ ፡ በመዋጮ ፡ ያገባውን ፡ ዐይነት ፡ መልሶ ፡ እንዲወስድ ፡ መጠየቅ ፡ አይችልም ።

(፪) መዋጮውን ፡ ሲያገባ ፡ የተገመተውን ፡ ዋጋ ፡ ለመቀበል ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) ዋጋው ፡ ግን ፡ ያልተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መዋጮው ፡ ገቢ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ያወጣ ፡ በነበረው ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ይከፈላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፸ ። የትርፍና ፡ የኪሣራ ፡ አከፋፈል ።**

(፩) የማኅበሩ ፡ ዕዳዎች ፡ ከተከፈሉና ፡ እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ያገቡት ፡ መዋጮ ፡ ከተከፈለ ፡ በኋላ ፡ ትርፍ ፡ ቢኖር ፡ ይህ ፡ ትርፍ ፡ በማኅበረተኞች ፡

BACK



መካከል ፡ ይከፋፈላል ።

(፪) ዕዳዎቹ ፡ ወጪዎችና ፡ ብድሮች ፡ ከተከፈሉ ፡ በኋላ ፡ የማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ መዋጮውን ፡ ለመክፈል ፡ የማይበቃ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ኪሣራው ፡ በማኅበረተኞች ፡ መካከል ፡ ይከፋፈላል ።

(፫) በውሉ ፡ ሌላ ፡ ያከፋፈል ፡ መጠን ፡ ካልተወሰነ ፡ በቀር ፡ ትርፍና ፡ ኪሣራው ፡ በማኅበረተኞቹ ፡ መካከል ፡ እኩል ፡ ይከፋፈላል ።

## አንቀጽ ፡ ፫ ።

## የእሽሙር ፡ ማኅበር ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፩ ። ትርጓሜ ።**

የእሽሙር ፡ ማኅበር፡ ማለት ፤ ማኅበረተኞቹ፡ ስለ ፡ ሽርክና፡ ማኅበሮች፡ ሕግ ፡ የወጣው፡ ጠቅላላ ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ የሚመራ ፡ ሆኖ ፡ የእሽሙር ፡ ማኅበር፡ ማኅበረተኞች ፡ እንደ ፡ ፈቃዳቸው ፡ የውላቸውን ፡ ሁኔታዎች ፡ ወስነው ፡ ያቋቋሙት ፡ ማኅበር ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፪ ። የማኅበሩ ፡ ስውር ፡ መሆን ።**

(፩) የእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ መኖሩ ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ የታወቀ ፡ አይደለም ።

(፪) የእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ በጽሑፍ ፡ መረጋገጥና ፡ ለሌሎቹ ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ የተደነገጉት ፡ የማስታወቂያና ፡ የማስመዝገብ ፡ ሥርዐቶች ፡ አይፈጸሙበትም ።

(፫) የእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ በሕግ ፡ የተሰጠ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የለውም ።

(፬) አንድ ፡ የእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ መቋቋሙ ፡ ለሌሎች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ የታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ስላለው ፡ግንኙነት ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፫ ። የመዋጮዎች ፡ ሁኔታ ።**

ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ገቢ ፡ ሳደረገው ፡ መዋጮ ፡ ባለሀብትነቱን ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ይቈያል ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፬ ። የማኅበሩ ፡ ድርሻዎች ።**

(፩) ማኅበሩ ፡ የሚተላለፉ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶችን ፡ ለማውጣት ፡ አይፈቀድለትም።

(፪) ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የማኅበሩን ፡ ድርሻዎች ፡ ለማስተላለፍ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ሁሉ ፡ እንዲስማሙበት ፡ ያስፈልጋል ።

**ቍ ፡ ፪፻፸፭ ። የሥራ ፡ አመራር ።**

(፩) የእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ ማኅበረተኞች ፡ በሆኑ ፡ ወይም ፡ ባልሆኑት ፡ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙዎች ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ይተዳደራል ።

(፪) ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ያልተሾመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ሁሉ ፡ የሥራ፡ አስኪያጅነት ፡ መብት ፡ አላቸው ።

(፫) ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ የሆነውን ፡ ማኅበረተኛ ፡ ያለበቂ ፡ ምክንያት ፡ ለመሻር ፡ አይቻልም ።

(፬) የሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ሥልጣን፡ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ፡ ጽሑፍ ፡ ይወሰናል ። ይህን ፡ ሥልጣን ፡ የሚወስነው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ለሌሎች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

ቁ ፡ ፪፻፸፯ ። ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ያልሆኑ ፡ ማኅበረተኞች ።

(፩) ለሌሎች ፡ ሦስተኛ፡ ወገኖች ፡ የሚታወቀው፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ብቻ ፡ ነው ። እርሱም ፡ ለማኅበሩ ፡ ዕዳዎች ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ አላፊና ፡ ተጠያቂ ፡ ነው ።

(፪) ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ያልሆኑ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ለማኅበሩ ፡ ዕዳዎች ፡ ተካፋይ ፡ የሚሆኑት ፡ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ በተወሰነው ፡ መጠን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፫) ማኅበረተኞቹ ፡ የሥራ ፡ አስኪያጁን ፡ ሥራ ፡ ለመቆጣጠር ፡ ይችላሉ ።

(፬) የእሽሙር ፡ ንግድ ፡ ማኅበር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ያልሆኑ ፡ ማኅበረተኞች ፡ በሥራ፡ ማካሄዱ ፡ ተካፋይ ፡ የሆኑ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እርስ ፡ በርሳቸውና ፡ ከሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ ኀላፊዎች ፡ ናቸው ።

(፭) ማንኛውም ፡ ማኅበረተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ከሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቁ ፡ ፪፻፸፰ ። የማስረዳት ፡ ግዴታ ።

ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ለማኅበረተኞቹ ፡ ሥራውን ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ። ከዚህም ፡ ግዴታ ፡ የሚያድን ፡ ሌላ ፡ ማናቸውም ፡ የውል ፡ ቃል ፡ የማይጸናና ፡ ውጤት ፡ የሌለው ፡ ነው ።

ቁ ፡ ፪፻፸፱ ። የማፍረሻ ፡ ምክንያቶች ።

(፩) የእሽሙር ፡ ማኅበር ፡ መፍረሻ ፡ ምክንያቶች ፡ እንደሚከተሉት ፡ ናቸው ።

(ሀ) ለማኅበሩ ፡ ሥራ፡ በመመሥረቻ ፡ ጽሑፍ፡ ውስጥ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ደርሶ፡ ይህንኑ፡ ጊዜ፡ የሚያራዝም፡ የውል፡ ቃል፡ ከሌለ፡በቀር ፡ የዚህ፡ ጊዜ ፡ መድረሻ ፤

(ለ) የታሰበው ፡ ሥራ ፡ መፈጸሙ ፤

(ሐ) የንብረቱ ፡ መጥፋት ፡ ወይም፡ ታስቦ ፡ የነበረው፡ የማኅበሩ ፡ ጉዳይ፡አለመቻል፤

(መ) ማኅበረተኞች ፡ በአንድ ፡ ድምፅ ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ እንዲፈርስ ፡ የተስማሙበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሠ) ለማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ ማለቂያው ፡ ጊዜ ፡ ያልተወሰነ ፡ ሲሆን ፡ ከማኅበረተኞች ፡ አንዱ ፡ እንዲፈርስ ፡ የጠየቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ረ) በቂ ፡ ምክንያቶች ፡ ኖረው ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ አንዱ ፡ ባቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ የተወሰነ ፡ ሲሆን ፤

(ሰ) ድርሻዎች ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ እጅ ፡ የገቡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሸ) ሌላ ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ አንዱ ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የከሠረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ችሎታ ፡ ያጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ቀ) የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚፈቅድለት ፡ ከሆነ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ በሰጠው ፡ ውሳኔ ፤ ማኅበሩ ፡ ይፈርሳል ።

(፪) በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳን ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፪፻፷፱ ። ማኅበረተኛን ፡ ከማኅበሩ ፡ ስለ ፡ ማስወጣት ።

(፩) ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ የቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ በአንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ከሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሌሎቹ ፡ ማኅበረተኞች ፡ አመልካችነት ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ በመወሰን ፡ ፈንታ ፡ ጥፋተኛ ፡ የሆነው ፡ ማኅበረተኛ ፡ ከማኅበሩ ፡ እንዲወጣ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ የማስወጣቱን ፡ ምክንያት ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ።

(፫) ከማኅበሩ ፡ የወጣ ፡ ማኅበረተኛ ፡ እርሱ ፡ እንዲወጣ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ የነበረውን ፡ ድርሻ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

## አንቀጽ ፡ ፬ ።

## የኅብረት ፡ ሽርክና ፡ ማኅበር ።

ቍ ፡ ፪፻፸ ። የኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ጠባይ ።

(፩) የኅበረት፡ የሽርክና፡ ማኅበር፡ የሚባለው ፡ ማኅበረተኞች፡ እያንዳንዳቸው፡ ባንድነትና፡ ሳይከፋፈል፡ እርስ፡ በርሳቸውና ፡ ለማኅበሩ ፡ ግዴታዎች ፡ አላፊዎች ፡ የሚሆኑበት ፡ ማኅበር ፡ ነው ። ማናቸውም ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

(፪) ማኅበሩ ፡ የተመሠረተው ፡ ለንግድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ማኅበረተኞቹ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ነጋዴዎች ፡ ይቈጠራሉ ።

(፫) ማኅበሩ ፡ የማኅበር ፡ ስም ፡ ይኖረዋል ።

BACK



(፬) ከማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ የእያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ድርሻ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፹፪ ፡ እንደተመለከተው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሊሰጥ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ሊተላለፍ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፪፻፹፭ ። የማኅበሩ ፡ ስም ።

(፩) የማኅበሩ ፡ ስም ፡ የማኅበረተኞቹ ፡ ስም ፡ ሁሉ ፡ ይኖርበታል ። ነገር፡ግን ፡ ቢያንስ ፡ የሁለት ፡ ማኅበረተኞች ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ተጽፎበት ፡ ቀጥሎም ፡ «የኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር» ፡ ተብሎ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ። የማኅበሩ ፡ ስም ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ ስም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ስም ፡ ሊኖርበት ፡ አይችልም ።

(፪) ከማኅበረተኞቹ ፡ መካከል ፡ አንዱ፡ ከማኅበሩ ፡ የወጣ ፡ እንደሆነ ፤ የማኅበሩ ፡ ስም ፡ መለወጥ ፡ አለበት ።

(፫) አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ ዐውቆ ፡ ስሙ ፡ በማኅበሩ፡ስም፡ውስጥ፡ ሲጻፍ ፡ ዝም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ለማኅበሩ ፡ ግዴታዎች ፡ ሁሉ ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፪፻፹፮ ። የድርሻዎች ፡ ሁኔታ ።

(፩) ማኅበረተኞች ፡ ሁሉ ፡ ፈቃደኛ ፡ ከሆኑ ፤ አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ድርሻውን ፡ ለሌላ ፡ ለመተው ፡ ወይም ፡ ለማስተላለፍ ፡ ይችላል ።

(፪) የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ይህን ፡ ስምምነት ፡ በድምፅ ፡ ብልጫም ፡ ለማድረግ ፡ መቻሉን ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ።

(፫) ማኅበረተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ያለውን ፡ ድርሻ ፡ ከማስተላለፉ ፡ በፊት፡ስለ፡ማኅበሩ ፡ ዕዳዎች ፡ የነበሩትን ፡ ግዴታዎች ፡ ከማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ሰዎች፡ ካልፈቀዱ ፡ በቀር ፡ አላፊነትን ፡ ለማስወረድ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፪፻፹፯ ። ለሦስተኛ ፡ ወገን ፡ በድርሻ ፡ ላይ ፡ የጥቅም ፡ መብቶች፡ ስለ፡ መስጠት ።

(፩) አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የሌሎቹን ፡ ማኅበረተኞች ፡ ፈቃድ ፡ ሳይጠይቅ ፡ የድርሻውን ፡ መብቶችና ፡ ጥቅሞች ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ እንዲጠቀምባቸው ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) ይህ ፡ ስምምነት ፡ ግን ፡ ማኅበሩን ፡ ግዴታ ፡ ውስጥ ፡ አያገባውም ።

(፫) ስምምነቱም ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የማኅበረተኛነት ፡ መብት ፡ አይሰጠውም ።

ቍ ፡ ፪፻፹፰ ። የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ።

የማኅበሩን ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ሊያዘጋጁት ፡ ይችላሉ ። ስለ ፡ ሆነም ፡ በጽሑፉ ፡ ቀጥለው ፡ የተዘረዘሩት ፡ እንዲኖሩ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

BACK



(፩) ያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ስም ፤ አድራሻና ፡ ዜግነቱ ።
(፪) የማኅበሩ ፡ ስም ።
(፫) የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤትና ፡ እንዳሉም ፡ የማኅበሩ ፡ ቅርንጫፎች ።
(፬) ማኅበሩ ፡ የተመሠረተበት ፡ ጕዳይ ፡ (ዓላማ) ።
(፭) እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ለማኅበሩ ፡ ያደረገው ፡ መዋጮ ፡ የዚሁም ፡ ዋጋውና ፡ አገማመቱ ።
(፮) የሞያ ፡ ሥራቸውን ፡ ብቻ ፡ መዋጮ ፡ ያደረጉት ፡ ማኅበረተኞች፡ የሚደርሱባቸው ፡ ግዴታዎች ።
(፯) የያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የትርፍ ፡ ወይም ፡ የኪሣራ ፡ ተካፋይነትና ፡ ለትርፍ፡ የተወሰነ ፡ የአከፋፈሉ ፡ ሁኔታ ።
(፰) የማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆችና ፡ ወኪሎች ፤
(፱) ለማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።

ቍ ፡ ፪፻፹፫ ። ማስታወቂያ ፡ ስለ ፡ ማውጣትና ፡ ስለ ፡ መመዝገብ ።

(፩) በቍጥር ፡ ፪፻፲፱ ፡ ንኡስ ፡ ቍ (፪) (ሀ) እና ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፳፯ ፡ መሠረት ፡ የሚታተመው ፡ ማስታወቂያ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፹፪ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) እስከ ፡ (፯) ንኡስ፡ቍ፡ (፰) እና፡ (፱) ውስጥ፡ የተዘረዘሩት፡ ሐተታዎች፡ ሊኖሩበት፡ ይገባል።
(፪) በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ለመመዝገቢያ ፡ በሚቀርበውም ፡ ማመልከቻ ፡ ውስጥ ፡ ይኸው ፡ ዝርዝሮ ፡ ሐተታ፡ እንዲኖር ፡ ያስፈልጋል ፤ ማመልከቻውን ፡ የሚፈርመው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ወይም ፡ የእሱ ፡ ወኪል ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፹፬ ። የማኅበሩ ፡ ግዴታዎች ።

ማኅበሩ ፡ መብት ፡ ማግኘትና ፡ የግዴታ ፡ ውል ፡ መግባት ፤ በማኅበሩ ፡ ስም ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ መክሰስ ፡ ወይም ፡ መከሰስ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፪፻፹፭ ። የማኅበሩ ፡ አስተዳደር ።

(፩) ማኅበሩ ፡ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙዎች ፡ ማኅበረተኞች ፡ በሆኑ ፡ ወይም ፡ ባልሆኑ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ይተዳደራል ።
(፪) ሥራ፡ አስኪያጅ ፡ ያልተሾመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ መብት ፡ የማኅበረተኞቹ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፪፻፹፮ ። የሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ብዛት ።

(፩) ማኅበረተኞቹ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡ የሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ የያንዳንዳቸው ፡ ሥራ ፡ ሳይወሰን ፡ የተሾሙ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ከሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ አንዱ ፡ ለብቻ ፡ ሆኖ ፡ መሥራት ፡ መብት ፡ የለውም ፡ የሚል ፡ ስምምነት ፡ የሌለ ፡ እንደ፡ሆነ ፤ በየበኩላቸው፡ የማ

ስተዳደርን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ለመፈጸም ፡ ይችላሉ ።

(፪) የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ከሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ የየአንዳንዳቸውን ፡ ሥልጣን ፡ የሚወስን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ካለበት ፡ የውሉ ፡ ቃሎች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን፡ መቃወሚያ ፡ የሚሆነው ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ የተመዘገበ ፡ እንደ ፡ ሆን ፤ ወይም ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ አኳኋኑን ፡ የሚያውቁ ፡ መሆናቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ነው ።

(፫) የሥራ፡ አስኪያጆች፡ ብዙዎች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ከመካከላቸው ፡ አንዱ፡ ሌሎቹ ፡ እንሠራለን ፡ ብለው ፡ ያሰቡትን ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ። እንዲህም ፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ በሥራ፡ አስኪያጆች፡ በሁሉም፡ ድምፅ፡ ብልጫ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

## ቍ ፡ ፪፻፹፱ ። የሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ግዴታ ፡ ወሰን ።

(፩) ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ ሆነው ፡ ማናቸውንም ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ ሥራ፡ ለመፈጸምና፡ ማኅበሩ ፡ የሚገደድበትን ፡ ለመፈጸም ፡ መብት ፡ አላቸው ።

(፪) ሥልጣናቸውን፡ የሚወስኑት ፡ የውል፡ ቃሎች ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን፡ መቃወሚያ ፡ የማይሆኑት ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ የተመዘገቡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም፡ ሦስተኛ፡ ወገኖች፡ አኳኋኑን፡ የሚያውቁ፡ መሆናቸው፡ የተረጋገጠ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፪፻፺ ። ሥራ፡ አስኪያጅ፡ በሥልጣኑ ፡ ስለ፡ መገልገል ።

(፩) ሥራ ፡ አስኪያጁ፡ የማኅበሩን፡ ስም ፡ ጠቅሶ ፤ ለግል ፡ ጥቅሙ ፡ ብቻ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ለሆኑ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ማኅበሩ ፡ አላፊ ፡ ነው። ነገር፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ የማኅበሩን ፡ ስም ፡ ያለ፡ ደንብ፡መጥቀሱን ፡ ማወቃቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አላፊነቱ ፡ የማኅበሩ ፡ ሳይሆን ፡ የሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ብቻ ፡ ይሆናል ።

(፪) ሥራ፡ አስኪያጁ፡ የማኅበሩን ፡ ስም ፡ ሳይጠቅስ ፡ ከሦስኛ ፡ ወገን፡ ጋራ፡ስምምነት ፡ ቢያደርግ ፡ ለግል ፡ ጕዳዩ ፡ እንዳደረገው ፡ ይቈጠራል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ያደረገው ፡ ለማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ መሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ የቻለ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ማኅበሩ ፡ አላፊ ፡ ነው ።

(፫) ሥራ፡ አስኪያጁ ፡ ከሥልጣኑ ፡ በላይ ፡ ለሚሠራው ፡ ሁሉ ፡ አላፊነቱ ፡ የማኅበሩ ፡ ሳይሆን ፡ የሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፪፻፺፩ ። ከማኅበሩ ፡ ጋራ ፡ የሚደረግ ፡ ስምምነት ።

ሥራ ፡ አስኪያጆቹ፡ ማኅበረተኞች ፡ በተለይ፡ ካልፈቀዱላቸው ፡ ለግል ፡ ጕዳያቸው ፡ ከማኅበሩ ፡ ጋራ ፡ ስምምነት ፡ ለማድረግ ፡ አይችሉም ።

## ቍ ፡ ፪፻፺፪ ። ውድድር ፡ ማድረግ ፤ ክልክል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) ማናቸውም ፡ ማኅበረተኛ ፡ የሆነ፡ ሰው ፡ ሌሎች ፡ ማኅበረተኞች ፡ ካልፈቀዱ ፡

ለት ፡ በቀር ፡ ማኅበሩ ፡ የሚፈጽማቸውን ፡ ተመሳሳይ ፡ ሥራዎች ፡ ለራሱ ፡ ወይም ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ለመሥራት ፡ እንደዚሁም ፡ ተመሳሳይ ፡ ለሆነ ፡ በሌላ ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ድርጅት ፡ አላፊነቱ ፡ ባንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ ማኅበረተኛ ፡ ሆኖ ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍ፡ (፩) መሠረት ፡ በስምምነቱ ፡ ውስጥ ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የተሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ የሚረጋው ፡ ለአንድ ፡ ዓመት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፫ ። ሥራ ፡ አስኪያጁን ፡ ስለ ፡ መሻር ።**

(፩) ማኅበሩ ፡ በተቋቋመበት ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ ማኅበሩ፡በተቋቋመበት፡ ጽሑፍ ፡ ማሻሻያ ፡ መሠረት ፤ የተሾመውን ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ በበቂ ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሥራ ፡ ውጭ ፡ እንዲሆን ፡ ያደርገዋል ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) መሠረት ፡ ያልተሾመ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ በማኅበረተኞች ፡ ፈቃድ ፡ ከሥራ ፡ እንዲወጣ ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፬ ። የማኅበረተኞች ፡ አላፊነት ።**

ከማኅበሩ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ የሚፈልጉት፡ ባለገንዘቦች፡ ማኅበሩ ፡ ያለበትን ፡ እንዲከፍል ፡ አስቀድሞ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ካልሰጡ ፡ ማኅበረተኞቹን ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችሉም ። ስለ ፡ ሆነም ፡ ትርፍ ፡ ሳይኖር ፡ እንደ ፡ ትርፍ ፡ ድርሻዎች ፡ የተቀበሉትን ፡ እንዲመልሱ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ማኅበረተኞቹን ፡ በቀጥታ ፡ ለመክሰስ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፭ ። ተፈጻሚዎች ፡ ስለሚሆኑ ፡ ሌሎች ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ።**

በዚህ፡ ሕግ፡ በቍ ፡ ፪፻፳፯ ፡ እስከ ፡ ፪፻፴፪ ፤ ፪፻፴፫ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) ፪፻፴፭ ፤ ፪፻፴፰ ፤ ፪፻፴፱ ፤ ፪፻፶፫ ፤ ፪፻፷ ፤ ፪፻፷፪ ፡ እስከ ፡ ፪፻፸ ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በኅብረት ፡ ሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

## አንቀጽ ፡ ፫ ።

## ሁለት ፡ ዐይነት ፡ አላፊነት ፡ ያለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ (ኮማንዲት) ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፮ ። የማኅበሩ ፡ ጠባይ ።**

ሁለት ፡ ዐይነት ፡ ኀላፊነት፡ ያለበት፡ የሽርክና፡ ማኅበር ፡ ማኅበርተኞች ፡ ዓይነታቸው ፡ ሁለት ፡ ነው ፤ እነሱም ፡ ኀላፊነቱ ፡ ያልተወሰነ፡ ማኅበረተኛና ፡ (ኮማንዲቴ) ፡ ኀላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ ማኅበረተኛ ፡ (ኮማንዲቴር)፡ ይባላሉ ። ኀላፊነታቸው ፡ ያልተወሰነ ፡ ማኅበረተኞች ፡ የሚባሉት ፡ ለየራሳቸውና ፡ ያለ ፡ ወሰን ፡ አንድ ፡ ላይ፡ ሆነው ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ለማኅበሩ ፡ ግዴታዎች ፡ ሙሉ፡ ኀላፊ፡ የሆኑ ፡ ናቸው ። ኀላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ ማኅበረተኞች ፡ የሚባሉት ፡ ደግሞ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ባገቡት ፡መዋጮ ፡ መጠን፡ ብቻ፡ ኀላፊ፡ የሚሆኑ፡ ናቸው ።

BACK



**ቍ ፡ ፪፻፺፯ ። የማኅበሩ ፡ ስም ።**

(፩) ሁለት ፡ ዐይነት ፡ አላፊነት ፡ ያለበት ፡ ማኅበር ፡ የማኅበር ፡ ስም ፡ አለው ።

(፪) በዚህም ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡ የማኅበረተኞቹን ፡ ስም ፡ ይይዛል ። ከስሙ ፡ ቀጥሎ ፡ "ሁለት ፡ ዐይነት ፡ አላፊነት ፡ ያለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር" ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ መኖር ፡ አለበት ።

(፫) አላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ስሙ ፡ ከማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገባ ፡ የፈቀደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ለሚፈጽሙት ፡ ተግባር ፤ አላፊነታቸው ፡ ያልተወሰነ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ለማኅበሩ ፡ ግዴታዎች ፡ አላፊ ፡ እንደሚሆኑት ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፰ ። በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚገባ ፡ ማስታወሻ ።**

በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፹፩ ፡ ከተመለከተው ፡ ሌላ ፡ በተጨማሪ ፡ አላፊነታቸው ፡ ያልተወሰነ ፡ ማኅበረተኞች ፡ የሚባሉትንና ፡ አላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ የተባሉትን ፡ ማኅበረተኞች ፡ ስም ፡ ተለይቶ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፪፻፺፱ ። ማስታወቂያ ፡ ስለ ፡ ማውጣትና ፡ ስለ ፡ መመዝገብ ።**

(፩) ቍ ፡ ፪፻፲፱ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ (ሀ) እና ፡ በቍ ፡ ፪፻፳ ፡ መሠረት ፡ የሚወጣው ፡ ማስታወቂያ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፹፩ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) እስከ ፡ ፮ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፰ ፡ እና ፡ ፱ ፡ እና ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፺፰ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ሐተታዎች ፡ ሊኖሩበት ፡ ይገባል ።

(፪) በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ለመመዝገቢያ ፡ በሚቀርበውም ፡ ማመልከቻ ፡ እነዚሁ ፡ ዝርዝሮች ፡ ሊኖሩበት ፡ ይገባል ፤ ማመልከቻውን ፡ የሚፈርመው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ወይም ፡ የእሱ ፡ ወኪል ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫፻ ። አላፊነታቸው ፡ ያልተወሰነ ፡ ማኅበረተኞች ።**

በኅብረት ፡ ሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ ማኅበረተኞች ፡ የወጣ ፡ ሕጋዊ ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ሁለት ፡ ዐይነት ፡ አላፊነት ፡ ባለው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ አላፊነታቸው ፡ ባልተወሰነ ፡ ማኅበረተኞችም ፡ ላይ ፡ ይጸናል ። የማኅበሩም ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ መሆን ፡ የሚችሉት ፡ እነሱ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፫፻፩ ። አላፊነታቸው ፡ ስለ ፡ ተወሰነ ፡ ማኅበርተኞች ።**

(፩) ከሽርክና ፡ ማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ መዋጮውን ፡ ያላገቡትን ፡ አላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ ማኅበረተኞችን ፡ በቀጥታ ፡ መዋጮውን ፡ እንዲያገቡ ፡ ሊያስገድዷቸው ፡ ይችላሉ ።

(፪) በደንብ ፡ በተረጋገጠ ፡ በሒሳብ ፡ ማመዛዘኛ ፡ መሠረት ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ የተቀበሉትን ፡ የትርፍ ፡ ድርሻ ፡ አላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ ማኅበርተኞች ፡ መመለስ ፡ የለባቸውም ።

(፫) የተወከሉ ፡ ቢሆኑም ፡ እንኳ ፡ አላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ ማኅበርተኞች ፡ በማኅበሩ ፡ የሥራ ፡ አስኪያጅነት ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ አይችሉም ። ይህን፡ ክልከላ፡ የተላለፈ ፡ ኅላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ ማኅበረተኛ ፡ በአሠራሩ ፡ ለደረሱት ፡ ግዴታዎች ፡ ከማኅበሩ ፡ ጋራ ፡ ባንድነትና ፡ ሳይከፋፈል ፡ ያለወሰን ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ። እንደ ፡ ሥራዎቹ ፡ ብዛት ፡ ወይም ፡ ከባድነት ፡ በተለይ ፡ ለማኅበሩ ፡ ግዴታዎች ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ ለአንዳንድ ፡ ግዴታ ፡ ብቻ ፡ ባንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ አላፊ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ለመወሰን ፡ ይቻላል ።

(፬) አላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ ማኅበርተኞች ፡ በማኅበሩ ፡ ሥራ፡ አስኪያጅነት ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ገቡ ፡ የማይቈጠረው ፤

(ሀ) በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ በሚደረጉት ፡ ምክሮች ፡ ተካፋይ ፡ መሆን ፤

(ለ) ከማኅበሩ ፡ ጋራ ፡ ግዴታ ፡ መግባት ፤

(ሐ) የሥራ ፡ አስኪያጆቹን ፡ ሥራ ፡ መቈጣጠር ፤

(መ) ለማኅበሩ ፡ አስተያየትና ፡ ምክር ፡ መስጠት ፤

(ሠ) ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ከሥልጣናቸው ፡ በላይ ፡ እንዲሠሩ ፡ መፍቀድ ፤

(፭) ኅላፊነታቸው፡ የተወሰነ፡ ማኅበርተኞች ፡ ለማኅበሩ ፡ የውስጥ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ ከማኅበሩ ፡ ጋራ ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ ማድረግ ፡ ይፈቀድላቸዋል ።

(፮) ኅላፊነታቸው ፡ የተወሰነ ፡ ማኅበርተኞች ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ የትርፍና ፡ የኪሣራ ፡ ሒሳቦች ፡ እንዲቀርቡላቸው ፡ ለመጠየቅና ፡ እንዚህንም ፡ የማኅበሩን ፡ መዝገቦችና ፡ ሌሎች ፡ ሰነዶች ፡ ትክክልነታቸውን ፡ ለመቈጣጠር ፡ መብት ፡ አላቸው ።

(፯) ኅላፊነቱ፡ በተወሰነው፡ ማኅበርተኛ ፡ ላይ ፡ የሚደርሱት ፡ ጉዳይ ፡ ምክንያቶች ፡ ማኅበሩን ፡ ለማፍረሻ ፡ ምክንያቶች ፡ አይሆኑም ፡ ለዚህ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫፻፪ ። ድርሻዎችን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።**

ሥራ ፡ አስኪያጁና፡ የተወሰነ፡ አላፊነት፡ ያላቸው፡ ማኅበረተኞች ፤ አብዛኞቹ፡ ካልተስማሙ ፡ በስተቀር ፡ ድርሻዎችን ፡ ማስተላለፍ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፫፻፫ ። ተፈጻሚዎች ፡ የሚሆኑ ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ሌሎች ፡ ድንጋጌዎች ።**

ከዚህ፡ በላይ፡ ባሉት፡ ቍጥሮች፡ የተመለከቱት፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ፡ ተጠበቁ፡ ሆኖ ፡ ከቍ ፡ ፪፻፳፯ ፡ እስከ ፡ ፪፻፴፪ ፤ ቍጥር ፡ ፪፻፴፫ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፤ ቍ ፡ ፪፻፴፭ ፤ ፪፻፵፰ ፤ ፪፻፵፱ ፤ ፪፻፶፰ ፤ ፪፻፷ ፤ ፪፻፷፪ ፡ እስከ ፡ ፪፻፸ ፤ ፪፻፸፪ ፤ ፪፻፸፫ ፤ ፪፻፹፯ ፡ እስከ ፡ ፪፻፺፩ ፤ ፪፻፺፫ ፤ ፪፻፺፬ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ሁለት ፡ ዐይነት ፡ ኅላፊነት ፡ ባለው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

BACK



## አንቀጽ ፡ ፤ ።

## የአክሲዮን ፡ ማኅበር ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፫፻፬ ። የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ትርጓሜ ።**

(፩) የአክሲዮን፡ ማኅበር፡ የሚባለው ፤ ዋናው ፡ ገንዘቡ ፡ (ካፒታሉ) ፡ አስቀድሞ ፡ ተወስኖ ፡ በአክሲዮን ፡ የተከፋፈለና ፡ ለዕዳውም ፡ ንብረቱ ፡ ብቻ ፡ ዋስ ፡ የሆነ፡ ማኅበር ፡ ነው ።

(፪) ማኅበርተኞች ፡ ለማኅበሩ፡ ግዴታዎች፡ አላፊ ፡ የሚሆኑት ፡ ባላቸው ፡ ድርሻ ፡ ልክ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫፻፭ ። የማኅበሩ ፡ መጠሪያ ።**

ለጠቅላላው ፡ ጸጥታ፡ ተቃራኒ፡ ካልሆነና፡ የሥስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መብት ፡ ካል ተነካ ፡ የማኅበሩ ፡ መጠሪያ ፡ እንደ ፡ ፈቀዱት ፡ ሊመረጥ ፡ ይቻላል ። ከመጠሪያው ፡ ቀጥሎ ፡ «የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ » የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ መኖር ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫፻፮ ። የማኅበሩ ፡ አነስተኛ ፡ ዋና ፡ ገንዘብና ፡ በየአንዳንዱ ፡ አክሲዮን፡ ላይ ፡ የተጻፈው ፡ ዋጋ ።**

(፩) የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ከ፶ሺሕ፡ የኢ.ት ፡ ብር ፡ ያነሰ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

(፪) ያንዱ፡ አክሲዮን፡ ዋጋ ፡ ከ፲ ፡ የኢ.ት ፡ ብር ፡ ያነሰ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫፻፯ ። መሥራቾች ።**

(፩) ማኅበሩ ፡ ሲመሠረት ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ አምስት ፡ ማኅበርተኞች ፡ እንዲኖሩት ፡ ያስፈልጋል ።

(፪) በሕግ፡ በኩል፡ መሥራቾች ፡ የሚባሉት ፡ ማኅበሩ፡የሚመሠረትበትን፡ጽሑፍ፡ የፈረሙና ፡ በሙሉ ፡ የማኅበሩን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ያዋጡ ፡ ናቸው ።

(፫) እንዲሁም፡ የሚቋቋመው፡ ማኅበር ፡ አክሲዮን ፡ በግልጽ ፡ ለሕዝብ ፡ እንዲሸጥ ፡ የወጣ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የማኅበሩን ፡ መግለጫ ፡ (ፕሮስፔክቱስ) ፡ የሚፈርሙት ፡ ለማኅበሩ ፡ በዐይነት ፡ መዋጮ ፡ የሚያደርጉ ፡ ወይም ፡ ከትርፉ ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ ተከፋይነት ፡ እንዲኖራቸው ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሁሉ ፡ መሥራቾች ፡ ይባላሉ ።

(፬) በማኅበሩ፡ ያልገቡ ፡ ማንኛዎቹም ፡ ሰዎች ፡ የማኅበሩ ፡ መቋቋም ፡ እንዲጸና ፡ ሲሉ ፡ ማንኛውንም ፡ እርምጃና ፡ ለማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ ያደረጉ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ መሥራቾች ፡ ይቈጠራሉ ።

## ቍ ፡ ፫፻፰ ። መሥራቾች ፡ የገቡበት ፡ ግዴታዎች ።

(፩) ማኅበሩን ፡ ለማቋቋም ፡ ሲሉ ፡ ለገቡባቸው፡ ግዴታዎች፡ መሥራቾቹ ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ባንድነትና ፡ ሳይከፋፈል ፡ ያለወሰን ፡ ኀላፊዎች ፡ ናቸው ። ይህ ፡ ኀላፊነት ፡ ማኅበሩ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ከመመዝገቡ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ ሆነው ፡ በሠሩት ፡ ሰዎችም ፡ ላይ ፡ ይጸናል ።

(፪) ማኅበሩ፡ ከመሥራቾች፡ ላይ ፡ የተባሉትን ፡ ግዴታዎች ፡ የሚቀበለው ፡ ማኅበሩን ፡ ለማቋቋም፡ አስፈላጊ፡ በሆነው፡ ግዴታና ፡ ወጪ ፡ መጠን ፡ ወይም ፡ አክሲዮኑን ፡ ለመግዛት ፡ የጻፉት ፡ ሰዎች ፡ ጉባኤ ፡ ያጸደቀው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መሥራቾች ፡ ያወጡትን ፡ ወጪ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፫) በማናቸውም፡ ምክንያት፡ ቢሆን ፡ ማኅበሩ ፡ ሳይቋቋም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መሥራቾች ፡ ለገቡበት ፡ ግዴታዎችና ፡ ላደረጉት ፡ ወጪ ፡ አክሲዮኑን ፡ ለመግዛት ፡ የጻፉትን ፡ ሰዎች ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አይኖራቸውም ።

## ቍ ፡ ፫፻፱ ። የመሥራቾች ፡ ኀላፊነት ።

(፩) መሥራቾች፡ ለማኅበሩና፡ ለሦስተኛ፡ ወገኖች ፡ ባንድነት፡ ሳይከፋፈል፡ ከዚህ፡ በታች፡ በተመለከቱት ፡ ምክንያቶች፡ ለሚደርሱት፡ ጉዳቶች፡ ኀላፊ፡ የሚሆኑት ፤

(ሀ) የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ እንዲገዛና ፡ ለማቋቋሚያውም ፡ አስፈላጊው ፡ ገንዘብ ፡ ገቢ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፤

(ለ) በዐይነት ፡ የተደረጉት ፡ መዋጮዎች ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፲፭ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፤

(ሐ) ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ አቋቋም ፡ ለሕዝብ ፡ ያቀረቡት ፡ ማስታወቂያ ፡ እርግጠኛ ፡ ለመሆኑ ።

(፪) በዚህ፡ ቍጥር፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ባለው ፡ ኀላፊነት ፡ ላይ ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ተጎጂው ፡ ጉዳቱን ፡ ወይም ፡ ኀላፊውን ፡ ካወቀበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፫ ፡ ዓመት ፡ ክስ ፡ ያላቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በይርጋ ፡ ይታገዳል ። በሌላው ፡ በማናቸውም ፡ ሁናቴ ፡ ግን ፡ ጉዳት ፡ ከደረሰበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ክስ ፡ ካልቀረበ ፡ በይርጋ ፡ ይታገዳል ።

(፫) ወንጀል ፡ በመሥራታቸው ፡ መሥራቾቹ ፡ ያለባቸውን ፡ ኀላፊነት ፡ የሚመለከቱ ፡ ሁናቴዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

## ቍ ፡ ፫፻፲ ። ለመሥራቾች ፡ የሚሆኑት ፡ ትርፎች ፡ ወሰን ።

(፩) በማኅበሩ፡ መመሥረቻ፡ ከማኅበርተኛነታቸው ፡ መብት ፡ በላይ፡ መሥራቾች፡ ቢበዛ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ በሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ መሠረት ፡ ከሚገኘው ፡ ከተጣራው ፡ ትርፍ ፡ ውስጥ ፡ በጠቅላላው ፡ ለራሳቸው ፡ ከአምስት ፡ አንድ፡ እጅ፡ የማይበልጥ ፡ ድርሻ ፡ ከተጣራው ፡ ትርፍ ፡ ሊካፈሉ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ከዚህም፡ በቀር፡ ለራሳቸው፡ ሲሉ ፡ ሌላ ፡ ማናቸውም ፡ ጥቅም ፡ እንዲሰጣቸው፡ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ለመወሰን ፡ አይችሉም ።

(፫) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተፈቀዱት፡ ጥቅሞች፡ ለመሥራቹ ፡ ለራሱ ፡ ብቻ ፡ የሚሰጡ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ የመሥራቾች ፡ ጥቅሞች ፡ በሚተላለፉ ፡ አክሲዮኖች ፡ ሊወጡ ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፩ ። የማኅበርተኞች ፡ ብዛት ፡ በሕግ ፡ ከተወሰነው ፡ በታች ፡ መቀነስ ።**

(፩) በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ የማኅበርተኞች ፡ ብዛት ፡ ከአምስት ፡ ያነሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማኅበሩ ፡ የማኅበርተኞች ፡ ብዛት ፡ ካነሰበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ሥራውን ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ሊቀጥል ፡ አይችልም ። ማናቸውም ፡ ማኅበርተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የማኅበርተኞች ፡ ሕጋዊ ፡ ብዛት ፡ ማነሱን ፡ ዐውቆ ፡ ማኅበሩ ፡ ከተባሉት ፡ ስድስት ፡ ወሮች ፡ በኋላ ፡ ሥራውን ፡ የቀጠለ ፡ እንደ ፡ሆነ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ማኅበሩ ፡ ላደረጋቸው ፡ ዕዳዎች ፡ በግል ፡ ኀላፊነት ፡ ሊጠየቅ ፡ ይቻላል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ማኅበሩ ፡ የተወሰነ ፡ የሥራ ፡ ድርጅቶች ፡ ክፍል ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከማኅበርተኞች ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የጠየቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማኅበሩን ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመፍረድ ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሕጋዊ ፡ አኳኋን ፡ እንዲመለስ ፡ ለማኅበሩ ፡ ጊዜ ፡ መስጠትና ፡ ማናቸውንም ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑትን ፡ ለጊዜው ፡ የመጠበቂያ ፡ ውሳኔዎች ፡ ለማዘዝ ፡ እንዲቻል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔውን ፡ ለማዘግየት ፡ ይችላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## የማኅበሩ ፡ አቋቋም ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፪ ። አቋቋሙን ፡ እንዲረጋ ፡ የሚያደርጉ ፡ ጠቅላላ ፡ ሁኔታዎች ።**

(፩) ማናቸውም፡ የአክሲዮን፡ ማኅበር ፡ በሕግ ፡ እንደ ፡ ተቋቋመ ፡ የሚቈጠረው ፤

(ሀ) የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ ሲፈረም ።

(ለ) በገንዘብ ፡ ከሚሸጡት ፡ አክሲዮኖች ፡ ውስጥ ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ ሩብ ፡ በማኅበሩ ፡ ስምና ፡ ሒሳብ ፡ በአንድ ፡ ባንክ ፡ ሲገባ ፡ ነው ።

(፪) ይህ፡ ንኡስ፡ ቍ፡ (፩) መሠረት ፡ የተቀመጠ ፡ ገንዘብ ፡ ማኅበሩ ፡ በንግድ ፡ መገባ ፡ መመዝገቡ ፡ ሳይረጋገጥ ፡ ለማኅበሩ ፡ ሕጋዊ ፡ ለሆኑት ፡ እንደራሴዎች አይሰጣቸውም ።

(፫) ይህ፡ መመዝገቡ ፤ ገንዘቡ ፡ ባንክ፡ ከተቀመጠበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስካንድ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ያልተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገንዘቡ ፡ አክሲዮን ፡ እንገዛለን

BACK



ብለው ፡ ለፈረሙት ፡ ይመለሳል ። የሚመለሰውም ፡ በመሥራቾች ፡ ጥንቃቄ ፡ ሆኖ ፡ እነሱም ፡ ባንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ ኀላፊዎች ፡ ናቸው ። ይህ ፡ ጊዜ ፡ የተ ላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እነዚህ ፡ የሚመለሱት ፡ ገንዘቦች ፡ ሕጋዊ ፡ ወለድ፡ያፈራሉ።

## ቍ ፡ ፫፻፲፫ ። የመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ።

ማኅበሩ ፡ በሕግ ፡ በታወቀ ፡ ጽሑፍ ፡ ይቋቋማል ፤ በዚህም ፡ ጽሑፍ ፡ ሊኖር በት ፡ የሚገባው ፤

(፩) የማኅበርተኞች፡ ስም፤ ዜግነታቸው ፤ አድራሻቸው ፤ ለመግዛት ፡ የፈረሙት ፡ የአክሲዮኖች ፡ ብዛት ። ማኅበርተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ካንድ ፡ አክሲዮን ፡ ያነሰ ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም ።

(፪) የማኅበሩ ፡ መጠሪያ ፤

(፫) የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤትና ፡ ያሉም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቅርንጫፎቹ ፡ ስፍራ ፤

(፬) ማኅበሩ ፡ የቆመበት ፡ ጉዳይ ፤

(፭) የተፈረመና ፡ ገቢ ፡ የሆነው ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፤

(፮) የአክሲዮኑ ፡ ዋጋ ፤ ብዛቱ ፤ ዐይነትና ፡ የአክሲዮኑ ፡ ልዩነት ፤

(፯) በዐይነት ፡ የተደረጉት ፡ መዋጮዎች ፡ ዋጋና ፡ ያገልግሎታቸው ፡ ዐይነት ፤ በምን ፡ ዋጋ ፡ ታስቦ ፡ እንደ ፡ ተቀበሉ ፤ ባለንብረቱ ፡ የሆነ ፡ ማኅበርተኛና ፡ ገቢ ፡ ላደረገው ፡ መዋጮ ፡ የተሰጠ ፡ የአክሲዮኖች ፡ ብዛት ፤

(፰) የትርፉ ፡ አከፋፈል ፡ አኳኋን ፤

(፱) ለመሥራቾች ፡ የተወሰነው ፡ ትርፍ ፤ የተከፋይነቱ ፡ ምክንያት ፤

(፲) የአስተዳዳሪዎች ፡ ብዛትና ፡ ሥልጣን ፤ እንደዚሁም ፡ ለማኅበሩ ፡ እንደራሴ ፡ የመሆን ፡ አኳኋን ፤

(፲፩) የተቈጣጣሪዎች ፡ (ኦዲተሮች) ፡ ብዛት ፤

(፲፪) ማኅበሩ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፤

(፲፫) ማኅበሩ ፡ የሥራ ፡ ራፖር ፡ የሚያስታውቅበት ፡ ሁኔታ ።

## ቍ ፡ ፫፻፲፬ ። የማኅበሩ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ።

(፩) በሕግ፡ በተመለከተው፡ መሠረት ፡ የማኅበሩን ፡ ሥራ ፡ የሚወስነውን ፡ የመተ ዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ መሥራቾቹ ፡ ማዘጋጀት ፡ አለባቸው ።

(፪) የንግድና፡ የኢንዱስትሪ፡ ሚኒስቴር ፡ ለዐይነት ፡ እንዲሆን ፡ ያዘጋጃቸው ፡ ደን ቦች ፡ መሥራቾች ፡ ከሚለዉጡት ፡ በቀር ፡ በዚያው ፡ ዐይነት ፡ መሥራት ፡ ይቻላል ።

(፫) መተዳደሪያው፡ ደንብ፡ ከመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ተቈ ጥሮ ፡ ከርሱ ፡ ተያይዞ ፡ መገኘት ፡ አለበት ።

## ቍ ፡ ፫፻፲፮ ። በዐይነት ፡ የተደረጉት ፡ መዋጮዎች ፡ አገማመት ።

(፩) በዐይነት ፡ መዋጮ ፡ የሚያደርግ ፡ ማኅበርተኛ ፡ ከንግድና ፡ ከኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ የተመረጡት ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡ ገማቾች ፡ በመሓላ ፡ ያደረጉትን ፡ ሪፖርት ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) በዚህ፡ ሪፖርት ፡ በመዋጮ ፡ የገቡትን ፡ ንብረቶች ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ የተሰጠውን ፡ ዋጋ ፡ ግምቱ ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ እንደ ፡ ተገኘ ፡ በዝርዝር ፡ ይገልጻል ፤ ይህ ፡ ሪፖርት ፡ ከመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ጋራ ፡ ይያያዛል ።

(፫) አስተዳዳሪዎቹና፡ ተቈጣጣሪዎቹ ፡ ማኅበሩ ፡ ከተቋቋመበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ በሪፖርቱ ፡ ውስጥ ፡ የተገለጹትን ፡ ግምቶች ፡ መቈጣጠርና ፡ አስፈላጊ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝም ፡ የተደረጉትን ፡ ግምቶች ፡ እንደገና ፡ መመርመርና ፡ መገመት ፡ አለባቸው ። በዐይነት ፡ ለተደረጉት ፡ መዋጮዎች ፡ የተሰጡት ፡ አክሲዮኖች ፡ ይህ ፡ ምርመራ ፡ እስከ ፡ ተደረገ ፡ ድረስ ፡ የማይሸጡና ፡ የማይለወጡ ፡ ሆነው ፡ በማኅበሩ ፡ እጅ ፡ መቀመጥ ፡ አለባቸው ።

(፬) በንኡስ፡ ቍ፡ ፫ ፡ መሠረት ፡ በተደረገው ፡ ምርመራ ፡ የተነሣ ፡ በመዋጮ ፡ የገቡት ፡ ንብረቶች ፡ ዋጋ ፡ ከተሰጣቸው ፡ ግምት ፡ አንድ ፡ አምስተኛ ፡ አንሶ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በገቡት ፡ መዋጮዎች ፡ ዋጋ ፡ ምልተው ፡ የተገኙትን ፡ አክሲዮኖች ፡ ማኅበሩ ፡ በዚሁ ፡ ልክ ፡ ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ መቀነስ ፡ አለበት ። ያለዚያ ፡ መዋጮውን ፡ ያገባው ፡ ማኅበረተኛ ፡ የጐደለውን ፡ ገንዘብ ፡ መሙላት ፡ ወይም ፡ ከማኅበሩ ፡ መውጣት ፡ ይችላል ።

(፭) ዋናውን፡ ገንዘብ፡ ለማዋጣት ፡ የፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ ስብሰባ ፡ በዚህ ፡ ቍጥር፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ የቀረበውን ፡ የገማቾችን ፡ ሪፖርት ፡ መቀበሉ ፤ ማኅበሩን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፫ ፡ እና ፡ ፬ ፡ የተደነገገውን ፡ ከመፈጸም ፡ አይከለክለውም ።

## ቍ ፡ ፫፻፲፯ ። በመሥራቾች ፡ መሓከል ፡ የሚደረግ ፡ አቋቋም ።

የማኅበሩ ፡ አክሲዮኖች ፡ ለሕዝብ ፡ የሚሸጡ ፡ ካልሆኑ ፡ መሥራቾች፣ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፤

(፩) አክሲዮኖችን ፡ በሙሉ ፡ ለመግዛት ፡ መፈረማቸውን ፤

(፪) ለነዚህ፡ አክሲዮኖች ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፲፪ ። ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩፡ (ለ) መሠረት ፡ የተወሰነው ፡ ጠቅላላ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲቀመጥ ፡ መደረጉን ፤

(፫) በዐይነት ፡ የሆነው ፡ መዋጮ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፲፮ ፡ በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ መገመቱንና ፡ ዋጋውም ፡ በሙሉ ፡ መከፈሉን ።

(፬) ለማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ ክፍሎች ፡ የሥራ ፡ መሪዎች ፡ መሾማቸውን ፡ ማረጋገጥ ፡ አለባቸው ።

BACK



**ቍ ፡ ፫፻፲፯ ። ሕዝቡ ፡ ፈርሞ ፡ በመግዛት ፡ የሚቋቋም ፡ ማኅበር ።**

እንዲሁም፡ ሕዝቡ ፡ አክሲዮኑን ፡ እየፈረመ ፡ በመግዛት ፡ ለተቋቋመው ፡ ማኅበር ፡ ከቍጥር ፡ ፫፻፲፰ ፡ እስከ ፡ ፫፻፳፪ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፰ ። የማኅበር ፡ መግለጫ ፡ (ፕሮስፔክቱስ) ።**

(፩) ሕዝብ፡ አክሲዮን ፡ እንዲገዛ ፡ የሚደረገው ፡ ጥሪ ፡ መሥራቾች ፡ ሁሉ ፡ በሚፈርሙበት ፡ የማኅበር ፡ መግለጫ ፡ ነው ። በዚሁ ፡ የማኅበር ፡ መግለጫ ፡ ላይ ፡ ሊጻፍ ፡ የሚገባው ፤

(ሀ) የመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ረቂቅ ፤

(ለ) የማኅበሩ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ረቂቅ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ውሳኔ ፡ ባጭሩ ፤

(ሐ) በቍጥር ፡ ፫፻፲፩ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ተያይዞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የግምቱ ፡ ራፖር ፡ አጭር ፡ መግለጫ ፡ ቢኖር ፤

(መ) አክሲዮን ፡ ለመግዛት ፡ ፈራሚው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ እንደሚገደድ ፤

(ሠ) አክሲዮኖቹ ፡ የሚሸጡበት ፡ ዋጋ ፤

(ረ) ለመግዛት ፡ የፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ እስኪደረግ ፡ ድረስ ፡ ከአክሲዮኖች ፡ ዋጋ ፡ መከፈል ፡ የሚገባው ፡ ልክ ፤

(ሰ) ፈራሚዎች ፡ ለመግዛት ፡ የሚያመለክቱበትና ፡ ገንዘብ ፡ የሚከፍሉበት ፡ ቦታ ፡ ነው ።

(፪) ፈራሚዎች ፡ በሚፈርሙባቸው ፡ ቦታዎች ፡ የማኅበሩ ፡ መግለጫዎችና ፡ የግምቱን ፡ ራፖር፡ ግልባጭ ፡ ፈራሚዎች ፡ እንዲመለከቱት ፡ በተባለው ፡ ቦታ ፡ መገኘት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫፻፲፱ ። አክሲዮኖች ፡ ለመግዛት ፡ ስለ፡ ማስታወቅ ።**

(፩) አክሲዮን፡ ለመግዛት፡ የሚቀርቡ ፡ ጥያቄዎች ፡ ሁሉ ፤ አክሲዮኖቹን ፡ ለመግዛት ፡ በተወሰነው ፡ ቦታ ፡ በሚገኙት ፡ መጠየቂያ ፡ ፎርሞች ፡ (ወረቀቶች) ፡ ተሞልተው ፡ መሰጠት ፡ አለባቸው ።

(፪) አክሲዮን ፡ ለመግዛት ፡ ጥያቄ ፡ ያቀረበው ፡ ሰው ፡ መግለጫውንና ፡ የተጠቀሰውን ፡ ልዩ ፡ ራፖር ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መመልከቱን ፡ መግለጽ ፡ አለበት። በመፈረሚያው ፡ ፎርም ፡ ላይ ፡ ስሙንና ፡ አድራሻውን ፡ ለመግዛት ፡ የሚፈልጋቸውን ፡ የአክሲዮን ፡ ቍጥሮችና ፡ ያመለከተበትን ፡ ቀን ፡ መጥቀስ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫፻፳ ። የፈራሚዎቹ ፡ ጉባኤ ።**

(፩) የመፈረሚያው፡ ቀን ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ መሥራቾች ፡ ለመግዛት ፡ የፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ ጉባኤ ፡ እንዲደረግ ፡ መጥራት ፡ አለባቸው ።

(፪) በቍጥር፡ ፫፻፴፱፡ የተመለከተው፡ እንደተጠበቀ፡ ሆኖ፡ ስለ፡ ድንገተኛ፡ ጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ አጠራርና፡ ውሳኔ፡ የተደነገገው፡ ለፈራሚዎቹም፡ ጉባኤ፡ የሚፈጸም፡ ነው።

ቍ ፡ ፫፻፵፩ ። የጉባኤው ፡ ዓላማ ።

በቍ ፡ ፫፻፵ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የፈራሚዎች ፡ ጉባኤ ፡ ዓላማ ፤

(፩) የማኅበሩ ፡ ማቋቋሚያ ፡ ሁኔታዎች ፡ መፈጸማቸውንና ፡ አለመፈጸማቸውን ፡ ለመቈጣጠር ፤

(፪) የመጨረሻውን፡ የመመሥረቻ፡ ጽሑፍና ፡ የማኅበሩን ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ለመወሰን ፤

(፫) አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ በዐይነት ፡ የሆነውን ፡ መዋጮና ፡ የመሥራቾቹንም ፡ የትርፍ ፡ ድርሻ ፡ ልክ ፡ ለማጽደቅ ፤

(፬) በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፡ የሚሾሙትን ፡ ለመሾም ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፵፪ ። ስለ ፡ ጉባኤው ፡ ውሳኔዎች ፡ ልዩ ፡ ደንብ ።

(፩) የፈራሚዎቹ ፡ ጉባኤ ፡ የሰጣቸው ፡ ውሳኔዎች ፡ መሥራቾቹ ፡ ሁሉ ፡ በፈረሙበት ፡ ጽሑፍ ፡ ተጽፎ ፡ መገኘት ፡ አለበት ፤ ከዚሁ ፡ ጽሑፍ ፡ ጋራ ፡ ጉባኤው ፡ እነሱን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ውሳኔውን ፡ የሰጠባቸው ፡ ጽሑፎች ፡ ሁሉ ፡ ከዚሁ ፡ ጋራ ፡ መያያዝ ፡ አለባቸው ።

(፪) ማናቸውም፡ አክሲዮኑን፡ ለመግዛት ፡ የፈረመ ፡ ሰው ፡ በስብሰባዎቹ ፡ ተካፋይ፡ ለመሆንና ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንደ ፡ ተወሰነው ፡ ድምፅ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፫) በዐይነት፡ መዋጮ፡ ያደረጉት ፡ ሰዎች ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ በሚገመትበት ፡ እንዲሁም ፡ ከትርፍ፡ ልዩ ፡ ድርሻ ፡ በሚወስንላቸው፡ ጊዜ ፡ መሥራቾች ፡ በባለአክሲዮንነታቸው ፡ መብት ፡ ወይም ፡ በውክልና ፡ ድምፅ ፡ ለመስጠት ፡ አይችሉም ።

(፬) ጉባኤው ፤ ፈራሚዎቹ፡ ሁሉ፡ ካልፈቀዱ ፡ በቀር ፡ የማቋቋሚያውን ፡ ውልና ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንቦችን ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ለመለወጥ ፡ አይችልም ። ነገር ፡ ግን ፡ በዐይነት ፡ ገቢ፡ የሆነውን፡ መዋጮ ፡ ወይም ፡ የመሥራቾችን ፡የትርፍ ፡ ድርሻቸውን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ጉባኤው ፡ ስለሚያደረገው ፡ ማሻሻል ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ለመወሰን ፡ ይቻላል ።

(፭) ጉባኤው፡ ለይዐነት ፡ መዋጮ፡ ያገቡት፡ ሰዎች ፡ የሚደርሳቸውን ፡ የአክሲዮኖች ፡ ብዛት ፡ ብቻ ፡ ለመቀነስ ፡ እስከ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፲፩ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ የተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፫፻፵፫ ። ማኅበሩ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ እንዲመዘገብ ፡ ስለ ፡ ማድረግና ፡ የማኅበሩን፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

(፩) ማኅበሩ፡ የተቋቋመበት፡ ሁኔታ ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆንም ፡ ከቍጥር፡ ፪፻፲፱፡

BACK



እስከ ፡ ፪፻፳፬ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) የሚከተሉትም ፡ ሰነዶች ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ።

(ሀ) የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፤

(ለ) የማኅበሩ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እንዳለ ፤

(ሐ) የማኅበሩ ፡ መግለጫ ፤

(መ) አክሲዮን ፡ የፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ ስብሰባ ፡ ቃለ ፡ ጉባኤና ፡ ሌሎችም ፡ ተጨማሪ ፡ ሰነዶች ፡ ሁሉ ፤

(፫) በቍጥር ፡ ፫፻፲፫ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ እስከ ፡ ፯ ፡ እና ፡ ከንኡስ ፡ ቍ ፡ ፲ ፡ እስከ ፡ ፲፪ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ሐተታዎች ፡ ሕጋዊ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ በሚወጡበት ፡ ጋዜጣና ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ለመመዝገብ ፡ በቀረበው ፡ ማመልከቻ ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፫፻፳፬ ። ማስታወቅ ፡ ስለሚሰጠው ፡ ውጤት ።

(፩) ምንም ፡ እንኳ ፡ ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ መቋቋም ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሳይፈጸሙ ፡ ቢቀሩ ፤ በመዝገብ ፡ ከገባና ፡ በማስታወቂያ ፡ ከተገለጠ ፡ የማኅበሩ ፡ መኖር ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ መሆኑ ፡ በሕግ ፡ የታወቀ ፡ ይሆናል ።

(፪) በሕጉ ፡ ወይም ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንቡ ፡ መሠረት ፡ መፈጸም ፡ የሚገባቸው ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ ሳይፈጸሙ ፡ በመቅረታቸው ፡ ምክንያት ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎችና ፡ የባለአክሲዮኖቹ ፡ ጥቅም ፡ ጉዳት ፡ የሚያገኘው ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ከገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ወይም ፡ ከባለአክሲዮኖቹ ፡ አንዱ ፡ በሚያቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ማድረግ ፡ ወይም ፡ ለጊዜው ፡ አስፈላጊ ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፡ ይችላል ።

(፫) በንግድ ፡ ኦፊሴል ፡ ጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ ከወጣ ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የማመልከት ፡ መብት ፡ ቀሪ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ አክሲዮኖችና ፡ ስለ ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ መብትና ፡ ግዴታዎች ።

ቍ ፡ ፫፻፳፭ ። የአክሲዮኖች ፡ ዐይነት ።

(፩) ባለአክሲዮኑ ፡ እንደ ፡ መረጠ ፤ አክሲዮኖቹ ፡ በስሙ ፡ ወይም ፡ ላምጪው ፡ ተብለው ፡ ሊጻፉ ፡ ይቻላል ።

(፪) በሕግ ፡ ወይም ፡ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንቡ ፡ ላምጪው ፡ የሚባል ፡ የአክሲዮን ፡ ዐይነት ፡ ተከልክሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አክሲዮኖቹ ፡ በስም ፡ ብቻ ፡ የሚወጡ ፡ ይሆናሉ ።

(፫) ላምጪው ፡ የሚል ፡ የአክሲዮን ፡ ዐይነት ፡ በሚገኝባቸው ፡ ማኅበሮች ፡

ማንኛውም ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ቢኖር ፡ እንኳ ፡ ባለአክሲዮን ፡ የሆነ ፡ ሰው፡ ሁሉ ፡ ላምጪው ፡ ተብለው ፡ የወጡትን ፡ የራሱን ፡ አክሲዮኖች ፡ በስሙ ፡ እንዲ ለወጡ ፡ እንዲሁም ፡ በስሙ ፡ የወጡትን ፡ ላምጪው ፡ ተብለው ፡ እንዲለወጡ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፫፻፳፮ ። አክሲዮኖች ፡ የሚወጡበት ፡ ዋጋ ።**

(፩) ከተጻፈባቸው ፡ ዋጋ ፡ በታች ፡ አክሲዮኖችን ፡ ለማውጣት ፡ አይቻልም ።

(፪) በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንቡ ፡ ወይም ፡ በድንገተኛ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከተጻፈባቸው ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ዋጋ ፡ አክሲዮኖችን ፡ ለማውጣት ፡ ይቻላል ። በተጻፈበት ፡ ዋጋና ፡ በሚ ወጣበት ፡ ዋጋ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ የዋጋ ፡ ብልጫ ፡ ( ፕሪሚዮም ) ፡ ይባላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፳፯ ። ማኅበሩ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ከመመዝገቡ ፡ በፊት፡ስለ፡ወጡ፡አክሲዮኖች።**

ማኅበሩ፡ በንግድ፡ መዝገብ፡ ከመመዝገቡ ፡ በፊት ፡ የወጡ ፡ አክሲዮኖች ፡ አይ ጸኑም ፡ ( ውድቅ ፡ ናቸው ) ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አክሲዮኖቹን ፡ በማውጣት ፡ ያስከተ ሉት ፡ ግዴታዎች ፡ እንዳሉ ፡ ሆነው ፡ ይቈያሉ ።

**ቍ ፡ ፫፻፳፰ ። አክሲዮኖቹ ፡ ስላለመከፋፈላቸው ።**

(፩) አክሲዮኖቹ ፡ የማይከፋፈሉ ፡ ናቸው ።

(፪) ብዙዎች፡ ሰዎች ፡ የአክሲዮኖች፡ የጋራ ፡ ባለሀብት ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የማ ኅበረተኛነትን ፡ መብት ፡ ሊሠራባቸው ፡ እንዲችል ፡ ለሁሉም ፡ እንደራሴ ፡ የሚ ሆን ፡ መሾም ፡ አለባቸው ።

(፫) ለሁሉም፡ እንደራሴ፡ የሚሆን ፡ ያልተሾመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለአንዱ ፡ ባለሀ ብት ፡ ማኅበሩ ፡ የሚሰጣቸው ፡ ማስታወቂያዎችና ፡ መግለጫዎች ፡ በሁሉም ፡ ላይ ፡ የሚጸኑ ፡ ናቸው ።

(፬) የጋራ፡ ባለሀብቶች፡ ከባለአክሲዮንነት ፡ የተነሣ ፡ ላሉት ፡ ግዴታዎች ፡ በአን ድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ አላፊ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፫፻፳፱ ። መያዣ ፡ ወይም ፡ የአላባ ፡ መብት ።**

(፩) አንድ ፡ አክሲዮን ፡ በመያዣ ፡ ወይም ፡ በአላባ ፡ መብት ፡ የተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በጉባኤዎች ፡ ድምፅ ፡ የመስጠት ፡ መብት ፡ አክሲዮኑን ፡ በመያዣ ፡ ለተቀበለው ፡ ወይም ፡ ለአላባ ፡ ጥቅም ፡ ተቀ ባዩ ፡ ነው ።

(፪) አክሲዮኑን ፡ ሲገዛ ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ መብት ፡ የማኅበረተኛው ፡ ነው ፤ መብቱን ፡ ማኅበረተኛው ፡ ሳይሠራበት ፡ ቢቀር ፡ ለማኅበረተኛው ፡ ጥቅም ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፵፪ ፡ በተወሰነው ፡ ሁናቴ ፡ መሠረት ፡ ይሸጣል ።

(፫) አክሲዮኖቹ፣ በመያዣ፣ ተሰጥተው ፡ ለአክሲዮኖቹ ፡ የሚከፈል ፡ ቀሪ፡ገንዘብ ፡ በተጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ እንዚህን ፡ ገንዘብ ፡ መክፈል ፡ ያለበት ፡ ማኅበረተኛው ፡ ነው። ማኅበረተኛው ፡ የተባለውን ፡ ገንዘብ ፡ ሳይከፍል ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አክሲዮኑን ፡ በመያዣ ፡ የያዘው ፡ ሰው ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፴፪ ፡ በተደነገገው ፡ አሠራር ፡ መሠረት ፡ የያዛቸውን ፡ አክሲዮኖች ፡ ለመሸጥ ፡ ይችላል ።

(፬) አክሲዮኖቹ ፡ የተሰጡት ፡ በአላባ ፡ ጥቅም ፡ እንደ፣ ሆነ ፡ የአላባው ፡ መብት ፡ ጊዜ ፡ ሲያልቅ ፡ የከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲመለስለት ፡ ያለው ፡ መብት ፡ እንደ፣ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ለአክሲዮኑ ፡ የተጠየቀውን ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ መክፈል ፡ ያለበት ፡ ባለአላባው ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፴ ። በአክሲዮኖች ፡ ላይ ፡ የሚጻፍ ።

በየአንዳንዱ ፡ አክሲዮን ፡ አንዱ ፡ አስተዳዳሪ ፡ መፈረም ፡ አለበት ። የሚከተሉትም ፡ ዝርዝር ፡ ነገሮች ፡ በአክሲዮኑ ፡ ላይ ፡ መገለጽ ፡ አለባቸው ።

(ሀ) የማኅበሩ ፡ መጠሪያ ፡ ስሙና ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፤

(ለ) የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብና ፡ በአንዱ ፡ አክሲዮን ፡ ላይ ፡ የተጻፈበት ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፤

(ሐ) የመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፤ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ የተመዘገበበት ፡ ቀንና ፡ የተመዘገበበት ፡ ስፍራ ፤

(መ) የአክሲዮኑ ፡ መለያ ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ( ሴሪ ) ፡ ወይም ፡ ዐይነት ፤ ተራ ፡ አክሲዮን ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ አክሲዮን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዲሁ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የልዩ ፡ መብቱ ፡ ዐይነት ፤

(ሠ) በሙሉ ፡ ዋጋቸው ፡ ካልተከፈለው ፡ አክሲዮኖች ፡ ላይ ፡ የተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ ዋጋቸው ፡ መከፈሉን ፤

(ረ) አክሲዮኑ ፡ ለማኅበሩ ፡ ባዕድ ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ መተላለፍ ፡ መቻሉን ፡ ወይም ፡ አለመቻሉን ፡ በአክሲዮኖቹ ፡ ውስጥ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፫፻፴፩ ። የባለአክሲዮኖቹ ፡ መዝገብ ።

(፩) ማናቸውም ፡ የአክሲዮን፣ ማኅበር፣ በስማቸው ፡ አክሲዮን ፡ ያላቸውን፡ሰዎች ፡ ዝርዝር ፡ የሚያመለክት ፡ መዝገብ፡በዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መያዝ ፡ አለበት።

(፪) በዚህ፣ መዝገብ፣ የባለአክሲዮኖቹ ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፡ የአክሲዮኖቹ፡ብዛትና ፡ ቍጥራቸው ፤ በየአንዱ ፡ አክሲዮን ፡ የተከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ልክና ፡ ባለአክሲዮኑ ፡ መዝገብ ፡ የገባበትን ፡ ቀን ፡ መዝገቡ ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

(፫) ባለአክሲዮን፣ የሆነው፣ ሰው ፡ መዝገቡን ፡ ገንዘብ ፡ ሳይከፍል፡ሊመለከተው ፡ ይችላል ። ሌላው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የተወሰነውን ፡ ገንዘብ ፡ ከፍሎ ፡ መዝገቡን ፡ ለማየት ፡ ይችላል ።

(፬) ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የተወሰነውን ፡ ገንዘብ ፡ ከፍሎ፡ የመዝገቡን ፡ ግልባጭ ፡ ወይም ፡ ባጭር ፡ የተውጣጣውን ፡ ጽሑፍ ፡ ለመቀበል ፡ ይችላል ። ጥያቄው ፡ ባንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ሊፈጸምለት ፡ ይገባል ።

(፭) ማናቸውም፡ ጥቅም፡ ያለው፡ ሰው ፤ ወይም፡ ማኅበረተኛ፡ ወይም፡ ማኅበሩ፡ ራሱ፡ በመዝገቡ ፡ አጻጻፍ ፡ ላይ ፡ ስሕተቶች ፡ መኖራቸውን ፡ የተመለከተ ፡ እንደ፡ሆነ፡ እንዲስተካከል ፡ ለማድረግ ፡ ለንግድና ፡ እንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ ማመልከት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፫፻፵፪ ። ማኅበሩ ፡ የራሱ ፡ የሆኑትን ፡ አክሲዮኖች ፡ ስለ ፡ መግዛት ።

(፩) ማኅበሩ ፡ የራሱ ፡ የሆኑትን ፡ አክሲዮኖች ፡ ለመግዛት ፡ የሚችለው ፤

(ሀ) የባለአክሲዮኖች ፡ ጉባኤ ፡ ለመግዛት ፡ ፈቅዶለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) የሚገዛውም ፡ በደንብ ፡ በሒሳብ ፡ ከታወቀው ፡ ከተጣራ ፡ ትርፍ ፡ ላይ ፡ በተነሣ ፡ ገንዘብ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ሐ) የአክሲዮኖቹም ፡ ዋጋ፡ በሙሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ተከፍሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) በእንደዚህ፡ ያለ ፡ አኳኋን፡ የተገዙትን ፡ አክሲዮኖች ፤ አስተዳዳሪዎቹ ፡ ሊያዙ ባቸው ፡ አይችሉም ፤ እንዲሁም ፡ የማኅበሩ ፡ ሀብት ፡ ሆነው ፡ እስከሚቈዩበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የየአክሲዮኖቹ ፡ የድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብት ፡ ታግዶ ፡ ይቈያል ።

(፫) ማኅበሩ፡ አክሲዮኑን፡ የገዛው ፤ የድንገተኛው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ የማኅበሩን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ እንዲቀነስ ፡ በወሰነው ፡ መሠረት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

(፬) ማኅበሩ፡ የራሱ፡ የሆኑትን ፡ አክሲዮኖች ፡ በመያዣ ፡ ለመቀበል፡የፈለገ፡እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፫፻፵፫ ። አክሲዮኖችን ፡ እንደ ፡ ፈለጉ ፡ ማስተላለፍን ፡ የሚቀንስ ፡ ሁኔታ ።

(፩) በመተዳደሪያ፡ ደንብ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ድንገተኛ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ በሚያደርገው ፡ ውሳኔ ፡ አክሲዮኖችን ፡ እንደ ፡ ፈቀዱ ፡ እንዳይተላለፉ ፡ ለመወሰን ፡ ይቻላል ።

(፪) የማኅበሩ ፡ አስተዳደር ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አክሲዮኖችን ፡ ለማስተላለፍ ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲፈቅድ ፡ ያስፈልጋል ፡ የሚለው ፡ ድንጋጌ ፡ የሚጸናው ፤

(ሀ) ለማኅበሩ ፡ ወይም ፡ ለማኅበረተኞቹ ፡ ወይም ፡ ከነዚሁ ፡ ለአንዱ ፡ በቀደምትነት ፡ መልሶ ፡ የመግዛት ፡ መብት ፡ የተጠበቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

(ለ) ይህም ፡ መብት ፡ የሚሠራበት ፡ አኳኋንና ፡ የሚገዛበት ፡ ዋጋው ፡ ተወስኖ ፡ ተጽፎበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፫) በማናቸውም፡ አኳኋን፡ ቢሆን ፡ የተወሰኑት ፡ ሁኔታዎችና ፡ ዋጋ፡አክሲዮኑን ፡ ማስተላለፍ ፡ የሚከለክሉና ፡ ወይም ፡ በባለአክሲዮኑ ፡ ከባድ ፡ ጉዳት ፡ የሚያደ

ርሱበት ፡ እንዳይሆን ፡ ያስፈልጋል ።

(፬) መልሶ ፡ የመግዛት የቀደሚነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ለማኅበሩ ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ ሆነ፡ አክሲዮኖቹን፡ የሚገዛው ፡ ተቀማጭ ፡ በሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ነው።

ቍ ፡ ፫፻፴፬ ። አንድ ፡ ማኅበር የራሱ ፡ ከሆኑት ፡ አክሲዮኖች ፡ ብድር ፡ መስጠትን ፡ መከልከል ።

አንድ፡ ማኅበር፡ ለሌሎች፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች፡ የራሱ፡ ከሆኑት፡ አክሲዮኖች፡ ላይ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ አክሲዮኖቹን ፡ እንዲገዛበት ፡ ብድር ፡ መስጠት፡ክልክል ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፴፭ ። የአክሲዮኖቹ ፡ ዐይነት ።

(፩) የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ፡ ጽሑፍ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ የሚለውጠው፡የጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ብዙ ፡ ዐይነቶች ፡ አክሲዮኖች፡ እንዲወጡ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

(፪) በያንዳንድ፡ የአክሲዮን፡ ዐይነት ፡ ውስጥ ፡ አክሲዮኖቹ ፡ የተጻፈባቸው ፡ ዋጋ፡ እኩል ፡ እንዲሆንና ፡ ለባለአክሲዮኖቹም ፡ ትክክለኛ ፡ መብት ፡ የሚሰጡ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።

(፫) ለዚሁ ፡ ለተመለከተው ፡ ለአክሲዮን ፡ ዐይነት ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ በሆኑት ፡ ልዩ ፡ ጉባኤ ፡ ፈቃድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለዚሁ ፡ የአክሲዮን ፡ ዐይነት ፡ የተሰጡትን ፡ መብቶች ፡ ለመለወጥ አይቻልም ። ይህም ፡ ልዩ ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔውን ፡ የሚሰጠው ፡ አለዋወጡን ፡ የወሰነው ፡ የባለአክሲዮኖች ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ባደረገው ፡ አሠራር ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፴፮ ። ልዩ ፡ መብት ፡ ስላላቸው ፡ አክሲዮኖች ።

(፩) በአክሲዮን ፡ የተቋቋመ ፡ ማኅበር ፡ ማናቸውም ፤ በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ ድንገተኛው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ በሚያደርገው ፡ ውሳኔ ፡ ከሌሎች ፡ አክሲዮኖች ፡ የተለየ ፡ ጥቅም ፡ ያላቸው ፡ ወደፊት ፡ ለሚወጡት ፡ አክሲዮኖች ፡ በቀደምትነት ፡ የመግዛት ፡ መብት ፡ ወይም ፡ ከትርፉ ፡ ወይም ፡ ከማኅበሩ፡ንብረት ፡ ወይም ፡ ከሁለቱም ፡ ላይ ፡ የቀደምትነት ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ማግኘት ፡ ያሉ፡ልዩ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ልዩ ፡ አክሲዮኖች ፡ ለማውጣት ፡ ይቻላል ።

(፪) በድምፅ ፡ መስጠት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ መብት፡ የሚሰጣቸው፡ አክሲዮኖችን ፡ ማውጣት ፡ ክልክል ፡ ነው ።

(፫) በቍጥር፡ ፫፻፷፭፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፫፡ የተመለከተው ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ፡በትርፍ፡ አከፋፈልና ፡ ማኅበሩ ፡ ሲፈርስ ፡ በዋና ፡ ገንዘብ ፡ አመላለስ ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ አክሲዮኖች ፡ ድምፅ ፡ የሚሰጡት ፡ በድንገተኛው ፡ ጉባኤ ፡ ሥልጣን፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ጉዳዮች ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ፡ጽሑፍ፡ ውስጥ ፡ ለመወሰን ፡ ይቻላል ።

(፬) በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፫ ፡ መሠረት ፡ የድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብት ፡ የተቀነሰባቸው ፡

አክሲዮኖች ፡ ቍጥር ፡ ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ግማሽ ፡ ለመብለጥ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፫፻፴፯ ። ትርፍ ፡ ብቻ ፡ የሚያስገኙ ፡ አክሲዮኖች ።

(፩) አንድ ፡ ማኅበር ፡ ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ ሳይቀንስ ፡ ካገኘው ፡ ትርፍን ፡ ወይም ፡ ካስቀመጠው ፡ መጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፡ ለባለአክሲዮኖቹ ፡ በአክሲዮኑ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመመለስ ፡ ይችላል ።

(፪) እንደዚህ ፡ በማድረግ፡ ገንዘብ፡ የተመለሰላቸው፡ ባለአክሲዮኖች፡ ትርፍ ፡ ብቻ፡ የሚያስገኙ ፡ አክሲዮኖችን ፡ ይቀበላሉ ። እነዚህ ፡ አክሲዮኖች ፡ ግን ፡ በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ የተወሰነውን ፡ የአክሲዮን ፡ ወለድ ፡ እንደዚሁም ፡ ማኅበሩ፡ ሲፈርስ ፡ ገቢ ፡ የተደረጉትን ፡ መዋጮ ፡ ለመውሰድ ፡ መብት ፡ የላቸውም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብት ፡ አላቸው ፤ እንዲሁም ፡ ከአክሲዮኑ ፡ ወለድ ፡ በላይ ፡ ለሆነው ፡ ትርፍና ፡ ማኅበሩም ፡ ሲጣራ ፡ በሚተርፈው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ የመክፈል ፡ መብት ፡ አላቸው ።

ቍ ፡ ፫፻፴፰ ። የገንዘብ ፡ አክሲዮኖች ፡ አከፋፈል ።

(፩) የገንዘብ ፡ አክሲዮኖች፡ በሚገዙበት፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከተጻፈባቸው፡ ዋጋ ፡ አንድ ፡ ሩብ ፤ ወይም ፡ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ እንደ ፡ ተወሰነው ፡ ምቹ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ከተጻፈባቸው ፡ በላይ ፡ የሆነው ፡ ዋጋ ፡ በሙሉ ፡ መከፈል ፡ አለበት ። ዋጋቸው ፡ በሙሉ ፡ እስኪከፈል ፡ ድረስ ፡ አክሲዮኖቹ ፡ በማኅበሩ ፡ ስም ፡ መቈየት ፡ አለባቸው ።

(፪) ማኅበሩ፡ በንግድ፡ መዝገብ ፡ ከተመዘገበበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ቢበዛ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ቀሪው ፡ በየጊዜው ፡ መከፈል ፡ አለበት ።

(፫) ይህ ፡ የንግድ ፡ ሕግ፡ ከመጽናቱ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ ማኅበሮች ፡ ላወጡት ፡ አክሲዮኖች ፡ አከፋፈል ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተው ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ፡ መቈጠር ፡ የሚጀመረው ፡ ሕጉ ፡ ከሚጸናበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፴፱ ። ስለ ፡ ዐይነት ፡ መዋጮ ፡ የሚሰጡ ፡ አክሲዮኖች ፡ አከፋፈል ።

(፩) በዐይነት፡ መዋጮ፡ የተገዙ ፡ አክሲዮኖች ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ማኅበሩ ፡ ሲቋቋም ፡ ወይም ፡ እጅግ ፡ ቢዘገይ ፡ ማኅበሩ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ እስከ ፡ ተመዘገበበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በሙሉ ፡ መከፈል ፡ አለባቸው ።

(፪) እነዚህም ፡ ከቀረው ፡ ካርኔ ፡ ላይ ፡ የማይነጠሉትና ፡ ለማስተላለፍ ፡ የሚቻለው ፡ መመዝገቢያው ፡ ከተፈጸመ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፵ ። አክሲዮኖችን ፡ ማስተላለፍ ።

(፩) ላምጪው፡ ተብሎ፡ የተጻፈባቸው ፡ አክሲዮኖች ፡ ያላንዳች ፡ ዐይነት፡አሠራር፡

(ፎርማሊቴ) ፡ አክሲዮኑን ፡ በመስጠት ፡ ብቻ ፡ ይተላለፋሉ ።

(፪) ሌላ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ እነዚህ ፡ አክሲዮኖች ፡ ለትርፍ ፡ አከፋፈል ፡ ወይም ፡ መልሶ ፡ ገንዘቡን ፡ ለመክፈል ፤ ወይም ፡ ለጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ አባል ፡ ለመሆን ፡ ለያዛቸው ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ።

(፫) ላምጪው፡ የተባሉ ፡ አክሲዮኖች ፡ ሲጠፉ ፡ ወይም ፡ ሲሰረቁ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፴፩ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፵፭ ። ስም ፡ የተጻፈባቸውን ፡ አክሲዮኖች ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።</u>

(፩) ስም፡ የተጻፈባቸው፡ አክሲዮኖች ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ መሆናቸው ፡ የሚረጋገጠው ፡ በማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚገኘው ፡ መዝገብ ፡ በሚያመለክተው ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) እነዚህን ፡ አክሲዮኖች ፡ ለማስተላለፍ ፡ የሚቻለው ፡ በተባለው ፡ መዝገብ ፡ መተላለፋቸው ፡ ከተመዘገበ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፵፮ ። የገንዘብ ፡ ማስገቢያ ፡ ጥያቄ ፡ አላፊነት ።</u>

(፩) የአክሲዮኖቹ፡ ባለይዞታዎች ፤ በየጊዜው፡ የተላለፈላቸው ፡ ሰዎችና ፡ ለመግዛት ፡ የፈረሙ ፡ ሰዎች ፡ ለአክሲዮኑ ፡ ዋጋ ፡ ባንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ አላፊዎች ፡ ናቸው ።

(፪) ማንኛውም፣ ለመግዛት ፡ የፈረመ ፡ ሰው፡ ወይም ፡ ባለአክሲዮን ፡ የሆነ፡ ሰው፡ ባለቤትነቱን፣ ያስተላለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ካስተላለፈበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ሁለት፡ ዓመት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ገና ፡ ላልተከፈለው ፡ ገንዘብ፡አላፊነት ፡ የለበትም ።

(፫) ቀሪውን ፡ ገንዘብ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ያልከፈለ፡ ባለአክሲዮን ፡ በማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ የተለየ ፡ የወለድ ፡ ልክ ፡ ካልተወሰነ ፡ በቀር ፡ ሕጋዊ ፡ ወለድ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፬) ደግሞም፡ ማኅበሩ፡ ረኮማንዲ ፡ በሆነ ፡ ደብዳቤ ፡ እንዲከፍል፡ማስጠንቀቂያ ፡ ለባለአክሲዮኑ ፡ ከደረሰው ፡ ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፤ ገንዘቡን ፡ ባልከፈለው ፡ ባለአክሲዮን ፡ ዋጋቸው ፡ በሙሉ ፡ ያልተከፈለውን ፡ አክሲዮኖች ፡ በሐራጅ ፡ ለመሸጥ ፡ ይችላል ። እነዚህ ፡ አክሲዮኖች ፡ ተሰርዘው ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ አክሲዮኖች ፡ ለገዢው ፡ ይሰጣሉ ።

(፭) ገዢ ፡ ባለመገኘቱም ፡ ምክንያት ፡ ለመሸጥ ፡ ካልተቻለ ፡ የማኅበሩ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ አክሲዮኖቹን ፡ ወርስ ፡ አድርገውና ፡ የማኅበረተኛውን ፡ ስም ፡ ሰርዘው ፡ ተጨማሪ ፡ ኪሣራ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ሳይነካ ፤ የተከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ለማስቀረት ፡ ይችላሉ ።

(፮) ያልተከፈለባቸው ፡ አክሲዮኖች ፡ ውርስ ፡ እንዲሆኑ ፡ በተወሰነበት ፡ የሒሳብ ፡ ማጠቃለያ፣ ዓመት፣ ውስጥ፡ ያልተሸጡት፡ አክሲዮኖች፣ ያልተሠራባቸው፣ እንደ፡ ሆነ፣ ተሰርዘው፡ ዋናውም፡ ገንዘብ፣ በነሱ፣ ዋጋ፣ መጠን፣ ተቀናሽ፡ መሆን፣ አለበት ።

(፯) የገንዘብ ፡ መክፈያውን ፡ ጊዜ ፡ ያሳለፈ ፡ ማኅበረተኛ ፡ በጉባኤው ፡ ውስጥ ፡ በድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብቱ ፡ ሊሠራበት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፫፻፴፫ ። ለጊዜው ፡ የሚሰጥ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ።

(፩) ላምጪው ፡ ተብሎ ፡ ለተጻፈባቸው ፡ አክሲዮኖች ፡ ለጊዜው ፡ ላምጪው ፡ ተብሎ ፡ የተሰጠ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ለመስጠት ፡ የሚቻለው ፡ የአክሲዮኑ ፡ ዋጋ ፡ በሙሉ ፡ ተከፍሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፤ ገንዘቡ ፡ በሙሉ ፡ ከመከፈሉ ፡ በፊት ፡ የተሰጡት ፡ የምስክር ፡ ወረቀቶች ፡ ዋጋ ፡ የላቸውም ።

(፪) ላምጪው ፡ ተብለው ፡ ለተጻፉት ፡ አክሲዮኖች ፡ ለጊዜው ፡ በባለአክሲዮኑ ፡ ስም ፡ የተመዘገበ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ የተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባለሀብትነታቸውን ፡ ለማስተላለፍ ፡ የሚቻለው ፡ ዕዳን ፡ ለማስተላለፍ ፡ በተደነገገው ፡ ሥርዓት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፫) ስም ፡ ለተጻፈባቸው ፡ አክሲዮኖች ፡ ለጊዜው ፡ የሚሰጥ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ የተመዘገበ ፡ መሆን ፡ አለበት ። አስተላለፋቸውም ፡ ለነዚሁ ፡ አክሲዮኖች ፡ በተወሰነው ፡ ድንጋጌ ፡ ይመራል ።

ቍ ፡ ፫፻፴፬ ። አንድ ፡ ማኅበር ፡ በሌላ ፡ ማኅበር ፡ ተካፋይ ፡ ስለ ፡ መሆን ።

(፩) የአንዱ ፡ ማኅበር ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ዐሥር ፡ በመቶ ፡ ወይም ፡ ከዚሁ ፡ በበለጠው ፡ የሌላ ፡ ማኅበር ፡ ሀብት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ በሁለተኛው ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ የመጀመሪያው ፡ ማኅበር ፡ አክሲዮኖች ፡ ሊኖሩት ፡ አይችልም ።

(፪) ሁለት ፡ ማኅበሮች ፡ አክሲዮናቻቸውን ፡ የተገዛዙ ፡ ሲሆን ፡ አንዱ ፡ ማኅበር ፡ ከሌላው ፡ ማኅበር ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ ከመቶ ፡ ዐሥር ፡ ወይም ፡ በላይ ፡ የገዛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ማኅበሮቹ ፡ የተገዛዙትን ፡ ለንግድና ፡ ለእንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ፤ ሚኒስቴሩም ፡ የተገዛዙትን ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ በተወሰነው ፡ ልክ ፡ ተስማምተው ፡ እንዲቀንሱ ፡ ይጠይቃቸዋል ። በሁለቱም ፡ ማኅበሮች ፡ መካከል ፡ ስምምነትን ፡ ለማግኘት ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ ካንደኛው ፡ ማኅበር ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ አነስተኛ ፡ ይዞታ ፡ ያለውን ፡ ማኅበር ፡ ይዞታውን ፡ እንዲሸጥ ፡ ያዝዛል ።

(፫) አንዱ ፡ ማኅበር ፡ ባንዱ ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የዋና ፡ ገንዘብ ፡ ተካፋይነት ፡ ትክክል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ አንዱ ፡ ማኅበር ፡ የያዘውን ፡ የሌላውን ፡ አክሲዮኖች ፡ ለመሸጥ ፡ ያልተስማማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ከዋና ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ ድርሻውን ፡ ዐሥር ፡ ከመቶ ፡ በታች ፡ መቀነስ ፡ አለበት ።

(፬) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ ወይም ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፫ ፡ የተመለከተውን ፡ የፈጸሙ ፡ ለመሆናቸው ፡ ማኅበሮቹ ፡ ለንግድና ፡ ለኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ በሙሐላ ፡ የሆነ ፡ መግለጫ ፡ መስጠት ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፫፻፵፭ ። አክሲዮኖቹ ፡ የሚያስገኟቸው ፡ መብቶች ።

(፩) እያንዳንዱ ፡ አክሲዮን ፡ የተጣራ ፡ ከሆነ ፡ ከዓመት ፡ ትርፍ ፡ ድርሻና ፡ እንዲሁም ፡ ማኅበሩ ፡ ሲፈርስ ፡ ከተጣራው ፡ ድርሻ ፡ የማግኘትን ፡ መብት ፡ ይሰጣል ።

(፪) በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በማኅበሩ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ተቃራኒ ፡ ውሳኔዎች ፡ ከሌሉ ፡ በቀር ፤ የትርፉ ፡ ድርሻዎችና ፡ ማኅበሩ ፡ ሲፈርስ ፡ ከተጣራው ፡ ድርሻ ፡ ለማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ በተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ይታሰባሉ ።

(፫) በቍጥር ፡ ፫፻፵፮ ፡ የተመለከቱት ፡ ውሳኔዎች ፡ ሳይነኩ ፡ ማናቸውም ፡ አክሲዮን ፡ ሁሉ ፡ የድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብትን ፡ ይሰጣል ።

(፬) ባለአክሲዮኖች ፡ ሁሉ ፡ በአክሲዮኖቻቸው ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲጨመር ፡ ለማድረግ ፡ የወጡትን ፡ በገንዘብ ፡ የሆኑ ፡ አክሲዮኖችን ፡ ፈርመው ፡ እንዲገዙ ፡ የቀደምትነት ፡ መብት ፡ አላቸው ።

(፭) ይህ ፡ መብት ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፸ ፡ እና ፡ በሚቀጥሉት ፡ በተወሰኑት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ ይከናወናል ።

(፮) ልዩ ፡ መብት ፡ ላላቸው ፡ አክሲዮኖች ፡ ባለሀብት ፡ ለሆኑት ፡ በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በማኅበሩ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንቦች ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ውሳኔ ፡ እነዚሁ ፡ መብቶች ፡ ሊጠበቅላቸው ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፫፻፵፮ ። የመሥራቾችና ፡ የአስተዳዳሪዎች ፡ አላፊነት ።

መሥራቾችና ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፱ ፡ በተነገረው ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ በዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ ለተሰጡት ፡ ድንጋጌዎች ፡ አጠባበቅ ፡ ለማኅበሩና ፡ ለሦስተኞች ፡ ወገኖች ፡ ባንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ አላፊዎች ፡ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## ስለ ፡ አስተዳዳሪዎች ፤ ሒሳብ ፡ አጣሪዎችና ፡ የባለአክሲዮኖች ፡ ጉባኤ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ።

ቍ ፡ ፫፻፵፯ ። ስለ ፡ አስተዳዳሪዎች ።

(፩) የማኅበሩ ፡ አስተዳደር ፡ ሥራ ፡ ለማኅበረተኞች ፡ እንጂ ፡ ለሌላ ፡ ሊሰጥ ፡ አይቻልም ።

(፪) ማኅበሩ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ሦስት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ሊኖሩት ፡ ይገባል ። ግን ፡ ከአሥራ ፡ ሁለት ፡ የበለጠ ፡ ሊኖሩት ፡ አይችልም ፤ እነዚሁም ፡ የአስተዳዳደር ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ (ቦርድ) ፡ ይባላሉ ።

(፫) የመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ የአስተዳዳሪዎችን ፡ ቍጥር ፡ ሳይወስን ፡ በከፍተኛና ፡ በአነስተኛ ፡ ብቻ ፡ የወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መጀመሪያ ፡ አክሲዮን ፡ ለመግዛት ፡ በፈረሙ ፡ ሰዎች ፡ ጉባኤ ፡ ይወሰነዋል ።

(፬) በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጣቸው ፡ ማኅበሮች ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። ግን ፡ አንድ ፡ የአስተዳደር ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ አካል ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ አለበት ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፵፫ ። ፕሬዚዳንት ፤ ዋና ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፤ ጸሐፊ ።</u>

(፩) የባለአክሲዮኖች ፡ ወይም ፡ መጀመሪያ ፡ አክሲዮን ፡ ለመግዛት ፡ በፈረሙ ፡ ሰዎች ፡ ጉባኤው ፡ ያልመረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአስተዳደር ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ ከአባሎቹ ፡ አንዱን ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ይመርጣል ።

(፪) ምክር ፡ ቤቱ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ፕሬዚዳንቱን ፡ ሊሽረው ፡ ይችላል ።

(፫) የአስተዳደሩ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ዋና ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ይሾማል ፤ የአንቀጽ ፡ መጽሐፍ ፡ ቍ ፡ ፴፬ ፤ ፴፭ ፤ ፺፱ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፤ (ሪ) ቍ ፡ ፶፳፩ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፫ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፬) ዋናውም ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ የማኅበሩ ፡ ሠራተኛ ፡ ነው ፡ አስተዳዳሪም ፡ ላይሆን ፡ ይችላል ።

(፭) የአስተዳደሩ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ጸሐፊ ፡ ሊመርጥ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፵፬ ። የዋስትና ፡ አክሲዮኖች ።</u>

(፩) አስተዳዳሪዎቹም ፡ የመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ በወሰነው ፡ ልክ ፡ በስማቸው ፡ የተመዘገቡትን ፡ አክሲዮኖች ፡ በማኅበሩ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ ማስቀመጥ ፡ አለባቸው ።

(፪) እነዚህ ፡ አክሲዮኖች ፡ የአስተዳዳሪው ፡ ሥራዎች ፡ እስከ ፡ ቈነበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስና ፡ በአስተዳዳሪነታቸው ፡ ስላለባቸው ፡ አላፊነት ፡ እስኪያስረዱ ፡ ድረስ ፡ አክሲዮኖቹ ፡ ሊመለሱላቸው ፡ አይችሉም ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፵፭ ። የአስተዳዳሪዎች ፡ መሾም ።</u>

(፩) የመጀመሪያዎቹ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በማስተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ለመመረጥ ፡ ይችላሉ ፤ ይኸውም ፡ ምርጫ ፡ እንዲጸና ፡ መጀመሪያ ፡ አክሲዮን ፡ ለመግዛት ፡ ለፈረሙ ፡ ሰዎች ፡ ጉባኤ ፡ ይቀርባል ። ይህ ፡ ምርጫ ፡ ያልጸና ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጉባኤው ፡ ሌሎች ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ይመርጣል ።

(፪) ወደፊት ፡ የሚመረጡት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ በጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ይመረጣሉ ።

BACK



(፫) በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ የአስተዳዳሪዎቹ ፡ ሹመት ፡ የሚጸናው ፡ ለሦስት ፡ ዓመት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፬) በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ተቃራኒ ፡ ውሳኔዎች ፡ ከሌሉ ፡ በቀር ፡ እንደገና ፡ ሊመረጡ ፡ ይችላሉ ።

(፭) የሚመረጡት ፡ ከሁለት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ በላይ፡ የሆኑ ፡ እንደሆነ ፡ ምርጫው፡ ባንድነት ፡ ሳይሆን ፡ ድምፅ ፡ የሚሰጠው ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ በተለይ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፶፩ ። የአስተዳዳሪዎች ፡ መለወጥ ።

(፩) በሥራው ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ የጐደሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቀሩት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ምትኮቻቸውን ፡ ይመርጣሉ ። የተመረጡት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ውክልና ፡ የሚያልቀው ፡ ከነርሱ ፡ በፊት ፡ ለነበሩት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ የተሰጠው ፡ የውክልና ፡ ጊዜ ፡ በሚያልቅበት ፡ ጊዜ ፡ ነው።

(፪) በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ እነዚህን ፡ ምርጫዎች ፡ ለማጽደቅ ፡ ለሚቀጥለው፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ። ጉባኤውም ፡ የነዚሁን ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ምርጫ ፡ ለማጽደቅ ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ አስተዳዳሪዎችን ፡ ሊመርጥ ፡ ይችላል ። ሌሎችም ፡ አስተዳዳሪዎችን ፡ የመረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) መሠረት ፡ ተሹመው ፡ በተጠባባቂነት ፡ ጊዜ ፡ የተደረጉት ፡ ሥራዎች ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ ይሆናሉ ።

(፫) በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ቀሪ ፡ የሆኑት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ቍጥር ፡ ከምክር ፡ ቤቱ ፡ አባሎች ፡ ከግማሽ ፡ በታች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ አስፈላጊውን ፡ ምርጫ ፡ ለማድረግ ፡ ጠቅላላውን ፡ ጉባኤ፡ መጥራት ፡ አለባቸው ።

(፬) አስተዳዳሪዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ሥራቸውን ፡ የተዉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሌሎች ፡ አስተዳዳሪዎችን ፡ ለመምረጥ ፡ ተቈጣጣሪዎቹ ፡ ጠቅላላውን ፡ ጉባኤ ፡ በሚያስቸኩል ፡ አኳኋን ፡ መጥራት ፡ አለባቸው ።

(፭) በንኡስ፡ ቍ፡ (፬) መሠረት ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ፡ እስኪሰበሰብ ፡ ድረስ ፡ ተቈጣጣሪዎቹ ፡ የአስተዳደርን ፡ ሥራዎች ፡ መፈጸም ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፫፻፶፪ ። ስለ ፡ አነስተኛ ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ መብት ።

ልዩ፡ ልዩ ፡ የሆነ፡ ብዙ ፡ የባለአክሲዮኖች ፡ ክፍል ፡ (ግሩፕ) ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታቸውም ፡ የተለየ ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለአስተዳደር ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ እንደራሴ ፡ እንዲመርጡ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ የማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ያረጋግጥላቸዋል ።

ቍ ፡ ፫፻፶፫ ። የሥራ ፡ ዋጋ ።

(፩) አስተዳዳሪዎች ፡ በጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነና ፡ በዋናው ፡ ወጪ ፡ ውስጥ፡ የሚታሰብ ፡ በዓመት ፡ የተወሰነ ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ መቀበል ፡ ይችላሉ ።

(፪) ከዚህም ፡ በላይ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ከዓመት ፡ ሥራው ፡ የተጣራ ፡ ትርፍ ፡ ላይ ፡ የተወሰነ ፡ ድርሻ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ ሊወሰን ፡ ይችላል ።

(፫) ለአስተዳዳሪዎቹ ፡ የተወሰነው ፡ የሥራው ፡ ዋጋና ፡ የትርፉ ፡ ድርሻ ፡ የሚሰጠው ፡ በጠቅላላው ፡ ነው ። ምክር ፡ ቤቱም ፡ ለአባሎቹ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ እንደሚታየው ፡ ያከፋፍላቸዋል ።

(፬) ከተጣራው ፡ ትርፍ ፡ ላይ ፡ የሚሰጣቸው ፡ ድርሻ ፡ በመቶ ፡ ከዐሥር ፡ ለመብለጥ ፡ አይችልም ። ይኸውም ፡ ድርሻ ፡ የሚታሰበው ፡

(ሀ) በሕጉ ፡ ወይም ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንቡ ፡ እንደ ፡ ተጸፋት ፡ ለመጠባበቂያ ፡ የሚሆኑ ፡ ገንዘቦች ፤

(ለ) በመተዳደሪያ ፡ ደንቡ ፡ ተመልክቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚሁ ፡ የተመለከተው ፡ ድርሻ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከአክሲዮኖቹ ፡ ውስጥ ፡ ዋጋቸው ፡ ተመላሽ ፡ ያልሆነና ፡ በሙሉ ፡ ከተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ከመቶ ፡ አምስት ፤

(ሐ) ተጠባባቂ ፡ ሆኖ ፡ እንዲቋቋም ፡ በጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነው ፡ መጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፤

(መ) ካመት ፡ ወደ ፡ ዓመት ፡ የተላለፈው ፡ ገንዘብ ፤ ከተቀነሰ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

(፭) ለአስተዳዳሪዎች ፡ የሚደርሰውን ፡ ትርፍ ፡ ድርሻ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፬ ፡ መሠረት ፡ ለመወሰን ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ እንዲጸና ፡ ከተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ለተሠሩት ፡ ሥራዎች ፡ ድርሻዎች ፡ ከሆኑት ፡ በቀር ፡ የተከፈሉ ፡ ወይም ፡ ካለፉት ፡ የሒሳብ ፡ ማጠቃለያ ፡ ዘመን ፡ ከተገኘው ፡ ትርፍ ፡ ላይ ፡ ተነሥተው ፡ ለዋናው፡ ገንዘብ ፡ የተጨመሩትን ፡ በሒሳብ ፡ ላይ ፡ ለማግባት ፡ ይቻላል ።

(፮) ከዚህም ፡ በቀር ፡ ለአስተዳዳሪዎች ፡ ከተጣራው ፡ ትርፍ ፡ ድርሻ ፡ ላይ ፡ የሚከፈለው ፡ ለባለአክሲዮኖቹ ፡ ድርሻቸው ፡ ተከፍሏቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፯) ለአስተዳዳሪዎች ፡ የሚሰጠው ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ ጠቅላላ ፡ ገንዘብ ፡ በመሥራችነታቸው ፡ ዐይነት ፡ አንዳንድ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ሊጠቀሙበት ፡ የሚችሉበትን ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ የገንዘብ ፡ ጥቅሞችን ፡ አንድነት ፡ በማሰብ ፡ የማኅበሩን ፡ አኳኋን፡ በመመልከትና ፡ ለሠራተኞቹ ፡ ከሚደርሱት ፡ ክደመወዝና ፡ ከሌሎች ፡ ጥቅሞች ፡ ከመጠን ፡ ያለፉ ፡ ሆኖ ፡ የታየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ በመቶ ፡ ዐሥር ፡ የሚደርስ ፡ አነስተኛ ፡ ገንዘብ ፡ ባላቸው ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ጥያቄ ፡ የንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይህን ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ ሊቀንስ ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፫፻፶፩ ። ስለ ፡ መሻር ።

ከዚህ ፡ ተቃራኒ ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ በጠ

BACK



ቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ሊሻሩ ፡ ይችላሉ ። መሻሩ ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ ያልያዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ አስተዳዳሪው ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፫፻፶፭ ። ውድድርን ፡ ስለ ፡ መከልከል ።

አስተዳዳሪዎቹ ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ካልፈቀደ ፡ በቀር ፡ ለራሳቸው ፡ ወይም ፡ ለሦስተኛ ፡ ሰውም ፡ ፋንታ ፡ ሆነ ፡ ከማኅበሩ ፡ ጋራ ፡ የውድድር ፡ ተግባር ፡ መሥራትና ፡ በሚወዳደሩ ፡ ማኅበሮች ፡ ውስጥ ፡ አላፊነታቸው ፡ በአንድነት ፡ ያልተከፋፈለ ፡ ሆኖ ፡ በማኅበረተኛነት ፡ ለመግባት ፡ አይችሉም ።

ቍ ፡ ፫፻፶፮ ። በማኅበሩና ፡ በአስተዳዳሪዎች ፡ መካከል ፡ የሚደረጉ ፡ ስምምነቶች ።

(፩) በማኅበሩና ፡ በአስተዳዳሪዎች ፡ መካከል ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በዘወርዋራ ፡ የሚደረገው ፡ ስምምነት ፡ ሁሉ ፡ የአስተዳደር ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲፈቅድ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ። ለዚሁም ፡ ለተቈጣጣሪዎች ፡ ማስታወቂያ ፡ ይሰጣል ።

(፪) የማኅበሩ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ለአንድ ፡ ሌላ ፡ የሥራ ፡ ድርጅት ፡ ባለሀብት ፡ የንግድ ፡ ሸሪክ ፡ (ማኅበረተኛ) ፡ ወኪል ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ወይም ፡ አስተዳዳሪ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በአንድ ፡ ማኅበርና ፡ በሌላ ፡ አንድ ፡ የሥራ ፡ ድርጅት ፡ መካከል ፡ ለሚደረገው ፡ ስምምነት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ ያለው ፡ ውሳኔ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፫) ተቈጣጣሪዎቹም ፡ በአስተዳዳሪዎች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በተፈቀዱት ፡ ስምምነቶች ፡ ላይ ፡ የተለየ ፡ ራፖር ፡ ለጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ያቀርባሉ ። ጉባኤውም ፡ በዚህ ፡ ራፖር ፡ መሠረት ፡ የፈለገውን ፡ ለመወሰን ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

(፬) ጉባኤው ፡ የተቀበላቸውን ፡ ስምምነቶች ፡ የማታለል ፡ ነገር ፡ ካልተገኘባቸው ፡ በቀር ፡ ለመቃወም ፡ አይቻልም ።

(፭) ጉባኤውም ፡ የማይቀበላቸው ፡ ስምምነቶች ፡ ውጤታቸውን ፡ አያጡም ። ከማታለል ፡ የተነሣ ፡ የሚደርሱት ፡ ጉዳቶች ፡ ሁሉ ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ አስተዳዳሪ ፡ ያልከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በአስተዳዳሪ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ አላፊነቱ ፡ ይጣላል ።

(፮) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከደንበኞቹ ፡ ጋራ ፡ ማኅበሩ ፡ በሚያደርጋቸው ፡ ደንበኛ ፡ ስምምነቶች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ አይሆኑም ።

ቍ ፡ ፫፻፶፯ ። ከማኅበሩ ፡ ዘንድ ፡ ብድር ፡ እንዳይወስዱ ፡ አስተዳዳሪዎችን ፡ ስለመከልከል ።

(፩) በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ከተሰጣቸው ፡ ድርጅቶች ፡ በቀር ፡ ያንድ ፡ ማኅበር ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ቢሆን ፡ ከማኅበሩ ፡ ዘንድ ፡ መበደር ፡ ወይም ፡ ማኅበሩ ፡ ባንክ ፡ ባለው ፡ ተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ከሦስተኛ ፡

BACK



ወገኖች ፡ ጋራ ፡ ላሉባቸው ፡ ዕዳዎች ፡ ማኅበሩን ፡ ዋስ ፡ ማድረግ ፡ ክልክል ፡ ነው ።

(፪) የሆነ፡ ሆኖ ፡ የማኅበሩ፡ ሥራ ፡ የባንክ ፡ ድርጅት፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ ያለው ፡ ክልከላ ፡ ደንበኛ ፡ በሆኑት ፡ የዘወትር ፡ የንግድ ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ አይፈጸምም ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፵፰ ። የአስተዳዳሪ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎች ።</u>

(፩) ውሳኔዎች ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ እንዲሆኑ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ካሉት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ የሚበዙት ፡ በጉባኤው ፡ እንዲገኙ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ውሳኔዎቹም ፡ የሚደረጉት ፡ ፍጹም ፡ በሆነ ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ነው ። በእንደራሴነትም ፡ ድምፅ ፡ መስጠት ፡ ይቻላል ።

(፪) የምክር ፡ ቤቱ ፡ አባል ፡ ካልሆነ ፡ ለምክር ፡ ቤቱ ፡ አባል ፡ እንደራሴ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ። እንደራሴ ፡ ለመሆን ፡ የሚችለውም ፡ ላንድ ፡ አባል ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፫) ውሳኔዎችም ፡ በፕሮሲቨርባል ፡ ተጽፈው ፡ በፕሬዚዳንቱና ፡ በአንድ ፡ ጸሐፊ ፡ ይፈረማሉ ። ፕሮሲቨርባሎችም ፡ ለዚሁ ፡ በተወሰነ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ይሆናሉ ።

(፬) የውሳኔዎችም ፡ ቅጂዎች ፡ እንዲሁ ፡ በፕሬዚዳንቱና ፡ ባንድ ፡ ጸሐፊ ፡ መፈረም ፡ አለባቸው ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፵፱ ። የአስተዳዳሪዎች ፡ መዝገብ ።</u>

(፩) ማናቸውም ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ በማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የአስተዳዳሪ ዎችንና ፡ የሥራ ፡ አስኪያጆችን ፡ የክብር ፡ መዝገባቸውን ፣ ሞያቸውን ፣ እንዲሁም ፡ በሌሎች ፡ ማኅበሮች ፡ ውስጥ ፡ ሊኖራቸው ፡ የሚችሉትን ፡ የአስተዳዳሪነት ፡ ሥራቸውን ፡ የሚያመለክት ፡ መዝገብ፡ መያዝ፡ አለበት ። አስተዳዳሪው ፡ አንድ፡ ማኅበር፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ግን ፡ የማኅበሩ ፡ መጠሪያ ፡ ስሙና ፡ ዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አድራሻ ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

(፪) በዚሁ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የተመዘገቡትን ፡ ሐተታዎች ፡ እንዲሁም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚደረገውን ፡ መሻሻል ፡ ሁሉ ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ ከተጻፋበት ፡ ጀምሮ ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ማስታወቅ ፡ ይገባል ።

(፫) ይህን ፡ መዝገብ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፴፩ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፫ ፡ በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት፡ ማኅበረተኛው ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሁሉ፡ ሊያየው ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፶ ። አስተዳዳሪዎች ፡ የሚይዙት ፡ የአክሲዮኖችና ፡ የግዴታ ፡ ወረቀት ፡ መዝገብ ።</u>

(፩) ማናቸውም ፡ ማኅበር ።

(ሀ) በማኅበሩ ፡

(ለ) በተነጣዩ ፡ ማኅበሮች ፤

(ሐ) እርሱ፡ ራሱ ፡ ተነጣይ ፡ በሆነበት ፡ በሆልዲንግ ፡ ማኅበር ፤ ውስጥ ፡ እያንዳንዱ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ያሉዋቸውን ፡ አክሲዮኖች ፡ ቍጥርና ፡ ዋጋቸውን ፡ የሚያመለክት ፡ መዝገብ ፡ በዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መያዝ ፡ አለበት ።

(፪) የዓመት ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ መዝገብና ፡ አስፈላጊ ፡ ከሆኑት ፡ ሰነዶች ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ ለጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ የሚቀርቡትን ፤ የማኅበሩን ፡ አክሲዮኖች ፡ ወይም ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶችን ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ለማየት ፡ ይችላል ።

(፫) ከዚህ፡ ጊዜ ፡ ውጭ ፡ መዝገቡን፡ የንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ወኪል ፡ ሊያየው ፡ ይችላል ። ይህም ፡ የሚኒስቴሩ ፡ ወኪል ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የመዝገቡን ፡ ግልባጭ ፡ ወይም ፡ ባጭር ፡ የተወጣጣውን ፡ ጽሑፍ ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፬) የአስተዳዳሪዎችም ፡ መዝገብ ፡ ለዓመቱ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፤ ቀርቦ ፡ በስብሰባው ፡ ጊዜ ፡ በዚሁ ፡ ጉባኤ ፡ የሚገኘው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሊያየው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፭ ። ስለ አስተዳዳሪዎች ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ የሚሰጡ ፡ መግለጫዎች ።**

(፩) ለዓመቱ፡ ጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ በሚቀርቡት ፡ የሒሳብ ፡ ማመዛዘኛ ፡ ውስጥ ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ ለሥራቸው ፡ ዋጋ ፤ ለልዩ ፡ ወጪ ፤ ለጡረታ ፤ በየጊዜው ፡ የሚከፈል፡ ገንዘብ ፡ የተከፈላቸውን ፤ በዐይነት ፡ የሚያገኙአቸው ፡ ጥቅሞች ፡ ጠቅላላ ፡ ድምር ፡ መኖር ፡ አለበት ።

(፪) ለአስተዳዳሪዎች ፡ ብድር ፡ ወይም ፡ ዋስትና ፡ ተደርጎላቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እነዚህን ፡ የሚገልጹ ፡ ማስረጃዎች ፡ መኖር ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፮ ። የአስተዳዳሪዎች ፡ ግዴታዎች ።**

በቍጥር ፡ ፫፻፷፬ ፡ እንደተመለከተው ፡ ያለባቸው ፡ ጠቅላላ ፡ የጥንቃቄ ፡ ግዴታ ፡ ሳይነካ ፤ አስተዳዳሪዎች ፤

(ሀ) ስለ ፡ አስተዳደርና ፡ ስለ ፡ ጉባኤዎች ፡ ፕሮሴቬርባሎች ፡ ደንበኛ ፡ አያያዝ ፤

(ለ) ስለ ፡ ሒሳብ ፡ አሠራርና ፡ ስለ ፡ ሒሳብ ፡ መዝገቦች ፡ አያያዝ ፤

(ሐ) ሒሳቦችን ፡ ለተቈጣጣሪዎች ፡ ስለ ፡ ማቅረብና ፡ የሥራውን ፡ አካሄድ ፡ የገንዘብን ፡ ሁኔታ ፡ የሚገልጥ ፡ ራፖር ፡ ለጉኤባው ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ፤

(መ) በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ እንደተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ለጉባኤው ፡ ጥሪ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፤

(ሠ) ከዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ሦስት ፡ ሩብ ፡ የጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ በሚያስቸኩል ፡ አኳኋን ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ ጥሪ ፡ ማድረግ ፤

BACK



(ረ) በሕጉ ፡ ወይም ፡ በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ የተደነገጉትን ፡ መጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲደራጅ ፡ ለማድረግ ፤

(ሰ) ማኅበሩ ፡ ዕዳ ፡ መክፈሉን ፡ የተወ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ጋራ ፡ የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ እንዲደረግ ፡ ወይም ፡ የመክሠር ፡ ሥነ ፡ ሥር ዐት ፡ እንዲከፈት ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማመልከት ፡ አላፊነት ፡ አለባቸው ።

ቊ ፡ ፫፻፷፫ ። የአስተዳዳሪዎች ፡ ሥልጣን ።

(፩) የአስተዳዳሪዎቹ ፡ ሥልጣን ፡ በሕግ ፤ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በማኅበሩ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ወይም ፡ በባለአክሲዮኖች ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔዎች ፡ የሚሰጠው ፡ ነው ።

(፪) የማኅበሩ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ በአንድነት ፡ ሥራውን ፡ የሚ ያካሂዱና ፡ ስለ ፡ ማኅበሩም ፡ እንደራሴ ፡ መሆናቸውን ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ለዚሁ ፡ ተግባር ፡ በተለይ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ መለየት ፡ አለበት ።

(፫) ለማኅበሩ ፡ እንደራሴ ፡ ለመሆን ፡ የተፈቀደላቸው ፡ ሰዎች ፡ በዚሁ ፡ ማኅበር ፡ ስም ፡ ለማኅበሩ ፡ ጕዳይ ፡ አፈጻጸም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ በእንደራሴነት ፡ ስም ፡ ለመሥራት ፡ መብት ፡ አላቸው ። ሥልጣናቸው ፡ የተወሰነ ፡ ቢደረግም ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ባላቸው ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ዘንድ ፡ ውጤት ፡ የለውም ።

ቊ ፡ ፫፻፷፬ ። አስተዳዳሪዎች ፡ ለማኅበሩ ፡ ያላቸው ፡ ኀላፊነት ።

(፩) አስተዳዳሪዎቹ ፡ ወኪል ፡ እንደሚያደርገው ፡ ጥንቃቄ ፡ በሕግ ፤ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፤ ወይም ፡ በማኅበሩ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብና ፡ በጉባኤው ፡ ውሳኔዎች ፡ የተሰጧቸውን ፡ ተግባሮች ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ።

(፪) አስተዳዳሪዎቹም ፡ ግዴታዎቻቸውን ፡ ያጓደሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለሚደርሰው ፡ ጕዳት ፡ በማኅበሩ ፡ ዘንድ ፡ በአንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ ኀላፊዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፫) በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ ባንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ ኀላፊ ዎች ፡ የሆኑበትን ፡ የማኅበሩን ፡ ጠቅላላ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ለሚመለከተው ፡ የጠቅላላ ፡ ጥንቃቄ ፡ ግዴታ ፡ ኀላፊዎች ፡ ናቸው ።

(፬) ለማኅበሩ ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጡ ፡ ሥራዎች ፡ መኖራቸውን ፡ እያወቁ ፡ ይህን ፡ የመሰሉ ፡ ሥራዎች ፡ እንዳይፈጸሙ ፡ ለመከልከል ፡ ወይም ፡ የጉዳቶቹን ፡ ምክ ንያቶች ፡ ለማቃለል ፡ የሚቻላቸውን ፡ ያላደረጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በአንድነት ፡ ሳይ ከፋፈል ፡ ኀላፊዎች ፡ ናቸው ።

(፭) አስተዳዳሪዎቹም ፡ በቅን ፡ ሕሊናና ፡ በትጋት ፡ ለመሥራታቸው ፡ ማስረዳት ፡ አለባቸው ።

(፮) ጥፋት ፡ ያላደረገው ፡ አስተዳዳሪው ፡ በማስተዳደሪያው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ውሳ ኔዎች ፡ ፕሮሴቬርባል ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ከጓደኞቹ ፡ ተለይቶ ፡ አለማግባቱን ፡ ወዲያውኑ ፡

BACK



የጸፈ፡ እንደ፡ ሆነና፡ ለተቈጣጣሪዎቹም ፡ ያስታወቀ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተመለከተው ፡ ኀላፊነት ፡ ይድናል ።

ቍ ፡ ፫፻፷፭ ። ስለ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ኀላፊነት ፡ ማኅበሩ ፡ የሚያቀርበው ፡ ክስ ።

(፩) በኀላፊነት ፡ በአስተዳዳሪዎቹ ፡ ላይ ፡ ማኅበሩ ፡ ክስ ፡ የማቅረቡን ፡ ጒዳይ፡የሚ ወስነው ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ነው ። በዕለት ፡ ጒዳይ ፡ ማስታወሻ ፡ ላይ ፡ ያልተ ጻፈም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ኀላፊነትን ፡ በመመልከት ፡ ለሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ውሳኔ ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) አስተዳዳሪዎች ፡ እንዲከሰሱ ፡ ወይም ፡ ክኑሱ ፡ የሚፈለገው ፡ ነገር ፡ በግልግል ፡ እንዲያልቅ ፡ ለማድረግ ፡ ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ከአምስት ፡ አንድ ፡ የማ ያንስ ፡ ያላቸው ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ድምፅ ፡ ሰጥተው ፡ የወሰኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በነገሩ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ መሻር ፡ ያስከትላል ። እንዲሁም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ይኸው ፡ ጉባኤ ፡ በተሻሩት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ፋንታ ፡ ምትክ ፡ ይሾማል ።

(፫) ማኅበሩ ፡ ስለ ፡ ኀላፊነት ፡ የሚያቀርበውን ፡ ክስ ፡ ለመተውና ፡ ግልግል ፡ ለማ ድረግ ፡ ይችላል ። ክሱን ፡ ለመተውና ፡ ለመገላገል ፡ ጉባኤው ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከአምስት ፡ አንድ ፡ ያላቸው ፡ ባለ አክሲዮኖች ፡ ድምፅ ፡ በመስጠት ፡ የማይቃወሙት ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፬) ክሱ ፡ እንዲቀርብ ፡ ከተወሰነበት ፡ እንሥቶ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ማኅበሩ ፡ ያልከሰሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፪፡ መሠረት ፡ ክስ ፡ እንዲቀ ርብ ፡ ውሳኔውን ፡ የደገፉት ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ በኀላፊነት ፡ የማኅበሩን ፡ ክስ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፫፻፷፮ ። አስተዳዳሪዎቹ ፡ ከማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ለሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ ስላላ ቸው ፡ ኀላፊነት ።

(፩) አስተዳዳሪዎቹ ፡ የማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ሙሉ ፡ ሆኖ ፡ እንዲጠበቅ ፡ የሚወድቅ ባቸውን ፡ ግዴታዎች ፡ ካለመጠበቃቸው ፡ የተነሣ ፤ ከማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ለሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ በኀላፊነት ፡ ተጠያቂዎች ፡ ናቸው ።

(፪) የማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ የማኅበሩን ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ የማይበቃ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፤ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ በአስተዳዳሪዎቹ ፡ ላይ ፡ የኀላፊነትን ፡ ክስ ፡ ሊያቀርቡ ፡ ይችላሉ ።

(፫) ማኅበሩ ፡ በአስተዳዳሪዎቹ ፡ ላይ ፡ የሚያቀርበውን ፡ ክስ ፡ ለመተው ፡ ቢወስን፡ ከማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ለሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ የክስ ፡ ማቅረብ ፡ መብት ፡ መሰ ናከል ፡ አይሆንም ።

(፬) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ እንደተወሰነው ፡ አንድ ፡ ነገርን ፡ ስለ፡ማሻር ፡ ክስ ፡

BACK



ለማቅረብ ፡ ከተደነገጉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ውጭ ፡ ከማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ የሚ ጠይቁት ፡ ሰዎች ፡ የማኅበሩን ፡ ግልግል ፡ ሊቃወሙት ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፯ ። ባለአክሲዮኖችና ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ስለሚያቀርቡት ፡ ክስ ።**

በአስተዳዳሪዎች፡ ጥፋት፡ ወይም ፡ የማጭበርበር ፡ ተግባር ፡ በቀጥታ ፡ የተጎ ዳው ፡ ባለአክሲዮን ፡ ወይም ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ኪሣራ ፡ ለማግኘት ፡ ያለው ፡ የክስ ፡ ማቅረብ ፡ መብት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፉት ፡ ክፍል ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ተቈጣጣሪዎች ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፰ ። ተቈጣጣሪዎችን ፡ ስለ ፡ መሾም ።**

(፩) በማናቸውም ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ በጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ደንበኛ ፡ ተቈጣጣሪዎች ፤ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ረዳት ፡ ተቈ ጣጣሪዎች ፡ ይሾማል ።

(፪) በማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ ቢያንስ ፡ ከመቶ ፡ ሐያ ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ ባለአክሲዮን ፡ ወይም ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ራሳቸው ፡ የመረጡትን ፡ ተቈጣጣሪ ፡ ለመሾም ፡ ይችላሉ ።

(፫) ተቈጣጣሪዎቹ ፡ ብዙዎች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሥራቸውን ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ወይም ፡ ለየብቻ ፡ ለመሥራት ፡ ይችላሉ ።

(፬) በሕግ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ማኅበር ፡ ተቈጣጣሪ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፷፱ ። መሾምና ፡ ሥራው ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ።**

(፩) ተቈጣጣሪዎቹ ፡ በመጀመሪያ ፡ የሚመረጡት ፡ አክሲዮን ፡ ለመግዛት ፡ በፈረ ሙት፡ ሰዎች፡ ጉባኤ፡ ቀጥሎም፡ በዓመት፡ በሚሰበሰበው፡ ጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ ነው ።

(፪) አክሲዮን ፡ ለመግዛት ፡ በፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ ጉባኤ ፡ የተመረጡት ፡ ተቈጣጣ ሪዎች ፡ ሥራቸው ፡ የሚቈይበት ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ እስኪሚደረግ ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ ቀጥሎም ፡ በጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ የሚመረጡት ፡ ተቈጣጣሪዎች፡ በሥራቸው ፡ የሚቈዩት ፡ ለሦስት፡ ዓመት ፡ ሒሳብ ፡ ማጠቃለያ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

(፫) ተቈጣጣሪዎቹ ፡ በተቈጣጣሪነት ፡ ስም ፡ በሚፈርሙበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ሒሳ ቡን ፡ የሚቈጣጠሩትን ፡ ማኅበር ፡ ስም ፡ መጥቀስ ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፫፻፸ ። ለመሾም ፡ ስለ ፡ ማይችሉ ፡ ሰዎች ።**

(፩) ተቈጣጣሪ ፡ እንዲሆኑ ፡ ለመመረጥ ፡ የማይችሉ ፡ ሰዎች ።

(ሀ) የማኅበሩ ፡ መሥራቾች ፡ በዐይነት ፡ መዋጮ ፡ ያገቡ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥቅም ፡

የሚያገኙ ፤ የማኅበሩ ፡ ተካፋዮች ፤ ወይም ፡ ማኅበሩ ፡ ወይም ፡ የማኅበሩ ፡ ሆልዲንግ ፡ ማኅበር ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ የሆኑ ፤

(ለ) በንኡስ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ (ሀ) የተመለከቱት ፡ ሰዎች ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ አራተኛው ፡ ደረጃ ፡ የሥጋ ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዘመድ ፡ የሆኑ ።

(ሐ) በተቈጣጣሪነት ፡ ከሚያገኙት ፡ በቀር ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ (ሀ) ከተመለከቱት ፡ ሰዎች ፤ በሌላ ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ ደመወዝ ፡ ወይም ፡ በየጊዜው ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ የሚያገኙት ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

(፪) ተቈጣጣሪዎቹ ፡ ሥራቸው ፡ ከቀረበት ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የሚቈጣጠሩት ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ የተካፋዩ ፡ ወይም ፡ የማኅበሩ ፡ ሆልዲንግ ፡ ማኅበር ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ለመሆን ፡ አይችሉም ።

(፫) አንድ ፡ ተቈጣጣሪ ፡ ባቀረበው ፡ ራፖር ፡ መሠረት ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ የሰጠበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የማታለል ፡ ሥራ ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ በዚሁ ፡ ቍጥር ፡ የተጻፉትን ፡ ድንጋጌዎቹን ፡ በመጣስ ፡ የተደረገ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ውሳኔዎቹን ፡ ለማፍረስ ፡ አይቻልም ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፸፩ ። ተቈጣጣሪውን ፡ ከሥራ ፡ መሻር ።</u>

ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ተቈጣጣሪዎች ፡ ለመሻር ፡ ይችላል ። ትክክለኛ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ የተደረገው ፡ መሻር ፡ ለተሻረው ፡ ሰው ፡ የገንዘብ ፡ ኪሣራ ፡ የሚያሰጠው ፡ ይሆናል ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፸፪ ። የሥራ ፡ ዋጋ ።</u>

(፩) ለተቈጣጣሪዎቹ ፡ የሚሰጣቸውን ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ የሚቈርጥ ፡ እነርሱን ፡ የሚሾመው ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ነው ።

(፪) አስቸጋሪ ፡ ሆኖ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ በማናቸውም ፡ ባለጕዳይ ፡ ጥያቄ ፡ የንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይህን ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ ለመቍረጥ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ፫፻፸፫ ። የሞያ ፡ ሥራ ፡ ምሥጢር ።</u>

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፺ ፡ የሞያ ፡ ሥራ ፡ ምሥጢር ፡ ስለ ማውጣት ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ በተቈጣጣሪዎቹ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል።

<u>ቍ ፡ ፫፻፸፬ ። የተቈጣጣሪዎች ፡ ተግባር ።</u>

የተቈጣጣሪዎች ፡ ተግባር ፡ እንደሚመለከተው ፡ ነው ።

(ሀ) የማኅበሩን ፡ መዝገቦችና ፡ ያለውን ፡ የገንዘብ ፡ ዋስትና ፡ ሰነዶችን ፡ መመርመር ፤

(ለ) የንብረት ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ እና ፡ የሒሳቡ ፡ ሚዛኖች ፤ የኪሣራውና ፡

BACK



የትርፉ ፡ ሒሳብ ፡ በደንብና ፡ በእውነተኛ ፡ አሠራር ፡ ተሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ መቈጣጠር ፤

(ሐ) ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ ሁኔታ ፡ የአስተዳደሩ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ያቀረበው ፡ ራፖር ፡ ውስጥ ፡ የተሰጡት ፡ መግለጫዎች ፡ ትክክለኞች ፡ እንደሆኑ ፡ ማረጋገጥ ፤

(መ) ከዚህም ፡ በቀር ፡ በልዩ ፡ ውሳኔዎች ፡ የታዘዙትን ፡ ሁሉ ፡ መሥራት ፤

ቍ ፡ ፫፻፸፱ ። ለጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ የሚቀርብ ፡ ራፖር ።

(፩) ተቈጣጣሪዎቹ ፡ በየዓመቱ ፡ ለሚሰበሰበው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ የሥራቸውን ፡ ውጤት ፡ የሚገልጽ ፡ አንድ ፡ ራፖር ፡ በጽሑፍ ፡ ያቀርባሉ ። በአስተዳደሩ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ራፖር ፡ ላይ ፡ በተጻፉት ፡ ውስጥ ፡ ተገቢ ፡ መስለው ፡ ያገኙዋቸውን ፡ ማስገንዘቢያዎች ፡ ያመለክታሉ ።

(፪) ለጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ የማኅበሩን ፡ ሒሳቦች ፡ በሙሉ ፡ እንዲያጸድቀው ፡ ወይም ፡ የመጠባበቂያ ፡ ቃል ፡ ጨምሮ ፡ እንዲያጸድቀው ፡ ወይም ፡ ውድቅ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ እንዲላክ ፡ አሳብ ፡ ያቀርባሉ ።

(፫) ስለ ፡ ትርፉ ፡ አከፋፈል ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ በአቀረቡት ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ አሳባቸውን ፡ ይሰጣሉ ።

(፬) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተነገረው ፡ ራፖር ፡ ካልቀረበለት ፡ በቀር ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ በሒሳቡ ፡ ሚዛን ፡ ላይ ፡ አሳብ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፫፻፹ ። ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ ተግባር ፡ ሲሠራ ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።

(፩) ተቈጣጣሪዎቹ ፡ ሥራቸውን ፡ በሚፈጽሙበት ፡ ጊዜ ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ የታዘዙትን ፡ ነገሮች ፡ ደንበኛ ፡ ባልሆነ ፡ አሠራር ፡ ሲሠሩ ፡ ወይም ፡ ሲጣሱ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ለአስተዳዳሪዎቹ ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ። ነገሩም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሆኖ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ለጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ተቈጣጣሪዎቹ ፡ ሥራቸውን ፡ በሚፈጽሙበት ፡ ጊዜ ፡ በሕግ ፡ የተከለከለ ፡ ወንጀል ፡ መሠራቱን ፡ ሲያውቁ ፡ ለዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ የማስታወቅ ፡ ግዴታ ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፫፻፹፩ ። ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ የሚደረገው ፡ ጥሪ ።

(፩) በሕግ ፡ ወይም ፡ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፤ ወይም ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ተለይተው ፡ የተነገሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ ጥሪ ፡ ሳያደርጉ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጥሪውን ፡ ተቈጣጣሪዎቹ ፡ ማድረግ ፡ አለባቸው ።

(፪) እንዲሁም ፡ በማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ ቢያንስ ፡ ከመቶ ፡

ሓያ ፡ ያላቸው ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ በጠየቁ ፡ ጊዜ ፡ ተቈጣጣሪዎቹ ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ ጥሪ ፡ ማድረግ ፡ አለባቸው ።

(፪) ተቈጣጣሪዎቹ ፡ ብዙዎች ፡ እንደሆኑ ፡ እርስ፡በራሳቸው ፡ በመስማማት ፡ በመተዳደሪያ፡ ደንብ ፡ መሠረት፡ ጠቅላላው፡ ጉባኤ፡ እንዲሰበሰብ፡ ጥሪ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ። አስፈላጊ፡ መስሎ፡ ሲታያቸው፡ የማኅበሩ፡ መኖሪያ፡ ከሆነው፡ ቦታ ፡ አካባቢ፡ ወይም ፡ በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ ከተመለከተው ፡ ቦታ ፡ ሌላ ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ የሆነ፡ የመሰብሰቢያ ፡ ስፍራ ፡ ለመወሰን ፡ ይላችሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ የተባለው ፡ ስፍራ፡ በማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አካባቢ ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፫) የስብሰባውን ፡ የዕለት ፡ ጉዳይ ፡ ማስታወሻ፡ይወስናሉ ። ጥሪ ፡ ያደረጉበትንም፡ ምክንያት ፡ ለጉኤባው ፡ በሚነበብ ፡ ራፖር ፡ ላይ ፡ ይገልጻሉ ፡ ከነርሱ ፡ አንዱ ፡ ለጉባኤው ፡ ሰብሳቢ ፡ ይሆናል ።

(፬) ጉባኤ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ ጥሪ ፡ ማድረግ ፡ ይጠቅማል ፡ አይጠቅምም ፡ በመባባል ፡ ተቈጣጣሪዎቹ ፡ በማይስማሙበት ፡ ጊዜ ፡ አንዱ ፡ ተቈጣጣሪ ፡ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለበት ፡ ቀበሌ ፡ ለሚገኘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፫ እና፡ ፬፡ መሠረት ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ ጥሪ ፡ የሚያደርግ ፤ የስብሰባውን ፡ የዕለት ፡ ጉዳይ ፡ ማስታወሻ ፡ የሚወስን ፡ ሰብሳቢ ፡ የሚሆነውንም፡የሚመርጥ፡አንድ ፡ ሰው ፡ እንዲታዘዝ ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ፡ይችላል ።

(፭) በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ በጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ስብሰባ ፡ ምክንያት ፡ የሚደረገውን ፡ ወጪ ፡ ሁሉ ፡ የሚችል ፡ ማኅበሩ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፸፫ ። ሥልጣን ።

(፩) የተቈጣጣሪዎቹ ፡ ሥራ ፡ ነዋሪነት ፡ ያለው ፡ የማያቋርጥ ፡ ነው ። በዓመት ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ በታያቸው ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ አንድ፡ላይ፡ በመሆን ፡ ወይም ፡ ለየብቻቸው ፤ ማናቸውንም ፡ የመቈጣጠርና ፡ የምርመራ ፡ ሥራ፡ ለማድረግ፡ እዚያው ፡ ከስፍራው ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ስምምነቶችንና ፡ ውሎችን ፤ የሒሳቦችን ፡ መዝገቦችና ፡ ሰነዶችን ፤ የፕሮሴቬርባሎችን ፡ መዝገቦችና ፡ እንዲሁም ፡ በሥራቸው ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ የታያቸውን ፡ አስረጂ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ያለመቀነስ ፡ [illegible] ፡ ይችላሉ ።

(፪) የባለአክሲዮኖቹ፡ ጉባኤ ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ተቈጣጣሪዎቹ ፡ ሁሉ፡ መጠራት ፡ አለባቸው ። በየዓመቱ ፡ በሚደረገው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ የተቈጣጣሪዎች ፡ መገኘት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፸፬ ። የሆልዲንግን ፡ ማኅበር ፡ ሒሳብ ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ።

(፩) በቍጥር ፡ ፫፻፶፩ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ለጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ የተነጣዮቹን ፡ ማኅበር ፡ የተጠቃለሉ ፡ ሒሳቦች ፡ ለማቅረብ ፡ ግዴታ ፡ ያለበትን ፡ የሆልዲ

ንግን ፡ ማኅበሮች ፡ ለሚመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ተቈጣጣሪዎቹ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፴፰፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ የሒሳብ ፡ ምርመራ ፡ ሥራ ፡ ማድረግ ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፫፻፵ ። የተቈጣጣሪዎቹ ፡ ኀላፊነት ።

(፩) ተቈጣጣሪዎቹ ፡ ሥራቸውን ፡ በሚፈጽሙበት ፡ ጊዜ ፡ በሚያደርጉዋቸው ፡ ጥፋቶች ፡ ለማኅበሮቹና ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ኀላፊዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ማንኛውም ፡ ተቈጣጣሪ ፡ በሚያቀርበው ፡ ራፖር ፡ ላይ ፡ በክፉ ፡ ልቡና ፡ በማኅበሩ፡ ሁኔታ፡ ላይ፡ ሐሰተኛ፡ መግለጫ፡ የሰጠ ፡ ወይም ፡ ያረጋገጠ ፡ ወይም ፡ ወንጀል ፡ መሥራቱን፡ እያወቀ፡ ለዐቃቤ፡ ሕግ፡ ሳያስታውቅ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፷፬ ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፴፰ ፡ እንደ ፡ ጕዳዩ ፡ ዐይነት ፡ የተጻፉት ፡ ቅጣቶች ፡ ይፈጸሙበታል ።

ቍ ፡ ፫፻፵፩ ። ባለአክሲዮኖቹ ፡ ባቀረቡት ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ ሁኔታ ፡ የሚደረግ ፡ ምርመራ ።

(፩) ከወጣው ፡ አክሲዮን ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ ዐሥረኛው ፡ ያላቸው ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ባቀረቡት ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ የንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የማኅበሩን ፡ ሁኔታ ፡ እንዲመረምሩና ፡ ራፖር ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸውን ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡ እንስፔክተሮች ፡ ለመምረጥ ፡ ይችላል ።

(፪) ጥያቄውም ፡ ለሚኒስቴሩ ፡ አስፈላጊ ፡ መስለው ፡ የሚታዩት ፡ ማስረጃዎች ፡ እንዲኖረው ፡ ያስፈልጋል ። ጠያቂዎቹም ፡ ለሚደረገው ፡ ምርመራ ፡ ለሚያስፈልገው ፡ ወጪ ፡ ማረጋገጫ ፡ የሚሆን ፡ ቢበዛ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ እንዲያስቀምጡ ፡ ለማስገደድ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፫፻፵፪ ። የግዴታ ፡ የሆነ ፡ ምርመራ ።

ምርመራው፡ የተጠየቀው፡ በጠቅላላው፡ ጉባኤ፡ ወይም፡ በፍርድ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ምርመራ ፡ ለማድረግና ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፴፫ ፡ የተመለከተው ፡ ምርመራና ፡ ራፖር ፡ ለማዘጋጀት ፡ ችሎታ ፡ ያላቸውን ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡ እንስፔክተሮች ፡ መምረጥ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፫፻፵፫ ። የንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ በፈቃዱ ፡ ስለሚያደርገው ፡ ምርመራ ።

የማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፤

(ሀ) ገንዘብ ፡ ጠያቂዎችን ፡ የማታለል ፤

(ለ) የአንዱን ፡ ክፍል ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ የመጉዳት ፡ ተግባር ፡ ያለበት ፤

(ሐ) ከሕግ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ የአታላይነት ፡ ዓላማ ፡ የሚከተል ፤

(መ) በጠቅላላውም ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፤ መሆኑን ፡ ማሰብ ፡ ለንግድ ፡

ሚኒስቴር ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ ሲታየው ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ መር ማሪዎችን ፡ ለመምረጥ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፹፬ ። በሆልዲንግና ፡ በተነጣይ ፡ ማኅበሮች ፡ ነገር ፡ መርማሪዎች ፡ ስለ ፡ አላ ቸው ፡ ሥልጣን ።**

በቍጥር ፡ ፫፻፹፩ ፡ ፫፻፹፪ ፡ ፫፻፹፫ ፡ በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ የተመረጠው ፡ መርማሪ ፡ ( እንስፔክተር ) ስለ ፡ ምርመራው ፡ መልካም ፡ አሠ ራር ፡ በሆልዲንግ ፡ ወይም ፡ በተነጣይ ፡ ማኅበሮች ፡ ምርመራውን ፡ ማስፋፋት ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ በታየው ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ለማድረግ ፡ ምርመራውን ፡ ለንግ ድና ፡ እንዱስትሪ ፡ ሚኒስትር ፡ አመልክቶ ፡ ከተፈቀደለት ፡ በራፖሩ ፡ ውስጥ ፡ እንዲመረመር ፡ ከተላከበት ፡ ማኅበር ፡ አልፎ ፡ ምርመራ ፡ ያደረገባቸውን ፡ የነ ዚህኑ ፡ የሌሎቹን ፡ ማኅበሮች ፡ ሁኔታ ፡ ጨምሮ ፡ ለመጻፍ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፫፻፹፭ ። ምርመራ ፡ የሚደረግባቸው ፡ ማኅበሮች ፡ ስላሉባቸው ፡ ግዴታዎች ።**

(፩) ምርመራ ፡ የታዘዘባቸው ፡ ማኅበሮች ፡ በሕግ ፡ የታወቁ ፡ እንደራሴዎችና ፡ አስተዳዳሪዎችም ፡ ጭምር ፡ መርማሪዎቹ ፡ ኢንስፔክተሮች ፡ የሚጠይቋቸውን ፡ መዝገቦችና ፡ ሰነዶች ፡ ለማቅረብና ፡ ለሚጠይቋቸውም ፡ የመረጃ ፡ ጥያቄዎች ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ አለባቸው ።

(፪) ማናቸውም ፡ አስተዳዳሪ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ የታወቀ ፡ እንደራሴ ፡ አልታዘ ዝም ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ መርማሪዎቹ ፡ ለታዘዙበት ፡ ሥራ ፡ መሰናክል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መርማሪዎቹ ፡ ነገሩን ፡ ለንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ አስረድተው ፡ ሚኒ ስቴሩ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፹፫ ፡ ክስ ፡ እንዲቀርብ ፡ ያደርጋል ።

**ቍ ፡ ፫፻፹፮ ። የመርማሪዎች ፡ ራፖር ።**

የንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ መርማሪዎቹ ፡ ያቀረቡትን ፡ ራፖር ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፤ የዚህን ፡ ሃራፖር ፦

(ሀ) አንድ ፡ ግልባጭ ፤ ለተመረመረው ፡ ማኅበር ፡

(ለ) አንድ ፡ ግልባጭ ፡ ምርመራ ፡ እንዲደረግ ፡ ለጠየቁት ፡ ባለአክሲዮኖች ፤

(ሐ) ምርመራውን ፡ ላዘዘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይልካል ።

**ቍ ፡ ፫፻፹፯ ። ስለባለአክሲዮኖች ፡ የትውስት ፡ ስም ።**

(፩) በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ የተጻፉ ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ማኅበሩን ፡ በርግጥ ፡ ለሚቈጣ ጠሩትና ፡ ከውስጡ ፡ የገንዘብ ፡ ጥቅም ፡ ላላቸው ፡ ሰዎች ፡ ስማቸውን ፡ ያዋሱ ፡ ለመሆናቸው ፡ ትክክለኛ ፡ ምክንያት ፡ ያለ ፡ ለመሆኑ ፡ ለንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የመሰለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፹፫ ፡ በተደነገጉት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠ

ረት ፡ እርግጠኛ ፡ የሆኑትን ፡ የአክሲዮኖቹን ፡ ባለሀብቶች ፡ ለማወቅ ፡ እንዲመ ረምሩ ፡ መርማሪዎች ፡ ለመሾም ፡ ይችላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከወጣው ፡ አክሲዮን ፡ ከዐሥር ፡ አንድ ፡ ያላ ቸው ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ባቀረቡት ፡ ጥያቄ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡(፩)፡ መሠረት ፡ መርማሪ ፡ እንስፔክተሮችን ፡ መርጦ ፡ የንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ለመሾም ፡ ይች ላል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለባለአክሲዮኖች ፡ ጉባኤ ።

### ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

### አጠቃላይ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፫ ። ጠቅላላ ፡ ደንቦች ።**

(፩) በደንብ ፡ ሆኖ ፡ የተቋቋመውና ፡ ሕጋውያን ፡ በሆኑት ፡ ሁኔታዎች ፡ የሚወሰ ነው ፡ የባለአክሲዮኖች ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ለባለአክሲዮኖች ፡ ሁሉ ፡ እንደራሴ ፡ ነው ። የዚህ ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ የሌሉትንም ፤ በአሳብ ፡ የሚለዩትንም ፤ ችሎታ ፡ የሌላቸውንም ፡ ወይም ፡ ድምፅን ፡ የመስጠት ፡ መብት ፡ የተከለከሉ ትን ፡ ባለአክሲዮኖችንም ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፤ ሁሉንም ፡ ያስገድዳል ።

(፪) የንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) ድንጋጌ ፡ ለባለአክሲዮኖቹ ፡ እንደራሴ ፡ ለሆኑት ፡ ልዩ ፡ ጉባኤዎችም ፡ የሚጸና ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፬ ። የባለአክሲዮኖቹ ፡ የራሳቸው ፡ የሆኑ ፡ መብቶች ።**

(፩) በቍጥር ፡ ፫፻፺፫ ፡ የተመለከተው ፡ ቢኖርም ፡ እንኳን ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ በየ ራሳቸው ፡ ፈቃድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በማኅበረተኝነታቸው ፡ ያሏቸው ፡ መብቶች ፡

(፪) ሊቀሩባቸው ፡ አይችሉም ። በባለአክሲዮንነታቸው ፡ እንዳገኙዋቸው ፡ የሚ ቈጠሩት ፡ መብቶች ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ከጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ወይም ፡ ከአስ ተዳዳሪዎቹ ፡ ወኪሎች ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ የሌላቸው ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ ካላቸው ፡ መብት፡ የሚመነጩት ፡ ናቸው ። ይኸ ውም ፡ በተለይ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የመሆን ፡ መብት ፤ ድምፅ ፡ የማግኘት ፡ መብ ትና ፡ የመስጠት ፡ መብት ፤ የማኅበሩ ፡ ውሳኔ ፡ የመቃወም ፡ መብት ፤ እንዲ ሁም ፡ የትርፍን ፡ ድርሻና ፡ ማኅበሩም ፡ ሲፈርስ ፡ በመጨረሻ ፡ በሚደረገው ፡ በሒሳብ ፡ መጣራት ፡ ጊዜ ፡ ድርሻን ፡ የመክፈል ፡ መብት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፭ ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ጉባኤዎች ።**

(፩) የባለአክሲዮኖች ፡ ጉባኤዎች ፡ ጠቅላላ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ለመሆን ፡ ይችላሉ ።

(፪) ጠቅላላዎቹ ፡ ጉባኤዎች ፡ ደንበኛ ፡ ወይም ፡ ድንገተኛ ፡ ይሆናሉ ። እነዚህም ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎችን ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ የሚጠቀልሉ ፡ ናቸው ።

(፫) ልዩ ፡ በሆኑት ፡ ጉባኤዎች ፡ የሚገኙት ፡ በተለይ ፡ የአንድ ፡ ክፍል ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

ቍ፡ ፫፻፺፭ ። የጉባኤው ፡ ጥሪ ።

(፩) ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ ጥሪን ፡ የሚያደርጉት ፡ አስተዳዳሪዎች ፤ ተቈጣጣሪዎች ፤ ሒሳብ ፡ አጣሪዎች ፤ አስፈላጊም ፡ ቢሆን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ።

(፪) እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ከዐሥር ፡ አንድ ፡ ያላቸው ፡ ባለ አክሲዮኖች ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ ጥሪ ፡ የሚያደርግና ፡ የዕለት ፡ ጉዳይ ፡ ማስታወቂንም ፡ የሚወስን ፡ አንድ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ወኪል ፡ እንዲመረጥ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ በማስረዳት ፡ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ለሚገኝበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፫፻፺፮ ። የአጠራሩ ፡ ዐይነት ።

(፩) ለጉባኤዎቹ ፡ ሁሉ ፡ የሚላኩት ፡ ጥሪዎች ፡ በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ እንደተወሰነው ፡ ሆኖ ፡ እንዲሁም ፡ በንግድ ፡ ኦፊሲዩል ፡ ጋዜጣ ፡ ጥሪው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ። እንዲሁም ፤ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ ሕጋዊ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለማውጣት ፡ የተፈቀደለት ፡ ጋዜጣ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚሁ ፡ ጋዜጣ ፡ ጥሪው ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

(፪) ቢሆንም ፡ የአክሲዮኖቹ ፡ ሁሉ ፡ በየባለአክሲዮን ፡ ስም ፡ ተጽፈው ፡ በሚገኙባቸው ፡ ማኅበሮች ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) በተመለከቱት ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ፋንታ ፡ ጥሪው ፡ በማኅበሩ ፡ ኪሣራ ፡ ለየአንዳንዱ ፡ ባለአክሲዮን ፡ በረኮማንዴ ፡ በሚላክ ፡ ደብዳቤ ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

(፫) በየስም ፡ ለተጻፉት ፡ አክሲዮኖች ፡ ባለሀብት ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ጥሪው ፡ በረኮማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ እንዲደርሰው ፡ ለማኅበሩ ፡ ጥያቄ ፡ ያቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ፤ ስለ ፡ ጉባኤው ፡ ጥሪ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ በራሱ ፡ ኪሣራ ፡ በረኮማንዴ ፡ በሚላክ ፡ ደብዳቤ ፡ መጠራት ፡ አለበት ።

(፬) የጉባኤው፡ አባሎች፡ የሚገኙበት፡ አስፈላጊው፡ በቂ፡ የሆነ ፡ ቍጥር፡ (ኮረም) ፡ ባልተገኘ ፡ ጊዜ ፡ የሚደረገው ፡ ልዩ ፡ ጥሪ ፡ በየአንዳንዱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ አክሲዮኖች ፡ ልዩ ፡ ጉባኤ ፡ የተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፫፻፺፯ ። የአባሎች ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ቍጥር ፡ ስላለመሙላቱ ፡ የሚደረግ ፡ የደንበኛው ፡ ጉባኤ ፡ ጥሪ ።

በቍጥር ፡ ፬፻፳፩ ፡ የተወሰነው ፡ የጉባኤው ፡ አባሎች ፡ ቍጥር ፡ ባለመሙላቱ ፡

ደንበኛው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ለመምከር ፡ ሳይችል ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለሁለተ ተኛ ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ የሚደረገው ፡ ጥሪ ፡ ለመጀመሪያው ፡ ጉባኤ ፡ በተወሰነ ፡ ፎርምና ፡ ጊዜ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፬ ። የአባሎቹ ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ቍጥር ፡ ስላለመሙላቱ ፡ የድንገተኛ ፡ ወይም ፡ የልዩ ፡ ጉባኤ ፡ ጥሪ ።**

ድንገተኛ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ጉባኤ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፳፭ ፡ እና ፡ ፬፻፳፮ ፡ ቍጥራቸው ፡ የተወሰነውን ፡ የጉባኤ ፡ አባሎች ፡ ለመሰብሰብ ፡ ሳይችል ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፤ በንግድ ፡ ኦፊሲዬል ፡ ጋዜጣና ፡ ሕጋዊ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ለማውጣት፡ በተፈቀደለት ፡ ጋዜጣ ፡ ላይ ፡ ይህም ፡ ባይሆን ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፺፪ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ መሠረት ፡ በሁለት ፡ ማስታወቂያዎች ፡ የመጀመሪያውን ፡ ባሳተመ ፡ በሳምንቱ ፡ ሁለተኛውን ፡ በማውጣት ፡ ጉባኤው ፡ ሁለተኛ ፡ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ ጥሪ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፭ ። የጥሪው ፡ ጊዜ ።**

ጉባኤዎቹ ፡ እንዲሰበሰቡ ፡ ለሚደረጉት ፡ ጥሪዎች ፡ ሁሉ ፡ የጥሪው ፡ ማስታወቂያ ፡ የሚጸናበት ፡ ጊዜ ፡ መሰጠት ፡ የሚገባው ፤ የጀመሪያው ፡ ስብሰባ ፡ ከሚደረግበት ፡ ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ በፊት ፤ እንዲሁም ፡ ለስብሰባው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ የማኅበረተኞቹ ፡ ቍጥር ፡ በማነሱ ፡ ምክንያት ፡ ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ለተከታዮች ፡ ስብሰባ ፡ የሚላኩት ፡ ጥሪዎች ፡ ስብሰባው ፡ ከመደረጉ ፡ ከስምንት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ መሆን ፡ አለበት ።

**ቍ፡ ፫፻፺፮ ። በጥሪው ፡ ማስታወቂያ ፡ ላይ ፡ የሚጠቀሰው ።**

(፩) የጥሪው ፡ ማስታወቂያ ፡ የማኅበሩን ፡ ስምና ፡ ዐይነቱን ፤ የማኅበሩን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፤ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ያለበትን ፤ ለአምጪው ፡ የሚል ፡ የተጻፈባቸው ፡ አክሲዮኖች ፡ እንዳሉም ፡ ሊቀመጡበት ፡ የሚገባውን ፡ ቦታ ፤ እንዲሁም ፡ ይህ ፡ የአክሲዮኑን ፡ ማስቀመጥ ፡ በምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መደረግ ፡ እንዳለበት ፡ መጥቀስ ፡ አለበት ።

(፪) ከዚህ ፡ በቀር ፡ በሁለተኛው ፡ ወይም ፡ በሦስተኛው ፡ ጥሪ ፡ ለተሰበሰበው ፡ ጉባኤ ፡ የተሰጠው ፡ የጥሪ ፡ ማስታወቂያ ፡ የአባሎቹ ፡ ቍጥር ፡ ባለመሙላት ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ሳይችል ፡ የተበተነውን ፡ ጉባኤ ፡ ወይም ፡ ጉባኤዎች ፡ ጊዜ ፡ መጥቀስ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፫፻፺፯ ። የዕለት ፡ ጉዳዮች ፡ ማስታወሻ ፡ ( አጀንዳ ) ።**

(፩) በቍጥር ፡ ፫፻፺፩፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪፡ የተጻፈው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ የጉባኤዎቹን ፡ የዕለት ፡ ጉዳይ ፡ ማስታወሻ ፡ የሚያደራጀው ፡ ጥሪ ፡ አድራጊው ፡ ነው ።

BACK



(፪) ሌላ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በየዕለት ፡ ጕዳዮች ፡ ማስታወሻ ፡ ውስጥ ፡ ያልተገኘው ፡ ማናቸውም ፡ ጕዳይ ፡ ሊመከርበት ፡ አይችልም ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጉባኤው ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ለመሻርና ፡ በምትካቸው ፡ ሌላ ፡ ለመሾም ፡ ይችላል ።

(፫) በቍጥር ፡ ፫፻፺፫ ፡ እና ፡ ፫፻፺፬ ፡ በተደነገጉት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ በሁለተኛው ፡ ወይም ፡ በሦስተኛው ፡ ጥሪ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ጉባኤዎች ፡ ለመወሰን ፡ የሚችሉት ፤ ለመጀመሪያው ፡ ጉባኤ ፡ በተመደበው ፡ የዕለት ፡ ማስታወሻ ፡ ጕዳይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፫፻፺፭ ። የባለአክሲዮኖች ፡ እንደራሴነት ።

(፩) አንድ ፡ ባለአክሲዮን ፡ ከአንድ ፡ እንደራሴ ፡ በቀር ፡ ለመሾም ፡ አይችልም ። በጉባኤውም ፡ ላይ ፡ እንደራሴ ፡ አድርጎ ፡ ራሱ ፡ ድምፅ ፡ መስጠት ፡ አይችልም ።

(፪) ያልተከፋፈሉት ፡ አክሲዮኖች ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፤ የአክሲዮኖቹን ፡ የአላባ ፡ ጥቅም ፡ (ሪም) ፡ ሰጭና ፡ መያዣ ፡ የተቀበለ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ እንደራሴነት ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፷፰ ፡ እና ፡ ፫፻፷፱ ፡ በተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይመራሉ ።

## ቍ ፡ ፫፻፺፮ ። ውሳኔዎቹ ፡ እንዲጸኑ ፡ የሚያስፈልጉ ፡ ሁኔታዎች ።

(፩) ማናቸውም ፡ ጉባኤ ፡ ቢሆን ፡ ሁለት ፡ ሁኔታዎች ፡ አሉት ፤ እነዚህም ፡ የአብዛኛዎቹ ፡ የጉባኤው ፡ አባሎች ፡ ድምፅ ፡ ብልጫና ፡ ስብሰባ ፡ ለማድረግ ፡ አስፈላጊው ፡ አነስተኛ ፡ የአባሎች ፡ ቍጥር ፡ ካልተገኘ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ውሳኔ ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ።

(፪) በሚደረጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ላይ ፡ መገኘት ፡ ያለበት ፡ አስፈላጊው ፡ አነስተኛ ፡ የአባሎች ፡ ቍጥር ፡ ከዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ጋራ ፡ ባለው ፡ ግንኙነት ፡ ለያንዳንዱ ፡ የጉባኤ ፡ ዐይነት ፡ በተወሰነው ፡ መሠረት ፡ ነው ። በሚደረጉት ፡ ጉባኤዎች ፡ ሁሉ ፡ አስፈላጊው ፡ አነስተኛ ፡ የአባሎች ፡ ቍጥር ፡ የሚታሰበውም ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ የድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብት ፡ ያልተሰጣቸው ፡ አክሲዮኖች ፡ ከተቀነሱ ፡ በኋላ ፡ የማኅበሩን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ በሚጠቀልሉት ፡ አክሲዮኖች ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፫) በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ አባሎቹ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫና ፡ ስብሰባ ፡ ለማድረግ ፡ አስፈላጊው ፡ አነስተኛ ፡ የአባሎች ፡ ቍጥርን ፡ የሚመለከቱትን ፡ ሕጋውያን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለማሻሻል ፡ ለመለወጥ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፬፻ ። ማኅበሩ ፡ መልሶ ፡ በገዛቸው ፡ አክሲዮኖች ፡ ድምፅ ፡ እንዳይሰጥ ፡ ክልክል ፡ ስለ፡ መሆኑ ።

ማኅበሩ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፹፪ ፡ በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ መልሶ ፡ በገዛቸው ፡ አክሲዮኖች ፡ ድምፅን ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፬፻፩ ። የአክሲዮኖቹ ፡ መመዝገቢያ ፡ ጊዜ ።

ስም ፡ በተጻፈባቸው ፡ አክሲዮኖች ፡ ባለሀብቶች ፡ በማኅበሩ ፡ መዝገብ ፡ የሚጻፉበትንና ፤ ለአምጪው ፡ ተብሎ ፡ የተጻፉባቸውም ፡ አክሲዮኖች ፡ በማኅበሩ ፡ ጉባኤ ፡ የመቀመጥ ፡ መብት ፡ እንዲኖራቸው ፡ አክሲዮኖቹን ፡ የሚያገቡበትን ፡ ጊዜ ፡ የማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ይወስናል ፤ ይኸውም ፡ ጊዜ ፡ ጉባኤው ፡ ከሚሰበሰብበት ፡ ከአምስት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ለማለቅ ፡ አይችልም ፤ ይህንኑም ፡ ጊዜ ፡ በማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ለመቀነስ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፬፻፪ ። የእንደራሴነት ፡ ሥልጣን ።

የእንደራሴነት ፡ ሥልጣኖች ፡ ፎርም ፡ የሚቀመጡበትን ፡ ጊዜና ፡ ቦታውን ፡ የሚወስኑ ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ ናቸው ፤ ይህም ፡ ሲሆን ፡ የተባለው ፡ ጊዜ ፡ ጉባኤው፡ ከሚሰበሰቡበት ፡ ከሦስት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ለማለቅ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፬፻፫ ። በጉባኤው ፡ ላይ ፡ የመገኘት ፡ ማስረጃ ፡ ወረቀት ።

(፩) በያንዳንዱ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ የአባሎቹን ፡ በጉባኤ ፡ መኖር ፡ የሚያስረዳ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ይደረጋል ፤ ራሳቸው ፡ ያሉትን ፡ ወይም ፡ እንደራሴ ፡ የላኩትን ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ስምና ፡ አድራሻቸውን ፤ እያንዳንዱ ፡ ባለአክሲዮን ፡ ያለውን ፡ የአክሲዮንና ፡ የሚሰጠውንም ፡ ድምፅ ፡ ቍጥር ፡ ዝርዝር ፡ ይናገራል ።

(፪) በዚህ ፡ በጉባኤው ፡ የመገኘት ፡ ማስረጃ ፡ ወረቀቶች ፡ ዳር ፡ ላይ ፡ ራሳቸው ፡ ያሉት ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ወይም ፡ እንደራሴዎቻቸው ፡ የፈረሙበትና ፡ ትክክለኛ ፡ ለመሆኑም፡ የጉባኤው ፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ የመሰከረለት፡ መሆን ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፬፻፬ ። የጉባኤው ፡ ፕሬዚዳንት ።

(፩) የጉባኤው ፡ ሰብሳቢ ፡ የአስተዳደር ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ነው ፤ እሱም ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከአስተዳዳሪዎቹ ፡ በሥራ ፡ ቀደምትነት ፡ ያለው ፡ ሰብሳቢ ፡ ይሆናል ። እሱም ፡ የሌለ ፡ ሲሆን ፡ በማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ የተመረጠው ፡ ሰው ፤ ይህም ፡ ከሌለ ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ የመረጠው ፡ ሰብሳቢ ፡ ይሆናል ።

(፪) ተቈጣጣሪዎች ፤ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ወኪል ፤ ወይም ፡ የመጨረሻውን ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪ ፡ ወይም ፡ አጣሪዎች ፡ የስብሰባ ፡ ጥሪ ፡ በሚያደርጉበት ፡ ጊዜ ፤ ለጉባኤው ፡ ሰብሳቢ ፡ የሚሆነው ፤ ጥሪ ፡ ያደረገው ፡ ነው ።

BACK



ቍ ፡ ፬፻፭ ። ድምፅ ፡ ተቀባዮችና ፡ ጸሐፊ ።

(፩) በባለቤትነት ፡ ሆነ ፡ በእንደራሴነት ፡ ስም ፡ በጉባኤው ፡ ስብሰባ ፡ ላይ ፡ ከቀረቡት ፡ በአክሲዮን ፡ ብልጫ ፡ ያላቸውና ፡ ፈቃደኛ ፡ የሆኑት ፡ ሁለት ፡ አባሎች ፡ ድምፅ ፡ ቈጣሪ ፡ ሆነው ፡ ይመረጣሉ ።

(፪) የጉባኤው ፡ ጽሕፈት ፡ ቤትም ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንቡ ፡ ለተሰጡት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ከባለአክሲዮኖቹ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ጸሐፊ ፡ ለመምረጥ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፬፻፮ ። የማኅበሩን ፡ ሰነዶች ፡ ለማወቅ ፡ የመቻል ፡ መብት ።

(፩) ማናቸውም ፡ ባለአክሲዮን ፡ ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉትን ፡ ሰነዶች ፡ ለማወቅ ፡ ወይም ፡ ቅጂዎቻቸውን ፤ ለመውሰድ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ መብት ፡ አለው ። እነዚሁም ፤

(ሀ) የሒሳብ ፡ ሚዛኖችና ፡ የትርፍና ፡ የኪሣራ ፡ ሒሳቦች ፤

(ለ) አስተዳዳሪዎቹና ፡ ተቈጣጣሪዎች ፡ ባለፉት ፡ የመጨረሻ ፡ ሦስት ፡ የሒሳብ ፡ ማጠቃለያ ፡ ጊዜዎች ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ ለጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ያቀረቡዋቸው ፡ ራፖሮች ፤

(ሐ) እነዚሁም ፡ ጉባኤ ፡ ፕሮሴቬርባሎችና ፡ በጉባኤው ፡ ላይ ፡ የመገኘት ፡ ማስረጃ ፡ ወረቀት ፡ ናቸው ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የሚመለከቱትን ፡ ሰነዶች ፡ ማኅበሩ ፡ ላንድ ፡ ባለአክሲዮን ፡ እንዳይሰጡት ፡ የተቃወመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጉዳዩ ፡ ለንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይቀርባል ።

(፫) እንዲሁም ፡ ያልተከፋፈሉት ፡ አክሲዮኖች ፡ የጋራ ፡ ባለሀብቶች ፡ የአክሲዮን ፡ አላባ ፡ ተቀባዩ ፤ ባለሪም ፤ መያዣ ፡ የተቀበለ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተሰጠው ፡ የማኅበሩን ፡ ጉዳይ ፡ የማወቅ ፡ መብት ፡ አላቸው ።

ቍ ፡ ፬፻፯ ። ከአክሲዮኖች ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ የድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብት ።

(፩) ከዋናው ፡ ገንዘብ ፡ አክሲዮኖች ፤ ወይም ፡ ትርፍ ፡ ብቻ ፡ ከሚያስጡ ፡ አክሲዮኖች ፡ ጋራ ፡ የተያያዘው ፡ የድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብት ፡ ብዛት ፤ ከዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ ባላቸው ፡ ድርሻ ፡ መጠን ፡ ነው ።

(፪) እያንዳንዱ ፡ አክሲዮን ፡ አንድ ፡ ድምፅን ፡ የመስጠት ፡ መብት ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፬፻፰ ። የድምፅ ፡ መስጠት ፡ ወሰን ።

የሚደረገው ፡ የድምፅ ፡ መስጠት ፡ ወሰን ፡ ለአክሲዮኖቹ ፡ ልዩነት ፡ ሳይደረግ ፡ ለሁሉም ፡ አንድ ፡ ከሆነ ፤ በማንኛቸውም ፡ ጉባኤዎች ፡ ውስጥ ፡ እያንዳንዱ ፡ ባለ

BACK



አክሲዮን ፡ የሚሰጠው ፡ ድምፅ ፡ ቊጥር ፡ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ ወሰን ፡ ሊደረግለት ፡ ይቻላል ።

**ቊ ፡ ፬፻፶፱ ። የጥቅም ፡ አለመስማማት ።**

(፩) አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ከማኅበሩ ፡ ጥቅም ፡ ጋራ ፡ የማይስማማበት ፡ ጥቅም ፡ ባለባቸው ፡ ምክሮች ፡ ውስጥ ፡ በድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብቱ ፡ ሊሠራበት ፡ አይችልም ።

(፪) በንኡስ ፡ ቊጥር ፡ ፩ ፡ የተመለከተው ፡ በማይጠበቅበት ፡ ጊዜ ፡ ውሳኔው ፡ ለማኅበሩ ፡ ጥቅም ፡ በሚያመጣው ፡ ጉዳት ፡ መጠን ፡ ድምፅ ፡ ከመስጠት ፡ ቀሪ ፡ መሆን ፡ የነበረባቸው ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ድምፅ ፡ ባይሰጡ ፡ ኖሮ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ቊጥር ፡ አይሞላም ፡ ነበር ፡ በሚያሰኝበት ፡ ጊዜ፤ በቊጥር ፡ ፬፻፶፰ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ውሳኔውን ፡ ለመቃወም ፡ ይቻላል ።

(፫) የነርሱን ፡ አላፊነት ፡ በሚመለከታቸው ፡ ምክሮች ፡ ውስጥ ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ ድምፅ ፡ ለመስጠት ፡ አይችሉም ።

(፬) በዚህ ፡ ቊጥር ፡ ውስጥ ፡ እንደተመለከተው ፡ አነጋገር ፡ የድምፅ ፡ መስጠት፡ መብት ፡ የላቸውም ፡ የተባሉት ፡ አክሲዮኖች ፡ ለጉባኤው ፡ መሙላት ፡ አስፈላጊ ፡ ለሆነው ፡ አነስተኛ ፡ ቊጥር ፡ ገብተው ፡ ይታሰባሉ ።

**ቊ ፡ ፬፻፷ ። ድምፅን ፡ የመስጠት ፡ መብት ፡ በነጻ ፡ እንዳይሠራበት ፡ ስለሚከለክሉ ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ አለማጽናት ።**

በባለአክሲዮኖቹ ፡ ጉባኤ ፡ ውስጥ ፡ በነጻ ፡ ድምፅ ፡ የመስጠት ፡ መብትን ፡ የሚከለክሉ ፡ ወይም ፡ የመከልከል ፡ ውጤት፡ያላቸው ፡ ማናቸውም ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ የማይጸኑና ፡ ምንም ፡ ውጤት ፡ የሌላቸው ፡ ናቸው ።

**ቊ ፡ ፬፻፷፩ ። ፕሮሴቬርባሎች ።**

(፩) የጉባኤዎች ፡ የክርክር ፡ ውሳኔዎች ፡ በፕሮሴቬርባሎች ፡ በጽሑፍ ፡ ተደርገው፡ እጅግ ፡ ቢያንስ፡ የጉባኤው፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ በአብዛኛው ፡ ቊጥር፡ ከተፈረመባቸው ፡ በኋላ ፡ በአንድ ፡ መዝገብ ፡ ይገለበጣሉ ። ይህም ፡ የፕሮሴቬርባሎቹ ፡ በመዝገብ ፡ መጻፍ ፡ ትክክለኛነት ፡ በማኅበሩ ፡ የአስተዳደር ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ወይም ፡ በሁለት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ የተረጋገጠ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) የጉባኤው ፡ ፕሮሴቬርባሎች ፤

(ሀ) የጉባኤውን ፡ ጥሪ ፡ አደራረግ ፤

(ለ) የስብሰባውን ፡ ቦታና ፡ ቀኑን ፤

(ሐ) የዕለቱን ፡ ጉዳይ ፡ ማስታወሻ ፤

(መ) የጉባኤውን ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ አባሎች ፤

(ሠ) በስብሰባው ፡ ውስጥ ፡ የተገኙትን ፡ አክሲዮኖች ፡ ብዛትና ፡ ለጉባኤው ፡ ስብሰባ ፡ አስፈላጊው ፡ ባለአክሲዮን ፡ ቍጥር ፤

(ረ) ፡ ለጉባኤው ፡ የቀረቡትን ፡ ሰነዶች ፤

(ሰ) የክርክሩን ፡ አጭር ፡ ቃል ፤

(ሸ) የተሰጡትን ፡ ድምፆች ፡ ውጤት ፤

(ቀ) ጉባኤው ፡ የተቀበላቸውን ፡ ውሳኔዎች ፤ ያመለክታሉ ።

ቍ ፡ ፬፻፲፪ ። ፪፻፷ ፡ ለስብሰባ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ቍጥር ፡ ባልሞላ ፡ ጊዜ ፡ የሚደረግ ፡ ፕሮሴቬርባል ።

ለስብሰባው ፡ አስፈላጊው ፡ የሆነው ፡ ቍጥር ፡ ባለመሙላቱ ፡ ምክንያት ፡ ጉባኤው ፡ ለመማከር ፡ ሳይችል ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የጉባኤው ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ይህንኑ ፡ በፕሮሴቬርባል ፡ ያገባዋል ።

ቍ ፡ ፬፻፲፫ ። የፕሮሴቬርባሎች ፡ ቅጂዎች ፡ ወይም ፡ ግልባጮች ።

የፕሮሴቬርባሎቹ ፡ ባጭር ፡ የተውጣጡ ፡ ቅጂዎች ፤ ወይም ፡ ግልባጮች ፤ በአስተዳደሩ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ወይም ፡ በሁለት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ከተፈረመባቸው ፡ የሚጸኑ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፬፻፲፬ ። የጉባኤውን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ መቅጠር ።

(፩) ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ሲሶ ፡ ያላቸው ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ሊመከርባቸው ፡ በቀረቡት ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ማስረጃ ፡ ያልቀረበላቸው ፡ የመሰላቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ስብሰባው ፡ ቢበዛ ፡ ለሦስት ፡ ቀን ፡ እንዲቀጠር ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

(፪) በዚህም ፡ መብት ፡ ለአንድ ፡ ጊዜና ፡ ለዚያው ፡ ጉዳይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሊሠሩበት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፬፻፲፭ ። በስምምነት ፡ የሚደረግ ፡ የባለአክሲዮኖች ፡ ሙሉ ፡ ጉባኤ ።

(፩) የጠቅላላው ፡ አክሲዮኖች ፡ ባለቤቶች ፡ ወይም ፡ እንደራሲዎች ፡ በስምምነት ፤ ስለ ፡ ጥሪው ፡ የተመለከቱት ፡ ፎርሞች ፡ ሳይጠበቁ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤን ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

(፪) የአክሲዮኖቹ ፡ ሁሉ ፡ ባለቤቶች ፡ ወይም ፡ ወኪሎች ፡ ባሉበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የተባለው ፡ ይህ ፡ ጉባኤ ፡ በጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ሥልጣን ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ለመምክርና ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፬፻፲፮ ። የጉባኤው ፡ ውሳኔዎች ፡ ውጤት ።

(፩) ሕግን ፤ የማኅበሩን ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፎችንና ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብን ፡ በመከተል ፡ የተደረጉት ፡ የጉባኤው ፡ ውሳኔዎች ፡ በጉባኤው ፡ ያልተገኙትን ፡ ወይም ፡ በአሳብ ፡ ያልተስማሙትን ፡ ማኅበረተኞችን ፡ ሁሉ ፡ ያስገድዳል ።

BACK



(፱) ሕግን ፤ የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍና ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብን ፡ ባለ መከተል ፡ የተደረጉትን ፡ ውሳኔዎች ፤ ውሳኔው ፡ ከተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ተመዝግቦ ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ ከተመዘገበበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ማንኛውም፡ ባለጥቅም ፡ ሊቃወማቸው ፡ ይችላል ።

(፲) ውሳኔውን ፡ ለማፍረስ ፡ የሚደረገው ፡ ክስ ፡ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መኖሪያ ፡ ከሚ ገኝበት ፡ ክፍል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቀርባል ። ውሳኔውን ፡ ለማፍረስ ፡ የቀረበው፡ ክስ ፡ ምናልባት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የማይቀበለው ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በማ ለት ፤ ለኪሣራው ፡ ዋስ ፡ እንዲጠራ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ክስ ፡ አቅራቢውን ፡ ለማ ስገደድ ፡ ይችላል ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከባድ ፡ የሆኑ ፡ ምክንያቶች ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አስተዳዳሪዎቹ ንና ፡ ተቈጣጣሪዎቹን ፡ ካዳመጠ ፡ በኋላና ፡ በከሳሹ ፡ ጥያቄ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፡ ተቃዋሚ ፡ የተነሣበትን ፡ ውሳኔ ፡ እንዳይፈጸም ፡ ለማገድ ፡ ይችላል ።

(፭) የውሳኔው ፡ ፈራሽነት ፡ በማኅበረተኞቹ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ከመሆ ኑም ፡ በላይ ፡ ይህንኑ ፡ ውሳኔ ፡ ለማስፈጸም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትንም ፡ ነገሮች ፡ በራሳቸው ፡ አላፊነት ፡ እንዲያደርጉ ፡ አስተዳዳሪዎቹንም ፡ ውሳኔው ፡ ያስገድዳል ።

(፮) የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ውሳኔውን ፡ ለመፈጸም ፡ በተደረጉት ፡ ሥራዎች ፡ ምክንያት ፤ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ያገኙዋቸው ፡ መብቶች ፡ እንደ ፡ ጸኑ ፡ ይቀራሉ ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።

## ደንበኛ ፡ ጉባኤ ።

**ቍ ፡ ፬፻፲፪ ። ሰነዶችን ፡ የማወቅ ፡ መብት ።**

በቍጥር፡ ፬፻፷፪ የተመለከተው፡ሰነዶችን፡ የማወቅ፡ መብት፡ ሳይነካ፤ ባለአክሲዮን፡ ሁሉ ፡ በየዓመቱ ፡ መደበኛ ፡ የሆነ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ ባለው፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ በማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለጠቅላላ፡ ጉባኤው ፡ የሚቀርበውን ፡ የሒሳቡን ፡ ሚዛን ፤ የኪሣራና ፡ የትርፉን ፡ ሒሳብ ፤ የአስተዳዳሪዎችንና ፡ የተቈጣጣሪዎችን ፡ ራፖር ፤ ራሱ ፡ ለማወቅ ፡ ወይም ፡ ግልባጭ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፬፻፲፫ ። ስለ ፡ ጉባኤዎች ።**

(፩) የሒሳቡ ፡ ማጠቃለያ ፡ ጊዜ ፡ ከተዘጋበት ፡ ቀን ፡ በሚቀጥለው ፡ አራት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ በአስተዳዳሪዎቹ ፡ ጥሪ ፡ በየዓመቱ ፡ አንድ ፡ ደንበኛ ፡ የሆነ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ይደረጋል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሊራዘም ፡ ይችላል ።

(፫) አስፈላጊም ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ሌላ ፡ ደንበኛ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

## ቍ ፡ ፩፻፲፱ ። የጉባኤው ፡ ሥልጣን ።

(፩) ለደንበኛው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ የሒሳቡ ፡ ሚዛን ፤ የኪሣራውና ፡ የትርፉ ፡ ሒሳብ ፤ የአስተዳዳሪዎቹና ፡ የተቈጣጣሪዎቹ ፡ ራፖር ፡ ይነበባል ። ባለፈው ፡ የሒሳብ ፡ ማጠቃለያ ፡ ጊዜ ፡ የተሠራውን ፡ ሒሳብ ፡ ተከራክሮበት ፡ ያጸድቀዋል ፡ ወይም ፡ አይቀበለውም ፤ አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ የትርፉን ፡ አመዳደብና ፡ አከፋፈል ፡ እንዲሁም ፡ በጠቅላላው ፡ ባለፈው ፡ የሒሳብ ፡ ማጠቃለያ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ የሒሳብ ፡ ጕዳዮች ፡ ሁሉ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

(፪) አስተዳዳሪዎችን ፡ ወይም ፡ ተቈጣጣሪዎችን ፡ ይሾማል ፡ ወይም ፡ ይሽራል ። የሥራቸውንም ፡ ዋጋ ፡ ይወስናል ፤ አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፸፮ ፡ የተመለከተው ፡ ራፖር ፡ ከተነበበ ፡ በኋላ ፡ ሒሳቦችን ፡ ያስተካክላል ፤ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ እንዲወጡ ፡ ለነዚህም ፡ ዋስትና ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ማረጋገጫዎች ፡ ይፈቅዳል ። በጠቅላላውም ፡ ለድንገተኛ ፡ ጉባኤ ፡ ከተሰጡት ፡ ጕዳዮች ፡ በቀር ፡ በሌላው ፡ ጕዳይ ፡ ሁሉ ፡ ክርክር ፡ ያደርጋል ።

## ቍ ፡ ፩፻፳ ። በጉባኤው ፡ ስለ ፡ መግባት ።

(፩) ሌላ ፡ ተቃራኒ ፡ ውሳኔ ፡ ቢኖርም ፡ እንኳን ፡ ማናቸውም ፡ በማኅበርተኛ ፡ ያለው ፡ አክሲዮን ፡ ብዛት ፡ ሳይታይ ፡ በደንበኛው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ውስጥ ፡ ለመገኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ተቃራኒ ፡ ውሳኔ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ማንኛውም ፡ ባለአክሲዮን ፡ አንዱን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ባለአክሲዮንም ፡ ባይሆን ፡ ለመወከል ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፩፻፳፩ ። የደንበኛ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤዎች ፡ ድምፅ ፡ ብልጫና ፡ አስፈላጊው ፡ አነስተኛ ፡ የባለአክሲዮኖች ፡ ቍጥር ።

(፩) በደንበኛው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤዎች ፡ ውስጥ ፡ በመጀመሪያው ፡ ጥሪ ፤ ድምፅ ፡ የመስጠት ፡ መብት ፡ ካላቸው ፡ አክሲዮኖች ፡ ቢያንስ ፡ ሩብ ፡ ያላቸው ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ራሳቸው ፡ ወይም ፡ እንደራሴዎቻቸው ፡ እንዲገኙበት ፡ ያስፈልጋል ።

(፪) በሁለተኛው ፡ ጥሪ ፡ ድምፅ ፡ ለመስጠት ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ የአክሲዮኖች ፡ ቍጥር ፡ ማናቸውም ፡ ቢሆን ፡ ጉባኤው ፡ የሚጸና ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፫) ውሳኔዎቹም ፡ የሚደረጉት ፡ ተራ ፡ በሆነ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ነው ። ስለድ

ምዕ ፡ ብልጫውም፡ አቈጣጠር ፡ ድምፅ ፡ ያልሰጡትም ፡ ሆነ ፤ ቢኖርም ፤ ያልተ ጻፈባቸው ፡ የድምፅ ፡ መስጫ ፡ ወረቀቶች ፡ ከግምት ፡ ውስጥ ፡ አይገቡም ።

## ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ድንገተኛ ፡ ጉባኤዎች ።

### ቍ ፡ ፬፻፹፪ ። ሰነዶችን ፡ የማወቅ ፡ መብት ።

(፩) ድንገተኛ ፡ ጉባኤ ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ ባሉት ፡ በሀሥራ ፡ አምስት ፡ ቀኖች፡ ውስጥ ፡ ማንኛውም ፡ ባለአክሲዮን ፡ በማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለውሳኔ ፡ የሚቀርቡት ፡ ጽሑፎች ፡ ቢኖሩም ፤ የተቈጣጣሪዎቹን ፡ ራፖሮች ፡ ራሱ ፡ ለማወቅ ፡ ወይም ፡ ግልባጩን ፡ ለመውሰድ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) እነዚሁም ፡ ጽሑፎች ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በጽሑፍ ፡ ጥያቄ ፡ ለሚያደርግ ፡ ባለአክሲዮን ፡ ሁሉ ፡ በራሱ ፡ ኪሣራ ፡ ይላኩለታል ።

### ቍ ፡ ፬፻፹፫ ። ሥልጣን ።

በሕግ ፡ የተወሰነ ፡ ተቃራኒ ፡ ነገር ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ድንገተኛ ፡ የሆኑ ፡ ጉባኤዎች ፡ ብቻ ፡ የማኅበሩን ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ የማኅበሩን ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ የመለውጥ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

### ቍ ፡ ፬፻፹፬ ። በጉባኤው ፡ ስለ ፡ መግባት ።

ማንኛውም ፡ ባለአክሲዮን ፤ ያሉት ፡ የአክሲዮኖቹ ፡ ብዛት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ቢሆን ፡ በድንገተኛ ፡ ጉባኤዎች ፡ ተሳታፊ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ። ይህ ፡ ውሳኔ ፡ የቀደምትነት ፡ መብት ፡ ላላቸው ፡ አክሲዮን ፡ አምጪዎችም ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል።

### ቍ ፡ ፬፻፹፭ ። የድንገተኛ ፡ የጠቅላላ ፡ ጉባኤዎች ፡ ስለ ፡ ድምፅ ፡ ብልጫና ፡ ኮረም ።

(፩) የድንገተኛው ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ እንዲሆን ፡ ከተሰጠው ፡ ድምፅ ፡ ከሦስት ፡ እጅ ፡ በሁለቱ ፡ የተደገፈ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ስለ ፡ ብልጫውም ፡ አቈጣጠር ፡ ሒሳብ ፡ ድምፅ ፡ ያልሰጡትም ፡ ሆነ ፤ ቢያጋጥምም ፡ ያልተጻፈባቸው ፡ የድምፅ ፡ መስጫ ፡ ወረቀቶች ፡ ከግምት ፡ ውስጥ ፡ አይገቡም ።

(፪) በድንገተኛ ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔዎች ፡

(ሀ) የማኅበሩን ፡ ዜግነት ፡ ለመለወጥ ፤

(ለ) ባለአክሲዮኖቹ ፡ በማኅበሩ ፡ ባገቡት ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ እንዲጨምሩ ፡ ለማድረግ ፤ የተሰበሰበው ፡ ድንገተኛ ፡ ጉባኤ ፡ የድምፅ ፡ መስጠት፡ መብት፡ ያላቸውን ፡ ጠቅላላ ፡ አክሲዮኖች ፡ መሰብሰብና ፡ ውሳኔዎቻቸውም ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ የተሰጡ ፡ እንዲሆኑ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

(፫) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ ከተመለከቱት ፡ ሌላ ፤ የመተዳደሪያውን ፡ ደንብ ፡ ለመለወጥ ፡ ውሳኔ ፡ እንዲሰጡ ፡ የተደረገው ፡ ድንገተኛ ፡ ጉባኤ ፤
(ሀ) ድምፅ ፡ ለመስጠት ፡ መብት ፡ ካላቸው ፡ ባለአክሲዮኖቹ ፡ በመጀመሪያው ፡ ጥሪ ፡ ግማሽ ፤
(ለ) በሁለተኛ ፡ ጥሪ ፡ ከሦስት ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ ያላቸው ፡ ባለአክሲዮኖች ፤
(ሐ) በሦስተኛው ፡ ጥሪ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከዐሥር ፡ አንድ ፡ ያላቸው ፡ ባለአክሲዮኖች ፤ ራሳቸው ፡ ወይም ፡ እንደራሴዎቻቸው ፡ መገኘት ፡ አለባቸው ።

(፬) ከማኅበሩ ፡ ስለ ፡ መውጣት ፡ መብት ፡ የቍጥር ፡ ፬፻፳፫ ፡ ውሳኔዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ናቸው ።

ንኡስ ፡ ክፍል ፡ ፬ ።

**ልዩ ፡ ጉባኤዎች ።**

**ቍ ፡ ፬፻፳፮ ። ልዩ ፡ ጉባኤን ፡ ለመሰብሰብ ፡ የሚያስፈልግበት ፡ ጊዜ ።**

ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ያንዱን ፡ ክፍል ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ መብቶች ፡ ለመለወጥ ፡ የወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዚህን ፡ ክፍል ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ የሚሰበሰብ ፡ ልዩ ፡ ጉባኤ ፡ ካላጸናው ፡ ውሳኔው ፡ የመጨረሻ ፡ አይሆንም ።

**ቍ ፡ ፬፻፳፯ ። ሰነዶችን ፡ የማወቅ ፡ መብት ።**

በቍጥር ፡ ፬፻፳፪ ፡ የተጻፈው ፡ ድንጋጌ ፡ ለልዩ ፡ ጉባኤ ፡ ማወቅ ፡ መብት ፡ ጉዳይም ፡ ላይ ፡ በተመሳሳይነት ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፬፻፳፰ ። የልዩ ፡ ጉባኤዎች ፡ የድምፅ ፡ ብልጫና ፡ አስፈላጊ ፡ አነስተኛ ፡ የባለአክሲዮኖቹ ፡ ቍጥር ።**

(፩) በልዩ ፡ ጉባኤዎች ፤
(ሀ) በመጀመሪያው ፡ ጥሪ ፤ ድምፅ ፡ ለመስጠት ፡ መብት ፡ ካላቸው ፡ አክሲዮኖች ፡ ግማሽ ፤
(ለ) በሁለተኛው ፡ ጥሪ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከተባሉት ፡ አክሲዮኖች ፡ ሲሶ ፤
(ሐ) በሦስተኛው ፡ ጥሪ ፤ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከተባሉት ፡ አክሲዮኖች ፡ ሩብ ፡ ያላቸው ፡ ባለአክሲዮኖች ፤ ራሳቸው ፡ ወይም ፡ ወኪሎቻቸው ፡ እንዲኖሩበት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

(፪) በልዩ ፡ ጉባኤዎች ፡ ውስጥ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫው ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፳፭ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፰ ።

**የማይታ ፡ ወረቀቶች ።**

**ቍ ፡ ፬፻፳፱ ። የማይታ ፡ ወረቀቶችን ፡ ማውጣት ፡ የሚከለከልበት ፡ ሁኔታ ።**

የሚተላለፉ ፡ የማይታ ፡ ወረቀቶችን ፡ ለማውጣት ፡ የተከለከሉት ፤
(፩) የግል ፡ ሰዎች ፤

BACK



(፪) በሙሉ ፡ ዋና ፡ ገንዘባቸው ፡ ያልተከፈለ ፡ ማኅበሮች ፤
(፫) በመጀመሪያው ፡ የሒሳብ ፡ ማጠቃለያ ፡ ጊዜ ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛናቸውን ፡ ገና ፡ ያላወጡ ፡ ማኅበሮች ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፬፻፴ ። የግዴታ ፡ ወረቀት ፡ ለማውጣት ፡ የሚቻልበት ፡ ከፍተኛ ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ።

(፩) አንድ ፡ ማኅበር ፡ ለማውጣት ፡ የሚቻለው ፡ የግዴታ ፡ ወረቀት ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፤ በመጨረሻው ፡ ከጸደቀው ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ ውስጥ ፡ ከተገለጸው ፤ ከተከፈለው ፡ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ለመብለጥ ፡ አይችልም ። ከዚህ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ለመብለጥ ፡ የሚችለው ፤

(ሀ) የማኅበሩን ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ መያዣ ፡ በማድረግ ፤ የነዚህኑ ፡ የንብረቶች ፡ ዋጋ ፡ ከሦስት ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ የማይበልጥ ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ በማውጣት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡

(ለ) ከተከፈለው ፡ ዋጋ ፡ ገንዘብ ፡ በላይ ፡ የሚወጡት ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፤

(፩) በተመዘገቡ ፡ በግዴታ ፡ የምስክር ፡ ሰነዶች ፡ ወይም፡ መንግሥት፡ ባወጣቸው ፡ ወይም ፡ ዋስ ፡ ሆኖላቸው ፡ በወጡ ፡ ሰነዶችና ፡ የመክፈያቸውም ፡ ጊዜ ፡ ከግዴታ ፡ ወረቀቶቹ ፡ መክፈያ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ ባልሆነ ፡ ዋስትና፡ የተረጋገጡ ፡ እንደሆኑ ፤ ወይም ፡

(፪) መንግሥት ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በየዓመቱ ፡ በሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ዋስትና ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) ብድሩ ፡ እስኪለቀ ፡ ድረስ ፡ ዋስትና ፡ የተሰጣቸውን ፡ ወለዶች ፡ ለመክፈልና ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶችንም ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ለመክፈል ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነው፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፤ ዋስ ፡ የሆኑት ፡ ሰነዶች ፡ በባንክ ፡ አደራ ፡ መቀመጥና ፡ በየዓመቱ፡ መክፈል፡ ያለበትም ፡ ሰነድ ፡ ባንድ ፡ ባንክ ፡ ውስጥ፡መያዝ ፡ አለበት ።

(፫) በንኡስ ፡ ቍጥር፡ (፩) የተነገረው ፡ የመቀነስ ፡ ውሳኔ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ ወይም ፡ እርሻን ፡ በመያዝ ፡ በሚያበድሩ ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ፡ አይፈጸምባቸውም ።

ቍ ፡ ፬፻፴፩ ። የግዴታ፡ ወረቀቶች፡ ባሉ፡ ጊዜ፡ የማኅበሩን፡ ዋና፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መቀነስ።

የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ያወጣ ፡ ማኅበር ፡ በከፈላቸው ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ልክ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ ዋና፡ ገንዘቡን ፡ ለመቀነስ ፡ አይችልም ፤ በኪሣራ ፡ ምክንያት ፡ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ እንዲቀነስ ፡ ግዴታ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብና ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነው ፡ መጠባበቂያው ፡ ገንዘብ ፡ በመዘዋወር ፡ ላይ ፡ ካሉት ፡ ዋጋቸው ፡ ያልተከፈለ ፡ የግዴታ ፡

ወረቀቶች ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ እስኪ ተካከል ፡ ድረስ ፡ ሕጋዊ ፡ ለሆነው ፡ መጠባበቂያ ፡ የሚደረገው ፡ ቅናሽ ፡ የግዴታ ሥነዶች ፡ ወረቀቶች ፡ በወጡበት ፡ ጊዜ ፡ በነበረው ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ መታሰብ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፬፻፴፪ ። ከዋጋቸው ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ወይም ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶችን ፡ ስለ ፡ ማውጣት ።

(፩) የግዴታ ፡ ወረቀቶችን ፡ ከዋጋቸው ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ለማውጣት ፡ ይቻላል ።

(፪) በተለየ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶችን ፡ ከዋጋቸው ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ለማውጣት ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፬፻፴፫ ። የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ የሚጻፈው ፡ ቃል ።

የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ የምስክር ፡ ወረቀቶች ፡ ቀሪ ፡ ጉርድ ፡ ካለው ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ይሰጣሉ ፤ በእነሱም ፡ ላይ ፡ የሚጻፈው ፤

(ሀ) የማኅበሩን ፡ መጠሪያ ፤ ጉዳዩንና ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱን ፤ እንዲሁም ፡ ማኅበሩ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ የተመዘገበበትን ፡ ቦታ ፤

(ለ) የተመሠረተበትንና ፡ የሚያልቅበትን ፡ ቀን ፤

(ሐ) የግዴታ ፡ ወረቀቶችም ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ የተከፈለውን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፤

(መ) ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔውን ፡ የሰጠበትን ፡ ቀንና ፡ ይኸው ፡ የተመዘገበበትን ፡ ቀን ፤

(ሠ) ተራ ፡ ቍጥሩን ፤ በምስክር ፡ ወረቀቱ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፤ የወለዱን ፡ መጠንና ፡ የሚከፈልበትን ፡ ጊዜ ፤ ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ የሚመለስበትን ፡ ሁኔታ ፡ ዐይነት ፤

(ረ) የወጡትን ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ገንዘብ ፡ ልክና ፡ ከዚሁ ፡ ጋራ ፡ የተሳሰሩትን ፡ ልዩ ፡ ዋስትናዎች ፤ እንዲሁም ፡ እነዚሁ ፡ ዋስትናዎች ፡ የተቋቋሙበትን ፡ ግልጽ ፡ ጽሑፍ ፡ ቀን ፤

(ሰ) አስቀድሞ ፡ ከወጡት ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ወይም ፡ የብድር ፡ ሰነዶች ፡ ዋጋ፡ ላይ፡ መተኪያ ፡ ገንዘብ ፡ (አሞርቲስማን) ፡ ያልተደረገለትን ፡ ልክና ፡ ለነዚህም ፡ የተሰጠውን ፡ ዋስትና ፤

(ቀ) ምናልባት ፡ ቢኖርም ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶችን ፡ አምጪ ፡ ለሆኑት ፡ ሰነዳቸውን ፡ በአክሲዮን ፡ ለመለወጥ ፡ እንዲችሉ ፡ የተሰጣቸውን ፡ ምርጫ ፡ እንዲሠሩበት ፡ የተወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ጊዜዎችና ፡ እንዲሁም ፡ ለአለዋወጡ ፡ መሠረት ፡ የሚሆነውን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፩፻፴፬ ።  አክሲዮኖችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚነት ።**

በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፲፰ ፤ ፫፻፲፱ ፤ ፫፻፳፩ ፤ ፫፻፳፫ ፤ ፫፻፳፱ ፤ ፫፻፵ ፡ እና ፡ ፫፻፵፩ ፡ የተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፤ በጠቅላላ ፡ ድንጋጌነታቸው ፡ በተመሳሳ ይነት ፡ በግዴታ ፡ ወረቀቶችም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፩፻፴፭ ።  የባለ ፡ ግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ጉባኤ ።**

(፩) በአንድ ፡ ጊዜ ፡ የወጡትን ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ አምጪዎች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በሚከተሉት ፡ ቍጥሮች ፡ በተወሰነው ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፤ የሰውነት ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ተሰጠው ፡ ሆነው ፡ የጋራ ፡ ጥቅማቸውን ፡ ለመከላከል ፡ ለመሰብሰብ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ማናቸውም ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ ቢኖር ፡ እንኳ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) መሠረት ፡ ባንድ ፡ ዐይነት ፡ የወጡ ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ባለቤቶች ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፩፻፴፮ ። የግዴታ ፡ ወረቀት ፡ ባለቤቶች ፡ ጥሪ ፡ አደራረግ ።**

(፩) የግዴታ ፡ ወረቀት ፡ ባለቤቶች ፡ ጉባኤ ፡ በማኅበሩ ፡ ወይም ፡ የተሾመ ፡ እን ዳለ ፡ በኅብረቱ ፡ እንደራሴ ፡ ይጠራል ።

(፪) እንዲሁም ፡ የወጡትንና ፡ ዋጋቸው ፡ ተመልሶ ፡ ካልተከፈለባቸው ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ሐያ ፡ ከመቶ ፡ ባላቸው ፡ አምጪዎች ፡ ጥያቄ ፡ ጉባኤው ፡ ሊጠራ ፡ ይቻላል ።

(፫) የግዴታ ፡ ወረቀት ፡ ባለሀብቶች ፡ ጉባኤ ፡ ጥሪና ፡ አደራረግ ፡ ላይ ፡ የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፴፰ ፡ የተከታዩ ፡ ውሳኔዎች ፡ በተመሳሳይነት ፡ ይፈጸሙ ባቸዋል ።

(፬) ባለዕዳ ፡ የሆነው ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ ለብድሩ ፡ ዋስ ፡ የሆኑ ፡ ማኅበሮች ፡ አስ ተዳዳሪዎች ፤ ተቈጣጣሪዎች ፤ ሠራተኞች ፡ በጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ውስጥ ፡ ለግ ዴታ ፡ ወረቀት ፡ ባለቤቶች ፡ እንደራሴ ፡ ለመሆን ፡ አይችሉም ።

(፭) ለዋጋቸው ፡ መክፈያ ፡ መተኪያ ፡ ገንዘብ ፡ የተደረገላቸውና ፡ ዋጋቸውም ፡ ተመልሶ ፡ የተከፈሉትን ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ የያዙ ፡ በጉባኤዎቹ ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ አይችሉም ።

(፮) ራሱ ፡ መልሶ ፡ በገዛቸው ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ማኅበሩ ፡ በጉባኤው ፡ ተካ ፋይ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ፤ ይህ ፡ ክልከላ ፡ ባለዕዳ ፡ ከሆነው ፡ ማኅበር ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ሠላሳ ፡ ከመቶ ፡ የማያንስ ፡ በያዙ ፡ ማኅበሮችም ፡ ላይ ፡ ይጸናል ።

(፯) የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ባለሀብት ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤዎች ፡ ጥሪና ፡ አያያዝ ፡ የሚደረጉትን ፡ ወጪዎች ፡ የሚችለው ፡ ዕዳ ፡ ከፋይ ፡ የሆነው ፡ ማኅ በር ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፬፻፴፯ ። የጉባኤው ፡ መብት ።**

(፩) የባለግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ጉባኤ ፡ በቀሩትም ፡ በተቃወሙትም ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ በሌላቸውም ፡ ቢሆን ፡ በኅብረቱ ፡ ያሉትን ፡ የግዴታ ፡ ወረቀት ፡ ባለ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ የሚያስገድድ ፡ ውሳኔዎች ፡ ይሰጣል ።

(፪) ጉባኤውም ፡ ለግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ባለቤቶች ፡ ጥቅም ፡ ጥበቃና ፡ ለብድሩ ፡ ውል ፡ አፈጻጸም ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ሁሉ ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ለማ ድረግና ፡ እንዲሁም ፡ እነዚህንም ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ለማስፈጸም ፡ ስለሚያስፈል ጉት ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

**ቍ ፡ ፬፻፴፰ ። የጉባኤው ፡ ሥልጣን ።**

(፩) እንዲሁም ፡ ዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ ማኅበር ፤

(ሀ) የማኅበሩን ፡ ዐይነት ፡ ፎርም ፡ ለመለወጥ ፤

(ለ) ማኅበሩን ፡ ከሌላ ፡ ማኅበር ፡ ጋራ ፡ ለማቀላቀል ፤

(ሐ) በኅብረቱ ፡ ውስጥ፡ ያሉት ፡ የግዴታ ፡ ወረቀት፡ ባለቤቶች ፡ ባላቸው ፡ የገ ንዘብ ፡ መብት ፡ ላይ ፡ የቀደምትነት ፡ መብት ፡ ያላቸውን ፡ ሌሎች ፡ የግዴታ፡ ወረቀቶች ፡ ለማውጣት ፡ በሚያቀርበው ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ ጉባኤው ፡ ሊመክር በት ፡ ይችላል ።

(፪) የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ባለቤቶች ፡ ጉባኤ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተመለከ ቱትን ፡ አሳቦች ፡ ያልተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የማኅበሩን ፡ ዐይነት ፡ ፎርም ፡ ማለ ዋወጥ ፤ የማኅበሩን ፡ መቀላቀል ፡ ወይም ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ፡ ያላቸውን ፡ ሌሎች ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ለማውጣት ፡ የመጨረሻ ፡ ከሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፤ ቢዘገይ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ጥያቄ ፡ የሚያቀርቡትን ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ አምጪዎችን ፡ ገንዘብ ፡ መልሶ ፡ ካልከፈለ ፡ ዕዳ ፡ ከፋይ ፡ የሆነው፡ ማኅበር ፡ የጉባኤውን ፡ ውሳኔ ፡ ለማለፍ ፡ አይችልም ።

(፫) እንዲሁም ፡ ጉባኤው ፡ የብድር ፡ ውለታዎችን ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ፡ በሚቀር በው ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ ይመክርበታል ።

(፬) ጉባኤው ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ባለቤቶች ፡ ያለባቸውን ፡ ግዴታ ፡ ሊያከብድ፤ በተለይም ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲያገቡ ፡ ሊያስገድድ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶችን ፡ በአክሲዮን ፡ እንዲለውጡ ፡ ሊፈቅድ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ኅብረት ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙት ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ባለቤቶች ፡ መካከል ፡ ትክክልነት ፡ የሌለው ፡ አስተያየትን ፡ ሊሰጥ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፬፻፴፱ ። ውሳኔዎችን ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ የሚያደርጉ ፡ ሁኔታዎች ፤ (ኮረም) ።**

(፩) ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ በጉባኤው ፡ ላይ ፡ መገኘት ፡ ከሚገባቸው ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ቢያንስ ፡ ከሦስት ፡ አንዱ ፡ እጅ ፡ ያላቸው ፡ አባሎች ፡ ካሌሉበት ፡ በሚጸና ፡ አኳኋን ፡ ለመምከር ፡ አይችልም ።

(፪) በቍጥር ፡ ፬፻፶፭ ፡ የተመለከተውን ፡ ጕዳይ ፡ ለመወሰን ፡ ኮረሙ ፡ ሦስት ፡ ሩብ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፫) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ እና ፡ ፪ ፡ የተመለከተው ፡ ኮረም ፡ በመጀመሪያው ፡ ያል ሞላ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚያው ፡ አሠራር ፡ ዐይነትና፡ ጊዜ፡ ሁለተኛ ፡ ጉባኤ ፡ ለማ ድረግ ፡ ጥሪ ፡ ይደረጋል ። ይኸውም ፡ ጥሪ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ ጉባኤ ፡ የዕለት ፡ ጉዳይ ፡ ማስታወሻና ፡ ያለፈውን ፡ ጉባኤ ፡ ቀንና ፡ ውጤት ፡ ያመለክ ታል ። በጉባኤው ፡ ላይ ፡ የሚገኙት ፡ የማኅታ ፡ ወረቀቶች ፡ ቍጥር ፡ ምን ፡ ያህ ልም ፡ ቢሆን ፡ ይህ ፡ ሁለተኛ ፡ ጉባኤ ፡ በሚጸና ፡ አኳኋን ፡ ምክሩን ፡ ይቈርጣል ።

(፬) በቍጥር ፡ ፬፻፶፭ ፡ ለተመለከተው ፡ ጕዳይ ፡ በዚህ ፡ በሁለተኛው ፡ ጉባኤ ፡ ድምፅ ፡ ለመስጠት ፡ ኮረም፡ ማማሽ፡ ያልሞላ ፡ እንደ፤ ሆነ ፡ በዚያው ፡ አሠራር ፡ ዐይነትና ፡ ጊዜ ፡ አዲስ ፡ ጉባኤ ፡ ለማድረግ ፡ ጥሪ ፡ ያደርጋል ። ይህ ፡ አዲስ ፡ ጉባኤ ፡ በሚጸና ፡ አኳኋን ፡ ምክሩን ፡ ለመቍረጥ ፡ የሚችለው ፡ በጠቅላው ፡ ጉባኤ ፡ ለመግባት ፡ ከሚችሉት ፡ የማኅታ ፡ ወረቀቶች ፡ ቍጥር ፡ አንዱን ፡ ሩብ ፡ የሰበሰበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፶፯ ። የድምፅ ፡ ብልጫ ።

(፩) የቀረቡትን ፡ አሳቦች ፤ ያሉት ፡ ወይም ፡ የተወከሉት ፡ የማኅታ ፡ ወረቀት ፡ ባለቤቶች ፡ ድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ካልተቀበሏቸው ፡ በቀር ፡ ተፈጻሚነት ፡ የላቸውም።

(፪) በቍጥር ፡ ፬፻፶፭ ፡ መሠረት ፡ ለሚቀርቡት ፡ አሳቦች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ከሦስት ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፫) ከማኅታዎች ፡ ወረቀት ፡ ጋራ ፡ የተያያዘው ፡ የድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብት ፡ እያ ንዳንዱ ፡ የማኅታ ፡ ወረቀት ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ የድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብት ፡ የሚሰጥ ፡ ሆኖ ፡ ከጠቅላላው ፡ የብድር ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ ባላቸው ፡ ድርሻ ፡ መጠን ፡ የተመዛዘነ ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልጋል ።

ቍ ፡ ፬፻፶፰ ። አንዳንድ ፡ ውሳኔዎችን ፡ ስለ ፡ ማጽደቅ ።

(፩) በቍጥር ፡ ፬፻፶፭ ፡ መሠረት ፡ የተደረጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እን ዲያጸናቸው ፡ ያስፈልጋል ። ውሳኔዎቹም ፡ እንዲጸኑ ፡ ለማድረግ ፡ ማኅበሩ ፤ የማ ኅታ ፡ ወረቀቶች ፡ ባለቤቶች ፡ ኅብረት ፡ እንደራሴዎች ፤ ወይም ፡ እነዚህ ፡ የሌሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማናቸውም ፡ የማኅታ ፡ ወረቀቶች ፡ ያሉት ፡ ጉባኤው ፡ በተደረገ ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ። ይህ ፡ ካልሆነ ፡ ግን ፡ ውሳኔዎች ፡ ዋጋ ፡ እንደሌላቸው ፡ ሆነው ፡ አይ ቈጠሩም ።

(፪) በውሳኔዎቹ ፡ ላይ ፡ ተቃራኒ ፡ በመሆን ፡ ድምፅ ፡ የሰጡ ፡ ወይም ፡ በጉባኤው ፡ ውስጥ ፡ ያልነበሩ ፡ የማኅታ ፡ ወረቀት ፡ ባለቤቶች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዳያጸድ ቃቸው ፡ ለመቃወም ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፬፻፺፪ ። በግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ኅብረት ፡ እንደራሴ ።

(፩) ስለ፡ጉባኤ፡ስብሰባ፡ አስፈላጊ ፡ ቍጥር ፡ (ኰረም) ፡ ሁኔታዎች ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፺፱ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ እና ፡ ፫ ፡ በተወሰነው ፡ አኳኋንና ፡ ስለ ፡ ድምፅ ፡ ብልጫ ፡ በቍጥር፡ ፬፻፴ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ በተወሰነው ፡ መሠረት ፡ የግዴታ ፡ ወረቀት ፡ ባለቤቶች ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ የግዴታ ፡ ወረቀት ፡ ባለቤቶች፡ እንደራሴ ፡ ወይም ፡ እንደራሴ ዎች ፡ ለመሾም ፡ ለመሻር ፡ ለመተካት ፡ ይችላል ።

(፪) ስለ ፡ እንደራሴዎቹ ፡ ሥልጣንና ፡ ስለሚከፈላቸውም ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ ይህን ፡ መቻል ፡ ያለበት ፡ ዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ ማኅበር ፡ ሆኖ ፡ ጉባኤው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተነገረው ፡ የድምፅ ፡ ብልጫና ፡ ኰረም ፡ ምክሩን ፡ ይቈርጣል ።

(፫) የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ባለቤቶች ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ እንደራሴ ፡ ያልመ ረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ ማኅበር ፡ ጥያቄ ፡ ወይም ፡ ከወጡት ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ጠቅላላ ፡ ገንዘብ ፡ ከሓያው ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ ባላቸው ፡ ወይም ፡ ባለው ፡ ጥያቄ ፡ አስቸኳይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የኅብረቱን ፡ እንደራሴ ዎች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊመርጣቸው ፡ ወይም ፡ ሊተካቸው ፡ ይችላል ።

(፬) የቍጥር ፡ ፬፻፸፯ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፬ ፡ ድንጋጌ ፡ ስለ ፡ ግዴታ ፡ ወረቀት ፡ ባለቤ ቶች ፡ እንደራሴ ፡ ምርጫ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፬፻፺፫ ። የእንደራሴዎች ፡ ሥልጣን ።

(፩) የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ባለቤቶች ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ የተለየ ፡ ውሳኔ ፡ ካላ ደረገ ፡ በቀር ፡ የኅብረት ፡ እንደራሴዎቹ ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ባለቤቶች ፡ የጋራ ፡ ጥቅም ፡ በሆነው ፡ መጠን ፡ በተለይ ፡ ለብድሩ ፡ የተሰጡትን ፡ ዋስትናዎ ችን ፡ ለመቀበልና ፡ ለማኖር ፡ በኅብረቱ ፡ ስም ፡ ሆነው ፡ ማናቸውንም ፡ የሥራ ፡ አካሄድ ፡ ለመፈጸም ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

(፪) በፍርድ ፡ ቤት ፡ በከሳሽነትም ፡ ሆነ ፡ በተከሳሽነት ፡ እንደራሴዎቹ ፡ የኅብ ረቱ ፡ ነገረ ፡ ፈጆ ፡ ናቸው ።

(፫) በባለአክሲዮኖቹ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ለመገኘት ፡ መብት ፡ አላቸው ።

(፬) የግዴታ ፡ ወረቀቶችን ፡ ለመክፈል ፡ ዕጣ ፡ እንዲወጣ ፡ በሚደረገው ፡ ሥር ዐት ፡ መገኘት ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፬፻፺፬ ። ዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ ማኅበር ፡ በከሠረ ፡ ጊዜ ፡ እንደራሴዎቹ ፡ ያላቸው ፡ ሥልጣን ።

(፩) ዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ ማኅበር ፡ መክሠሩ ፡ በፍርድ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ የመጠበ ቂያ ፡ ስምምነት ፡ ተደርጎለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተመረጠ ፡ የኅብረት ፡ እንደራሴ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በኅብረቱ ፡ ውስጥ ፡ ስላሉት ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ባለቤ ቶች ፡ ሁሉ ፡ የመብታቸውን ፡ ማስረጃ ፡ ያቀርባል ። ለግዴታ ፡ ወረቀት ፡ ባለሀ ብቶች ፡ የተላኩትን፡የጥሪ፡ማስታወቂያዎች፡ሁሉ ፡ በስማቸው ፡ ሆኖ ፡ ይቀበላል ።

(፪) በኅብረቱ ፡ ስምና ፡ በጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ በሚገባ ፡ የተፈቀደለት ፡ እንደራሴ፡

BACK



ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ባለቤቶች ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ውስጥ ፡ ማንኛውንም ፡ ድምፅ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ፤ ለኮረምና ፡ ለድምፅ ፡ ብልጫ ፡ አቈጣጠር ፡ ባንድ ፡ ኅብረት ፡ ለተሰበሰቡት ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ የሚሰጠው ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብት ፡ ብቻ ፡ ይቈጠራል ።

## ምዕራፍ ፡ ፭ ።

## የማኅበር ፡ ሒሳቦች ።

### ቍ ፡ ፬፻፵፮ ። ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

የተለየ ፡ ሕግ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ንግድና ፡ ስለ ፡ ሒሳብ ፡ መዝገቦች ፡ በዚህ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ የተደነገገት ፡ በአክሲዮን ፡ ማኅበሮች ፡ ሒሳቦችም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

### ቍ ፡ ፬፻፵፯ ። ሒሳቦች ፤ የዓመት ፡ ራፖር ።

(፩) እያንዳንዱ ፡ የሒሳብ ፡ ማጠቃለያ ፡ በሚዘጋበት ፡ ጊዜ ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ በማኅበሩ ፡ ያሉትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ንብረቶችና ፡ (አክቲፍ) ፡ ያሉበትን ፡ ዕዳዎች ፡ (ፓሲፍ) ፡ ግምት ፡ የሚያመለክትና ፡ የንብረቱን ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ያደራጃሉ ።

(፪) እንዲሁም ፡ አንድ ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛን ፤ የኪሣና ፡ የትርፍ ፡ ሒሳብ ፡ ባለፈውም ፡ የሒሳብ ፡ ማጠቃለያ ፡ ሥራ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ ሁኔታና ፡ አሠራር ፡ አንድ ፡ ራፖር ፡ ያደራጃሉ ።

(፫) ራፖሩም ፡ የኪሣራውንና ፡ የትርፉን ፡ ሒሳብ ፡ የሚገልጽ ፡ ዝርዝር ፡ ማስረጃ ፡ አስተዳዳሪዎችና ፡ ተቈጣጣሪዎች ፡ በጠቅላላው ፡ የሚያገኙትን ፡ የሥራ ፡ ዋጋዎችን ፡ የሚያመለክት ፡ ትክክለኛ ፡ ማስረጃ ፤ ያለ ፡ እንደሆነም ፡ ስለ ፡ ትርፉ ፡ አከፋፈል ፡ የቀረቡት ፡ ሒሳቦች ፡ እንዲኖሩበት ፡ ያስፈልጋል ።

### ቍ ፡ ፬፻፵፰ ። ሒሳቦችንና ፡ ራፖሩን ፡ ለተቈጣጣሪዎች ፡ አዘጋጅቶ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

ለጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ጥሪ ፡ ከሚደረግበት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ካርባ ፡ ቀን ፡ በማያንስ ፡ ጊዜ ፡ የንብረቱ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፤ የሒሳቡ ፡ ሚዛን ፤ የኪሣራና ፡ የትርፍ ፡ ሒሳብ ፤ የአስተዳዳሪዎቹ ፡ ራፖር ፡ ለተቈጣጣሪዎቹ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ መሰጠት ፡ አለበት ፤ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እነዚሁ ፡ ሰነዶች ፡ ለንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ መተላለፍ ፡ አለባቸው ።

### ቍ ፡ ፬፻፵፱ ። የሒሳብ ፡ ሚዛንና ፡ የኪሣራና ፡ የትርፍን ፡ ሒሳብ ፡ ስለ ፡ ማሰናዳት ።

(፩) የሒሳብ ፡ ሚዛን ፤ የኪሣራና ፡ የትርፍ ፡ ሒሳብ ፤ የግምቶች ፡ አደራረግ ፡ ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ በተሠሩት ፡ ዐይነት ፡ ልክ ፡ በየዓመቱ ፡ መደራጀት ፡ አለባቸው ፤ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ተቈጣጣሪዎቹ ፡ ባቀረቡት ፡ ራፖር ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ምክንያቶች ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ የሒሳብን ፡ አቀራረብ ፡ ሁኔታ ፡ ወይም ፡

BACK



የማምቱን ፡ አደራረግ ፡ እንዲለወጥ ፡ የቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ ካላጸደቀው ፡ በቀር ፤ የሒሳቡ ፡ አቀራረብ ፡ የግምቱ ፡ አደራረግ ፡ አሠራሩ ፡ የማይለወጥ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) የኪሣራውና ፡ የትርፋም ፡ ሒሳብ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ምንጮች ፡ የመጡትን ፡ ኪሣራዎች ፡ ወይም ፡ ትርፎች ፡ በተለየ ፡ አርእስት ፡ ውስጥ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ።

**ቊ ፡ ፬፻፹፱ ። ተጨማሪ ፡ ሰነዶች ።**

ከሒሳብ ፡ ውጭ ፡ ያሉት ፡ እንደ ፡ ዋስትና ፡ የሆኑት ፡ የግዴታ ፡ ውሎች ፡ ከሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ ጋራ ፡ ተያይዘው ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ።

**ቊ ፡ ፬፻፺ ። አላቂ ፡ ለሚሆን ፡ ነገር ፡ መተኪያ ፡ ገንዘብና ፡ (አሞርቲስማን ፡) የገንዘብ ፡ ሥንቅ ፡ (ፕሮቪዚዮን) ።**

(፩) አላቂ ፡ ለሆኑት ፡ ንብረቶች ፡ መተኪያ ፡ የሚሆነው ፡ ገንዘብ ፡ (አሞርቲስማን) ፡ ንብረቶቹ ፡ ያገልግሎታቸው ፡ ጊዜ ፡ ሲያልቅ ፡ ከማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ እንደሚያልቁበት ፡ ሁኔታ ፡ መጠን ፡ በየዓመቱ ፡ መታሰብ ፡ አለበት ፤ በየዓመቱ ፡ የሚታሰበው ፡ የመተኪያ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ የማይበቃ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ንብረቱ ፡ እንደሚያልቅ ፡ በተገመተበት ፡ መጠን ፡ መተኪያው ፡ ገንዘብ ፡ መጨመር ፡ አለበት ።

(፪) የማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ዋጋ ፡ እያጣ ፡ ስለ ፡ መሄዱ ፡ የሚደረገው ፡ የመተኪያ ፡ ገንዘብና ፡ የገንዘብ ፡ ሥንቅ ፤ ትርፍ ፡ ባይኖርም ፡ እንኳ ፡ እያንዳንዱ ፡ የሒሳብ ፡ ማጠቃለያ ፡ በሚዘጋበት ፡ ዓመት ፡ እየተቀነሱ ፡ መታሰብ ፡ አለባቸው ።

(፫) ለማኅበሩ ፡ መመሥረቻና ፡ ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመጨመር ፡ የሚደረጉት ፡ ወጪዎች ፡ ወጪ ፡ ከተደረጉበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ቢዘገይ ፡ አምስተኛው ፡ የሒሳብ ፡ ማጠቃለያ ፡ ጊዜ ፡ ሲያልቅ ፡ መተካት ፡ አለባቸው ።

**ቊ ፡ ፬፻፺፩ ። « የሆልዲንግ » ፡ ማኅበር ፡ ሒሳቦች ።**

(፩) ማኅበሩ ፡ አንድ ፡ « የሆልዲንግ » ፡ ማኅበር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የራሱን ፡ ሒሳቦች ፡ በሚያቀርባቸው ፡ ሁኔታዎችና ፡ ጊዜያቶች ፡ የተነጣይ ፡ ማኅበሮቹን ፡ ሒሳቦች ፡ ለዓመቱ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) በተለይም ፡ ለተነጣይ ፡ ማኅበሮቹና ፡ ለሆልዲንግ ፡ ማኅበር ፡ አንድ ፡ አጠቃላይ ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛንና ፡ የኪሣራዎችና ፡ የትርፎች ፡ ሒሳብ ፡ ይደራጃሉ ።

(፫) ስለ ፡ ሆነም ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ የሒሳብ ፡ ድርጅት ፡ የማይመች ፡ ወይም ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ወጪ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ወይም ፡ የማኅበሩ ፡ የገንዘብ ፡ ጥቅም ፡ አነስተኛ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ለማኅበሩ ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ የማይጠቅም ፡

BACK



መሆኑን ፡ የገመቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) መሠረት ፡ አንድ ፡ አጠቃላይ ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛንና ፡ የኪሣራዎችና ፡ የትርፍ ፡ ሒሳብ ፡ ማደራጀት ፡ የለባቸውም ።

(፫) የሆልዲንጉ ፡ ማኅበር ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ከዚሀ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱትን ፡ የሒሳብ ፡ ማደራጀት ፡ ለማኅበሩ ፡ ወይም ፡ ለተነጣይ ፡ ማኅበሮቹ ፡ ጉዳት ፡ ለማምጣት ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ የገመቱ ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ወይም ፡ ማኅበሩና ፡ ተነጣይ ፡ ማኅበሮቹ ፡ ሥራቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በመሆኑ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ የሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ ድርጅት ፡ ሆነው ፡ ለመቈጠር ፡ ለአእምሮ ፡ ግምት ፡ የማይመች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የንግድ ፡ ሚኒስቴርም ፡ ይህንኑ ፡ ሐሳብ ፡ ሲያጸድቀው ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) መሠረት ፡ አንድ ፡ አጠቃላይ ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛንና ፡ የኪሣራዎችና ፡ የትርፍ ፡ ሒሳብ ፡ የማደራጀት ፡ ግዴታ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

## ቍ ፡ ፬፻፶፪ ። ትርፍ ።

(፩) የተጣሩ ፡ ትርፎች ፡ የሚባሉት ፡ የማኅበሩ ፡ ጠቅላላ ፡ ወጪዎችና ፡ ሌሎችም፡ የማኅበሩ ፡ ወጪዎች ፡ እንዲሁም ፡ አላቂ ፡ ለሚሆኑት ፡ ነገሮች ፡ መተኪያ ፡ ገንዘብና ፡ የገንዘብ ፡ ሥንቆች ፡ ሁሉ ፡ በሒሳብ ፡ ማጠቃለያው ፡ ጊዜ ፡ ከተገኙት ፡ ጠቅላላ ፡ ገቢዎች ፡ ላይ ፡ ከተቀነሱ ፡ በኋላ ፡ የሚገኙት ፡ ትርፎች ፡ ናቸው ።

(፪) የሚከፈለውም ፡ ትርፍ ፡ በሒሳቡ ፡ ማጠቃለያ ፡ ጊዜ ፡ ከተገኘው ፡ ትርፍ ፡ ላይ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ኪሣራዎች ፡ ከተቀነሱና ፡ እንዲሁም ፡ በፊት ፡ ታስበው፡ ያልተከፋፈሉ ፡ ትርፎችና ፡ አስፈላጊም ፡ ቢሆን ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ በተለይ ፡ ውሳኔ ፡ ሊያዝባቸው ፡ ከሚችለው ፡ መጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ተነሥተው ፡ በሒሳብ ፡ ማጠቃለያ ፡ ጊዜ ፡ በተገኘው ፡ ትርፍ ፡ ላይ ፡ ከተጨመሩ ፡ በኋላ ፡ የሚገኘው ፡ ትርፍ ፡ ነው ።

(፫) ጠቅላላውም ፡ ጉባኤ ፤ ለትርፍ ፡ አከፋፈል ፡ የሚነሡት ፡ ገንዘቦች ፡ ከየትኛው ፡ መጠባበቂያ ፡ ገንዘቦች ፡ ላይ ፡ እንደሚደረጉ ፡ በውሳኔ ፡ በግልጽ ፡ ያመለክታል ።

## ቍ ፡ ፬፻፶፫ ። የመጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ።

(፩) ከኪሣራዎችና ፡ ከትርፎች ፡ ሒሳብ ፡ ቀሪ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ ከሚያመለክታቸው ፡ የተጣሩ ፡ ትርፎች ፡ ላይ ፡ የመጠባበቂያ ፡ ገንዘቦች ፡ ይነሣሉ ።

(፪) የመጠባበቂ ፡ ገንዘቦች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ በተዘረዘሩት ፡ ዐይነት ፡ ይመደባሉ ፤

(ሀ) በሕግ ፡ አስገዳጅነት ፡ የታዘዘ ፡ ሕጋዊ ፡ መጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፤

(ለ) በማኅበሩ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ መሠረት፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ እንዲያቋቁመው ፡ ያዘዘው ፡ ተጨማሪ ፡ የሆነ ፡ መጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፤

(ሐ) በማኅበሩ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፤ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ እንዲያቋቁመው ፡ የፈቀደለት ፡ በግዴታ ፡ ያልሆነ ፡ የመጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፤

(መ) ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ በሕግ ፡ ወይም ፡ በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ ከተፈቀደው ፡ ከማናቸውም ፡ ትእዛዝ ፡ ውጭ ፡ እንዲቋቋም ፡ የወሰነው ፡ ነጻ ፡ የሆነ ፡ የመጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ።

(፫) በማኅበሩ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ሌላ ፡ ውሳኔ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ መጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፡ ወለድ ፡ የለውም ።

ቍ ፡ ፬፻፶፬ ። ሕጋዊ ፡ መጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ።

(፩) አንድ ፡ የመጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፡ ለማቋቋም ፡ ከተጣራው ፡ ትርፍ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ በየዓመቱ ፡ አንድ ፡ ሐያኛ ፡ ይነሣል ። ሕጋዊ ፡ የሆነው ፡ የመጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፡ ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ከአምስት ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ የደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የመነሣቱ ፡ አስገዳጅነት ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

(፪) በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነው ፡ የመጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ ከተወሰነው ፡ ቍጥር ፡ በታች ፡ ያነሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ተመልሶ ፡ ሊቋቋም ፡ ይገባዋል ።

ቍ፡ ፬፻፶፭። ከዋጋው፡በላይ፡በማውጣት፡በተገኘው፡ትርፍ፡የተቋቋመ፡የመጠባበቂያ፡ገንዘብ።

(፩) ድንገተኛ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲጨመር ፡ የወሰነው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከአክሲዮኑ ፡ ዋጋ ፡ በላይ ፡ የተጨመረው ፡ ትርፍ ፡ እመጠባበቂያው ፡ ገንዘብ ፡ ተቀማጭነት ፡ እንዲገባ ፡ ይወስናል ።

(፪) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ ወደፊት ፡ ስለሚደረገው ፡ የዚህ ፡ የመጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፡ አከፋፈል ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ አዲሶቹና ፡ የዱሮዎቹ ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፬፻፶፮ ። የትርፎቹ ፡ አደላደልና ፡ አከፋፈል ።

(፩) በቍጥር ፡ ፬፻፶፬ ፡ በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ በሒሳብ ፡ ማጠቃለያው ፡ ጊዜ ፡ ከተጣራው ፡ ትርፍ ፡ ላይ ፡ ለሕጋዊ ፡ የመጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፡ ማቋቋሚያ ፡ አስቀድሞ ፡ ይነሣል ።

(፪) የሕጉ ፡ ልዩ ፡ ውሳኔዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ከትርፉ ፡ ላይ ፡ ቀሪ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ይከፋፈላል ።

(፫) ለአስተዳዳሪዎቹ ፡ ስለሚሰጣቸው ፡ ገንዘብ ፡ የሚደረገው ፡ አከፋፈል ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፶፩ ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

ቍ ፡ ፬፻፶፯ ። የተወሰኑ ፡ ወይም ፡ በየጊዜው ፡ የሚሰጡ ፡ ወለዶች ።

(፩) የተወሰነ ፡ ወይም ፡ በየጊዜው ፡ የሚሰጥ ፡ ወለድ ፤ ትርፍም ፡ ባይኖር ፤ ለባለአክሲዮኖቹ ፡ ይከፈላል ፡ ተብሎ ፡ በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ ሊወሰን ፡ ይችላል ።

(፪) ይህም ፡ ልኩ ፡ የተወሰነ ፡ ወለድ ፡ ለማኅበሩ ፡ መቋቋሚያ ፡ ባለበት ፡ ሒሳብ ፡ ክፍል ፡ ይገባል ። ይህንንም ፡ ለመወሰን ፡ የሚቻለው ፤ የሥራው ፡ ማከናወኛ ፡ ድርጅት ፡ በሚሰናዳበትና ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ድርጅቱም ፡ ያን በኛ ፡ ሥራውን ፡ እንደ ፡ ጀመረ ፤ ይህ ፡ ወለድ ፡ መከፈሉ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ፤ በዚ. ሁም ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የወለዶቹም ፡ መከፈል ፡ ከምን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እንደ ሚቀር ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

(፫) በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ እና ፡ ፪ ፡ የተመለከቱት ፡ ወለዶች ፡ የሚወስን ፡ መተዳደ. ሪያ ፡ ደንብ ፡ በግልጽ ፡ ካልወጣ ፡ የማይጸናና ፡ ውጤት ፡ የሌለው ፡ ይሆናል ።

## ቍ ፡ ፩፻፶፰ ። የትርፍ ፡ ድርሻዎች ፡ አከፋፈል ፤ የባለአክሲዮኖች ፡ መብት ።

(፩) በደንብ ፡ ከጸደቀው ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ ውስጥ ፡ ከተገለጸው ፡ ከተ፡ራ ፡ ትርፍ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የትርፍ ፡ ድርሻዎችን ፡ ለባለአክሲዮኖቹ ፡ ለመክፈል ፡ አይቻ ልም ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተመለከተውን ፡ ውሳኔ ፡ ተቃራኒ ፡ በመሆን ፡ የተከ ፈሉ ፡ የትርፍ ፡ ድርሻዎች ፡ እንደ ፡ ሐሰተኛ ፡ ትርፍ ፡ ድርሻዎች ፡ ተቈጥረው ፡ እንዲከፈሉ ፡ ያደረጓቸውን ፡ ሰዎች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ በወንጀል ፡ አላፊ ፡ ያደርጉዋቸዋል ።

(፫) የትርፍ ፡ ድርሻዎች ፡ የሚከፈሉበት ፡ ቀንና ፡ ዐይነት ፡ በጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ የሚወሰኑ ፡ ናቸው ።

(፬) ለአከፋፈሉ ፡ እስከ ፡ ተወሰነው ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ትርፎችን ፡ ወይም ፡ የመጠባበቂያ ፡ ገንዘቦችን ፡ ለሚመለከተው ፡ ክፍያ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በነበረው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ የተደረጉትን ፡ ውሳኔዎች ፡ በበቂ ፡ ምክንያቶች ፡ ለማሻሻል ፡ ወይም ፡ ለመሻር ፡ ይችላል ።

(፭) ትርፉ ፡ ድርሻ ፡ እንዲከፈል ፡ ከተወሰነው ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በትርፉ ፡ ድርሻ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ባለአክሲዮኑ ፡ ከማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ይሆናል ።

## ቍ ፡ ፩፻፶፱ ። የትርፍ ፡ ድርሻዎችን ፡ ስለ ፡ መመለስ ።

የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ማኅበር ፤ ወይም ፡ ክፍያው ፡ የተደረገው ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ ሳይኖር ፡ ወይም ፡ በደንብ ፡ ከጸደቀው ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ ከሚያሳዩ ፡ ውጤት ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በቍጥር ፡ ፩፻፶፰ ፡ የተመለከቱትን ፡ ውሳ ኔዎች ፡ በመጣስ ፡ የተከፈሉት ፡ የትርፍ ፡ ድርሻዎች ፡ ከባለአክሲዮኖቹ ፡ ሊጠየቁ ፡ አይችሉም ።

## ቍ ፡ ፩፻፷ ። የሒሳቡን ፡ ሚዛን ፡ ማጽደቅ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

ጉባኤው ፡ ሒሳቡን ፡ ማጽደቁ ፤ በማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ሊደርስባቸው ፡ ከሚችለው ፡ አላፊነት ፤ አስተዳዳሪዎችን ፤ ተቈጣጣሪዎችንና ፡ ዋና ፡ ሥራ ፡ አስኪ. ያጆችን ፡ ነጻ ፡ አያወጣቸውም ።

**ቍ ፡ ፬፻፷፩ ። የሒሳብ ፡ ሚዛንን ፡ በግልጽ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ።**

የሒሳቡ ፡ ሚዛን ፡ ከሚጸድቅበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ በሠላሳ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ የዚሁ ፡ ግልባጭ ፡ እንዲሁም ፡ ጉባኤው ፡ ያጸደቀበት ፡ ፕሮሴቬርባል ፡ ግልባጭ ፡ በንግድ ፡ ኦፊሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ እንዲወጣ ፡ በአስተዳዳሪዎቹ ፡ አማካይነት ፡ ለንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ መተላለፍ ፡ አለበት ።

## ምዕራፍ ፡ ፺ ።

## በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍና ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረገው ፡ መለዋወጥ ።

**ቍ ፡ ፬፻፷፪። ጠቅላላ፡ ድንጋጌዎች፡ ተፈጻሚዎች ፡ ስለ፡ መሆናቸው ።**

(፩) የመመሥረቻውን ፡ ጽሑፍና ፡ የመተዳደሪያውን ፡ ደንብ ፡ ለመለዋወጥ ፡ ድምፅ ፡ እንዲሰጡ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ድንገተኛ ፡ ጉባኤዎች ፡ ውሳኔያቸውን ፡ የሚሰጡት ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፺፫ ፡ እስከ ፡ ፬፻፲፮ ፡ እና ፡ ከ፬፻፳፪ ፡ እስከ ፡ ፬፻፳፭ ፡ በተነገሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በቍ ፡ ፪፻፳፬ ፡ በተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ውሳኔዎቹም ፡ በማስታወቂያ ፡ መውጣት ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፬፻፷፫ ። ከማኅበሩ ፡ የመውጣት ፡ መብት ።**

(፩) የማኅበሩን ፡ ጉዳይ ፡ ወይም ፡ ዐይነት ፡ ለመለወጥ ፡ ወይም ፡ የማኅበሩን ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ለማዘዋወር ፡ የሚመለከቱትን ፡ ውሳኔዎች ፡ የሚቃወሙ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ከማኅበሩ ፡ ለመውጣትና ፡ የአክሲዮናቸውንም ፡ ገንዘብ ፡ ዋጋቸው ፡ በገበያ ፡ ላይ ፡ የተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባለፈው ፡ ፮ ስድስት ፡ ወር ፡ በነበራቸው ፡ መካከለኛ ፡ ዋጋ ፡ መሠረት ፡ ይህም ፡ ካልሆነ ፡ በመጨረሻው ፡ ማጠቃለያ ፡ ጊዜ ፡ በቀረበው ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ መሠረት ፡ በተመለከተው ፡ ማኅበሩ ፡ ያለው ፡ መላ ፡ ንብረት ፡ መጠን ፡ ለማስመለስ ፡ መብት ፡ አላቸው ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ባለአክሲዮኑ ፡ ከማኅበሩ ፡ ስለ ፡ መውጣት ፡ የሚያደረገው ፡ ማስታወቂያ ፡ ለማኅበሩ ፡ ሊሰጥ ፡ የሚገባው ፡ በሪኮማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ ሆኖ ፤

(ሀ) በጉባኤው ፡ ለነበሩት ፡ ማኅበረተኞች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጉባኤው ፡ ከተዘጋበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ቢበዛ ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፤

(ለ) በጉባኤው ፡ ላልነበሩ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ሲሆን ፡ ግን ፡ የሚሰጠው ፡ ጊዜ ፡ ውሳኔው ፡ በንግድ ፡ ኦፊሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ ከወጣበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ መላክ ፡ አለበት ።

BACK



(፫) በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ሌላ ፡ ተቃራኒ ፡ ድንጋጌ ፡ ቢኖርም ፡ እንኳን ፡ የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፬፻፸፩ ። የማኅበሩን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መጨመር ፤ አሠራሩ ።

(፩) የማኅበሩን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ አዲስ ፡ አክሲዮኖችን ፡ በማውጣትም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ያሉትን ፡ አክሲዮኖች ፡ ዋጋ ፡ በማብዛት ፡ መጨመር ፡ ይቻላል ።

(፪) የሚወጡትን ፡ አዲስ ፡ አክሲዮኖች ፤

(ሀ) በጥሬ ፡ ገንዘብም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፤

(ለ) በማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ያሉበትን ፡ ያልተከፈሉ ፡ ዕዳዎችን ፡ በአክሲዮን ፡ በማቻቻል ፡ ወይም ፤

(ሐ) መጠባበቂያ ፡ የሆኑትን ፡ ገንዘቦች ፡ ወይም ፡ ማኅበሩ ፡ ሊያዝባቸው ፡ የሚችለውን ፡ ሌሎች ፡ ገንዘቦች ፡ እዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ በማግባት፡ ወይም ፡

(መ) የማዴታ ፡ ወረቀቶችን ፡ በአክሲዮን ፡ በመለወጥ ፤ ለመክፈል ፡ ይቻላል ።

(፫) መጠባበቂያ ፡ የሆኑትን ፡ ገንዘቦች ፡ ወይም ፡ ማኅበሩ ፡ ሊያዝባቸው፡የሚችለውን ፡ ሌሎች ፡ ገንዘቦች ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ በማግባት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የአክሲዮኖቹን ፡ ዋጋ ፡ ከፍ ፡ በማድረግ ፡ የሚደረገው ፡ የዋና ፡ ገንዘብ ፡ መጨመር ፡ የሚቻለው ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፷፰ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ በተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፸፪ ። ለአስተዳዳሪዎች ፡ ሥልጣን ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

(፩) ድንገተኛው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲጨመር ፡ ሲል ፡ ያደረገውን ፡ ውሳኔ ፡ ለመፈጸም ፡ እንዲችል ፡ አስፈላጊውን ፡ ሥልጣን ፡ ለአስተዳዳሪዎች ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፪) ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመጨመር ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ እንዲወስኑ ፡ በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንቡ ፡ አስቀድሞ ፡ የሚፈቅድ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ፈራሽና ፡ እንዳልተጻፈ ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፸፫ ። የዋናው ፡ ገንዘብ ፡ አጨማመር ፡ የሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ።

የተፈቀዱት ፡ የዋና ፡ ገንዘቦች ፡ አጨማመር ፤ ዋጋ ፡ የሌላቸው ፡ ሆነው ፡ እንዳይቀሩ ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ በቍ ፡ ፬፻፸፪ ፡ መሠረት ፡ ከወሰናቸው ፡ ወይም ፡ ከፈቀዳቸው ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በአምስት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ። የማዴታ ፡ ወረቀቶችን ፡ በአክሲዮን ፡ በመለወጥ ፡ በሚደረገው ፡ የዋና፡ ገንዘብ ፡ አጨማመር ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ ጊዜ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

BACK



**ቍ ፡ ፬፻፷፮ ። አዲስ ፡ አክሲዮን ፡ ከመውጣት ፡ በፊት ፡ የማኅበሩን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ ማገባት ።**

የዋናው ፡ ገንዘብ ፡ አጨማመር ፡ ፈራሽ ፡ እንዳይሆን ፡ ማንኛውም ፡ አዲስ ፡ የሚወጣ ፡ አክሲዮን ፡ ከመውጣቱ ፡ ወይም ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ዋጋው ፡ ከመግባቱ ፡ ወይም ፡ የግዴታዎቹ ፡ ወረቀቶች ፡ በአክሲዮን ፡ ከመለወጣቸው ፡ በፊት ፡ የማኅበሩ ፡ ካፒታል ፡ በሙሉ ፡ ገቢ ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልጋል ።

**ቍ ፡ ፬፻፷፯ ። አዲስ ፡ አክሲዮኖች ፡ የሚወጡበት ፡ ሁኔታዎች ።**

ተቃራኒ ፡ ሕጋዊ ፡ ውሳኔ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ በአክሲዮን ፡ የሆኑ ፡ ማኅበሮችን ፡ ለማቋቋም ፡ ተፈጻሚዎች ፡ የሚሆኑትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ካላደረገ ፡ አዲስ ፡ አክሲዮኖችን ፡ ለማውጣት ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፬፻፷፰ ። ለሕዝብ ፡ ጥሪ ፡ በማድረግ ፡ ስለሚደረግ ፡ አክሲዮን ፡ መጻፍ ።**

ሕዝብ ፡ አክሲዮን ፡ እንዲገባ ፡ አዲሶች ፡ አክሲዮኖች ፡ የቀረቡለት ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ የሚደረግለት ፡ ጥሪ ፡ የማኅበሩ ፡ እንደራሴ ፡ በፈረመበት ፡ የማኅበር ፡ መግለጫ ፡ (ፕሮስፔክቱስ) ፡ አማካይነት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ የማኅበር ፡ መግለጫ ፡ ሊጻፍበት ፡ የሚገባው ።

(፩) ማኅበሩ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ የተጻፈበት ፡ ቀን ።

(፪) የማኅበሩ ፡ መጠሪያ ፡ ስምና ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ።

(፫) ማኅበሩ ፡ ያለው ፡ የዋና ፡ ገንዘብ ፡ ልክና ፡ የዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ዐይነት ፡ ዝር ዝር ፤ የአክሲዮኑን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነትና ፡ ክፍል ፡ ከተጻፈባቸው ፡ ዋጋና ፡ እንዳለም ፡ ከተሰጣቸው ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ጋራ ።

(፬) ሥራ ፡ አስኪያጆችና ፡ ተቈጣጣሪዎች ።

(፭) የመጨረሻው ፡ የኪሣራና ፡ የትርፍ ፡ ሒሳብ ፤ የመጨረሻው ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛንና ፡ የተቈጣጣሪዎቹ ፡ ራፖር ።

(፮) ባለፈው ፡ የመጨረሻ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ ማኅበሩ ፡ ከተመሠረተ ፡ ጀምሮ ፡ የተከፈሉት ፡ የትርፍ ፡ ድርሻዎች ።

(፯) ማኅበሩ ፡ ያወጣቸው ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ።

(፰) አዲስ ፡ አክሲዮኖችን ፡ ስለ ፡ ማውጣት ፡ የጠቅላላውን ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ በተለየም ፡ አዲስ ፡ የሚወጡትን ፡ አክሲዮኖች ፡ ጠቅላላ ፡ ገንዘብ ፤ ቍጥራቸው ፤ በአክሲዮኑ፡ ላይ፡ የተጻፈው፡ የገንዘብ፡ ልክ፤ ዐይነታቸውና፡ የሚወጡበትን፡ዋጋ።

(፱) በዐይነት ፡ የገቡትን ፡ መዋጮዎችና ፡ የተሰጡትንም ፡ ልዩ ፡ ጥቅሞች ።

(፲) አዲሶቹ ፡ አክሲዮኖች ፡ የትርፍ ፡ ድርሻን ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ የሚጀምሩ

በት ፡ ጊዜ ፤ ይኸንኑ ፡ መብት ፡ የሚቀንሱት ፡ ውሳኔዎች ፡ እንዲሁም ፡ የተሰ ጡዋቸው ፡ ልዩ ፡ መብቶች ።

(፲፩) አክሲዮን ፡ ለመግዛት ፡ የፈረመው ፡ ሰው ፡ ግዴታ ፡ የሚቈየው ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፸ ። አክሲዮን ፡ ለመግዛት ፡ የቀደምትነት ፡ መብት ።</u>

(፩) ባለአክሲዮኖች ፤ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ የሚወጣውን ፡ አዲስ ፡ አክሲዮን ፡ ለመግ ዛት ፡ ባላቸው ፡ አክሲዮን ፡ መጠን ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ፡ አላቸው ።

(፪) አክሲዮን ፡ ለመግዛት ፡ መጻፍ ፡ በሚቈይበት ፡ ጊዜ ፤ ለአክሲዮኑ ፡ በተደነገ ጉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ዐይነት ፡ ይህን ፡ መብት ፡ ለመሸጥ፡ ወይም ፡ ለማስተላለፍ ፡ ይቻላል ።

(፫) ይህ ፡ መብት ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ በአክሲዮን ፡ በሚለወጡበት ፡ ጊዜ ፡ አይ ፈጸምም ። ስለ ፡ አክሲዮኖቹ ፡ በአምጪዎች ፡ ፈቃድ ፡ በአክሲዮን ፡ የሚወጡት፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ በሚወጡበት ፡ ጊዜ ፤ በቍጥር ፡ ፬፻፷፬ ፡ በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ ይህን ፡ መብት ፡ ትቻለሁ ፡ ማለት ፡ ይገባቸዋል ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፸፩ ። የሚቀንስ ፡ የአክሲዮን፡ መግዛት ፡ መብት ።</u>

እንዳንድ ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ በቀደምትነት ፡ ስም ፡ መብት ፡ ያላቸውን ፡ አክሲ ዮኖች ፡ ለመግዛት ፡ ያልጻፉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በቀደምትነት ፡ ለመግዛት ፡ መጻፍ ፡ ከሚ ችሉት ፡ አክሲዮኖች ፡ በላይ ፡ ጠይቀው ፡ የነበሩት ፡ ሌሎች ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ከዋናው ፡ ገንዘብ ፤ውስጥ ፡ ባላቸው ፡ ድርሻ ፡ መጠንና ፡ ባደረጉት ፡ ጥያቄ ፡ ወሰን ፡ መሠረት ፡ እነዚህ ፡ የቀሩት ፡ አክሲዮኖች ፡ ይደለድሉላቸዋል ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፸፪ ። ቀሪውን ፡ ስለ ፡ ማከፋፈል ።</u>

አክሲዮኑ ፡ በቀደምትነት ፡ ከተጻፈ ፡ በኋላና ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፸፩ ፡ የተመለከተው፡ በቅናሽ ፡ የሚሆን፡ አደላደል ፡ ለዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ተጨማሪ ፡ የሆነውን ፡ በሙላው ፡ ሊጠቀልሉት ፡ ያልቻሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቀሩት ፡ አክሲዮኖች ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ በሚወስነው ፡ መሠረት ፡ ይደለደላሉ ።

<u>ቍ ፡ ፬፻፸፫ ። በቀደምትነት ፡ መብት ፡ ላይ ፡ የሚደረጉት ፡ ልዩነቶች ።</u>

(፩) ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲጨመር ፡ የሚወስነው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፸ ፡ ፬፻፸፩ ፡ እና ፡ ፬፻፸፪ ፡ የተደነገጉትን ፡ ውሳኔዎች ፡ በሙላው ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዳይሠራባቸው ፡ ለማድረግ ፡ የሚችለው ፡—

(ሀ) ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ የሚጨመርበትን ፡ ምክንያትና ፡ በቀደምትነት ፡ መብት ፡ የአክሲዮኖቹ ፡ መጻፍ ፡ የሚቀርበትን ፤ አዲሶቹን ፡ አክሲዮ ኖች ፡ የሚከፋፈሉትን ፡ ሰዎች ፤ ለያንዳንዳቸው ፡ የሚደርሱዋቸውን፡ አክሲ

ዮኖች ፡ ልክ ፤ አክሲዮኖቹ ፡ የሚወጡበትን ፡ ዋጋና ፡ ዋጋውንም ፡ ለመወሰን፡ የተወሰደውን ፡ መሠረት ፡ የሚያመለክት ፡ የአስተዳዳሪዎች ፡ ራፖር ፤

(ለ) የአስተዳዳሪዎቹን ፡ መግለጫዎች ፡ ትክክለኛነታቸውን ፡ የሚገምት ፡ የተቈጣጣሪዎች ፡ ራፖር ፤ ካመዛዘነ ፡ በኋላ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) አዲሶችን ፡ አክሲዮኖች ፡ ክፍያ ፡ የደረሳቸው ፡ ሰዎች ፡ ለራሳቸው ፡ በሚጠቅማቸው ፡ አኳኋን፡ በቍጥር ፡ ፬፻፸ ፡ ፬፻፸፩ ፡ እና ፡ ፬፻፸፪ ፡ የተደነገጉትን ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዳይሆኑ ፡ በሚደረገው ፡ ውሳኔ ፡ ራሳቸው ፡ ወይም ፡ በእንደራሴዎቻቸው ፡ በጉባኤው ፡ ድምፅ ፡ ለመስጠት ፡ አይችሉም ።

(፫) ለዚህ ፡ ውሳኔ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ኮረምና ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ልክ ፡ የሚታሰበው ፡ እነዚሁ ፡ አዲስ ፡ አክሲዮን ፡ በመግዛት ፡ የተከፋፈሉት ፡ ሰዎች ፡ ያሉዋቸው ፡ ወይም ፡ የተወከለላቸው ፡ አክሲዮኖች ፡ ከተቀነሱ ፡ በኋላ ፡ የማኅበሩን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ በሚጠቀልሉት ፡ አክሲዮኖች ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፸፬ ። በአክሲዮን ፡ የሚለወጡ ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶችን ፡ ስለ ፡ ማውጣት ።

(፩) በአክሲዮን ፡ የሚለወጡትን ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ለማውጣት ፡ ድንገተኛ ፡ ከሆነው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ አስቀድሞ ፡ ፈቃድ ፡ ያስፈልጋል ።

(፪) ይህም ፡ ፈቃድ ፤ በአክሲዮን ፡ ተለዋጭ ፡ ለሆኑ ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ አምጪዎች ፡ ጥቅም ፤ በነዚሁ ፡ ግዴታዎች ፡ መለወጥ ፡ ለሚወጡት ፡ አክሲዮኖች ፤ ባለአክሲዮኖቹ ፡ በቀደምትነት ፡ መብት ፡ ለመግዛት ፡ የመጻፍ ፡ መብታቸውን ፡ በመግለጽ ፡ መተዋቸውን ፡ የገለጹ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።

(፫) እንዲሁ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፸፫ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ (ሀ) የተመለከተው ፡ የአስተዳዳሪዎቹ ፡ ራፖር ፤ የሚወጣበትን ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ ለግዴታ፡ ወረቀት ፡ አምጪዎች ፡ የቀረበው ፡ ምርጫ ፡ ለመጠቀም ፡ የሚቻልበትን ፡ ጊዜ ፡ እንዲሁም ፡ የግዴታዎቹ ፡ ወረቀቶች ፡ በአክሲዮኖቹ ፡ የሚለወጡበትን ፡ መሠረት ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

(፬) ለአለዋወጡ ፡ መሠረት ፡ የሆኑትን ፡ ጉዳዮች ፡ በመመልከት ፡ ለጉባኤው ፡ በቀረቡት ፡ አሳቦች ፡ ላይ ፡ ተቈጣጣሪዎቹ ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ ራፖር ፡ ያዘጋጃሉ ።

ቍ ፡ ፬፻፸፭ ። አክሲዮኖችን ፡ ለመግዛት ፡ ልዩ ፡ የመጻፍ ፡ ቀደምትነት ፡ መብትን ፡ የሚሰጡ ፡ ጽሑፎች ፡ ማውጣት ፡ ክልክል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆን ፤ አክሲዮንን ፡ ለመግዛት ፡ ልዩ ፡ የመጻፍ ፡ ቀደምትነት ፡ መብትን ፡ የሚሰጥ ፡ ጽሑፍ ፡ማውጣት ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፬፻፸፮ ። አክሲዮንን ፡ ለመግዛት ፡ የመጻፍ ፡ መብት ፡ የሚሠራበት ፡ ጊዜ ።

በፊት ፡ ለነበሩት ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ አክሲዮንን ፡ ለመግዛት ፡ የመጻፍ ፡ መብታቸውን ፡ እንዲሠሩበት ፡ የተፈቀደው ፡ ጊዜ ፡ አክሲዮኑን ፡ ለመግዛት ፡ መጻፍ ፡ ከተ

፫መረበት ፡ ጊዜ ፡ እንሥቶ ፤ ከሠላሳ ፡ ቀን ፡ ያነሰ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፬፻፸፯ ። አክሲዮንን ፡ ለመግዛት ፡ የመጻፍ ፡ ማስታወቂያ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ።**

(፩) አክሲዮን ፡ ለመግዛት ፡ መጻፍ ፡ የሚጀመርበትን ፡ ቀን ፡ በንግድ ፡ ኦፊሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ አስተድሞ ፡ ከዐሥር ፡ ቀን ፡ በማያንስ ፡ ጊዜ ፡ ማስታወቂያ ፡ በማውጣት ፤ እንዲሁም ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑትን ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ለመቀበል ፡ የተፈቀደለት ፡ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ ባለና ፡ የቀደምትነት ፡ መብታቸውን ፡ በአክሲዮን ፡ ለመግዛት ፡ መጻፉ ፡ የሚጀምርበትንና ፡ የሚያልቅበትን ፡ ቀን ፤ እንዲሁም ፡ አክሲዮኖቹ ፡ የሚወጡበትን ፡ ዋጋና ፡ ከዋጋቸውም ፡ ላይ ፡ የሚከፈለውን ፡ ልክ ፡ በሚገልጽ ፡ ጋዜጣ ፡ ባለአክሲዮኖቹ ፡ እንዲያውቁት ፡ ይደረጋል ።

(፪) አክሲዮኖቹ ፡ ሁሉ ፡ በስም ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አክሲዮን ፡ ለመግዛት ፡ መጻፉ ፡ ከሚጀመርበት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ከዐሥር ፡ ቀን ፡ በማያንስ ፡ ጊዜ ፤ ይህ ፡ ማስታወቂያ ፡ ባንድ ፡ ሪኮማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ ለባለአክሲዮኖቹ ፡ ሁሉ ፡ ለመላክ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፬፻፸፰ ። አዲስ ፡ አክሲዮኖችን ፡ ለመግዛት ፡ ስለ ፡ መጻፍ ።**

(፩) ተከፋይ ፡ የሚሆነውን ፡ ገንዘብ ፡ ይዞ ፡ ካልቀረበ ፡ አክሲዮንን ፡ ለመግዛት ፡ መጻፍ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

(፪) ስለ ፡ ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ አጨማመር ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ አክሲዮንን ፡ ለመግዛት ፡ መጻፍ ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፤ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ቍ ፡ ፫፻፲፪ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፫) እና ፡ ፫፻፲፱ ፡ እስከ ፡ ፫፻፳፩ ፡ የተሰጡት ፡ ውሳኔዎች ፡ ይፈጸሙባቸዋል ።

**ቍ ፡ ፬፻፸፱ ። አክሲዮንን ፡ ለመግዛት ፡ መጻፍን ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።**

አስተዳዳሪዎቹ ፡—

(ሀ) የአዲስ ፡ አክሲዮኖች ፡ በሙሉ ፡ ለመግዛት ፡ መጻፋቸውን ፤

(ለ) ከዋጋውም ፡ ላይ ፡ ተከፋይ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ መግባቱን ፤

(ሐ) የዋናው ፡ ገንዘብ ፡ መጨመር ፡ በርግጥ ፡ መፈጸሙን ፤

(መ) እንዲሁም ፡ ከዚህ ፡ አሠራር ፡ የተነሣ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንቡን ፡ መለወጥን ፤ መመዝገብ ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፬፻፹ ። በዐይነት ፡ መዋጮ ፡ ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መጨመር ።**

የዋናው ፡ ገንዘብ ፡ መጨመር ፡ የተፈጸመው ፡ በዐይነት ፡ መዋጮ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ጥቅም ፡ ያለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፲፰ ፡ ፫፻፳፩ ፡ እና ፡ ፫፻፳፪ ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፩ ። በማቻቻል ፡ ዋጋቸውን ፡ ስለ ፡ መክፈል ።**

(፩) የማኅበሩን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለመጨመር ፡ የወጡት ፡ የጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ አዲስ ፡ አክሲዮኖች ፤ አክሲዮንን ፡ ለመግዛት ፡ መጻፍ ፡ በሚጀምርበት ፡ ጊዜ ፡ ገንዘብ ፡ ተከፋይ ፡ ከሆኑትና ፡ ከማኅበሩ ፡ ጋራ ፡ በማቻቻል ፡ ዋጋቸው ፡ ፡ በዕዳው ፡ ሊከፈል ፡ ይቻላል ።

(፪) እነዚህ ፡ አክሲዮኖች ፡ በአስተዳዳሪዎቹ ፡ ጥንቃቄና ፡ በተቈጣጣሪዎች ፡ በተረጋገጠ ፡ የሒሳብ ፡ መግለጫ ፡ ውስጥ ፡ እንዲሆኑ ፡ ይደረጋሉ ፤ እንዲሁም ፡ በተከፈለው ፡ ዕዳ ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ ተቈጣጣሪዎቹ ፡ ራፖር ፡ ያዘጋጃሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፪ ። የማኅበሩን ፡ መጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፡ በማግባት ፡ ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መጨመር ።**

የቍጥር ፡ ፬፻፶፬ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ ውሳኔዎች ፡ አፈጻጸም ፡ ሳይነካ ፤ ድንገተኛው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ የማኅበሩን ፡ መጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ በቀጥታ ፡ በማግባት ፡ ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመጨመርና ፡ በዚሁም ፡ ምክንያት ፡ የመተዳደሪያውን ፡ ደንብ ፡ ለመለወጥ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ። ስለ ሆነም ፡ ከሕግ ፡ የሆነው ፡ መጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፡ ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ጋራ ፡ በተቀላቀለ ፡ ጊዜ ፡ ከሕግ ፡ የሆነው ፡ የድሮው ፡ መጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ እንደገና ፡ እስከ ፡ ተጠራቀመ ፡ ድረስ ፡ ለባለአክሲዮኖች ፡ ትንድም ፡ ማከፋፈል ፡ ሊደረግ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፫ ። የማኅበሩን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ መልሶ ፡ ስለ ፡ መክፈል ፡ (አሞርቲስማን) ።**

(፩) በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ድንጋጌ ፡ ወይም ፡ በድንገተኛ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የማኅበሩን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ መልሶ ፡ መክፈል ፡ አይቻልም ።

(፪) ሕጋዊ ፡ የሆነው ፡ የመጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፡ ሳይነካ ፡ ከማኅበሩ ፡ ትርፎች ፡ ወይም ፡ መጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ፡ ብቻ ፡ የማኅበሩን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ መክፈል ፡ ይቻላል ።

(፫) ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ መክፈሉ ፡ የሚፈጸመው ፤ በአንድ ፡ ዐይነት ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ አክሲዮኖች ፡ መልሶ ፡ በመግዛት ፡ ነው ። አክሲዮኖቹ ፡ መልሰው ፡ የሚገዙት ፡ በዕጣ ፡ ሊመረጡ ፡ ይችላሉ ።

(፬) ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ የመክፈል ፡ ተግባር ፤ የማኅበሩን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ መቀነስ ፡ ሊያስከትል ፡ አይገባውም ።

**ቍ ፡ ፬፻፹፬ ። የማኅበሩን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መቀነስ ።**

የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ መቀነስ ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡

ከሚጠራው ፡ ጉባኤ ፡ ጥሪ ፡ በፊት ፤ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከፀሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ አስቀድሞ ፡ ለተቈጣጣሪዎቹ ፡ አሳቡ ፡ መሰጠት ፡ አለበት ። ተቈጣጣሪዎቹም ፡ በአሠራሩ ፡ ምክንያቶችና ፡ ሁኔታዎች ፡ ላይ ፡ አስተያየታቸውን ፡ ባንድ ፡ ራፖር ፡ ለጉባኤው ፡ ያስታውቃሉ ።

ቍ ፡ ፬፻፹፭ ። የዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ መቀነስ ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።

የዋናው ፡ ገንዘብ ፡ መቀነስ ፤ በንግድ ፡ መዝገብና ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፷፬ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በማስታወቂያ ፡ መውጣት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፬፻፹፮ ። በኪሣራ ፡ ምክንያት ፡ ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መቀነስ ።

በኪሣራ፡ ምክንያት ፡ ዋናው፡ ገንዘብ ፡ የተቀነሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ ከቍጥር፡ ፬፻፹፩፡ እስከ ፡ ፬፻፺ ፡ ያሉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፬፻፹፯ ። የአቀናነሱ ፡ ዐይነት ።

(፩) ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ መቀነስ ፡ የሚቻለው ፤
 (ሀ) በአክሲዮኖች ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ዋጋ ፡ በመቀነስ ፤
 (ለ) ብዛታቸው ፡ ከድሮ ፡ አክሲዮኖች ፡ ባነሱ ፡ አዲስ ፡ አክሲዮኖች ፡ የድሮዎቹን ፡ በመተካት ፡ ነው ።

(፪) ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ የተቀነሰው ፤ ብዛታቸው ፡ የድሮ ፡ አክሲዮኖች ፡ ባነሱ፡ አዲስ፡ አክሲዮኖች ፡ የድሮዎቹን ፡ በመለወጥ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ ለማከናወን ፡ በቂ ፡ የሆኑ ፡ ብዛት ፡ ያላቸው ፡ አክሲዮኖች ፡ የሌላቸው ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ቅናሹን ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ (ለ) መሠረት ፡ የሚወስነው ፡ ጠቅላላ፡ ጉባኤ ፡ በወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለመለወጥ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ አክሲዮኖች፡ መግዛት ፤ ይህንን ፡ ካልቻለ ፡ ለሌላ ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ መሸጥ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፬፻፹፰ ። ለባለአክሲዮኖች ፡ የተጠበቁ ፡ ወይም ፡ የተሰጡ ፡ መብቶች ።

ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲቀነስ ፡ የሚወስነው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ በአክሲዮኖቹ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ የአክሲዮኖቹ ፡ ቍጥር ፡ ብዛት ፡ በመቀነሱ ፡ ባለአክሲዮኖቹ ፡ በተቀነሰባቸው ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ማናቸውም ፡ ትርፍ ፡ ከመከፈሉ ፡ በፊት ፡ ገንዘባቸው ፡ ተመልሶ ፡ እንዲከፈላቸው ፡ መብት ፡ አላቸው፡ ብሎ ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፬፻፹፱ ። የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መብት ።

ከማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆኑ ፡ መብታቸው ፡ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ መቀነስ ፡ በማስታወቂያ ፡ ከመነገሩ ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገንዘቡ ፡ ካልተከፈላቸው ፡ ወይም ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ዋስትና ፡ ካልተሰጣቸው ፡ በቀር ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ መሆናቸው ፡ ሲጀመር ፡ ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ተመልሶ ፡ እስኪሞላ ፡ ድረስ ፡ በቍ ፡ ፬፻፹፰ ፡ የተሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡

ወይም ፡ ማናቸውም ፡ የትርፍ ፡ ክፍያ ፡ እንዳይደረግ ፡ መቃወም ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፺ ። ሕግ ፡ ከሚያዘው ፡ አነስተኛ ፡ ገንዘብ ፡ በታች ፡ ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መቀነስ ።**

(፩) በደረሰው ፡ ኪሳራ ፡ ምክንያት ፡ ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፷፰ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ ከተመለከተው ፡ አነስተኛ ፡ ገንዘብ ፡ በታች ፡ የተቀነሰ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፹፰ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በንግድ ፡ ኦፊሲዮል ፡ ጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ ከወጣበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በቍ ፡ ፫፻፷፰ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ በተፈቀደው ፡ መሠረት ፡ ከዚሁ ፡ አነስተኛ ፡ ገንዘብ ፡ በላይ ፡ እንዲጨመር ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

(፪) የዚሁ ፡ ቍጥር ፡ ውሳኔ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፹፱ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ መብት ፡ ሳይነካ ፡ ነው ።

(፫) በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ የዋናው ፡ ገንዘብ ፡ መጨመር ፡ ሊፈጸም ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማኅበሩ ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ እንዲለወጥ ፡ ካልተደረገ ፡ በማናቸውም ፡ ባለጥቅም ፡ ጥያቄ ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፩ ። በኪሳራ ፡ ምክንያት ፡ ሳይሆን ፡ ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መቀነስ ።**

በኪሳራ ፡ ምክንያት ፡ ሳይሆን ፡ ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ የተቀነሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከቍጥር ፡ ፬፻፺፪ ፡ እስከ ፡ ፬፻፺፬ ፡ ያሉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፪ ። የባለአክሲዮኖች ፡ ትክክለኛነት ።**

የዋናው ፡ ገንዘብ ፡ መቀነስ ፡ በባለአክሲዮኖች ፡ መብት ፡ ትክክለኛነት ፡ ሊያፋልስ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፬፻፺፫ ። የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መብት ።**

(፩) ከማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ መብታቸው ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፹፰ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ በንግድ ፡ ኦፊሲዮል ፡ ጋዜጣ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ መቀነስ ፡ ከመቶ ፡ ዐሥር ፡ በበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ከዚሁ ፡ በላይ ፡ የተነገረው ፡ ማስታወቂያ ፡ ከወጣበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ የቀረበውን ፡ ለመቃወም ፡ ይችላሉ ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ የቀረበውን ፡ መቃወሚያውን ፡ አልቀበልም ፡ ለማለት ፡ ወይም ፡ ተቃዋሚ ፡ ለሆኑት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍላቸው ፡ ወይም ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጥ ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፫) የመቀነሱ ፡ ተግባር ፡ ሊጀመር ፡ የሚቻለው ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተነገረው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፬፻፺፬ ። ስለ ፡ መቀነስ ፡ የሚደረግ ፡ ፕሮሴቨርባል ።

(፩) የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ መቀነስ ፡ ከሚወሰንበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ባንድ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፹፰ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ በንግድ ፡ አፊሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ ከወጣበት ፡ ጀምሮ ፡ እጅግ ፡ ቢዘገይ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ በሠሩት ፡ ፕሮሲቨርባል ፡ መገለጽ ፡ አለበት ።

(፪) ይህ ፡ ፕሮሴቨርባል ፤ የመተዳደሪያ ፡ ደንቡን ፡ የሚያሻሽሉት ፡ የጠቅላላ ፡ ጉባኤዎች ፡ ውሳኔዎች ፡ በሚደረጉት ፡ ዐይነትና ፡ ጊዜ ፡ በማስታወቂያ ፡ ይወጣል ።

ምዕራፍ ፡ ፰ ።

ስለ ፡ ማኅበር ፡ መፍረስና ፡ ስለ ፡ ሒሳብ ፡ ማጣራት ።

ቍ ፡ ፬፻፺፭ ። ማኅበሩ ፡ የሚፈርስባቸው ፡ ምክንያቶች ።

(፩) በአክሲዮን ፡ የሆኑ ፡ ማኅበሮች ፡ የሚፈርሱባቸው ፡ ምክንያቶች ፤

(ሀ) በድንገተኛ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲቀጥል ፡ ካልተወሰነ ፡ በቀር ፡ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፤

(ለ) ማኅበሩ ፡ የተቋቋመበት ፡ ሥራ ፡ ሲያልቅ ፤

(ሐ) በነገሩ ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ የማኅበሩ ፡ ጉዳይ ፡ (ዓላማ) ፡ ሊደርስበት ፡ የማይቻል ፡ ሲሆን ፤

(መ) አስቀድሞ ፡ እንዲፈርሱ ፡ ድንገተኛ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ፈቅዶ ፡ ሲወስን ፤

(ሠ) ከማኅበረተኞቹ ፡ አንዱ ፡ ባቀረበው ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲያዝ ፤

(ረ) በቍጥር ፡ ፫፻፲፩ ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ አክሲዮኖቹ ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ እጅ ፡ ሲጠቀለሉ ፤

(ሰ) የኪሣራ ፡ ክስ ፡ ሲጀመር ፤

(ሸ) ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ሦስቱ ፡ ሩብ ፡ ሲጠፋ ፡ ነው ።

(፪) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ በ (ሸ) የተመለከተው ፡ ሁናቴ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲፈርስ ፡ ወይም ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲቀጥል ፡ ለመወሰን ፡ ድንገተኛ ፡ የሆነ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ መጠራት ፡ አለበት ።

(፫) በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ ወይም ፡ ተቈጣጣሪዎቹ ፡ ጠቅላላውን ፡ ጉባኤ ፡ ለመጥራት ፡ ሳይችሉ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ጉባኤው ፡ በደንብ ፡ ለመቋቋም ፡ የማይችል ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ማናቸውም ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፸፪ ። ሒሳብ ፡ አጣሪዎችን ፡ ስለ ፡ መሾምና ፡ ስለ ፡ መሻር ።**

(፩) ሒሳብ ፡ አጣሪ ፡ ወይም ፡ አጣሪዎች ፡ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ሊመረጡ ፡ ይቻላል ፤ እንዲህ ፡ ባልሆነ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የማኅበሩን ፡ መፍረስ ፡ የሚወስነው ፡ ጉባኤ ፡ ይሾማቸዋል ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪዎች ፡ ያልተመረጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እነዚሁን ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪዎች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲመርጥ ፤ ማኅበረተኞች ፤ አስተዳዳሪዎች ፡ ወይም ፡ ተቈጣጣሪዎች ፡ ሊጠየቁ ፡ ይችላሉ ።

(፫) ሒሳብ ፡ አጣሪዎችን ፡ ጉባኤው ፡ ሊሽራቸው ፡ ይችላል ። ሒሳብ ፡ አጣሪዎቹን ፡ በቂ ፡ በሆኑ ፡ ምክንያቶች ፡ ማኅበረተኞች ፡ ወይም ፡ ተቈጣጣሪዎች ፡ በሚያቀርቡት ፡ ጥያቄ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊሽራቸው ፡ ይችላል ።

(፬) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ በ፩ኛውና ፡ በ፪ኛው ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ አዲስ ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪዎች ፡ በመሾም ፡ ጕዳይ ፡ ላይም ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፫፻፸፫ ። ሒሳቡ ፡ በሚጣራበት ፡ ጊዜ ፡ የማኅበሩ ፡ መቈየት ።**

(፩) የሒሳብ ፡ ማጣራት ፡ ሥራዎች ፡ እስከሚቈዩበት ፡ ጊዜ ፡ በሒሳብ ፡ ማጣራት ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ማኅበር ፡ ከመጠሪያ ፡ ስሙ ፡ ጋራ ፡ « በማጣራት ፡ ላይ ፡ ያለ » የሚል ፡ ቃል ፡ ተጨምሮበት ፡ በሕግ ፡ የተሰጠውን ፡ የሰውነት ፡ መብቱና ፡ የመጠሪያ ፡ ስሙን ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ይቈያል ።

(፪) ሒሳቡ ፡ በሚጣራበት ፡ ጊዜ ፡ የማኅበሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሥራዎች ፡ ለዚሁ ፡ ተግባር ፡ አስፈላጊ ፡ በሆኑት ፡ ሥራዎች ፡ የተወሰኑና ፡ በዐይነታቸውም ፡ ከሒሳብ ፡ አጣሪዎች ፡ ሥልጣን ፡ ውስጥ ፡ ያልሆኑት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፫፻፸፬ ። መክሠርና ፡ ሒሳብ ፡ ማጣራት ።**

(፩) ከሠረ ፡ ተብሎ ፡ ማኅበሩ ፡ በፍርድ ፡ የተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሒሳቡ ፡ ማጣራት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በአምስተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ በተደነገጉት ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

(፪) የማኅበሩ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ለማኅበሩ ፡ ለመወከል ፡ ሥልጣን ፡ የሚኖራቸው ፡ በነገሩ ፡ እንዲገቡ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነበት ፡ መጠን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፫፻፸፭ ። የሒሳብ ፡ አጣሪዎች ፡ ግዴታዎችና ፡ ኀላፊነት ።**

(፩) በሕጉ ፡ ወይም ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንቡ ፡ ልዩ ፡ ውሳኔዎች ፡ ከሌሉ ፡ በቀር ፡ የሒሳብ ፡ አጣሪዎቹ ፡ ግዴታዎችና ፡ ኀላፊነት ፡ እንደ ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

(፪) ሒሳብ ፡ አጣሪዎቹ ፡ ከአስተዳዳሪዎቹ ፡ እጅ ፡ የማኅበሩን ፡ ሀብቶችንና ፡ የሒሳብ ፡ ሰነዶችን ፡ በኀላፊነት ፡ ይቀበላሉ ። አስተዳዳሪዎቹም ፡ የመጨረሻው ፡ የሒሳብ ፡

ማጠቃለያ ፡ ጊዜና ፡ የሒሳቡ ፡ ማጣራት ፡ በተጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ መካከል፡ባለው፡ ጊዜ ፡ ያደረጉትን ፡ የሥራቸውን ፡ መግለጫ ፡ ያስረክቧቸዋል ።

(፫) ተቈጣጣሪዎችና ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ ማኅበሩ ፡ ያሉትን ፡ ንብረትና ፡ ያሉበትን ፡ ዕዳዎች ፡ የሚገልጽ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ያደራጃሉ ። በዚህም ፡ ዝርዝር ፡ አስተዳዳሪዎቹና ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪዎቹ ፡ ይፈርሙበታል ።

(፬) ያለው ፡ ገንዘብ ፡ የማኅበሩን ፡ ዕዳዎች ፡ ለመክፈል ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ያልተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪዎቹ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ በአክሲዮኖቻቸው ፡ ላይ ፡ ያልከፈሉትን ፡ ድርሻ ፡ መጠየቅ ፡ ይገባቸዋል ።

ቍ ፡ ፭፻ ። የሒሳብ ፡ አጣሪዎች ፡ ሥልጣን ።

(፩) ሒሳብ ፡ አጣሪዎች ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንቡ ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በሾማቸው ፡ ጉባኤ ፡ ሥልጣናቸውን ፡ የሚቀንሱ ፡ ውሳኔዎች ፡ ካልደተረጉ ፡ በቀር ፡ የሒሳብ ፡ ማጣራቱን ፡ ተግባር ፡ በመልካም ፡ ለማካሄድ ፡ ሙሉ ፡ የሆነ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ። በተለይም ፡ የማኅበሩን ፡ ሀብት ፡ በጅምላ ፡ ለመሸጥ ፤ ነገሩንም ፡ በስምምነት ፡ ለመጨረስና ፡ በመግባባት ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላሉ ፤ በፍርድ ፡ ቤትም፡ የማኅበሩ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ተጀምሮ ፡ ለነበረው ፡ ውል ፡ አፈጻጸም ፡ አዲስ ፡ ሥራዎች ፡ አስፈላጊዎች ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ ወይም ፡ የሒሳብ ፡ ማጣራቱ ፡ ጥቅም ፡ ያስገደደ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር፡ አዲስ ፡ ሥራዎች ፡ ለመጀመር ፡ አይችሉም ። በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ከተነገሩት ፡ ውሳኔዎች ፡ ውጭ ፡ ለሚሠሩት ፡ ሥራዎች ፡ እየራሳቸው ፡ ባንድነት ፡ ሳይከፋፈል፡ አላፊዎች ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፭፻፩ ። የማኅበሩ ፡ ዕዳዎች ፡ በሙሉ ፡ ከመከፈላቸው ፡ በፊት ፡ ያለውን ፡ ንብረት ፡ በማኅበረተኞቹ ፡ መካከል ፡ ማከፋፈልን ፡ ስለ ፡ መከልከል ።

ከማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የሆኑት ፡ ካልተከፈሉ ፡ ወይም ፡ የነሱን ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ ተይዞ ፡ ካልተቀመጠ ፡ በቀር ፡ አጣሪዎች ፡ በማኅበረተኞቹ ፡ መካከል ፡ የማኅበሩን ፡ ንብረት ፡ በከፊልም፡ ቢሆን፡ ለማከፋፈል ፡ አይችሉም ።

ቍ ፡ ፭፻፪ ። ገንዘብ ፡ ጠያቂዎችን ፡ ስለ ፡ መጥራት ።

(፩) የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ አከፋፈል ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪዎቹ ፡ ሥራ ፡ በሚጀምሩበት ፡ ጊዜ ፡ ባዘጋጁት ፡ በሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

(፪) ስለዚሁ ፡ ነገር ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ የማኅበሩ ፡ መፍረስ ፡ ተነግሮዋቸውና ፡ አቤቱታቸውን ፡ እንዲያስታውቁና ፡ ለሚጠይቁትም ፡ ገንዘብ ፡ ደጋፊ ፡ የሚሆኑ ፡ ሰነዶቻቸውን ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ይደረግላቸዋል ።

BACK



(፫) በማኅበሩ ፡ መዝገቦች ፡ ውስጥ ፡ ለተጻፉት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ለታወቁም ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በሪኮማንዴ ፡ ደብዳቤዎች ፡ በቀጥታ ፡ ይላክላቸዋል ። ለሌሎቹ ፡ ግን ፡ በንግድ ፡ ኦፊሲዩል ፡ ጋዜጣና ፡ በተጨማሪም ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ ይነገራቸዋል ። በንግድ ፡ ኦፊሲዩል ፡ ጋዜጣ ፡ የሚወጡት ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ለሦስት ፡ ጊዜ ፡ በተከታይነት ፡ በወር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተደጋግመው ፡ መውጣት ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፫፻፫ ። የገንዘብ ፡ ጠያቂዎችን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ።

(፩) የታወቁት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ማስረጃቸውን ፡ ሳያቀርቡ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሚከፈላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቀመጣል ።

(፪) እንዲሁም ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ለሚፈልጉት ፡ ሒሳብ ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሆኑ ፡ ዋስትናዎች ፡ ካልተሰጡአቸው ፡ ወይም ፡ የማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ አከፋፈል ፡ እነዚሁ ፡ ግዴታዎች ፡ እስኪከፈሉ ፡ ድረስ ፡ ቀን ፡ ካልተደረገለት ፡ በቀር ፡ ሳልተፈጸመው ፡ ሥራ ፡ ድርጅት ፡ ግዴታ ፡ መፈጸሚያው ፡ ጊዜ ፡ ሳልደረሰው ፡ ወይም ፡ በክርክር ፡ ላይ ፡ ላሉት ፡ የማኅበሩ ፡ ግዴታዎች ፡ ተመዛዛኝ ፡ የሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ተይዞ ፡ መቀመጥ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፫፻፬ ። የመጨረሻው ፡ ሒሳብ ፡ ሚዛን ።

(፩) የማኅበሩ ፡ ዕዳ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪዎቹ ፡ ለያንዳንዱ ፡ አክሲዮን ፡ የሚደርሰውን ፡ የተጣራውን ፡ ንብረት ፡ ድርሻ ፡ በማመልከት ፤ የመጨረሻውን ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ ማደራጀት ፡ አለባቸው ።

(፪) በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆኑ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከሌሉ ፡ በቀር ፡ የድርሻው ፡ አከፋፈል ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ የሚወሰነው ፡ ልክ ፡ ከአክሲዮኖቹ ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ በርግጥ ፡ በተከፈለው ፡ መጠንና ፡ ከአክሲዮኖቹም ፡ ጋራ ፡ በተያያዙት ፡ የቀዳሚነት ፡ መብቶች ፡ መጠን ፡ ይደረጋል ።

(፫) የሒሳብ ፡ አጣሪዎቹ ፡ የፈረሙበት ፡ የሒሳቡ ፡ ሚዛን ፡ ከተቈጣጣሪዎቹ ፡ ራፖር ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ ለንግድና ፡ ለእንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይሰጣል ።

(፬) በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፫ ፡ መሠረት ፡ የተደረገው ፡ አሰጣጥ ፡ በተፈጸመ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ማንኛውም ፡ ማኅበርተኛ ፡ ስለ ፡ ተሰጠው ፡ ሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ ተቃዋሚ ፡ የሆነውን ፡ ቃል ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ። ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተቃውመው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ሁሉ ፡ ሊገቡ ፡ በሚችሉበት ፡ በአንድ ፡ ሥርዐት ፡ ነገሩ ፡ ይታያል ፤ ሥርዐቱም ፡ የሚጀመረው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተው ፡ ጊዜ ፡ ሲያልቅ ፡ ነው ፤ ስለዚሁ ፡ በጕዳዩ ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ በማኅበረተኞቹ ፡ ሁሉ ፡ በክርክሩ ፡ ውስጥ ፡ ሳልገቡትም ፡ ማኅበረተኞች ፡ ጭምር ፡ የመጨረሻ ፡ ፍርድ ፡ ይሆናል ።

(፫) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተመለከተው ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አንዳች ፡ አቤቱታ ፡ ያልቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመጨረሻውን ፡ ሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ እንዳጸደቁት ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፫፻፮ ። ክፍያው ፡ እንዲቈይ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

ባለአክሲዮኖቹ ፡ የተጣራውን ፡ ነጻ ፡ ገንዘብ ፡ ለመከፋፈል ፡ የሚችሉት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ እንዲሰበሰቡ ፡ በቍ ፡ ፫፻፱ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ በጋዜጣ ፡ በሚወጣው ፡ በንግድ ፡ አፊሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ ሦስተኛው ፡ ጥሪ ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለሆነም ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ጉዳት ፡ የማያመጣ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተባለው ፡ ጊዜ ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ የተጣራው ፡ ነጻ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፋፈል ፡ የሚፈቅድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫፻፯ ። ያልተወሰደውን ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥ ።

የባለአክሲዮኖቹ ፡ ድርሻ ፡ የሆነ ፡ ገንዘብ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፬ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፪) መሠረት ፡ ተቀማጭ ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ባለአክሲዮኖቹ ፡ ሳይወስዱት ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሒሳብ ፡ አጣሪዎቹ ፡ የባለአክሲዮኖቹን ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ገንዘቡ ፡ የአምጪው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአክሲዮኖቹን ፡ ቍጥር ፡ ጭምር ፡ ከማመልከት ፡ ጋራ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ባንክ ፡ በልዩ ፡ ሒሳብ ፡ ተቀማጭ ፡ ያደርጋሉ ።

ቍ ፡ ፫፻፰ ። ማኅበሩ ፡ ከንግድ ፡ መዝገብ ፡ መሰረዝ ።

ሒሳቡ ፡ የተጣራበት ፡ የመጨረሻው ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ ከጸደቀ ፡ በኋላ ፡ በቍጥር ፡ ፪፻፹፯ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ማኅበሩ ፡ ከመዝገብ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪዎቹ ፡ ማመልከቻ ፡ ማቅረብ ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፫፻፱ ። ከማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ መብት ።

(፩) በቍጥር ፡ ፫፻፰ ፡ መሠረት ፡ ማኅበሩ ፡ ከንግድ ፡ መዝገብ ፡ ከተሰረዘ ፡ በኋላ ፡ የሚገባቸውን ፡ ድርሻ ፡ ያልተቀበሉት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ሒሳቡ ፡ በተጣራበት ፡ በመጨረሻው ፡ ሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ መሠረት ፡ ከተጣራው ፡ ንብረት ፡ ለባለአክሲዮኖቹ ፡ በደረሳቸው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ባለአክሲዮኖቹን ፡ ራሳቸውን ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አላቸው ።

(፪) እንዲሁም ፡ ድርሻቸውን ፡ ያላገኙበትን ፡ ምክንያት ፡ በሒሳብ ፡ አጣሪዎቹ ፡ ቸልተኝነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በተባሉት ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪዎች ፡ ላይ ፡ መብታቸውን ፡ ሊጠይቁ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፭፻፱ ። የማኅበሩን ፡ መዝገቦች ፡ ጠብቆ ፡ ስለ ፡ መያዝ ።**

(፩) የፈረሰው ፡ ማኅበር ፡ መዝገቦች ፡ በንግድና ፡ እንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ፡ ተቀምጠው ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ይጠበቃሉ ።

(፪) እነዚህን ፡ መዝገቦች ፡ ለመመርመር ፡ የሚከፈለውን ፡ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ አስቀድሞ ፡ ተከፍሎ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሊመረምራቸው ፡ ይችላል ።

## አንቀጽ ፡ ፫ ።

## የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ስላላቸው ፡ የግል ፡ ማኅበሮች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎችና ፡ የማኅበሩ ፡ አቋቋም ።

**ቍ ፡ ፭፻፲ ። ትርጓሜ ፤ ጠባይ ።**

(፩) የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ያለው ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ ማለት ፡ ማናቸውም ፡ ማኅበረ ተኛ ፡ ካገባው ፡ መዋጮ ፡ በላይ ፡ አላፊ ፡ የማይሆንበት ፡ ማኅበር ፡ ማለት ፡ ነው ።

(፪) ይኸውም ፡ ማኅበር ፡ ከሁለት ፡ ማኅበረተኛ ፡ ያነሰ ፡ ከኀምሳ ፡ ማኅበረተኞች ፡ በላይ ፡ ያለበት ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ። የማኅበሩ ፡ ዓላማ ፡ ማንኛውም ፡ ዐይነት፡ ቢሆን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ነው ።

(፫) ማኅበሩ፡ በማናቸውም፡ ፎርም ፡ ቢሆን፡ የሚተላለፉ ፡ የንግድ ፡ ወረቀቶችን ፡ (ሰነዶች) ፡ ለማውጣት ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፭፻፲፩ ። በሕግ ፡ ከተወሰነው ፡ አነስተኛ ፡ ቍጥር ፡ በታች ፡ የማኅበረተኛ ፡ ቍጥር ፡ ማነስ ።**

የማኅበረተኞቹ ፡ ቍጥር ፡ ከሁለት ፡ በታች ፡ የወረደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ለማ ኅበሩ ፡ ሥራ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ መኖራቸው ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ማኅበሩም ፡ በሚገባ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታውን ፡ እንደገና ፡ ያላቋቋመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመፍረድ ፡ ይችላል ። እንዲሁም ፡ ክሱ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለጊዜው፡ መጠባበቂያ ፡ የሆኑ ፡ ውሳኔዎች ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፭፻፲፪ ። የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ።**

(፩) የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ያለው ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ከኻምሳ ፡ አምስት ፡ ሺሕ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ያነሰ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

(፪) የያንዳንዱ ፡ አክሲዮን ፡ ዋጋ ፡ ከዐሥር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ያነሰ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

(፫) የአክሲዮኖቹ ፡ ዋጋ ፡ ሁሉ ፡ ትክክል ፡ መሆን ፡ አለበት ። እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ከአንድ ፡ አክሲዮን ፡ የበለጠ ፡ ለመግዛት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፭፻፲፫ ። የተከለከሉ ፡ ሥራዎች ።**

የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ያለው ፡ የግል ፡ ማኅበር ፤ የባንክ ፤ የኢንሹራንስ ፡ እንደዚሁም ፡ እነዚህን ፡ የመሰለ ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ድርጅቶች ፡ ለማቆም ፡ የተከለከለ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፭፻፲፬ ። አጠራር ።**

(፩) የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ያለው ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ የሚጠራበት ፡ የማኅበሩን ፡ የሥራ ፡ ዓላማ ፡ የሚገልጽ ፡ የማኅበር ፡ ስም ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ።

(፪) ከማኅበሩ ፡ ስም ፡ ቀጥሎ ፡ «የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ያለው ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡» የሚሉ ፡ ቃላት ፡ በሙሉ ፡ ተጽፈው ፡ እንዲገኙበት ፡ ያስፈልጋል ።

**ቍ ፡ ፭፻፲፭ ። በማኅበሩ ፡ ወረቀቶች ፡ ላይ ፡ የሚጻፍ ፡ መግለጫ ።**

በማንኛቸውም ፡ ከማኅበሩ ፡ በሚወጡ ፡ ጽሑፎች ፡ የማስታወቂያ ፡ ጽሑፎች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ሰነዶች ፡ ላይ ፡ በቍ ፡ ፭፻፲፬ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ በተመለከተው ፡ የማኅበሩ ፡ ስም ፡ ወይም ፡ አጠራር ፡ ሁል ፡ ጊዜም ፡ አላፊነቱ ፡ የተወሰነበት ፡ ማኅበር ፡ የሚሉ ፡ እንደሚታዩ ፡ ሆነው ፡ በሙሉ ፡ ፊደላት ፡ የተጻፉትን ፡ ቃላት ፡ ማስቀደም ፡ ወይም ፡ ማስከተል ፡ እንዲሁም ፡ የማኅበሩን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ መግለጽ ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፭፻፲፮ ። ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ አመሠራረት ።**

ማኅበሩ ፡ የሚቋቋመው ፤ በማኅበር ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ዐይነት ፡ የተዘጋጀው ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ሁሉ ፡ ራሳቸው ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸው ፡ እንደራሴዎቻቸው ፡ የፈረሙበት ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፭፻፲፯ ። በመመሥረቻው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ የሚጻፈው ፡ ቃል ።**

በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ሊጻፉ ፡ የሚገባቸው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ የተዘረዘሩት ፡ ናቸው ።

(ሀ) የማኅበረተኞች ፡ ስም ፤ ዜግነት ፤ አድራሻ ፤
(ለ) የማኅበሩ ፡ ስም ፤ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፤ እንዲሁም ፡ ቅርንጫፎቹ ፤
(ሐ) የማኅበሩ ፡ የንግድ ፡ ዓላማ ፤
(መ) የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፤
(ሠ) እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ያገባው ፡ የመዋጮ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፤
(ረ) በዐይነት ፡ ያገባው ፡ የመዋጮ ፡ ግምት ፤
(ሰ) የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ መግባቱን ፡ የሚያስረዳ ፡ መግለጫ ፤
(ሸ) የንግዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የሚደርሰው ፡ የአክሲዮን ፡ ድልድል ፡ ልክ ፤
(ቀ) የትርፉን ፡ ክፍያ ፡ አፈጻጸም ፡ ሥርዐት ፤

BACK



(በ) የሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ቍጥር ፤ ሥልጣናቸው ፡ እንዲሁም ፡ የማኅበሩ ፡ ወኪሎች ፤

(ተ) እንዲሁም ፡ የተቈጣጣሪዎች ፡ ብዛት ፤

(ቸ) ማኅበሩ ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፤

ቍ ፡ ፫፻፲፰ ። የማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ።

በቍጥር ፡ ፫፻፲፩ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተወሰነ ፡ ኣላፊነት ፡ ባለው ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ላይም ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፫፻፲፱ ። በዐይነት ፡ የሚገባ ፡ መዋጮ ።

(፩) ከማኅበረተኞቹ ፡ አንዱ ፡ በዐይነት ፡ መዋጮ ፡ ያገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የዚህን ፡ መዋጮ ፡ ዐይነትና ፡ ግምት ፡ ሌሎቹ ፡ ማኅበረተኞች ፡ የተቀበሉበትን ፡ ዋጋና ፡ ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ መዋጮ ፡ ግምት ፡ የተሰጠውን ፡ ድርሻ ፡ ልክ ፡ የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

(፪) ግምቱም ፡ የሚደረገው ፡ ለማኅበረተኞቹ ፡ መልካም ፡ መስሎ ፡ በታያቸው ፡ በማናቸውም ፡ አሠራር ፡ ነው ።

(፫) በዐይነት ፡ የሚገቡት ፡ መዋጮዎች ፡ በገቡበት ፡ ጊዜ ፡ ለተደረገላቸው ፡ ግምት ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ሁሉ ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ በአንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ ኣላፊዎች ፡ ናቸው ።

(፬) በዐይነት ፡ ለገባው ፡ መዋጮ ፡ የተደረገው ፡ ግምት ፡ ከዋጋው ፡ በላይ ፡ መደረጉ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መዋጮውን ፡ ያገባው ፡ ማኅበረተኛ ፡ ከግምት ፡ የጐደለውን ፡ ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ማግባት ፡ አለበት ።

ለዚሁም ፡ ገንዘብ ፡ መክፈል ፡ ከዋጋው ፡ በላይ ፡ መዋጮው ፡ መገመቱን ፡ ባያውቁትም ፡ እንኳ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ባንድነት ፡ ሳይከፈል ፡ ኣላፊዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፫፻፳ ። ስለ ፡ መታወቅ ።

(፩) በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ከቍጥር ፡ ፫፻፲፱ ፡ እስከ ፡ ፫፻፳፬ ፡ ባለው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ማኅበሩ ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ እንዲታወቅ ፡ ማስታወቂያ ፡ እንዲወጣ ፡ ያደርጋል ፤ የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍና ፡ ያለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የማኅበሩን ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍና ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አግብቶ ፡ ማስቀመጥ ፡ ግዴታ ፡ ነው ።

(፪) የሚታተመው ፡ ማስታወቂያና ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ለመመዝገቢያ ፡ የሚቀርበው ፡ ማመልከቻ ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፲፯ ፡ (ሀ) እስከ ፡ (ሸ) እና ፡ (በ) እስከ ፡ (ቸ) የተዘረዘሩት ፡ ሐተታዎች ፡ እንዲኖሩት ፡ ያስፈልጋል ።

(፫) በቍጥር ፡ ፫፻፳፬ ፡ የተነገረው ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ አክሲዮኖች ።

**ቍ ፡ ፫፻፵፩ ፡ የአክሲዮኖች ፡ ድርሻ ፡ መዝገብ ።**

(፩) የማኅበሩ ፡ አክሲዮኖች ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ይጻፋሉ ፤ መዝገቡም ፤

(ሀ) የማኅበረተኞቹን ፡ ስም ፤

(ለ) እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ማግባት ፡ ያለበትን ፡ የመዋጮዎቹን ፡ ግምት ፤

(ሐ) ማናቸውንም ፡ የማኅበር ፡ አክሲዮኖች ፡ በስም ፡ መተላለፍ ፤

(መ) ማንኛውንም ፡ ስለነዚሀ ፡ ሐተታዎች ፡ የተደረገውን ፡ መሻሻል ፤ መግለጽ ፡ አለበት ።

(፪) ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ የመጨረሻው ፡ ሊስት ፡ ከተሰጠ ፡ ወዲሀ ፡ የተለወጠ ፡ አን ዳች ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ብለው ፡ ካላስታወቁ ፡ በቀር ፡ በየዓመቱ ፡ መጀመሪያ ፡ በን ኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ በ(ሀ) እና ፡ በ(ለ) እንደተመለከተው ፡ የማኅበረተኞቹን ፡ ስም ፡ መግባት ፡ ያለበትን ፡ መዋጮ ፡ ግምት ፡ የሚያመለክት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆቹ ፡ የፈረሙበት ፡ አንድ ፡ ሊስት ፡ ለንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይሰጣል ።

(፫) በማኅበሩ ፡ የአክሲዮን ፡ መዝገብና ፡ ሊስቶች ፡ ትክክል ፡ ባልሆነ ፡ አጻጻፍ፡ ምክንያት ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ እየራሳቸውና ፡ በአን ድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ አላፊዎች ፡ ናቸው ። የተሰጡትም ፡ ሊስቶች ፡ በግልጽ ፡ ማንም ፡ ሊያያቸው ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፫፻፵፪ ። አክሲዮኖቹን ፡ ለሌላ ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።**

የአክሲዮኖቹ ፡ መተላለፍ ፡ በጽሑፍ ፡ የተረጋገጠ ፡ መሆን ፡ አለበት ። መተላ ለፉም ፡ በአክሲዮኖቹ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ካልተጻፈ ፡ በቀር ፡ ማኅበሩንና ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፫፻፵፫ ። አክሲዮኑ ፡ የተላለፈለት ፡ ለማኅበሩ ፡ ባዕድ ፡ የሆነ ፡ ሰው ።**

(፩) በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆኑ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከሌሉ ፡ በቀር ፡ በማኅበረተኞቹ ፡ መካከል ፡ አክሲዮኖችን ፡ ለማስተላለፍ ፡ ይቻላል ።

(፪) የማኅበሩ ፡ አክሲዮኖች ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ሦስት ፡ ሩብ ፡ ያላቸው ፡ የማኅበረተኞቹ ፡ አብዛኛው ፡ ቍጥር ፡ ካልፈቀደ ፡ በቀር ፡ የማኅ በሩ ፡ አክሲዮኖች ፡ ለማኅበሩ ፡ ባዕድ ፡ ለሆኑ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ሊተላ ለፉ ፡ አይችሉም ። ከዚህ ፡ የበዛ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ወይም ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ሁሉ ፡ እንዲፈቅዱ ፡ ያስፈልጋል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ ሊጻፍ ፡ ይቻላል ።

(፫) ማኅበረተኞቹም ፡ የተስማሙበት ፡ ውሳኔ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡

እንዲመዘገብ ፡ ያስፈልጋል ።

(፬) ማኅበሩ ፡ በመጣራት ፡ ላይ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳን ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) የተመለከተው ፡ ውሳኔ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

(፭) ባንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ አክሲዮን ፡ ላይ ፡ በግድ ፡ የማስፈጸም ፡ ሥርዐት ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ የሌሎቹን ፡ ማኅበረተኞች ፡ ፈቃድ ፡ ስለ ፡ ማግኘት ፡ ያለው ፡ ግዴታ ፡ አክሲዮኑን ፡ በሚገዛውም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

<u>ቍ ፡ ፭፻፳፬ ። በውርስ ፡ ስለሚገኙ ፡ አክሲዮኖች ።</u>

(፩) በማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ የተነገሩ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆኑ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ከሌሉ ፡ በቀር ፡ የአንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ወራሾች ፡ ለሟቹ ፡ አክሲዮኖች ፡ በደንብ ፡ ወራሾች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) በማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ አንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ከወራሾቹ ፡ መካከል ፡ ላንዱ ፡ ብቻ ፡ ድርሻው ፡ እንዲደርሰው ፡ ለመምረጥ ፡ መብቱን ፡ የሚጠብቅበት ፡ የውል ፡ ቃል ፡ የሚጸና ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

<u>የማኅበሩ ፡ አደረጃጀት ።</u>

<u>ቍ ፡ ፭፻፳፭ ። ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅነት ።</u>

(፩) የተወሰነ ፡ ኣላፊነት ፡ ያለው ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ መተዳደር ፡ አለበት ።

(፪) ከሓያ ፡ በላይ ፡ የሚሆኑ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ባሉበት ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ውሳኔ ፡ የሚደረገው ፡ በማኅበረተኞቹ ፡ ጉባኤ ፡ ነው ። ተቈጣጣሪዎችንም ፡ መምረጥ ፡ አለባቸው ።

(፫) ከሓያ ፡ ወይም ፡ ከሓያ ፡ በታች ፡ የሆኑ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ባሉባቸው ፡ ማኅበሮች ፡ ውስጥ ፡ የጉባኤ ፡ መሰብሰብና ፡ የተቈጣጣሪዎችን ፡ መምረጥ ፡ ጉዳይ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፪) በተነገረው ፡ አይገደዱም ።

<u>ቍ ፡ ፭፻፳፮ ። የሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ መሾም ።</u>

ሥራ ፡ አስኪያጆቹን ፡ ከማኅበረተኞች ፡ ውጭ ፡ ለመምረጥ ፡ ይቻላል ። በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ወሰን ፡ ላልተደረገለት ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆቹን ፡ የሚሾሙ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ናቸው ።

<u>ቍ ፡ ፭፻፳፯ ። የሥራ ፡ አስኪያጆቹ ፡ መሻር ።</u>

(፩) በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የተሾመውን ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፴፯ ፡ በተነገሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ በተሰጠ ፡ ውሳኔ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡

ማኅበረተኞቹ ፡ ሊሽሩት ፡ አይችሉም ።

(፪) በማኅበረተኞች ፡ የተሾመ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፴፭ ፡ በተነገሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ በተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ ይሻራል ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊቀበል ፡ በሚችለው ፡ ተገቢ ፡ ምክንያቶች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሊሻር ፡ አይቻልም ። የተሻረው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ከተሻረበት ፡ እንሥቶ ፡ ሥራውን ፡ ለመሥራት ፡ አይችልም ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ የተሻረበት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ያለመሆኑን ፡ የተረዳው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተሻረው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲያገኝ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ።

(፬) ምንም ፡ እንኳ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ የተነገሩት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ቢኖሩ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆቹ ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ቢሾሙ ፡ በማኅበረተኞቹ ፡ ነጻ ፡ ፈቃድ ፡ ሊሻሩ ፡ የሚችሉ ፡ ለመሆናቸው ፡ በማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ሊጻፉ ፡ ይቻላል ።

(፭) በሚገባ ፡ ምክንያት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ እንዲሻር ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ማንኛውም ፡ ማኅበረተኛ ፡ በየራሱ ፡ ሊያቀርበው ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፭፻፷፫ ። የሥራ ፡ አስኪያጆቹ ፡ ሥልጣን ።

(፩) ሥራ ፡ አስኪያጆቹ ፡ ከማኅበሩ ፡ ዓላማ ፡ ወሰን ፡ ሳያልፉ ፤ በማንኛዎቹም ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ በማኅበሩ ፡ ስም ፡ ለመሥራት ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

(፪) ለሥራ ፡ አስኪያጆቹ ፡ ሥልጣን ፡ ወሰን ፡ በመስጠት ፡ በማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ የሚነገሩ ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ በማኅበረተኞቹና ፡ በሥራ ፡ አስኪያጆቹ ፡ መካከል ፡ ላሉት ፡ ግንኙነቶች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ውጤት ፡ የላቸውም ። በደንብ ፡ ሆነው ፡ በማስታወቂያ ፡ ቢወጡም ፡ እንኳ ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ዘንድ ፡ ውጤት ፡ የላቸውም ።

## ቍ ፡ ፭፻፷፬ ። ስለ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆቹ ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ።

የሥራ ፡ አስኪያጆችን ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፡ የሚወስኑ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ናቸው ። ይህም ፡ የተባለው ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ፤ የቍርጥ ፡ አደር ፡ ደመወዝ ፡ ወይም ፡ የትርፍ ፡ ተካፋይ ፡ ወይም ፡ ሁለቱንም ፡ በማግኘት ፡ እንዲሆን ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

## ቍ ፡ ፭፻፷፭ ። የሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ አላፊነት ።

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆቹ ፡ በዚህ ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ የተሰጡትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ወይም ፡ የማኅበሩን ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በመጣስም ፡ ቢሆን ፤ በሥራ ፡ አስኪያጅነታቸው ፡ በሠሩዋቸው ፡ ጥፋቶችም ፡ ስሕተቶችም ፡ ቢሆን ፡ በማኅበሩና ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ፊት ፡ በየራሳቸው ፡ ወይም ፡ በአንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ አላፊዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፬፻፴፩ ። የማኅበሩ ፡ መክሠር ።

(፩) የማኅበሩ ፡ መክሠር ፤ የንብረቱን ፡ በቂ ፡ አለመሆኑን ፡ ያሳየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የከሠረ ፡ ማኅበር ፡ ንብረት ፡ ጠባቂ ፡ (ሰንዴክ ፡) በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፤ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እስከሚወሰነው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ የማኅበሩን ፡ ዕዳዎች ፡ ሁሉንም ፡ ወይም ፡ ጥቂቱን ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆቹ ፤ ማኅበረተኞች ፡ ወይም ፡ ሁለቱም ፡ ወይም ፡ ከሥራ ፡ አስኪያጆዎቹና ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ባንድነት ፡ ወይም ፡ በየራሳቸው ፡ የማኅበሩን ፡ ዕዳዎች ፡ ይችላሉ ፡ ብሎ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊመወስን ፡ ይችላል ።

(፪) ለማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅነት ፡ ተካፋይ ፡ ሆነው ፡ ካልተገኙ ፡ በቀር ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ የተመለከተው ፡ አላፊነት ፡ ማኅበረተኞቹን ፡ ሊያገኛቸው ፡ አይችልም ። አላፊነቱ ፡ የሚመለከታቸው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆዎችና ፡ ማኅበረተኞች ፡ አላፊነታቸውን ፡ ለማስወገድ ፡ ለማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ተገቢ ፡ ሥራና ፡ ትጋት ፡ የፈጸሙ ፡ መሆናቸውን ፡ ያስረዱ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) የተነገረው ፡ ውሳኔ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንባቸውም ።

ቍ ፡ ፬፻፴፪ ። ጉባኤዎች ።

(፩) ከሓያ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ባሉባቸው ፡ ማኅበሮች ፡ ውስጥ ፡ ቢያንስ ፡ እንኳን ፡ በዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በተወሰነ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ መደረግ ፡ አለበት ።

(፪) ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆቹ ፡ እነዚህም ፡ ባይኖሩ ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቈጣጣሪዎቹ ፤ እነዚህም ፡ ባይኖሩ ፡ ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ከእኩሌታው ፡ በላይ ፡ ያላቸው ፡ ማኅበረተኞች ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ሌሎቹ ፡ ጉባኤዎች ፡ እንዲደረጉ ፡ ጥሪ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፬፻፴፫ ። ጉባኤ ፡ ሳይደረግ ፡ የሚሰጡ ፡ ውሳኔዎች ።

ጉባኤ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ የማኅበሩ ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በሚያስገድዱበት ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆቹ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የቀረቡትን ፡ አሳቦች ፡ ወይም ፡ ውሳኔዎች ፡ የሚያመለክተውን ፡ ጽሑፍ ፡ ድምፁን ፡ በጽሑፍ ፡ እንዲሰጥ ፡ እያሳሰቡ ፡ መላክ ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፬፻፴፬ ። የማኅበረተኞቹ ፡ የድምፅ ፡ ብዛት ።

(፩) በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ የተጻፈ ፡ ማናቸውም ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ማንኛውም ፡ ማኅበረተኛ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ በሚደረገው ፡ ጉባኤ ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

(፪) እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ አክሲዮኖች ፡ ልክ ፡ የድምፅ ፡ ብዛት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፳፻፴፭ ። የድምፅ ፡ ብልጫና ፡ ኮረም ።**

(፩) ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ እኩሌታ ፡ በላይ ፡ ያላቸው ፡ በአብዛኛዎቹ ፡ ማኅበረተኞች ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ካልተቀበለው ፡ በቀር ፡ በቍጥር ፡ ፳፻፴፪ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ እና ፡ በቍጥር ፡ ፳፻፴፫ ፡ በተመለከቱት ፡ ሁለት ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ማንኛውንም ፡ ዋጋ ፡ ያለውን ፡ ውሳኔ ፡ ማድረግ ፡ አይችልም ።

(፪) ይህ ፡ የተባለው ፡ የአብዛኛው ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ በመጀመሪያው ፡ ስብሰባ ፡ ጊዜ ፡ ሊገኝ ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ በሬኮማንዴ ፡ በሚላኩት ፡ ደብዳቤዎች ፡ ሁለተኛ ፡ ይጠራሉ ፤ ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ የሆነው ፡ ክፍል ፡ ምን ፡ ያህልም ፡ ቢሆን፣ ውሳኔው ፡ በአብዛኛው ፡ በሚሰጠው ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ይወሰናል ።

**ቍ ፡ ፳፻፴፮ ። የማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።**

(፩) ማኅበረተኞቹ ፡ በአንድ ፡ ቃል ፡ ካልተስማሙ ፡ በቀር ፤ የማኅበሩን ፡ ዜግነት፡ ለመለወጥ ፡ አይችሉም ።

(፪) ስለሆነም ፡ ከማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ለሚደረጉት ፡ ማናቸውም ፡ አለዋወጥ ፡ ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ሦስት ፡ ሩብ ፡ ባላቸው ፡ በአብዛኛዎቹ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ድምፅ ፡ ብልጫ ፡ መወሰን ፡ አለበት ። ይህም ፡ የሚሆነው፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ያልተወሰነ ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ነው ። ማኅበረተኛው ፡ ካልፈቀደ፡ በቀር፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ፡ ባለው ፡ ድርሻ ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲያገባ ፡ ለማስገደድ ፡ አይችሉም ።

(፫) የሚደረጉት ፡ መለዋወጦች ፡ ሕጉ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ በማስታወቂያ ፡ መውጣት ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፳፻፴፯ ። ሰነዶችን ፡ የማወቅ ፡ መብት ።**

(፩) ቍጥራቸው ፡ ከሓያ ፡ የማይበልጥ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ባሉባቸው ፡ ማኅበሮች ፡ ሁሉ ፡ ማናቸውም ፡ ማኅበረተኛ ፡ ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በራሱ ፡ ወይም ፡ በወኪሉ ፤ የንብረት ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፤ የሒሳቡን ፡ ሚዛን ፤ እንዳለ ፡ የተቈጣጣሪዎች ፡ ራፖር ፡ ለማወቅ ፡ ወይም ፡ ቅጂ ፡ ለመውሰድ ፡ ይችላል ።

(፪) ቍጥራቸው ፡ ከሓያ ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ባሉባቸው ፡ ማኅበሮች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጠቅላላው ፡ ጉባኤ ፡ ከመሰብሰቡ ፡ በፊት ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ አስቀድሞ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ የተመለከተው ፡ የማወቅ ፡ መብት ፡ አይፈቀድም ።

**ቍ ፡ ፭፻፴፰ ።  ተቈጣጣሪዎች ።**

(፩) ቍጥራቸው ፡ ከሓያ ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ባሉበት ፡ ማኅበር ፡ ከሦስት ፡ የማያንሱ ፡ ተቈጣጣሪዎች ፡ እንዲመረጡ ፡ ያስፈልጋል ። ይህም ፡ የተባለው ፡ ምርጫ ፡ የሚደረገው ፡ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ነው ።

(፪) እነዚህም ፡ ተቈጣጣሪዎች ፡ በማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በተወሰኑት ፡ ጊዜዎችና ፡ ምክንያቶች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለመመረጥ ፡ ይቀርባሉ ።

(፫) ተቈጣጣሪዎቹ ፡ የሚሾሩባቸውም ፡ ሁኔታዎች ፡ በማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ሊጻፉ ፡ ይችላል ። ያልተጻፉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በቍጥር ፡ ፭፻፴፭ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

(፬) የተቈጣጣሪዎቹ ፡ ሥራና ፡ ሥልጣን ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፷፱ ፡ እና ፡ በቍጥር ፡ ፫፻፸፫ ፡ የተመለከቱት ፡ ናቸው ።

(፭) ተቈጣጣሪዎቹ ፡ ሥራቸውን ፡ በሚፈጽሙበት ፡ ጊዜ ፡ ራሳቸው ፡ በሚያደርጓቸው ፡ ጥፋቶች ፡ ወይም ፡ ቸልተኝነት ፡ በየራሳቸው ፡ ወይም ፡ በአንድነት ፡ ሳይከፋፈሉ ፡ ለማኅበሩና ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ኣላፊዎች ፡ ናቸው ።

(፮) ነገሩን ፡ ዐውቀው ፡ ሳለ ፤ በራፖራቸው ፡ ውስጥ ፡ ለጉባኤው ፡ ሳይገልጹት ፡ በመቅረታቸው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆቹ ፡ ለሠሩት ፡ ወንጀል ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ በኩል ፡ ኣላፊዎች ፡ አይደሉም ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## የማኅበሩ ፡ ሒሳቦች ።

**ቍ ፡ ፭፻፴፱ ።  ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ መጠባበቂያ ፡ ገንዘብ ።**

በየዓመቱ ፡ መጠባበቂያ ፡ የሚሆነውን ፡ ገንዘብ ፡ ለማደራጀት ፡ ከትርፉ ፡ ላይ ፡ ቢያንስ ፡ ከሓያ ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ እየተነሣ ፡ ይቀመጣል ። ይኸውም ፡ የተባለው ፡ ገንዘብ ፡ መነሣት ፤ መጠባበቂያው ፡ ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ከዐሥር ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ ሲደርስ ፡ የግዴታ ፡ መሆኑ ፡ ያቋርጣል ።

**ቍ ፡ ፭፻፵ ።  ሐሰተኛ ፡ ትርፍ ።**

(፩) ሐሰተኛ ፡ የሆኑትን ፡ የትርፎች ፡ ክፍያ ፡ የተቀበሉዋቸው ፡ ማኅበረተኞች ፡ እንዲመልሱ ፡ መጠየቅ ፡ ይቻላል ።

(፪) ትርፎቹን ፡ ለማካፈል ፡ ከተወሰነው ፡ ቀን ፡ እንሥቶ ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ተቀበለው ፡ ክፍያ ፡ መመለስ ፡ የሚቀርበውን ፡ ክስ ፡ ይርጋ ፡ ያግደዋል ።

BACK



ቍ ፡ ፬፻፷፩ ። የተወሰነ ፡ ወለድ ።

(፩) ማኅበሩ ፡ ሥራውን ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ሥራዎች ፡ ለሚከናወኑበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ትርፍ ፡ ባይኖርም ፡ እንኳ ፡ ማኅበረተኞቹ ፡ ልኩ ፡ የተወሰነ ፡ ወለድ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ እላቸው ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ፡ በማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ለማግባት ፡ ይቻላል ። የተባለውን ፡ ጊዜ ፡ የሚወስነው ፡ የማኅበሩ ፡ መመሥረቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ነው ።

(፪) ይህም ፡ የተባለው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ፈራሽ ፡ እንዳይሆን ፡ በንግድ ፡ ኦፊሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ መውጣት ፡ አለበት ።

(፫) የመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ በሚወስነው ፡ አሠራር ፡ እነዚህ ፡ የተከፈሉት ፡ ወለዶች ፡ ማኅበሩን ፡ ለማቋቋም ፡ ከሚደረጉት ፡ መጀመሪያ ፡ ወጪዎች ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ትርፍ ፡ በሚያሳዩት ፡ ዓመታት ፡ ላይ ፤ ከነዚህ ፡ ወጪዎች ፡ ጋራ ፡ ይደላደላሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## የማኅበሩ ፡ መፍረስ ።

ቍ ፡ ፬፻፷፪ ። የሚፈርሱበት ፡ ምክንያቶች ።

(፩) የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ያለው ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ ለማኅበሮች ፡ ሁሉ ፡ መፍረሻ ፡ በሆኑት ፡ ምክንያቶችና ፡ ማኅበሩ ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የተቋቋመ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ባንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ አቤቱታ ፡ ማቅረብ ፤ እንዲሁም ፡ በቂ ፡ በሆኑ ፡ ምክንያቶች ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ ይፈርሳል ።

(፪) ለማኅበረተኛው ፡ ጥቅም ፡ በተወሰነ ፡ ዋጋ ፡ የማኅበረተኞችን ፡ አክሲዮኖች ፡ መልሶ ፡ የመግዛት ፡ ሥልጣን ፡ ለመስጠት ፡ በመተዳደሪያው ፡ ደንብ ፡ የሚያመለክተው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነው ።

(፫) ያንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ መከልከል ፤ መክሠር ፤ ዕዳን ፡ መክፈል ፡ ያለመቻል ፡ ወይም ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የማኅበረተኛው ፡ መሞት ፤ ማኅበሩን ፡ አያፈርሰውም ።

(፬) ለሞተ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ወራሾች ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ ወይም ፡ በመጨረሻው ፡ የንብረት ፡ መዝገብ ፡ ዝርዝር ፡ መሠረት ፡ የሚገባቸውን ፡ መልሶ ፡ ለመክፈል ፡ የምርጫ ፡ መብት ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ለመወሰን ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፬፻፷፫ ። ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ሦስት ፡ ሩብ ፡ ስለ ፡ መጥፋት ።

(፩) ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ሦስት ፡ ሩብ ፡ የጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሥራ ፡ አስኪያጆቹ ፡ የማኅበሩን ፡ መፍረስ ፡ ማስታወቅ ፡ የሚያስፈልግ ፡ መሆኑን ፡ ለማወቅና ፡ ለመወሰን ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ መመካከር ፡ አለባቸው ።

(፪) ሥራ ፡ አስኪያጆቹ ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ መመካከር ፡ ያላደረጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ በደንበኛ ፡ ውሳኔ ፡ ለማድረግ ፡ የማይችሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማናቸውም ፡ ጥቅም፡ ያለው ፡ ሰው፡ ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ፡ ፍርድ፡ ቤትን፡ ለመጠየቅ፡ ይችላል።

## አንቀጽ ፡ ፰ ።

## የማኅበሮች ፡ መለዋወጥና ፡ መቀላቀል ።

### ቍ ፡ ፭፻፶፩ ። ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

(፩) ዐይነቱ ፡ የተወሰነ ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ማኅበር ፡ መለዋወጡ ፤ በመሠረቱ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ አዲስ ፡ ድርጅት ፡ መፍጠርን ፡ አያስከትልም ።

(፪) እንደሁኔታው ፡ በማኅበረተኞቹ ፡ መላ፡ድምፅ ፡ ወይም ፡ በመተዳደሪያ ፡ ደንብ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ በተወሰነው ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ መለወጡ ፡ መወሰን ፡ አለበት ። በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ የማኅበረተኞቹ ፡ ግዴታዎች ፡ በያንዳንዱ ፡ የግል ፡ ፈቃድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሊጨመሩበት ፡ አይችሉም ።

(፫) እንዲሁም ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የማኅበረተኛነትን ፡ መብት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዲተው ፡ የማስገደድ ፡ ዐሥጤት ፡ ያለውን ፡ የማኅበርን ፡ መለወጥ ፡ ውሳኔ ፡ ማኅበረተኛው ፡ እንዲፈቅድ ፡ ያስፈልጋል ።

(፬) የማኅበረተኞቹ ፡ ውሳኔ ፡ በግልጽ ፡ ጽሑፍ ፡ የተዘጋጀና ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፳፬ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ በማስታወቂያ ፡ እንዲወጣለት ፡ ያስፈልጋል ።

(፭) ማኅበሩ ፡ ለተለወጠበት ፡ ማኅበር ፡ ዐይነት ፡ መቋቋም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ የመመሥረቻ ፡ ደንቦች ፡ በሙሉ ፡ መጠበቅ ፡ አለባቸው ። ስለሆነም ፡ የሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ መብቶች ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ በተለይ ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

### ቍ ፡ ፭፻፶፪ ። የኅብረት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፤ ሁለት ፡ ዐይነት ፡ አላፊነት ፡ ያለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበርን ፡ አላፊነቱ ፡ ወደ ፡ ተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

(፩) ይህ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ወይም ፡ በኋላ ፡ የተቋቋሙ ፡ የኅብረት ፤ የሽርክና ፡ ማኅበሮች ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ዐይነት ፡ አላፊነት ፡ ያለው ፡ የሽርክና ፡ ማኅበሮችና ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ኀላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ በሆነ ፡ ማኅበር ፡ ለመለወጥ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ማኅበሩ ፤ የአክሲዮን፡ ማኅበር፡ የሆነ ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ውሳኔውን ፡ የሚያደርገው፡ በቍጥር ፡ ፭፻፳፭ ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ ድንገተኛው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ነው ።

(፫) ያልተስማሙት ፡ ማኅበረተኞች ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፳፫ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት፡

ከማኅበሩ ፡ የመውጣት ፡ መብታቸውን ፡ ሊሠሩበት ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፭፻፷፯ ።  የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መብት ።**

(፩) የተለወጠው ፡ ማኅበር ፡ ንብረት ፡ ያላንዳች ፡ ሌላ ፡ አሠራር ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ እንደ ፡ ተመዘገበ ፡ ላዲሱ ፡ ማኅበር ፡ ይተላለፋል ።

(፪) ይህ ፡ ከተመዘገበ ፡ በኋላ ፡ ወዲያውኑ ፡ ከተለወጠው ፡ ማኅበር ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በሚበቃ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ ማስረጃቸውን ፡ እንዲያቀርቡና ፡ ተቃራኒም ፡ አሳብ ፡ ካላቀረቡ ፡ አዲሱ ፡ ማኅበር ፡ ዕዳ ፡ ከፋያቸው ፡ መሆኑ ፡ ይነገራቸዋል ።

(፫) በቍጥር ፡ ፭፻፷፮ ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) በተመለከተው ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ አጠራር ፡ ላይ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ይሆናሉ ።

(፬) አዲሱ ፡ ማኅበር ፡ ዕዳ ፡ ከፋይ ፡ መሆኑን ፡ ሳይቀበሉ ፡ ሰነዶቻቸውን ፡ ለሚያቀርቡ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ገንዘባቸውን ፡ እንዲከፈሉ ፡ ወይም ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ማድረግ ፡ ግዴታ ፡ ነው ። የነዚህ ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መብት ፡ ሁሉ ፡ በእንደዚህ ፡ ዐይነት ፡ እስከ ፡ ተጠበቀ ፡ ድረስ ፡ የተለወጠው ፡ ማኅበር ፡ ንብረት ፡ ለባለአክሲዮኖቹ ፡ ሊከፋፈል ፡ አይቻልም ።

(፭) ከተለወጠው ፡ ማኅበር ፡ ገንዘብ ፡ ለሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ እስከ ፡ ፬ ፡ ያሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ አፈጻጸም ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ እየራሳቸውና ፡ በአንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ አላፊዎች ፡ ናቸው ።

(፮) ማኅበሩ ፡ በተለወጠ ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ የማኅበሩ ፡ መለወጥ ፡ እንዲገለጽ ፡ ያደርጋል ፤ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፬ ፡ የተወሰነው ፡ ከተፈጸመ ፤ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ የመጀመሪያው ፡ ማኅበር ፡ ከመዝገብ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ያደርጋሉ ።

**ቍ ፡ ፭፻፷፰ ።  የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ያለውን ፡ የግል ፡ ማኅበርን ፡ በአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።**

(፩) የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ ያላቸው ፡ የግል ፡ ማኅበሮች ፡ በአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ለመለወጥ ፡ ይችላሉ ፡ ውሳኔውም ፡ የሚደረገው ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፵፮ ፡ በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) እንዲለወጥ ፡ ድምፅ ፡ የሰጡ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ስም ፡ በፕሮሴቬርባሉ ፡ ላይ ፡ መጻፍ ፡ አለባቸው ። እነዚህም ፡ ማኅበረተኞች ፡ እንደ ፡ መሥራቾች ፡ ይቈጠራሉ ።

(፫) በቃለ ፡ ጉባኤው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ እንዲጻፍለት ፡ ስለ ፡ ማኅበሩ ፡ መለወጥ ፡ ተቃዋሚነቱን ፡ ያስታወቀ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ሁሉ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፺፫ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ከማኅበሩ ፡ የመውጣት ፡ መብቱን ፡ ሊሠራበት ፡ ይችላል ።

BACK



**ቍ ፡ ፭፻፵፰ ። የማኅበረተኞቹ ፡ አላፊነት ።**

(፩) ከአመዘጋገቡ ፡ የተነሣ ፡ ማኅበሩ ፡ እንዲለወጥ ፡ ከማኅበሩ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ ፈቃዳቸው ፡ መሆኑ ፡ ካልተመለከተ ፡ በቀር ፡ የመለወጡ ፡ ውሳኔ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ከመጻፉ ፡ በፊት ፡ ለማኅበሩ ፡ ግዴታዎች ፡ ያለወሰን ፡ አላፊዎች ፡ የሆኑትን ፡ ማኅበረተኞች ፡ የማኅበሩ ፡ መለወጥ ፡ ከአላፊነት ፡ ነጻ ፡ አያደርጋቸውም ።

(፪) የማኅበሩ ፡ መለወጥ ፡ ውሳኔ ፡ በረኰማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ ተላልፎላቸው ፡ ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ ከተላለፈበት ፡ አንሥቶ ፡ በሠላሳ ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መቀበላቸውን ፡ በግልጽ ፡ እንቢ ፡ ያላሉ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ፈቃዳቸውን ፡ እንደ ፡ ሰጡ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፭፻፵፱ ። የማኅበሮች ፡ መቀላቀል ።**

(፩) አንድ ፡ ማኅበር ፤ አንዱን ፡ ወይም ፡ ብዙዎቹን ፡ ማኅበሮች ፡ በመጠቅለል ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ ማኅበር ፡ በማቋቋም ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ማኅበሮች ፡ ለመቀላቀል ፡ ይችላሉ ።

(፪) በማጣራት ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ማኅበሮች ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በመቀላቀል ፡ መንገድ ፡ በሚቋቋመው ፡ አዲስ ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ለመቀላቀል ፡ ወይም ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፭፻፶ ። የመቀላቀል ፡ ውሳኔ ።**

መቀላቀሉ ፤ በሚቀላቀለው ፡ በያንዳንዱ ፡ ማኅበር ፡ መወሰን ፡ አለበት ። አስፈላጊም ፡ ከሆነ ፡ በጠቅላይ ፡ ወይም ፡ በጠቅላዩ ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ቢሆን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ባለአክሲዮኖች ፡ ልዩ ፡ ጉባኤዎች ፡ ወይም ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ባለቤቶች ፡ ጉባኤ ፡ መቀላቀሉን ፡ እንዲፈቅዱ ፡ ያስፈልጋል ።

**ቍ ፡ ፭፻፶፩ ። ስለ ፡ ማቀላቀያ ፡ ጽሑፍ ።**

(፩) የመቀላቀሉ ፡ ሁኔታዎች ፡ ባንድ ፡ ስምምነት ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ፤ ይኸውም ፡ ስምምነት ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በቍጥር፡ ፪፻፳፬ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በማስታወቂያ ፡ መገለጽ ፡ አለበት ።

(፪) ማስታወቂያውም ፡ በጠቅላዩ ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ ከመቀላቀል ፡ በተገኘው ፡ አዲስ ፡ ማኅበር ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ እንዲሁም ፡ ከመቀላቀሉ ፡ የተነሣ ፡ በጠፉት ፡ ማኅበሮች ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ መለጠፍ ፡ አለበት ።

(፫) ጠቅላዩ ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ በመቀላቀሉ ፡ የተገኘው ፡ ማኅበር ፤ የጠፉትን ፡ ማኅበሮች ፡ መብትና ፡ ግዴታዎች ፡ ይወስዳሉ ።

**ቍ ፡ ፭፻፶፪ ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መብት ።**

(፩) ከተቀላቀሉት ፡ ማኅበሮች ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ ማኅበር ፡ ከተቋቋመባቸው ፡ ማኅ

BACK



በሮች ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ መብታቸው ፡ የመቀላቀሉ ፡ ጽሑፍ ፡ ማስታወቂያ ፡ በንግድ ፡ አፈሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከወጣበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ለመቀላቀሉ ፡ ሥራ ፡ ተቃዋሚ ፡ ለመሆን ፡ ይችላሉ ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፤ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ሁሉ ፡ መቀላቀሉን ፡ የፈቀዱ ፡ መሆናቸውን ፡ እንዲሁም ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ያልሰጡ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ገንዘባቸውን ፡ የተቀበሉ ፡ ወይም ፡ ከሚጠይቁት ፡ የሚተካከል ፡ ገንዘብ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ባንክ ፡ የተቀመጠ ፡ መሆኑን ፡ የተረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተቃዋሚነትን ፡ ማስወገድ ፡ አለበት ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱ ፤ ተቃዋሚነትን ፡ አስወግዶና ፡ ጠቅላዩን ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ ከመቀላቀል ፡ የተገኘውን ፡ አዲስ ፡ ማኅበር ፡ የሚጠየቀውን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍል ፡ ወይም ፡ ዋስትና ፡ እንዲሰጥ ፡ በማስገደድ ፡ የመቀላቀሉ ፡ ውል ፡ ሙሉና ፡ ጠቅላላ ፡ ውጤትን ፡ እንዲያገኝ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፭፻፶፫ ። የባለግዴታ ፡ ወረቀት ፡ ባለቤቶች ፡ መብት ።

(፩) የተጠቀለለው ፡ ማኅበር ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ ባለቤቶች ፡ ጉባኤ ፡ መቀላቀሉን ፡ ያላጸደቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዕዳ ፡ ከፋይ ፡ የሆነው ፡ ማኅበር ፡ የመቀላቀሉ ፡ ውል ፡ በንግድ ፡ አፈሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ በማስታወቂያ ፡ ከወጣበት ፡ ጀምሮ ፡ እጅግ ፡ ቢዘገይ ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ጥያቄ ፡ ለሚያደርጉ ፡ አምጪዎች ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶችን ፡ ዋጋ ፡ መልሶ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፪) አዲስ ፡ ማኅበር ፡ ለማቋቋም ፡ መቀላቀሉን ፡ የሚወስኑ ፡ የማኅበሮች ፡ የግዴታ ፡ ወረቀት ፡ ባለቤቶች ፡ እንደዚሁ ፡ ያለ ፡ መብት ፡ አላቸው ።

ቍ ፡ ፭፻፶፬ ። ለገንዘብ፡ ጠያቂዎችና ፡ ለግዴታ ፡ ወረቀት ፡ ባለቤቶች ፡ የተፈቀደ ፡ መብት ፡ ማስታወቂያ ።

በንግድ ፡ መዝገብ ፡ የወጣው ፡ ማስታወቂያ ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፶፪ ፡ እና፡ ለግዴታ፡ ወረቀት፡ ባለቤቶች፡ በቍጥር፡ ፭፻፶፫ ፡ የተሰጠው ፡ መብት ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ሁኔታ ፡ የተገለጸ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

## አንቀጽ ፡ ፲ ።

## በውጭ ፡ አገር ፡ የተቋቋሙ ፡ ወይም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የሚሠሩ ፡ ማኅበሮች ።

ቍ ፡ ፭፻፶፭ ። ዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤታቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሆኖ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የተቋቋሙ ፡ ማኅበሮች ።

በውጭ ፡ አገር ፡ የተቋቋሙና ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤታቸው ፡ ወይም ፡ ዋናው ፡ የንግድ ፡ ሥራቸው ፡ ዓላማ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሆኑ ፡ ማኅበሮች ፡ የመመሥረቻቸው ፡

ጽሑፍ ፡ የሚጸናበትን ፡ ሁኔታ ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ቢሆንም ፡ የዚህ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ ውሳኔዎችና ፡ ተጨማሪ ፡ ሕጎች ፡ ጽሑፎች ፡ ሁሉ ፡ ይጸኑባቸዋል ።

ቍ ፡ ፭፻፵፩ ። በውጭ ፡ አገር ፡ ተቋቁመው ፡ በኢትዮጵያ ፡ አንድ ፡ ተነጣይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ቅርንጫፎች ፡ ያሏቸው ፡ ማኅበሮች ።

(፩) በውጭ ፡ አገር ፡ የተቋቋሙ ፡ ማኅበሮችና ፡ በኢትዮጵያ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ተነጣይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ካንዱ ፡ ነዋሪ ፡ እንደራሴ ፡ ጋራ ፡ የሚቋቋሙ ፡ ማኅበሮች ፡ የመመሥረቻውን ፡ ጽሑፍ ፡ ስለ ፡ ማኖርና ፡ ስለማስታወቅ ፡ እንዲሁም ፡ የሒሳቡን ፡ ሚዛን ፡ በማስ ታወቂያ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ፡ የሚመለከተው ፡ የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውሳኔዎች ፡ በየ ንዳንዱ ፡ ተነጣይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ቅርንጫፎች ፡ ላይ ፡ ይጸኑባቸዋል ።

(፪) እነዚሁ ፡ ማኅበሮች ፡ በኢትዮጵያ ፡ በነዋሪነት ፡ ዐይነት ፡ እንደራሴ ፡ የሚሆ ናቸውን ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ማስታወቅና ፡ የነዚህኑ ፡ ሰዎች ፡ የጅ ፡ ጽሑፍ ፡ ፊርማ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ማስቀመጥ ፡ አለባቸው ።

(፫) እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ተነጣይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶቻቸውን ፡ ወይም ፡ ቅርንጫ ፎቻቸውን ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፤ የሥራ ፡ ማከናወኛ ፡ ድርጅቱን ፡ ያሠራር ፡ ደንብ ፡ የሚመለከቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ወይም ፡ በአሠራራቸው ፡ እንዲጠብቁ ፡ የተ ወሰኑ ፡ ልዩ ፡ ሁናቴዎች ፡ ይጸኑባቸዋል ።

ቍ ፡ ፭፻፵፪ ። ከኢትዮጵያ ፡ ማኅበሮች ፡ ዐይነት ፡ የተለዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ማኅበሮች ።

በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ከተደነገጉትና ፡ ከተመለከቱት ፡ ማኅበሮች ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ሆነው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የተቋቋሙ ፡ ማኅበሮች ፡ የማኅበሮችን ፡ ውሎ ችና ፡ የአስተዳዳሪዎችን ፡ አላፊነትና ፡ ግዴታዎችን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበሮች ፡ ውሳኔዎች ፡ ይፈጸሙባቸዋል ።

ቍ ፡ ፭፻፵፫ ። ደንቦች ፡ ያልተፈጸሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚደርስ ፡ አላፊነት ።

በቍ ፡ ፭፻፵፩ ፡ እስከ ፡ ፭፻፵፪ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የተመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ ሳይፈ ጸሙ ፡ በሚቈዩበት ፡ ጊዜ ፡ በማኅበሩ ፡ ስም ፡ የሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ለማኅበሩ ፡ ግዴታ ዎች ፡ በሙሉ ፡ ባንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ ለፈጸሙት ፡ አላፊዎች ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፭፻፵፬ ። የሥራ ፡ ክንውናቸው ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሆኖ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የተቋቋሙ ፡ ማኅበሮች ።

በኢትዮጵያ ፡ የተቋቋሙ ፡ ማኅበሮች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የሥራ ፡ ክንውናቸው ፡ ጉዳይ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ቢገኝ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውሳኔዎች ፡ ይፈጸሙባቸዋል ።

**ቍ ፡ ፭፻፷ ። የውጭ ፡ አገር ፡ ጥቅሞች ፡ በውስጣቸው ፡ የሚገኙባቸው ፡ ማኅበሮች ።**

የውጭ ፡ አገር ፡ ጥቅሞች ፡ በውስጣቸው ፡ ለሚገኙባቸው ፡ ማኅበሮች ፡ የተወሰነውን ፡ የሥራ ፡ ክንውን ፡ ልዩ ፡ ሁናቴዎች ፡ የሚደነግጉ ፡ ወይም ፡ ሥራውን ፡ የሚከለክሉ ፡ የልዩ ፡ ሕጎች ፡ ውሳኔዎች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ።

# ሦስተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## ስለ ፡ ማጓጓዝ ፡ (ማመላለስ) ፡ ሥራና ፡ ስለ ፡ ኢንሹራንስ ።

## አንቀጽ ፡ ፩ ።

## በየብስ ፡ ስለሚደረግ ፡ የማጓጓዝ ፡ ሥራ ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፭፻፷፩ ። የማጓጓዝ ፡ ውል ።**

የማጓጓዝ ፡ ውል ፡ ማለት ፡ አጓጓዥ ፡ ዋጋ ፡ በመቀበል ፡ ሰውን ፤ ጓዝንና ፡ ዕቃዎችን ፡ እተወሰነ ፡ ስፍራ ፡ ለማድረስ ፡ ግዴታ ፡ የገባበት ፡ ስምምነት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፭፻፷፪ ። ጓዝ ።**

(፩) መንገደኛው ፡ ራሱ ፡ በሻንጣው ፤ በቅርጫቶች ፡ ወይም ፡ በእጅ ፡ የሚይዘው ፡ ቀላል ፡ ከረጢት ፡ ወይም ፡ በመጠቅለያና ፡ ይህን ፡ በመሳሰሉ ፡ ነገሮች ፡ የሚይዛቸው ፡ ሁሉ ፡ ጓዝ ፡ ይባላሉ ።

(፪) አጓጓዡ ፡ ያልመዘገባቸው ፡ መንገደኛው ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ የሚጓዘው ፡ ሁሉ ፡ በእጅ ፡ የሚያዝ ፡ ጓዝ ፡ ይባላል ።

(፫) ለአጓጓዡ ፡ ተሰጥተው ፡ በእሱ ፡ አላፊነትና ፡ አደራ ፡ የሚጓዙ ፡ ጓዞች ፡ የተመዘገቡ ፡ ጓዞች ፡ ይባላሉ ።

**ቍ ፡ ፭፻፷፫ ። በመሬት ፡ ስለሚደረግ ፡ ማጓጓዝ ።**

በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የተመለከተው ፡ ውሳኔ ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ በመቀበል ፡ ሰዎችን ፤ ጓዝን ፤ ወይም ፡ ዕቃዎችን ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ የተዘረጋ ፡ በተለየም ፡ በመንገድ ፤ በምድር ፡ ባቡር ፡ መንገድ ፡ ወይም ፡ በመሬት ፡ መሐል ፡ በሚገኙት ፡ ኈረቶች ፡ ወንዞች ፤ ቦዮች ፡ (ካናልስ) ፡ ወይም ፡ ሐይቆች ፡ ላይ ፡ በሚደረገው ፡ መጓጓዝ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

BACK



ቍ ፡ ፭፻፺ ። በአየር ፡ ላይ ፡ ስለ፡ማጓጓዝ ።

ሰዎችን ፤ ጓዝን ፤ ወይም ፡ ዕቃዎችን ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ የማጓጓዝ ፡ ጕዳይ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በአንቀጽ ፡ ሁለት ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

ቍ ፡ ፭፻፺፩ ። በባሕር ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መጓዝ ።

ሰዎችን ፤ ጓዝንና ፡ ወይም ፡ ዕቃዎችን ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ የማጓጓዝ ፡ ጕዳይ ፡ በባሕር ፡ ሕግ ፡ ተገቢ ፡ በሆኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

ቍ ፡ ፭፻፺፪ ። በወኪል ፡ አማካይነት ፡ ለማጓጓዝ ፡ የሚደረግ ፡ ውል ።

በወኪል ፡ አማካይነት ፡ ስለሚደረግ ፡ የማጓጓዝ ፡ ውል ፡ ስለ ፡ ውክልና ፤ ስለ ፡ ኮሚሲዮንና ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ በሚለው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቍ ፡ ፪ሺ፪፻፶፩ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

የማጓጓዝ ፡ (የማመላለሻ) ፡ ሰነድ ።

ክፍል ፡ ፩ ።

ስለ ፡ መንገደኞች ፡ ቲኬት ።

ቍ ፡ ፭፻፺፫ ። የማጓገዣ ፡ ሰነድ ፡ እንዲያገዘ ፡ ማስገደድ ፡ የሚቻል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) ሰውን ፡ ለማጓጓዝ ፡ የሚደረግ ፡ ውል ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ነው ። ስለ ፡ ሆነም ፡ አጓዡ ፡ መንገደኛው ፡ የማጓዣ ፡ ሰነድ ፤ ቲኬት ፤ ወይም ፡ የደንበኛነት ፡ ቲኬት ፤ እንዲቀበልና ፡ ጕዞው ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ጠብቆ ፡ መያዝ ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ ሊያስታውቀው ፡ ይችላል ።

(፪) የመጓዣ ፡ ሰነድ ፡ ሳይኖረው ፡ የሚጓዝ ፡ መንገደኛ ፡ ከዋጋው ፡ በላይ ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ይከፍላል ፡ የሚል ፡ ማስታወቂያ ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

(፫) ስለ ፡ ሆነም ፡ ለመንገደኛው ፡ በሚሰጠው ፡ ቲኬት ፡ ላይ ፡ የሚከፈለው ፡ ዋጋና ፡ የሰዓቱ ፡ መነሻና ፡ መድረሻ ፡ የተመለከተ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

ክፍል ፡ ፪ ።

የጓዝ ፡ ቲኬት ።

ቍ ፡ ፭፻፺፬ ። የመንገደኛ ፡ መብት ።

ስለ ፡ ተመዘገቡ ፡ ጓዞች ፤ አጓጓዡ ፡ ለመንገደኛው ፡ ቀኑንና ፡ የተሰጠበትን ፡ ስፍራ ፤ ጓዙ ፡ ከየት ፡ ጀምሮ ፡ እስከየት ፡ እንደሚጓዝ ፤ የጥቅሉን ፡ ብዛት ፤ የጓዙን ፡ ክብደትና ፡ በመንገደኛው ፡ የመጓጓዣ ፡ ዋጋ ፡ ላይ ፡ የተጨመረ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡

የጓዙን ፡ ማጓጓዣ ፡ ዋጋ ፡ የሚያመለክት ፡ ቲኬት ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባል ።

**ቍ ፡ ፭፻፷፱ ። የጓዝ ፡ ቲኬት ፡ የሚሰጥበት ፡ ምክንያት ።**

(፩) ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የጓዝ ፡ ማጓጓዣ ፡ ቲኬት ፡ ጓዙ ፡ ለመመዝገቡና ፡ ስለ ፡ መጓጓዣውም ፡ ሁኔታ ፡ አስረጅ ፡ ነው ።

(፪) የጓዝ ፡ ማጓጓዣ ፡ ቲኬት ፡ አለመኖር ፡ ወይም ፡ የቲኬቱ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ መሆን ፡ ወይም ፡ የቲኬቱ ፡ መጥፋት ፡ የማጓጓዣ ፡ ውል ፡ መኖሩንና ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ ውሉ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ የሚያስቀር ፡ አይሆንም ። ነገር ፡ ግን ፡ አጓጓዡ ፤ የዕቃው ፡ ጠያቂው ፡ ባለመብት ፡ መሆኑን ፡ ካላስረዳ ፡ በቀር ፡ የመጓጓዣው ፡ ቲኬት ፡ ሳይቀርብለት ፡ ዕቃውን ፡ ማስረከብ ፡ አይገባውም ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ዕቃዎች ፡ የማጓጓዣ ፡ ሰነድ ።

**ቍ ፡ ፭፻፸ ። ዕቃዎቹን ፡ የማጓጓዝ ፡ ሁኔታ ፡ የሚገልጽ ፡ ሰነድ ፡ አለመኖር ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ መሆን ፡ ወይም ፡ መጥፋት ።**

ዕቃዎቹን ፡ የማጓጓዝ ፡ ሁኔታ ፡ የሚገልጽ ፡ ሰነድ ፡ አለመኖር ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ መሆን ፡ ወይም ፡ መጥፋት ፤ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የተመለከተውን ፡ ድንጋጌና ፤ ዕቃዎቹን ፡ ስለ ፡ ማጓጓዝ ፡ የተደረገውን ፡ ውል ፡ ዋጋ ፡ ያለውና ፡ ተፈጻሚ ፡ መሆኑን ፡ ሊያስቀረው ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፭፻፸፩ ። የዕቃ ፡ ማጓጓዝ ፡ ሰነድ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።**

ዕቃውን ፡ አጓጓዥ ፡ የሆነው ፤ ዕቃውን ፡ የሚልከውን ፡ ሰው ፡ የማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ አዘጋጅቶ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ። ላኪውም ፡ ይህንን ፡ የማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ አጓጓዡ ፡ እንዲቀበለው ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፭፻፸፪ ። የዕቃ ፡ ማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ ግልባጮች ።**

(፩) የዕቃ ፡ የማጓጓዣው ፡ ሰነዶች ፡ በሦስት ፡ ግልባጮች ፡ ይዘጋጃሉ ።

(፪) የመጀመሪያው ፡ ግልባጭ ፡ ላኪው ፡ ፈርሞበት ፡ ለአጓጓዥ ፡ ይሰጣል ።

(፫) ሁለተኛው ፡ ግልባጭ ፡ ላኪውና ፡ አጓጓዡ ፡ ፈርመውበት ፡ ከዕቃው ፡ ጋራ ፡ ይሆናል ።

(፬) ሦስተኛው ፡ ግልባጭ ፡ አጓጓዡ ፡ ፈርሞበት ፡ ዕቃውን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ አጓጓዡ ፡ ለላኪው ፡ ይሰጠዋል ።

**ቍ ፡ ፭፻፸፫ ። የዕቃ ፡ ማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ የሚመለከት ፡ ዝርዝር ።**

የዕቃ ፡ ማጓጓዣው ፡ ሰነድ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ዝርዝሮች ፡ ሊኖሩበት ፡ ይገባል ።

BACK



(፩) የተሰጠበትን ፡ ቀንና ፡ ስፍራ ፤
(፪) ዕቃው ፡ ከምን ፡ ስፍራ ፡ እስከየት ፡ ድረስ ፡ እንደሚጓዝ ፤
(፫) የላኪውና ፡ የተቀባዩ ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፤
(፬) የአጓጓዡ ፡ ሰው ፡ ስም ፤
(፭) የማጓጓገሪው ፡ ዐይነት ፤
(፮) የዕቃው ፡ ዐይነት ፤ ብዛት ፤ መጠኑ ፡ ወይም ፡ ክብደቱ ፤
(፯) በጥቅሉ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ልዩ ፡ ምልክት፡ ወይም ፡ ያለም ፡ እንደ፡ሆነ ፡ የተለጠፈበት ፡ ቊጥር ፤
(፰) የማጓጓዣው ፡ ዋጋ ፤ ዕቃው ፡ የሚደርሰበት ፡ ጊዜና ፡ የሚጓዝበት ፡ አቅጣጫ ፡ መሥመር ።

ቍ ፡ ፰፻፸፬ ። ለታዘዘለት ፡ የሚል ፡ የዕቃ ፡ ማጓጓዣ ፡ ሰነድ ።

ላኪውና ፡ አጓዡ ፡ የሚስማሙ ፡ ከሆነ ፡ የማጓጓዣው ፡ ሰነድ ፡ በትእዛዝ ፡ የሚል ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፰፻፸፭ ። ሌላ ፡ የማጓጓዣ ፡ ሰነዶች ።

ላኪውና ፡ አጓዡ ፡ የሚስማሙ ፡ ከሆነ ፡ የማጓጓዣው ፡ ሰነድ ፡ በሌላ ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ወረቀት ፡ በተለየም ፡ ተገቢውን ፡ ማስታወቂያ ፡ ሁሉ ፡ ሞልቶ ፡ አጓዡ ፡ ለላኪው ፡ በሚሰጠው ፡ ደረሰኝ ፡ ሊተካ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፰፻፸፮ ። የማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ የሚሰጠው ፡ ውጤት ።

ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ ውሉ ፡ የተፈጸመ ፡ ለመሆኑ ፤ ዕቃዎቹን ፡ ለመቀበሉ ፤ ስለ ፡ ዕቃዎቹ ፡ ዐይነት ፡ ብዛት ፤ መጠንና ፡ ክብደት ፡ የማጓጓዣው ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ አጓዡ ፡ የሚሰጠው ፡ ደረሰኝ ፡ አስረጅ ፡ ይሆናል ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ስለ ፡ መጓጓዝ ፡ በሚደረገው ፡ ውል ፤ የተዋዋዮቹ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ።

ክፍል ፡ ፩ ።

ዕቃዎቹን ፡ የላከውና ፡ የተቀባይ ፡ ሰው ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ።

ቍ ፡ ፰፻፸፯ ። ላኪው ፡ የሚያዘጋጀው ፡ ማስታወቂያ ።

(፩) እያንዳንዱ ፡ የማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተሉትን ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።
(ሀ) የላኪውና ፡ የተቀባዩ ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፤
(ለ) ዕቃው ፡ ከየት ፡ እስከ ፡ የት ፡ እንደሚጓዝ ፤
(ሐ) የዕቃው ፡ ዐይነት ፤ ብዛት ፤ ዋጋ ፤ ክብደት ፤
(መ) በጥቅሎቹ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ ወይም ፡ ተጽፎበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቍጥሩን ።

BACK



(፪) ስለ ፡ መጓጓዙ ፡ በተደረገው ፡ ያልተሟላ ፤ ትክክለኛና ፡ ሥርዐት ፡ ባልያዘ ፡ ማስታወቂያ ፡ በሚደርሰው ፡ ጕዳይ ፡ ላኪው ፡ ሰው ፡ ለአጓጓዡ ፡ ወይም ፡ አጓዡ ፡ ግዴታ ፡ ለገባለት ፡ ሰው ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፭፻፸፯ ። መጠቅለል ።**

(፩) የዕቃዎቹ ፡ ዐይነት ፡ መጠቅለል ፡ የሚያስፈልጋቸው ፡ ሲሆን ፡ ዕቃዎቹን ፡ እንዳይጠፉና ፡ እንዳይበላሹ ፡ ወይም ፡ ሰውን ፤ ጓዝንና ፡ ሌሎቹን ፡ ዕቃዎች ፡ እንዳይጎዱ ፡ (እንዳይበላሹ) ፡ አድርጎ ፡ ላኪው ፡ ሊጠቀልላቸው ፡ ይገባል ።

(፪) ከመጠቅለል ፡ ጕድለት ፡ የተነሣ ፡ ለሚደርሰው ፡ ጕዳት ፡ ላኪው ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ፤ ስለሆነም ፡ መጠቅለል ፡ የሚገባቸው ፡ መሆኑን ፡ ሲያውቅ ፡ ሳይጠቀለሉ ፡ ወይም ፡ በተሟላ ፡ ሁኔታ ፡ ሳይጠቀለሉ ፡ ዕቃዎቹን ፡ አጓዡ ፡ የተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ራሱ ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፭፻፸፰ ። ላኪው ፡ በዕቃው ፡ ለማዘዝ ፡ ስላለው ፡ መብት ።**

(፩) በማጓጓዣው ፡ ውል ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ግዴታዎች ፡ ሁሉ ፡ ከፈጸመ ፡ ላኪው ፡ ዕቃውን ፡ በአጓጓዡ ፡ እጅ ፡ መልሶ ፡ ለመውሰድ ፡ ወይም ፡ ዕቃው ፡ በመጓዝ ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ለማቆም ፤ ወይም ፡ በመጓዝ ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ወይም ፡ ዕቃው ፡ እተላከበት ፡ ስፍራ ፡ ሲደርስ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ለተመከተው ፡ ተቀባይ ፡ ሳይሆን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ እንዲሰጡ ፡ ለማድረግ ፡ ላኪው ፡ በዕቃዎቹ ፡ ላይ ፡ የማዘዝ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) የማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ ለላኪው ፡ ተሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ላኪው ፡ ይህንን ፡ የመጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ ለአጓዡ ፡ ሳያቀርብ ፡ በዕቃው ፡ የማዘዝ ፡ መብቱን ፡ ሊሠራበት ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፭፻፸፱ ። ላኪው ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ሊያዝ ፡ መብት ፡ የሚያጣበት ፡ ምክንያት ።**

የማጓጓዣው ፡ ሰነድ ፡ ዕቃው ፡ ለተላከለት ፡ ሰው ፡ ከተሰጠው ፡ በኋላ ፡ ወይም ፡ ዕቃው ፡ እመድረሻው ፡ ስፍራ ፡ ደርሶ ፡ ተቀባዩ ፤ አጓጓዡ ፡ ዕቃውን ፡ እንዲያስረክበው ፡ ከጠየቀ ፡ በኋላ ፡ ላኪው ፡ በዕቃዎቹ ፡ ላይ ፡ ሊያዝባቸው ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፭፻፹ ። የተቀባይ ፡ መብት ።**

በቍጥር ፡ ፭፻፸፰ ፡ እና ፡ ፭፻፸፱ ፡ ለላኪው ፡ የታወቁለት ፡ መብቶች ፡ እንዲጠበቁ ፡ ሆነው ፡ ተቀባዩ ፡ ስለ ፡ ማጓጓዙ ፡ የተዋዋለው ፡ ውል ፡ የሚያስገኛቸውን ፡ መብቶች ፡ ሊጠቀምባቸውና ፡ ለሚያስከትላቸውም ፡ ግዴታዎች ፡ ኀላፊ ፡ ሆኖ ፡ ሊጠየቅ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፭፻፹፩። የማጓጓዣው፡ ዋጋ ።**

(፩) የማጓጓዣውን ፡ ዋጋና ፡ ተጨማሪውን ፡ ጥቃቅን ፡ ወጪ ፡ ላኪው ፡ ይከፍላል ።

BACK



(፪) የማጓጓዣውን ፡ ዋጋ ፡ የሚከፈለው ፡ ከዕቃዎቹ ፡ መድረሻ ፡ ስፍራ ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ ሆነ፤ የማጓጓዣው፡ ዋጋና፡ ማናቸውንም፡ ጥቃቅን፡ ወጪ፡ ላኪና፡ ተቀባዩ፡ እያንዳንዳቸው፡ ለመክፈል፡ በንአድነት፡ የማይከፋፈል፡ ኀላፊነት፡ ይኖርባቸዋል።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ዕቃዎችና ፡ ስለ፡ ተመዘገቡ ፡ ጓዞች ፡ የአጓጓዥ ፡ ግዴታዎች ።

### ቍ ፡ ፭፻፺፫ ። ዕቃዎችን ፡ ወይም ፡ ጓዞችን ፡ ስለ ፡ ማድረስ ።

(፩) አጓዡ ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ የሚገባውን ፡ ሙሉ ፡ ጥንቃቄ ፡ አድርጎ ፡ ዕቃ ዎቹን ፡ ማጓዝና ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜና ፡ ስፍራ ፡ አድርሶ ፡ ለተቀባዩ ፡ ማስረ ከብ ፡ አለበት ።

(፪) እንዲሁም ፡ የተመዘገቡ ፡ ጓዞችን ፡ በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ አጕዞ ፡ ለተቀባዩ ፡ ወይም ፡ ስለእሱ ፡ ሁኖ ፡ መቀበል ፡ ለሚገባው ፡ ሰው ፡ ማስረከብ ፡ አለበት ።

### ቍ ፡ ፭፻፺፬ ። ለተቀባዩ ፡ ማሳሰቢያ ፡ ስለ ፡ መላክ ።

ዕቃዎቹ ፡ ለተቀባዩ ፡ የሚሰጡት ፡ በደንበኛ፡ መኖሪያው፡ ቦታ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ፤ ወይም፡ ተቀባዩ ፡ የተላኩትን ፡ ዕቃዎች ፡ መድረሳቸውን ፡ ዐውቆ ፡ ያልተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አጓዡ ፡ ያለመዘግየት ፡ የዕቃዎቹን ፡ መድረስና ፡ ሊረከብ ፡ የሚችልበትን ፡ ስፍራና ፡ ሰዓት ፡ በመግለጽ ፡ ማሳሰቢያ ፡ ይላክለታል ።

### ቍ ፡ ፭፻፺፭ ፤ ለማስረከብ ፡ ስላልተቻለ ፡ ዕቃ ።

(፩) ዕቃዎቹን ፡ ለማስረከብ ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አጓዡ ፡ ላኪው ፡ አስፈላጊ ውን ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጠው ፡ ሳይዘገይ ፡ ማሳሰቢያ ፡ ይልክለታል ። አጓዡ ፡ ዕቃውን ፡ ለማኖር ፡ የሚያዳግተው ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፡ ዕቃው ፡ በሌላ ፡ በሦስተኛ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲያዝለት ፡ ያመለክታል ።

(፪) ለማስረከብ ፡ ያልቻለው ፡ ዕቃ ፡ ዐይነት ፡ የሚበላሽ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፤ አጓዡም ፡ ላኪው ፡ የሚሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ በጊዜው ፡ ያልደረሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዕቃው ፡ እንዲሸጥ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

### ቍ ፡ ፭፻፺፮ ። ለማስረከብ ፡ ስላልተቻለ ፡ ጓዝ ።

(፩) የተመዘገበ፡ጓዝ፡ ተቀባዩ፡ በደንበኛ፡ መኖሪያው፡ቦታ፡ የሚሰጥ፡ ባልሆነ፡ ጊዜ፡ መንገደኛው፡ ወይም፡ ስለሱ፡ ሆኖ፡ መቀበል፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ ዕቃው ፡ እንደ ደረሰ ፡ ያልወሰደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አጓዡ ፡ መንገደኛውን ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጥ ፡ ማሳሰቢያ ፡ ይልክለታል ።

(፪) ለማስረከብ ፡ ያልቻለውን ፡ የተመዘገበ ፡ ጓዝ ፡ አጓዡ ፡ ለማስቀመጥ ፡ ያል ቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የጓዙ ፡ ዐይነት ፡ የሚበላሽ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በቍ

ጥር ፡ ፮፻፺፩ ፡ እንደተወሰነው ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ሰው ፡ ማጓጓዝ ፡ ውል ፡ የተዋዋዮቹ ፡ ግዴታዎች ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፪ ። የመንገደኛው ፡ ግዴታ ።**

መንገደኛው ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ የተወሰነውን ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ፤ ጕዞው ፡ የሚጀ ምርበት ፡ ስፍራ ፡ በተወሰነው ፡ ሰዓት ፡ መድረስና ፡ እንዲሁም ፡ በጕዞው ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ አጓዡ ፡ የሚሰጠውን ፡ ትእዛዝና ፡ እንዲሁም ፡ በሕግ ፡ የታዘዘውን ፡ ማክ በር ፡ ይገባዋል ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፫ ። የአጓዥ ፡ ግዴታ ።**

አጓዡ ፡ መንገደኛውን ፡ በመልካም ፡ ይዞታና ፡ ጥበቃ ፡ እንዲሁም ፡ ስለ ፡ ምቾ ቱና፡ ስለ፡ ጕዞው ፤ በውሉ ፡ የተወሰነውን፡ ጊዜ ፡ አክብሮ ፡ እንደተወሰነው ፡ እመ ድረሻ ፡ ስፍራ ፡ ያደርሰዋል ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## የአጓዥ ፡ አላፊነት ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፬ ፤ በእጅ ፡ የሚያዝ ፡ ቀላል ፡ ጓዝ ።**

በእጅ ፡ የሚያዝ ፡ ቀላል ፡ ጓዝ ፡ በመንገደኛው ፡ ኀላፊነት ፡ ብቻ ፡ የሚያዝ ፡ ስለ፡ሆነ ፤ ይህን ፡ የመሰለው ፡ ጉዳት ፡ ቢደርስበት ፡ ወይም ፡ ቢጠፋ ፡ አጓዡ ፡ በኀ ላፊነት ፡ አይጠየቅም ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፭ ። የተመዘገቡ ፡ ጓዞች ፤ ወይም ፡ ዕቃዎች ፤ የጠፉ ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ የደረሰ ባቸው ፡ ሲሆን ።**

ከዚህ ፡ በሚከተሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከተው ፡ ውሳኔ ፡ ሳይነካ ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ የተመዘገቡ ፡ ጓዞች ፡ ሲጠፉ ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ ሲያገኛቸው ፡ ወይም ፡ የማስረከቢያው ፡ ጊዜ ፡ ቢያልፍና ፡ ቢዘገይ ፡ አጓዡ ፡ በኀ ላፊነት ፡ ይጠየቃል ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፮ ። በተለዩ ፡ ምክንያቶች ፡ ከኀላፊነት ፡ መዳን ።**

በከፊልም፡ ሆነ፡ በሙሉ፡ አጓዡ ፡ ከተመዘገቡት ፡ ዕቃዎችና ፡ ጓዞች፡ በቍጥር፡ ፮፻፺ ፡ መሠረት ፡ ከአላፊነት ፡ የሚድነው ፡ የጠፋው ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ የደረ ሰው ፡ ወይም ፡ የዘገየው ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ከፍተኛ ፡ ኀይል ፡ ወይም ፡ በዕ ቃው ፡ ውስጣዊ ፡ ጕድለት ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ በላኪና ፡ በተቀባዩ ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፪ ። በጕዞ ፡ ላይ ፡ ስለሚደርስ ፡ መቀነስ ።**

በዕቃዎች ፡ ወይም ፡ በተመዘገቡ ፡ ጓዞች ፡ ምክንያት ፡ ከብዶታቸው ፡ ወይም ፡ መጠናቸው ፡ ቢቀንስ ፡ ይህ ፡ ሁኔታ ፡ ከዕቃው ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ፡ እንደ፡ መጣ፡ ውስጣዊ ፡ ጕድለት ፡ ስለሚቈጠር ፡ ከተለመደው ፡ መጠን ፡ በላይ ፡ ካልሆነ ፡ አጓዡ ፡ በአላፊነት ፡ አይጠየቅም ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፫ ። ከአላፊነት ፡ ውጭ ፡ የሚያደርግ ፡ የውል ፡ ቃል ።**

(፩) ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ የተመዘገቡ ፡ ጓዞች ፡ ከማስረከብ ፡ ስለ ፡ መዘግየት ፡ አጓዡ ፡ ከአላፊነት ፡ የሚያድነውን ፡ ውል ፡ ቢዋዋል ፡ ይጸናል ።

(፪) በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለጠፉ ፡ ወይም ፡ ለተጎዱ ፡ ዕቃዎች ፤ ለተመዘገቡ ፡ ጓዞች ፡ አጓዡን ፡ ከአላፊነት ፡ የሚያድነው ፡ ሌላ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፬ ። የአላፊነትን ፡ መጠን ፡ ስለ ፡ መወሰን ።**

የአጓዡን ፡ አላፊነት ፡ በማቅለል ፡ በአላፊነት ፡ የሚከፍለውን ፡ የካሣ ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ከዕቃው ፡ ግምት ፡ በእጅጉ ፡ ዝቅ ፡ በማድረግ ፡ የተደረገ ፡ ውል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ የተመዘገቡ ፡ ጓዞች ፡ በከፊልም ፡ ሆነ ፡ በሙሉ ፡ ሲጠፉ ፡ ወይም ፡ ሲጎዱ ፡ አጓዡ ፡ የሚጠይቀውን ፡ የአላፊነት ፡ ልክ ፡ በውለታ ፡ መወሰን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፭ ። ስለ ፡ መንገደኞች ፡ አጓዡ ፡ ያለበት ፡ አላፊነት ።**

ከዚህ ፡ በታች ፡ በተጻፉት ፡ ቍጥሮች ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከተው ፡ ውሳኔ ፡ በስተቀር ፡ ሰውን ፡ የሚያጓዝ ፤ መንገደኛው ፡ በጕዞው ፡ ላይ ፡ ስለሚደርስበት ፡ መዘግየት ፡ እንዲሁም ፡ በጕዞው ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ በሚሳፈርበትና ፡ ወይም ፡ በሚወርድበት ፡ ጊዜ ፡ በአደጋ ፡ ምክንያት ፡ ለሚደርስበት ፡ መቍሰል ፡ ወይም ፡ የአካል ፡ መጕደል ፡ ወይም ፡ የሕይወት ፡ ማለፍ ፡ አጓዡ ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፮ ። በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ ከአላፊነት ፡ ስለ ፡ መዳን ።**

በቍጥር ፡ ፮፻፺፭ ፡ እንደተገለጸው ፡ የሞቱ ፡ ወይም ፡ የአካሉ ፡ ከፊል ፡ ወይም ፡ ጠቅላላ ፡ አደጋ ፡ የደረሰው ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ከፍተኛ ፡ ኀይል ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰውና ፡ ወይም ፡ በመንገደኛው፡ ጥፋት፡ መሆኑን፡ ያስረዳ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ አጓዡ ፡ በአላፊነት ፡ ከመጠየቅ ፡ ይድናል ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፯ ። የአላፊነትን ፡ መጠን ፡ ስለ ፡ መወሰን ።**

(፩) የተጎዳው ፡ ማንኛውም ፡ ዐይነት ፡ መንገደኛ ፡ ቢሆንም ፡ አጓዡ ፡ በአላፊነት ፡ ለአንድ፡ መንገደኛ፡ የሚከፈለው፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ከ፴ሺ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ አይበልጥም ።

(፪) ካሣው ፡ በየጊዜው ፡ በመጠሪያ ፡ ዐይነት ፡ የሚከፈል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የመጠሪያው ፡ ገንዘብ ፡ የሚገኝበት ፡ ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ከ፺ሺ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ሊበልጥ ፡ አይገባም ።

ቍ ፡ ፮፻፺፰ ። ከአላፊነት ፡ የሚያድኑ ፡ የውል ፡ ቃሎች ።

(፩) በጕዞው ፡ ላይ ፡ ለሚደርሰው ፡ ማናቸውም ፡ መዘግየት ፡ አጓዡ ፡ በውለታ ፡ ከአላፊነት ፡ ለመዳን ፡ ይችላል ።

(፪) ለሞት ፡ ወይም ፡ ለአካል ፡ መጕደል ፡ ወይም ፡ ለመቁሰል ፡ አጓዡን ፡ ከአላፊነት ፡ የሚያድንና ፡ ወይም ፡ የአላፊነቱን ፡ ከፍተኛው ፡ መጠን ፡ ከ፺ሺ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ በማሳነስ ፡ የሚወሰን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ዋጋ ፡ አይኖረውም ።

ቍ ፡ ፮፻፺፱ ። በልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ የአላፊነት ፡ መጠንን ፡ መወሰን ፡ ስላለመቻል ።

ጉዳት ፡ የደረሰው ፡ አጓዡ ፡ በፈጸመው ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ ባደረገው ፡ ጕድለትና ፡ እንዲሁም ፡ ይህ ፡ ተግባርና ፡ አደጋ ፡ ጉዳት ፡ ሊያደርስ ፡ ወይም ፡ ሊፈጥር ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በቍ ፡ ፮፻፺፯ ፡ እና ፡ ፮፻፺፰ ፡ የተደነገገው ፡ ውሳኔ ፡ አይጸናም ።

ቍ ፡ ፯፻ ። የተቀባባይ ፡ አጓዥ ፡ አላፊነት ።

(፩) የማጓዙ ፡ ውለታ ፡ የተደረገው ፡ በአንድ ፡ አጓዥ ፡ ሳይሆን ፡ ከአንድ ፡ በበለጡ ፡ አጓዦች ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መንገደኛው ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መንገደኛው ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ በውለታው ፡ ላይ ፡ መጀመሪያው ፡ አጓዥ ፡ ለመላ ፡ ጕዞው ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ፤ ተብሎ ፡ በግልጽ ፡ የተዋዋሉ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በአላፊነት ፡ መጠየቅ ፡ የሚቻለው ፡ አደጋው ፡ ወይም ፡ መዘግየቱ ፡ በደረሰበት ፡ ጊዜ ፡ አጓዥ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) ስለ ፡ ዕቃዎቹ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ተመዘገቡ ፡ ጓዞች ፡ ላኪው ፡ በአላፊነት ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችለው ፡ የመጀመሪያውን ፡ አጓዥ ፡ ነው ፤ ተቀባዩ ፡ ግን ፡ በአላፊነት ፡ የሚይዘው ፡ የመጨረሻውን ፡ አጓዥ ፡ ነው ፤ ላኪውም ፡ ሆነ ፡ ተቀባዩ ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ ለሆነው ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ መዘግየት ፡ ጉዳት ፡ በደረሰበት ፡ ጊዜ ፡ ያጕዝ ፡ የነበረውን ፡ በተጨማሪ ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) የተጠቀሱት ፡ አጓዦች ፡ ለላኪውና ፡ ለተቀባዩ ፡ የጋራ ፡ አላፊነት ፡ አለባቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## በፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ መክሰስ ።

ቍ ፡ ፯፻፩ ። በልዩ ፡ ዐዋቂ ፡ ስለ ፡ ማስመርመር ፤ ስለ ፡ ማስቀመጥና ፡ ስለ ፡ መሸጥ ።

(፩) ስለ ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ተመዝገቡ ፡ ጓዞች ፡ ክርክር ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

BACK



ዕቃው ፡ ወይም ፡ የተመዘገበው ፡ ጓዝ ፡ በሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማመልከቻ ፡ ሲቀርብለት ፡ ለነገሩ ፡ ልዩ ፡ ዐዋቂ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ የአስረጂነት ፡ ቃሉን ፡ እንዲሰጥ ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል ፤ አመልካቹ ፡ ጉዳዩ ፡ ለሚመለከታቸው፡ወገኖች፡እንዲገኙ፡መጥሪያ፡ይልካል ፤ ነገር፡ግን፡ነገሩ ፡ አስቸኳይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መጥሪያ ፡ መላኩ ፡ እንዲቀር ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ።

(፪) ዕቃው ፡ ወይም ፡ የተመዘገበው ፡ ጓዝ ፡ በሦስተኛ ፡ ወገን ፡ እጅ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዕቃውን ፡ ሁኔታ ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ ዕቃው ፡ ወይም ፡ የተመዘገበው ፡ ጓዝ ፡ እንዲሸጥ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፮፻፪ ። ስለ ፡ መቀበልና ፡ ስለ ፡ መቃወም ።

(፩) በከፊል፡ ወይም፡ በጠቅላላው፡ በዕቃው ፡ ላይ፡ ለደረሰ፡ ጉዳት ፤ መዘግየትና ፡ መጥፋት ፡ ተቀባዩ ፡ ባለው ፡ የመከራከር ፡ መብት ፤ ዕቃዎችን ፡ ወይም ፡ የተመዘገቡ ፡ ጓዞችን ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ሲቀበል ፡ በአጓዡ ፡ በኩል ፡ የማታለል ፡ ነገር ፡ ካልተሠራ ፡ በቀር ፡ አንዳች ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ።

(፪) ስለሆነም ፡ ቀድሞ ፡ ያልታወቀ ፡ የማይታይ ፡ ጉድለት ፡ ከሆነ ፡ ይህንኑ ፡ ጉድለት ፡ ተቀባዩ ፡ ወዲያውኑ ፡ እንዳወቀ ፡ ወይም ፡ ከተረከበ ፡ ጀምሮ ፡ ከስባት ፡ ቀን ፡ ባልበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ክርክር ፡ ቢያቀርብ ፡ አጓዡ ፡ በኃላፊነት ፡ ከመጠየቅ ፡ አይድንም ።

ቍ ፡ ፮፻፫ ። ስለ ፡ ይርጋ ።

(፩) የመንገደኛው ፡ ወይም ፡ የዕቃ ፡ ወይም ፡ የተመዘገቡ ፡ ጓዞች ፡ መድረሻ ፡ ከሆነው ፡ ስፍራ ፡ ከደረሱበት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ መድረስ ፡ ይገባቸው ፡ ከነበረበት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ጕዞው ፡ እንዲቆም ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ እንሥቶ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ከቈዩ ፡ በኋላ ፡ የማጓጓዣ ፡ ውል ፡ ምክንያት ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይርጋው ፡ ያግዳቸዋል ።

(፪) ክሱ ፡ በይርጋ ፡ ከታገደ ፡ በኋላ ፡ በዚሁ ፡ ግዴታ ፡ ምክንያት ፡ ገንዘብ ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የተከሳሽ ፡ ከሳሽ ፡ ለመሆን ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ መከላከያ ፡ አድርጎ ፡ ለማንሣት ፡ አይችልም ።

## አንቀጽ ፡ ፪ ።
## የአየር ፡ ጕዞ ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።
### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌ ።

ቍ ፡ ፮፻፬ ። ተፈጻሚ ፡ የሚሆንበት ፡ ወሰን ።

የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውሳኔ ፡ ዋጋ ፡ በመክፈል ፡ ወይም ፡ በነጻ ፡ በአይሮፕላን ፡ ለሚ

ጓዙ ፡ ሰዎች ፤ ጓዝና ፡ ዕቃዎች ፤ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፮፻፰ ። የአይሮፕላን ፡ ትርጓሜ ።**

በአየር ፡ ላይ ፡ የሚንሳፈፍ ፡ ወይም ፡ የሚበር ፡ ማናቸውም ፡ መኪና ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፬ ፡ መሠረት ፡ አይሮፕላን ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ማጓጓዣ ፡ ሰነዶች ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### የመንገደኛ ፡ ቲኬት ።

**ቍ ፡ ፮፻፱ ። ስለ ፡ ቲኬት ፡ አሰጣጥ ።**

(፩) በአየር ፡ ለሚጓዝ ፡ ለማናቸውም ፡ ሰው ፡ ቲኬት ፡ ይሰጠዋል ።

(፪) ቲኬቱ ፡ የሚያመለክተው ፤

(ሀ) የተሰጠበትን ፡ ስፍራና ፡ ቀን ፤

(ለ) የአጓዡን ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፤

(ሐ) መንገደኛው ፡ ከየት ፡ እስከየት ፡ ድረስ ፡ እንደሚጓዝና ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አጓዡ ፡ እግረ ፡ መንገዱን ፡ የሚደርስበት ፡ ቦታዎች ፤

(መ) የማጓጓዣው ፡ ዋጋ ፤

(፫) ለመንገደኛው ፡ የሚሰጠው ፡ ቲኬት ፡ ስለ ፡ ሞት ፡ አደጋ ፤ ስለ ፡ አካል ፡ ጉዳትና ፡ ስለ ፡ ጠፋ ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ ስለ ፡ ደረሰበት ፡ ጓዝ ፤ አጓዡ ፡ ኀላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጽ ፡ የቲኬት ፡ ማስታወቂያ ፡ ሊኖርበት ፡ ይገባል ።

**ቍ ፡ ፮፻፲ ። የቲኬት ፡ አገልግሎትና ፡ ምክንያት ።**

(፩) ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ ቲኬቱ ፡ ስለ ፡ ጉዞው ፡ ውል ፡ መደረግና ፡ ስለ ፡ ሁኔታውም ፡ አስረጅ ፡ ይሆናል ።

(፪) የቲኬት ፡ አለመኖር ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ቲኬት ፡ አለመሆን ፡ ወይም ፡ የቲኬቱ ፡ መጥፋት ፡ የማጓጓዣ ፡ ውል ፡ መኖሩንና ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ውል ፡ መሆኑንና ፡ ተፈጻሚነቱን ፡ የሚያስቀር ፡ አይሆንም ። አጓዡም ፡ መንገደኛው ፡ ቲኬት ፡ ሳይሰጠው ፡ እንዲሳፈር ፡ የፈቀደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ በቲኬቱ ፡ ላይ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፱ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተመለከተው ፡ ማስታወቂያ ፡ ያልተጻፈበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የአጓዡን ፡ ኀላፊነት ፡ የተወሰነ ፡ ለማድረግ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፴፩ ፥ ፮፻፴፪ ፡ እና ፡ ፮፻፴፫ ፡ የተመለከተው ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## የንዝ ፡ ቲኬት ።

**ቍ ፡ ፮፻፰ ። የንዝ ፡ ቲኬት ፡ ስለ ፡ መስጠት ።**

(፩) የንዝ ፡ ቲኬት ፡ የሚሰጠው ፡ የተመዘገበው ፡ ጓዝ ፡ በአየር ፡ የሚጓዝ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) የንዝ ፡ ቲኬት ፡ የሚያመለክተው ፤

(ሀ) የተሰጠበትን ፡ ስፍራና ፡ ቀን ፤

(ለ) የአንዡን ፡ ወይም ፡ የአንዦችን ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፤

(ሐ) የመንገደኛውን ፡ ቲኬት ፡ ቍጥር ፤

(መ) ጓዙ ፡ ከየት ፡ እስከየት ፡ ቦታ ፡ እንደሚጓዝ ፤

(ሠ) የጥቅሉ ፡ ብዛትና ፡ ክብደት ፤

(፫) የንዙ ፡ ቲኬት ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፮ ፡ ከተመለከተው ፡ ከመንገደኛው ፡ ቲኬት ፡ ጋራ ፡ ያልተያያዘና ፡ ወይም ፡ ያልተጨመረ ፡ ሲሆን ፡ ጓዙ ፡ የጠፋ ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የአንዡ ፡ ኀላፊነት ፡ የተወሰነ ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ጓዙ ፡ የተሰጠው ፡ ቲኬት ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፮፻፱ ። የንዝ ፡ ቲኬት ፡ አገልግሎትና ፡ ምክንያት ።**

(፩) ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ የንዙ ፡ ቲኬት ፡ ጓዙ ፡ ለመመዝገቡና ፡ ለማንጓዣውም ፡ ውል ፡ ሁኔታ ፡ አስረጅ ፡ ይሆናል ።

(፪) የንዝ ፡ ቲኬት ፡ አለመኖር ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ቲኬት ፡ አለመሆን ፡ ወይም፡ የቲኬቱ፡ መጥፋት፡ የማንጓዙ፡ ውል፡ መኖሩንና፡ በዚሁ፡ አንቀጽ፡ ውሳኔ፡ መሠረት፡ ዋጋ፡ ያለው፡ ውል፡ መሆኑንና፡ ተፈጻሚነቱን፡ የሚያስቀር፡ አይሆንም። አንዡ ፡ ጓዙን ፡ የተቀበለው ፡ ያለማንጓዣ፡ቲኬት፡ ወይም ፡ የማንጓዣው፡ ቲኬት ፡ ከመንገደኛው፡ ቲኬት፡ ያልተያዘና ፡ ወይም ፡ ያልተጨመረ ፡ ወይም ፡ በቲኬቱ ፡ ላይ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፰ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተመለከተው ፡ ማስታወቂያ ፡ ያልተደረገበት ፡ እንደ ፡ ሆነ፤ ስለ፡ አንዡ ፡ የተወሰነ ፡ ኀላፊነት ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፴፯ ፡ የተመለከተውን ፡ ሊከራከርበት ፡ አይችልም ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## የአየር ፡ ማንጓዣ ፡ ሰነድ ።

**ቍ ፡ ፮፻፲ ። የማንጓዣ ፡ ሰነድ ፡ ስለ ፡ መስጠት ።**

ዕቃ ፡ የሚያንጓጕዝ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ላኪው ፡ በአየር ፡ የማንጓዣ ፡ ሰነድ ፡ የተ ባለውን ፡ አዘጋጅቶ ፡ እንዲሰጠው ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ። ማናቸውም ፡

ላኪ ፡ ይህን ፡ ጽሑፍ ፡ አጓጓዡ ፡ እንዲቀበለው ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፲፩ ። የማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ አለመኖር ፤ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ መሆን ፡ ወይም ፡ መጥፋት ።**

የማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ አለመኖር ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ መሆን ፡ ወይም ፡ መጥፋት ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የተመለከተውን ፡ ውሳኔ ፡ መጽናትና ፡ ዕቃዎቹን ፡ ስለማጓጓዝ ፡ የተደረገውን ፡ ውል ፡ ተፈጻሚ ፡ ከመሆን ፡ ሊያስቀር ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፲፪ ። የማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ ግልባጮች ።**

(፩) የማጓጓዣውን ፡ ሰነድ ፡ በሦስት ፡ ግልባጭ ፡ ላኪው ፡ አዘጋጅቶ ፡ ለአጓዡ ፡ ከዕቃው ፡ ጋራ ፡ ይሰጠዋል ።

(፪) የመጀመሪያውን ፡ ግልባጭ ፡ "ለአጓዡ ፡" የሚል ፡ ስያሜ ፡ ተሰጥቶት ፡ ላኪው ፡ ይፈርምበታል ።

(፫) ሁለተኛውን ፡ ግልባጭ ፡ "ለተቀባይ ፡" የሚል ፡ ስያሜ ፡ ተሰጥቶት ፤ ላኪውና ፡ አጓዡ ፡ ፈርመውበት ፡ ከዕቃው ፡ ጋራ ፡ ይሆናል ።

(፬) ሦስተኛውን ፡ ግልባጭ ፡ አጓዡ ፡ ፈርሞበት ፡ ዕቃውን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ለላኪው ፡ ይሰጠዋል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፲፫ ። ፊርማዎች ።**

(፩) አጓዡ ፡ ዕቃውን ፡ ከመጫኑ ፡ በፊት ፡ በማጓጓዣው ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ ይፈርማል ።

(፪) የአጓዡ ፡ ፊርማ ፡ በማኅተም ፡ ሊተካ ፡ ይችላል ፤ የላኪውም ፡ ፊርማ ፡ በማኅተም ፡ ተቀርጾ ፡ ሊታተም ፡ ወይም ፡ በማኅተም ፡ ሊተካ ፡ ይችላል።

(፫) ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ አጓዡ ፡ በላከው ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፤ የማጓጓዣውን ፡ ሰነድ ፡ ያዘጋጀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ስለ ፡ ላኪው ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ሠራ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፲፬ ። ከአንድ ፡ ጥቅል ፡ በላይ ፡ ሲሆን ።**

የሚጓዘው ፡ ዕቃ ፡ ከአንድ ፡ ጥቅል ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አጓዡ ፡ ላኪውን ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ጥቅል ፡ የተለየ ፡ የማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፪፻፲፭ ። በማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ የሚመለከት ፡ ዝርዝር ።**

(፩) የማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ዝርዝሮች ፡ ሊኖሩበት ፡ ይገባል ።
- (ሀ) የተሰጠበትን ፡ ስፍራና ፡ ቀን ፤
- (ለ) ዕቃው ፡ ከየት ፡ እስከ ፡ የት ፡ እንደሚጓጓዝ ፤
- (ሐ) የላኪ ፤ የተቀባይና ፡ የመጀመሪያ ፡ አጓዥ ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፤
- (መ) የዕቃው ፡ ዐይነት ፤ የጥቅሉ ፡ ብዛት ፤ መጠኑና ፡ ክብደቱ ፤
- (ሠ) በጥቅሉ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፤ ቍጥሩ ፤

(ረ) የዕቃዎቹ ፡ ሁኔታ ፤ እንዲሁም ፡ እንዳለ ፡ የጥቅሉ ፡ ዐይነትና ፡ ሁኔታ ፤

(ሰ) የማጓጓዣው ፡ ዋጋ ፤

(ሸ) ዕቃው ፡ የሚደርስበት ፡ ጊዜና ፡ የሚሄድበት ፡ መሥመር ፤

(፪) ዕቃው ፡ በጠፋና ፡ ጉዳት ፡ በደረሰበት ፡ ጊዜ ፡ የአጓዡ ፡ ኀላፊነት ፡ የተወሰነ ፡ መሆኑን ፡ ለላኪው ፡ የሚገልጽ ፡ ማስታወቂያ ፡ በማጓጓዣው ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ ሊኖር በት ፡ ያስፈልጋል ።

ቍ ፡ ፮፻፲፮ ። ለታዘዘለት ፡ የሚል ፡ የዕቃ ፡ ማጓጓዣ ፡ ሰነድ ።

ላኪውና ፡ አጓዡ ፡ ከተስማሙ ፡ የማጓጓዣው ፡ ሰነድ ፡ ለታዘዘለት ፡ የሚል ፡ ሆኖ ፡ ሊዘጋጅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፮፻፲፯ ። የማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ ያልተሰጠ ፡ ወይም ፡ ያልተሟላ ፡ እንደ ፡ ሆነ ።

አጓዡ ፡ ዕቃዎቹን ፡ ያለማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፲፭ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ የተመለከተው ፡ ማስታወቂያ ፡ ሳይደረግበት ፡ በአይሮፕላን ፡ የጫነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ አጓዡ ፡ የተወሰነ ፡ አላፊነት ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፴፯ ፡ የተገለጸው ፡ ተፈ ጻሚ ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፮፻፲፰ ። የላኪ ፡ ኀላፊነት ።

(፩) ላኪው ፡ በማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ የጻፈው ፡ ቃል ፡ ትክክለኛ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለመሆኑ ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

(፪) በማጓጓዣው ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ በተጻፉት ፡ ሥርዐትን ፡ ያልተከተሉ ፡ ወይም ፡ እውነ ተኛ ፡ ያልሆኑ ፡ ወይም ፡ ያልተሟሉ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ምክንያት ፡ በአ ጓዡ ፡ ወይም ፡ አጓዡ ፡ ኀላፊ ፡ በሆነበት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ላኪው ፡ በኀላፊነት ፡ ይጠየቃል ።

ቍ ፡ ፮፻፲፱ ። የማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ የሚሰጠው ፡ ውጤት ።

(፩) ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ የማጓጓዣው ፡ ሰነድ ፡ ውሉ ፡ የተፈ ጸመ ፡ ለመሆኑ ፤ አጓዡ ፡ ዕቃውን ፡ ለመቀበሉና ፡ ስለ ፡ ጕዞው ፡ ሁኔታ ፡ ማስረጃ ፡ ይሆናል ።

(፪) ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ዕቃው ፡ ክብደት ፤ ወርድና ፡ ቁመት ፤ ስለ ፡ ዕቃው ፡ አጠቃለልና ፡ እንዲሁም ፡ ስለ ፡ ጥቅሎቹ ፡ ብዛት ፡ በአየር ፡ ማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ የተጻፈው ፡ መግለጫ ፡ ትክክለኛ ፡ ለመሆኑ ፡ ማስረጃ ፡ ይሆናል ።

(፫) ስለ ፡ ዕቃው ፡ ብዛት ፡ ወይም ፡ መጠን ፡ ወይም ፡ ሁኔታ ፡ ከአጓጓዡ ፡ ጋራ ፡ መከራከር ፡ የሚቻለው ፡ የማጓጓዣው ፡ ሰነድ ፡ ትክክለኛ ፡ መሆኑ ፡

ላኪው ፡ ባለበት ፡ አጓዡ ፡ ካጣራውና ፡ መጣራቱ ፡ በማጓጓዣው ፡ ውለታ ፡ ላይ ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ዕቃው ፡ የሰፈረ ፡ ሐተታ ፡ ትክክል ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## የላኪና ፡ የተቀባይ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ።

### ቍ ፡ ፭፻፹ ። ላኪው ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የማዘዝ ፡ መብት ።

(፩) በማጓጓዣው ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ያሉበትን ፡ ግዴታዎች ፡ ከፈጸመ ፤ ላኪው ፡ ዕቃው ፡ ከሚነሣበት ፡ ወይም ፡ ከሚደርስበት ፡ ኤሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ መልሶ ፡ ዕቃውን ፡ በመውሰድ ፡ ወይም ፡ ኤሮፕላን ፡ እግረ ፡ መንገዱን ፡ በሚያርፍበት ፡ ቦታ ፡ ዕቃዎቹን ፡ እተወሰነበት ፡ ቦታ ፡ ሳይደርሱ ፡ በማቆም ፡ ወይም ፡ በመጓጓዣው ፡ ውል ፡ ላይ ፡ ተቀባይ ፡ ተብሎ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ሰው ፡ ይልቅ ፡ አሳልፎ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ በጕዞው ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ጕዞው ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ እንዲሰጡ ፡ በማድረግ ፡ ወይም ፡ ኤሮፕላኑ ፡ ወደ ፡ ተነሣበት ፡ ስፍራ ፡ እንዲመለሱ ፡ በማድረግ ፡ በዕቃዎቹ ፡ ላይ ፡ ሊያዝባቸው ፡ ይችላል ።

(፪) በአጓዡ ፡ ወይም ፡ በሌሎቹ ፡ ላኪዎች ፡ ላይ ፡ አንዳች ፡ ጉዳት ፡ ያልደረሰባቸው ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ አጓዡ ፡ በኡንስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ለመፈጸም ፡ መብት ፡ አለው ። ይህንኑ ፡ መብቱን ፡ በሚፈጽምበት ፡ ጊዜ ፡ የሚደርሰውን ፡ ወጪ ፡ ሁሉ ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

(፫) ላኪው ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመፈጸም ፡ የማይቻል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አጓዡ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለላኪው ፡ ሊያስታውቀው ፡ ይገባል ።

### ቍ ፡ ፭፻፹፩ ። የማጓዣ ፡ ሰነድ ፡ ስላለማቅረብ ።

(፩) አጓዡ ፡ የማጓዣውን ፡ ሰነድ ፡ ከላኪው ፡ ሳይቀበል ፡ የላኪውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመፈጸም ፡ ዕቃውን ፡ ያስረከበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የማጓዣውን ፡ ሰነድ ፡ በሚገባ ፡ በያዘ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ ካሣ ፡ የከፈለ ፡ አጓዥ ፡ የከፈለውን ፡ ካሣ ፡ ላኪው ፡ እንዲተካለት ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

### ቍ ፡ ፭፻፹፪ ። ላኪው ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የማዘዝ ፡ መብት ፡ ስለሚቀርበት ።

የተቀባዩ ፡ መብት ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፹፫ ፡ መሠረት ፡ በሚጀምርበት ፡ ጊዜ ፡ ላኪው ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የማዘዝ ፡ መብቱ ፡ ይቀራል ። ስለሆነም ፡ ተቀባዩ ፡ ዕቃውን ፡ ወይም ፡ የማጓዣውን ፡ ሰነድ ፡ አልቀበልም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ያልተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ላኪው ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፹ ፡ የተሰጠው ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ የማዘዝ ፡ መብቱ ፡ ይመለስለታል ።

## ቍ ፡ ፲፯፻፹፫ ። የተቀባይ ፡ መብት ።

(፩) ላኪው ፡ በቍጥር ፡ ፲፯፻፹ ፡ እንደ ፡ ተነገረው ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ያዘዘበት ፡ ካል ሆነ ፡ በቀር ፡ ተቀባዩ ፡ ዕቃው ፡ እመድረሻው ፡ ቦታው ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ አጓዡ ፡ ዕቃውንና ፡ የማጓጓዣውን ፡ ሰነድ ፡ ግልባጭ ፡ እንዲሰጠው ፡ ጥያቄ ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ።

(፪) ስለሆነም ፡ ተቀባዩ ፡ በማጓጓዣ ፡ ሰነድ ፡ የተነገሩትን ፡ ግዴታዎች ፡ ካልፈጸመና ፡ ሊከፍል ፡ የሚገባውን ፡ ካልከፈለ ፡ በቀር ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ እንደ ተነገረው ፡ ተፈጻሚ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

## ቍ ፡ ፲፯፻፹፬ ። ለተቀባይ ፡ ማሳሰቢያ ፡ ስለ ፡ መላክ ።

ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ አጓዡ ፡ የዕቃውን ፡ መድረስ ፡ የሚገልጽ ፡ ማሳሰቢያ ፡ ለተቀባዩ ፡ ይልክለታል ።

## ቍ ፡ ፲፯፻፹፭ ። የዕቃው ፡ መጥፋት ።

አጓዡ ፡ ዕቃው ፡ መጥፋቱን ፡ ካመነ ፡ ወይም ፡ ዕቃው ፡ ሊደርስ ፡ ከሚገባበት ፡ ቀን ፡ ተላልፎ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ የቈየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተቀባዩ ፡ በማጓጓዣው ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ የሚገባውን ፡ ከአጓዡ ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፲፯፻፹፮ ። ለሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ጥቅም ፡ የሚሠራበት ፡ መብት ።

በማጓጓዣው ፡ ውል ፡ የገቡትን ፡ ግዴታዎች ፡ ከፈጸሙ ፡ ላኪና ፡ ተቀባዩ ፡ ራሳቸው ፡ ለራሳቸው ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ጥቅም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች ፡ በተሰጣቸው ፡ መብቶች ፡ ለመጠቀም ፡ ይችላሉ ።

## ቍ ፡ ፲፯፻፹፯ ። ስለ ፡ ላኪና ፡ ተቀባይ ፡ ግንኙነት ።

በቍጥር ፡ ፲፯፻፹ ፡ እስከ ፡ ፲፯፻፹፮ ፡ የተመለከተው ፡ በላኪውና ፡ በተቀባዩ ፡ ወይም ፡ ከላኪውና ፡ ከተቀባዩ ፡ ጋራ ፡ አግባብ ፡ ያላቸውን ፡ የሦስተኛ ፡ ወገኖችን፡ መብት ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ሊነካው ፡ አይችልም ።

## ቍ ፡ ፲፯፻፹፰ ። ከቍጥር ፡ ፲፯፻፹ ፡ እስከ ፡ ፲፯፻፹፮ ፡ የተመለከተው ፡ በአንዳንድ ፡ ጉዳዮች፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስላለመሆኑ ።

ከቍጥር ፡ ፲፯፻፹ ፡ እስከ ፡ ፲፯፻፹፮ ፡ ካለው ፡ ውሳኔ ፡ የተለየ ፡ የሆነ ፡ የውል ፡ ቃል፡ በመጓጓዣው ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ ካልተጻፈ፡ በቀር፡ ዋጋ ፡ያለው፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

## ቍ ፡ ፲፯፻፹፱ ። ላኪው ፡ ሊሰጥ ፡ ስለሚገባው ፡ መግለጫ ።

(፩) ላኪው ፡ ጉምሩክ ፡ ቀረጥ ፡ አከፋፈል ፡ ስለ ፡ መቈጣጠር ፡ ውሳኔ ፡ የሚያገለግለውን ፡ አስረጅ ፡ ሁሉ ፡ ከማጓጓዣው ፡ ሰነድ ፡ ጋራ ፡ በማያያዝ ፡ ዕቃው ፡ ለተቀባዩ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ መስጠት ፡ ግዴታ ፡ ነው ።

(፪) ላኪው ፡ የተባሉትን ፡ አስረጂዎች ፡ ወይም ፡ መግለጫዎች ፡ ባለመግለጹ ፡ ወይም ፡ አስረጂውን ፡ ባለመስጠቱ ፡ ወይም ፡ ያልተሟላና ፡ ያልተስተካከለ ፡ ነገር፡ በመግለጹና ፡ ወይም ፡ አስረጂውን ፡ ባለመስጠቱ ፡ ምክንያት ፡ በአጓዡ ፡ ላይ ፡ ለሚደርስበት ፡ ለማናቸውም ፡ ጉዳት ፡ ተጠያቂ ፡ ይሆናል ።

(፫) ጥፋቱ ፡ የአጓዡ ፡ ወይም ፡ የእሱ ፡ ወኪል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ አይፈጸምም ።

(፬) አጓዡ፡ የተሰጠው ፡ መግለጫ ፡ ወይም ፡ አስረጅ ፡ ትክክለኛ ፡ ወይም ፡ በቂ፡ ለመሆኑ ፡ እንዲመረመር ፡ አይገደድም ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## የአጓዥ ፡ ኀላፊነት ።

**ቍ ፡ ፯፻፴ ። በሰው ፡ ላይ ፡ ስለሚደርስ ፡ ጉዳት ።**

መንገደኛው ፡ በኤሮፕላን ፡ ጕዞው ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ወይም ፡ ለመጓዝ ፡ ሲሳፈር ፡ ወይም ፡ ሲወርድ ፡ የሞት ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ ቢደርስበት ፡ አጓዡ ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፯፻፴፩ ። የጓዝ ፡ ወይም ፡ የዕቃ ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መበላሸት ።**

የተመዘገቡ፡ ጓዞች፡ ወይም ፡ ዕቃዎች ፡ በአየር ፡ ጕዞ፡ጊዜ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ ቢጠፉ ፡ ወይም ፡ ቢበላሹ ፡ አጓዡ ፡ በኀላፊነት ፡ ይጠየቅበታል ።

**ቍ ፡ ፯፻፴፪ ። በአየር ፡ ስለ፡ ማጓዝ ።**

(፩) በቍጥር፡ ፯፻፴፩፡ በተመለከተው፡ አነጋገር ፡ በአየር፡ ማጓዝ ፡ የተባለው ፡ ቃል፡ አጓዡ ፡ ሸቀጡን ፡ ወይም ፡ ጓዙን ፡ ተረክቦ ፡ በአኤሮፕላን ፡ ጣቢያ ፡ ወይም ፡ በአኤሮፕላን ፡ ውስጥ ፡ የነበረበትን ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ኤሮፕላኑ ፡ ከአኤሮፕላን ፡ ጣቢያ ፡ ውጭ ፡ የሚያርፍበትን ፡ ማናቸውንም ፡ ጊዜ ፡ ይጨምራል ።

(፪) በአየር ፡ ማጓዝ ፡ የተባለው ፡ አኤሮፕላን ፡ ጣቢያ ፡ ውጭ ፡ በመሬት ፤ በወንዝ ፤ በባሕር ፡ የሚያረገውን ፡ ማጓዝ ፡ የሚጠቀልል ፡ ባይሆንም ፤ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ በአየር ፡ የማጓዙን ፡ ውል ፡ ዕቃውን ፡ ወደ ፡ ኤሮፕላኑ ፡ ለማድረስ ፤ ለማስረከብ ፡ ወይም ፡ ለመጫን ፡ ዕቃው ፡ በመሬት ፤ በወንዝ ፤ በባሕር ፡ በሚጓዝበት ፡ ጊዜ ፡ በጓዙ ፡ ወይም ፡ በሸቀጡ ፡ ላይ ፡ የሚደርስ ፡ ጉዳት፡ ወይም ፡ መጥፋት ፡ ሸቀጡ ፡ ወይም ፡ ጓዙ ፡ በአየር ፡ በሚጓዝበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፯፻፴፫ ። ስለ ፡ መዘግየት ።**

በአየር ፡ መጓዝ ፡ በሚያረግበት ፡ ጊዜ ፡ በመንገደኞች ፤ በጓዞች ፡ ወይም ፡ በዕቃዎች፡ ዘግይቶ፡በመድረስ፡ ምክንያት ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ አጓዡ፡ኣላፊ ፡ነው ።

BACK



**ቊ ፡ ፲፻፴፩ ። እንገኛ ፡ በጥንቃቄ ፡ የሠራ ፡ ስለመሆኑ ፡ ስለሚያቀርበው ፡ ማስረጃ ።**

እንገኛና ፡ ወኪሉ ፡ ጉዳት ፡ እንዳይደርስ ፡ አስፈላጊውን ፡ ጥንቃቄ ፡ ያደረገ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ ለማድረግ ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አላፊነት ፡ የለበትም ።

**ቊ ፡ ፲፻፴፪ ። ስለ ፡ ተጎዳው ፡ ሰው ፡ ጥፋት ።**

ጉዳት ፡ የደረሰው ፡ ሰው ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ የጥፋት ፡ ተካፋይነት ፡ መሆኑን ፡ እንገኛ ፡ ያስረዳ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የእንገኛን ፡ ኀላፊነት ፡ ሊያስቀርለት ፡ ወይም ፡ ሊያቀልለት ፡ ይችላል ።

**ቊ ፡ ፲፻፴፫ ። ስለ ፡ መንገደኛ ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፤ የኀላፊነት ፡ ወሰን ።**

(፩) እንገኛ፡ ለያንዳንዱ፡ መንገደኛ፡ የሚከፈለው፡ የካሣ፡ መጠን ፡ ከ፵ሺ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ አይበልጥም ፤ ካሣው ፡ በጡረታ ፡ ሀይነት ፡ በየጊዜው ፡ የሚከፈል ፡ ሲሆን ፡ የጡረታው ፡ አበል ፡ የሚገኝበት ፡ ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ ከ፵ሺ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ሊበልጥ ፡ አይገባም ።

(፪) ስለሆነም ፡ መንገደኛው ፡ ከእንገኛ ፡ ጋራ ፡ ባደረገው ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ የኀላፊነት ፡ መጠን ፡ በንኡስ ፡ ቊጥር ፡ ፩ ፡ ከተወሰነው ፡ በላይ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

**ቊ ፡ ፲፻፴፬ ። ስለ ፡ ጓዝ ፤ ስለ ፡ ዕቃና ፡ ሽቀጦች ፡ የኀላፊነት ፡ ወሰን ።**

(፩) እንገኛ ፡ ለተጓገኛ ፡ ዕቃዎችና ፡ ለተመዘገቡ ፡ ጓዞች ፡ የሚከፈለው ፡ የካሣ ፡ መጠን ፡ በእንዳንዱ ፡ ኪሎ ፡ ከ፵ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ አይበልጥም ።

(፪) ላኪው፡ ዕቃውን ፡ ለእንገኛ ፡ በሚያስረክብበት ፡ ጊዜ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ ባለው፡ ልዩ ፡ ጥቅም ፡ ምክንያት ፡ ተገቢውን ፡ ተጨማሪ ፡ ዋጋ ፡ ከፍሎ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ካሣ ፡ ለመጠየቅ ፡ የተዋዋለ ፡ ከሆነ ፡ በንኡስ ፡ ቊጥር ፡ ፩ ፡ የተመለከተው ፡ ውሳኔ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

(፫) በንኡስ፡ ቊጥር ፡ ፪ ፡ መሠረት ፡ ለተላከው ፡ ዕቃ ፡ እንገኛ ፡ የተስማማውን፡ ካሣ ፡ መክፈል ፡ አለበት ፤ ሆኖም ፡ የተጓዘው ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ ከጠየቀው ፡ ካሣ ፡ በታች ፡ መሆኑን ፡ እንገኛ ፡ ካስረዳ ፡ በመጠኑ ፡ ኀላፊነቱ ፡ ይቀነስለታል ።

(፬) በተመዘገበው ፡ ጓዝ ፤ ዕቃ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ብሆን ፡ ዕቃ ፡ ላይ፡ የሚደርሰው ፡ መጥፋት ፤ መበላሸት ፡ ወይም ፡ መዘግየት ፡ በከፊል ፡ የሆን ፡ እንደሆን ፤ የእንገኛ ፡ ኀላፊነት፡ የሚቈጠረው ፡ የነዚሁኑ ፡ ጓዞች፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ በውስጣቸው ፡ ያሉ ፡ ዕቃዎች ፡ ጠቅላላ ፡ ክብደት ፡ በማሰብ ፡ ነው ።

(፭) በንኡስ፡ ቊጥር ፡ ፬ ፡ የተጠቀሰው ፡ መጥፋት ፤ ጉዳት ፡ ወይም ፡ መዘግየት ፡ በዚያው ፡ በአንዱ ፡ የማጓዣ ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ በጓዝ ፡ ደረሰኝ ፡ መሠረት ፡ የተላኩትን ፡ ሌሎች ፡ ዕቃዎች ፡ የሚነካ ፡ ሲሆን ፡ የእንገኛ ፡ ኀላፊነት ፡ የሚወ

ስነው ፡ የተባለውን ፡ ዕቃ ፡ ጠቅላላ ፡ ክብደት ፡ በማሰብ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፻፹፰ ። በመንገደኛው ፡ ጠባቂነት ፡ ውስጥ ፡ ስላሉ ፡ ዕቃዎች ።

በመንገደኛው ፡ ጠባቂነት ፡ ውስጥ ፡ ስላሉ ፡ ዕቃዎች ፡ አጓዡ ፡ ለያንዳንዱ ፡ መንገደኛ ፡ ከ፭፻ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ ለመክፈል ፡ ኀላፊነት ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፲፻፹፱ ። መጠኑን ፡ ከፍ ፡ ስለሚያደርጉ ፡ ምክንያቶች ።

(፩) ከዚህ፡ በላይ፡ ባሉት ፡ ከ፲፻፹፮ ፡ እስከ ፡ ፲፻፹፰ ፡ በተመለከቱት፡ ቍጥሮች ፡ የተወሰነው ፡ የኀላፊነት ፡ መጠን ፡ ከሳሽ ፡ ለክሱ ፡ ያወጣውን ፡ ወጪ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ለከሳሽ ፡ ለማስከፈል ፡ ሊያግደው ፡ አይችልም ።

(፪) ለከሳሽ ፡ የሚከፈለውን ፡ ካሣ ፡ መጠን ፡ አጓጓዥ ፡ ሳይከሰስ ፡ በዕቃው ፡ ላይ፡ ጉዳት፡ በደረሰበት፡ በስድስት፡ ወር፡ ውስጥ፡ ለመክፈል፡ ዝግጁ ፡ መሆኑን ፡ በጽሑፍ ፡ ካስታወቀና ፡ ከሳሽ ፡ ከሆነውም ፡ ክሱን ፡ ያቀረበው ፡ ጉዳቱ ፡ ከሆነ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሳሹ ፡ ለክሱ ፡ ካወጣው ፡ ወጪ፡ በቀር፡ ስለ ፡ ጉዳት፡ ካሣ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተነገረው ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፲፻፺ ። ኀላፊነትን ፡ ስለሚያስቀር ፡ የውል ፡ ቃል ።

ከዚህ፡ በላይ፡ ባሉት ፡ ቍጥሮች፡ ውስጥ ፡ ካሉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ውጭ ፡ አጓዡን ፡ ከኀላፊነት ፡ ነጻ ፡ የሚያደርገው ፡ ወይም ፡ ከተወሰነው ፡ የአከፋፈል ፡ መጠን ፡ በታች ፡ መደቡን ፡ ዝቅ ፡ የሚያደርግ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ፍርስ ፡ ነው ። የውል ፡ ቃል ፡ ሳይፈርስ ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውሳኔዎችም፡ ተፈጻሚዎች፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፲፻፺፩ ። በዕቃዎቹ ፡ ላይ ፡ ስላለ ፡ ጕድለት ።

ከዚሀ ፡ በላይ ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፺ ፡ የተደነገገው ፡ ውሳኔ ፡ ቢኖርም ፡ በሚጓዙት ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ ባለ ፡ ጕድለት ፡ ምክንያት ፡ ስለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ ጥፋት ፡ አጓዡ፡ ኀላፊ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፲፻፺፪ ። ሕጋዊ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

(፩) ከቍጥር ፡ ፲፻፹፩ ፡ እስከ ፡ ፲፻፹፯ ፡ በተጠቀሰው ፡ መሠረት ፡ ስለ፡ ካሣ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ በዚሀ ፡ አንቀጽ ፡ ሁኔታና ፡ ልክ ፡ መሠረት ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) ክስ፡ ለማቅረብና ፡ እንደየመብታቸው ፡ የሚጠይቁ፡ ሰዎች፡ መብት ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ በንኡስ ፡ ቍ፡ ፩፡ የተመለከቱት፡ ውሳኔዎች ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፹፡ መሠረት ፡ ስለሚቀርበውም ፡ ክስ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፲፻፶፫ ። ስለ ፡ አንዳንድ ፡ ጕዳዮች ፡ ኀላፊነት ፡ ያልተወሰነ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) ጕዳቱ፡ የደረሰው ፡ እንግዳ ፡ ወይም ፡ ወኪሉ ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣ ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ ባደረገው ፡ አድራጎት ፡ ወይም ፡ ማድረግ ፡ የሚገባውን ፡ ባለማድረጉ ፡ ለመሆኑ፡ ማስረጃ፡ የቀረበ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ በቍጥር፡ ፲፻፴፮ ፡ ፲፻፴፯ ፡ ፲፻፴፰ ፡ የተወሰነው ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

(፪) ጥፋቱ፡ ወይም፡ ጉዳቱ ፡ የወኪሉ ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ሆነ ፤ ወኪሉ ፡ በሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ የሠራው ፡ ለመሆኑ ፡ ሊረጋገጥ ፡ ይገባል ።

**ቍ ፡ ፲፻፶፬ ። በእንግዳ ፡ ወኪል ፡ ላይ ፡ ስለሚቀርብ ፡ ክስ ።**

(፩) በዚህ ፡ አንቀጽ፡ መሠረት፡ ለካሣ ፡ በእንግዳ ፡ ወኪል ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ወኪሉ ፡ በሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ያደረገው ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንግዳ ፡ ለኀላፊነቱ ፡ ወሰን፡ ሊከራከር ፡ በሚችልበት ፡ በ፲፻፴፮ ፡ በ፲፻፴፯ ፡ እና ፡ በ፲፻፴፰ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ወኪሉም ፡ ሊከራከር ፡ ይችላል ።

(፪) ከእንግዳና፡ ከወኪሉ፡ የሚጠየቀው ፡ ጠቅላላ ፡ ካሣ ፡ ወሰን ፡ በቍ፡ ፲፻፴፮ ፡ ፲፻፴፯፡ እና ፡ ፲፻፴፰ ፡ ላይ ፡ ከተወሰነው ፡ ሊበልጥ ፡ አይገባም ።

(፫) ጉዳት፡ የደረሰው፡ ወኪሉ፡ ጕድለት ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣ ፡ መሆኑን ፡ እያወቀ ፡ በሠራው ፡ ወይም ፡ ሳይሠራ ፡ በተወው ፡ ወይም ፡ ባደረገው ፡ ጕድለት፡ መሆኑ፡ በማስረጃ፡ የተረጋገጠ፡ እንደ፡ ሆነ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ እና ፡ ፪፡ የተደነገገው ፡ ተፈጻሚ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፲፻፶፭ ። ስለ ፡ መቀበልና ፡ ስለ ፡ መቃወም ።**

(፩) ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር፡ ተቀባዩ ፡ ሳይከራከር፡ ጓዞቹን ፡ ወይም ፡ ዕቃዎቹን ፡ የተረከበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዕቃዎቹን ፡ በመልካም ፡ ሁኔታና ፡ በማጓዣው ፡ ሰነድ ፡ መሠረት ፡ እንደ፡ ተቀበለ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ጉዳት ፡ ለደረሰበት ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ ጓዝ፡ ተቀባዩ፡ ጉዳት ፡ መድረሱን ፡ እንዳወቀ ፡ ጓዞቹን፡ ከተረከበበት፡ ቀን ፡ ጀምሮ፡ ሰባት፡ ቀንና ፡ ዕቃዎችን ፡ ከተረከበበት፡ ቀን፡ ከዐሥራ፡ አራት፡ ቀን፡ በማይበልጥ፡ ጊዜ፡ ለእንግዳ ፡ አስፈላጊውን ፡ መቃወሚያ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፫) የመዘግየት፡ የሆነ ፡ እንደ፡ ሆነ፤ ጓዙን ፡ ወይም፡ ዕቃዎቹን ፡ ተቀባዩ ፡ ከተረከበበት፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ከሐያ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ባልበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መቃወሚያውን ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፬) በዚህ፡ ቍጥር፡ መሠረት ፡ ለሚቀርበው ፡ መቃወሚያ ፡ በማጓዣው ፡ ሰነድ ፡ ላይ፡ መብት፡ መጠበቂያ፡ ቃል፡ በመጻፍ፡ ወይም፡ ለመቃወሚያ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ በመላክ ፡ የሚቃወምበትን ፡ ነገር ፡ ማስታወቅ ፡ ይገባዋል ።

(፫) እንገዙ ፡ ያደረገው፡ የማታለል፡ ነገር ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መቃወሚያ ፡ ያልቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእንገዙ ፡ ላይ ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ተቀባይነት ፡ የለውም ።

ቍ ፡ ፮፻፵፮ ። ስለ ፡ ባለዕዳው ፡ መሞት ።

ባለዕዳው፡ የሞተ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ኀላፊነት ፡ የሚ ቀርበው ፡ ክስ ፡ ስለ ፡ እሱ ፡ መከሰስ ፡ በሚገባቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ይቀርባል ።

ቍ ፡ ፮፻፵፯ ። የዳኝነት ፡ ሥልጣን ።

(፩) በዚህ፡ አንቀጽ፡ መሠረት፡ ስለ፡ ኣላፊነት፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ከሳሹ ፡ እንደ፡ መረጠ ፡ እንገዙ ፡ በመደበኛ ፡ መኖሪያው ፡ ወይም ፡ ዋና ፡ ሥራው ፡ ባለ በት ፡ ወይም ፡ ውሉን ፡ የተዋዋለው ፡ ወኪል ፡ ባለበት ፡ ወይም ፡ ዕቃና ፡ ጓዙ ፡ በሚደርስበት ፡ ቦታ ፤ ላለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማቅረብ ፡ ይገባዋል ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ ከተመለከተው፡ ውሳኔ፡ ጋራ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ውል፡ ፍርስ ፡ ነው ።

(፫) ስለሆነም ፡ ስለ፡ ዕቃዎቹ፡ ማጓጓዣ ፡ የሚነሣውን ፡ ክርክር ፡ በሽማግሌ ፡ ዳኝ ነት ፡ ለመጨረስ፡ ውል ፡ ተደርጎ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ የሽምግልናው ፡ ዳኝነት ፡ የሚደ ረገው ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ በተጠቀሱት ፡ ስፍራዎች ፡ ከሆነ ፡ ውሉ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፮፻፵፰ ። ይርጋ ።

በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ካሣ ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ አይሮፕላኑ ፡ ከደረሰበት ፡ ወይም ፡ ሊደርስ ፡ ከሚገባበት፡ ወይም ፡ ጕዞው ፡ ከተቋ ረጠበት ፡ ቀን ፡ እንሥቶ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም።

ቍ ፡ ፮፻፵፱ ። ስለ ፡ ቀን ፡ አቈጣጠር ።

በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ቀን ፡ ሲባል ፡ የሥራና ፡ የበዓላቶችን ፡ ቀን ፡ ሳይለይ ፡ ማንኛውም ፡ ቀን ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፭ ።

## በአንዳንድ ፡ ዐይነት፡ መጓጓዣዎች፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑ፡ ድንጋጌዎች ።

ቍ ፡ ፮፻፶ ። የተለዩ ፡ ሁኔታዎች ።

ደንበኛ ፡ ከሆነው ፡ የአየር ፡ ሥራ ፡ ውል ፡ በልዩ ፡ አጋጣሚ ፡ ምክንያት ፡ ስለ ሚደረግ፡ የአየር ፡ ጕዞ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ከቍጥር ፡ ፮፻፮ ፡ እስከ ፡ ፮፻፲፮ ፡ ስለ ፡ ማጓ ጓዣ ፡ ሰነዶች ፡ የተደነገገው ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፮፻፶፩ ። ስለ ፡ ተቀባባይ ፡ አጓጕዦች ።

ተቀባባይ፡ የአየር፡ አጓጕዦች፡ የሚያደርጉትን፡ ጕዞ ፡ ተዋዋዮቹ ፡ በአንድም፡ ሆነ ፡ ከአንድ ፡ በበለጠ ፡ ውል ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ጕዞ ፡ አድርገው ፡ ከተመለከቱት ፡ ለዚህ ፡ አንቀጽ ፡ አፈጻጸም ፡ አንድ ፡ ጕዞ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፮፻፶፪ ። የተቀባባይ ፡ አጓጓዦች ፡ ኀላፊነት ።

(፩) ተቀባባይ፡ አጓዦች፡ ሰዎችን ፤ ጓዞችንና ፤ ዕቃዎችን ፤ በአየር ፡ የሚያጕዙ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውሳኔዎች ፡ በያንዳንዱ ፡ አጓዥ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ። እንዲሁም ፡ ውሉ ፡ አጓዡ ፡ በኀላፊነቱ ፡ ያደረገውን ፡ ጕዞ ፡ ክፍል ፡ የሚመለከት ፡ ከሆነ ፡ በጕዞው ፡ ውል ፡ ከገቡት ፡ አጓዦች ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) የመጀመሪያው፡ አጓዥ ፡ ለመላው ፡ ጕዞ ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ፡ የሚል ፡ በተለይ ፡ የተደረገ ፡ ስምምነት ፡ ካልኖረ ፡ በቀር፡ መንገደኛው ፡ ወይም ፡ የእሱ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ በንኡርስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ ስለ ፡ ተመለከተው ፡ ማጓጓዝ ፡ በኀላፊነት ፡ መጠየቅ፡ የሚችሉት፡ አደጋው፡ ወይም፡ መዘግየቱ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ለጕዞው ፡ ኀላፊ ፡ የነበረውን ፡ አጓዥ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፫) ስለ ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም፡ የተመዘገቡ ፡ ጓዞች ፡ ላኪው፡ ለመክሰስ ፡ የሚችለው፡ የመጀመሪያውን ፡ አጓጓዥ ፡ ሲሆን ፤ ተቀባዩ ፡ ሊከስ ፡ የሚገባው ፡ የመጨረሻውን ፡ አጓጓዥ ፡ ነው ፤ እንዲሁም ፡ ላኪውና ፡ ተቀባዩ ፡ በዕቃው ፡ ላይ ፡ በሙሉም፡ ሆነ ፡ በከፊል ፡ መበላሸት ፤ መጐዳት ፡ ወይም ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መዘግየት ፡ በደረሰበት ፡ ጊዜ ፡ ለጕዞው ፡ ኀላፊ ፡ የነበረውንም ፡ አጓጓዥ ፡ መክሰስ ፡ ይችላሉ ።

(፬) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሱት ፡ አጓጓዦች ፡ ለላኪውና ፡ ለተቀባዩ ፡ ድርሻ ፡ የማይከፋፈል ፡ የአንድነት ፡ ኀላፊነት ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፮፻፶፫ ፡ የተያያዘ ፡ መጓጓዝ ።

(፩) ገሚሱ ፡ ጕዞ ፡ በአየር ፡ ገሚሱ ፡ ጕዞ ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ማጓጓዣ ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውሳኔ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆነው ፡ ለአየሩ ፡ ጕዞ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) በዚህ፡ አንቀጽ፡ ውሳኔ፡ ውስጥ፡ስለ፡አየር፡ ጕዞ፡ የተወሰነውን፡ አክብረው፤ ተዋዋዮቹ ፡ ባየሩ ፡ ጕዞ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሌላው ፡ ዐይነት ፡ ማጓጓዣ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ሊያገቡበት ፡ ይችላሉ ።

## አንቀጽ ፡ ፫ ።
## ስለ ፡ ኢንሹራንስ ።
### ምዕራፍ ፡ ፩ ።
### ጠቅላላ ፡ ውሳኔዎች ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፬ ፡ ትርጓሜ ።**

(፩) የኢንሹራንስ፡ ውል፡ ፖሊሲ ፡ ማለት ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪ ፡ የሚባለው ፡ በአንድ ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ የተመደበውን ፡ የኢንሹራንስ ፡ መግቢያ ፡ ዋጋ፡ (ፕሬምዮም) ፡ ተቀብሎ ፡ በውሉ ፡ የተመለከተው ፡ አደጋ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ለገባው ፡ ሰው ፡ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ ግዴታ ፡ የሚገባበት ፡ ውል ፡ ነው ።

(፪) ኢንሹራንሱ፡ የተደረገው፡ ስለ፡ ጉዳት፡ የሆነ፡ እንደ፡ሆነ፤ የኢንሹራንስ፡ውል፡ ግዴታ ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ የሚደርሰውን ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ የሚደርስበትን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ኀላፊነትም ፡ ይጨምራል ።

(፫) ኢንሹራንሱ፡ ለሰው ፡ ሕይወት፡ የሆነ ፡ እንደ፡ሆነ ፤ የኢንሹራንሱ ፡ ግዴታ ፤ በሞት ፤ በሕይወት ፡ ወይም ፡ በአካል ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ በሕመም ፡ የሚደርሰውን ፡ አደጋ ፡ ይጨምራል ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፭ ። የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ወሰን ።**

(፩) የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውሳኔ ፡ ተፈጻሚ፡ የሚሆነው፡ በመሬት ፤ በወንዝና ፡ በአየር ፡ ለሚደርሱ ፡ አደጋዎች ፡ ነው ።

(፪) ይህ ፡ ውሳኔ ፡ በባሕር ፡ ሕግ ፡ የሚተዳደረውን ፡ የባሕርን ፡ ኢንሹራንስ ፡ ወይም ፡ የሶሺያልንና ፡ የክሬዲት ፡ ( መንግሥት ፡ የሚያቋቁመው ) ፡ ኢንሹራንስን ፡ አይመለከትም ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፮ ። ስለ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ማኅበሮች ።**

የኢንሹራንስ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የተፈቀደላቸው ፡ ማኅበሮችና ፡ ሰዎች ፡ ለመሥራት ፡ የሚችሉት ፡ የኢንሹራንስ ፡ ሥራ ፡ በሕግ ፡ ይወሰናል ።

### ምዕራፍ ፡ ፪ ።
### ልዩ ፡ ልዩ ፡ ለሆኑ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ማኅበሮች ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑ ፡ ድንጋጌዎች ።
#### ክፍል ፡ ፩ ።
#### የኢንሹራንስ ፡ ፖሊሲ ፡ ውል ።

**ቍ ፡ ፮፻፶፯ ። የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ማስረጃ ።**

(፩) የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ በኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ፖሊሲ ፡ በሚባል ፡ ጽሑፍ ፡ መደገፍ ፡ አለበት ።

(፪) የኢንሹራንስ፡ ፖሊሲ፡ ተጨማሪ፡ በሆነ ፡ ጽሑፍ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሊለወጥ ፡ አይቻልም ።

(፫) ስለሆነም፡ ፖሊሲው፡ ወይም ፡ የፖሊሲው ፡ ተጨማሪ ፡ ጽሑፍ ፡ ከመፈ ረሙ፡ በፊት ፡ ለጊዜው፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ኢንሹራንስ ፡ ለሚገባው ፡ ሰው፡ ፖሊሲው፡ ወይም፡ ለፖሊሲው ፡ ተጨማሪ ፡ ጽሑፍ ፡ እስከ፡ ተፈረመ ፡ ድረስ ፡ ማረጋገጫ ፡ መድን ፡ የሚሆነው ፡ ጽሑፍ ፡ የሰጠው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ኢንሹራ ንስ ፡ ሰጪውና፡ ኢሹራንስ ፡ ገቢው ፡ አንዱ ፡ ለአንዱ፡ ግዴታ ፡ እንደ፡ገቡ ፡ ይቈ ጠራል ።

## ቍ ፡ ፮፻፶፰ ። በኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ፖሊሲው ፡ ላይ ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ነገሮች ።

በኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ፖሊሲ ፡ ውስጥ ፡ ሊጻፍ ፡ የሚገባው ፤

(ሀ) የተዋዋሉበት ፡ ስፍራና ፡ ቀን ፤

(ለ) የተዋዋዮቹ ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፤

(ሐ) ኢንሹራንሱ፡ የተደረገለት ፡ ንብረት፤ አላፊነት ፤ ወይም ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባ ፡ ሰው ፤

(መ) ኢንሹራንሱ ፡ የተገባበት ፡ አደጋ ፡ ዐይነት ፤

(ሠ) የዋስትናው ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፤

(ረ) ለኢንሹራንስ ፡ መግቢያ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፤

(ሰ) የውሉ ፡ ዘመን ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፮፻፶፱ ። የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ መጽናት ፡ የሚጀመርበት ፡ ጊዜ ።

(፩) ተቃራኒ ፡ ውሳኔ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ፖሊሲው ፡ ከተ ፈረመበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ይጸናል ።

(፪) ስለሆነም ፡ የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ተፈጻሚነቱን ፡ የሚጀምረው ፡ የመጀመ ሪያው ፡ መደብ ፡ የኢንሹራንሱ ፡ መግቢያ ፡ ገንዘብ ፡ ሲከፈል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ለመዋዋል ፡ ይቻላል ።

## ቍ ፡ ፮፻፷ ። ለታዘዘለት ፡ የሚል ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ፖሊሲ ።

(፩) የኢንሹራንስ፡ ውል፡ ፖሊሲ፡ በአንድ ፡ የተለየ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ለታ ዘዘለት ፡ ሰው ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

(፪) የኢንሹራንስ ፡ ሰጪው፡ በመጀመሪያው፡ ተጠቃሚ ፡ ላይ ፡ ማቅረብ ፡ የሚ ችለው ፡ መከራከሪያውን፡ የኢንሹራንስ ፡ ጥቅም ፡ በተዛወረለት ፡ ወይም ፡ በጀ ርባ ፡ በተፈረመለት ፡ ጥቅሙን ፡ ባገኘ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፮፻፷፩ ። ስለ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የሚደረግ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ፖሊሲ ።

(፩) የኢንሹራንስን ፡ ውል ፡ በወኪል ፡ ለመዋዋል ፡ ይቻላል ።

(፪) ገንዘብ፡ ከፋዩ፡ ወኪል ፡ ባይሆንም ፡ የኢንሹራንሱን ፡ ውል ፡ ለሦስተኛው ፡ ወገን ፡ መዋዋል ፡ ይችላል ። ተጠቃሚው ፡ ሰው ፡ የኢንሹራንሱን ፡ ውል ፡ ያጸደቀው፡ እንደ፡ ሆነ ፤ በውሉ ፡ ሊጠቀምበት ፡ ይችላል ። ስለሆነም ፡ ለውሉ፡ የተነገረው ፡ አደጋ ፡ ከደረሰም ፡ በኋላ ፡ ውሉን ፡ ከመቀበል ፡ የሚያግደው ፡ ነገር ፡ የለም ፤ በውሉ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ውሉን ፡ እተቀበለ ፡ ድረስ፡ ገንዘብ ፡ ከፋዩ ፡ ሰው ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ግዴታ ፡ ኀላፊነት ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፮፻፷፪ ። ተለይቶ ፡ ላልታወቀ፡ ለሦስተኛ፡ ወገን ፡ የሚደረግ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል።

(፩) የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ተለይቶ ፡ ላልታወቀ ፡ ለሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ። ይህም ፡ በተባለው ፡ የወደፊት ፡ ተጠቃሚ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ።

(፪) በንኡስ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ መሠረት፡ የኢንሹራንስን ፡ ውል ፡ የፈረመው ፡ ሰው ፡ ለኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ መክፈል ፡ አለበት ። ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ የኢንሹራንሱን ፡ ውል ፡ ፈራሚ ፡ በሆነው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ማቅረብ ፡ የሚችለውን ፡ መከራከሪያ ፡ በኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ተጠቃሚ ፡ በሆነው ፡ ሰው ፡ ላይም ፡ ማቅረብ ፡ ይችላል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## የተዋዋዮቹ ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ።

ቍ ፡ ፮፻፷፫ ። ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ መድን ፡ የሚሆንበት ፡ አደጋ ።

(፩) የኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ በውሉ ፡ ለተመለከተው ፡ አደጋ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ለገባው ፡ ሰው ፡ መድን ፡ ይሆናል ።

(፪) ተቃራኒ፡ ውል፡ ካልኖረ፡ በቀር፡ ኢንሹራንስ፡ በገባው፡ ሰው፡ ቸልተኝነትና ፡ ባልታሰበ ፡ አደጋ ፡ ለሚያደርሰው ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፡ መድን ፡ ነው ።

(፫) ተቃራኒ፡ ውል ፡ ቢኖርም ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ ዐውቆ ፡ በሚያደርገው ፡ ጥፋት ፡ ለሚያደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ መድን ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፮፻፷፬ ። ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ኀላፊ ፡ የሚሆንባቸው ፡ ሰዎች ፡ ስለሚያደርጉት ፡ ጥፋት ።

(፩) ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ኀላፊ ፡ የሚሆንባቸው ፡ ሰዎች ፡ ባደረጉት ፡

ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ ለሚደርስ ፡ ጉዳትና ፡ ኪሣራ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ መድን ፡ ነው ።

(፪) የተደረገው ፡ ጥፋት ፡ ዐይነትና ፡ ክብደት ፡ ሳይታይ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተጻፈው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፮፻፷፭ ። የኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ግዴታ ።

(፩) ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተው ፡ አደጋ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የተስማሙበት ፡ ቀን ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የተስማሙበትን ፡ ገንዘብ ፡ በውሉ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ መክፈል ፡ ይገባዋል ።

(፪) ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ የሚከፍለው ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ በውሉታው ፡ ላይ ፡ ከተጠቀሰው ፡ አይበልጥም ።

ቍ ፡ ፮፻፷፮ ። ለኢንሹራንስ ፡ መግቢያ ፡ ስለሚከፈለው ፡ ገንዘብ ።

(፩) ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ ለኢንሹራንስ ፡ መግቢያ ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ መክፈል ፡ ግዴታው ፡ ነው ።

(፪) ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ተጠቃሚው ፡ ለኢንሹራንስ ፡ መግቢያ ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ባለመክፈሉ ፡ ብቻ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ አይቻልም ። ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ገንዘቡ እንዲከፈለው ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ።

(፫) ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ መሠረት ፡ ገንዘቡ ፡ እንዲከፈለው ፡ ጥያቄ ፡ ካደረገ ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ገንዘቡ ፡ ሳይከፈለው ፡ ቢቀር ፡ ውሉ ፡ ይታገዳል ።

(፬) የአንድ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ተጠቃሚው ፡ ለኢንሹራንስ ፡ መግቢያ ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈለው ፡ ወይም ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይቻላል ።

(፭) የኢንሹራንሱ ፡ ገንዘብ ፡ የተከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ ገንዘቡ ፡ በተከፈለበት ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

(፮) የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ውሳኔዎች ፡ ስለ ፡ ሕይወት ፡ ለተደረገ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ አይሆኑም ።

ቍ ፡ ፮፻፷፯ ። ውሉ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚሰጥ ፡ መግለጫ ።

ውሉን ፡ በሚዋዋልበት ፡ ጊዜ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ የሚያውቃቸውን ፡ ማናቸውንም ፡ ሁኔታዎችና ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ኀላፊነት ፡ የሚወስድባቸውን ፡ አደጋዎች ፡ ለማመዛዘን ፡ የሚያስችሉትን ፡ ማናቸውንም ፡ ሁኔታዎች ፡ በትክክል ፡ መግለጥ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፮፻፷፰ ። ስለ ፡ ተሸሸጉ ፡ ነገሮችና፡ ስለ፡ ሐሰት ፡ መግለጫዎች ።

(፩) ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ እያወቀ ፡ እውነቱን ፡ ነገር ፡ የሸሸገ ፡ ወይም፡ የሐሰት ፡ መግለጫ ፡ የሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እውነተኛው ፡ ነገር ፡ ተገልጾለት ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ኢንሹራንስ፡ሰጪው ፡ ይህን ፡ ውል ፡ አይዋዋልም ፤ ወይም፡ተጠቃሚው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍል ፡ የሚያደርግለት ፡ ውል ፡ ይዋዋል ፡ ነበር ፡ እስከሚያሰኝ ፡ ድረስ ፡ እነዚህ ፡ የተሸሸጉ ፡ ነገሮችም ፡ በሐሰት ፡ የተሰጡ ፡ መግለጫዎች ፡ የኢንሹራንስ ፡ ሰጪውን ፡ የአደጋውን ፡ አስተያየት ፡ ለውጠውበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉ ፡ ፍርስ ፡ ይሆናል ። ኢንሹራንስ ፡ ሰጪውም ፡ ስለ ፡ ኢንሹራንስ ፡ መግቢያ ፡ የተከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ያስቀራል ።

(፪) ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ መሸሸጉ ፡ ወይም ፡ የሐሰት ፡ መግለጫው ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ያልተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፤ ኢንሹራንስ ፡ ገቢውም ፡ በመጥፎ ፡ ልቡና ፡ ያደረገው ፡ መሆኑን ፡ ማስረዳት ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉ ፡ አይፈርስም ።

(ሀ) መሸሸጉ ፡ ወይም ፡ የሐሰት ፡ መግለጫ ፡ መሰጠቱ ፡ አደጋው ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ የተገለጸ ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ኢንሹራንስ፡ ሰጪው ፡ ለኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ ማስታወቂያ ፡ ከሰጠ ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ወይም ፡ የኢንሹራንስ ፡ መግቢያ ፡ ገንዘብ ፡ ተጨምሮ ፡ ውሉ ፡ እንዲቀጥል ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(ለ) የተሸሸገው ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፡ የተሰጠ ፡ መግለጫ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀው ፡ አደጋው ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሊደርስ ፡ የሚችለው ፡ አደጋ ፡ በሙሉና ፡ በትክክል ፡ ተገልጾ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ለኢንሹራንስ ፡ ሊከፈል ፡ ይገባ ፡ በነበረውና ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በተከፈለው ፡ ኢንሹራንስ ፡ መግቢያ ፡ ገንዘብ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ ታይቶ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ለኪሣራ ፡ የሚከፍለው ፡ ገንዘብ ፡ በዚሁ ፡ ልክ ፡ ተቀናሽ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፮፻፷፱ ። ሊደርስ ፡ የሚችለው ፡ አደጋ ፡ እየከበደ ፡ የሄደ ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ መግለጽ ።

(፩) ሊደርስ ፡ የሚችለው ፡ አደጋ ፡ እየከበደ ፡ መሄዱ ፡ ውሉ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ አደጋው፡ በዚሁ፡ ሁኔታ፡ እየከበደ፡ የሚሄድ፡ መሆኑ፡ ቢታወቅ፡ ኖሮ፡ ኢንሹራንስ፡ ሰጪው፡ የማይዋዋል፡ መሆኑ፡ ወይም፡ ቢዋዋልም፡ ኢንሹራንስ፡ ገቢውን፡ ከፍ፡ ያለ፡ ኢንሹራንስ፡ መግቢያ፡ ገንዘብ፡ አስከፍሎ፡ ይዋዋል፡ ነበር፡ የሚያሰኝ፡ሆኖ፡ ሲገኝ፡ ኢንሹራንስ፡ በገባው፡ ሰው፡ ምክንያት ፡ ሲሆን ፡ አደጋው ፡ እየጨመረ ፡ እንዲሄድ፡ ያደረገው፡ ሁኔታ፡ በተደረገ ፡ በዐሥራ፡ አምስት፡ ቀን፡ ውስጥ ፡ ወይም፡ ይህን ፡ ድርጊት ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገቢው፡ ካወቀበት ፡ ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ በማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ ለኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ማስታወቅ፡ አለበት ። ይህ፡ ጊዜ፡ በኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ሊቀነስ፡ አይቻልም ።

(፪) ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ውሉን ፡ ለማፍረስ ፡ ወይም ፡ለኢንሹራንስ ፡ የሚከ ፈለውን ፡ ገንዘብ፡ ጨምሮ፡ ውሉ ፡ እንዲጸና ፡ (እንዲቈይ) ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፫) ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ በተነገረው ፡ መሠረት ፡ ለኢንሹራንስ ፡ ሰጪው፡ ባያስታውቅ፡ (ባይገልጽ) ፡ ወይም ፡ ትክክለኛ ፡ መግ ለጫ፡ ሳይሰጥ፡ ሲቀር፡ በቍጥር ፡ ፮፻፷፰፡ የተጻፈው፡ ድንጋጌ፡ ተፈጻሚ፡ ይሆናል።

(፬) የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌዎች ፡ ስለ ፡ ሕይወት ፡ በተደረገ ፡ ኢንሹራንስ፡ ተፈ ጻሚዎች ፡ አይሆኑም ።

ቍ ፡ ፮፻፸ ። አደጋን ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።

(፩) ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ምክንያት ፡ ያልቻለ ፡ መሆኑን ፡ ካላስረዳ፡ በተቀር፡ ኢንሹራንስ፡ የገባው፡ ሰው ፡ ኢንሹራንስ፡ ሰጪው፡ መድን ፡ የሆነበት ፡ አደጋ ፡ መድረሱን ፡ እንዳወቀ ፡ ወዲያውኑ ፡ ወይም ፡ እጅግ ፡ ቢዘገይ ፡ በአም ስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ለኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፪) ይህን ፡ የተባለውን ፡ ቀን ፡ በውል ፡ ማሳጠር ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፮፻፸፩ ። ስለ ፡ መክሠር ።

(፩) ኢንሹራንስ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የከሠረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ አይፈርስም ፤ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ፡ በውሉ ፡ ተጠ ቃሚና ፡ ለኢንሹራንስ ፡ መግቢያ ፡ ስለሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ባለዕዳ ፡ ሆነው ፡ የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ጸንቶ ፡ ይቈያል ።

(፪) ስለሆነም፡ ንብረት፡ ጠባቂዎቹና፡ ኢንሹራንስ፡ ሰጪው፡ ከሠረ፡ ተብሎ፡ ፍርድ፡ ከተፈረደበት፡ ቀን፡ እንሥቶ፡ በሦስት፡ ወር፡ ውስጥ፡ ውሉን ፡ ማፍረስ ፡ይችላሉ ።

(፫) ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ የከሠረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከሠረ ፡ ተብሎ ፡ ከተፈረደበት ፡ ቀን ፡ እንሥቶ ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ውሉ ፡ ያልቃል ።

ቍ ፡ ፮፻፸፪ ። የኢንሹራንሱ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ መሞት ።

(፩) ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆ ነው ፡ ሰው ፡ ሲሞት ፡ የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ መብት ፡ ወደ ፡ ወራሾቹ ፡ ተላ ልፎ ፡ ይቀጥላል ።

(፪) ስለሆነም ፡ ወራሾቹና ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ በኢንሹራንሱ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነው፡ ሰው፡ ከሞተበት፡ ቀን ፡ እንሥቶ ፡ በሦስት፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ፡ ውሉን፡ ለማፍረስ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፮፻፸፫ ። ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለትን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

(፩) ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለት ፡ ነገር ፡ ለሌላ ፡ በተላለፈ ፡ ጊዜ ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ በሙሉ ፡ መብት ፡ ለተላለ

ፈለት ፡ ሰው ፡ ይቀጥላል ።

(፪) ስለሆነም ፡ ንብረቱ ፡ የተላለፈለትና ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ኢንሹራንስ ፡ የተደረገበት፡ ነገር፡ ለሌላ ፡ ከተላለፈበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሦስት ፡ ወር፡ ጊዜ፡ ውስጥ ፡ ውሉን ፡ ሊያፈርሱ ፡ ይችላሉ ።

### ክፍል ፡ ፫ ።

### ስለ ፡ ይርጋ ።

**ቍ ፡ ፮፻፸፬ ። ይርጋ ።**

(፩) በኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ምክንያት ፡ የሚቀርብ ፡ ማንኛውም ፡ ክስ ፡ የሚታገደው ፡ ለክሱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ጉዳት ፡ ከተደረገበት ፡ ወይም ፡ በጉዳዩ ፡ ጥቅም ፡ ያላቸው ፡ ወገኖች ፡ ጉዳቱን ፡ ካወቁበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ነው ።

(፪) የተሸሸገ ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፡ ቃል ፡ የቀረበ ፡ ጕዳይ ፡ ያጋጠመ ፡ ሲሆን ፡ የይርጋው ፡ ዘመን ፡ የሚታሰበው ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ ካወቀበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

(፫) ይህን ፡ ለይርጋ ፡ የተወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ በውል ፡ ለማሳጠር ፡ አይቻልም ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ኢንሹራንስ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### የዕቃዎች ፡ ኢንሹራንስ ።

**ቍ ፡ ፮፻፸፭ ። ኢንሹራንስ ፡ ለማድረግ ፡ ስለ ፡ መቻሉ ።**

(፩) ዕቃውን ፡ ከጉዳት ፡ ለመጠበቅ ፡ የሚፈልግ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሊያስገባው ፡ ይችላል ።

(፪) ጉዳት ፡ እንዳይደርስ ፡ በማለት ፡ ማንኛውም ፡ ቀጥተኛ ፡ ወይም ፡ ቀጥተኛ ፡ ያልሆነ ፡ ጥቅም ፡ ሁሉ ፤ ኢንሹራንስ ፡ ሊገባበት ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፮፻፸፮ ። አላፊነትን ፡ የሚያስከትሉ ፡ ጕዳዮች ።**

(፩) ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ጋራ ፡ በተደረገ ፡ ጦርነት ፡ ወይም ፡ በአገር ፡ ውስጥ ፡ በሆነ ፡ የእርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ በመነሣቱ ፡ ምክንያት ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ ጥፋት ፡ አላፊ ፡ ለመሆን ፡ ካልተዋዋለ ፡ በቀር፡ አላፊነት ፡ የለበትም ።

(፪) ጥፋቱ ፡ ወይም ፡ ጉዳቱ ፡ የደረሰው ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ በተመለከቱት ፡ ምክንያቶች ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ማስረዳት ፡ ያለበት ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፮፻፸፯ ። የዕቃው ፡ መጥፋት ።

ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ዕቃ ፡ በኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ባልተመለከተ ፡ ምክንያት ፡ የጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ያደርገዋል ።

ቍ ፡ ፮፻፸፰ ። ካሣ ።

ኢንሹራንስ ፡ የገባ ፡ ዕቃ ፡ ውል ፡ ማለት ፡ ዕቃው ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባበት ፡ ካሣ ፡ የመጠየቂያ ፡ ውል ፡ ነው ፤ ካሣውም ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ዕቃ ፡ ጉዳት ፡ በደረሰበት ፡ ቀን ፡ ከሚያወጣው ፡ ዋጋ ፡ አይበልጥም ።

ቍ ፡ ፮፻፸፱ ። ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ከተደረገበት ፡ ዋጋ ፡ የበለጠ ፡ ሲሆን ።

ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ዕቃ ፡ ጉዳት ፡ በደረሰበት ፡ ቀን ፡ ያወጣ ፡ የነበረው ፡ ዋጋ፡ ኢንሹራንስ ፡ ከገባበት ፡ ዋጋ ፡ በልጦ ፡ ሲገኝ ፤ በልጦ ፡ ለሚገኘው ፡ ዋጋ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ ራሱ ፡ እንደ ፡ ኢንሹራንስ ፡ አድራጊ ፡ ተቈጥሮ ፡ ከጉዳቱ ፡ በመጠኑ ፡ በከፊል ፡ ይችላል ፤ ከጉዳቱ ፡ በመጠኑ ፡ ይችላል ፡ የተባለውን ፡ ውሳኔ ፡ በውል ፡ ለማስቀረት ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፮፻፹ ። ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ዕቃ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ከተደረገበት ፡ ዋጋ ፡ ያነሰ ፡ ሲሆን ።

(፩) በኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሰው ፡ ካሣ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ከገባው ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ ሲበልጥና ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ አታሎ ፡ ወይም ፡ አጭበርብሮ ፡ ሲገኝ ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለማድረግ ፡ ከመቻሉም ፡ በላይ ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ማታለልና ፡ ማጭበርበር ፡ የሌለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ የሚቈየው ፡ ኢንሹራንስ ፡ ለገባው ፡ ዕቃ ፡ እውነተኛ ፡ ዋጋ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፫) በኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ ጥያቄ ፡ ኢንሹራንሱ ፡ የተቀነሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ ለወደፊቱ ፡ ለኢንሹራንሱ ፡ በየጊዜያቱ ፡ የሚከፈለው ፡ ሒሳብ ፡ ዝቅ ፡ ይላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ቅናሹ ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ ለኢንሹራንሱ ፡ በየጊዜያቱ፡የተከፈለውን፡ሒሳብ፡ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው፡ለማስቀረት፡መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፮፻፹፩ ። ተደራራቢ ፡ ኢንሹራንስ ።

(፩) አያሌ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪዎች ፡ አንዱን ፡ ዕቃ ፡ ለአንዱ ፡ ዐይነት ፡ ጉዳት ፡ ኢንሹራንስ ፡ በመስጠታቸው ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ ኢንሹራ

ንስ ፡ ከተደረገበት ፡ ዋጋ ፡ የበለጠ ፡ ሲሆን ፡ እያንዳንዱ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ሰጪ ፡ በኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ በኩል ፡ ማታለል ፡ ከተደረገ ፡ ውሉ ፡ እንዲፈርስና ፡ ኪሣራም ፡ እንዲከፍለው ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ያደረገው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አደጋ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪ ፡ ስለ ፡ ኢንሹራንሱ ፡ በተዋዋለበት ፡ ሒሳብ ፡ መጠን ፡ ካሣ ፡ ከፋይ ፡ ይሆናል ።

<u>ቍ ፡ ፲፻፷፪ ። ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ዕቃ ፡ ስለ ፡ መጥፋቱ ።</u>

(፩) ኢንሹራንስ ፡ በገቡበት ፡ ጊዜ ፡ ከጉዳት ፡ እንዲጠበቅ ፡ የተፈለገው ፡ ዕቃ ፡ አስቀድሞ ፡ የጠፋ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፡ ወይም ፡ አደጋ ፡ የማይደርስበት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ አይጸናም ፤ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ባለጥቅሙ ፡ ሰው ፡ በየጊዜያቱ ፡ ለኢንሹራንሱ ፡ የከፈለው ፡ ሒሳብ ፡ ይመለስለታል ።

(፪) በመጥፎ ፡ ልቡና ፡ የተደረገ ፡ ሲሆን ፡ ማንኛውም ፡ ወገን ፡ ኪሣራ ፡ ይከፍላል ።

<u>ቍ ፡ ፲፻፷፫ ። ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ በምትክነት ፡ ስለ ፡ መግባት ።</u>

(፩) ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ በከፈለው ፡ ካሣ ፡ መጠን ፡ ጉዳቱ ፡ እንዲደርስ ፡ ባደረጉት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ለገባው ፡ ሰው ፡ በተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ባሉት ፡ መብቶችና ፡ ክሶች ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ምትክ ፡ ሆኖ ፡ ይገባል ።

(፪) ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ ባደረገውም ፡ ምክንያት ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ እንደተመለከተው ፡ በኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ ምትክ ፡ ለመተካት ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ አላፊነት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ይቀርለታል ።

(፫) ስለሆነም ፡ ሌላ ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ በክፋት ፡ ያደረጉት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ በኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የሚቈጠሩ ፡ ተወላጆች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ወላጆች ፡ ወኪሎች ፡ ሠራተኞች ፡ ወይም ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ዘወትር ፡ አብረው ፡ በሚኖሩት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ።

<u>ቍ ፡ ፲፻፷፬ ። የቀዳሚነት ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ወይም ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ።</u>

(፩) ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ለአንድ ፡ ንብረት ፡ የሚከፈለው ፡ የኢንሹራንስ ፡ ገንዘብ ፡ በዚሁ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የቀዳሚነት ፡ ወይም ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ላላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ይሰጣል ። እነዚህ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ላይ ፡ በቀጥታ ፡ ክስ ፡

ማቅረብ ፡ ይችላሉ ፤ እርሱም ፡ ደግሞ ፡ ኢንሹራንስ ፡ በገባው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችል ፡ የነበረውን ፡ መከላከያ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ።

(፪) ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ዕቃው ፡ በብድር ፡ መያዣ ፡ መሰጠቱን ፡ ባለማወቅ ፡ ለተጠቃሚው ፡ ክፍሎ ፡ ቢገኝ ፡ አከፋፈሉ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## የኀላፊነት ፡ ኢንሹራንስ ።

### ቍ ፡ ፮፻፹፭ ። ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ አላፊ ፡ የሚሆንበት ።

በኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሰው ፡ ጉዳት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ኢንሹራንስ ፡ በገባው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በስምምነት ፡ ጥያቄ ፡ ካላደረገ ፡ በቀር ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ በአላፊነት ፡ አይጠየቅም ።

### ቍ ፡ ፮፻፹፮ ። አላፊነትን ፡ ስለ ፡ ማመን ።

(፩) ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ሳይኖር ፡ የተደረገ ፡ አላፊነትን ፡ ማመን ፡ ወይም ፡ የተደረገ ፡ ግልግል ፡ በኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ላይ ፡ መከራከሪያ ፡ አይሆንበትም ፡ የሚል ፡ የስምምነት ፡ ቃል ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) የተፈጸመው ፡ የሁኔታ ፡ ማመን ፡ አላፊነትን ፡ ማመን ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሊቈጠር ፡ አይችልም ።

### ቍ ፡ ፮፻፹፯ ። ስለ ፡ ክሱ ፡ አመራር ።

(፩) ጉዳት ፡ የደረሰበት ፡ ወገን ፡ ለአላፊነት ፡ የሚያቀርበውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ መሪ ፡ ለመሆን ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ የተዋዋለው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ይጸናል ።

(፪) በመጀመሪያ ፡ ተጠቃሚ ፡ ላይ ፡ የቀረበበት ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ሲሆን ፡ ማንኛውንም ፡ የወንጀል ፡ ጉዳይ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ የሚመራ ፡ ለመሆኑ ፡ የተጻፈ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ አይጸናም ። ኢንሹራንስ ፡ ገቢው ፡ አቤቱታ ፡ የማቅረብ ፡ መብቱን ፡ ሊሠራበት ፡ ወይም ፡ ሊተወው ፡ ይችላል ።

### ቍ ፡ ፮፻፹፰ ። ጉዳት ፡ ለደረሰበት ፡ ወገን ፡ በቀደምትነት ፡ ስለ ፡ መክፈል ።

(፩) ጉዳት ፡ ለደረሰበት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ በሚከፍለው ፡ ኪሣራ ፡ ሒሳብ ፡ ልክ ፡ ካሣውን ፡ እስኪከፍለው ፡ ድረስ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ኢንሹራንስ ፡ ለገባው ፡ ሰው ፡ ካሣ ፡ አይከፍልም ።

(፪) የዚህን ፡ ቍጥር ፡ ውሳኔ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም ፡ የውል ፡ ቃል ፡ አይጸናም ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## የሰዎች ፡ ኢንሹራንስ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

**ቍ ፡ ፮፻፹፱ ። ኢንሹራንስ ፡ የተገባበትን ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ በፈቃድ ፡ ስለ ፡ መወሰን ።**

ስለ ፡ ሰዎች ፡ የተደረገ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ እንደ ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ ውል ፡ የሚ ቈጠር ፡ አይደለም ። ኢንሹራንስ ፡ የተገባበትን ፡ ገንዘብ ፡ በኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ በነጻ ፡ የሚወሰን ፡ ሆኖ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ የደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ሳይገመት ፡ ሊከፍል ፡ ይገባዋል ።

**ቍ ፡ ፮፻፺ ። መተካት ፡ የማይቻል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ ኢንሹራንስ ፡ ስምምነት ፡ ተደርጎበት ፡ የነበረውን ፡ ሒሳብ ፡ ለባለውሉ ፡ ወይም ፡ ለተጠቃሚው ፡ የከፈለ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪ ፤ ጉዳት ፡ እንዲደርስ ፡ ባደረጉት ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ በእነርሱ ፡ መብት ፡ ተተክቶ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ።

### ክፍል ፡ ፪ ።

### ስለ ፡ ሕይወት ፡ ኢንሹራንስ ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፩ ። ትርጓሜ ።**

የሕይወት ፡ ኢንሹራንስ ፡ ማለት ፡ ባለኢንሹራንሱ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከአ ንድ ፡ ጊዜ ፡ በበለጠ ፡ ስለ ፡ ኢንሹራንሱ ፡ የሚከፍለውን ፡ ገንዘብ ፡ ተቀብሎ ፡ በተ ዋዋዩ ፡ ወይም ፡ ኢንሹራንስ ፡ በተገባበት ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ሕይወት ፡ ወይም ፡ ሞት ፡ ጋራ ፡ የተያያዙ ፡ አንዳንድ ፡ ሁኔታዎች ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፤ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ ለተዋዋዩ ፡ ወይም ፡ ለተጠቃሚው ፡ ለመክፈል ፡ የሚዋዋለው ፡ ውል ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፪ ። ስለ ፡ ሕይወት ፡ ኢንሹራንስ ።**

(፩) የሕይወት ፡ ኢንሹራንስ ፡ የሚዋዋለው ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ በኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በሕይወት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተወሰነ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ በሕይወት ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ ወይም ፡ በየጊዜው ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ ነው ።

(፪) ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ የተዋዋለው ፡ ኢንሹራንስ ፡ ስለገባው ፡ ሰው ፡ ሞት ፡

የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ኢንሹራንስ ፡ ከገባው ፡ ሰው፡ መብት ፡ ላላቸው ፡ ወይም፡ በኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ለተጠቀሰው ፡ ተጠቃሚ ፡ የተወሰነ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ በሕይወት ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ በየጊዜው ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ለመክፈል ፡ ነው ።

(፫) ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ እና ፡ በንኡስ፡ቍጥር ፡ ፪፡የተጠቀሱትን ፡ ለመክፈል ፡ ግዴታ ፡ የገባ ፡ ሲሆን ፤ የተጣመረ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ መዋዋል ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፮፻፹፫ ። ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የሚያደርገው ፡ የሕይወት ፡ ኢንሹራንስ ።**

የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተብሎ ፡ ኢንሹራንስ ፡ በገባለት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ሊዋዋል ፡ ይችላል ። ኢንሹራንስ ፡ የተገባለት ፡ ሰው ፡ የኢንሹራንስን ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ከሚያመለክት ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ በጽሑፍ ፡ ስምምነቱን ፡ ካልሰጠ ፡ በቀር ፡ ውሉ ፡ ፍርስ ፡ ነው ። ኢንሹራንስ ፡ የተገባለት ፡ ሰው ፡ ያገባ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተጋቢውም ፡ በውሉ ፡ እንዲስማማ ፡ ያስፈልጋል ።

**ቍ ፡ ፮፻፹፬ ። ችሎታ ፡ በሌለው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ኢንሹራንስ ።**

ችሎታ፡ የሌለው ፡ ሰው፡ ወይም፡ እንደራሴው ፡ ቢስማማም፡ የሞተ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ተብሎ ፡ ችሎታ ፡ በሌለው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል፡ፍርስ፡ ነው ፤ ማንኛውም ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ባቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ እንዲፈርስ ፡ ይደረጋል ፤ ለኢንሹራንስ ፡ መግቢያ ፡ የተከፈለውም ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፮፻፹፭ ። ስለ ፡ ሕይወት ፡ ኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ፖሊሲ ፡ ዝርዝር ።**

የሕይወት ፡ ኢንሹራንስ፡ ውል ፡ ፖሊሲ ፡ በቍጥር፡፮፻፶፰ ፡ ከተመለከተው ፡ ዝርዝር ፡ ሐተታ ፡ በቀር ፤ በተጨማሪ ፤

(ሀ) ስለ ፡ ሕይወት ፡ ኢንሹራንስ ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ የግል ፡ ስም ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ ስምና ፡ የተወለደበትን ፡ ቀን ፤

(ለ) ተጠቃሚው ፡ ተለይቶ ፡ የታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተጠቃሚው ፡ ቤት ፡ ዘመድ ፡ ስምና ፡ የግል ፡ ስም ፤

(ሐ) የተስማሙበት ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈል ፡ የሚደረግበት ፡ ሁኔታ ፤

(መ) ቅናሽ ፡ የሚደረግበትና ፡ መልሶ ፡ የሚገዛበት ፡ ሁኔታ ፤ በኢንሹራንስ ፡ ፖሊሲ ፡ ውስጥ ፡ በትክክል ፡ መገለጽ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፮፻፹፮ ። ለታዘዘለት ፡ የሚል ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ።**

የሕይወት ፡ ኢሹራንሱ ፡ ፖሊሲ ፡ ለታዘዘለት ፡ የሚል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤

በውሉ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ፊርማ ፡ የተጠቃሚው ፡ ስምና ፡ ቀን ፡ ከሌለ በት ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፯ ። የኢንሹራንሱን ፡ ውል ፡ መያዣ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።**

ለታዘዘለት ፡ የሚል ፡ የሕይወት ፡ ኢንሹራንስን ፡ ውል ፡ በተጨማሪ ፡ ስምም ነት ፡ ወይም ፡ ለታዘዘለት ፡ በሚለው ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ስለ ዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ በመፈረም ፡ ወይም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪ሺ፫፻፴፯ ፡ መሠረት ፡ ማያዣ ፡ ማድረግ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፰ ። መያዣ ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ ለማስተላለፍ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ስምምነት ፡ አስፈላጊ ፡ ስለመሆኑ ።**

ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ በጽሑፍ ፡ ካልተስማማ ፡ የኢንሹራንስን ፡ ውል ፡ ለሌላ ፡ ለማዛወር ፡ ወይም ፡ በጀርባው ፡ ላይ ፡ በመፈረም ፡ ጥቅምን ፡ ለሌላ ፡ ማሳ ለፍ ፤ ወይም ፡ በመያዣነት ፡ መስጠት ፡ ወይም ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጾ ፡ የተመ ለከተውን ፡ ተጠቃሚ ፡ መለወጥ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፮፻፺፱ ። ራስን ፡ ስለ ፡ መግደል ።**

(፩) ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ለሕይወት ፡ የሚደረግ ፡ ኢንሹራ ንስ ፤ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ራሱን ፡ የገደለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ኢንሹራንሱ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ፤ ሆን ፡ ብሎ ፡ ራሱን ፡ የገደለ ፡ መሆኑን ፡ ማስ ረዳት ፡ ያለበት ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ነው ።

(፪) ሆን ፡ ብሎ ፡ ራሱን ፡ ያልገደለ ፡ መሆኑን ፡ ተጠቃሚው ፡ ማስረዳት ፡ የቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፯፻ ። ገዳዩ ፡ ተጠቃሚው ፡ ሲሆን ።**

ኢንሹራንሱ ፡ የሕይወት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባውን ፡ ሰው ፤ ተጠቃ ሚው ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ የገደለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚሁም ፡ በወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተፈረደበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

**ቍ ፡ ፯፻፩ ። ለሞት ፡ በሆነ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ሰው ።**

(፩) ለሞት ፡ የሚደረግ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ለአንድ ፡ የተለየ ፡ ተጠቃሚ ፡ ጥቅም ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) ስማቸው ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ተለይቶ ፡ ባይጠቀስም ፤

(ሀ) ጋብቻው ፡ የተደረገው ፡ የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ከተፈረመ ፡ በኋላም ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ የኢንሹራንሱን ፡ ውል ፡ የፈረመው ፡ ሰው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፤

(ለ) የኢንሹራሱ ፡ ውል ፡ ሲፈረም ፡ የተወለዱት ፡ የኢሹራሱ ፡ ውል ፡ ፈራሚ ፡ ሰው ፡ ልጆች ፤ ተለይተው ፡ የታወቁ ፡ ተጠቃሚዎች ፡ ተብለው ፡ ይቈጠራሉ ።

(፫) በኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ የተለየ ፡ ተጠቃሚ ፡ ያልተጠቀሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የተጠቀሰው ፡ ተጠቃሚ ፡ ውሉን ፡ አልቀበልም ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የኢንሹራንሱን ፡ ውል ፡ የተዋዋለው ፡ በኑዛዜ ፡ የኢንሹራንሱን ፡ ውል ፡ በተጨማሪ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ ለታዘዘለት ፡ የሚለውን ፡ ኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ በጀርባው ፡ ላይ ፡ በመፈረም ፡ አንድ ፡ ተጠቃሚ ፡ መምረጥ ፡ ወይም ፡ በአንዱ ፡ ተጠቃሚ ፡ ሌላ ፡ ምትክ ፡ ተጠቃሚ ፡ መተካት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፯፻፪ ። የኢንሹራንሱ ፡ ገንዘብ ፡ ሊጠየቅ ፡ በሚቻልበት ፡ ጊዜ ፡ የተጠቃሚው ፡ በሕይወት ፡ መኖር ።

ሌላ ፡ ስምምነት ፡ ካልኖረ ፡ በቀር ፡ ለተጠቃሚው ፡ የሚከፈለው ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ በየጊዜው ፡ በሕይወት ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ሊጠየቅ ፡ በሚቻልበት ፡ ጊዜ ፡ ተጠቃሚው ፡ በሕይወት ፡ መኖር ፡ አለበት ፡ በሚል ፡ ሁናቴ ፡ የሚከፈል ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፯፻፫ ። ተጠቃሚው ፡ እንዲስማማ ፡ አስፈላጊ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

(፩) ለአንድ ፡ ተለይቶ ፡ ለታወቀ ፡ ተጠቃሚ ፡ የተሰጠ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ተጠቃሚው ፡ እንዲቀበል ፡ መፍቀዱን ፡ ካስታወቀ ፡ በኋላ ፡ ሊሻር ፡ አይቻልም ።

(፪) በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ተለይቶ ፡ የተጠቀሰው ፡ ተጠቃሚ ፡ እቀበላለሁ ፡ ብሎ ፡ እስካስታወቀ ፡ ድረስ ፡ ተዋዋዩ ፡ ተጠቃሚውን ፡ መለወጥ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፯፻፬ ። በባለኢንሹራንሱ ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጠው ፡ የመቃወም ፡ ውጤት ።

ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ያወቀው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የተጠቃሚው ፡ ፈቃደኛ ፡ መሆን ፡ ወይም ፡ የተጠቃሚው ፡ ጥቅሙን ፡ አልፈልግም ፡ ብሎ ፡ መሻር ፡ በኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ መቃወሚያ ፡ ሆኖ ፡ ሊቀርብ ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፯፻፭ ። ተጠቃሚው ፡ ሳይለይ ፡ የተደረገ ፡ ኢንሹራንስ ።

ተጠቃሚው ፡ ተለይቶ ፡ ያልታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ተሽሮ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ በሕይወት ፡ የሌለ ፡ በመሆኑ ፡ ውድቅ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ስለ ፡ ሞት ፡ የተደረገው ፡ የኢንሹራንስ ፡ ዋናው ፡ ገንዘብ ፡ የሚከፈለው ፡ ኢንሹራንሱን ፡ ለተዋዋለው ፡ ሰው ፡ ውርስ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፯፻፮ ። ስለ ፡ ተጠቃሚው ፡ መብት ።

(፩) ተጠቃሚው ፡ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪውን ፡ በቀጥታ ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) ለተጠቃሚው ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ከገባው ፡ ሰው ፡ ውርስ ፡ ክፍል ፡ አይሆንም ። ተጠቃሚው ፡ ፈቃደኛ ፡ መሆኑን ፡ ያስታወቀ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እንኳ ፡ የኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ከተፈረመበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ባለመብት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይቈጠራል ።

BACK



(፫) ለተዋዋይ ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ለዚያው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ የግል ፡ ንብረት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፮፻፺ ። መልሶ ፡ ስላለመክፈል ።

ለተጠቃሚው ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ለውርሱ ፡ ተመልሶ ፡ እንዲገባ ፡ ወይም ፡ ተጠቃሚው፡ በውርስ፡ ከሚያገኘው፡ ድርሻው፡ ላይ፡ ተቀናሽ፡ ሊሆን፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፮፻፺፩ ። ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መብት ።

(፩) ኢንሹራንስ ፡ ከገባው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ለተጠቃሚው ፡ ከሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ መብት ፡ የላቸውም ።

(፪) ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ በከሠረ ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ሺ፳፬ ፡ (ሀ) የተጻፈው ፡ ድንጋጌ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፮፻፺፪ ። ስላልተከፈለ ፡ የኢንሹራንስ ፡ መግቢያ ፡ ገንዘብ ።

(፩) ባለኢንሹራንሱ ፡ ስለ ፡ ሕይወት ፡ የሚከፍለው ፡ የኢንሹራንስን ፡ መግቢያ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈለው ፡ ለማስገደድ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ አይችልም ።

(፪) ስለሆነም ፡ በየዓመቱ ፡ ለሦስት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ አከፋፈል ፡ የተመደቡ ፡ ገንዘቦች ፡ ያነሰ ፡ የተከፈለ ፡ ሆኖ ፤ በየዓመቱ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ያልተከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ኢንሹራንስ፡ ሰጪው፡ እንዲከፈለው፡ መጠየቅና ፡ ጠይቆም ፡ ለማግኘት ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ጥያቄ ፡ ካደረገ ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ውሉን ፡ ማፍረስ ፡ ይችላል። ይህን፡ ጊዜ፡ በኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ለማሳጠር ፡ አይቻልም ።

(፫) በየዓመቱ ፡ ለሦስት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ አከፋፈል ፡ የተመደቡ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ገንዘቦች ፡ ከተከፈሉና ፡ በየዓመቱ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ያልተከፈለ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ እንዲከፈለው ፡ ከጠየቀበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ያልተከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የኢንትራንሱ፡ ውል፡ ውድቅ፡ አይሆንም።ባለኢንሹራንሱ ፡ ማድረግ፡ የሚችለው ፡ ለተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ፖሊሲ ፡ መስጠት ፡ ወይም ፡ በውል ፡ የተስማሙበትን ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ በየጊዜው ፡ በሕይወት ፡ እስካለ ፡ ድረስ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፺፯ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ መቀነስ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፮፻፺፫ ። መልሶ ፡ ስለ ፡ መግዛት ።

(፩) ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ በዓመት ፡ ለሦስት ፡ ጊዜ ፡ አከፋፈል ፡ የተመደበው ፡ የኢንሹራንሱ ፡ ገንዘብ ፡ ከተከፈለ ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሞት ፡ የተደረገውን ፡ የኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ፖሊሲ ፡ መልሶ ፡ ለመግዛት ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) መልሱ፡ መግዣው፡ ዋጋ፡ የሚታሰብበትን፡ ሁኔታ፡ በቍጥር፡ ፮፻፺፯ ፡ የተመለከተው፡ ውሳኔ፡ ቅናሹ ፡ የሚደረግበትን ፡ ሁኔታ ፡ የሚወስን ፡ ሊሆን፡ ይችላል።

(፫) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ውሳኔዎች ፡ ለጊዜው ፡ ለተደረጉ ፡ ኢን ሹራንስ ፡ ውሎች ፡ የጸኑ ፡ አይሆኑም ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ አካል ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሕመም ፡ የሚደረግ ፡ ኢንሹራንስ ።

### ቍ ፡ ፯፻፲፩ ። ኢንሹራንስ ፡ ስለ ፡ ተገባበት ፡ አደጋ ።

(፩) ስለ፡ አካል ፡ አደጋ ፡ የሚደረግ፡ የኢንሹራንስ፡ ውል ፡ ፖሊሲ ፡ ማለት ፡ ኢንሹ ራንስ ፡ ሰጪው ፡ በኢንሹራንሱ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ተለይቶ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ኢንሹራንስ ፡ በገባው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ የደረሰበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ኢንሹ ራንስ ፡ ለገባው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ኢንሹራንስ ፡ የገባው ፡ ሰው ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ለተጻፈው ፡ ተጠቃሚ ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ ግዴታ ፡ የገባበት ፡ ውል ፡ ነው ።

(፪) ባለኢንሹራንሱ ፡ መድንነቱን ፡ ለተወሰነ ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ አደጋው ፡ ስለ ሚያስከትለው ፡ የተወሰነ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ለይቶ ፡ መወሰን ፡ ይችላል ።

(፫) አደጋ ፡ ማለት ፡ ሳይታሰብ ፡ ከየትም ፡ የሚደርስ ፡ ማንኛውም ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ ጭምር ፡ ነው ።

(፬) ኢንሹራንስ ፡ ሰጪው ፡ ስለ ፡ ሕመም ፡ ኢንሹራንስ ፡ ውል ፡ ማድረግ ፡ ይችላል ።

### ቍ ፡ ፯፻፲፪ ። ስለ ፡ ሕይወት ፡ ኢንሹራንስ ፡ የተሰጡት ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ስላለመሆናቸው ።

ስለ ፡ ሕይወት ፡ ኢንሹራንስ ፡ የተነገሩት ፡ የዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የክፍል ፡ ፪ ፡ ድን ጋጌዎች ፡ ስለ ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሕመም ፡ በሚደረግ ፡ ኢንሹራንስ ፡ ላይ ፡ ተፈ ጻሚዎች ፡ አይሆኑም ።

## አንቀጽ ፡ ፬ ።

## ስለ ፡ ውርርዶችና ፡ ስለ ፡ ኪማራ ፡ ጨዋታ ።

### ቍ ፡ ፯፻፲፫ ። ውርርድና ፡ የኪማራ ፡ ጨዋታ ።

(፩) የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውሳኔዎች ፡ በውርርድና ፡ በኪማራ ፡ ጨዋታ ፡ ዐይነት ፡ ስለሚደረጉ ፡ ነገሮች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ አይሆኑም ።

(፪) በቍጥር ፡ ፯፻፲፬ ፡ በተመለከተው ፡ ነገር ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በውርርድና ፡ በኪ ማራ ፡ ጨዋታ ፡ የተገኘ ፡ ገንዘብ ፡ ይከፈለኝ ፡ ብሎ ፡ ክስ ፡ የማቅረብ ፡ መብት ፡ ሊሰጥ ፡ አይችልም ።

(፫) ስለሆነም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ማታ

BACK



ለል ፡ ሳይደረግበት ፡ በውርርድና ፡ በኪሣራ ፡ ጨዋታ ፡ ምክንያት ፡ ወዲያው ፡ የከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ይመልስልኝ ፡ ብሎ ፡ መጠየቅ ፡ አይችልም ።

**ቊ ፡ ፯፻፲፩ ፤ በውርርድ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ መከላከያን ፡ ስላለመቀበል ።**

(፩) የወገኖቹ ፡ ሥራቸው ፤ ሐሳባቸው ፤ የጕዳዩም ፡ ትልቅነት ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆን ፡ ሒሳቡም፡ የሚጠናቀቀው ፡ ቀሪውን ፡ ዋጋ ፡ በመክፈል ፡ ቢሆን ፡ በአክሲዮን ፡ ገበያ ፡ የተፈጸመውን ፡ ጕዳይ ፡ የኪሣራ ፡ ጨዋታ ፡ ውርርድ ፡ መልክ ፡ የያዘ ፡ ነው ፡ አይጸናም ፡ ብሎ ፡ መከራከርን ፡ ሊቀበሉት ፡ አይገባም ።

(፪) ከስፖርት ፡ ግንኙነት ፡ ያለውን ፡ የኪሣራ ፡ ጨዋታ ፡ ውርርድ ፡ ነው ፡ አይጸናም ፡ ብሎ ፡ መከራከርን ፡ ሊቀበሉት ፡ አይገባም ። ስለሆነም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተጠየቀው ፡ ገንዘብ ፡ እጅግ ፡ የበዛ ፡ መስሎ ፡ የታየው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መቀነስ ፡ ይችላል ።

(፫) በማንኛውም ፡ መንግሥት ፡ በፈቀደው ፡ ዕጣ ፡ ማውጣትና ፡ ሎተሪ ፡ ላይ ፡ የውርርድ ፡ መከላከያ ፡ አድርጎ ፡ ማቅረብ ፡ አይቻልም ።

# አራተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## የሚተላለፉ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶችና ፡ የባንክ ፡ ሥራዎች ፡ ሕግ ።

### አንቀጽ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ውሳኔዎች ።

**ቊ ፡ ፯፻፲፭ ። ትርጓሜ ።**

(፩) የሚተላለፍ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነድ ፡ ማለት ፡ መብቱ ፡ ከሰነዱ ፡ ተለይቶ ፡ ሊሠራበት ፡ ወይም ፡ ሊተላለፍ ፡ የማይችል ፡ ያገልግሎት ፡ መብት ፡ ያለበት ፡ ሰነድ ፡ ሁሉ ፡ ነው ።

(፪) በተለይም ፡ ሕግ ፡ እንደሚተላለፍ ፡ ገንዘብ ፡ ሰነድ ፡ የሚቈጥራቸው ፡ የንግድ ፡ ወረቀቶችን ፤ የሚተላለፉ ፡ የግዴታ ፡ የምስክር ፡ ወረቀቶችን ፡ የሸቀጥ ፡ ማረጋገጫ ፡ ሰነዶችን ፡ ነው ።

**ቊ ፡ ፯፻፲፮ ። ከሚተላለፉ ፡ ገንዘብ ፡ ሰነዶች ፡ የመጡ ፡ ግዴታዎች ።**

(፩) በሕግ ፡ እንደታዘዘው ፡ ሕጋዊ ፡ ይዞታ ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ ያረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አንድ ፡ የሚተላለፍ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነድ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ይኸንኑ ፡ ለዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ በማቅረብ ፡ በሰነዱ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ ማግኘት ፡ ይገባዋል ።

BACK



(፪) ባለዕዳውም ፡ ሰነዱ ፡ ካልተሰጠው ፡ በቀር ፡ ግዴታውን ፡ ለመፈጸም ፡ አይገደድም ።

(፫) ዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ አታላይነት ፡ ወይም ፡ ቸልተኝነት ፡ ካላደረገ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ እውነተኛው ፡ ባለመብት ፡ ባይሆንም ፡ እንኳ ፡ ሰነዱ ፡ የባለገንዘብነትን ፡ ስም ፡ ለሰጠው ፤ የመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፤ የከፈለ ፡ ባለዕዳ ፡ ከዕዳው ፡ ነጻ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፯፻፲፯ ። መቃወሚያ ።

(፩) ዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ ሰነዱን ፡ በያዘው ፡ ሰው ፤ በሁለቱ ፡ የግል ፡ ግንኙነቶች ፡ ላይ ፡ በተመሠረቱት ፤ በሰነዱ ፡ አጻጻፍ ፡ ፎርምና ፡ እንዲሁም ፡ በሰነዱ ፡ ላይ ፡ በተጻፉት ፡ ቃሎች ፡ ካልሆነ ፡ ሌላ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊያቀርብበት ፡ አይችልም ።

(፪) እንዲሁም ፡ ፊርማን ፡ በማስመሰል ፡ የተሠራ ፤ ችሎታ ፡ ወይም ፡ ሰነዱ ፡ ሲወጣ ፡ የውክልና ፡ ሥልጣን ፡ ባለመኖሩ ፡ ወይም ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ ሁኔታዎች ፡ ባለመሙላታቸው ፡ የተነሡትን ፡ መቃወሚያዎች ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፫) አምጪው ፡ ይህን ፡ ሰነድ ፡ ባገኘበት ፡ ጊዜ ፡ ዕዳ ፡ ከፋዩን ፡ ለመጉዳት ፡ እያወቀ ፡ ያደረገው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ሰነዳን ፡ ይዘው ፡ ከነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ በግል ፡ ግንኙነቶች ፡ ላይ ፡ በተመሠረቱ ፡ ነገሮች ፡ ዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ ሰነዱ ፡ የያዘውን ፡ ሰው ፡ ሊቃወመው ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፯፻፲፰ ። በቅን ፡ ልቡና ፡ የመያዝ ፡ ውጤት ።

መዘዋወሩን ፡ በሚመሩት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ አንድ ፡ የሚተላለፍ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነድ ፡ እጁ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ መልስ ፡ ተብሎ ፡ ሊከሰስ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፯፻፲፱ ። የማስተላለፍ ፡ ሥርዐቶች ፡ ( ፎርም ) ።

ስለ ፡ መተላለፋቸው ፡ እንደ ፡ ተደነገጉት ፡ ፎርሞች ፤ የሚተላለፉ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶች ፡ ላምጪው ፡ ወይም ፡ ስሙ ፡ ለተጠቀሰው ፡ ወይም ፡ ለታዘዘለት ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፯፻፳ ። ሰነዶችን ፡ ስለ ፡ መለወጥ ።

(፩) የሚተላለፉ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶችን ፡ በያዘው ፡ ሰው ፡ ጥያቄና ፡ ኪሣራ ፤ ሰነዱን ፡ ያወጣው ፡ ሰው ፡ ለአምጪው ፡ የተባሉትን ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶች ፤ ስም ፡ በተጻፈባቸው ፡ ሰነዶች ፡ መለወጥ ፡ ይችላል ።

(፪) የሰነዶቹ ፡ መለወጥ ፤ በሕግ ፡ ወይም ፡ አውጪው ፡ በአደረገው ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ የስምምነት ፡ ቃል ፡ የተከለከለ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፳፫ ፡

BACK



በንኡስ ፡ ቊጥር ፡ ፪ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ መታወቂያውንና ፡ ችሎታውን ፡ ማስረዳት ፡ በሚችለው ፡ በአምጪው፡ ጥያቄና ፡ ኪሣራ ፡ ስም ፤ የተጻፈባቸውን ፡ ሰነዶች ፡ ለአምጪው ፡ በሚሉ ፡ ሰነዶች ፡ መለወጥ ፡ ይቻላል ።

ቊ ፡ ፯፻፷፩ ። ለአምጪው፡የሆነውን ፡ ሰነድ ፡ ማስተላለፍና ፡ በጁ ፡ የያዘውን ፡መብት፡ ስለማረጋገጥ ።

(፩) ለአምጪው ፡ የሚል ፡ ሰነድን ፡ የማስተላለፍ ፡ ተግባር ፡ ሰነዱን ፡ በመስጠት ፡ ይፈጸማል ።

(፪) ለአምጪው ፡ የሚል ፡ ሰነድ ፡ በእጁ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ይህነኑ ፡ በማቅረብ ፡ ብቻ ፡ በሰነዱ ፡ ውስጥ ፡ ለተነገረው ፡ ግዴታ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ለመሆኑ ፡ ማረጋገጫ ፡ ይሆነዋል ።

ቊ ፡ ፯፻፷፪ ። በስም ፡ የሆኑ ፡ ሰነዶች ፡ በእጁ ፡ የያዘውን ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ስለ፡ ማረጋገጥ።

በስም ፡ የሆነ ፡ ሰነድን ፡ በእጁ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ተጠቃሚ ፡ ለመሆኑ ፡ በሰነዱ፡ ላይና ፡ በአውጪው ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ መጻፉ ፤ በሰነዱም ፡ ላይ ፡ ለተነገረው ፡ ግዴታ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ለመሆኑ ፡ ማረጋገጫ ፡ ይሆነዋል ።

ቊ ፡ ፯፻፷፫ ። በስም ፡ የሆኑ ፡ ሰነዶችን ፡ ማስተላለፍ ።

(፩) በስም ፡ የሆነውን ፡ ሰነድ ፡ የማስተላለፍ ፡ ተግባር ፡ የሚፈጸመው ፤ የተላለፈለትን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ በሰነዱ ፡ ላይ ፡ በማግባትና ፡ በአውጪው ፡ መዝገብም ፡ ውስጥ ፡ በመጻፍ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ በአዲሱ ፡ አምጪ ፡ ስም ፡ የተጻፈ ፡ አዲስ ፡ ሰነድ ፡ በመስጠት ፤ መተላለፉ ፡ ሊፈጸም ፡ ይቻላል ፤ ይኸውም ፡ አስጣጥ ፡ በመዝገብ ፡ ውስጥ ፡ መመልከት ፡ አለበት ።

(፪) ሰነዱን ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ እንዲመዘገብ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ የተመዘገበው ፡ ሰነድ ፡ እንዲሰጠው ፡ የሚጠይቅ ፡ ሰው ፡ መታወቂያውንና ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ሊያዝዝበት ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ። ከነዚህ ፡ አሠራሮች ፡ አንዱን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ፡ የሚጠይቀው ፡ ሰነዱ ፡ የተላለፈለት ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሰነዱን ፡ ማቅረብና ፡ መብቱንም ፡ ባለሥልጣን ፡ ባዘጋጀው ፡ ጽሑፍ ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ።

(፫) በመዝገቡና ፡ በሰነዱ ፡ ላይ ፡ የሚደረጉት ፡ ጽሑፎች ፡ በሰነዱ ፡ አውጪ ፡ አላፊነትና ፡ ትጋት ፡ ይፈጸማሉ ።

(፬) ጥፋት ፡ ካላደረገ ፡ በቀር ፡ በዚሁ ፡ ቊጥር ፡ በተነገሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ የሰነድን ፡ ማስተላለፍ ፡ ተግባር ፡ የፈጸመ ፡ ሰነድ ፡ አውጪ ፡ ከአላፊነት ፡ ሁሉ ፡ ይድናል ።

**ቍ ፡ ፯፻፳፬ ። በትእዛዝ ፡ የሆኑ ፡ ሰነዶችን ፡ ማስተላለፍና ፡ በጁ ፡ የያዘውን ፡ ሰው ፡ መብት፡ ስለ፡ ማረጋገጥ።**

(፩) በትእዛዝ ፡ የሚለውን ፡ ሰነድ ፡ የማስተላለፍ ፡ ተግባር ፡ በጀርባው ፡ በመፈረምና ፡ ባለጥቅም ፡ ለሆነው ፡ ሰው ፡ ሰነዱን ፡ በመስጠት ፡ ይፈጸማል ።

(፪) በትእዛዝ ፡ የሚለውን ፡ ሰነድ ፡ በእጁ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፤ ሰነዱ ፡ በመጨረሻው ፡ በጀርባው ፡ ሲፈረም ፡ ስም ፡ ያልተሞላበትም ፡ ቢሆን ፡ ተከታትሎ ፡ ሳያቋርጥ ፡ በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ መፈረሙን ፡ በማሳየት ፡ በሰነዱ ፡ ላይ ፡ ለተነገረው ፡ ግዴታ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ለመሆኑ ፡ ማረጋገጫ ፡ ይሆነዋል ። በጀርባው ፡ ተጽፈው ፡ የተሰረዙትም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ላለው ፡ ጕዳይ ፡ እንዳልተጻፉ ፡ ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ። በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ስም ፡ ያልተሞላበት ፡ ሆኖ ፡ ከተፈረመ ፡ በኋላ ፡ በጀርባው ፡ ላይ ፡ ተከታትሎ ፡ ሌላ ፡ የተፈረመበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህንኑ ፡ የፈረመው ፡ ሰው ፡ ሰነዱን ፡ ያገኘው ፤ ስም ፡ ካልተሞላበት ፡ ፊርማ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፯፻፳፭ ። በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ የአፈራረም ፡ ፎርም ።**

(፩) በጀርባውም ፡ የመፈረም ፡ ተግባር ፤ በሰነዱ ፡ ላይ ፡ መጻፍና ፡ በጀርባውም ፡ በጻፈው ፡ ሰው ፡ መፈረም ፡ አለበት ።

(፪) የተፈረመለት ፡ ሰው ፡ ስም ፡ የሌለበት ፡ ቢሆንም ፡ በጀርባው ፡ የተፈረመ ፡ ጽሑፍ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነው ።

(፫) "ለአምጪው" ፡ ተብሎ ፡ በወረቀቱ ፡ ጀርባ ፡ የተፈረመ ፡ ፊርማ ፡ ስም ፡ እንዳልተሞላበት ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

(፬) በጀርባው ፡ የመፈረም ፡ ተግባር ፡ ያለ ፡ ሐተታ ፡ መሆን ፡ አለበት ። በጀርባው ፡ ላይ ፡ በሚጻፈው ፡ የተነገረ ፡ ሐተታ ፡ ሁሉ ፡ እንዳልተጻፈ ፡ ይቈጠራል ።

(፭) በከፊል ፡ በጀርባው ፡ ላይ ፡ መፈረም ፡ የማይጸና ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፯፻፳፮ ። የሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ ፊርማ ፡ ውጤቶች ።**

(፩) በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ መፈረም ፡ በሰነዱ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ ያስተላልፋል ።

(፪) የሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ ጽሑፍ ፡ ስም ፡ ያልተሞላበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አምጪው ፤

(ሀ) ባዶውን ፡ ቦታ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ መሙላት ፤

(ለ) ሰነዱን ፡ እንደገና ፡ ስም ፡ ሳይጽፍ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ማስተላለፍ ፤

(ሐ) ባዶውን ፡ ቦታ ፡ ሳይሞላና ፡ በጀርባው ፡ ሳይፈርም ፡ ሰነዱን ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገን ፡ መስጠት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፰፻፹፯ ። በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ የሚፈርም ፡ ሰው ፡ ግዴታዎች ።

ተቃራኒ ፡ ሕጋዊ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ወይም ፡ ከሰነዱ ፡ የተነሣ ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ የሚፈርመው ፡ ሰው ፡ ሰነዱን ፡ ያወጣው ፡ ሰው ፡ ስላልፈጸመው ፡ ግዴታ ፡ አላፊነት ፡ የለበትም ።

ቍ ፡ ፰፻፹፰ ። ገንዘብ ፡ ለመቀበል ፡ ወይም ፡ ለመወከል ፡ በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ መፈረም።

(፩) "ገንዘብ፡ ስለ፡ ማግባት"፤ "ስለ፡መቀበል"፤ " ስለመወከል፡ " ወይም፡ ይህን፡ የመሰለ ፡ ማናቸውም ፡ የውክልና፡ትእዛዝ ፡ አለበት ፡ የሚያሰኝ ፡ ጽሑፍ ፡ በሰነዱ፡ ጀርባ ፡ ተፈርሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አምጪው ፡ በሰነዱ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ ሊሠራባቸው ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በውክልና ፡ ስም ፡ ካልሆነ፡ በቀር ፡ ሰነዱን ፡ በጀርባው ፡ ላይ ፡ ፈርሞ ፡ ሊያስተላልፍ ፡ አይችልም ።

(፪) በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ የፈረመውን ፡ መቃወሚያ ፡ ከሚሆኑት ፡ መከራከሪያዎች ፡ በቀር ፡ በመወከል ፡ ባለጥቅም ፡ በሆነው ፡ ላይ ፤ ሰነድ ፡ አውጪው ፡ ሌላ ፡ መቃወሚያ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ።

(፫) በሰነድዱ ፡ ጀርባ ፡ በተፈረመ ፡ ሰነድ ፡ ውስጥ ፡ የገባ ፡ ውክልና ፤ በወካዩ ፡ መሞት ፡ ወይም ፡ በሚደርስበት ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ አይቀርም ።

ቍ ፡ ፰፻፹፱ ። በዋስትና ፡ ስም ፡ በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ መጻፍ ።

(፩) በሰነዱ፡ጀርባ ፡ የተጻፈው ፡ ጽሑፍ ፡ " ስለ ፡ ዋስትና ፡ ዋጋ ፡ " " ስለመያዣ፡ ዋጋ ፡ " ወይም ፡ መያዣን ፡ የሚያስከትል ፡ ሌላ ፡ ቃል ፡ ያለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አምጪው ፡ በሰነዱ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ ሊሠራባቸው ፡ ይችላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ በመጻፍ ፡ የሚያደርገው ፡ ማስተላለፍ፡ የሚቈጠረው፤ ውክልና፡ እንደ፡ ተደረገ፡ ማስተላለፍ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) ሰነዱ ፡ የተላለፈለት ፡ ሰው ፡ ሰነዱን ፡ ሲቀበል ፡ እያወቀ ፡ ዕዳ ፡ ከፋዩን ፡ ለመጕዳት ፡ ካላደረገ ፤ ሰነድ ፡ አውጪው ፡ ከሰነድ ፡ ፈራሚው ፡ ጋራ ፡ ባለው ፡ በግል ፡ ግንኙነቶች ፡ ላይ ፡ ከተመሠረቱት ፡ መከራከሪያዎች ፡ በቀር ፡ በዋስትና ፡ ስም ፡ ሰነዱ ፡ የተላለፈለትን ፡ ሰው ፡ ሊቃወምባቸው ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፰፻፺ ። የትእዛዝ ፡ ሰነድን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ በመፈረም፡ ከሚደረገው ፡ የማስተላለፍ ፡ አሠራር ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ የተገኘ ፡ የትእዛዝ ፡ ሰነድ ፤ የመደበኛ ፡ ማስተላለፍ ፡ ውጤት ፡ ብቻ ፡ ይኖረዋል ።

ቍ፡ ፰፻፺፩።የተበላሹ፡የወደሙ፤የጠፉ፤ወይም፡ የተሰረቁ፡ የሚተላለፉ፡የገንዘብ ፡ ሰነዶች ።

የሚተላለፉ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶች ፡ በተበላሹ ፤ በወደሙ ፤ በጠፉ ፡ ወይም ፡ በተሠረቁ ፡ ጊዜ፡ ሊከተሏቸው ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ሥርዐቶች ፡ በሕግ ፡ ይወሰናሉ ።

BACK



## አንቀጽ ፡ ፬ ።

## የንግድ ፡ ወረቀቶች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ውሳኔዎች ።

**ቍ ፡ ፯፻፴፪ ፡ ትርጓሜ ።**

(፩) የንግድ ፡ ወረቀቶች ፡ ማለት ፡ በገንዘብ ፡ መክፈል ፡ የሚሆነውን ፡ ግዴታ ፡ የሚናገሩ ፡ የሚተላለፉ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶች ፡ ናቸው ።

(፪) የሐዋላ፡ ወረቀትን ፤ ለመክፈል ፡ የተሰፋ ፡ ሰነድን ፤ ቼክን ፤ የመንገድ ፡ ቼክን፡ በዕቃ ፡ መጋዘን ፡ ለተቀመጡ ፡ ዕቃዎች ፡ ምስክር ፡ ወረቀቶችን ፡ ይህ ፡ የንግድ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ወረቀቶች ፡ ይቈጥራቸዋል ።

(፫) የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯፻፳፯ ፡ እስከ ፡ ፲፯፻፳፱ ፡ ድንጋጌ ዎች ፡ በዕቃ ፡ መጋዘን ፡ ለተቀመጡ ፡ ዕቃዎች ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፯፻፴፫ ። ሕጋዊ ፡ ችሎታ ።**

ማናቸውም ፡ በውል ፡ ለመግደድ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በንግድ ፡ ወረቀትም ፡ ለመግደድ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፯፻፴፬ ። ፊርማ ።**

(፩) በንግድ ፡ ወረቀት ፡ የተደረጉ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ ( ዴክላራሲዮን ) ፡ እነዚ ሁኑ፡ማስታወቂያዎች፡የሰጠው፡ሰው፡የጅ፡ጽሑፍ፡ፊርማ፡ሊኖርባቸው ፡ ይገባል ።

(፪) የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በእጅ ፡ ወይም ፡ በመኪና ፡ አሠራር ፡ ምልክት ፡ በሚያደርግ ፡ ዘዴ ፡ ማኅተምን ፡ በመሰለ ፡ ፊርማ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

(፫) አንድ ፡ ሰው ፡ ለመፈረም ፡ የአካል ፡ ችሎታ ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መፍ ቀዱ ፡ በሰነዱ ፡ ላይ ፡ በባለሥልጣኑ ፡ ፊት ፡ በተደረገ ፡ ማስታወቂያ ፡ መረጋ ገጥ ፡ አለበት ።

### ምዕራፍ ፡ ፪ ።

### ስለ ፡ ሐዋላ፡ ወረቀት ።

#### ክፍል ፡ ፩ ።

#### ስለ ፡ ሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ አጻጻፍና ፡ ፎርም ።

**ቍ ፡ ፯፻፴፭ ። መገለጽ ፡ ስለሚገባው ።**

በሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ መጻፍ ፡ ያለበት ፤

BACK



(ሀ) በሰነዱ ፡ ውስጥ ፡ ሰነዱ ፡ በተጻፈበት ፡ ቋንቋ ፡ "የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡" የሚል ፡ ቃል ፤
(ለ) የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ ሐተታ ፡ የሌለበት ፡ ትእዛዝ ፤
(ሐ) መክፈል ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ (ከፋዩ) ፤
(መ) የሚከፈልበት ፡ ጊዜ ፤
(ሠ) ገንዘቡ ፡ ሊከፈልበት ፡ የሚገባው ፡ ቦታ ፤
(ረ) ገንዘቡ ፡ የሚከፈለው ፡ ወይም ፡ እንዲከፈለው ፡ የታዘዘለት ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ወረቀቱ ፡ ለአምጪው ፡ መከፈል ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ ማመልከት፤
(ሰ) ወረቀቱ ፡ የተጻፈበት ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፤
(ሸ) ወረቀቱን ፡ የሚያወጣው ፡ ሰው ፡ (አውጪው) ፡ ፊርማ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፯፻፴፮ ። የአገላለጽ ፡ ጕድለት ።

ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ በ(ሀ) (ለ) (ሐ) ከተወሰኑት ፡ በቀር ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፴፭ ፡ ከተመለከቱት ፡ አገላለጾች ፡ አንድ ፡ ጕድለት ፡ ያለው ፡ ሰነድ ፡ እንደ ፡ ሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ ሊቈጠር ፡ አይችልም ።

(ሀ) የሚከፈልበት ፡ ጊዜ ፡ ያልተጻፈበት ፡ የሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ ወዲያውኑ ፡ የሚከፈል ፡ ሆኖ ፡ ይገመታል ።
(ለ) ልዩ ፡ ማመልከቻ ፡ የሌለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በከፋዩ ፡ ስም ፡ አጠገብ ፡ የተመለከተው ፡ ቦታ ፡ ገንዘቡ ፡ የሚከፈልበት ፡ ቦታና ፡ እንዲሁም ፡ የከፋዩ ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የሚቈጠር ፡ ይሆናል ።
(ሐ) የተጻፈበትን ፡ ቦታ ፡ የሚያመለክት ፡ የሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ በአውጪው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ አጠገብ ፡ ከተመለከተው ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ይገመታል ።

ቍ ፡ ፯፻፴፯ ። ልዩ ፡ ሁኔታዎች ።

(፩) የሀዋላው ፡ ወረቀት ፡ ለአውጪው ፡ ሰው ፡ ለራሱ ፡ የሚከፈል ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።
(፪) የሐዋላውን ፡ ወረቀት ፡ ያወጣው፡ሰው ፡ ራሱ ፡ ከፋይ ፡ ሊሆንበት ፡ ይችላል ።
(፫) የሀዋላውን ፡ ወረቀት ፡ ሳንድ ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ጥቅም ፡ ለማውጣት ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፯፻፴፰ ። መክፈያ ፡ ቦታ ፡ የተወሰነለት ፡ የሀዋላ ፡ ወረቀት ።

የሀዋላው ፡ ወረቀት ፡ በአንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ በከፋዩ ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ባለበት ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ ለመከፈል ፡ ይቻላል ።

BACK



### ቍ ፡ ፮፻፴፱ ። የወለድ ፡ ውል ።

(፩) እንደ ፡ ቀረበ ፡ በሚከፈል ፡ ወይም ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ በአንድ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በሚከፈል ፡ የሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ ውስጥ ፡ የሀዋላውን ፡ ወረቀት ፡ ያወጣው ፡ ገንዘቡ ፡ ወለድ ፡ የሚሰጥ ፡ እንዲሆን ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላል ፤ በማናቸውም ፡ ሌላ፡የሀዋላ ፡ ወረቀት፡ ውስጥ ፡ የወለድ ፡ ነገር፡ቢጻፍ፡እንዳልተጻፈ፡ ይቈጠራል ።

(፪) የወለዱ ፡ ልክ ፡ በወረቀቱ ፡ ውስጥ ፡ መመልከት ፡ አለበት ፤ ይህ ፡ ማመልከት ፡ ከሌለ ፡ ግን ፡ የውሉ ፡ ቃል ፡ እንዳልተጻፈ ፡ ይቈጠራል ።

(፫) ሌላ ፡ ቀን ፡ ካልተመለከተበት ፡ በቀር ፤ የሀዋላው ፡ ወረቀት ፡ ከተጻፈበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ወለዱ ፡ ይታሰባል ።

### ቍ ፡ ፮፻፵ ። በገንዘብ ፡ ልክ ፡ አጻጻፍ ፡ ስለሚገኝ ፡ ልዩነት ።

(፩) የሀዋላው ፡ ወረቀት ፡ በፊደልና ፡ በአኀዝ ፡ ተጽፎ ፡ ልዩነት ፡ በተገኘበት ፡ ጊዜ ፡ በፊደል ፡ የተጻፈው ፡ ገንዘብ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ይሆናል ።

(፪) በፊደልም ፡ ቢሆን ፡ በአኀዝ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የገንዘቡ ፡ ልክ ፡ የተጻፈበት ፡ የሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ ልዩነት ፡ ሲያመጣ ፡ በአነስተኛ ፡ የተጻፈው ፡ ገንዘብ ፤ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ይሆናል ።

### ቍ ፡ ፮፻፵፩ ። ውል ፡ ለመዋዋል ፡ (ለመገደድ) ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ፊርማ ።

የሀዋላው ፡ ወረቀት ፤ በሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ ለመገደድ ፡ ችሎታ ፡ በሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ተፈርሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ሐሰተኞች ፡ ፊርማዎች ፡ ወይም ፡ የሌሉ ፡ ሰዎች ፡ ፊርማዎች ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ የሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ የፈረሙትን ፡ ሰዎች ፡ ለማስገደድ ፡ የማይችሉ ፡ ፊርማዎች ፡ ወይም ፡ በነሱ ፡ ስም ፡ የተፈረመ ፡ ፊርማ ፡ ያለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሌሎቹ ፡ ግዴታ ፡ ለመግባት ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ፊርማ ፡ የሚጸና ፡ መሆኑ ፡ አይቀርም ።

### ቍ ፡ ፮፻፵፪ ። ሥልጣን ፡ ሳይኖር ፡ ስለ ፡ መፈረም ።

ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ እንደራሴ ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ ሥልጣን ፡ ሳይሰጠው ፡ በሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ፊርማውን ፡ ያደረገ ፤ በወረቀቱ ፡ መሠረት ፡ የተገደደ ፡ ይሆናል ፤ የከፈለም ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ በእንደራሴነት ፡ ፈረምኩለት ፡ የሚለው ፡ ሰው ፡ ሊኖረው ፡ የሚችለው ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ። ይኸውም ፡ መብት ፡ ከሥልጣኑ ፡ ተላልፎ ፡ ለሠራ ፡ እንደራሴ ፡ ይጸናል ።

### ቍ ፡ ፮፻፵፫ ። የሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ አውጪው ፡ አላፊነት ።

የሀዋላውን ፡ ወረቀት ፡ ከፋዩ ፡ ለመቀበሉና ፡ ለመክፈሉ ፡ የሀዋላውን ፡ ወረቀት ፡ ያወጣው ፡ ሰው ፡ ዋስ ፡ ነው ። ከፋዩ ፡ የሀዋላ ፡ ወረቀቱን ፡ ለመቀበሉ፡

BACK



አላፊ ፡ እንዳይሆን ፡ አውጪው ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላል ። ስለ ፡ አከፋፈሉ ፡ ዋስትና፡ ግን ፡ ከአላፊነት ፡ ለመዳን ፡ የተደረገው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ እንዳልተጻፈ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፯፻፵፬ ። ስም ፡ ያልተሞላበት ፡ የሀዋላ ፡ ወረቀት ።**

የሀዋላው ፡ ወረቀት ፡ በሚወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ጐደሎ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፤ ለአሞላሉ ፡ ከተደረጉት ፡ ስምምነቶች ፡ ተቃራኒ ፡ በመሆን ፡ የተሞላ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሀዋላውን ፡ ወረቀት ፡ ያገኘው ፡ በክፉ ፡ ልቡና ፡ ካልሆነ ፡ ወይም ፡ ሲያገኝ ፡ ከባድ ፡ ጥፋት ፡ ካላደረገ ፡ በቀር ፡ የእነዚህ ፡ ስምምነቶች ፡ አለመፈጸም ፡ በአምጪው ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆኑበት ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፯፻፵፭ ። ከቀኑ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ በኋላ ፡ ቀን ፡ የተደረገበት ፡ የሀዋላ ፡ ወረቀት ።**

(፩) እነዚህ ፡ ቀኖች ፡ በሀዋላው ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ በማታለል ፡ ሒሳብ ፡ ሳይሆን ፡ ወይም ፡ ከሕግ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ዓላማ ፡ ያለው ፡ ባለመሆን ፡ የተደረጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በፊት ፡ ወይም ፡ በኋላ ፡ ቀን ፡ የተደረገበት ፡ የሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ ፈራሽ ፡ አይሆንም ።

(፪) በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ቀን ፡ የተደረገበት ፡ ሰነድ ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ በዚያው ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተሰጠው ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ስለ፡ ማስተላለፍ ።

**ቍ ፡ ፯፻፵፮ ። አስተላለፉ ።**

(፩) ለአምጪው ፡ የሆነው ፡ የሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ ሰነዱን ፡ በመስጠት ፡ ብቻ ፡ ይተላለፋል ።

(፪) በተለይ ፡ በትእዛዝ ፡ የሚል ፡ ሆኖ ፡ ባይወጣም ፡ እንኳ ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ የሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ በጀርባው ፡ በመፈረም ፡ ይተላለፋል ፤ አውጪው ፡ በሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ ውስጥ ፡ "በትእዛዝ ፡ ያልሆነ ፡" የሚል ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የሚመሳሰል ፡ ቃል ፡ ያገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወረቀቱ ፡ ለመደበኛ ፡ አስተላለፍ ፡ በተደነገገው ፡ ፎርምና ፡ ይኸውም ፡ ከሚሰጠው ፡ ውጤት ፡ ጋራ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሊተላለፍ ፡ አይቻልም ።

(፫) ለተቀበለው ፡ ወይም ፡ ላልተቀበለው ፡ ከፋይ ፡ ቢሆንም ፡ ወይም ፡ ለአውጪው፡ ወይም ፡ ለማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፤ ወረቀቱ፡ በጀርባው ፡ ላይ ፡ በመፈረም ፡ ሊተላለፍ ፡ ይቻላል ።

(፬) እነዚህም ፡ ሰዎች ፡ የሀዋላውን ፡ ወረቀት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በጀርባው ፡ በመፈረም ፡ ሊያስተላልፉት ፡ ይችላሉ ።

BACK



## ቍ ፡ ፯፻፵፯ ። በወረቀቱ ፡ ጀርባ ፡ ለመፈረም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ።

(፩) በጀርባው ፡ የመጻፍና ፡ የመፈረም ፡ ተግባር ፡ ያለሐተታ ፡ መሆን ፡ አለበት ። በጀርባው ፡ ላይ ፡ በመጻፍ ፡ የተደረገ ፡ ምክንያታዊ ፡ ሁኔታ ፡ ሁሉ ፡ እንዳልተጻፈ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) በከፊል ፡ ለማስተላለፍ ፡ በጀርባው ፡ ላይ ፡ መፈረም ፡ የማይጸና ፡ ነው ።

(፫) "ለአምጪው"፡ ተብሎ ፡ በጀርባው ፡ የተፈረመ ፡ ፊርማ ፡ ስም፡ እንዳልተሞላበት ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

## ቍ ፡ ፯፻፵፰ ። በወረቀቱ ፡ ጀርባ ፡ የአፈራረም ፡ ፎርም ።

(፩) የጀርባውም ፡ ጽሑፍ ፡ በሀዋላው ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በተያያዘው ፡ አንድ ፡ ቅጠል ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ፤ በጀርባው ፡ የሚጽፈውም ፡ ሰው ፡ መፈረም ፡ አለበት ።

(፪) የጀርባውም ፡ ጽሑፍ ፡ ባለጥቅሙን ፡ ሳይጠራ ፡ ወይም ፡ በጀርባ ፡ በሚጻፈው ፡ ሰው ፡ ፊርማ ፡ ብቻ ፡ ( ስም ፡ ሳይሞላ ፡ እንደ ፡ መጻፍ ) ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ። የዚህ ፡ የመጨረሻው ፡ አጻጻፍ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ እንዲሆን ፡ የጀርባው ፡ ጽሑፍ ፡ በሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ ጀርባ ፡ ወይም ፡ ቅጥል ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

## ቍ ፡ ፯፻፵፱ ፡ የጀርባ ፡ ፊርማ ፡ ውጤት ።

(፩) የጀርባ ፡ ፊርማ ፡ በሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ የሚገኙትን ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ ያስተላልፋል ።

(፪) የጀርባውም ፡ ጽሑፍ ፡ ስም ፡ ያልተሞላበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አምጪው ፤

(ሀ) ስም ፡ ያልተሞላበትን ፡ በስሙ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ መሙላት ፤

(ለ) ለሌላ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በወረቀቱ ፡ ጀርባ ፡ ስም ፡ ሳይሞላ ፡ መፈረም ፤

(ሐ) ስም ፡ ሳይሞላና ፡ በጀርባው ፡ ሳይፈረም ፡ ወረቀቱን ፡ ለአንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ መስጠት ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፯፻፶ ። ዋስትናዎች ።

(፩) በጀርባ ፡ የሚጽፈው ፡ ሰው ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ለወረቀቱ ፡ መቀበልና ፡ ለመክፈል ፡ ዋስ ፡ ነው ።

(፪) በጀርባ ፡ የሚፈርመው ፡ ሰው ፡ አዲስ ፡ በጀርባ ፡ መፈረምን ፡ መከልከል ፡ ይችላል ። እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በወረቀቱ ፡ በጀርባው ፡ እየተፈረመ ፡ ለተላለፈላቸው ፡ ሰዎች ፡ ዋስትና ፡ የለበትም ።

ቍ ፡ ፰፻፶፩ ። አምጪውን ፡ በሕግ ፡ የታወቀ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

(፩) የመጨረሻው ፡ የጀርባ ፡ ፊርማ ፡ ስም ፡ ባይሞላበትም ፡ እንኳ ፡ አከታትሎ ፤ ባለማቋረጥ ፡ በጀርባ ፡ ፊርማ ፡ መብቱን ፡ ያገኘ ፡ መሆኑን ፡ ካረጋገጠ ፡ የሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ እንደ ፡ ታወቀ ፡ አምጪ ፡ ይገመታል ። የተሰረዙ ፡ የጀርባ ፡ ፊርማዎች ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ እንዳልተጻፉ ፡ ይቈጠራሉ ። አንድ ፡ የጀርባ ፡ ስም ፡ ሳይሞላ ፡ መጻፍ ፡ በሌላ ፡ በጀርባ ፡ ፊርማ ፡ የተከታተለ ፡ እንደ፡ሆነ፡ ይኸንኑ ፡ ወረቀት ፡ የፈረመው ፡ ሰው ፡ በጀርባ ፡ ስም ፡ ሳይሞላ ፡ በመፈረም ፡ ወረቀቱን ፡ እንዳገኘ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) አንድ ፡ ሰው ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ የሀዋላው ፡ ወረቀት ፡ የተወሰደበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አምጪው ፡ በክፉ ፡ ልቡና ፡ ያገኘው ፡ ካልሆነ ፡ ወይም ፡ ሲያገኘው ፡ ከባድ ፡ ጥፋት ፡ ካላደረገ ፡ በቀር ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ በተጠቀሰው ፡ ዐይነት ፡ መብቱን ፡ ያገኘ ፡ መሆኑ ፡ያረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወረቀቱ ፡ ሊወሰድበት ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፰፻፶፪ ። መከላከያዎች ።

አምጪው ፡ ወረቀቱን ፡ ባገኘ ፡ ጊዜ ፡ ዐውቆ ፡ ዕዳ ፡ ከፋዩን ፡ ለመጉዳት ፡ ካላደረገ ፡ በቀር ፤ በሀዋላው ፡ ወረቀት ፡ መሠረት ፡ እንዲከፍሉ ፡ የተጠየቁት ፡ ሰዎች ፡ ከአምጪው ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ ከቀድሞዎቹ ፡ አምጪዎች ፡ ጋራ ፡ ባላቸው ፡ በግል ፡ ግንኙነታቸው ፡ በተመሠረቱት ፡ መከላከያዎች ፡ አምጪውን ፡ ሊቃወሙት ፡ አይችሉም ።

ቍ ፡ ፰፻፶፫ ። በመወከል ፡ በጀርባ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ።

(፩) "ገንዘብ ፡ ስለ ፡ ማስገባት ፡" "ስለ ፡ መቀበል ፡" "በውክልና ፡" ወይም፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ማናቸውም ፡ ትእዛዝ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ የሚያሰኝ ፡ ጽሑፍ ፡ በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ ተጽፎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አምጪው ፡ በሰነዱ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ ሊሠራባቸው ፡ ይችላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በውክልና ፡ ስም ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሰነዱን ፡ በጀርባው ፡ ላይ ፡ ፈርሞ ፡ ሊያስተላልፍ ፡ አይችልም ።

(፪) እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በጀርባ ፡ ለሚጽፈው ፡ ወካይ ፡ መቃወሚያ ፡ በሚሆኑት ፡ መከላከያዎች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ተገዳጆቹ ፡ በአምጪው ፡ ሌላ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊያቀርቡበት ፡ አይችሉም ።

(፫) በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ በተጻፈ ፡ ሰነድ ፡ ውስጥ ፡ የገባ ፡ ውክልና ፡ በወካዩ ፡ መሞት፡ ወይም ፡ በሚደርስበት ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ ምክንያት ፡ አይቀርም ።

ቍ ፡ ፰፻፶፬ ። በመያዣ ፡ ስም ፡ በጀርባ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ።

(፩) በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ የተጻፈው ፡ ጽሑፍ ፡ "ስለ ፡ ዋስትና ፡ ዋጋ ፡" "ስለ፡መያዣ፡

ዋጋ ፡ ” የሚል ፡ ወይም ፡ መያዣን ፡ የሚያስከትል ፡ ሌላ ፡ ቃል ፡ ያለበት ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ አምጪው ፡ የሀዋላው ፡ ወረቀት ፡ የሚያስገኙትን ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ ሊሠራባቸው ፡ ይችላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እሱ ፡ በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ በመፈረም ፡ የሚያደርገው ፡ ማስተላለፍ ፡ የሚቈጠረው ፡ ስለ ፡ ውክልና ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ማስተላለፍ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) አምጪው ፡ ወረቀቱን ፡ በተቀበለ ፡ ጊዜ ፡ ዐውቆ ፡ ዕዳ ፡ ከፋዩን ፡ ለመጉዳት ፡ ካላደረገ ፡ በቀር ፡ ተገዳጆቹ ፡ በጀርባ ፡ ከፈረመው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ባሏቸው ፡ በግል፡ ግንኙነታቸው ፡ የተመሠረቱትን ፡ መከላከያዎች ፡ በአምጪው ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊያደርጓቸው ፡ አይችሉም ።

ቍ ፡ ፯፻፶፰ ። የመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፤ ወይም ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተደረገ፡ በኋላ፡ በጀርባ ፡ መፈረም ።

(፩) የመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ በጀርባ ፡ መፈረም ፤ ጊዜው ፡ ከማለፉ ፡ በፊት ፡ በጀርባ ፡ የመፈረምን ፡ ውጤቶች ፡ ይሰጣል ፤ የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ባለመክፈሉ ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተደረገ ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለመጻፍ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ በጀርባው ፡ ላይ ፡ መፈረም ፡ የመደበኛ ፡ ማስተላለፍ ፡ ውጤቶች ፡ ብቻ ፡ ይኖሩታል ።

(፪) ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ቀን ፡ የሌለበት ፡ በጀርባ ፡ መፈረም ፡ ባለመክፈሉ ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለማድረግ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ።

(፫) የመክፈሉ ፡ እንቢታ ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፵፩ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ መሠረት ፡ በከፋዩ ፡ ማስታወቂያ ፡ የተገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ቀን፡ የሌለበት፡ በጀርባ ፡ መፈረም፡ የመክፈል ፡ እንቢታው ፡ ከመነገሩ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፯፻፶፱ ። የጀርባው ፡ አፈራረም ፡ የተደረገበትን ፡ ቦታ፡የሚመለከት፡የሕሊና፡ግምት።

ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የጀርባው ፡ ፊርማ ፤ የጀርባው ፡ ፊርማ ፡ ቀን ፡ በተደረገበት ፡ ቦታ ፡ የሆነ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ እሺታ ።

ቍ ፡ ፯፻፷ ። ለእሺታ ፡ ማቅረብ ።

የመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ እስከሚደርስበት ፡ ቀን ፡ የሀዋላውን ፡ ወረቀት ፡ አምጪው ፡ ወይም ፡ ማንኛውም ፡ ያዢ ፡ ከፋዩ ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ መቀበሉን ፡ እንዲያረጋግጥበት ፡ በመደበኛ ፡ መኖሪያው ፡ ቦታ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

BACK



ቍ ፡ ፲፻፺፰ ። ማቅረብን ፡ ስለ ፡ ማዘዝ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ መከልከል ።

(፩) በሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ ውስጥ ፡ ሁሉ ፤ ጊዜውን ፡ በመወሰን ፡ ወይም ፡ ባለመወሰን ፡ ለእሺታ ፡ መቅረብ ፡ ይገባዋል ፡ ብሎ ፡ አውጪው ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ለማግባት ፡ ይችላል ።

(፪) በአንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ አድራሻ ፡ ወይም ፡ የከፋዩ ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ባልሆነ ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ የሚከፈል ፤ ወይም ፡ ከቀረበበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሲቀርብ፡ የሚከፈል ፡ የሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ ካልሆነ ፡በቀር ፡ አውጪው ፤ በወረቀቱ ፡ ውስጥ ፡ ለእሺታ ፡ ማቅረብን ፡ መከልከል ፡ ይችላል ።

(፫) እንዲሁም ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ለእሺታ ፡ ማቅረብ ፡ ሊደረግ ፡ አይቻልም ፡ ብሎ ፡ ሊጽፍ ፡ ይችላል ።

(፬) አውጪው ፡ ለእሺታ ፡ መቀበል ፡ ማቅረብ ፡ አይቻልም ፡ ብሎ ፡ ከላስታወቀ፡ በቀር ፡ በጀርባ ፡ የሚፈርመው፡ ሰው ፡ ሁሉ፡ ጊዜውን ፡ በመወሰን ፡ ወይም ፡ ባለመወሰን ፡ ወረቀቱ ፡ ለእሺታ ፡ መቅረብ ፡ ይገባዋል ፡ ብሎ ፡ መጻፍ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፻፺፱ ። ሲቀርቡ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሚከፈሉትን ፡ የሀዋላ ፡ ወረቀቶች ፡ ስለ ፡ እሺታ ፡ የማቅረብ ፡ ግዴታ ።

(፩) ሲቀርቡ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚከፈሉት ፡ የሀዋላ ፡ ወረቀቶች ፤ ቀን ፡ ከተደረገባቸው ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ለእሺታ ፡ መቅረብ ፡ ይገባቸዋል ።

(፪) አውጪው ፡ ይህን ፡ የመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ለማሳጠር ፡ ወይም ፡ ለማስረዘም ፡ ይችላል ።

(፫) በጀርባ ፡ የሚፈርሙት ፡ ሰዎች ፡ እነዚህን ፡ ጊዜዎች ፡ ለማሳጠር ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፲፻፻ ። ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ለእሺታ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

(፩) ከፋዩ ፡ መጀመሪያ ፡ ለእሺታ ፡ በቀረበለት ፡ ማግሥት ፡ የሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ለሁለተኛ ፡ ለእሺታ ፡ እንዲቀርብለት ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ፤ ይህ ፡ የሁለተኛው ፡ ማቅረብ ፡ በመከፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ውስጥ ፡ ካልተመለከተ ፡ በቀር፡ ባለጥቅሞቹ ፡ ሳቀረቡት ፡ ጥያቄ ፡ የሚገባው ፡ አልተደረገልንም ፡ ለማለት ፡ አይችሉም ።

(፪) ለእሺታ ፡ የቀረበውን ፡ ወረቀት ፡ አምጪው ፡ በከፋዩ ፡ እጅ ፡ ለመተው ፡ አይገደድም ።

ቍ ፡ ፲፻፻፩ ። ስለ ፡ እሺታ ፡ ፎርም ።

(፩) እሺታው ፡ በሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ይጻፋል ። « ተቀብዬዋለሁ » ፡ በሚል ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በሚመስል ፡ ሌላ ፡ ቃል ፡ እሺታው ፡ መገለጽ ፡ አለበት ። ከፋዩም ፡ ይፈርምበታል ። በወረቀቱ ፡ ጀርባ ፡ የሚደረገው ፡ የከፋዩ ፡ ፊርማ ፡ ስለ ፡ እሺታ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) የሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ ሲቀርብ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሚከፈል ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ በልዩ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለእሺታ ፡ መቅረብ ፡ ያለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አምጪው ፡ በሚያቀርብበት ፡ ቀን ፤ ቀኑ ፡ ይጻፍልኝ ፡ ብሎ ፡ ካላስገደደ ፡ በቀር ፡ እሺ ፡ በተባለበት ፡ ጊዜ ፡ የእሺታው ፡ ቀን ፡ መጻፍ ፡ አለበት ፤ ይህ ፡ ከሌለ ፡ ግን ፡ አምጪው ፡ በጀርባ ፡ በሚፈርሙት ፡ ሰዎችና ፡ በአውጪው ፡ ላይ ፡ የአቤቱታ ፡ መብቶቹን ፡ ጠብቆ ፡ ለማኖር ፡ በሚገባ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በተደረገ ፡ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ይህን ፡ ጕድለት ፡ ማጻፍ ፡ አለበት ።

ቊ ፡ ፯፻፺፪ ። በከፊል ፡ የተሰጠ ፡ እሺታ ።

(፩) እሺታ ፡ ያለ ፡ ሐተታ ፡ የሚደረግ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከፋዩ ፡ የሚከፍለውን ፡ ገንዘብ ፡ አሳንሶ ፡ ለመቀበል ፡ ይችላል ።

(፪) በእሺታው ፡ ጊዜ ፡ በዋላ ፡ ወረቀት ፡ አገላለጾች ፡ ላይ ፡ ማናቸውንም ፡ መለዋወጥ ፡ ማድረግ ፡ እሺታውን ፡ እንቢ ፡ ከማለት ፡ ይቈጠራል ፤ የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እሺ ፡ ባዩ ፡ በእሺታው ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ጽሑፎች ፡ መሠረት ፡ ይገደዳል ።

ቊ ፡ ፯፻፺፫ ። መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታና ፡ የመክፈያው ፡ ቦታ ።

(፩) የከፋዩ ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ሳይሆን ፡ አከፋፈሉ ፡ የሚደረግበትን ፡ ያንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ቦታ ፡ ለይቶ ፡ ሳይወስን ፡ በሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ ውስጥ ፡ የሚከፈልበትን ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ አውጪው ፡ ያመለከተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እሺታው ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ ከፋዩ ፡ ቦታውን ፡ ሊያመለክት ፡ ይችላል ። ይህ ፡ ማመልከት ፡ ያልተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መክፈሉ ፡ በሚደረግበት ፡ ቦታ ፡ እሺ ፡ ባዩ ፡ ራሱ ፡ ለመክፈል ፡ እንደ ፡ ተገደደ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ወረቀቱ ፡ በከፋዩ ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ የሚከፈል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እሺታውን ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ገንዘቡ ፡ ሊከፈል ፡ ከሚገባበት ፡ ቦታ ፡ ከፋዩ ፡ ሌላ ፡ አድራሻ ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ።

ቊ ፡ ፯፻፺፬ ። ስለ ፡ እሺታ ፡ ውጤቶች ።

(፩) እሺታውን ፡ በመስጠቱ ፡ ከፋዩ ፡ የሀዋላውን ፡ ወረቀት ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ገንዘቡን ፡ ለመክፈል ፡ ይገደዳል ።

(፪) ሳይከፍል ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አምጪው ፡ ራሱ ፡ አውጪው ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፤ እሺ ፡ ባዩን ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፶፩ ፡ እና ፡ ፯፻፶፪ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ለማስገደድ ፡ በሚችልበት ፡ ሁሉ ፡ የሀዋላው ፡ ወረቀት ፡ የሚሰጠውን ፡ መብት ፡ ለማግኘት ፡ በቀጥታ ፡ ለመክሰስ ፡ ይችላል ።

ቊ ፡ ፯፻፺፭ ። ስለ ፡ ተሰረዘ ፡ እሺታ ።

(፩) የሐዋላውን ፡ ወረቀት ፡ ከመመለሱ ፡ በፊት ፡ በሀዋላው ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡

እሺታውን ፡ የጻፈው ፡ ከፋዩ ፡ እሺታውን ፡ የሰረዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እሺታውን ፡ እንቢ ፡ እንዳለ ፡ ይቈጠራል ። ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ መሰረዙ ፡ ሰነዱ ፡ ከመመለሱ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ከፋዩ ፡ እሺታውን ፡ በጽሑፍ ፡ ላምጪው ፡ ወይም ፡ የሀዋላውን ፡ ወረቀት ፡ ለፈረመው ፡ ለማናቸውም ፡ ሰው ፡ ያስታወቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በእሺታው ፡ ጽሑፎች ፡ መሠረት ፡ በነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ በኩል ፡ የተገደደ ፡ ይሆናል ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

## ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ማለት ፡ (አቫል) ።

### ቍ ፡ ፯፻፳፱ ። ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባዮች ።

(፩) የሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

(፪) ይኸውም ፡ ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ለማለት ፡ በአንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ወረቀቱን ፡ በሚፈርመው ፡ ሰው ፡ የተሰጠ ፡ ይሆናል ።

### ቍ ፡ ፯፻፴ ። ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ የማለት ፡ ሥርዐት ፡ (ፎርም) ።

(፩) በሀዋላ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ቅጥል ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ የተሰጠበትን ፡ ቦታ ፡ በሚያመለክት ፡ ልዩ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺታ ፡ ይሰጣል ።

(፪) ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺታ ፡ አሰጣጥ ፡ «ለመክፈል ፡ ዋስ ፡ ነኝ» ፡ በሚል ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ በሌላ ፡ ተመሳሳይ ፡ በሆነ ፡ ቃል ፡ ይገለጻል ፤ ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባዩም ፡ ቀጥሎ ፡ ይፈርምበታል ።

(፫) በሀዋላው ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ በተደረገው ፡ ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ ፊርማ ፡ ብቻ ፡ ዋስትናው ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ መሠረት ፡ እንደ ፡ ተሰጠ ፡ ይቈጠራል ።

(፬) የመክፈል ፡ ዋስትናው ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ ለማን ፡ ጥቅም ፡ እንደ ፡ ተሰጠ ፡ ማመልከት ፡ አለበት ። ይህ ፡ ማመልከት ፡ ከሌለ ፡ ግን ፡ ለአውጪው ፡ እንደ ፡ ተሰጠ ፡ ይቈጠራል ።

### ቍ ፡ ፯፻፴፩ ። ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ የማለት ፡ ውጤቶች ።

(፩) ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ እንደ ፡ ባለዕዳው ፡ ዐይነት ፡ ልክ ፡ የሚገደድ ፡ ይሆናል ።

(፪) በፎርም ፡ ጕድለት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ሁሉ ፡ ዋስ ፡ የሆነበት ፡ ግዴታ ፡ ፈራሽ ፡ ቢሆን ፡ እንኳ ፡ ውል ፡ የገባበት ፡ ቃል ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

(፫) የሀዋላውን ፡ ወረቀት ፡ ሲከፍል ፡ ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ በሀዋላው ፡ ወረቀት ፡ መሠረት ፡ ዋስትና ፡ በሰጠለት ፡ ባለዕዳና ፡ እንዲሁም ፡ ከሀዋላው ፡ ወረቀት ፡ የተነሣ ፡ ለዚሁ ፡ ባለዕዳ ፡ ተገዳጅ ፡ በሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መብቶች ፡ ያገኛል ።

## ክፍል ፡ ፭ ።

## ለመክፈል ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።

### ቍ ፡ ፯፻፸፱ ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ለመክፈያ ፡ የተወሰኑ ፡ ጊዜዎች ።

(፩) አንድ ፡ የሀዋላ ፡ ወረቀት ፤
 (ሀ) እንደ ፡ ቀረበ ፤
 (ለ) ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፤
 (ሐ) ከተጻፈበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፤
 (መ) ቍርጥ ፡ በሆነ ፡ ቀን ፤
 እንዲከፈል ፡ ሆኖ ፡ ለማውጣት ፡ ይቻላል ።

(፪) በሌሎች ፡ የመክፈያ ፡ ጊዜዎች ፡ ወይም ፡ በሚከታተሉ ፡ የመክፈያ ፡ ጊዜዎች ፡ የሆኑ ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀቶች ፡ የማይጸኑ ፡ ናቸው ።

### ቍ ፡ ፯፻፹ ። እንደ ፡ ቀረበ ፡ የሚከፈልበት ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ።

(፩) እንደ ፡ ቀረበ ፡ የሚከፈልበት ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የሚከፈል ፡ ነው ። ከተጻፈበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንዲከፈልበት ፡ መቅረብ ፡ ይገባዋል ። አውጪው ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ለማሳጠር ፡ ወይም ፡ ለማርዘም ፡ በወረቀቱ ፡ ላይ ፡ ለመጻፍ ፡ ይችላል ። እነዚህን ፡ ጊዜዎች ፡ በጀርባ ፡ የሚፈርሙት ፡ ሰዎች ፡ ሊያሳጥሯቸው ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንደ ፡ ቀረበ ፡ የሚከፈልበትን ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ አውጪው ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ከማለፉ ፡ በፊት ፡ እንዲከፈል ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ፡ ብሎ ፡ ለመጻፍ ፡ ይችላል ። እንዲሁም ፡ ሲሆን ፡ የማቅረቢያው ፡ ጊዜ ፡ የሚጀመረው ፡ ከዚሁ ፡ ከተወሰነው ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፯፻፹፩ ። ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚከፈልበት ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ።

(፩) ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚከፈልበት ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ የመክፈያው ፡ ቀን ፡ የሚወሰነው ፡ እሺታው ፡ በተደረገበት ፡ ወይም ፡ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያው ፡ በተጻፈበት ፡ ቀን ፡ ነው ።

(፪) የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እሺ ፡ ባዩን ፡ ለሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ቀን ፡ የሌለበት ፡ እሺታ ፤ ለእሺታ ፡ ማቅረብ ፡ በተደነገገው ፡ መጨረሻ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተሰጠ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፯፻፹፪ ። የጊዜ ፡ አቈጣጠር ።**

(፩) ከወጣበት ፡ ወይም ፡ ከቀረበበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ካንድ ፡ ወይም ፡ ከብዙ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ የሚከፈልበት ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ የመክፈያው ፡ ቀን ፡ በሚከፈል በት ፡ ወር ፡ በቍጥር ፡ ተመሳሳይ ፡ በሆነው ፡ በሚገናዘብበት ፡ ቀን ፡ መሆን ፡ አለ በት ፤ ይህ ፡ ተመሳሳይ ፡ ቀን ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የመክፈያው ፡ ቀን ፡ በዚሁ ፡ በመክፈያው ፡ ወር ፡ መጨረሻ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) ከወጣበት ፡ ወይም ፡ ከቀረበበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ከአንድ ፡ ወይም ፡ ከብዙ ፡ ወሮች ፡ ተኩል ፡ በኋላ ፡ ለሚከፈልበት ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ አስቀድሞ ፡ የሚ ቈጠሩት ፡ ሙሉ ፡ ወሮቹ ፡ ናቸው ።

(፫) የሚከፈልበት ፡ ቀን ፡ በወሩ ፡ መጀመሪያ ፤ በወሩ ፡ መካከል ፤ በወር ፡ መጨ ረሻ ፡ ቀን ፡ ተብሎ ፡ የተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እነዚህ ፡ ቃላት ፡ የሚያመለክቱት ፤ የወሩን ፡ መጀመሪያ ፡ ቀን ፤ ዐሥራ ፡ አምስተኛውን ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ የወሩን ፡ መጨረሻ ፡ ቀን ፡ ነው ።

(፬) «ስምንት ፡ ቀን» ፡ ወይም ፡ «ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን» ፡ የሚሉት ፡ ቃሎች ፡ የሚያመለክቱት ፤ የአንድ ፡ ወይም ፡ የሁለት ፡ ሳምንት ፡ ሳይሆን ፡ የስምንት ፡ ወይም ፡ የዐሥራ ፡ አምስት ፡ ሙሉ ፡ ቀኖችን ፡ ቍጥር ፡ ነው ።

(፭) የወር ፡ እኩሌታ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ቍጥርን ፡ ያመለክታል ።

**ቍ ፡ ፯፻፹፫ ። ስለ ፡ ቀን ፡ መቈጠሪያዎች ፡ ልዩነት ።**

(፩) የሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ የሚከፈልበት ፡ የተወሰነው ፡ ቀን ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ሆኖ ፤ የሚከፈልበት ፡ ቦታ ፡ ቀን ፡ መቍጠሪያ ፡ ከወጣበት ፡ ቦታ ፡ ቀን ፡ መቍጠሪያ ፡ ልዩነት ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሚከፈልበት ፡ ቦታ ፡ የቀን ፡ መቍጠሪያ ፡ መሠረት ፡ የመክፈያው ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተወሰነ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) አንድ ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ሁለት ፡ ልዩ ፡ የቀን ፡ መቈጠሪያ ፡ ባላቸው ፡ ቦታ ዎች ፡ መካከል ፤ ከወጣበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ እንዲከፈል ፡ ሆኖ ፡ የወጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የወጣበት ፡ ቀን ፡ በመክፈያው ፡ ቦታ ፡ ቀን ፡ መቍ ጠሪያ ፡ በሚገናዘብበት ፡ ቀን ፡ ይሆናል ፤ የመክፈያውም ፡ ቀን ፡ በዚሁ ፡ መሠ ረት ፡ ይወሰናል ።

(፫) የሐዋላ ፡ ወረቀቶችን ፡ ማቅረቢያ ፡ ቀኖች ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ እና ፡ ፪ ፡ በተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይታሰባሉ ።

(፬) በሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ የወረቀቱ ፡ አገ ላለጽ ፡ ልዩ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ስለ ፡ ጊዜው ፡ አቈጣጠር ፡ ያመለከቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ያሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚነት ፡ የላቸውም ።

## ክፍል ፡ ፮ ።

## ስለ ፡ አከፋፈል ።

**ቍ ፡ ፯፻፸፬ ። ለማስከፈል ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።**

(፩) ቍርጥ ፡ በሆነ ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ከተጻፈበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ፡ ወይም ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚከፈልበት ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ አምጪ ፤ ተካፋይ ፡ በሆነበት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ከሚከተሉት ፡ ሁለት ፡ የሥራ ፡ ቀኖች ፡ ባንዱ ፡ ለማስከፈል ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀትን ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) በመንግሥት ፡ በተፈቀደ ፡ አንድ ፡ ገንዘብ ፡ ነክ ፡ ለሆነ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ማቅረብ ፤ ለማስከፈል ፡ እንደ ፡ ማቅረብ ፡ ሆኖ ፡ ይገመታል ።

**ቍ ፡ ፯፻፸፭ ። ደረሰኝ ፤ በከፊል ፡ የሚሆን ፡ አከፋፈል ።**

(፩) ከፋዩ ፡ የሐዋላውን ፡ ገንዘብ ፡ ሲከፍል ፡ በሐዋላው፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ የደረሰ ኙን ፡ ፊርማ ፡ እንዲሰጠው ፡ አምጪውን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) አምጪው ፡ በከፊል ፡ የሆነውን ፡ አከፋፈል ፡ እንቢ ፡ ማለት ፡ አይችልም ።

(፫) አከፋፈሉ ፡ በከፊል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከፋዩ ፡ የዚህ ፡ አከፋፈል ፡ ጽሑፍ ፡ በወረቀቱ ፡ ላይ ፡ እንዲደረግና ፡ የደረሰኝ ፡ ሰነዱም ፡ እንዲሰጠው ፡ ለማስገደድ፡ ይችላል ።

(፬) በሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ በየጊዜው ፡ የተደረጉ ፡ የቅናሽ ፡ አከፋፈሎች ፡ አውጪውንና ፡ በጀርባ ፡ የሚፈርመውን ፡ ሰው ፡ በተከፈለው ፡ መጠን ፡ ከዕዳ ቸው ፡ ነጻ ፡ ያደርጋቸዋል ።

(፭) ለቀረው ፡ ገንዘብ ፡ አምጪው፡ በሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ የመክፈል ፡ እን ቢታ ፡ ማስደረግ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፯፻፸፮ ። አስቀድሞ ፡ ስለ ፡ መክፈልና ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ መክፈል ።**

(፩) አንድ ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ አምጪ ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የሚከፈለ ውን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲቀበል ፡ ሊገደድ ፡ አይቻልም ።

(፪) ከተወሰነውም ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የሚከፍል ፡ ከፋይ ፡ አላፊነቱ ፡ የራሱ ፡ ነው ።

(፫) አንድ ፡ ማታለል ፡ ወይም ፡ ከባድ ፡ ጥፋት ፡ በርሱ ፡ በኩል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በተ ወሰነው ፡ ጊዜ ፡ የከፈለ ፡ ሰው ፡ በሚገባ ፡ ነጻ ፡ ነው ። እሱም ፡ በጀርባ ፡ የፈረሙ ትን ፡ ሰዎች ፡ ፊርማ ፡ ሳይሆን ፡ በጀርባ ፡ ያሉትን ፡ ፊርማዎች ፡ ደንበኛነታቸ ውን ፡ ለመመርመር ፡ የተገደደ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፯፻፸፯ ። በውጭ ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መክፈል ።**

(፩) በሚከፈልበት ፡ አገር ፡ ሳይሆን ፡ በሌላው ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ በአንድ ፡ ሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ የተጻፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገንዘቡ ፤ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ መክፈያ ፡ ቀን ፡ ባለው ፡ ዋጋ ፡ በሚከፈልበት ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ ሊከፈል ፡ ይቻላል ፤ ዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ ከመክፈል ፡ የዘገየ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አምጪው ፡ በመረጠው ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ በሚከፈልበት ፡ ቀን ፡ ባለው ፡ ምንዛሬ ፡ የሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ገንዘብ ፡ በሚከፈልበት ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈለው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) የውጭ ፡ አገሩን ፡ ገንዘብ ፡ ዋጋ ፡ በሚከፈልበት ፡ አገር ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል ። አውጪው ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ በወረቀቱ ፡ ውስጥ ፡ በተወሰነ ፡ ምንዛሬ ፡ መሠረት ፡ ይታሰባል ፡ ብሎ ፡ ለመዋዋል ፡ ይችላል ።

(፫) በአንድ ፡ በተለየ ፡ ገንዘብ ፡ ይከፈላል ፡ ብሎ ፡ አውጪው ፡ የጽሑፍ ፡ ቃል ፡ ያገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገሩት ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ አይሆኑም ፤ (የመጨረሻው ፡ አከፋፈል ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ እንዲሆን ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡)

(፬) በሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ ገንዘብ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ስም ፡ ባለው ፡ ገንዘብ ፡ የተመለከተ ፡ ሆኖ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በወጣበትና ፡ በሚከፈልበት ፡ አገር ፡ ዋጋው ፡ ልዩነት ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፤ የሚከፈልበትን ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ ለመጥቀስ ፡ እንደ ፡ ታሰበ ፡ ይገመታል ።

**ቍ ፡ ፯፻፸፰ ። ስለ ፡ ማስረከብ ።**

በቍጥር ፡ ፯፻፸፩ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ለማስከፈል ፡ የሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ያልቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በአምጪው ፡ ኪሣራና ፤ ሙሉ ፡ ኀላፊነት ፡ ማናቸውም ፡ ባለዕዳ ፡ በመንግሥት ፡ ለተፈቀደ ፡ አንድ ፡ ገንዘብ ፡ ነክ ፡ ለሆነ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ገንዘቡን ፡ በአደራ ፡ ለማስረከብ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፯፻፸፱ ። መክፈልን ፡ ስለ ፡ መቃወም ።**

የሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ካልጠፋ ፡ ወይም ፡ አምጪው ፡ ካልከሠረ ፡ በቀር ፡ መክፈልን ፡ መቃወም ፡ አይፈቀድም ።

## ክፍል ፡ ፯ ።

## የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ እሺ ፡ ባልተባለና ፡ ባልተከፈለ ፡ ጊዜ ፡ አቤቱታዎችን ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

**ቍ ፡ ፯፻፹ ። የአምጪው ፡ አቤቱታዎች ።**

አምጪው ፤ በጀርባው ፡ በፈረሙት ፡ ሰዎች ፤ በአውጪውና ፡ በሌሎች ፡ ተገዳጆች ፡ ላይ ፡ አቤቱታዎቹን ፡ ሊሠራባቸው ፡ የሚችለው ፤

(፩) የገንዘቡ ፡ መከፈያ ፡ ጊዜ ፡ ደርሶ ፤ ገንዘቡ ፡ ያልተከፈለ ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡
(፪) የመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ባይደርስም ፡ የሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ያልተከፈለው ፤
(ሀ) እሺታው ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንቢ ፡ የተባለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤
(ለ) እሺ ፡ ቢልም ፡ ባይልም ፡ ከፋዩ ፡ የከሠረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በፍርድ ፡ ባይረጋገጥም ፡ እንኳ ፡ ዕዳዎቹን ፡ መክፈል ፡ ያቋረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፤ ንብረቶቹ ፡ እንዲያዙ ፡ ተደርጎ ፡ ፍሬ ፡ ሳይሰጥ ፡ የቀረ ፡ ቢሆንም ፤ ወይም ፡
(ሐ) እሺታ፡የማይሰጥበትን ፡ የሐዋላ፡ወረቀት፡ያወጣው ፡ የከሠረ፡እንደ፡ሆነ፡ነው።

## ቍ ፡ ፯፻፹፩ ። የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፤ ሁናቴዎችና ፡ ጊዜዎች ።

(፩) እሺታን ፡ ወይም ፡ መክፈልን ፡ እንቢ ፡ ማለት ፡ በባለሥልጣን ፡ ጽሑፍ ፡ መረጋገጥ ፡ አለበት ፤ (እሺታን ፡ እንቢ ፡ ስለ ፡ ማለት ፡ ወይም ፡ ለአለመክፈሉ ፡ ማስታወቂያ ፡ ስለ ፡ ማስደረግ) ።

(፪) አውጪው ፡ በሰነዱ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ በባለሥልጣን ፡ የተጻፈ ፡ የመክፈል፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ እንዲደረግለት ፡ ካላስገደደ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ በሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ቀን ፡ ለይቶ ፡ በተጻፈ ፡ መግለጫ ፡ ሊተካ ፡ ይችላል ።

(፫) እሺ ፡ ባልተባለ ፡ ጊዜ ፡ የሚደረገው ፡ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቅ ፡ ለእሺታ ፡ ማቅረብ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መደረግ ፡ ይገባዋል ። በቍጥር ፡ ፯፻፹ ፤ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ የመጀመሪያው ፡ ማቅረብ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ የመጨረሻ ፡ ቀን ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቅ ፡ በማግሥቱም ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

(፬) በቍርጥ ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ከተጻፈበት ፡ እንሥቶ ፡ በተወሰነ፡ጊዜ፡ወይም፡ከቀረበ፡ በኋላ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚከፈል ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ያልተከፈለ ፡ እንደ፡ሆነ፤ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቅ ፡ የሚደረገው ፡ የሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ የሚከፈልበትን ፡ ቀን ፡ በሚከተሉት ፡ በሁለት ፡ የሥራ ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ። እንደ ፡ ቀረበ ፡ የሚከፈል ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እሺታ ፡ ባልተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ለሚደረገው ፡ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቅ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተደነገጉ ፡ ሁናቴዎች ፡ ላለመቀበልም ፡ ለሚደረገው ፡ ማስታወቂያ ፡ ተፈጻሚ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።

(፭) እሺ ፡ ስላልተባለ ፡ የተደረገው ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ የሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ እንዲከፈል ፡ ከማቅረብና ፡ ስላለመከፈሉም ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂ ፡ ከማጻፍ ፡ ያድናል ።

(፮) እሺ ፡ ቢልም ፡ ባይልም ፡ ተከፋዩ ፡ ዕዳውን ፡ መክፈል ፡ ያቋረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የንብረቱ ፡ መያዝ ፡ ፍሬ ፡ ያልሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከፋዩ ፡ እንዲከፍለው ፡ አምጪው ፡ ወረቀቱን ፡ ካላቀረበና ፡ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ካላጻፈ ፡ አቤቱታዎቹን ፡ ሊሠራባቸው ፡ አይችልም ።

(፪) እሺ ፡ ቢልም ፡ ባይልም ፡ ከፋዩ ፡ መክሠሩ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንዲሁም ፡ እሺ ፡ የማይባልበት ፡ ወረቀት ፡ አውጪ ፡ የሆነው ፡ መክሠሩ ፡ የተረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መክሠሩን ፡ የሚያረጋግጠውን ፡ ፍርድ ፡ ካሳየ ፡ አምጪው ፡ በአቤቱታው ፡ እንዲሠራባቸው ፡ ለመፍቀድ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፯፻፹፱ ። ደንበኛ ፡ የሆነ ፡ ባለሥልጣን ።

የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ባንድ ፡ ውል ፡ አዘጋጅ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ (ሬጂስትራር) ፡ መዘጋጀት ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፯፻፺ ። የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያው ፡ የሚዘጋጅበት ፡ ቦታ ።

የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሊዘጋጅ ፡ የሚገባው ፤

(ሀ) የሐዋላውን ፡ ወረቀት ፡ ሊከፍል ፡ በሚገባው ፡ ሰው ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ በታወቀው ፡ የመጨረሻ ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታው ፤

(ለ) በአስፈላጊው ፡ ጊዜ ፡ ለመክፈል ፡ በሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ሰዎች ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፤

(ሐ) በጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ለመክፈል ፡ እሺ ፡ ባለ ፡ በሦስተኛ ፡ ሰው ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ፡ቦታ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ሁሉም ፡ የሚደረገው ፡ በአንድ ፡ ጽሑፍ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፯፻፺፩ ። አስፈላጊ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ መግለጫዎች ።

(፩) የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያው ፡ ውስጥ ፡ ሊገኝ ፡ የሚገባው ፤

(ሀ) የሰውዬው ፡ ወይም ፡ የንግዱ ፡ ማኅበር ፡ ስም ፤ ለማንና ፡ በማን፡ላይ፡እንደ ፡ ተዘጋጀ ፤

(ለ) የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ የተደረገበት ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ከሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ የተነሣ ፡ ያለውን ፡ ግዴታ ፡ እንዲፈጽም ፡ ውጤት ፡ ያላገኘ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ የተላከለት ፡ መሆኑ ፡ ወይም ፡ ሁለቱንም ፡ ለማግኘት ፡ አለመቻሉ ፤

(ሐ) የተባለው ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ የተደረገበትን ፡ ወይም ፡ ሳይፈጸም ፡ የተሞከረበትን ፡ ቦታና ፡ ቀን ፤

(መ) የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያውን ፡ ያዘጋጀው ፡ ሰው ፡ ፊርማ ፡ ነው ።

(፪) በከፊል ፡ የተደረገ ፡ አከፋፈል ፡ በመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያው ፡ ውስጥ ፡ ይመለከታል ።

(፫) አንድ ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ለእሺታ ፡ የቀረበለት ፡ ከፋይ ፡ ሁለተተኛ ፡ በማግሥቱ ፡ እንዲቀርብለት ፡ ጠይቆ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ ጥያቄ ፡ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያው ፡ ውስጥ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፯፻፺፪ ። የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሥርዐት ።

(፩) የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያው ፡ በተለየ ፡ ጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ ከሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ጋራ ፡ ይያያዛል ።

(፪) የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያው ፡ የተደረገው ፡ ተባዝቶ ፡ የተጻፈ ፡ አንድ፡ የሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ ዋናው ፡ ወረቀትና ፡ ግልባጩ ፡ ቀርቦ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያውን ፡ ከተባዛው ፡ ካንዱ ፡ ወይም፡ ከዋናው ፡ ወረቀት ፡ ጋራ ፡ ማያያዝ ፡ በቂ ፡ ነው ፡፡

(፫) እንዲሁም ፡ መደረጉ ፡ በሌሎች ፡ በተባዙት ፡ ወይም ፡ በወረቀቱ ፡ ግልባጭ ፡ ላይ ፡ ይገለጻል ፡፡

ቍ ፡ ፯፻፴፯ ፡፡ በከፊል ፡ የሆነ ፡ እሺታ ፡፡

እሺታውን፡ የሰጠው፡ ከገንዘቡ ፡ ለከፊሉ ፡ ሆኖ ፡ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታ ወቂያው፡ የተደረገው፡ ለቀሪው፡ ገንዘብ፡ እንደ፡ ሆነ፤ የወረቀቱን፡ አንድ፡ ግልባጭ ፡ ማድረግና፡ በዚሁ፡ ግልባጭ፡ ላይ፡ የመክፈል ፡ እንቢታውን ፡ ማጻፍ፡ ያስፈልጋል ፡፡

ቍ ፡ ፯፻፴፰ ፡፡ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ግልባጭ ፡፡

(፩) የእንቢታውን ፡ ማስታወቂያ፡ የሚያዘጋጅ ፡ ባለሥልጣን ፡ የዚህኑ ፡ ግልባጭ ፡ ያዘጋጃል ፡፡ ይኸውም ፡ ግልባጭ ፡ የሚያስታውቀው ፤

(ሀ) የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፤

(ለ) የመክፈያውን ፡ ጊዜ ፤

(ሐ) የሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ የተጻፈበትን ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፤

(መ) አውጪውን ፤ ከፋዩን ፤ እንዲሁም ፡ ለማን ፡ ወይም ፡ በማን ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲከፈል ፡ የተደረገለትን ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፤

(ሠ) ከፋዩ፡ ያልሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለመክፈል ፡ የተመለከተውን ፡ ሰው፡ ወይም፡ የንግድ ፡ ማኅበር ፤

(ረ) አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ከፋዮች ፡ ተብለው ፡ የተመለከቱትን ፡ ሰዎችና ፡ በጣ ልቃ ፡ ገብነት ፡ ለመክፈል ፡ እሺ ፡ ባዮችን ፡ ነው ፡፡

ቍ ፡ ፯፻፴፱ ፡፡ ማስታወቂያ ፡፡

(፩) የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ፡የተደረገበትን ፡ ቀን ፡ በሚከተሉት ፡ አራት ፡ የሥራ፡ ቀኖች፡ ውስጥ፡ ወይም፡ «ያለ፡ ኪሣራ፡ ተመላሽ፡ ይሆናል»፡ የሚል፡ የውል ፡ቃል ፡ ሲኖር፡ በጀርባ፡ ለፈረመው፡ ሰውና፡ ለአውጪው፡ እሺታ፡ አለመስጠቱን፡ ወይም፡ ገንዘብ፡ አለመከፈሉን፡ አምጪው ፡ ማስታወቂያ፡ መስጠት ፡ ይገባዋል ፡፡

(፪) በሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ተገዳጆች ፡ የሚሆኑት ፡ ሰዎች ፡ በሐዋላ ፡ ወረቀቱ ፡ ላይ ፡ ለተመለከተው ፡ አድራሻቸው ፤ ወይም ፡ የእንቢታውን ፡ ማስታወቂያ ፡ ያዘጋጀው ፡ ባለሥልጣን ፡ አድራሻቸውን ፡ ያወቀው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የእን ቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ እንዲደረግ ፡ የጠየቁ ፡ ሰዎች ፡ አድራሻቸውን ፡ ያመለከቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያውን ፡ ያዘጋጀው ፡ ባለሥልጣን ፡ ወዲያውኑ፡ በጽሑፍ ፡ ማስታወቂያ ፡ እንዲልክላቸው ፡ ይገደዳል ፡፡ ለእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ማስ ታወቂያ ፡ የሚደረጉት ፡ ወጪዎች ፡ ሁሉ ፡ ለእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ በሚ ደረጉት ፡ ወጪዎች ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ ይሆናሉ ፡፡

BACK



(፫) እያንዳንዱ ፡ በጀርባ ፡ የሚፈርም ፡ ሰው ፡ ማስታወቂያ ፡ ከደረሰበት ፡ ቀን ፡ በሚከተሉት ፡ ሁለት ፡ የሥራ ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ ከአውጪው ፡ እስኪደርስ ፡ የፊተኞችን ፡ ማስታወቂያዎች ፤ የሰጡትን ፡ ሰዎች ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፡ በማመልከት ፡ በጀርባ ፡ ፈርሞ ፡ ላስተላለፈለት ፡ ሰው ፡ የደረሰውን ፡ ማስታወቂያ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ጊዜዎች ፡ የሚቈጠሩት ፡ የፊተኛው ፡ ማስታወቂያ ፡ ከደረሰበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

(፬) ኡሰበን ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ መሠረት ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ለፈረመው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ማስታወቂያው ፡ የተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይኸው ፡ ማስታወቂያ ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ መሰጠት ፡ አለበት ።

(፭) በወረቀቱ ፡ ጀርባ ፡ የፈረመ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አድራሻውን ፡ ያላመለከተ ፡ ወይም ፡ በሚነበብ ፡ ዐይነት ፡ ያልጻፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከሱ ፡ በፊት ፡ ለነበረው ፡ በጀርባ ፡ ለፈረመ ፡ ሰው ፡ ማስታወቂያውን ፡ መስጠት ፡ በቂ ፡ ነው ።

(፮) ማስታወቂያ ፡ መስጠት ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀትን ፡ መልሶ ፡ በመላክ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

(፯) ማስታወቂያውንም ፡ በተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ መስጠቱን ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ። በዚሁ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ማስታወቂያውን ፡ የያዘ ፡ ደብዳቤ ፡ ለፖስታ ፡ ቤት ፡ ተሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ የተወሰነ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ይቈጠራል ።

(፰) ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ማስታወቂያውን ፡ ያልሰጠ ፡ ሰው ፡ መብቱን ፡ አያጣም ። የጉዳቱ ፡ ካሣ ፡ ከሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ጠቅላላ ፡ ገንዘብ ፡ ለመብለጥ ፡ ሳይችል ፡ በቸልተኝነቱ ፡ ያደረገው ፡ ጉዳት ፡ ቢኖር ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

## ቍ ፡ ፲፻፹፱ ። « ያለእንቢታ ፡ ማስታወቂያ » ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ።

(፩) አውጪው ፤ በጀርባ ፡ የሚፈርመው ፡ ሰው ፤ ወይም ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ “ ያለ ፡ ኪሣራ ፡ ተመላሽ ፡ ” “ ያለእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ” ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ በሰነዱ ፡ ላይ ፡ በመጻፍና ፡ በመፈረም ፤ እሺታ ፡ ወይም ፡ መክፈል ፡ ባልተደረገ ፡ ጊዜ ፡ የአቤቱታዎቹን ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያን ፡ ከማጻፍ ፡ አምጪውን ፡ ሊያድነው ፡ ይችላል ።

(፪) ይህ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ በታዘዙት ፡ የተወሰኑት ፡ ቀኖች ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀትን ፡ ከማቅረብና ፡ ማስታወቂያዎችንም ፡ ከመስጠት ፡ አምጪውን ፡ ነጻ ፡ አያወጣውም ። የተወሰኑት ፡ ቀኖች ፡ ላለመጠበቃቸው ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ያለበት ፡ በዚሁ ፡ አምጪውን ፡ ለመቃወም ፡ የሚፈልገው ፡ ሰው ፡ ነው ።

(፫) ይህን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ የጻፈው ፡ አውጪው ፡ እንደ፡ሆነ ፤ በፈረሙት ፡ ሰዎች ፡

ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ውጤት ፡ ይኖረዋል ። አንድ ፡ በወረቀቱ ፡ ጀርባ ፡ የሚፈርም ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ የውሉን ፡ ቃል ፡ ጽፎት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውጤት ፡ ያለው ፡ በፈረመው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፬) አውጪው ፡ ምንም ፡ የውሉን ፡ ቃል ፡ ቢጽፍ ፡ አምጪው ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ አጽፎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወጪዎቹ ፡ በራሱ ፡ ሒሳብ ፡ ይሆናሉ ። የውሉን ፡ ቃል ፤ የጻፈው ፡ በወረቀቱ ፡ ጀርባ ፡ የፈረመው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ተጽፎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያውን ፡ ወጪዎች ፡ ከፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡ ለመክፈል ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፯፻፺፫ ። በሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ የሚገደዱ ፡ ሰዎች ፡ ያንድነት ፡ የማይከፋፈል ፡ ዋስትና ።

(፩) አንድ ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ያወጡ ፤ እሺ ፡ ያሉ ፡ በጀርባ ፡ የፈረሙ ፡ ወይም ፡ ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባዮች ፡ ሁሉ ፡ በአንድነት ፡ ሳይከፈል ፡ ለአምጪው ፡ አላፊ ፡ ናቸው ።

(፪) አምጪው ፤ ሰዎቹ ፡ ሊገደዱ ፡ የገቡበትን ፡ ተራ ፡ ለመከተል ፡ ሳይገደድ ፡ በነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በያንዳንዱ ፡ ወይም ፡ በሁሉም ፡ ላይ ፡ ለማስፈጸም ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) አንድ ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ የፈረመና ፡ የዚሁን ፡ ዋጋ ፡ ገንዘብ ፡ የከፈለ ፡ ሁሉ ፡ ይኸንኑ ፡ የመሰለ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፬) ግዴታ ፡ ከገቡት ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ የተጀመረ ፡ ክስ ፡ በፊት ፡ ከተከሰሰ ፡ ሰው ፡ በኋላ ፡ ቢሆንም ፡ በሌሎቹ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አይከለከልም ።

ቍ ፡ ፯፻፺፬ ። የአምጪው ፡ አቤቱታ ፡ የሚደርስበት ፡ ወሰን ።

(፩) አምጪው ፡ አቤቱታ ፡ ካቀረበበት ፡ ሰው ፡ መጠየቅ ፡ የሚችለው ፤

(ሀ) እሺ ፡ ያልተባለውን ፡ ወይም ፡ ያልተከፈለውን ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከነወለዱ ፤

(ለ) ከመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ያለውን ፡ የሚከፈለውን ፡ ሕጋዊ ፡ ወለድ ፤

(ሐ) ለእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ የተሰጡትንና ፡ ለማስታወቂያዎች ፡ የተደረጉትን ፡ ወጪዎችና ፡ እንዲሁም ፡ ሌሎቹን ፡ ወጪዎች ፤

(መ) ቢበዛ ፡ ከመቶ ፡ ያንዱን ፡ ሢሶ ፡ ስለ ፡ ኮሚሲዮን ፡ መብት ፡ ነው ።

(፪) አቤቱታው ፡ የቀረበው ፡ ከመክፈያው ፡ ጊዜ፡በፊት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከወረቀቱ ፡ ጠቅላላ ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ቅናሽ ፡ ይደረጋል ። ይህም ፡ የቅናሽ ፡ ገንዘብ ፡ የአምጪው ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ባለበት ፡ ቦታ ፡ አቤቱታ ፡ በቀረበበት ፡ ቀን ፡ ባለው ፡ ግልጽ ፡ በሆነው ፡ በታወቀው ፡ የገንዘብ ፡ ቅናሽ ፡ ልክ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፯፻፺፪ ። የሐዋላ ፡ ወረቀትን ፡ ዋጋ ፡ የከፈለ ፡ ሰው ፡ ያለው ፡ የአቤቱታ ፡ ወሰን ።**

የሐዋላውን ፡ ወረቀት ፡ ዋጋ ፡ የከፈለ ፡ ሰው ፡ ለእሱ ፡ የሚገደዱትን ፡ ሰዎች ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችለው ፤

(ሀ) የከፈለውን ፡ ሙሉ ፡ ገንዘብ ፤

(ለ) የተባለውን ፡ ገንዘብ ፡ ወለድ ፡ ከከፈለበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በሕጋዊ ፡ ወለድ ፡ መሠረት ፡ ታስቦ ፤

(ሐ) ያደረጋቸውን ፡ ወጪዎች ፤

(መ) እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ ከሺሕ ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ የሆነ ፡ የኮሚሲዮን ፡ መብት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፯፻፺፫ ። የሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ከመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ጋራና ፡ የደረሰኝ ፡ ወረቀት ፡ እንዲሰጠው ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ።**

(፩) አቤቱታ ፡ የተደረገበት ፡ ወይም ፡ አቤቱታ ፡ ሊደረግበት ፡ የሚያስፈራው ፡ ግዴታ ፡ የገባ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ዋጋውን ፡ በመክፈል ፡ ከሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ጋራ ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያውና ፡ ተከፍሏል ፡ የሚል ፡ የሒሳብ ፡ ወረቀት ፡ ደረሰኝ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) የሐዋላውን ፡ ወረቀት ፡ ዋጋ ፡ የከፈለ ፡ ማንኛውም ፡ በጀርባ ፡ የፈረመ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በጀርባ ፡ የተጻፈውን ፡ የራሱን ፡ ፊርማና ፡ ከሱ ፡ ቀጥለው ፡ በጀርባ ፡ የጻፉትን ፡ ሰዎች ፡ ፊርማ ፡ መሰረዝ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፯፻፺፬ ። በከፊል ፡ እሺታ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ አቤቱታ ፡ ማቅረብ ።**

(፩) በከፊል ፡ እሺታ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ አቤቱታ ፡ ቢቀርብ ፡ እሺ ፡ ያልተባለበትን ፡ የወረቀት ፡ ዋጋ ፡ የከፈለ ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ መከፈሉ ፡ በወረቀቱ ፡ ላይ ፡ እንዲመለከትና ፡ ለመክፈሉም ፡ ደረሰኝ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) አምጪው ፡ እንዲሁ ፡ የተረጋገጠ ፡ የወረቀቱን ፡ ትክክል ፡ ግልባጭና ፡ በኋላም ፤ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ እንዲችል ፡ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያውን ፡ ለከፋይ ፡ መስጠት ፡ ይገባዋል ።

**ቍ ፡ ፯፻፺፭ ። አዲስ ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ።**

(፩) አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፤ ተቃራኒ ፡ ውል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ተገዳጆች ፡ ከሆኑት ፡ አንዱ ፡ በሚገደድበት ፡ በመደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታው ፡ እንደ ፡ ቀረበ፡ በሚከፈል ፤ በአዲስ ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ዋጋውን ፡ ለመክፈል ፡ ይችላል ።

(፪) በቍጥር ፡ ፯፻፺፩ ፡ እና ፡ ፯፻፺፪ ፡ ውስጥ ፡ ከተመለከቱት ፡ ገንዘቦች ፡ በቀር ፡ አዲሱ ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፤ የደላላ ፡ መብትና ፡ የአዲሱ ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ የቴምብር ፡ መብት ፡ አለበት ።

(፫) አዲሱን ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ያወጣው ፡ አምጪው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የዚህ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ የሚታሰበው ፡ ለእሱ ፡ ተገዳጅ ፡ በሆነው ፡ ሰው ፡ በመደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ሊከፈል ፡ የነበረው ፡ የመጀመሪያው ፡ ወረቀት ፡ በወጣበት ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ የሚከፈል ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ዋጋ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፬) አዲሱን ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ያወጣው ፡ በጀርባ ፡ የጻፈው ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የዚህ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ የሚታሰበው ፡ አዲሱን ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ላመጣ ፡ ሰው ፡ ሕጋዊ ፡ መኖሪያ ፡ ከሆነው ፡ ቦታ ፡ ተገዳጅ ፡ በሆነው ፡ ሰው ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ የሚከፈል ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ዋጋ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፯፻፺፩ ። የአቤቱታ ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ማጣት ።

(፩) እንደ ፡ ቀረበ ፡ ወይም ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚከፈል ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀትን ፡ ለማቅረብ ፡ ወይም ፡ የእሺታን ፡ ወይም ፡ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያን ፡ ለማዘጋጀት ፤ ወይም ፡ ያለኪሣራ ፡ እንዲመለስ ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለማስከፈል ፡ የተወሰኑት ፡ ጊዜዎች ፡ ያለፉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከእሺ ፡ ባዩ ፡ በቀር ፡ በጀርባ ፡ በፈረሙት ፡ ሰዎች ፤ በአውጪውና ፡ በሌሎቹ ፡ ግዴታ ፡ በገቡት ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መብቶች ፡ አምጪው ፡ ያጣል ።

(፪) አውጪው ፡ በወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ወረቀቱ ፡ ለእሺታ ፡ ያልቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አውጪው ፡ ከእሺታው ፡ ዋስትና ፡ አላፊነት ፡ ብቻ ፡ ለመዳን ፡ ያደረገው ፡ ለመሆኑ ፡ ከውሉ ፡ ቃል ፡ የመነጨ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አምጪው ፡ የሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ዋጋ ፡ ባለመከፈሉ ፡ እንዲሁም ፡ እሺታ ፡ ባለመደረጉ ፡ አቤቱታ ፡ የማቅረብ ፡ መብቱን ፡ ያጣል ።

(፫) ወረቀቱን ፡ ለማቅረብ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በጀርባው ፡ ላይ ፡ በተፈረመው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የተገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚሁ ፡ ለመጠቀም ፡ የሚችለው ፡ በጀርባው ፡ የፈረመው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ፯፻፺፪ ። ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ኀይል ።

(፩) በማይቻል ፡ መሰናክል ፡ ( በማናቸውም ፡ ከመንግሥት ፡ በተሰጠ ፡ ሕጋዊ ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል ፡ ) ምክንያት ፡ በተወሰኑት ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተወሰኑት ፡ ቀኖች ፡ ይራዘማሉ ።

(፪) አምጪው ፤ በሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ቅጥል ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ከዐቅሙ ፡ በላይ ፡ የሆነውን ፡ መሰናክል ፡ ቀንና ፡ ፊርማ ፡ አድርጎ ፡ ሳይዘገይ ፡ በጀርባ ፡ ለፈረመለት ፡ ሰው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ። ተጨማሪ ፡ ለሆነውም ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፹፰ ፡ የተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፫) ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነው ፡ ኀይል ፡ ሲቀር ፡ አምጪው ፡ ሳይዘገይ ፡ ለእሺታ ፡

ወይም ፡ ለመክፈል ፡ ወረቀቱን ፡ ማቅረብና ፡ አስፈላጊም ፡ ቢሆን ፡ የመክፈል ፡ እንቢታውን ፡ ማጸፍ ፡ አለበት ።

(፪) ከመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነው ፡ ኀይል ፡ ከሠላሳ ፡ ቀን ፡ ወዲያ ፡ የቀጠለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የመክፈል ፡ እንቢታውን ፡ ማጸፍና ፡ ማቅረብ ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፫) እንደ ፡ ቀረቡ ፡ ወይም ፡ ከቀረቡ ፡ በኋላ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚከፈልባቸው ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀቶች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሠላሳው ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ መቈጠር ፡ የሚጀምረው ፡ የማቅረቡ ፡ ጊዜ ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ አምጪው ፡ ከዐቅሙ ፡ በላይ ፡ የሆነውን ፡ ምክንያት ፡ በጀርባ ፡ ለፈረመለት ፡ ሰው ፡ ማስታወቂያ ፡ ከሰጠበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ነው ። ከቀረቡበት ፡ አንሥቶ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሚከፈልባቸው ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀቶች ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ ሠላሳውን ፡ ቀን ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ከቀረበበት ፡ አንሥቶ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ ይሆናል ።

(፬) ለአምጪው ፡ ወይም ፡ ወረቀቱን ፡ እንዲያቀርብ ፡ ወይም ፡ የመክፈል ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያውን ፡ እንዲያደራጅ ፡ ለታዘዘው ፡ ሰው ፡ የግል ፡ የሆኑት ፡ ምክንያቶች ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ኀይል ፡ አይገመቱም ።

ቍ ፡ ፱፻፳፯ ። በሐዋላ ፡ ወረቀቶች ፡ የሚገደዱትን ፡ ሰዎች ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ በጥበቃ ፡ ስለ ፡ መያዝ ።

በዋስትና ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ከተደነገጉት ፡ ሥርዐቶች ፡ ሌላ ፤ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ የተደረገበት ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ አምጪ ፡ ከዳኛ ፡ ፈቃድ ፡ በማግኘት ፡ የአውጪዎቹን ፤ የአሺ ፡ ባዮቹንና ፡ በጀርባ ፡ የፈረሙትን ፡ ሰዎች ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ በጥበቃ ፡ ለማስያዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፱፻፳፰ ። ያለ ፡ አገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ።

(፩) በሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱት ፡ ግዴታዎቻቸው ፡ ግዜያቸው ፡ በማለፍ ፡ ወይም ፡ በይርጋ ፡ ምክንያት ፡ የቀሩ ፡ ቢሆኑም ፡ እንኳ ፡ አውጪውና ፡ እሺ ፡ ባዩ ፡ ሕግ ፡ በማይፈቅደው ፡ አኳኋን ፡ ያለአገባብ ፡ በመበልጸግ ፡ ባገኙት ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ለአምጪው ፡ ኀላፊዎች ፡ ናቸው ።

(፪) ያለአገባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ በከፋዩ ፤ በመደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ይከፍላል ፡ በተባለ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፤ የሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ በወጣለት ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በንግድ ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።

(፫) ግዴታቸው ፡ የቀረላቸው ፡ በጀርባ ፡ የፈረሙ ፡ ሰዎች ፡ ይህ ፡ ክስ ፡ አይቀርብባቸውም ።

(፩) አምጪው ፡ ለወረቀቱ ፡ ምክንያት ፡ በሆነው ፡ ነገር ፡ ለመክሰስ ፡ ካልቻለ ፡

ብቀር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፰፻ ። በወረቀቱ ፡ ምክንያት ፡ ክስ ፡ የማቅረብ ፡ መብት ፡ የተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ መቈየቱ ።**

(፩) መተካት ፡ (ኖቫሲዎን) ፡ የተደረገ ፡ ለመሆኑ ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ ካልቻለ ፡ በቀር ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀትን ፡ ለማውጣት ፡ ወይም ፡ ለማስተላለፍ ፡ ምክንያት ፡ ከሆነ ፡ ግንኙነት ፡ የተነሣ ፡ የክስ ፡ ማቅረብ ፡ መብት ፡ እንዳለ ፡ ይቈያል ።

(፪) የእሺታው ፡ አለመስጠት ፡ ወይም ፡ የሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ዋጋ ፡ አለመከፈል፡ ባንድ ፡ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ ይህን፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ።

(፫) ለባለዕዳው ፡ ለመሆን ፡ የሚችሉትን ፡ ክሶች ፡ ጠብቆ ፡ ለማቈየት ፡ አስፈላጊ፡ የሆኑት ፡ ደንቦች ፡ እንዲፈጸሙ ፡ አድርጎ ፡ ለባለዕዳው ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀትን ፡ ካልመለሰና ፡ በፍርድ ፡ ቤት፡ መዝገብ ፡ ሹም፡ ካላስቀመጠ፡ በቀር ፡ አምጪው ፡ በሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ምክንያት ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፰፻፩ ። ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ሥንቅና ፡ ተከታታይ ፡ ለሆኑ ፡ አምጪዎች ፡ ስለ ፡ መተላለፉ ።**

(፩) የመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ ከፋዩ ፡ የሐዋላውን ፡ ወረቀት ፡ ለመክፈል ፡ በሙሉ ፡ የሚችልበት፡ አንድ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሰነድ ፡ ወይም ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ በጁ ፡ ያለውና ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀቱን ፡ ለመክፈል ፡ አውጪው ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጪው ፡ አስበው ፡ ያደረጉት ፡ ሲሆን ፡ የገንዘብ ፡ ሥንቅ ፡ አለ ፡ ይባላል ።

(፪) አውጪው ፡ የከሠረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የገንዘቡ ፡ ሥንቅ ፡ እንዲመለስለት ፡ ወይም፡ ሊሰጡት ፡ የሚገቡት ፡ ገንዘቦች ፡ እንዲከፈሉት፡ በከፋዩ ፡ ላይ ፡ ለማቅ ረብ ፡ የሚችለው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፤ ለሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ አምጪ፡ በደንብ ፡ ይተላለፍለታል ፤ ይህ፡ የመክሰስ ፡ መብት ፡ በሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ በጀርባ ፡ በመፈረም ተከታይ ፡ ለሆኑ ፡ አምጪዎች ፡ ይተላለፋል ።

(፫) ከሠረ ፡ ተብሎ ፡ የተፈረደበት ፡ አውጪ ፡ ባጠራጣሪ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በሐዋ ላው ፡ ወረቀት ፡ ጀርባ ፡ የፈረመና ፡ የገንዘብም ፡ ሥንቅ ፡ ያደራጀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) የተመለከተው ፡ ውሳኔ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆንም ።

(፬) የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ተከፋይ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ከከፋዩ ፡ እጅ ፡ ከሚገ ኘው ፡ የገንዘብ ፡ ሥንቅ ፡ የተነሣ ፡ የተገኘው ፡ የገንዘብ ፡ መብት ፤ ከአውጪው ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ለሆኑት ፡ በቀደምትነት ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

(፭) አምጪው ፡ ቢከለክለው ፡ የገንዘብን ፡ ሥንቅ ፡ ከፋዩ ፡ ለመልቀቅ ፡ አይች ልም ። ይህ ፡ መከልከል ፡ የመክፈያ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ለመቅረብ ፡ የጥሪ ፡ ወረቀት ፡ የሚከተለው ፡ ሆኖ፡ በሬኮማንዴ፡ወረቀት፡ለመደረግ፡ይቻላል ። ገንዘቡም፡ስላልተከፈለ ፡ የሚደረገው ፡ የእንቢታ፡ማስታወቂያ፡በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌ ፡ ስለ ፡ መከልከል ፡ይቈጠራል ።

BACK



## ክፍል ፡ ፯ ።

## ለመክፈል ፡ ጣልቃ ፡ ስለ ፡ መግባት ።

### ቍ ፡ ፯፻፸፱ ። ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

(፩) አውጪው ፤ በወረቀቱ ፡ ጀርባ ፡ የፈረመ ፤ ወይም ፡ ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባይ ፤ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ እሺ ፡ የሚል ፡ ወይም ፡ የሚከፍል ፡ አንድ፡ ሰው ፡ ማመልከት ፡ ይችላሉ ።

(፪) ከዚህ ፡ በታች ፡ በተወሰኑት፡ ሁኔታዎች፡ መሠረት ፡ አቤቱታ ፡ ሊቀርብበት ፡ ለሚችለው ፡ ለማናቸውም ፡ ባለዕዳ ፡ በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀቱን ፡ እሺ ፡ ለማለት ፡ ወይም ፡ ለመክፈል ፡ ይችላል ።

(፫) እሺ ፡ ባዩ ፡ ሳይሆን ፡ በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ የሚገባው ፡ አንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፤ ከፋይ ፡ ወይም ፡ በሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ መሠረት ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የተገደደ ፡ ሰውም ፡ ለመክፈል ፡ ጣልቃ ፡ ገብ ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

(፬) በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ የሚገባው ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ ለሚገባለት ፡ ሰው ፡ በሁለት ፡ የሥራ ፡ ቀኖች ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ የመግባቱን ፡ ማስታወቂያ ፡ ለመስጠት ፡ ይገደዳል ። የዚህ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ግዴታ ፡ ያልተጠበቀ ፡ እንደ፡ሆነ ፤ በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ የሚገባው፡ ሰው ፡ በቸልተኝነቱ ፡ ጉዳት ፡ ቢያደርስ ፡ በሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ከተጻፈው ፡ ገንዘብ ፡ መብለጥ ፡ ለማይችል ፡ ኪሣራ ፡ አላፊ ፡ ይሆናል ።

### ቍ ፡ ፯፻፹ ። በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ በመግባት ፡ እሺ ፡ የማለት ፡ ሁኔታዎች ፤ የእምጪው ፡ ሁኔታ ።

(፩) ከመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፤ እሺ ፡ ሊባልበት ፡ ለሚቻል ፡ ለሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ እምጪ ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ሁሉ ፡ የአቤቱታ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ በመግባት ፡ ወረቀቱን ፡ እሺ ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

(፪) በሚከፈልበት ፡ ቦታ ፡ ወረቀቱን ፡ እሺ ፡ ለማለት ፡ አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ ለመክፈል ፡ በሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተመልክቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለዚህ ፡ ለተመለከተው ፡ ሰው ፡ ወረቀቱን ፡ አቅርቦለት ፡ ይኸውም ፡ ሰው ፡ እሺታውን ፡ እንቢ ፡ ብሎ ፡ እንቢታውም ፡ በእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ካልተገለጸ ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ ማመልከት ፡ ባደረገው ፡ ሰውና ፡ በኋላም ፡ በፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ እምጪው ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የአቤቱታውን ፡ መብቶች ፡ ተግባር ፡ ሊፈጽም ፡ አይችልም ።

(፫) ጣልቃ ፡ መግባቱ ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ የመግባቱን ፡ እሺታ ፤ እምጪው ፡ እንቢ ፡ ለማለት ፡ ይችላል ። የተቀበለው ፡ እንደ ፡

BACK



ሆን ፤ ግን ፡ እሺታ ፡ በተሰጠለት ፡ ሰውና ፡ በኋላ ፡ በፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ከመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የአቤቱታዎቹን ፡ መብት ፡ ያጣል ።

ቍ ፡ ፰፻፩ ። ሥርዐት ፡ (ፎርም) ።

በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ በመግባት ፡ እሺታ ፡ መስጠቱ ፡ በሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ይመለከታል ። በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ የሚገባ ፡ ሰው ፡ ይፈርምበታል ። ስለ ፡ ማን ፡ እንደሆነም ፡ ያመለክታል ። ይህ ፡ ማመልከት ፡ ከሌለ ፤ እሺታው ፡ ለአውጪው ፡ እንደ ፡ ተሰጠ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፰፻፪ ። የእሺ ፡ ባይ ፡ ግዴታዎች ፤ የአቤቱታን ፡ መብት ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ውጤቶች ።

(፩) በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ በመግባት ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ በገባለት ፡ ሰው ፡ ዐይነት ፡ ለአምጪውና ፡ በኋላ ፡ በጀርባው ፡ ለፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ የተገደደ ፡ ይሆናል ።

(፪) ምንም ፡ በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ በመግባት ፡ እሺታ ፡ የተሰጠ ፡ ቢሆንም ፡ ይህ ፡ እሺታ ፡ የተደረገለት ፡ ሰውና ፡ ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፹፱ ፡ የተመለከተውን ፡ ገንዘብ ፡ በመመለስ ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀቱን ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያውን ፡ የተከፈለበትን ፡ ሒሳብ ፡ ደረሰኝ ፡ እንዳለ ፡ ለመቀበል ፡ አምጪውን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፰፻፫ ። በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ በመግባት ፡ ስለ ፡ መክፈል ፡ ሁኔታዎች ።

(፩) በጣልቃ ፡ ገብነት ፡ የመክፈል ፡ ጕዳይ ፡ አምጪው ፡ የአቤቱታ ፡ ማቅረብ ፡ መብት ፡ ካለው ፡ በመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ጊዜ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊትም ፡ ቢሆን ፡ በማንኛውም ፡ ሁኔታ ፡ ሊፈጸም ፡ ይችላል ።

(፪) አከፋፈሉም ፡ የሚከፈልለት ፡ ሰው ፡ ሊከፍል ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ መጠቅለል ፡ አለበት ።

(፫) አከፋፈሉ ፡ እጅግ ፡ ቢዘገይ ፤ ላለመከፈሉ ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለማዘጋጀት ፡ በተወሰነው ፡ መጨረሻ ፡ ቀን ፡ ማግሥት ፡ መሆን ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፰፻፬ ። የአምጪው ፡ ግዴታዎች ።

(፩) የሐዋላውን ፡ ወረቀት ፡ ጣልቃ ፡ በማግባት ፡ እሺ ፡ ባዮች ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታቸው ፡ የሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ በሚከፈልበት ፡ ቦታ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆን ፤ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ ለመክፈል ፡ በዚሁ ፡ ቦታ ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታቸው ፡ ውስጥ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ የተመለከቱ ፡ እንደ ፡ሆን ፤ አምጪው ፡ ለነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ወረቀቱን ፡ ማቅረብና ፡ አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ እጅግ ፡ ቢዘገይ ፡ ላለመክፈሉ ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለማዘጋጀት ፡ በተወሰነው ፡ በመጨረሻ ፡ ቀን ፡ ማግሥት ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያውን ፡ ማጻፍ ፡ አለበት ።

(፪) በዚሁ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ያልተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ እንዲከፍል ፡ የተመለከተው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የሐዋላውን ፡ ወረቀት ፡ እንዲከፈለው ፡ እሺ ፡ የተባለለት ፡ ሰውና ፡ ከሱም ፡ በኋላ ፡ በጀርባ ፡ የፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ ከግዴታው ፡ ነጻ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፰፻፰ ። እንቢታ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ።

በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ በመግባት፡ የሚደረገውን ፡ አከፋፈል፡ እንቢ ፡ ያለ ፡ አምጪ፡ በዚሁ፡ ነጻ፡ይወጡ፡በነበሩት ፡ ሰዎች፡ላይ ፡ ያሉትን፡የአቤቱታ፡መብቶች፡ያጣል ።

ቍ ፡ ፰፻፱ ። የሐዋላ ፡ ወረቀቱን ፤ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያውን ፤ ደረሰኙን ፤ የመስጠት፡ መብት ።

(፩) በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ በመግባት ፡ የሚደረገው ፡ አከፋፈል ፡ የተከፈለው ፡ ለማን፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ደረሰኝ ፡ በመጻፍ ፡ መግለጽ ፡ አለበት ። ይህ ፡ ያልተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አከፋፈሉ ፡ ለአውጪው ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) የሐዋላው ፡ ወረቀትና ፡ የተዘጋጀም ፡ እንዳለ ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ በመግባት ፡ እሺ ፡ ብሎ፡ለከፈለው ፡ ሰው ፡ መሰጠት ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፰፻፲ ። የአምጪውን ፡ መብቶች ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ፤ በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ በመግባት፡ የእሺ፡ ባዮች ፡ መወዳደር ።

(፩) በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ በመግባት ፡ እሺ ፡ ባይ፡ በከፈለለት ፡ ሰውና፡ በሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ መሠረት ፡ ለዚሁ ፡ ሰው ፡ በሚገደዱት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ከሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ የሚገኙትን ፡ (የመነጩትን) መብቶች ፡ ያገኛል ። ሆኖም ፡ የሐዋላውን፡ወረቀት፡እንደ፡ገና ፡ በጀርባው ፡ ፈርሞ ፡ ለማስተላለፍ፡አይችልም ።

(፪) ከተከፈለለት፡ሰው፡በኋላ፡በወረቀቱ፡ ጀርባ፡የፈረሙት፡ሰዎች ፡ ነጻ፡ ይሆናሉ ።

(፫) በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ በመግባት ፡ ለሚደረገው ፡ አከፋፈል ፡ ውድድር ፡ ሲኖር፡ ይበልጥ ፡ ዕዳውን ፡ ነጻ ፡ የሚያደርገው ፡ እሺ ፡ ባዩ ፡ የተመረጠ ፡ ይሆናል ፤ ይህን፡ ደንብ ፡ ተቃራኒ ፡ በመሆን ፡ ምክንያቱን ፡ በማወቅ ፡ በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ በመግባት ፡ እሺ ፡ ባዩ ፤ ነጻ ፡ ይወጡ ፡ በነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የአቤቱታዎቹን ፡ መብቶች ፡ ያጣል ።

## ክፍል ፡ ፱ ።

## ተባዝቶ ፡ ስለ፡ተጻፈና፡ ስለ ፡ ግልባጮች ።

ቍ ፡ ፰፻፲፩ ። ተባዝቶ ፡ የተጻፉ ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀቶች ፤ የተባዙት ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀቶች ፡ የሚሰጡት ፡ መብት ።

(፩) የሐዋላ፡ወረቀት፡በአንድ፡ዐይነት፡በተጻፉ፡ብዙ ፡ ጽሑፎች ፡ ሊወጣ፡ይችላል ።

BACK



(፪) እነዚህ ፡ ጽሑፎች ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ሊደረግባቸው ፡ ይገባል ። ይህ ፡ ካልሆነ ፡ ግን ፡ እያንዳንዱ ፡ ጽሑፍ ፡ ልዩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ይገመታል ።

(፫) ባንድ ፡ ወረቀት ፡ ብቻ ፡ የተጻፈ ፡ መሆኑን ፡ የማያመለክት ፡ ወረቀት ፡ አምጪ ፡ ሁሉ ፡ በራሱ ፡ ኪሣራ ፡ ብዙ ፡ ጽሑፎች ፡ እንዲሰጡት ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ። ለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ በወረቀቱ ፡ በቅርብ ፡ ለርሱ ፡ የፈረመለትን ፡ ሰው ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ። ይኸውም ፡ ሰው ፡ ለእሱ ፡ በወረቀቱ ፡ ጀርባ ፡ ከፈረመለት ፡ ሰው ፡ የሚያስፈልገውን ፡ እንዲያገኝ ፡ ላምጪው ፡ ርዳታ ፡ መስጠት ፡ አለበት ። እንዲሁም ፡ በወረቀቱ ፡ ጀርባ ፡ የፈረሙ ፡ ሰዎች ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ ከአውጪው ፡ እስከ ፡ ደረሰ ፡ ድረስ ፡ ርዳታ ፡ መስጠት ፡ አለባቸው ፤ በጀርባ ፡ የፈረሙ ፡ ሰዎች ፡ ባዲሶቹ ፡ ወረቀቶች ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በጀርባው ፡ መፈረም ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፰፻፲፪ ። በተባዙት ፡ ጽሑፎች ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ ግንኙነት ።

(፩) ምንም ፡ ይህ ፡ የገንዘብ ፡ መክፈል ፡ የሌሎቹን ፡ ጽሑፎች ፡ ውጤት ፡ ይሽራል ፡ ተብሎ ፡ ባይነገር ፡ እንኳ ፡ ከጽሑፎቹ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ የተደረገ ፡ አከፋፈል ፡ ከግዴታዎች ፡ ነጻ ፡ ያወጣል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ከፋዩ ፡ እሺታ ፡ በሰጠባቸው ፡ እጁ ፡ ባልገቡት ፡ ወረቀቶች ፡ በያንዳንዱ ፡ ይገደዳል ።

(፪) የተባዙትን ፡ ጽሑፎች ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ሰዎች ፡ እንዲተላለፉ ፡ በወረቀቱ ፡ ጀርባ ፡ የፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ እንዲሁም ፡ ተከታትለው ፡ በጀርባው ፡ የፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ ፊርማቸው ፡ ላሉባቸውና ፡ ላልተመለሱላቸው ፡ ወረቀቶች ፡ ኀላፊዎች ፡ ናቸው ።

ቍ ፡ ፰፻፲፫ ። እሺ ፡ መባሉን ፡ ስለ ፡ መጻፍ ።

(፩) ለእሺታ ፡ ከጽሑፎቹ ፡ አንዱን ፡ የላከ ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ በእጁ ፡ የሚገኘውን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ በሌሎች ፡ ጽሑፎች ፡ ላይ ፡ ማመልከት ፡ ይገባዋል ። ይኸውም ፡ ሰው ፡ ከጽሑፎቹ ፡ አንዱን ፡ በሕግ ፡ ለታወቀው ፡ አምጪ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፪) ሰውዬው ፡ እንቢ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አምጪው ፤

(ሀ) ለእሺታ ፡ የተላከውን ፡ ጽሑፍ ፡ ጠይቆ ፡ ያልተሰጠው ፡ መሆኑን ፤

(ለ) እሺታው ፡ ወይም ፡ አከፋፈሉ ፡ በሌላው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ሊደረግ ፡ አለመቻሉን ፤ በእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ካላጸፈ ፡ በቀር ፡ የአቤቱታ ፡ መብቱን ፡ ሊሠራበት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፰፻፲፬ ። ሥርዐትና ፡ ( ፎርምና ) ፡ ውጤቶች ።

(፩) ማናቸውም ፡ የሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ አምጪ ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀቶቹን ፡ ግልባጮች ፡ ለማድረግ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ግልባጩም ፡ የዋናውን ፡ ወረቀት ፡ የጀርባ ፡ ፊርማዎችንና ፡ ሌሎች ፡ መግለጫዎችን ፡ ሁሉ ፡ በትክክል ፡ ሊኖሩበት ፡ ይገባል ። ጽሕፈቱም ፡ የሚቆምበትን ፡ ቦታ ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

(፫) ግልባጩም ፡ ዋናው ፡ ወረቀት ፡ በሚሰጠው ፡ ውጤቶች ፡ ዐይነት ፡ በጀርባ ፡ ሊፈረምበትና ፡ ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባይነት ፡ ሊደረግበት ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፰፻፲፮ ። ዋናውን ፡ ወረቀት ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ።

(፩) ግልባጩም ፡ ዋናውን ፡ ወረቀት ፡ የያዘውን ፡ ሰው ፡ ማመልከት ፡ አለበት ። ይኸውም ፡ ሰው ፡ ይኸንኑ ፡ ወረቀት ፡ በሕግ ፡ ለታወቀው ፡ ግልባጭ ፡ አምጪ ፡ ለመስጠት ፡ ይገደዳል ።

(፪) እንቢ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አምጪው ፡ ጥያቄ ፡ አቅርቦ ፡ ዋናው ፡ አልተሰጠኝም ፡ በማለት ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ካላጸፈ ፡ በቀር ፡ ግልባጩን ፡ በጀርባ ፡ በፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባዮች ፡ ላይ ፡ የአቤቱታ ፡ መብቱን ፡ ለመፈጸም ፡ አይችልም ።

(፫) ግልባጩ ፡ ከመሠራቱ ፡ በፊት ፡ በዋናው ፡ ወረቀት ፡ የመጨረሻው ፡ የጀርባ ፡ ጽሑፍ ፡ « ከዚህ ፡ እንሥቶ ፡ የጀርባው ፡ ጽሑፍ ፡ በግልባጩ ፡ ላይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይረጋም » ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ሌላ ፡ ተመሳሳይ ፡ ጽሑፍ ፡ የያዘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዋናው ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በጀርባ ፡ ተጽፎ ፡ የተፈረመ ፡ ሁሉ ፡ አይጸናም ።

ክፍል ፡ ፲ ።

ስለ ፡ መለዋወጥ ።

ቍ ፡ ፰፻፲፯ ። የፈራሚዎቹ ፡ ግዴታ ፡ ወሰን ።

አንድ ፡ የሐዋላ፡ ወረቀት፡ ቃል ፡ በተለወጠ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ መለወጥ ፡ በኋላ ፡ የፈረሙት ፡ ፈራሚዎች ፡ ሁሉ ፡ በተለወጠው ፡ ቃል ፡ ይገደዳሉ ። ከዚያ ፡ በፊት ፡ ያሉት ፡ ፈራሚዎች ፡ ግን ፡ ሳይለወጥ ፡ በነበረው ፡ በመጀመሪያው ፡ ቃል ፡ የተገደዱ ፡ ይሆናሉ ።

ክፍል ፡ ፲፩ ።

ስለ፡ይርጋ።

ቍ ፡ ፰፻፲፰ ። የተወሰኑ ፡ ጊዜዎች ።

(፩) ከሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ የተነሣ ፡ በእሺ ፡ ባዩ ፡ ላይ ፡ የሚደረጉ ፡ ክሶች ፡ ሁሉ ፡ ከመክፈያው ፡ ቀን ፡ እንሥቶ ፡ በሦስት ፡ ዓመት ፡ ይርጋ ፡ ቀሪዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) አምጪው ፤ በጀርባ ፡ በፈረሙ ፡ ሰዎችና ፡ በአውጪው ፡ ላይ ፡ የሚያቀርበው ፡ ክስ ፤ በሚገባው ፡ ጊዜ ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተደረገበት ፡ ወይም ፡ « ያለ ኪሣራ ፡ የሚመለስ » ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ባለበት ፡ ጊዜ ፡ ከመክፈያው ፡ ቀን ፡ እንሥቶ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ይርጋ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

BACK



(፫) በጅርባ፡ የሚፈርሙት፡ ሰዎች፡ እርስ፡ በርሳቸው፡ ወይም ፡ በአውጪው፡ ላይ ፡ የሚያቀርቡት ፡ ክስ ፡ በጅርባ ፡ የፈረመው ፡ ሰው ፡ የወረቀቱን ፡ ዋጋ ፡ ከከፈለ በት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ራሱ ፡ ከተከሰሰበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ ይርጋ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

(፬) ክስ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ የሚጀም ረው ፡ ከመጨረሻ ፡ ክስ ፡ ውሳኔ ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

(፭) ፍርድ ፡ ተሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ዕዳው ፡ በተለይ ፡ በሌላ ፡ ሰነድ ፡ ታምኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፉት ፡ የይርጋ ፡ ዘመኖች ፡ አይጸኑም ።

ቍ ፡ ፰፻፲፰ ። ስለ ፡ ማቋረጥ ።

(፩) ክስን ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ በማቅረብ ፤ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ያቀረበውን ፡ ክስ ፡ በማ ስታወቅ ፡ ወይም ፡ በንግድ ፡ ኪሣራ ፡ አሠራር ፡ ጊዜ ፡ ሙብት ፡ መጠየቂያ ፡ ወረ ቀትን ፡ በማቅረብ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ የሚቋረጥ ፡ ይሆናል ።

(፪) የይርጋው ፡ መቋረጥ ፡ ክሱ ፡ በተደረገበት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በሌ ላው ፡ ላይ ፡ ውጤት ፡ የለውም ።

(፫) የይርጋ ፡ ዘመኑ ፡ የተቋረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንደዚሁ ፡ የሚቈይ ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡ አዲስ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ ይጀምራል ።

## ክፍል ፡ ፲፪ ።

## ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

ቍ ፡ ፰፻፲፱ ። የተወሰኑ ፡ ጊዜዎች ፤ የበዓላት ፡ ቀኖች ።

(፩) ስለ፡ሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ አከፋፈል ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በሕግ ፡ የታወቀ ፡ የበ ዓል ፡ ቀን ፡ ሲሆን ፡ የሚከተለውም ፡ የሥራ ፡ ቀን ፡ ካልሆነ ፡ እንዲከፍል ፡ ሊገ ደድ ፡ አይችልም ፤ እንዲሁም ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ሌሎች ፡ ተግባሮች ፡ ሁሉ ፡ በተለይ ፡ ለእሺታ ፡ ማቅረብና ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ማጻፍ ፡ ባንድ ፡ በሥራ ፡ ቀን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሊደረጉ ፡ አይቻሉም ።

(፪) ከነዚህ ፡ ተግባሮች ፡ አንዱ ፡ የሚፈጸምበት ፡ የመጨረሻው ፡ ቀን ፡ በሕግ ፡ የታወቀ ፡ የበዓል ፡ ቀን ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የማለቂያው ፡ ቀን ፡ በሚከተለው ፡ እስከ ፡ መጀመሪያ ፡ የሥራ ፡ ቀን ፡ ጊዜው ፡ የሚራዘም ፡ ይሆናል ። ጣልቃ ፡ የሚገቡት ፡ የበዓል ፡ ቀኖች ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ግምት ፡ ውስጥ ፡ ይቈጠራሉ ።

ቍ ፡ ፰፻፳ ። በሕግ ፡ ከታወቁት ፡ የበዓል ፡ ቀኖች ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆኑ ፡ ቀኖች ።

ጸንተው ፡ በሚገኙት ፡ ሕጎች ፡ አነጋገር ፡ ምንም ፡ አከፋፈል ፡ እንዳይደረግባ ቸው ፡ እንዲሁም ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ እንዲጸፍባቸው ፡ የተከለከሉት ፡ ቀኖች ፡ በሕግ ፡ እንደታወቁት ፡ የበዓላት ፡ ቀኖች ፡ ይቈጠራሉ ።

ቊ ፡ ፰፻፳፩ ። የተወሰኑ ፡ ጊዜዎች ፡ አቈጣጠር ።

በሕግ ፡ ወይም ፡ በስምምነት ፡ ለተወሰኑ ፡ ጊዜዎች ፤ መነሻ ፡ የሆነው ፡ ቀን ፡ አይቈጠርም ።

ቊ ፡ ፰፻፳፪ ፡ በችሮታ ፡ የሚሰጠውን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ መከልከል ።

ምንም ፡ የችሮታ ፡ ቀን ፡ ለመስጠት ፡ አይፈቀድም ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

የተስፋ ፡ (ለመክፈል ፡ ቃል ፡ የሚሰጥበት) ፡ ወረቀት ።

ቊ ፡ ፰፻፳፫ ። ስለ ፡ አስፈላጊ ፡ መግለጫዎች ።

የተስፋ ፡ ወረቀት ፡ ሊኖርበት ፡ የሚገባው ፤

(ሀ) ፡ በሰነዱ ፡ ውስጥ « የተስፋ ፡ ወረቀት » ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ መገኘትና ፡ ሰነዱ ፡ በተጻፈበት ፡ ቋንቋ ፡ መግለጽ ፤

(ለ) ፡ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ ሐተታ ፡ የሌለበት ፡ ቃል ፡ መግባት ፤

(ሐ) ፡ የሚከፈልበት ፡ ጊዜ ፤

(መ) ፡ ገንዘቡ ፡ ሊከፈልበት ፡ የሚገባው ፡ ቦታ ፤

(ሠ) ፡ ገንዘቡ ፡ የሚከፈለው ፡ ወይም ፡ የታዘዘለት ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ወረቀቱ ፡ ለአምጪው ፡ መክፈል ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ ማመልከት ፤

(ረ) ፡ ሰነዱ ፡ የተጻፈበት ፡ ቀንና ፡ ቦታ ፤

(ሰ) ፡ ሰነዱን ፡ ያወጣው ፡ ሰው ፡ ፊርማ ፡ ነው ።

ቊ ፡ ፰፻፳፬ ። አስፈላጊ ፡ ስለሆኑት ፡ መግለጫዎች ፡ ጕድለት ።

ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ባሉት ፡ ኀይለ ፡ ቃሎች ፡ በ (ሀ) (ለ) (ሐ) ካልተወሰኑት ፡ ሁኔታዎች ፡ በቀር ፡ በቍጥር ፡ ፰፻፳፫ ፡ ከተመለከቱት ፡ አገላለጾች ፡ አንዱ ፡ ጕድለት ፡ ያለበት ፡ ሰነድ ፡ እንደ ፡ ተስፋ ፡ ወረቀት ፡ አይቈጠርም ።

(ሀ) የመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ያልተመለከተበት ፡ የተስፋ ፡ ወረቀት ፤ እንደ ፡ ቀረበ ፡ ወዲያውኑ ፡ የሚከፈል ፡ ሆኖ ፡ ይገመታል ።

(ለ) ሌላ ፡ ድንጋጌ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ከአውጪው ፡ ስም ፡ አጠገብ ፡ የተስፋ ፡ ወረቀት ፡ የተጻፈበት ፡ ቦታ ፤ ገንዘቡ ፡ የሚከፈልበት ፡ ቦታና ፡ እንዲሁም ፡ የአውጪው ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይቈጠራል ።

(ሐ) የተጻፈበትን ፡ ቦታ፤ የማያመለክት፡ የተስፋ ፡ ወረቀት ፡ ከአውጪው ፡ ስም ፡ አጠገብ ፡ የተመለከተው ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ይገመታል ።

ቊ፡ ፰፻፳፭። ወደ፡ ሐዋላ፡ ወረቀት፡ ድንጋጌዎች፡ ስለ፡መምራት ።

(፩) ከዚህ ፡ ሰነድ ፡ ዐይነት ፡ ጋራ ፡ የማይስማሙ ፡ ካልሆኑበት ፡ በቀር ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀትን ፡ የሚመለከቱት ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ያሉት ፡ ድንጋጌዎች ፤

(ሀ) በሰነድ ፣ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ስለ፡ መፈረም ፤ (ቍጥር ፡ ፯፻፴፭ ፡ እስከ ፡ ፯፻፵፰) ፤
(ለ) የመክፈያ ፡ ጊዜ ፡ ( ቍጥር ፡ ፯፻፸፱ ፡ እስከ ፡ ፯፻፹፫ ) ፤
(ሐ) ባልተከፈለ ፡ ጊዜ ፡ አቤቱታዎች ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ፡ ( ቍጥር ፡ ፯፻፹ ፡ እስከ ፡ ፯፻፹፫ ፤ ፯፻፹፭ ፡ እስከ ፡ ፯፻፹፯ ) ፤
(መ) ስለ ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ( ቍጥር ፡ ፯፻፹፰ ፡ እስከ ፡ ፯፻፺፩ ) ፤
(ሠ) አዲስ ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ስለ ፡ ማውጣት ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፺፫ ፤)
(ረ) በጕዳዩ ፡ ጣልቃ ፡ በመግባት ፡ ስለ ፡ መክፈል ፡ ( ቍጥር ፡ ፰፻፪ ፤ ፰፻፬ ፤ እስከ ፡ ፰፻፲ ) ፤
(ሰ) ስለ ፡ ግልባጮች ፡ ( ቍጥር ፡ ፰፻፲፬ ፡ እና ፡ ፰፻፲፭ ) ፤
(ሸ) ስለ ፡ መለዋወጥ ፡ ( ቍጥር ፡ ፰፻፲፯ ) ፤
(ቀ) ስለ ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፡ ( ቍጥር ፡ ፰፻፲፰ ፡ እና ፡ ፰፻፲፱ ፤ )
(በ) ስለ ፡ በዓል ፡ ቀኖች ፤ የተወሰኑ ፡ ጊዜዎች ፡ ግምትና ፡ የችሮታ ፡ ቀኖችን ፡ ስለ ፡ መከልከል ፡ ( ቍጥር ፡ ፰፻፲፮ ፡ እስከ ፡ ፰፻፳፪ ) ፤ በተስፋ ፡ ወረቀቶች ፡ ላይም ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ናቸው ።

(፪) እንዲሁም ፤ ባንድ ፡ በሦስተኛ ፡ ሰው ፡ አድራሻ ፡ ወይም ፡ የከፋዩ ፡ መደበኛ፡ መኖሪያ፡ ቦታ፣ ሳይሆን ፡ በሌላ፡ ቦታ፣ ውስጥ ፡ የሚከፈል ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀትን ፡ የሚመለከቱ፡ ውሳኔዎች)፤(ቍጥር፡ ፯፻፵፰፡ እና፡ ፯፻፸፫ ፤ የወለድ፡ ስምምነቶችን ፡ በውል ፡ ውስጥ ፡ ማግባት ፡ ( ቍጥር ፡ ፯፻፵፱ ) ፤ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ፡ ስለሚመለከቱት ፡ አገላለጾች ፡ ልዩነት ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፷) ፤ በቍጥር፡ ፯፻፷፭ ፡ በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ ፊርማን ፡ ማድረግ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ሥልጣን ፡ ሳይኖረው ፡ ወይም ፡ ከሥልጣኑ ፡ በላይ ፡ ስለሚያደርገው ፡ ፊርማ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፷፪) ፡ እና፡ ስም ፣ ሳይሞላ ፡ የወጣ ፡ የሐዋላ፡ ወረቀትን ፡ የሚመለከቱት ፡ የቍጥር ፡ ፯፻፷፬ ፡ ድንጋጌዎች ፤ በተስፋ ፡ ወረቀቶችም ፡ ላይ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ናቸው ።

(፫) እንዲሁም፣ ከዚህ፡ በታች፡ የተጠቀሱት፡ ቍጥሮች፡ በተስፋ፡ወረቀቶችም፡ ላይ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ። ስለ ፡ መክፈል ፡ ዋስትና ፡ የተመለከቱት፡ ድንጋጌዎች ፡ (ቍጥር፡ ከ፯፻፸፯፡እስከ፡ ፯፻፸፰) በቍጥር፡ ፯፻፸፯፡ በንኡስ፡ ቍ፡(፬) በተመለከቱት፡ ሁኔታዎች፡ ውስጥ፡ ለመክፈል፡ በዋስትና፡ እሺ፡ ባይነት፡ ለማን ፡ ተብሎ ፡ እንደ፡ ተሰጠ፡ያላመለከተ፡እንደ፡ሆነ፤ወረቀት፡ለአወጣው፡ሰው፡እንደ፡ተሰጠ፡ይቈጠራል።

ቍ ፡ ፰፻፹፯ ። ስለ ፡ አውጪው ፡ ኀላፊነት ፤ ስለ ፡ ማቅረብና ፡ ከቀረበበት ፡ አንሥቶ ፡ ስላለው ፡ ጊዜ ።

(፩) የተስፋ ፡ ሰነድ ፡ አውጪ ፤ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ በሚገደድበት ፡ ዐይነት ፡ ይገደዳል ።
(፪) ከቀረበበት ፡ አንሥቶ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚከፈል ፡ የተስፋ ፡ ወረቀት ፡ የሆነ ፡

እንደ ፡ ሆነ ፤ በቍጥር ፡ ፯፻፶፱ ፡ በተወሰኑት ፡ ጊዜዎች ፡ ውስጥ ፡ አውጪው ፡ ምልክት ፡ እንዲያደርግባቸው ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ። ከቀረበበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ የመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ የሚቈጠረው ፡ አውጪው ፡ ምልክት ፡ ካደረገና ፡ ከፈረመበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ። አውጪው ፡ ምልክትና ፡ ቀንን ፡ ለማድረግ ፡ እንቢ ፡ ያለ፡ እንደ፡ ሆነ፤ እንቢታው፡ በእንቢታ፡ ማስታወቂያ፡ ሕጋዊ፡ ጽሑፍ፡ መገለጽ፡ አለበት ። (ቍጥር ፡ ፯፻፷፩) ፤ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ የተጻፈበትም ፡ ቀን ፡ ወረቀቱ ፡ ከቀረበበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ለሚቈጠረው ፡ ቀን ፡ መነሻ ፡ ይሆናል ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## ስለ ፡ ቼክ ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ፡ ቼክ ፡ አጻጻፍና ፡ ሥርዐት ፡ ( ፎርም ) ።

**ቍ ፡ ፰፻፳፯ ። አስፈላጊ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ መግለጫዎች ።**

በቼክ ፡ ላይ ፡ የሚጻፈው ።

(ሀ) የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ ሐተታ ፡ የሌለበት ፡ ትእዛዝ ፤

(ለ) መክፈል ፡ የሚገባው ፡ ከፋይ ፡ ስም ፤

(ሐ) የሚከፈልበት ፡ ቦታ ፤

(መ) ቼኩ ፡ የወጣበት ፡ ቦታና ፡ ጊዜ ።

(ሠ) ቼኩን ፡ ያወጣው ፡ ሰው ፡ ፊርማ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፰፻፳፰ ። አስፈላጊ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ መግለጫዎች ፡ ጕድለት ።**

ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ባሉት ፡ ኀይለ ፡ ቃሎች ፡ በ (ሀ) (ለ) ውስጥ ፡ ከተወሰኑት ፡ ሁኔታዎች ፡ በቀር ፡ በቍጥር ፡ ፰፻፳፯ ፡ ከተመለከተው ፡ አገላለጽ ፡ አንዱ ፡ እንኳ፡ የሌለበት ፡ ሰነድ ፡ እንደ ፡ ቼክ ፡ አይቈጠርም ።

(ሀ) በልዩ ፡ የተመለከተ ፡ ቦታ ፡ ከሌለ ፡ በከፋዩ ፡ ስም ፡ አጠገብ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቦታ ፡ የመክፈያ ፡ ቦታ ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ። በከፋዩ ፡ ስም ፡ አጠገብ ፡ ብዙ ፡ ቦታዎች ፡ ተመልክተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መጀመሪያ ፡ በተመለከተው ፡ ቦታ ፡ ቼኩ ፡ ተከፋይ ፡ ይሆናል ።

(ለ) እነዚሁ ፡ ማመልከቻዎች ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ማመልከቻዎች ፡ ከሌሉ ፡ የከፋዩ ፡ ዋና ፡ ሥራ ፡ ማካሄጃ ፡ በሆነው ፡ ቦታ ፡ ቼኩ ፡ ተከፋይ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ፰፻፳፱ ። ከፋዩን ፡ ስለ ፡ ማመልከት ።**

ቼኩ ፡ ባንድ ፡ ባለባንክ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ እንደ ፡ ባንክ ፡ በታወቀ ፡ ባንድ ፡ ሥራ፡ ማካሄጃና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ካልሆነ ፡ እንዲከፈል ፡ ሊታዘዝ ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ፰፻፴ ። የገንዘብ ፡ ሥንቅ ፡ አስቀድሞ ፡ ስለ ፡ መኖር ።

(፩) አውጪው ፡ ለራሱ ፡ ተቀማጭ ፡ ገንዘብ ፡ በከፋዩ ፡ ዘንድ ፡ ያለውና ፡ በግልጽ፡ ወይም ፡ በዝምታ ፡ ባንድ ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ አውጪው ፡ በዚሁ ፡ የተነሣ፡ ገንዘቡን ፡ በቼክ ፡ ሊያዝበት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ቼኩ ፡ ተጽፎ ፡ ሊወጣ ፡ አይችልም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እነዚህ ፡ ትእዛዞች ፡ ያልተከበሩ ፡ ቢሆንም ፡ የቼኩ ፡ ባለዋጋንት ፡ አይነካም ።

(፪) እንቢ ፡ የተባለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አውጪው ፡ ሰነዱን ፡ በሰጠ ፡ ጊዜ ፡ ከከፋዩ ፡ ዘንድ ፡ የገንዘብ ፡ ሥንቅ ፡ መኖሩን ፡ ማስረዳት ፡ ያለበት ፡ አውጪው ፡ ብቻ ፡ ነው ። ያለዚያ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ የእንቢታው ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተወሰኑት ፡ ጊዜ ዎች ፡ በኋላ ፡ ቢደረግ ፡ አውጪው ፡ ዋስ ፡ እንዲሆነው ፡ ይገደዳል ።

ቍ ፡ ፰፻፴፩ ። እሺታ ፡ ስላለመኖሩ ።

ቼኩ ፡ ላይ ፡ እሺ ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ ሊጻፍበት ፡ አይቻልም ። የእሺታ ፡ ጽሑፍ ፡ በቼኩ ፡ ላይ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንዳልተጻፈ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፰፻፴፪ ። ገንዘብ ፡ መኖሩን ፡ በቼኩ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መመስከር ።

(፩) ተቃራኒ ፡ ውሳኔዎች ፡ ቢኖሩም ፡ አውጪው ፡ የሚያዝበት ፡ የገንዘብ ፡ ሥንቅ ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አውጪው ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ከፋዩ ፡ ገንዘብ ፡ መኖሩን ፡ በቼኩ ፡ ላይ ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ።

(፪) ለተረጋገጠው ፡ ቼክ ፡ የገንዘብ ፡ ሥንቅ ፡ ለአምጪው ፡ ጥቅም ፡ በቍጥር ፡ ፰፻፶፭ ፡ እስከ ፡ ተወሰነው ፡ የማቅረብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በልዩ ፡ ሒሳብ ፡ ተይዞ ፡ ይቈያል ።

(፫) በጽሑፍ ፡ የማረጋገጡ ፡ ተግባርም ፡ ከፋዩ ፡ በቼኩ ፡ ፊት ፡ በመፈረሙ ፡ ይታወቃል ።

ቍ ፡ ፰፻፴፫ ። ተከፋዩን ፡ ስለ ፡ ማመልከት ።

(፩) አንድ ፡ ቼክ ፤

(ሀ) ስሙ ፡ ለተጠቀሰው ፡ አንድ ፡ ሰው ፤ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ አጻጻፍ ፡ "በትእዛዝ ፡" የሚል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ ባይኖርም ፤ ወይም ፤

(ለ) ስሙ ፡ ለተጠቀሰ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ « ያለትእዛዝ » ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመ ሰለ ፡ ቃል ፡ ያለበት ፤ ወይም ፤

(ሐ) ለአምጪው ፤ እንዲከፍል ፡ ተብሎ ፡ ሊጻፍ ፡ ይቻላል ።

(፪) «ወይም ፡ ለአምጪው» ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ቃል ፡ ያለበት ፡ በአንዱ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ የወጣ ፡ ቼክ ፡ ለአምጪው ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ቼክ ፡ ይቈጠራል ።

(፫) የተከፋይ ፡ ስም ፡ የሌለበት ፡ ቼክ ፡ ለአምጪው ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ቼክ ፡ ይቈ ጠራል ።

ቍ ፡ ፰፻፴፩ ። በአውጪው ፡ ለራሱ ፡ የታዘዘ ፡ ቼክና ፡ በአውጪው ፡ ላይ ፡ የታዘዘ ፡ ቼክ ።

(፩) ቼኩ ፡ ለአውጪው ፡ ለራሱ ፡ የታዘዘ ፡ ለመሆን ፡ ይቻላል ።
(፪) ቼኩ ፡ ላንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ሊታዘዝ ፡ ይቻላል ።
(፫) ባለባንኩ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የሚያዘው ፡ ቼክ ፡ ለአምጪው ፡ እንዲከፈል ፡ የሚል፡ አይሆንም ።

ቍ ፡ ፰፻፴፪ ። ወለዱን ፡ በቼኩ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ መጥቀስ ።

በቼኩ ፡ ውስጥ ፡ ወለድን ፡ የሚጠቅስ ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ እንዳልተጻፈ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፰፻፴፫ ። የሚከፈልበት ፡ ቦታና ፡ የመክፈያው ፡ መደበኛ ፡ ቦታ ፡ የተወሰነለት ፡ ቼክ ።

ባንድ ፡ ሦስተኛ፡ ሰው ፡ መደበኛ፡ መኖሪያው፡ ቦታ ፡ ቼኩ ፡ ሊከፈል ፡ የሚቻለው ፡ የከፋይ ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ባለበት ፡ ቦታ ፤ ወይም ፡ ይህ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ባለባንክ ፡ ከሆነ ፡ በማንኛውም ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፰፻፴፬ ። በገንዘብ ፡ ልክ ፡ አጻጻፍ ፡ ስለሚገኝ ፡ ልዩነት ።

(፩) የቼኩ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በፊደልና ፡ በአኀዝ ፡ ተጽፎ ፡ ልዩነት ፡ በተገኘበት ፡ ጊዜ ፡ በፊደል ፡ ተገልጾ ፡ የተጻፈው ፡ ዋጋ ፡ መከፈል ፡ አለበት ።
(፪) በፊደልም ፡ ቢሆን ፡ በአኀዝ፡ብዙ፡ጊዜ፡የገንዘቡ ፡ ልክ ፡ የተጻፈበት ፡ ቼክ፡ ልዩነት፡ያመጣ፡እንደ፡ሆነ ፤ በአነስተኛ ፡ የተጻፈው ፡ ገንዘብ ፡ ዋጋ፡መከፈል፡አለበት ።

ቍ ፡ ፰፻፴፭ ። ለመገደድ ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ፊርማ ።

በቼኩ ፡ ወረቀት ፡ ለመገደድ ፡ ችሎታ ፡ በሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ፊርማዎች ፡ ቼኩ ፡ ተፈርሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ሐሰት ፡ የሆኑ ፡ ፊርማዎች ፡ ወይም ፡ የሌሉ ፡ ሰዎች ፡ ፊርማዎች ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ሁሉ ፡ ፊርማዎቹ ፡ ቼኩን ፡ የፈረሙትን ፡ ሰዎች ፡ ለማስገደድ ፡ የማይቻል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ በእነሱ ፡ ስም ፡ የተፈረመ ፡ ፊርማ ፡ ያለበት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ግዴታ ፡ ውስጥ ፡ የገቡ ፡ የሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ፊርማ ፡ የሚጸና ፡ መሆኑ ፡ አይቀርም ።

ቍ ፡ ፰፻፴፮ ። ሥልጣን ፡ ሳይኖር ፡ ስለ ፡ መፈረም ።

ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ ወኪል ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ ሥልጣን ፡ ሳይሰጠው ፡ ባንድ ፡ ቼክ ፡ ላይ ፡ የፈረመ ፡ በቼኩ ፡ መሠረት ፡ ራሱ ፡ የተገደደ ፡ ሆኖ ፡ የከፈለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተወከልኩለት ፡ የሚለው ፡ ሰው ፡ ሊኖረው ፡ የሚችለው ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ። ይኸውም ፡ መብት ፡ ከሥልጣን ፡ በላይ ፡ ለሠራ ፡ ወኪልም፡ ይጸናል ።

ቍ ፡ ፰፻፴፯ ። የአውጪው ፡ ኀላፊነት ።

አውጪው ፡ ለአከፋፈሉ ፡ ዋስ ፡ ነው ፤ ከዚህ ፡ ዋስትና ፡ ኀላፊነት ፡ ለመዳን ፡ የሚጻፈው ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ እንዳልተጻፈ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፰፻፵፩ ። በሚወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ጕድለት ፡ ስላለው ፡ ቼክ ።**

በሚወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ጕድለት ፡ ያለው ፡ ቼክ ፡ ለተደረጉት ፡ ስምምነቶች ፡ ተቃራኒ ፡ በመሆን ፡ የተሞላ ፡ እንደሆን ፤ በክፉ ፡ ልቡና ፡ ቼኩን ፡ ካላገኘ ፡ ወይም ፡ ሲያገኝ ፡ ከባድ ፡ ጥፋት ፡ ካላደረገ ፡ የነዚሁ ፡ ስምምነቶች ፡ አለመፈጸም ፡ በአምጪው ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ማስተላለፍ ።

**ቍ ፡ ፰፻፵፪ ፡ ሊተላለፍ ፡ የሚችል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።**

(፩) ስሙ ፡ ለተጠራ ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ አጻጻፍ ፡ « በትእዛዝ » ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ ባይኖርም ፡ እንዲከፈል ፡ የሚል ፡ አነጋገር ፡ ያለበት ፡ ቼክ ፡ በጀርባ ፡ በመፈረም ፡ የሚተላለፍ ፡ ይሆናል ።

(፪) ስሙ ፡ ለተጠራ ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ ጥቅም ፡ « የትእዛዝ ፡ ያልሆነ » ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ቃል ፡ የያዘ ፡ እንዲከፈል ፡ የሚል ፡ አነጋገር ፡ ያለበት ፡ ቼክ ፡ ሊተላለፍ ፡ የሚችለው ፡ መደበኛ ፡ በሆነው ፡ የማስተላለፍ ፡ ፎርምና ፡ ለዚሁ ፡ ማስተላለፍ ፡ ባለው ፡ ውጤት ፡ ነው ።

(፫) የጀርባው ፡ ፈርማ ፤ ለአውጪው ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ግዴታ ፡ ላለበት ፡ ሁሉ ፡ ጥቅም ፡ መደረግ ፡ ይቻላል ፤ እነዚህም ፡ ሰዎች ፡ እንደገና ፡ በቼኩ ፡ ጀርባ ፡ ፈርመው ፡ ለማስተላለፍ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፰፻፵፫ ። በጀርባው ፡ የመፈረም ፡ አቋሞች ።**

(፩) የጀርባውም ፡ ፈርማ ፡ ያለ ፡ ሐተታ ፡ መሆን ፡ አለበት ፤ በጀርባው ፡ ላይ ፡ በሚጻፈው ፡ ፈርማ ፡ ላይ ፡ የተደረገ ፡ ሐተታ ፡ ሁሉ ፡ እንዳልተጻፈ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) በከፊል ፡ ለማስተላለፍ ፡ በጀርባ ፡ መፈረም ፡ የማይጸና ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ከፋዩ ፡ በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ የፈረመው ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፫) "ለአምጪው" ፡ ተብሎ ፡ በጀርባ ፡ የተፈረመ ፡ ፈርማ ፡ ስም ፡ እንዳልተሞላበት ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ።

(፬) ከፋዩ ፡ ሌሎች ፡ ብዙ ፡ የባንክ ፡ የሥራ ፡ ማካሄጃ ፡ ቦታዎች ፡ ያሉት ፡ ከሆነና ፡ በቼኩ ፡ ጀርባ ፡ የተፈረመለት ፤ ቼኩን ፡ እንዲከፍል ፡ የተፈረመበት ፡ የሥራ ፡ ማካሄጃ ፡ ቅርንጫፍ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ሳይሆን ፡ ለሌላው ፡ ቅርንጫፍ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጥቅም ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለአምጪው ፡ የተደረገው ፡ የጀርባ ፡ ፈርማ ፡ እንደ ፡ ደረሰኝ ፡ ብቻ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፰፻፵፬ ። በወረቀቱ ፡ ጀርባ ፡ የአፈራረም ፡ ሥርዐት ፡ ( ፎርም ) ።**

(፩) የጀርባውም ፡ ፈርማ ፡ በቼኩ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በተያያዘው ፡ አንድ ፡

ቅጥል ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ፤ በጀርባ ፡ የሚጽፈውም ፡ ሰው ፡ መፈረም ፡ አለበት ።

(፪) የጀርባውም ፡ ፊርማ ፡ ተጠቃሚውን ፡ ሳይጠራ ፡ ወይም ፡ በጀርባ ፡ በሚጽፈው ፡ ሰው ፡ ፊርማ ፡ ብቻ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ። ( ስም ፡ ሳይሞላ ፡ መፈረም ) ፡ የዚህ ፡ የመጨረሻው ፡ ፊርማ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ እንዲሆን ፡ በቼኩ ፡ ጀርባ ፡ ወይም ፡ በተያያዘው ፡ አንድ ፡ ቅጥል ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ መጻፍ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፰፻፵፩ ። ውጤቶች ።

(፩) የጀርባ ፡ ፊርማውም ፡ በቼኩ ፡ የሚገኙትን ፡ መብቶችና ፡ በተለይም ፡ በቍጥር ፡ ፰፻፩ ፡ እንደ ፡ ተወሰነው ፡ አኳኋን ፡ በገንዘብ ፡ ሥንቅ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መብቶች ፡ ያስተላልፋል ።

(፪) የጀርባውም ፡ ፊርማ ፡ ስም ፡ ያልተሞላበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አምጪው ፤

(ሀ) ያልተሞላውን ፡ ስም ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ መሙላት ፡ ወይም ፤

(ለ) ቼኩን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሳይሞላ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ በጀርባው ፡ ፈርሞ ፡ ማስተላለፍ ፡ ወይም ፤

(ሐ) ስም ፡ ሳይሞላና ፡ በጀርባው ፡ ሳይፈርም ፡ ቼኩን ፡ ላንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ መስጠት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፰፻፵፪ ። ዋስትና ።

(፩) ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ካልኖረ ፡ በጀርባ ፡ የሚፈርመው ፡ ሰው ፡ ለአከፋፈሉ ፡ ዋስ ፡ ነው ።

(፪) አዲስ ፡ በጀርባ ፡ መፈረምን ፡ ለመከልከል ፡ ይችላል ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቼኩ ፡ ከዚያ፡በኋላ፡በጀርባ፡ተፈርሞ፡ ለተላለፈላቸው፡ሰዎች ፡ ዋስ ፡ መሆን ፡ የለበትም ።

ቍ ፡ ፰፻፵፫ ። የአምጪውን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ማረጋገጥ ።

በጀርባው ፡ ሊፈረምበት ፡ የሚቻል ፡ ቼክ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ የመጨረሻው፡ በጀርባ ፡ መፈረም ፡ ስም ፡ ያልተሞላበት ፡ ቢሆን ፡ ባለማቋረጥ ፡ ተከታትሎ ፡ በሚገኝ ፡ የጀርባ ፡ ፊርማ ፡ መብቱን ፡ ያረጋገጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሕጋዊ ፡ አምጪ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ይገመታል ። ለዚህ ፡ ጕዳይ ፡ የተሰረዙ ፡ የጀርባ ፡ ፊርማዎች ፡ እንዳልተጻፉ ፡ ይቈጠራል ። ስም ፡ ሳይሞላ ፡ በጀርባ ፡ መፈረም ፡ ሌላ ፡ የጀርባ ፡ ፊርማ ፡ ተከትሎት፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህንኑ ፡ የፈረመው ፡ ሰው ፡ ቼኩን ፡ ስም ፡ ሳይሞላ ፡ በጀርባው ፡ በተጻፈው ፡ ፊርማ ፡ እንዳገኘው ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፰፻፵፬ ። ለአምጪው ፡ የሆነ ፡ ቼክ ።

ለአምጪው ፡ በሆነ ፡ ቼክ ፡ ላይ ፡ የተደረገ ፡ የጀርባ ፡ ፊርማ ፡ በጀርባ ፡ የፈረመውን ፡ ሰው ፡ አቤቱታ ፡ መብት ፡ በሚመለከቱ ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ ኀላፊ ፡

ያደርገዋል ። በመፈረሙ ፡ ሰነዱን ፡ በትእዛዝ ፡ በሆነ ፡ ቼክ ፡ አይለውጠውም ።

**ቍ ፡ ፰፻፵፱ ። ይዞታን ፡ ስለማጣት ።**

አንድ ፡ ሰው ፡ በማንኛውም ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ ቼክ ፡ ከእጁ ፡ የወጣበት ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ቼኩ ፡ በጁ ፡ የደረሰው ፡ አምጪ ፡ (ቼኩ ፡ ላምጪው ፡ የሚል ፡ ቢሆንም ፡ ወይም ፡ በጀርባው ፡ ሊፈረምበት፡የሚቻል ፡ ቼክ ፡ ቢሆንም ፡ በቍጥር ፡ ፰፻፵፯ ፡ በተ መለከተው ፡ ዐይነት ፡ ለዚሁ ፡ ቼክ ፡ አምጪው ፡ መብቱን ፡ ካረጋገጠ ፡ ) በክፉ ፡ ልቡና ፡ ካላገኘው ፡ ወይም ፡ ሲያገኝ ፡ ከባድ ፡ ጥፋት ፡ ካላደረገ ፡ በቀር ፡ ቼኩን ፡ ለመልቀቅ ፡ አይገደድም ።

**ቍ ፡ ፰፻፶ ። መቃወሚያ ።**

አምጪው ፡ ቼኩን ፡ ሲያገኝ ፡ ዐውቆ ፡ ባለዕዳውን ፡ ለመጉዳት ፡ ካላደረገ ፡ በቀር፡ በቼኩ ፡ መሠረት ፡ የተከሰሱት ፡ ሰዎች፡ከአወጪው፡ጋራ ፡ ወይም ፡ በፊት ፡ አምጪ፡ ከሆኑት ፡ ጋራ ፡ በግል ፡ ግንኙነታቸው ፡ ላይ ፡ በተመሠረቱት ፡ ልዩነቶች ፡ አም ጪውን ፡ ሊቃወሙት ፡ አይችሉም ።

**ቍ ፡ ፰፻፶፩ ። በመወከል ፡ በጀርባ ፡ ስለ ፡ መፈረም ።**

(፩) "ገንዘብ ፡ ስለ ፡ ማስገባት" ፤ "ስለ ፡ መቀበል" ፤ "ስለ ፡ መወከል" ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ማናቸውንም ፡ የውክልና ፡ ትእዛዝ ፡ አለበት ፡ የሚያሰኝ ፡ ጽሑፍ ፡ በቼኩ ፡ ጀርባ ፡ ተጽፎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አምጪው ፡ በቼኩ ፡ ውስጥ፡ባሉት፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ ሊሠራባቸው ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በመወከል ፡ ስም ፡ ካል ሆነ ፡ በቀር ፡ ቼኩን ፡ በጀርባው ፡ ላይ ፡ ፈርሞ ፡ ሊያስተላልፍ ፡ አይችልም ።

(፪) እንዲሁ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በጀርባ ፡ ለፈረመ ፡ ሰው ፡ መቃወሚያ ፡ በሚሆኑት ፡ መከላከያ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ተገዳጆቹ ፡ በአምጪው ፡ ሌላ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊያ ቀርቡበት ፡ አይችሉም ።

(፫) በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ በተጻፈ ፡ ውስጥ ፡ የተሰጠው ፡ ውክልና ፡ ወካዩ ፡ መሞት ፡ ወይም ፡ በሚደርስበት ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ አይቀርም ።

**ቍ ፡ ፰፻፶፪ ። ከመክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ በኋላ ፡ በጀርባ፡ ስለ ፡ መፈረም ።**

(፩) ከእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ከመሰለ ፡ ማረጋገጫ ፡ ወይም ፡ ቼኩን ፡ ለማቅረብ ፡ ከተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ የሚደረገው ፡ የጀርባ ፡ ፊርማ ፡ የመደበኛ ፡ ማስተላለፍ ፡ ውጤት ፡ ይኖረዋል ።

(፪) ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ ቀን ፡ የሌለበት ፡ የጀርባ ፡ ፊርማ ፡ ከእን ቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ከመሰሉ ፡ ማረጋገጫዎች ፡ ወይም ፡ በን ኡስ ፡ ቍ ፡ ፩፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከማለፉ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ይቈጠራል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ስለ ፡ ማለት ፡ (አባል) ።

**ቍ ፡ ፰፻፶፫ ።** ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

ስለ ፡ መክፈል ፡ ዋስትና ፡ በመስጠት ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፸፮ ፡ እስከ ፡ ፯፻፹፯ ፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በቼክ ፡ ላይም ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

## ቼኩን ፡ ስለ ፡ ማቅረብና ፡ ስለ ፡ መክፈል ።

**ቍ ፡ ፰፻፶፬ ።** የመክፈያው ፡ ጊዜ ።

ቼክ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ የሚከፈልበት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፰፻፶፭ ።** ለመክፈል ፡ መቅረብ ።

ቼኩ ፡ የወጣበት ፡ ቀን ፡ ከግምት ፡ ውስጥ ፡ ሳይገባ ፤ በቼኩ ፡ ላይ ፡ ከተጻፈው ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሚከተሉት ፡ ስድስት ፡ ወራት ፡ ውስጥ ፤ እንዲከፈልበት ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፰፻፶፮ ።** ስለ ፡ ቀን ፡ መቍጠሪያዎች ፡ ልዩነት ።

አንድ ፡ ቼክ ፡ የቀን ፡ መቍጠሪያዎቻቸው ፡ ልዩ ፡ በሆኑ ፡ በሁለት ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ የወጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሚከፈልበት ፡ ቦታ ፡ ባለው ፡ የቀን ፡ መቍጠሪያ ፡ ባሚገናዘብበት ፡ ቀን ፡ የመውጫው ፡ ቀን ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፰፻፶፯ ።** መክፈልን ፡ ስለ ፡ ማቆም ።

ቼኩ ፡ ከመከፈሉ ፡ አስቀድሞ ፤ አውጪው ፡ እንዳትከፍል ፡ ብሎ ፡ የነገረው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባንኩ ፡ የቼኩን ፡ ዋጋ ፡ አልከፍልም ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፰፻፶፰ ።** ቼኩ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ አውጪው ፡ መሞት ።

ቼኩ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ የአውጪው ፡ ሞት ፡ ወይም ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ የቼኩን ፡ ውጤቶች ፡ አይነካም ።

**ቍ ፡ ፰፻፶፱ ።** የደረሰኝ ፡ ሰነድ ፡ በከፊል ፡ የሚሆን ፡ አከፋፈል ።

(፩) ከፋዩ ፡ የቼኩን ፡ ገንዘብ ፡ ሲከፍል ፡ ደረሰኝ ፡ እንዲፈረምበት ፡ አምጪውን ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፪) አምጪው ፡ በከፊል ፡ የሆነውን ፡ አከፋፈል ፡ እንቢ ፡ ማለት ፡ አይችልም ።

(፫) የገንዘቡ ፡ ሥንቅ ፡ በቼኩ ፡ ላይ ፡ ከተጻፈው ፡ ገንዘብ ፡ ያነስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አምጪው ፤ ባለው ፡ የገንዘብ ፡ ሥንቅ ፡ ልክ ፡ እንዲከፍለው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) አከፋፈሉ ፡ በከፊል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከፋዩ ፡ ይኸው ፡ አከፋፈል ፡ በቼኩ ፡ ላይ ፡ እንዲገለጽና ፡ ደረሰኝም ፡ እንዲሰጠው ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

(፫) ካንድ ፡ ቼክ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ በከፊል ፡ የተደረገ ፡ መክፈል ፡ አውጪዎቹንና ፡ በጀርባው ፡ የሚፈርሙትን ፡ ሰዎች ፡ በዚያ ፡ ልክ ፡ ከዕዳ ፡ ነጻ ፡ ያደርጋቸዋል ።

(፬) ስለ ፡ ቀሪው ፡ ገንዘብ ፤ አምጪው ፡ ለቼኩ ፡ የአንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ማስደረግ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፰፻፵፰ ። በቼኩ ፡ ጀርባ ፡ የተፈረሙትን ፡ ስለ ፡ መመርመር ።**

በጀርባው ፡ ላይ ፡ በመፈረም ፡ የሚተላለፍን ፡ ቼክ ፡ የሚከፍል ፡ ከፋዩ ፤ በቼኩ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ፈርመው ፡ ያስተላለፉትን ፡ ሰዎች ፡ ፊርማ ፡ መርምሮ ፡ እንዲያጣራ ፡ አይገደድም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የአውጪውንና ፡ የመጨረሻውን ፡ በጀርባ ፡ የተፈረመለትን ፡ ተቀባይ ፡ ፊርማ ፡ መርምሮ ፡ ማጣራት ፡ ይኖርበታል ።

**ቍ ፡ ፰፻፵፱ ። ስለ ፡ ከፋዩ ፡ ነጻ ፡ መውጣት ።**

ተቃዋሚ ፡ ነገር ፡ ሳይደርሰው ፡ በቅን ፡ ልቡናና ፡ በሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ በተለመደው ፡ አኳኋን ፡ አንድ ፡ ቼክ ፡ የከፈለ ፡ ከፋይ ፡ በሚገባ ፡ ነጻ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፰፻፶ ። በውጭ ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መክፈል ።**

(፩) በሚከፈልበት ፡ አገር ፡ ባልሆነ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ በአንድ ፡ ቼክ ፡ ላይ ፡ የተጻፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በቼኩ ፡ የተጻፈ ፡ ገንዘብ ፡ ቼኩ ፡ እንዲቀርብ ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በሚከፈልበት ፡ ቀን ፡ ባለው ፡ በአገሩ ፡ ገንዘብ ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ለመክፈል ፡ ይቻላል ። ቼኩ ፡ ቀርቦ ፡ ያልተከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አምጪው ፡ በመረጠው ፡ በሚያቀርብበት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ በሚከፈልበት ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ አገሩ ፡ ምንዛሪ ፡ የቼኩ ፡ ገንዘብ ፡ ቼኩ ፡ በሚከፈልበት ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈለው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ በቼኩ ፡ ውስጥ ፡ በተወሰነው ፡ ምንዛሪ ፡ የሚቈጠር ፡ መሆኑን ፡ አውጪው ፡ በጽሑፍ ፡ ለመግለጽ ፡ ይችላል ።

(፫) በአንድ ፡ በተለየ ፡ ገንዘብ ፡ ይከፈላል ፡ ብሎ ፡ አውጪው ፡ የጽሑፍ ፡ ቃል ፡ ያገባ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ እና ፡ ፪ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ አይሆኑም ፡ ( የመጨረሻው ፡ አከፋፈል ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ እንዲሆን ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ) ።

(፬) የቼኩ ፡ ገንዘብ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ስም ፡ ባለው ፡ ገንዘብ ፡ የተመለከተ ፡ ሆኖ ፡ በሚወጣበትና ፡ በሚከፈልበት ፡ አገር ፡ ዋጋው ፡ ልዩነት ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ የሚከፈልበትን ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ ለመጥቀስ ፡ እንደ ፡ ታሰበ ፡ ይገመታል ።

## ክፍል ፡ ፭ ።

## የስርዝ ፡ ምልክት ፡ ያለበት ፡ ቼክና ፡ ከሒሳብ ፡ ውስጥ ፡

## የሚገባ ፡ ቼክ ።

**ቍ ፡ ፰፻፷፫ ። የስርዝ ፡ ምልክት ፡ ያለበት ፡ ቼክ ፤ ትርጓሜ ።**

(፩) በቍጥር ፡ ፰፻፷፬ ፡ የተነገሩትን ፡ ውጤቶች ፡ ለማስገኘት ፡ ቼኩን ፡ የያዘ ፡ አምጪ ፡ ወይም ፡ አውጪ ፡ በቼኩ ፡ ላይ ፡ የስርዝ ፡ ምልክት ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) የስርዙም ፡ ምልክት ፡ በቼኩ ፡ ፊት ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ በሆኑ ፡ ሁለት ፡ መሥመሮች ፡ ይደረጋል ፤ ጠቅላላ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ስርዝ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

(፫) ስርዙም ፡ ጠቅላላ ፡ ለመሆን ፡ የሚችለው ፤ በሁለቱ ፡ መሥመሮች ፡ መካከል ፡ ምንም ፡ መግለጫ ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ « ባለባንኩ » ፡ የሚል ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ ቃል ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ። ልዩ ፡ ስርዝ ፡ የሚ ሆነውም ፡ በሁለቱ ፡ መሥመሮች ፡ መካከል ፡ የባለባንኩ ፡ ስም ፡ የተጻፈበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፬) ጠቅላላ ፡ አሰራረዝ ፡ በልዩ ፡ አሰራረዝ ፡ ለመለወጥ ፡ ይቻላል ፤ ልዩውን ፡ አሰ ራረዝ ፡ ግን ፡ በጠቅላላው ፡ አሰራረዝ ፡ ለመለወጥ ፡ አይቻልም ።

(፭) አሰራረዙ ፡ ወይም ፡ የተመለከተውን ፡ የባለባንክ ፡ ስም ፡ የተደመሰሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መደምሰሱ ፡ እንዳልተደረገ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፰፻፷፬ ። ውጤቶች ።**

(፩) ጠቅላላ ፡ አሰራረዝ ፡ ያለበት ፡ ቼክ ፤ ላንድ ፡ ባለባንክ ፡ ወይም ፡ ለከፋዩ ፡ አንድ ፡ ደንበኛ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሊከፈልበት ፡ አይቻልም ።

(፪) ልዩ ፡ አሰራረዝ ፡ ያለበት ፡ ቼክ ፡ ለተመለከተ ፡ ባለባንክ ፡ ወይም ፡ ይኸው ፡ ባለባንክ ፡ ከፋዩ ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ለደንበኛው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሊከፈል፡ አይቻልም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የተመለከተው ፡ ባለባንክ ፡ ገንዘቡን ፡ እንዲቀበል ለት ፡ ሌላውን ፡ ባንክ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) አንድ ፡ ባለባንክ ፡ ከደንበኞቹ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ ሌላ ፡ ባለባንክ ፡ ላይ ፡ ካልሆነ ፡ የስርዝ ፡ ምልክት ፡ ያለበት ፡ ቼክ ፡ ለመቀበል ፡ አይችልም ። ለነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ ካልሆነ ፤ ለሌሎች ፡ ፈንታ ፡ ብሎ ፡ ገንዘቡን ፡ ለመቀበል ፡ አይችልም ።

(፬) እንዱ ፡ ካንዱ ፡ ተቃራኒ ፡ ወይም ፡ የማይስማማ ፡ የሆነ ፡ ልዩ ፡ የአሰራረዝ ፡ ምልክት ፡ ያለበት ፡ ቼክ ፡ አይከፈልበትም ።

BACK



**ቍ ፡ ፰፻፷፮ ። « የማይተላለፍ » ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ የያዘ ፡ የስርዝ ፡ ምልክት ፡ ያለበት ፡ ቼክ ።**

(፩) የስርዝ ፡ ምልክት ፡ ያለበት ፡ ቼክ ፡ «የማይተላለፍ» ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ ሊኖርበት ፡ ይችላል ።

(፪) «የማይተላለፍ» ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ የተጻፈበትን ፡ የተሰረዘ ፡ ቼክ ፡ የተቀበለ ፡ ሰው ፤ በቼኩ ፡ ላይ ፡ ቼኩን ፡ ከሰጠው ፡ ሰው ፡ የበለጠ ፡ መብት ፡ ሊኖረው ፡ አይገባም ። ይኸንኑም ፡ ቼክ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ለማስተላለፍ ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፤ እሱ ፡ ራሱ ፡ ካለው ፡ የበለጠ ፡ መብት ፡ ለማስተላለፍ ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፰፻፷፯ ። የባለባንኩ ፡ ኀላፊነት ።**

(፩) በቍጥር ፡ ፰፻፷፬ ፡ እና ፡ ፰፻፷፭ ፡ የተመለከቱትን ፡ ውሳኔዎችን ፡ ያልጠበቀ ፡ ባለባንክ ፡ ለሚደረገው ፡ ጉዳት ፡ በቼኩ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ገንዘብ ፡ እስከ ሚተካከል ፡ ገንዘብ ፡ ድረስ ፡ ኀላፊ ፡ ነው ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ ቸልተኝነት ፡ ሳይኖርበት ፡ ቼኩን ፡ የሚከፍለው ፡ ባለባንክ ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑትን ፡ ደንቦች ፡ ተቃራኒ ፡ በመሆን ፡ እሰራረዙ ፡ የተበላሸ ፤ የተደመሰሰ፡ ወይም ፡ የተለወጠ ፡ ቢሆንም ፡ ኀላፊነት ፡ አይደርስበትም ። ለእውነተኛው ፡ የቼክ ፡ ባለሀብት ፡ እንደ ፡ ከፈለ ፡ ይቈጠራል ።

(፫) በቅን ፡ ልቡናና ፡ ቸልተኝነት ፡ ሳይኖረው ፡ ስላንድ ፡ ደንበኛ ፡ ሆኖ ፡ አንድ ፡ የስርዝ ፡ ምልክት ፡ ያለበት ፡ ቼክ ፡ እንዲከፈለው ፡ የሚቀበል ፡ ባለባንክ ፡ ደንበኛው ፡ በሰነዱ ፡ ላይ ፡ መብት ፡ የሌለው ፡ ወይም ፡ መብቱ ፡ አንድ ፡ ጕድለት ፡ ያለበት ፡ ቢሆንም ፡ ምንም ፡ ኀላፊነት ፡ አይደርስበትም ።

(፬) አንድ ፡ ባለባንክ ፡ አስቀድሞ ፡ የስርዝ ፡ ምልክት ፡ ባለበት ፡ ቼክ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ገንዘብ ፡ በደንበኛው ፡ ሰው ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ በማግባት ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተደነገጉትን ፡ ውሳኔዎች ፡ የሚሰጡትን ፡ ጥቅም ፡ አያሳጣውም ።

**ቍ ፡ ፰፻፷፰ ። ከሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ የሚገባ ፡ ቼክ ።**

(፩) በጀርባው ፡ ላይ ፡ « ከሒሳቡ ፡ ውስጥ ፡ የሚገባ » ፡ የሚል ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ቃል ፡ በማ ባት ፡ በፊቱ ፡ በአግድም ፡ መሥመር ፡ አጻጻፍ ፡ አምጪው ፡ ወይም ፡ አውጪው ፡ ቼኩ ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ እንዳይከፈለው ፡ መከልከል ፡ ይችላል ።

(፪) ይህ፡ ሲሆን፡ ለከፋዩ፡ በጽሑፍ፡ አከፋፈል፡ ካልሆነ፡ ቼኩ፡ ጥሬ፡ ገንዘብ፡ ሊከፈልበት፡አይቻልም።(በሒሳብ፡ ላይ፡ ማግባት፤ ከአንዱ፡ ሒሳብ፡ ወደሌላው፡ ሒሳብ፡ ማዘዋወር ፤ ወይም ፡ በሒሳብ ፡ ማቻቻል ፡ ወይም ፡ ቼኮች ፡ በሚሰበሰቡበት ፡ ቦታ ፡ ማቻቻል) ። በጽሑፍ ፡ የተደረገ ፡ አከፋፈል ፡ በገንዘብ ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ አከፋፈል ፡ ይቈጠራል ።

(፫) « በሒሳብ ፡ ላይ ፡ መግባት » ፡ የሚለው ፡ ጽሑፍ ፡ የተሰረዘ ፡ እንደ ፡ ሆን ፤ ስርዙ ፡ እንዳልተደረገ ፡ ይቈጠራል ።

(፬) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱትን ፡ ውሳኔዎች ፡ ያልጠበቀ ፡ ከፋይ ፡ በቍጥር ፡ ፰፻፹፪ ፡ በተደነገጉት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ ለሚደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ኀላፊ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፯ ።

## ሳይከፈል ፡ በመቅረቱ ፡ አቤቱታ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

### ቍ ፡ ፰፻፹፫ ። የእምጪው ፡ መብት ።

በሚገባው ፡ ጊዜ ፡ የቀረበው ፡ ቼክ፡ ያልተከፈለበት፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የአከፋፈሉም ፡ እንቢታ ፡ የተገለጸው ፤

(ሀ) ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ጽሑፍ ፡ ( የእሽታ ፡ ማስታወቂያ ) ፡ ወይም ፤

(ለ) በቼኩ ፡ ላይ ፡ ቀን ፡ በማድረግና ፡ በማጻፍ ፡ የቀረበበትንም ፡ ቀን ፡ በማመልከት ፡ ከፋዩ ፡ በሰጠው ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፤

(ሐ) ቼኩ ፡ በሚገባው ፡ ጊዜ ፡ ቀርቦና ፡ ያልተከፈለበት ፡ መሆኑ ፡ በአንድ ፡ መንግሥት ፡ በፈቀደለት ፡ ገንዘብ ፡ ነክ ፡ በሆነ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ቀን ፡ በተጻፈበት ፡ ማስታወቂያ ፡ የተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እምጪው ፤ በጀርባ ፡ በፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ በአውጪውና ፡ በሌሎቹ ፡ ተገዳጆች ፡ ላይ ፡ የአቤቱታውን ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ይችላል ።

### ቍ ፡ ፰፻፹፬ ። የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፤ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።

(፩) ለማቅረብ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ከማለፉ ፡ በፊት ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ ይህንኑ ፡ የመሰለ ፡ መግለጫ ፡ መደረግ ፡ አለበት ።

(፪) የማቅረቡ ፡ ተግባር ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ መጨረሻ ፡ ቀን ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያው ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ መግለጫ ፡ በሚከተለው ፡ የሥራ ፡ መጀመሪያ ፡ ቀን ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

### ቍ ፡ ፰፻፹፭ ። ማስታወቂያ ።

(፩) የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ መግለጫ ፡ የተደረገበትን ፡ ቀን ፡ በሚከተሉት ፡ አራት ፡ የሥራ ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፤ ወይም ፡ « ያለኪሣራ ፡ ተመላሽ ፡ ይሆናል » ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ሲኖር ፡ ለእሺታ ፡ በቀረበበት ፡ ቀን ፤ በቼኩ ፡ አለመከፈሉን ፡ እምጪው፤ በጀርባ ፡ ለፈረመው ፡ ሰውና ፡ ለአውጪው ፡ ማስታወቂያ ፡ መስጠት ፡ ይገባዋል ።

(፪) በቼኩ ፡ ተገዳጆች ፡ ለሚሆኑት ፡ ሰዎች ፡ አድራሻዎች ፡ በቼኩ ፡ ላይ ፡ የተመለከቱም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ያዘጋጀው ፡ ባለሥልጣን ፡

ያወቃቸውም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያውን ፡ እንዲደረግ ፡ የጠየቁ ፡ ሰዎች ፡ ያመለከቱም ፡ ቢሆን ፡ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያውን ፡ ያዘጋጀው ፡ ባለሥልጣን ፡ ወዲያውኑ ፡ በጽሑፍ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሊልክላቸው ፡ ይገባዋል ። ለእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ማስታወቂያ ፡ የሚደረጉት ፡ ወጪዎች ፡ ሁሉ ፡ ለእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ በሚደረጉት ፡ ወጪዎች ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ ይሆናሉ ።

(፪) እያንዳንዱ ፡ በወረቀቱ ፡ ጀርባ ፡ የሚፈርም ፡ ሰው ፡ ማስታወቂያው ፡ በደረሰበት ፡ ቀን ፡ በሚከተሉት ፡ ሁለት ፡ የሥራ ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ ከአውጪው ፡ እስኪደርስ ፡ የፊተኞዎቹን ፡ ማስታወቂያዎች ፡ የሰጡትን ፡ ሰዎች ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፡ በማመልከት ፡ በጀርባ ፡ ፈርሞ ፡ ላስተላለፈለት ፡ ሰው ፡ የደረሰውን ፡ ማስታወቂያ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ጊዜዎች ፡ የሚቈጠሩት ፡ የፊተኛው ፡ ማስታወቂያ ፡ ከደረሰበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

(፫) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ መሠረት ፡ ማስታወቂያው ፡ ቼኩን ፡ ለፈረመው ፡ ሰው ፡ የተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይኸው ፡ ማስታወቂያ ፡ ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(፬) በቼኩ ፡ ጀርባ ፡ የፈረመው ፡ ሰው ፡ አድራሻውን ፡ ያላመለከተ ፡ ወይም ፡ በሚነበብ ፡ ዐይነት ፡ ያልጻፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከእሱ ፡ በፊት ፡ ለነበረው ፡ በወረቀቱ ፡ ጀርባ ፡ ለፈረመው ፡ ሰው ፡ ማስታወቂያውን ፡ መስጠት በቂ ፡ ነው ።

(፭) ማስታወቂያ ፡ መስጠት ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ማስታወቂ'ውን ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፤ ቼኩን ፡ እንዲያው ፡ መልሶ ፡ በመላክ ፡ ብቻ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፤ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፮) ማስታወቂያውን ፡ በተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ መስጠቱን ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ። በዚሁ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ማስታወቂያውን ፡ የያዘ ፡ ደብዳቤ ፡ ለፖስታ ፡ ቤት ፡ ተሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ የተወሰነ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ይቈጠራል ።

(፯) ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ማስታወቂያውን ፡ ያልሰጠ ፡ ሰው ፡ መብቱን ፡ አያጣም ፤ በጊዜው ፡ ባለማስታወቁ ፡ በቸልተኝነት ፡ ያደረገው ፡ ጉዳት ፡ ቢኖር ፡ ግን ፡ በቼኩ ፡ ላይ ፡ ከተመለከተው ፡ ገንዘብ ፡ የማይበልጥ ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ ለመክፈል ፡ አላፊ ፡ ነው ።

ቍ ፱፻፵፰ ። « ያለእንቢታ ፡ ማስታወቂያ » ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ።

(፩) አውጪው ፡ ወይም ፡ በጀርባ ፡ የፈረመው ፡ ሰው ፤ ወይም ፡ ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ «ያለኪሣራ ፡ ተመላሽ» ፤ « ያለእንቢታ ፡ ማስታወቂያ» ፡ የሚል ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ በሰነዱ ፡ ላይ ፡ በመጻፍና ፡ በመፈረም ፡ አምጪው ፡ የአቤቱታዎቹን ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ እንዲችል የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከማጻፍ ፡ ሊያድነው ፡ ይችላል ።

(፪) ይህ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ በተወሰኑት ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ ቼኩን ፡ ከማቅ

ራብና ፣ ማስታወቂያዎችንም ፡ ከመስጠት ፡ አምጪውን ፡ ነጻ ፡ አያወጣውም ። የተወሰኑት ፡ ቀኖች ፣ ላለመጠበቃቸው ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ያለበት ፡ በዚሁ ፡ አምጪውን ፡ ለመቃወም ፡ የሚፈልገው ፡ ሰው ፡ ነው ።

(፫) ይህን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ የጻፈው ፡ አውጪው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ውጤት ፡ ይኖረዋል ፤ በቼኩ ፡ ጀርባ ፡ በሚፈርም ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ለመክፈል፡ በዋስትና፡ እሺ፡ ባይ፡ የውሉን፡ ቃል ፡ ጽፎት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውጤት፡ ያለው ፡ በጻፈው ፡ ሰውና ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ አውጪው፡ ምንም፡ የውሉን ፡ ቃል ፡ ቢጽፍ ፡ አምጪው ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ እጽፎ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ወጪዎቹ ፡ በራሱ ፡ ኪሣራ ፡ ይሆናሉ ።

(፬) የውሉን ፡ ቃል ፡ የጻፈው ፡ ለመክፈል ፡ በዋስትና ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ ሰው ፡ ወይም፡ በጀርባ ፡ የፈረመው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ተጽፎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለእንቢታ ፡ ማስታወቅያ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ለመሰለ ፡ መግለጫ ፡ የወጡትን ፡ ወጪዎች ፡ ከፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይቻላል ።

## ቍ ፡ ፰፻፹፩ ። የተገዳጆቹ ፡ በአንድነት ፡ ዋስ ፡ መሆን ።

(፩) ባንድ ፡ ቼክ ፡ መሠረት ፡ የሚገደዱ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለአምጪው ፡ በአንድ ነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ ኀላፊዎች ፡ ናቸው ።

(፪) ሊገደዱበት ፡ በገቡበት ፡ ተርታ ፡ ሳይገደድ ፡ በነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በያንዳንዱ ፡ ወይም ፡ በሁሉም ፡ ላይ ፡ አምጪው ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፫) አንድ ፡ ቼክ ፡ የፈረመና ፡ የዚሁኑ ፡ ገንዘብ ፡ የከፈለ ፡ ሁሉ ፡ ይኸንኑ ፡ የመሰለ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፬) ግዴታ ፡ ከገቡት ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ የተጀመረ ፡ ክስ ፡ በሌሎቹ ፡ ላይ ፡ ከተከሰ ሰው ፡ በኋላም ፡ ቢሆኑ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ አይከለክልም ።

## ቍ ፡ ፰፻፹፪ ። የአቤቱታው ፡ መብት ፡ ወሰን ።

አምጪው ፤

(ሀ) ከቼኩ ፡ ያልተከፈለውን ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፤

(ለ) ካቀረበበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ሕጋዊ ፡ ወለዱን ፤

(ሐ) ለእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ለመሰለ ፡ መግለጫ ፡ ወይም ፡ ለተላኩት ፡ ማስታወቂያዎች ፡ የወጡትንና ፡ እንዲሁም ፡ ያደረጋቸውን ፡ ሌሎች ፡ ወጪዎች ፤

(መ) ቢበዛ ፡ ከመቶው ፡ የአንዱን ፡ ሢሶ ፡ የኮሚሲዮን ፤ አቤቱታ ፡ ካቀረበበት ፡ ሰው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

## ቍ ፡ ፰፻፹፫ ። የቼኩን ፡ ዋጋ ፡ የከፈለው ፡ ሰው ፡ የአቤቱታ ፡ መብት ፡ ወሰን ።

የቼኩን ፡ ዋጋ ፡ የከፈለ ፡ ሰው ፤

(ሀ) የከፈለውን ፡ ሙሉ ፡ ገንዘብ ፤

BACK



(ለ) የተባለውን ፡ ገንዘብ ፡ ከከፈለበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ሕጋዊ ፡ ወለዱን ፤
(ሐ) ያደረጋቸውን ፡ ወጪዎች ፤
(መ) ከሺሕ ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ የማይበልጥ ፡ ኮሚሲዮን ፤ ተገዳጅ ፡ የሆኑትን ፡ ለመ ጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፰፻፸፰ ። ቼኩ ፤ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያና ፡ የደረሰኝ ፡ ወረቀቱ ፡ እንዲሰጠው ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ።

(፩) አቤቱታ ፡ የቀረበበት ፡ ወይም ፡ አቤቱታ ፡ ሊቀርብበት ፡ የሚችል ፡ ማንኛ ውም ፡ ግዴታ ፡ የገባ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ዋጋውን ፡ በመክፈል ፡ ከቼኩ ፡ ጋራ ፡ የእን ቢታ ፡ ማስታወቂያውን ፡ ወይም ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነው ፡ መግለጫና ፡ የደረሰኝ ፡ ወረቀት ፡ እንዲሰጠው ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።
(፪) የቼኩን ፡ ዋጋ ፡ የከፈለ ፡ ማንኛውም ፡ በጀርባ ፡ የፈረመ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የራ ሱን ፡ ጽሑፍና ፡ ከሱም ፡ ቀጥለው ፡ በጀርባ ፡ የፈረሙትን ፡ ሰዎች ፡ ጽሑፍ ፡ ለመሰረዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፰፻፸፱ ። ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ኀይል ።

(፩) በተወሰኑት ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ ቼኩን ፡ ለማቅረብ ፡ ወይም ፡ የእንቢታ ፡ ማስ ታወቂያ ፡ ወይም ፡ ተመሳሳይ ፡ ማስረጃ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ መሰናከል ፡ የተከለከለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ (በማናቸውም ፡ በአ ነድ ፡ መንግሥት ፡ በተ ሰጠ ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ኀይል) ፡ የተወሰኑት ፡ ቀኖች ፡ ይረዝማሉ ።
(፪) አምጪው ፡ ከዐቅሙ ፡ በላይ ፡ ስለ ፡ ሆነው ፡ ጕዳይ ፤ በቼኩ ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ቅጥል ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ማስታወቂያዎቹን ፡ ቀንና ፡ ፊርማ ፡ አድርጎ ፡ ሳይዘገይ ፡ በጀርባ ፡ ለፈረመለት ፡ ሰው ፡ ማስታወቂያ ፡ መስጠት ፡ አለበት ፤ ተጨማሪ ፡ ለሆነው ፡ በቍጥር ፡ ፰፻፸ ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።
(፫) ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነው ፡ ኀይል ፡ ሲቀር ፡ አምጪው ፡ ሳይዘገይ ፡ ለማስከ ፈል ፡ ቼኩን ፡ ማቅረብና ፡ አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ወይም ፡ ተመሳሳይ ፡ መግለጫ ፡ ማጻፍ ፡ አለበት ።
(፬) አምጪው ፡ በቼኩ ፡ ጀርባ ፡ ፈርሞ ፡ ላስተላለፈለት ፡ ሰው ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ ለሆ ነው ፡ ኀይል ፡ ምክንያት ፤ ማስታወቂያ ፡ ከሰጠው ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ የሆነው ፡ ኀይል ፡ ከዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ በላይ ፡ የቀጠለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቼኩ ፡ ማቅረቢያ ፡ ጊዜ ፡ ባይደርስም ፡ ቼኩን ፡ ማቅረብ ፡ ወይም ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወ ቂያ ፡ ወይም ፡ ተመሳሳይ ፡ ማስረጃ ፡ ማጻፍ ፡ ሳያስፈልግ ፡ የአቤቱታ ፡ ማቅረብ ፡ መብቱን ፡ ሊሠራበት ፡ ይችላል ።
(፭) ለአምጪው ፡ ወይም ፡ ቼኩን ፡ እንዲያቀርብ ፡ ወይም ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወ ቂያ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲጽፍ ፡ ለታዘዘው ፡ ሰው ፡ የግል ፡ የሆኑት ፡ ምክንያቶች ፡ ከዐቅም ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ኀይል ፡ አይቈጠሩም ።

BACK

## ክፍል ፡ ፯ ።

## አንዱን ፡ ቼክ ፡ አባዝቶ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ።

**ቍ ፡ ፰፻፶፯ ። እንዲበዛለት ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ።**

ለአምጪው ፡ ተብሎ ፡ ከተጻፈበት ፡ ቼክ ፡ በቀር ፤ የወጣበት ፡ አንድ ፡ አገር ፡ ሆኖ ፡ የሚከፈልበት ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ወይም ፡ የወጣበትና ፡ የሚከፈልበት ፡ አገር ፡ ክፍል ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ ቼክ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ በሆኑ ፡ ጽሑፎች ፡ አባዝቶ ፡ ለማውጣት፡ ይቻላል ፤ ቼኩ ፡ ተባዝቶ፡ ወጥቶ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ በተባዙት ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ሊኖርባቸው ፡ ይገባል ፤ ይህ፡ ካልሆነ፡ ግን ፡ እያንዳንዳቸው፡ እንደ፡ ተለየ ፡ ቼክ ፡ ይቈጠራሉ ።

**ቍ ፡ ፰፻፶፰ ። በተባዙት ፡ ጽሑፎች ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ ግንኙነት ።**

(፩) በአንዱ ፡ ጽሑፍ ፡ የተደረገው ፡ መክፈል ፡ የተባዙትን ፡ የሌሎችን ፡ ጽሑፎች ፡ ውጤት ፡ ይሽራል ፡ ተብሎ ፡ ባይነገር ፡ እንኳ ፤ ከጽሑፎቹ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ መክፈል ፡ ከግዴታዎቹ ፡ ነጻ ፡ ያወጣል ።

(፪) የተባዙትን ፡ ጽሑፎች ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ሰዎች ፡ ያስተላለፈ ፡ በቼኩ ፡ ጀርባ ፡ የፈረመ ፡ ሰውና ፡ እንዲሁም ፡ ከእሱ ፡ በኋላ ፡ በቼኩ ፡ ላይ ፡ የፈረሙ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ፊርማቸው ፡ ላለባቸው ፡ ለተባዙትና ፡ ላልተመለሱት ፡ ጽሑፎች ፡ ኀላፊዎች ፡ ናቸው ።

## ክፍል ፡ ፰ ።

## ስለ ፡ መለዋወጥ ።

**ቍ ፡ ፰፻፶፱ ። የፈራሚዎች ፡ ግዴታ ፡ ወሰን ።**

ያንድ ፡ ቼክ ፡ ጽሑፍ ፡ የተለወጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ መለወጥ ፡ በኋላ ፡ የፈረሙት ፡ ፈራሚዎች ፡ የሚጠይቁት ፡ በተለወጠው ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ነው ። ከመለወጡ ፡ በፊት ፡ የፈረሙት ፡ ግን ፡ በመጀመሪያው ፡ ቃል ፡ ይገደዳሉ ።

**ቍ ፡ ፰፻፷ ። የስርዝ ፡ ምልክት ፡ ያለበት ፡ ቼክ ፡ መለወጥ ።**

(፩) የስርዝ ፡ ምልክት ፡ ያለበት ፡ ቼክ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መለዋወጡን ፡ ባደረገው ፡ ወይም ፡ በፈቀደው ፡ ሰውና ፡ ከሱም ፡ በኋላ ፡ በቼኩ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ በፈረሙት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ የስርዙ ፡ ምልክት ፡ ያለፈቃድ ፡ መለዋወጥ ፡ ቼኩን ፡ ዋጋ ፡ ያሳጣዋል ።

(፪) መለወጡ ፡ የማይታይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በሕግ ፡ የተፈቀደለት ፡ አምጪ ፡ ቼኩ ፡ እንዳልተለወጠ ፡ ሁሉ ፡ መጀመሪያ ፡ በተጻፈበት ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ እንዲከፈለው ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ።

BACK



## ክፍል ፡ ፱ ።

## ስለ ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ።

**ቍ ፡ ፰፻፹፩ ። የተወሰኑ ፡ ጊዜዎች ።**

(፩) በጀርባ ፡ በሚፈርሙ ፡ ሰዎች ፡ በአውጪውና ፡ በሌሎች ፡ ተገዳጆች ፡ ላይ ፡ የሚቀርቡ ፡ የአምጪው ፡ የክስ ፡ አቤቱታዎች ፡ ቼኩን ፡ ለማቅረብ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ ጀምሮ ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ ይርጋ ፡ ይታገዳሉ ።

(፪) ተገዳጁ ፡ የቼኩን ፡ ዋጋ ፡ ከከፈለበት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ራሱ ፡ ከተከሰሰበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ላንድ ፡ ቼክ ፡ አከፋፈል ፡ እያንዳንዱ ፡ ተገዳጅ ፡ በሌሎች ፡ ተገዳጆች ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የክስ ፡ ማቅረብ ፡ መብት ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ ይርጋ ፡ ይታገዳል ።

(፫) አምጪው ፡ በከፋዩ ፡ ላይ ፡ የሚያቀርበው ፡ ክስ ፡ ቼኩን ፡ ለማቅረብ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለቀ ፡ ጀምሮ ፡ በሦስት ፡ ዓመት ፡ ይርጋ ፡ ይታገዳል ።

(፬) ክስ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ የሚጀመረው ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የመጨረሻው ፡ ክስ ፡ ከተፈጸመበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

(፭) ፍርድ ፡ ተሰጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ ዕዳው ፡ በተለይ ፡ በሌላ ፡ ሰነድ ፡ ታምኖ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ አይጸናም ።

**ቍ ፡ ፰፻፹፪ ። ስለ ፡ ማቋረጥ ።**

(፩) ክስን ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ በማቅረብ ፤ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ያቀረበውን ፡ ክስ ፡ በማስታወቅ ፤ ወይም ፡ በኪሣራ ፡ አሠራር ፡ ጊዜ ፡ መብት ፡ መጠየቂያ ፡ ወረቀትን ፡ በማቅረብ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ ይቋረጣል ።

(፪) ክሱ ፡ በተደረገበት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የይርጋው ፡ መቋረጥ ፡ በሌላው ፡ ላይ ፡ ውጤት ፡ የለውም ።

(፫) ይርጋው ፡ የተቋረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንደዚሁ ፡ የሚቈይ ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡ አዲስ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፡ ይጀመራል ።

## ክፍል ፡ ፲ ።

## ጠቅላላ ፡ ውሳኔዎች ።

**ቍ ፡ ፰፻፹፫ ። የተወሰኑ ፡ ጊዜዎች ፤ የበዓላት ፡ ቀኖች ።**

(፩) የሥራ ፡ ቀን ፡ ካልሆነ ፡ አንድ ፡ ቼክ ፡ ለማቅረብና ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለማጸፍ ፡ አይቻልም ።

(፪) ቼኩን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ተግባሮች ፡ አፈጻጸምና ፡ በተለይም ፡ ለማቅረብ ፡ ወይም ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለማጸፍ ፡ ወይም ፡ ተመሳሳይ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለማደራጀት ፡ በሕጉ ፡ የተፈቀደው ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ መጨረሻ ፡ በሕግ ፡ የታወቀ ፡ የበዓል ፡ ቀን ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የማለቂያውን ፡ ቀን ፡ እስከሚከተለው ፡

መጀመሪያ ፡ የሥራ ፡ ቀን ፡ ጊዜው ፡ የሚራዘም ፡ ይሆናል ፤ ጣልቃ ፡ የሚገቡት፡ የበዓል ፡ ቀኖች ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ግምት ፡ ውስጥ ፡ ይቈጠራሉ ።

(፫) ጸንተው ፡ በሚገኙት ፡ ሕጎች ፡ አነጋገር ፤ ምንም ፡ አከፋፈል ፡ እንዳይደረግባቸውና ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ እንዳይጻፍባቸው ፡ የተከለከሉት ፡ ቀኖች ፡ በሕግ ፡ እንደ ፡ ታወቁት ፡ የበዓል ፡ ቀኖች ፡ ይቈጠራሉ ።

**ቊ ፡ ፰፻፳፬ ። የተወሰኑ ፡ ጊዜዎች ፡ አቈጣጠር ።**

በሕግ፡ወይም፡በስምምነት፡ለተወሰኑ፡ጊዜዎች፡መነሻ፡የሆነው፡ቀን፡ አይቈጠርም ።

**ቊ ፡ ፰፻፳፭ ። በችሮታ ፡ የሚሰጠውን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ መከልከል ።**

ምንም ፡ የችሮታ ፡ ጊዜ ፡ ሊሰጥ ፡ አይፈቀድም ።

**ቊ ፡ ፰፻፳፮ ። የሐዋላ ፡ ወረቀትን ፡ ወደሚመለከቱ ፡ ውሳኔዎች ፡ መመራት ።**

ከዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ጋራ ፡ በሚስማሙበት ፡ መጠን ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀትን ፡ በተለይም ፤ በቊጥር ፡ ፯፻፹፩ ፡ እስከ ፡ ፯፻፹፬ ፡ እና ፡ ፯፻፹፰ ፡ (የእንቢታ፡ ማስታወቂያ) ፤ በቊጥር ፡ ፯፻፶፰ ፡ (በጥበቃ ፡ መያዝን) ፤ በቊጥር ፡ ፯፻፺፱ ፡ (ሕግ ፡ በማይፈቅደው ፡ ተግባር ፡ መበልጸግን ) ፤ በቊጥር ፡ ፰፻ ፡ ( ክስ ፡ የማቅረብን ፡ መብት ፡ ማቋየት ) ፡ እና ፡ በቊጥር ፡ ፰፻፩ ፡ (የገንዘብ ፡ ሥንቅን ) ፡ የሚመለከቱ ፡ ውሳኔዎች ፡ በቼክም ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፭ ።

## የመንገድ ፡ ቼክ ።

**ቊ ፡ ፰፻፳፯ ። ትርጓሜ ።**

(፩) የመንገድ ፡ ቼክ ፡ ማለት ፡ ገንዘብ ፡ ተከፋዩ ፡ የአውጪው ፡ ባንክ ፡ ቅርንጫፍ፡ በሆነ ፡ ባንክ ፡ ወይም ፡ ከዚሁ ፡ ከአውጪ ፡ ባንክ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ባለው ፡ በማንኛውም ፡ ባንክ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲቀበል ፡ በሰነዱ ፡ ውስጥ ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ጽፎ ፡ አንድ ፡ ባንክ ፡ ለደንበኛው ፡ የሚሰጠው ፡ ሰነድ ፡ ነው ።

(፪) የመንገድ ፡ ቼክ ፡ ለማውጣት ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸው ፡ ባንኮች ፡ በደንብ ፡ ይወሰናሉ ።

**ቊ ፡ ፰፻፳፰ ። በመንገደኞች ፡ ቼክ ፡ ላይ ፡ የሚጻፈው ፡ ዝርዝር ።**

ከዚህ ፡ የሚከተሉት ፡ ዝርዝሮች ፡ በግልጽ ፡ ያልተመለከተበት ፡ የመንገድ ፡ ቼክ ፡ ዋጋ ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም ።

(፩) “ የመንገድ ፡ ቼክ ፡ ” የሚል ፡ ቃል ።
(፪) ቼክን ፡ ያወጣው ፡ የባለባንኩ ፡ ስምና ፡ ፊርማ ።
(፫) ተከፋዩ ፡ ስም ።
(፬) የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ የመክፈል ፡ ቃል ።

(፰) “ በትእዛዝ ፡ ” ወይም ፡ “ የማይተላለፍ ፡ ” የሚል ፡ ቃል ።
(፱) የወጣበትን ፡ ቀንና ፡ ቦታ ።
(፲) ቼኩ ፡ የሚያገለግልበትን ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፤ ይህም ፡ ጊዜ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ መብለጥ ፡ የለበትም ።

ቍ ፡ ፰፻፹፱ ። የሚከፈልበት ፡ ሁኔታና ፡ ቦታ ።

(፩) ቼኩ ፡ የሚከፈልበት ፡ ቦታ ፡ በቼኩ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ለተከፋዩ ፡ በተሰጠው ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሰነድ ፡ ላይ ፡ ሊመለከት ፡ ይቻላል ።
(፪) ገንዘብ ፡ ተከፋዩ ፡ ገንዘቡ ፡ እንዲከፈለው ፡ የሚጠይቅበት ፡ ሁኔታ ፡ በቼኩ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ለተከፋዩ ፡ በተሰጠው ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ሊመለከት ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፰፻፺ ። ስለ ፡ ቼኮች ፡ የሚመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ስላለመሆናቸው ።

(፩) በቼኩ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ የሚሆኑት ፡ ሕጋዊ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በመንገድ ፡ ቼክ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ አይሆኑም ።
(፪) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተመለከቱት ፡ ቢኖሩም ፡ እንኳን ፤ ስለ ፡ ሐሰት ፡ ቼክ ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፡ ስለ ፡ ተለዋወጠ ፡ ቼክ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆነውን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌ ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

## የመክፈል ፡ እንቢታን ፡ ስለማስታወቅ ።

ቍ ፡ ፰፻፺፩ ። የመክፈል ፡ እንቢታን ፡ የመላክ ፡ ግዴታ ።

ስለሚተላለፉ ፡ የንግድ ፡ የገንዘብ ፡ ወረቀቶችን ፡ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ቃልን ፡ ለመጻፍ ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀቶች ፡ እሺ ፡ ተብለው ፡ ያልተከፈሉ ፤ የተሰፋ ፡ ወረቀቶችና ፡ ቼኮች ፡ ባለመከፈላቸው ፡ ምክንያት ፡ ባለፈው ፡ ወር ፡ ያዘጋጁትን ፡ የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ዎች ፡ ሊስት ፡ በሙሉ ፡ በሚሠሩበት ፡ ቦታ ፡ ባለሥልጣን ፡ ለሆነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመዝገብ ፡ ሹም ፡ በየወሩ ፡ ማስተላለፍ ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፰፻፺፪ ። የፍርድ ፡ ቤት ፡ የመዝገብ ፡ ሹሙ ፡ ተግባር ።

የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመዝገብ ፡ ሹም ፡ ስለያንዳንዱ ፡ ባለዕዳ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተ መለከቱትን ፡ በሠንጠረዥ ፡ አግብቶ ፡ ማኖር ፡ አለበት ።
(፩) ለመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ የተጻፈበት ፤
(፪) የተከፋዩን ፡ ወይም ፡ የአውጪውን ፡ ስም ፤ ሥራና ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፤
(፫) የተሰፋ ፡ ሰነድ ፡ አውጪ ፡ ወይም ፡ ቼኩን ፡ የሚከፍለው ፡ ወይም ፡ የሐዋላ ውን ፡ ወረቀት ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ ስም ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ስም ፤ ሥራውንና ፡ መደ በኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ።

(፬) ዕዳው ፡ የሚከፈልበት ፡ ቀን ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፤
(፭) በገንዘብ ፡ ሰነዱ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፤
(፮) ለመክፈል ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ተደርጎ ፡ ያስገኘውን ፡ ውጤት ።

ቍ ፡ ፰፻፺፫ ። ግልባጮች ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

የመክፈል ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተጻፈበት ፡ ቀን ፡ እንሥቶ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ካለፈ ፡ በኋላና ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ግልባጩ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ወጪ ፡ ራሱ ፡ ከፍሎ ፡ በቍጥር ፡ ፰፻፺፪ ፡ መሠረት ፡ የተዘጋጀውን ፡ ሠንጠረዥ ፡ ግልባጭ ፡ እንዲጠሰው ፡ የመዝገብ ፡ ሹሙን ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፰፻፺፬ ። ስለ ፡ መሰረዝ ።

(፩) ባለዕዳው ፡ ሰነዱን ፡ ወይም ፡ የመክፈል ፡ እንቢታን ፡ ማስታወቂያ ፤ ቼኩ ፡ የተከፈለ ፡ መሆኑን ፡ የሚያስረዳ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ደረሰኝ ፡ ተቀብሎ ፡ ያስቀመጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የፍርድ ፡ ቤት ፡ የመዝገብ ፡ ሹሙ ፡ ለዚህ ፡ ባለዕዳ ፡ ተብሎ ፡ በተዘጋጀው ፡ ሠንጠረዥ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ የመክፈል ፡ እንቢታን ፡ ማስታወቂያ ፡ በባለዕዳው ፡ ኪሣራ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።
(፪) በፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ተቀመጡት ፡ ወረቀቶች ፡ የመዝገብ ፡ ሹሙ ፡ ባለበት ፡ ኀላፊነት ፤ የመክፈል ፡ እንቢታን ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተጻፈበት ፡ ቀን ፡ እንሥቶ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ሊጠየቅበት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፰፻፺፭ ። ማሳተም ፡ የማይፈቀድ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ።

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ መሠረት ፡ የተዘጋጀውን ፡ ሠንጠረዥና ፡ ዝርዝር ፡ ሊስት ፡ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ አድርጎ ፡ ማሳተም ፡ ፈጽሞ ፡ የተከለከለና ፡ ካሣ ፡ የሚያስከፍለው ፡ ነው ።

## አንቀጽ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ባንክ ፡ ሥራዎች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ለባንክ ፡ የሚሰጡ ፡ አደራዎች ።

#### ክፍል ፡ ፩ ።

#### ገንዘብ ፡ በአደራ ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥ ።

ቍ ፡ ፰፻፺፮ ። የውሉ ፡ ዐይነት ።

ገንዘቡ ፡ ባንክ ፡ የገባው ፡ በምንም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆን ፤ ገንዘቦችን ፡ በአደራ ፡ የማስቀመጥ ፡ ውል ፤ ተቀማጭ ፡ ለተደረጉት ፡ ገንዘቦች ፡ ባንኩን ፡ ባለሀብት ፡ ያደር

ገዋል ። በውሉ ፡ በተመለከቱት ፡ ውለታዎች ፡ መሠረት ፡ የመመለስ ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ መሆኑ ፡ ሳይቀር ፤ አስፈላጊ ፡ ለሆኑት ፡ ሥራው ፡ እንዲያገለግሉት ፡ ለማድረግ ፡ መብት ፡ ይሰጠዋል ።

ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ከተጠቀሰው ፡ በመለየት ፡ ባንክ ፡ በዐይነታቸው ፡ እንዲመለስ ፡ በውሉ ፡ ግዴታ ፡ የገባባቸውን ፡ ተለይተው ፡ የተሰጡትን ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ምልክት ፡ ያለባቸውን ፡ ገንዘቦች ፡ ባለሀብትነት ፡ ወይም ፡ በነዚሁ ፡ የመገልገል ፡ መብት ፡ ባንኩ ፡ አያገኝም ።

**ቍ ፡ ፰፻፺፯ ። በአደራ ፡ የሚቀመጥ ፡ ገንዘብ ፡ ሒሳብ ።**

(፩) ገንዘቡን ፡ በአደራ ፡ የማስቀመጥ ፡ ውል ፡ ሲደረግ ፤ ባንኩ ፡ ከአደራ ፡ አስቀማጩ ፡ ወይም ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ከሦስተኞቹ ፡ ወገኖች ፡ ጋራ ፡ የሚያደርጋቸውን ፡ ተግባሮች ፡ ሁሉ ፡ የሚጽፍበት ፡ የገቢና ፡ የወጪ ፡ ሒሳብ ፡ ይከፍታል ።

(፪) ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በመስማማት ፡ ያስወገዷቸው ፡ ነገሮች ፡ በሒሳቡ ፡ ውስጥ ፡ የሚጻፉ ፡ አይሆኑም ።

**ቍ ፡ ፰፻፺፰ ። የአደራ ፡ አቀማመጡ ፡ ዐይነት ።**

(፩) ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የአደራው ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ተጠየቀ ፡ የሚከፈል ፡ ነው ፡ አደራ ፡ አስቀማጩም ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ በቀሪው ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ሊያዝበት ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተመለከተው ፡ በገንዘቡ ፡ የማዘዝ ፡ መብት ፡ አንድ ፡ የማስታወቂያ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ እንዲከፈል ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፰፻፺፱ ። ካለው ፡ በላይ ፡ ማውጣት ፡ ስለመከልከሉ ።**

ገንዘቡን ፡ በአደራ ፡ የማስቀመጥ ፡ ውል ፤ ካለው ፡ ከተቀማጭ ፡ ገንዘብ ፡ በላይ ፡ የማውጣት ፡ መብትን ፡ አይሰጥም ።

**ቍ ፡ ፱፻ ። ሒሳብ ፡ ስለ ፡ ማወቅ ።**

ገንዘብ ፡ በአደራ ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፤ ልማድ ፡ ወይም ፡ ስምምነት ፡ ያስገደደ ፡ ሲሆንም ፡ በየጊዜው ፡ ቀሪ ፡ ሆኖ ፡ የተላለፈውን ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ የሚያሳይ ፡ የተደራጀውን ፡ ሒሳብ ፡ ግልባጭ ፡ ባደራ ፡ ላስቀመጠው ፡ ሰው ፡ መላክ ፡ ይገባል ።

**ቍ ፡ ፱፻፩ ። ገንዘቡ ፡ የሚቀመጥበትና ፡ የሚወሰድበት ፡ ቦታ ።**

ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ የገንዘብ ፡ ማስቀመጥና ፡ መውሰድ ፡ የሚደረገው ፡ ሒሳቡ ፡ በተከፈተበት ፡ የባንክ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፱፻፪ ። ብዙ ፡ ሒሳቦች ።**

ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ ባንድ ፡ ባንክ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በቅርንጫፎቹ ፡

ውስጥ ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ሒሳቦች ፡ ተከፍተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሒሳብ ፡ አያያዝ ፡ ከሌሎች ፡ የተለየ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## በባንክ ፡ ሒሳብን ፡ ስለ ፡ ማዘዋወር ።

### ቍ ፡ ፱፻፫ ። ትርጓሜ ።

(፩) በባንክ ፡ ያለውን ፡ ሒሳብ ፡ ማዘዋወር ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ባንክ ፡ አደራ ፡ ሰጪው ፡ በጽሑፍ፡ በሚሰጠው፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ የዚህኑ ፡ ሒሳብ ፡ ወጪ ፡ በማድረግ ፡ የሌላው ፡ ሰው ፡ ሒሳብ ፡ በዚሁ ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ገቢ ፡ የሚያደርግበት ፡ አሠራር ፡ ነው ።

(፪) የሒሳብ ፡ ማዘዋወሩ ፡ ትእዛዞች ፡ የሚወጡባቸው ፡ ሁናቴዎች ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ስምምነት ፡ ይወሰናሉ ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የሒሳብ ፡ ማዘዋወር ፡ ትእዛዝ ፡ ለአምጪ ፡ ተብሎ ፡ እንዳይሰጥ ፡ የተከለከለ ፡ ነው ።

(፫) በሒሳብ ፡ ማዘዋወሪያው ፡ ትእዛዝ ፡ ተጠቃሚ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ በሒሳብ ፡ ማዘዋወሪያው ፡ ትእዛዝ ፡ የተጻፈውን ፡ ገንዘብ ፡ ላንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ሒሳብ ፡ ገቢ ፡ እንዲያደርግ ፡ ታዞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የዚሁ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ በሒሳብ ፡ ማዘዋወሪያው ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ እንዲኖር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

### ቍ ፡ ፱፻፬ ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ የሒሳብ ፡ ማዘዋወር ።

ገቢ ፡ የሚደረግበት ፡ ሒሳብና ፡ ገንዘቡ ፡ ወጪ ፡ የሚደረግለት ፡ ሒሳብ ፡ ቦታ ፡ ሁለቱም ፡ በአንድ ፡ የባንክ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ወይም ፡ በተለያዩ ፡ ሁለት ፡ የባንክ ፡ ቅርንጫፎች ፡ እንደመሆናቸው ፡ ውስጣዊ ፡ ወይም ፡ የውጭ ፡ የሒሳብ ፡ ማዘዋወር ፡ ይባላል ።

### ቍ ፡ ፱፻፭ ። የሒሳብ ፡ ማዘዋወር ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠበት ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ።

በትእዛዝ ፡ ሰጪው ፡ ሒሳብ ፡ ተጽፈው ፡ በሚገኙት ፡ ገንዘቦች ፡ ወይም ፡ ከባንክ ፡ ጋራ ፡ አስቀድሞ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይጻፋሉ ፡ ተብሎ ፡ በተስማሙባቸው ፡ ገንዘቦች ፡ ላይ ፡ የሒሳብ ፡ ማዘዋወሪያው ፡ ትእዛዝ ፡ በሚገባ ፡ የተሰጠ፡ ይሆናል ።

### ቍ ፡ ፱፻፮ ። ባለሀብትነቱን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ፤ የማዘዋወሩን ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ መሻር ።

(፩) ላንድ ፡ የሒሳብ ፡ ማዛወር ፡ ባለጥቅም ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ባንኩ ፡ ለሚዘዋወረው ፡ ገንዘብ ፡ የትእዛዝ ፡ ሰጪውን ፡ ሒሳብ፡ ወጪ ፡ ባለዕዳ ፡ በሚያደርግበት፡ ጊዜ፡ ባለጥቅሙ ፡ የተላለፈው ፡ ገንዘብ ፡ ባለሀብት ፡ ይሆናል ።

(፪) እስከዚሁ ፡ ጊዜ፡ድረስ፡የሒሳብ ፡ ማዘዋወሪያውን ፡ ትእዛዝ፡ለመሻር፡ይቻላል ።

(፫) የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፷፯ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ የሒሳብ ፡ ማዘዋወር ፡ ትእዛዝ ፤ በቍጥር ፡ ፲፻፷፬ ፤ የተነገረው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ የሒሳብ ፡ ማዘዋወር ፡ ትእዛዝ ፡ መሻር ፡ መብትን ፡ መተው ፡ ያስከትላል ።

ቍ ፡ ፲፻፷፯ ። ልዩ ፡ ስምምነቶች ።

(፩) የሒሳብ ፡ ማዘዋወሪያውን ፡ ትእዛዞች ፡ ባለጥቅሙ ፡ ራሱ ፡ ለባንክ ፡ ያቀርባቸዋል ፡ እንጂ ፡ በቀጥታ ፡ ለባንኩ ፡ አይላክም ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

(፪) እንዲሁም ፡ በየቀኑ ፡ መጨረሻና ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ከደረሱት ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ከሆኑት ፡ የሒሳብ ፡ ማዘዋወሪያ ፡ ትእዛዞች ፡ ጋራ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አንዳንድ ፡ የሒሳብ ፡ ማዘዋወሪያ ፡ ትእዛዞች ፡ የትእዛዝ ፡ ሰጪውን ፡ ቀጥታ ፡ ትእዛዝ ፡ በመቀበል ፡ ወይም ፡ ተጠቃሚዎቹ ፡ ሰነዱን ፡ በማቅረባቸው ፡ ብቻ ፡ ማዘዋወሩ ፡ አይፈጸምም ፡ ተብሎ ፡ ለመስማማት ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፲፻፷፰ ። በቂ ፡ ያልሆነ ፡ የገንዘብ ፡ ሥንቅ ።

የሚበቃ ፡ የገንዘብ ፡ ሥንቅ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባንኩ ፡ ሒሳቡን ፡ አላዛውርም ፡ ለማለት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፻፷፱ ። የትእዛዙ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ዕዳ ፡ ስለ ፡ መቈየቱ ።

ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ ሲባል ፡ የተሰጠው ፡ የሒሳብ ፡ ማዘዋወሪያ ፡ ትእዛዝ ፡ በዚሁ ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ የተመለከተው ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ በተጠቃሚው ፡ ሒሳብ ፡ ገቢ ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡ ለዚሁ ፡ ገንዘብ ፡ የተሰጡት ፡ ዋስትናዎችና ፡ ተጨማሪዎች ፡ እንዳሉ ፡ ይቈያሉ ።

ቍ ፡ ፲፻፸ ። የማዘዋወሪያውን ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ መቃወም ።

የባለጥቅሙን ፡ መክሠር ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ የመጠበቂያ ፡ ስምምነትን ፡ መፍቀዱን ፡ የሚገልጸው ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ የማዘዋወሪያው ፡ ትእዛዝ ፡ ለባለጥቅሙ ፡ በተሰጠ ፡ ባንድ ፡ ሰነድ ፡ የተረጋገጠ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፤ ትእዛዝ ፡ ሰጪው ፡ የሒሳቡ ፡ ማዘዋወሪያ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዳይፈጸም ፡ በሚገባ ፡ ሊቃወም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፻፸፩ ። ትእዛዝ ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ መክሠር ፡ ከመታወቁ ፡ በፊት ፡ የቀረቡ ፡ የሒሳብ ፡ ማዘዋወሪያ ፡ ትእዛዞች ።

ትእዛዝ ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ መክሠሩን ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ መፈቀዱን ፡ የሚገልጽ ፡ ፍርድ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ የቀረቡለትን ፡ የሒሳብ ፡ ማዘዋወሪያ ፡ ትእዛዞች ፡ በሚገባ ፡ አኳኋን ፤ ባንኩ ፡ ለትእዛዝ ፡ ሰጪው ፡ ሒሳብ ፡ ወጪ ፡ ሊያደርጋቸው ፡ ይችላል ።

BACK



## ክፍል ፡ ፫ ።

## ሰነዶችን ፡ በአደራ ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥ ።

**ቊ ፡ ፱፻፲፪ ። ባንክ ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ ሰነዶችን ፡ እንዳይገለገልባቸው ፡ ስለ ፡ መከልከል ።**

በጽሑፍ ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ለአደራ ፡ ሰጪው ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በአደራ ፡ የተቀመጡትን ፡ ሰነዶችና ፡ ከነዚህም ፡ ጋራ ፡ የተያያዙትን ፡ መብቶች ፡ ባንኩ ፡ ሊሠራባቸው ፡ አይችልም ።

**ቊ ፡ ፱፻፲፫ ። የመጠበቅ ፡ ግዴታ ።**

(፩) ደመወዘኛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አደራ ፡ አስቀማጭ ፡ ሁሉ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በሚያስገድደው ፡ መሠረት ፡ ባንክ ፡ ሰነዶችን ፡ መጠበቅና ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

(፪) ሰነዶቹን ፡ ከእጁ ፡ በሚያስወጣ ፡ ተግባር ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ባንኩ ፡ ሰነዶቹን ፡ ከእጁ ፡ ለማውጣት ፡ አይችልም ።

**ቊ ፡ ፱፻፲፬ ። ሰነዶችንና ፡ ተጨማሪ ፡ የሆኑ ፡ የግዴታ ፡ ወረቀቶች ፡ የሚሰጡትን ፡ ጥቅም ፡ ስለ ፡ መቀበል ።**

(፩) ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ በአደራ ፡ የተቀመጡት ፡ ሰነዶች ፡ የሚሰጡትን ፡ ወለድ ፤ የትርፍ ፡ ድርሻ ፤ ዋና ፡ ገንዘባቸውን ፡ መልሶ ፡ መቀበል ፤ የዋጋ ፡ መተኪያ፡ ገንዘባቸውንና ፡ በጠቅላላውም፡ የሚሰጡትን፡ ማንኛውንም ፡ ገንዘብ፡ ሁሉ፡ ተከፋይ ፡ በሚሆኑበት ፡ ጊዜ ፡ ባንኩ ፡ መቀበል ፡ አለበት ።

(፪) ገቢ ፡ የሆኑት ፡ ገንዘቦች ፡ አደራ ፡ ሰጪው ፡ የሚያዝባቸው ፡ ሆኖ ፡ በተለይም ፡ በአደራ ፡ ሰጪው ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ ሆነው ፡ ይጻፋሉ ።

(፫) እንዲሁም ፡ ባንኩ ፡ ከችሮታ ፡ የተነሣ ፡ የሚሰጡትን ፡ ሰነዶች ፡ አደራ ፡ ቢተቀመጡት ፡ ሰነዶች ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ አድርጎ ፡ ለማስቀመጥ ፡ መቀበል ፡ አለበት ።

(፬) እንዲሁም ፡ ባንኩ ፡ ሰነዶችን ፡ መሰብሰብን ፤ መለዋወጥን ፤ የድርሻ ፡ መቀበያ ፡ ኩርዶች ፡ መቀበልን ፤ ማኅተም ፡ ማስደረግንና ፡ ይህንን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ከሰነዶቹ ፡ ጋራ ፡ የተሳሰሩትን ፡ መብቶች ፡ ለመጠበቅ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

**ቊ ፡ ፱፻፲፭ ። ለአደራ ፡ አስቀማጭ ፡ የሚሰጥ ፡ ማስታወቂያ ።**

(፩) በሰነዶቹ ፡ ባለሀብት ፡ የሚደረጉ ፡ የምርጫ ፡ ተግባሮች ፡ ባጋጠመው ፡ ጊዜ ፤ አደራ ፡ ሰጪው ፡ እነዚህን ፡ ተግባሮች ፡ እንዲያውቃቸው ፡ ባንኩ ፡ በሬኮማንዴ ፡ በአደራ ፡ ሰጪው ፡ ኪሣራ ፡ ማስታወቂያ ፡ መላክ ፡ አለበት ።

BACK



(፪) ተገቢ ፡ በሆነው ፡ ጊዜ ፡ የአደራ ፡ ሰጪው ፡ ትእዛዞች ፡ ያልደረሱት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ አደራ ፡ ሰጪው ፡ ላልሠራባቸው ፡ መብቶች ፡ ባንኩ ፡ በአደራ ፡ አስቀ ማጩ ፡ ፈንታ ፡ ለመነጋገር ፡ ይገደዳል ፡፡

ቍ ፡ ፱፻፲፯ ፡፡ የመመለስ ፡ ግዴታ ፡፡

(፩) በአጠባበቁ ፡ ሁኔታዎች ፡ በተገለጹት ፡ ጊዜዎች ፡ ውስጥ ፤ ባንኩም ፡ የመያዝ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ መብቱ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ በአደራ ፡ ሰጪው ፡ ጥያቄ ፡ ሰነዶችን ፡ ለመመለስ ፡ ባንኩ ፡ ይገደዳል ፡፡

(፪) የመመለሱ ፡ ተግባር ፡ የሚፈጸመው ፤ የአደራ ፡ ማስቀመጥ ፡ በተደረገበት ፡ ቦታ ፡ ነው ፡፡ ተተኪ ፡ በሆኑ ፡ ነገሮች ፡ እንዲመለስ ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ስም ምነት ፡ ካልተደረገ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ ካልተፈቀደ ፡ በቀር ፡ እነዚያው ፡ በአ ደራ ፡ የተቀመጡት ፡ ሰነዶች ፡ መመለስ ፡ አለባቸው ፡፡

ቍ ፡ ፱፻፲፰ ፡፡ መመለሱ ፡ ለማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡

(፩) ምንም ፡ ሰነዶቹ ፡ የአንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ መሆናቸውን ፡ ቢያመለ ክቱ ፡ ለአደራ ፡ ሰጪው ፡ ወይም ፡ ከሱ ፡ ባለመብት ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ እነሱ ፡ ለመረጧቸው ፡ ሰዎች ፡ መመለስ ፡ አለባቸው ፡፡

(፪) የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ስም ፡ የተጻፈባቸው ፡ ሰነዶች ፡ በሪም ፡ ሰጪና ፡ በሪም ፡ ተቀ ባይ ፡ ስም ፡ የተመዘገቡ ፡ ሲሆኑ ፡ በሪሙ ፡ የሚጠቀመው ፡ ሰው ፡ መሞት ፡ ሲረጋገጥ ፡ ለሪም ፡ ሰጪው ፡ ሰነዶቹ ፡ ሊመለሱ ፡ ይቻላል ፡፡

ቍ ፡ ፱፻፲፱ ፡፡ ሰነዶችን ፡ ስለ ፡ መጠየቅ ፡፡

በአደራ ፡ ስለ ፡ ተቀመጡ ፡ ሰነዶች ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ መቅረቡን ፡ ባንኩ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ይኸንኑ ፡ ለአደራ ፡ ሰጪው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ፡፡

## ምዕራፍ ፡ ፪ ፡፡

## ስለ ፡ ካዝና ፡ ኪራይ ፡፡

ቍ ፡ ፱፻፲፱ ፡፡ ስለ ፡ ውሉ ፡ ጉዳይ ፡፡

የካዝና ፡ ኪራይ ፡ ውል ፡ ጉዳይ ፡ አንድ ፡ ካዝና ፡ ወይም ፡ የካዝናውን ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ዋጋ ፡ በማስከፈል ፡ ለተወሰነ፡ ጊዜ ፡ ለተከራዩ ፡ ዝግጁ ፡ ማድረግ ፡ ነው ፡፡

ቍ ፡ ፱፻፳ ፡፡ የባንኩ ፡ ግዴታዎች ፡፡

(፩) ለካዝናዎቹ ፡ መልካም ፡ ሁኔታና ፡ ጥበቃ ፡ ባንኩ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ጥን ቃቄዎች ፡ ሁሉ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ፡፡

(፪) የካዝናዎቹን ፡ አጠባበቅ ፡ የሚያሠጋ ፡ ማናቸውም ፡ አደጋ ፡ የሚደርስ ፡ ሲሆን ፤ ካዝናውን ፡ ለመክፈት ፡ ከተወሰኑት ፡ ደንበኛ ፡ ከሆኑት ፡ የሥራ ፡ ቀኖችና ፡ ሰዓ ቶች ፡ ውጭ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፤ ጉዳቱ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ተከራዮቹ ፡ ካዝ ናዎቻቸውን ፡ ባዶ ፡ ለማድረግ ፡ እንዲችሉ ፡ ባንኩ ፡ አስፈላጊዎቹን ፡ ድርጅ

BACK



ቶች ፡ ማድረግ ፡ አለበት ። ካዝናዎቹን ፡ ለተከራዩት ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ ማስታወቂያ ፡ ለመስጠት ፡ ባንኩ ፡ አይገደድም ።

ቍ ፡ ፱፻፷፩ ። ወደ ፡ ካዝናው ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ መግባት ፤ ቍልፎች ።

(፩) ለተከራዩ ፡ ወይም ፡ በደንብ ፡ ለተወከለው ፡ ሰው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ወደ ፡ ካዝና ፡ ቦታ ፡ መግባትን ፡ ባንኩ ፡ መፍቀድ ፡ አይችልም ።

(፪) የካዝናው ፡ ቍልፍ ፡ ገንዘብነቱ ፡ የባንክ ፡ ሆኖ ፡ መኖር ፡ አለበት ።

በካዝናው፡ውስጥ፡ያስቀመጠ፡እንደ፡ሆነ፤ባንኩ፡የኪራዩን፡ውል፡ሊያፈርስ፡ይችላል ።

ቍ ፡ ፱፻፷፪ ። የተከራዩ ፡ ግዴታዎች ።

ተከራዩ ፡ በተፈጥሮው ፡ አደጋ ፡ የሚያመጣ ፡ ወይም ፡ አደጋ ፡ የሚጥል ፡ ዕቃ ፡ በካዝናው፡ውስጥ፡ያስቀመጠ፡እንደ፡ሆነ፤ባንኩ፡የኪራዩን፡ውል፡ሊያፈርስ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፱፻፷፫ ። የኪራዩ ፡ ዋጋ ፡ ሳይከፈል ፡ ሲቀር ፡ የሚያደረግ ፡ የውል ፡ መፍረስ ።

(፩) በተወሰነው ፡ የመክፈያ ፡ ጊዜ ፡ ኪራዩ ፡ ያልተከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባንኩ ፡ በረ ኮማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ ማስታወቂያውን ፡ ልኮ ፡ ውጤት ፡ ሳያገኝ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ከቈየ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሳይሄድ ፡ ውሉ ፡ በቀጥታ ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ሲያልፍ ፡ ተከራዩ ፡ በተወሰነው ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፡ እካዝናው ፡ ዘንድ ፡ እንዲገኝ ፡ ጥሪ ፡ ካደረገለት ፡ በኋላ ፡ ባንኩ ፡ ካዝናውን ፡ እጁ ፡ ያደርጋል ።

(፪) የተጠራው፡ ተከራይ፡ ያልመጣ፡ እንደ፡ ሆነ፤ ወይም፡ ካዝናውን፡ ከፍቶና፡ ባዶ ፡ ለማድረግ ፡ የቍልፉንም፡ አከፋፈት፡ ምስጢር፡ አመልክቶ፡ ለመመለስ ፡ እንቢ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባንድ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ በተወከለ ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ የተባለው ፡ ካዝና ፡ በግድ ፡ የሚከፈት ፡ ይሆናል ። ይኸውም ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የተወከለው ፡ ሰው ፡ በውስጡ ፡ ስላለው ፡ በባለጉዳዮቹ ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ መተማመኛ ፡ የሚሆን ፡ የጽሑፍ ፡ ዝርዝር ፡ ያዘጋጃል ።

ቍ ፡ ፱፻፷፬ ። ስለ ፡ ካዝናው ፡ መያዝ ።

የካዝናው ፡ መያዝ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ሕግ ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ውል ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ትርጓሜ ፤ የተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ሁኔታዎችና ፡ የሚቈይበት ፡ ጊዜ ።

ቍ ፡ ፱፻፷፭ ። ትርጓሜ ።

(፩) የሒሳብ ፡ ግንኙነት ፡ አላቸው ፡ በሚባሉት ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የተ

BACK



መሳላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ውል ፡ አለ ፡ የሚባለው ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በተወሳሰበ ፡ አኳኋን ፡ ገንዘብ ፡ በማግባትና ፡ በማውጣት ፡ በመካከላቸው ፡ ካሉት ፡ የሥራ ፡ ግንኙነቶች ፡ የተነሣ ፡ የሚገኙትን ፡ የገንዘብ ፡ መብቶች ፡ ባንድ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ለማግባትና ፡ ለነዚሁም ፡ ልዩ ፡ ልዩና ፡ ተከታታይ ፡ ለሆኑት ፡ አሠራሮች ፡ ሒሳቡ ፡ በሚዘጋበት ፡ ጊዜ ፡ ቀሪ ፡ በሚሆነው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ጠቅላላ ፡ አከፋፈል ፡ እንዲኖር ፡ የሚስማሙበት ፡ ውል ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) አንዱ ፡ ወገን ፡ የሚያደርገው ፡ የገንዘብ ፡ ሒሳብ ፡ ማግባት ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ ገንዘብ ፡ ማግባቱን ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ስምምነት ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የሒሳቡ ፡ ምርመራ ፡ አሠራሩ ፡ እንደዚሁ ፡ መሆኑን ፡ የገለጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ አይሆኑም ።

ቍ ፡ ፱፻፳፮ ። በሒሳቡ ፡ የሚገቡ ፡ ዕዳዎች ።

(፩) ጠቅላላ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ በሆኑ ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ አንዳንዶቹን ፡ ለማስቀረት ፡ ስምምነት ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ የሒሳብ ፡ ግንኙነት ፡ ካላቸው ፡ ሰዎች ፡ የሚገኙና ፡ ሕጋዊ ፡ ወይም ፡ የስምምነት ፡ ዋስትና ፡ የሌላቸው ፡ ዕዳዎች ፡ ሁሉ ፤ በደንብ ፡ በተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ።

(፪) ስለሆነም ፡ የሒሳብ ፡ ግንኙነት ፡ ካላቸው ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ በስምምነት ፡ ዋስትና ፡ የሰጠላቸው ፡ ዕዳዎች ፡ ባለጕዳይ ፡ የሆኑ ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ በሚያደርጉት ፡ ባንድ ፡ ልዩና ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ስምምነት ፡ በተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፱፻፳፯ ። በልዩ ፡ ልዩ ፡ ገንዘቦች ፡ ወይም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ለመለዋወጥ ፡ በማይችሉ ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ የተገለጹ ፡ የገንዘብ ፡ መብቶች ።

(፩) አንዳንድ ፡ የገንዘብ ፡ መብቶች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ጥሬ ፡ ገንዘቦች ፡ ወይም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ለመለዋወጥ ፡ በማይችሉ ፡ ነገሮች ፡ የተገለጹ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሒሳብ ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ በተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ሊያስገቡዋቸው ፡ የሚችሉት ፤

(ሀ) ገቢ ፡ የሚደረጉት ፡ ገንዘቦች ፤ መለዋወጥ ፡ መቻላቸው ፡ ግዴታ ፡ በሚሆንበት ፡ በአንድ ፡ በተለየ ፡ አርእስት ፡ ተጽፈው ፡ እንደሆኑና ፤

(ለ) እንዲሁም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ሒሳቡ ፡ በብዙ ፡ አርእስት ፡ የተከፋፈለ ፡ ቢሆንም ፡ የተመላላሹን ፡ ሒሳብ ፡ አንድነት ፡ እያሳጣውም ፡ ተብሎ ፡ ስምምነት ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተነገረው ፡ ሲሆን ፡ የያንዳንዶቹ ፡ አርእስቶች ፡ ቀሪ ፡ ሒሳብ ፤ ጠቅላላ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ቀሪ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፤ የሒሳብ ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸው ፡ በወሰኑት ፡ እጅግም ፡ ቢዘገይ ፡ የተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ በሚዘጋበት ፡ ጊዜ ፡ ለመግባት ፡ እንዲችሉ ፡ አለዋወጣቸው ፡ የሚቻል ፡ መሆን ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፰፻፵፫ ። ተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ስለሚቈይበት ፡ ጊዜ ።

(፩) የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ ሳይወሰን ፡ የተከፈተ ፡ ተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ በስምምነቱ፡ መሠረት ፡ አስቀድሞ ፡ የማስታወቅ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ባይሆን ፡ በልማድ ፡ አስቀድሞ ፡ የማስታወቅ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የሒሳብ ፡ ግንኙነት ፡ ካላቸው ፡ ባንደኛው ፡ ፈቃድ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ የተዘጋ ፡ ይሆናል ።

(፪) የሚቈይበት ፡ ጊዜ ፡ የተወሰነ ፡ ሆኖ ፡ የተከፈተ ፡ ተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ በጊዜው ፡ ማለቅ ፡ ወይም ፡ የሒሳብ ፡ ግንኙነት ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ ስምምነት ፡ ከጊዜው ፡ አስቀድሞ ፡ ይዘጋል ።

(፫) በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ተመላላሹ ፡ ሒሳብ ፡ የሒሳብ ፡ ግንኙነት ፡ ካላቸው ፡ ባንዱ ፡ መሞት ፡ ወይም ፡ በደረሰበት፡ችሎታ፡ማጣት፡ወይም፡መክሠር ፡ ይዘጋል ።

ቍ ፡ ፰፻፵፬ ። የተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ መዘጋት ፡ ውጤቶች ።

የሒሳብ ፡ ግንኙነት ፡ ያሏቸው ፡ ሰዎች ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ካልተስማሙ ፤ ወይም ፡ በሒሳቡ ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ የሚያስከትሉና ፡ ገና ፡ ያልተፈጸሙት ፡ አንዳንድ ፡ ሥራዎች ፡ የሒሳቡን ፡ ቀሪ ፡ ሁኔታ ፡ የሚለውጡ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ የተመላላሹ ፡ ሒሳብ ፡ መዘጋት ፡ በሚሆንበት ፡ ቀን ፡ ያለው ፡ ሒሳብ ፡ ወደ ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ ይለወጣል ። ይኸውም ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ ወዲያውኑ ፡ ተከፋይ ፡ ይሆናል ።

ክፍል ፡ ፪ ።

የተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ውጤቶች ።

ቍ ፡ ፰፻፵፭ ። የሒሳቡን ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ ለሚገባው ፡ ዝግጁ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።

ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ስምምነት ፡ ከሌለ ፤ የሒሳብ ፡ ግንኙነት ፡ ካላቸው ፡ ሰዎች ፡ እያንዳንዱ ፤ ስለ ፡ እሱ ፡ ጥቅም ፡ የሒሳቡ ፡ ሁኔታ ፡ የሚያሳየው ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ፈቀደው ፡ ሊያዝበት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፰፻፵፮ ። የዕዳው ፡ መጥፋት ፡ ወይም ፡ መቀነስ ።

በሒሳቡ ፡ ውስጥ ፡ የገባው ፡ ዕዳ ፤ ከተጻፈበት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ በደረሰ ፡ ምክንያት ፤ የጠፋ ፡ ወይም ፡ የተቀነሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚሁ ፡ መጠን ፡ የተጻፈው ፡ ገንዘብ፡ መሰረዝ ፡ ወይም ፡ መቀነስና ፡ ሒሳቡም ፡ እንዲሁም ፡ መተካከል ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፰፻፵፯ ። ስለ ፡ ዕዳ ፡ ከተሰጠው ፡ ዋስትና ፡ የተገኘውን ፡ ፍሬ ፡ ስለ ፡ ማዘዋወር ።

(፩) በቍጥር ፡ ፰፻፴፯ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ እንደተመለከተው ፡ በልዩና ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ስምምነት ፡ ውስጥ ፡ የገባ ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ከተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ከገባው ፡ የገንዘብ ፡ መብት ፡ ጋራ ፡ በመጀመሪያ ፡ የተያያዘ ፡ ዋስትና ፡ የሚሰጠው ፡ ፍሬ ፡ ተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ በሚዘጋበት ፡

ጊዜ ፡ በሒሳቡ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ሊደርስ ፡ የሚችለው ፡ አለዋወጥ ፡ ሳይታይ ፡ ከሒሳቡ ፡ ቀሪ ፡ ለሚሆነው ፡ ገንዘብ ፡ የሚተላለፍ ፡ ይሆናል ።

(፪) ይህ ፡ ዋስትና ፡ ወደ ፡ ቀሪው ፡ ገንዘብ ፡ መዛወር ፤ የተባለውን ፡ ዋስትና ፡ ለመጠበቅ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በተነገሩት ፡ የማስታወቂያ ፡ ደንቦች ፡ ዐይነት ፡ ካልተፈጸመ ፤ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፫ ። ያንዱን ፡ ክፍል ፡ ሒሳብ ፡ ከሌላው ፡ ላይ ፡ ስላለመቀነስ ።**

በተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ የገባውን ፡ ያንዱን ፡ ክፍል ፡ ተቃራኒ ፡ ሒሳብ ፡ ከሆነው ፡ ከሌላው ፡ ክፍል ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፡ መቀነስ ፡ አይቻልም ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፬ ። የይርጋ ፡ ዘመንና ፡ የወለድ ፡ ደንቦች ።**

(፩) በተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ በሚገቡ ፡ ዕዳዎች ፡ የይርጋ ፡ ዘመንና ፡ የወለድ ፡ ደንቦች ፡ አይፈጸሙባቸውም ።

(፪) ስለ ፡ ሒሳቡ ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ ይርጋ ፡ ጉዳይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፫) የሒሳብ ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ በተስማሙበት ፡ ልክ ፤ ስምምነትም ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በሒሳቡ ፡ የሚገቡት ፡ ገንዘቦች ፡ ወለድ ፡ ይሰጣሉ ።

(፬) ተቃራኒ ፡ ስምምነት ፡ ከሌለና ፡ ሒሳቡ ፡ እስከ ፡ ተዘጋ ፡ ድረስ ፤ የገንዘቡ ፡ መግባት ፡ የተደረገው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የተወሰኑት ፡ የገንዘብ ፡ መግቢያ ፡ ጊዜዎችን ፡ በመጠበቅ ፡ ከሆነ ፡ ገንዘቡ ፡ በተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ከገባበት ፡ ጀምሮ ፡ ወለዶች ፡ ራሳቸው ፡ ወለድ ፡ ይሰጣሉ ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፭ ። በገቢና ፡ በወጪ ፡ ክፍል ፡ ለሚጻፉት ፡ ሒሳቦች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ የወለድ ፡ ልክ ።**

በተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ በገቢና ፡ በወጪ ፡ ክፍል ፡ የሚጻፉት ፡ ገንዘቦች ፡ የሚሰጡት ፡ ወለዶች ፡ ልዩ ፡ ይሆናሉ ፡ ተብሎ ፡ ስምምነት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በሒሳቡ ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ገቢ ፡ ሲደረግ ፡ ወለዶች ፡ የሚታሰቡት ፡ የመጨረሻው ፡ ገቢ ፡ በሒሳቡ ፡ ከገባ ፡ ወዲህ ፡ የሒሳቡን ፡ ሚዛን ፡ በሰጣቸው ፡ ወለዶች ፡ ላይ ፡ ከዚያም ፡ በፊት ፡ የዚያኑ ፡ የሒሳብ ፡ ወገን ፡ የሰጣቸውን ፡ በመጨመርና ፡ ወለዶች ፡ ከሒሳቡ ፡ ውስጥ ፡ በሚገቡበት ፡ ጊዜ ፡ ከሌላው ፡ ሒሳብ ፡ ወገን ፡ የሚገኙት ፡ ወለዶች ፡ እስከ ፡ ተቻቻሉ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፮ ። በአጣራጣሪ ፡ ጊዜ ፡ የሚደረጉትን ፡ ዋስትናዎች ፡ የባለዕዳውን ፡ ንብረት ፡ ሀብት ፡ መቃወሚያ ፡ ለማድረግ ፡ ስላለመቻሉ ።**

(፩) የሒሳብ ፡ ግንኙነቶች ፡ ካላቸው ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ የከሠረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በአጋጣሚ ፡ ከተመላላሹ ፡ ሒሳብ ፡ በዕዳ ፡ ተከፋይ ፡ ለሚሆነው ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡

BACK



ዋስትና ፤ በዚሁ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አምስተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ በቍጥር ፡ ፲፩፻፴፱ ፡ በተመለከተው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ዋስትና ፡ ሲሰጥ ፡ የተመላላሹ ፡ ቀሪ ፡ ሒሳብ ፡ ይህ ፡ በሒሳብ ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ባለዕዳ ፡ መሆኑን ፡ ቀሪ ፡ ሒሳብ ፡ ገልጾት ፡ በነበረው ፡ መጠን ፡ ለዚሁ ፡ ለተመላላሹ ፡ ሒሳብ ፡ ለተመለከተው ፡ ዕዳ ፡ በስምምነት ፡ በንብረቶች ፡ ላይ ፡ የሚሰጣቸው ፡ ዋስትናዎች ፡ በኅብረቱ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆንባቸው ፡ አይችልም ።

(፫) አስፈላጊም ፡ ሲሆን ፡ በዚሁ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ አምስተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ በቍጥር ፡ ፲፩፻ ፡ የተደነገገው ፡ ተፈጻሚ ፡ ካሆልነ ፡ በቀር ፡ ሒሳቡ ፡ በተዘጋበት ፡ ቀን ፡ ዕዳ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኘውን ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ ከቀሪው ፡ ገንዘብ ፡ ጋራ ፡ በማመዛዘን፡ ትርፍ ፡ ገንዘብ ፡ ከተገኘ ፡ የተሰጠው ፡ ዋስትና ፡ ለዚሁ ፡ ትርፍ ፡ ገንዘብ ፡ በኅብረት ፡ ሀብቱ ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆንበት ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፱፻፴፯ ። ተመላላሽ ፡ ሒሳብን ፡ ስለ ፡ ማስያዝ ።

(፩) በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ የተመላላሹ ፡ ቀሪ ፡ ሒሳብ ፤ ገንዘብ ፡ የሚያስጥ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ይኸው ፡ ገንዘብ ፡ እንዳይሰጥ ፡ ለማሳገድና ፡ ለማስያዝ ፡ ይችላል ።

(፪) በተባለው ፡ ገንዘብ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ባለዕዳው ፡ እንዳይያዝበት ፤ በሒሳብ ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ከባለዕዳው ፡ ጋራ ፡ ስምምነት ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ ማስያዙ ፤ ድርሻው ፡ ከታያዘበት ፡ ባለዕዳ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በስምምነቱ ፡ የሚያገኛቸውን ፡ መብቶች ፡ ሊያስቀርበት ፡ አይችልም ።

ክፍል ፡ ፫ ።

በተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ በቅናሽ ፡ የገቡት ፡ የንግድ ፡ ሰነዶች ፡ ገቢ ፡ በተደረጉ ፡ ጊዜ ፡ የሰጪው ፡ መክሰር ፡ የሚያስገኘው ፡ ውጤት ።

ቍ ፡ ፱፻፴፰ ። ሰነዶችን ፡ መልሶ ፡ ወደ ፡ ሒሳብ ፡ ስለ ፡ ማግባት ።

(፩) በንግዱ ፡ ወረቀቶች ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ቅናሽ ፡ በተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ገቢ ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ወረቀቶቹም ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ ሳይከፈልባቸው ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እነዚህን ፡ ወረቀቶች ፡ የተቀበለው ፡ ሰው ፤ ሰጪው ፡ መክሠሩ ፡ ከታወቀ ፡ በኋላ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ወረቀቶቹን ፡ በሒሳቡ ፡ ውስጥ ፡ መልሶ ፡ ማግባት ፡ ይችላል ። እንዲህም ፡ ማለት ፡ በቍጥር ፡ ፺፻፺፩ ፡ የተመለከቱትን ፡ ወጪዎች ፡ ተጨማሪ ፡ በማድረግ ፡ በንግድ ፡ ወረቀቶች ፡ ላይ ፡ በተጻፈው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በወጪ ፡ ስም ፡ በሒሳቡ ፡ ውስጥ ፡ ይጻፋሉ ፡ ማለት ፡ ነው ።

(፪) ሰጪው ፡ የከሠረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በመክፈያቸው ፡ ቀን ፡ ላልተከፈሉ ፡ ቀሪ ፡ ለሆኑ ፡ ሰነዶች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከሒሳቡ ፡ ውስጥ ፡ መልስ ፡ ማግባት ፡ አይፈቀድም ። ይህ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ስምምነት ፡ ሁሉ ፡ አይጸናም ።

ቍ ፡ ፱፻፴፱ ። በሒሳብ ፡ ተመልሰው ፡ የሚገቡት ፡ ወረቀቶች ፡ የወደፊት ፡ ሁኔታ ።

(፩) በሒሳብ ፡ ተመልሰው ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ በመክሠር ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ላለው ፡ ሰጪ ፤

የተመላላሹ ፡ ሒሳብ ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ ጥቅም ፡ የሚያስገኝ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተቀባዩ ፡ መልሶ ፡ ከሒሳብ ፡ ያገባቸውን ፡ ሰነዶች ፡ ለመስጠት ፡ ይገደዳል ።

(፪) በሒሳብ ፡ ተመልሰው ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ በመከሠር ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ላለው ፡ ሰጪ ፡ የተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ ዕዳ ፡ እንዳለበት ፡ የሚገልጽ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሚከፈሉበት ፡ ጊዜ ፡ ማናቸውም ፡ ቢሆን ፡ ተቀባዩ ፡ ሰነዶቹን ፡ እንደያዘ ፡ እንዲቈይ ፡ የተፈቀደ ፡ ነው ።

(፫) በቍጥር ፡ ፱፻፴፱ ። ያለው ፡ ቃል ፡ ተቀዳሚነት ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፤ የንግድ ፡ ወረቀቶቹን ፡ የተቀበለው ፡ ሰው ፡ በተመላላሹ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ተመልሰው ፡ ከገቡት ፡ ወረቀቶች ፡ ጋራ ፡ በተያያዙት ፡ መብቶችና ፡ ዋስትናዎች ፡ መሠረት ፡ ለወረቀቱ ፡ በአንድነት ፡ ላይ ፡ ከፋፈል ፡ ተገዳጆች ፡ ከሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ወደፊት ፡ የሚገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ ወረቀቶቹ ፡ ተመልሰው ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ ሒሳቡ ፡ በቆመ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚያገኘው ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ ከኪሣራው ፡ ውስጥ ፡ ከሚደርሰው ፡ ጋራ ፡ ጨምሮ ፡ ለመቀበል ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፱፻፵ ። የተቀባዩ ፡ መብቶች ፡ ወሰን ።

(፩) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ በቍጥር ፡ ፱፻፴፱ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፫ ፡ እንደተመለከተው ፡ የንግድ ፡ ወረቀቶቹን ፡ ተቀባይ ፡ በድምር ፡ የሚያገኘው ፡ ገንዘብ ፤ ወረቀቶቹ ፡ በተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ውስጥ ፡ ተመልሰው ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ የሒሳቡ ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ ከሚያስገኘው ፡ ልክ ፡ የሚበልጥ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ስለዚህም ፡ ወረቀቶቹን ፡ በሰጠው ፡ ሰው ፡ መክሠር ፡ አሠራር ፡ ውስጥ ፡ የሚያገኘው ፡ ድርሻ ፡ በደንብ ፡ ተቀናሽ ፡ ይሆናል ።

(፪) ከዚህም ፡ በቀር ፡ በኪሣራው ፡ ቀን ፡ የንግድ ፡ ወረቀቶቹ ፡ በተመላላሹ ፡ ሒሳብ ፡ ተመልሰው ፡ ከመግባታቸው ፡ በፊት ፡ የሒሳቡ ፡ ሚዛን ፡ በወረቀቶቹ ፡ ሰጪ ፡ ላይ ፡ ዕዳ ፡ መኖሩን ፡ ገልጸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከመደመር ፡ የተነሣ ፡ ወረቀቶቹን ፡ የሚቀበል ፡ ሰው ፡ በሒሳቡ ፡ ውስጥ ፡ ተመልሰው ፡ የገቡት ፡ ወረቀቶች ፡ ገንዘብ ፡ ልክና ፡ እነዚህም ፡ በሒሳቡ ፡ ተመልሰው ፡ ከመግባታቸው ፡ በፊት ፡ ሒሳቡ ፡ ያመለከተው ፡ የነበረው ፡ ቀሪ ፡ ገንዘብ ፡ ባንድነት ፡ ተደምረው ፡ ከሚያገኙት ፡ ገንዘብ ፡ የበለጠ ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ። ስለዚህም ፤ ወረቀቶቹን ፡ በሰጠው ፡ ሰው ፡ የመክሠር ፡ አሠራር ፡ ውስጥ ፡ የሚያገኘው ፡ ድርሻ ፡ በደንብ ፡ ተቀናሽ ፡ ይሆናል ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## ስለ ፡ ቅናሽ ።

ቍ ፡ ፱፻፵፩ ። ትርጓሜ ።

(፩) የቅናሽ ፡ ውል ፡ ማለት ፡ ባለባንክ ፡ የሆነው ፤ የሚከፈሉበት ፡ ጊዜ ፡ የተወሰኑትን ፡ የንግድ ፡ ሰዶኖች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ የሚተላለፉ ፡ ሰነዶችን ፡ ገንዘብ ፡ አስቀ

ድሞ ፡ ላምጪው ፡ ለመክፈል ፡ የሚገደድበትና ፡ አምጪውም ፡ ካልከፈለ ፡ ዋና ፡ ተገዳጁ ፡ ገንዘቡን ፡ ያልከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተቀበለውን ፡ ገንዘብ ፡ ለ መልስለት ፡ የሚደረግ ፡ ስምምነት ፡ ነው ።

(፪) ይኸውም ፡ አሠራር ፡ ለባለባንኩ ፡ ወለድ ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ወለድ ፡ ጋራ ፡ በወረቀቶቹ ፡ ጀርባ ፡ የመፈረም ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ ኮሚሲዮን ፡ የሚያስገኝለት ፡ ነው ።

(፫) ልዩ ፡ በሆነ ፡ ስምምነት ፡ ቍርጥ ፡ የሆነ ፡ ቅናሽን ፡ አስቀድሞ ፡ ለመዋዋል ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፱፻፵፪ ። የወለዶችና ፡ የኮሚሲዮኖች ፡ ሒሳብ ፡ አቈጣጠር ።

(፩) ወለዶቹ ፡ የሚታሰቡት ፡ ሰነዶች ፡ የሚከፈሉበት ፡ ቀን ፡ ለመድረስ ፡ በሚቀረው ፡ ጊዜ ፡ መሠረት ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የሰነዶቹን ፡ ዋጋ ፡ ባንኩ ፡ የሚቀበልበት ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ በቅናሹ ፡ ገንዘብ ፡ የወሰደው ፡ ሰው ፡ ከመክፈያ ፡ ጊዜያቸው ፡ አስቀድሞ ፡ በሚከፍልበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ወለዱ ፡ የሚታሰበው ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ባነሰ ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፡ ነው ።

(፪) የሚከፈለውም ፡ ኮሚሲዮን ፡ የሚታሰበው ፡ በሰነዶቹ ፡ ላይ ፡ በተጻፈው ፡ ገንዘብ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፫) ወለዱና ፡ ኮሚሲዮኑ ፡ ከዚህ ፡ አያንስም ፡ ተብሎ ፡ ሊወሰን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፱፻፵፫ ። የባለጥቅሙ ፡ ግዴታዎች ።

(፩) ቅናሽ ፡ ተደርጎ ፡ ገንዘብ ፡ የተቀበለው ፡ ሰው ፡ ባልተከፈሉት ፡ ወረቀቶች ፡ ወይም ፡ ሰነዶች ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ዋጋ ፡ ለባለባንኩ ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

(፪) የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ለወረቀቱ ፡ ከፊል ፡ ገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ቅናሽ ፡ እንዲደረግላቸው ፡ የሆኑ ፡ ሰነዶች ፡ በዚሁ ፡ ከፊል ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ብቻ ፡ ይከፈልባቸዋል ።

ቍ ፡ ፱፻፵፬ ። የባለባንኩ ፡ መብቶች ።

(፩) በንግድ ፡ ወረቀቶቹ ፡ ዋና ፡ ባለዕዳዎች ፤ ቅናሽ ፡ ተደርጎ ፡ ገንዘብ ፡ በተቀበለና ፡ በሌሎችም ፡ የጋራ ፡ ተገዳጆች ፡ ላይ ፡ ባለባንኩ ፡ ቅናሽ ፡ ካደረገባቸው ፡ ወረቀቶች ፡ ጋራ ፡ የተያያዙት ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ ይኖሩታል ።

(፪) ከዚህም ፡ በቀር ፡ ቅናሽ ፡ ተደርጎ ፡ ገንዘብ ፡ ከተቀበለው ፡ ሰው ፡ የወሰደውን ፡ ገንዘብ ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ ኮሚሲዮኖችና ፡ ወለዶች ፡ ተጨምረው ፡ ባንኩ ፡ መልሶ ፡ ለመክፈል ፡ የሚስያችለውን ፡ ሰነዶቹ ፡ በሚሰጡት ፡ መብቶች ፡ መሠረት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ። ያልተከፈለበት ፡ ምክንያት ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ቢሆን ፡ ባልተከፈለባቸው ፡ ሰነዶች ፡ ልክ ፡ ይህ ፡ መብት ፡ ይሠራበታል ። በሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ተመላላሽ ፡ ሒሳብ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከቍጥር ፡ ፱፻፴፰ ፡ እስከ ፡ ፱፻፵፩ ፡ በተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ መብቱን ፡ ይሠራበታል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## ብድር ፡ ስለሚያሰጡ ፡ ግንኙነቶች ፡ (ክሬዲ) ፤

### ክፍል ፡ ፩ ።

### የብድር ፡ መከፈት ።

**ቍ ፡ ፱፻፵፩ ። ዓላማው ።**

(፩) የብድር ፡ መከፈት ፤ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ መክፈያ ፡ የሆኑትን ፡ ዘዴዎች ፡ ለተጠቃሚው ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በዘወርዋራ ፡ እንዲያዝበት ፡ የሚያደርግ ፡ ዓላማ፡ ያለው ፡ አሠራር ፡ ነው ።

(፪) የብድሩ ፡ መከፈት ፡ ለተወሰነ ፡ ወይም ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚደረግ ፡ ነው ። ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን፤ በባለባንኩ፡ ፈቃድ ፡ በማናቸውም፡ ጊዜ ፡ ቀሪ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፱፻፵፪ ። ስለ ፡ መቅረት ።**

የብድሩ ፡ መከፈት ፡ ከስምምነቱ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፤ በባለጥቅሙ ፡ መሞት ፡ ወይም ፡ በደረሰበት ፡ ችሎታ ፡ ማጣት ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ያልተገለጸ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ዕዳ ፡ መክፈሉን ፡ በማቋረጥና ፡ በተሰጠው ፡ ክሬዲ ፡ ሥራ ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ከባድ ፡ ጥፋት ፡ ሲያደርግ ፡ ቀሪ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

### ክፍል ፡ ፪ ።

### ሰነድ ፡ አሲዞ ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መበደር ።

**ቍ ፡ ፱፻፵፫ ። ትርጓሜ ።**

ሰነድ ፡ አሲዞ ፡ ገንዘብ ፡ መበደር ፡ ማለት ፤ የሚጠቀመውን ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ፈቃድ ፡ የሚሰጠውን ፡ የሦስተኛ ፡ ወገን ፡ የሆኑትን ፡ ሰነዶች ፡ መያዣ ፡ በማድረግ ፡ ባለባንኩ ፡ የተወሰነ ፡ ብድር ፡ የሚሰጥበት ፡ አሠራር ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፱፻፵፬ ። ፎርም ።**

(፩) ሰነድ ፡ አሲዞ ፡ ገንዘብ ፡ ለመበደር ፡ በተፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ውሉ ፡ በጽሑፍ ፡ መሆን ፡ አለበት ። አለበለዚያ ፡ ውሉ ፡ ፍጹም ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።

(፪) ጽሑፍም ፡ የሚያሳየው ፤

(ሀ) በመያዣ ፡ የተሰጡትን ፡ ሰነዶች ፡ ዝርዝር ፤

(ለ) የተበዳሪውን ፡ ወይም ፡ የባለሀብቱን ፡ ስምና ፡ መደበኛ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፤

(ሐ) የተሰጠውን፡ ብድር ፡ ልክና ፡ የተሰጡበት ፡ ውለታዎች ፡ (ግዴታዎች) ፡ ነው።

BACK



**ቍ ፡ ፱፻፵፱ ። ሰነዶችን ፡ ስለ ፡ መሸጥ ።**

ተበዳሪው ፡ የተወሰነውን ፡ የግምት ፡ መጠን ፡ እንዳይጓደል ፡ ለማድረግ ፡ ያለ በትን ፡ ግዴታ ፡ ያልፈጸመ ፡ ወይም ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ የተበደረውን ፡ ገንዘብ ፡ ያልከፈለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባለባንኩ ፡ የያዛቸውን ፡ ሰነዶች ፡ ሊሸጥ ፡ ይችላል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ስለ ፡ ሰነዶቹ ፡ መያዣነት ።

**ቍ ፡ ፱፻፶ ። መሠረቱ ።**

ሊተላለፉ፡ የሚችሉ ፡ ሰነዶችን ፡ ሁሉ፡ ምንም፡ ዐይነት፡ ቢሆኑ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ በተነገሩት ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ በመያዣነት ፡ ሊሰጡ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፱፻፶፩ ። ዋስትና ፡ የሚሰጥባቸው ፡ ግዴታዎች ።**

(፩) የሚተላለፉ ፡ ሰነዶች ፤ ልኩ ፡ ላልተወሰነ ፡ ገንዘብም ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፤ ስለ ፡ ግዴታዎች ፡ ሁሉ ፡ አፈጻጸም ፡ በዋስትና ፡ ሊሰጡ ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንዲሁም ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ መያዣው ፡ በተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ መድረሳቸው ፡ ላልተረጋገጠ ፡ ግዴታዎች ፡ አፈጻጸም ፡ በዋስትና ፡ ሊሰጡ ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፱፻፶፪ ። ፎርም ።**

(፩) መያዣ ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ሰነዶቹ ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ በእጁ ፡ የሚገኙ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ውሉን ፡ ከተዋዋለበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በመያዣ ፡ ሆኖ ፡ እጁ ፡ እንዳገባቸው ፡ ሁኖ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) በመያዣ ፡ ለተሰጡት ፡ ሰነዶች ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ በያዛቸው ፡ አንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መያዣ ፡ የተቀበለው ፡ ባለገንዘብ ፡ እጁ ፡ እንዳገባቸው ፡ የሚቈጠረው ፡ ይህ ፡ የያዘው ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ በመጀመሪያ ፡ ጥያቄ ፡ መክፈት ፡ ባለበት ፡ በልዩ ፡ ሒሳብ ፡ የተባሉትን ፡ ሰነዶች ፡ ከገባለት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

(፫) በአውጪው ፡ ማኅበር ፡ መዝገቦች ፡ ውስጥ ፡ በተመዘገቡ ፡ ስም ፡ በተጻፈባቸው ፡ የምስክር ፡ ወረቀቶች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ሰነዶች ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ መያዣ ፡ ተቀብለው ፡ ባለገንዘብ ፡ እጁ ፡ እንዳገባቸው ፡ የሚቈጠረው ፡ የዋስትናው ፡ መተላለፍ ፡ ከተመዘገበበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፱፻፶፫ ። መያዣን ፡ የሚሰጠው ፡ ሰው ፡ ግዴታ ።**

መያዣን ፡ የሚሰጠው ፡ ሰው ፡ ዋስትና ፡ ላለው ፡ ግዴታ ፡ ራሱ ፡ በግል ፡ የማይገደድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የሚገደደው ፡ በዋስትና ፡ ብቻ ፡ ነው ።

BACK

ቍ ፡ ፲፪፻፺፩ ። ሪም ፡ ሰጭ ፡ የሚሰጠው ፡ ዋስትና ።

በሪምነት ፡ የተሰጡትን ፡ ሰነዶች ፡ ሪም ፡ ሰጪው ፡ በዋስትና ፡ ለሌላ ፡ የሰጣቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሪም ፡ የተሰጠበት ፡ ዘመን ፡ ሲፈጸም ፡ ዋስትናው ፡ በሀብትነታቸው ፡ ላይ ፡ በሙሉ ፡ ይተላለፋል ።

ቍ ፡ ፲፪፻፺፪ ። ሰነዶችን ፡ የያዘው ፡ ሰው ፡ መብቶችና ፡ ግዴታዎች ።

በመያዣ ፡ የተሰጡትን ፡ ሰነዶች ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ከቍጥር ፡ ፰፻፺፯ ፡ እስከ ፡ ፱፻ ፡ በተወሰኑት ፡ መብቶች ፡ ይሠራባቸዋል ፤ ለግዴታዎቹም ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፲፪፻፺፫ ። ሰነድን ፡ በጁ ፡ የያዘ ፡ የሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ሁኔታ ።

መያዣው ፡ እንዲያዝ ፡ በስምምነት ፡ ፈቃደኛ ፡ የሆነ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ስምምነቱን ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ በተቀበለ ፡ ጊዜ ፡ በግልጽ ፡ እንዲጠበቅለት ፡ ካላስታወቀ ፡ በቀር ፡ በፊት ፡ በነበሩበት ፡ ምክንያቶች ፡ ሁሉ ፡ የነበረውን ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ተወ ፡ ይቈጠራል ።

ቍ ፡ ፲፪፻፺፬ ። የመያዣ ፡ ተቀባዩ ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ።

በመያዣ ፡ ከተሰጡ ፡ ሰነዶች ፡ በተገኙት ፡ ጥቅሞች ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ ተመልሰው ፡ በተከፈሉት ፡ ገንዘቦች ፡ ላይ ፤ ወይም ፡ ስለነርሱ ፡ በተሰጡት ፡ ሌሎች ፡ ሰነዶች ፡ ላይ ፤ የመያዣ ፡ ተቀባዩ ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ፡ በተዋዋዮቹ ፡ መካከል ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ፊት ፤ ከመያዣው ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የጸና ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፲፪፻፺፭ ። መያዣ ፡ ሰጪው ፡ ግዴታዎቹን ፡ ስላለመፈጸሙ ፡

በጠፋው ፡ ወይም ፡ በተበላሸው ፡ ማረጋገጫ ፡ ሰነድ ፡ ምትክ ፡ በጣም ፡ አጭር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ዋጋቸው ፡ ተተካካይ ፡ የሆኑ ፡ አዲስ ፡ ማረጋገጫዎች ፡ ካልተሰጠ ፡ በቀር ፡ መያዣ ፡ ሰጪው ፡ ማናቸዎቹንም ፡ ግዴታዎች ፡ አለመፈጸሙ ፡ ዋስትና ፡ የተሰጠበትን ፡ ገንዘብ ፡ ወዲያውኑ ፡ እንዲከፍል ፡ ያደርገዋል ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

## በሰነድ ፡ ስለሚሰጡ ፡ ብድሮች ፡ (ክሬዲ) ።

ቍ ፡ ፲፪፻፺፮ ። ትርጓሜ ።

(፩) አንድ ፡ ባንክ ፡ ለራሱ ፡ ወይም ፡ ለወኪሉ ፡ የተወሰኑ ፡ ሰነዶች ፡ በቀረቡለት ፡ ጊዜ ፡ እነዚህን ፡ ሰነዶች ፡ መያዣ ፡ አድርጎ ፤ የሚከፈተው ፡ የብድር ፡ ሒሳብ ፡ በሰነድ ፡ የሚሰጥ ፡ ብድር ፡ ይባላል ። በሱና ፡ በባለቤቱ ፡ መካከል ፡ በተደረገው ፡ ውል ፡ መሠረት ፤ ባንኩ ፡ በነዚህ ፡ ሰነዶች ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱትን ፡ ዕቃዎች ፡ በጁ ፡ ሊያደርግና ፡ ሊሸጣቸው ፡ ይችላል ።

(፪) በሰነዱ ፡ የተሰጠው ፡ ብድር ፡ ባንኩ ፡ ካልተዋዋለው ፡ ለብድሩ ፡ መሠረት ፡ ከሆነው ፡ የሽያጭ ፡ ውል ፡ ሁሉ ፡ የተለየ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፱፻፷ ። ስለ ፡ ባንኩ ፡ ግዴታ ።

ስለ፡መክፈል፤ ስለ፡እሽታ ፤ ስለ ፡ ቅናሽ፡ ወይም፡ ስለ፡ማስተላለፍ ፡ የተደነገጉትን ፡ የውለታ ፡ ቃሎች ፡ ብድሩን ፡ የከፈተው ፡ ባንክ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፱፻፷፩ ። የሚሻርና ፡ የማይሻር ፡ ብድር ።

በሰነድ ፡ የሚሰጥ ፡ ብድር ፡ የሚሻር ፡ ወይም ፡ የማይሻር ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ። ግልጽ፡ የሆነ ፡ ተቃራኒ፡ የውል ፡ ቃል፡ ከሌለ ፤ በቍርጥ፡ለተወሰነ፡ ጊዜ ፡ የተከፈተ፡ ቢሆንም፡በሰነድ፡የሚሰጥ፡ብድር፡ሁሉ፡ለመሻር፡እንደሚቻል ፡ ሆኖ፡ ይገመታል ።

ቍ ፡ ፱፻፷፪ ። የሚሻር ፡ ብድር ፡ ውጤቶች ።

የሚሻር ፡ ብድር ፡ በባንኩና ፡ በባለ ፡ ጥቅሙ ፡ መካከል ፡ ሕጋዊ ፡ አስገዳጅነት ፡ የለውም ። ለባለ ፡ ጥቅሙ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሳይሰጥ ፤ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ባንኩ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ብድሩን ፡ ለመለወጥ ፡ ወይም ፡ ለመሻር ፡ ይችላል ። እንደዚህ ፡ ዐይነት ፡ ያለው ፡ ብድር ፡ በባንኩ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ባንክ ፡ በተዘዋወረ ፡ ጊዜ ፤ መለወጡ ፡ ወይም ፡ መሻሩ ፡ የሚጸናው ፤ ይህንኑ ፡ የሚገልጽ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለተባለው ፡ ለባንኩ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ወይም ፡ ለሌላው ፡ ባንክ ፡ በብድሩ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ገንዘብ ፡ ከመክፈሉ ፡ ወይም ፡ ሰነዱን ፡ ከማስተላለፉ ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ እንዲያወጣ ፡ ከመፈቀዱ ፡ በፊት ፡ የደረሰው ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፱፻፷፫ ። የማይሻር ፡ ብድር ፡ ውጤቶች ።

ሰነዶች ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ሁኔታው ፤ ሰነዶቹና ፡ የሐዋላው ፡ ወረቀት ፡ (ድራፍት ፡) በብድሩ ፡ ውስጥ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ የውል ፡ ቃሎችና ፡ ገደቦች ፡ ጋራ ፡ የተስማሙ ፡ ከሆኑ ፡ የብድር ፡ ሰነድ ፡ አውጪ ፡ ባንክ ፤ ለባለ ፡ ጥቅሙ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ሁኔታው ፤ ይህንኑ ፡ ብድር ፡ ተመርኵዞ ፡ ለወጣው፡ የሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ (ድራፍት) ባለጥቅም ፡ ለሆነው፡ ሰውና ፡ በቅን ፡ ልቡና፡ ባለይዞታ፡ ለሆኑትም ፡ ሰዎች፤ ጭምር ፤ ስለ፡ አከፋፈል ፤ ስለ ፡ መቀበልና ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ፡ በብድሩ ፡ ውስጥ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ግዴታዎች ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ማድረግ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፱፻፷፬ ። የማይሻር ፡ ብድርን ፡ ስለ፡ማጽናት ።

(፩) የማይሻር ፡ የብድር ፡ ሰነድ ፡ ያወጣውን ፡ ባንክ ፡ አጽድቅልኝ ፡ ብሎ ፡ ሌላውን ፡ ባንክ ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፤ ተጠያቂውም ፡ ባንክ ፡ ትእዛዙን ፡ ተቀብሎ ፡ ብድሩን ፡ ያጸደቀው ፡ እንደ፡ ሆነ፤ ካጸደቀበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ የተወሰነ ፡ ኀላፊነትን ፡ እንደ፡ ተቀበለ ፡ ይቈጠራል ።

(፪) ብድሮቹ ፡ የሚገኙት፡ የሐዋላውን ፡ ወረቀት ፡ (ድራፍት) ፡ በማስተላለፍ ፡ የሆነ፡ እንደ፡ሆነ ፤ የማይሻረውን ፡ ብድር፡ ያጸደቀው ፡ ባንክ ፡ ኀላፊ ፡ ሆኖ ፡ ግዴታ ፡ እንደ፡ገባ፡ የሚቈጠረው ፤ አውጪ ፡ የሆነውን ፡ ወገን ፡ ሳይጠይቅ፡ የሐዋላውን ፡ ወረቀት ፡ (ድራፍት) ፡ እንዲያስተላልፍ ፡ ነው ።

(፫) በነገሩ ፡ ተገቢነት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ካልተስማሙ ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ግዴታ ፡ ለመለወጥ ፡ ወይም ፡ ለመሻር ፡ አይቻልም ።

(፬) የብድር ፡ ሰነድ፡ መዘጋጀቱን፡ ለባለጥቅሙ፡አስታውቅ፡ ተብሎ፤ አገናኙውን ፡ በከብል ፡ ወይም ፡ በቴሌግራፍ ፡ ባዘዘው፡ ጊዜ፤ ይኸው ፡ ሰነዱን ፡ አውጪ ፡ ባንክ ፡ የብድር፡ ሰነድ፡ ራሱ ፡ እንደ፡ ገንዘብ፡ ሆኖ ፡ እንዲዘዋወር፡ ታስቦ፡እንደ ፡ ሆነ ፤ ዋናውን ፡ የብድር ፡ ሰነድ፡ ለተባለው ፡ አገናኝ ፡ መላክ ፡ አለበት ፤ ከዚህ፡ የተለየ ፡ መንገድ ፡ የተከተለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የተነሣ ፡ ለሚመጣው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሰነዱን ፡ አውጪ ፡ ባንክ ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፱፻፷፮ ። ሰነዶችን ፡ ስለ ፡ መመርመር ፡ ግዴታ ።

ባንኩ ፡ በብድሩ ፡ ውስጥ ፡ ካሉት ፡ ትእዛዞች ፡ ጋራ ፡ ሰነዶቹ ፡ ትክክለኛ ፡ መሆናቸውን ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ። ሰነዶቹን ፡ አልቀበልም ፡ ያለ ፡ እንደ፡ሆነ ፤ ባንኩ፡ በጣም ፡ አጭር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይህንን ፡ አለመቀበሉንና ፡ ያገኛቸውንም ፡ ጕድለቶች ፡ ሰነዶቹን ፡ ላቀረበው ፡ ሰው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፱፻፷፯ ። ስለ ፡ ባንኩ ፡ ኀላፊነት ።

የቀረቡትን ፡ ሰነዶች ፡ እንደሚታዩት ፡ በተቀበላቸው ፡ ትእዛዞች ፡ መሠረት ፡ ትክክል ፡ መስለው ፡ የታዩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባንኩ ፡ ምንም ፡ ኀላፊነት ፡ የለበትም ። ለከፈተው ፡ ብድር ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ለሚመለከት ፡ ጕዳይ ፤ ባንኩ ፡ ምንም ፡ ግዴታ ፡ የለበትም ።

ቍ ፡ ፱፻፷፰ ። ብድርን ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍና ፡ ስለ ፡ ማከፋፈል ።

በሰነድ ፡ የሚሰጥ ፡ ብድር ፡ የሚተላለፈው ፡ ወይም ፡ የሚከፋፈለው ፡ መጀመሪያው ፡ ባለጥቅም ፡ የሆነው ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ለአንድ፡ ወይም፡ ለብዙ፡ ለሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ እንዲከፍል ፡ ባንኩን ፡ ያዘዘው ፡ ሲሆን ፡ ነው ፤ ብድሩን ፡ በሚከፍተው ፡ ባንክ፡ግልጽ ፡ በሆኑ ፡ ትእዛዞች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለማስተላለፍ ፡ አይቻልም ። ተቃራኒ ፡ስምምነት ፡ ከሌለ ፡ ብድሩ ፡ የሚተላለፈው፡ ለአንድ፡ ጊዜ፡ ብቻ ፡ ነው ።

# አምስተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## የኪሣራና ፡ የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ።

### አንቀጽ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

ቍ ፡ ፱፻፷፱ ። ሕጉ ፡ የሚፈጸምበት ፡ ወሰን ።

(፩) የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ አንደኛ ፡ መጽሐፍ፡ በቍጥር፡ ፭ ፡ መሠረት ፡ ነጋዴ ፡ በሆኑ ፡ ሰዎችና ፤ በዚህ ፡ ሕግ ፡ አንደኛ ፡ መጽሐፍ፡ በቍ

ጥር ፡ ፲ ፡ መሠረት ፡ የእሽሙር ፡ ማኅበሮች ፡ ከሆኑት ፡ በቀር ፡ በንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ቡተለይ ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ በአራተኛው ፡ አንቀጽ፡ በተነገሩት፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ተፈጻሚ ፡ የሚሆኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ፡ ሆነው ፤ በዚህ ፡ መጽሐፍ፡ በአንቀጽ ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ እና ፡ አምስት፡ የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ በነጋዴዎችና ፡ በንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፱፻፸፱ ። ስለ ፡ መክሠር ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሁኔታ ።

ማንኛውንም ፡ ከንግዱ ፡ የተያያዘውን ፡ ዕዳውን፡ መክፈል ፡ ያቋረጠና፡ መክሠሩ፡ በፍርድ፡ የተወሰነ ፡ ነጋዴ ፡ ሁሉ ፡ የከሠረ ፡ ሆኖ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፱፻፹ ። ስለ ፡ መክሠር ፡ ሁኔታዎች ።

(፩) ነጋዴው ፡ የከሠረ ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ፍርድ ፡ ካልተሰጠ ፡ በቀር ፤ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ ዕዳውን ፡ ከመክፈል ፡ በማቋረጡ ፡ ብቻ ፡ ከሠረ ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ።

(፪) ስለሆነም ፡ የገንዘብ ፡ መክፈሉ ፡ መቋረጥና ፡ የነጋዴው ፡ መክሰር ፡ በፍርድ ፡ ባይወሰንም ፤ በመክሠር ፡ ላይ ፡ በሚደረግ ፡ የማጭበርበር ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ የወንጀል ፡ ሥራዎች ፤ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ ሊፈርድ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፱፻፹፩ ። የዕዳ ፡ መክፈል ፡ መቋረጥ ፡ ስለሚታወቅበት ፡ ሁናቴ ።

የዕዳ ፡ መክፈል ፡ መቋረጥ ፡ ሁናቴ ፤ ባለዕዳው ፡ በንግድ ፡ ሥራው ፡ ያሉበትን ፡ ግዴታዎች ፡ ለመክፈል ፡ አለመቻሉን ፡ ከሚገልጹ ፡ ከማንኛዎችም ፡ ሁኔታዎችና ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ ሰነዶች ፡ ይገኛል ።

ቍ ፡ ፱፻፹፪ ። የዕዳ ፡ መክፈልን ፡ መቋረጥ ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።

ማንኛውም ፡ ነጋዴ ፡ በንግድ ፡ ምክንያት ፡ የደረሰበትን ፡ ዕዳ ፡ ከመክፈል ፡ ያቋረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የመክሠር ፡ ወይም ፡ የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ እንዲጀመር ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ በቍጥር ፡ ፱፻፹፩ ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፶፫ ፡ መሠረት ፡ ባለሥልጣን ፡ ለሆነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ሁኔታውን ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፱፻፹፫ ። ከማስታወቂያው ፡ መያያዝ ፡ ስላለባቸው ፡ ሰነዶች ።

(፩) ስለ ፡ አከፋፈል ፡ መቋረጥ ፡ በቍጥር ፡ ፱፻፹፪ ፡ ከሚደረገው ፡ ማስታወቂያ ፡ ጋራ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ያሉት ፡ ጽሑፎች ፡ መያያዝ ፡ አለባቸው ። ጽሑፎቹም ፡ ቀን ፡ ይጻፍባቸውና ፡ ይፈረማሉ ።

BACK



(ሀ) የንግድ ፡ ቤቱ ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛን ፤

(ለ) የኪሣራና ፡ የትርፍ ፡ ሒሳብ ፤

(ሐ) የገንዘብ ፡ ጠያቂዎችንና ፡ የዕዳ ፡ ከፋዮችን ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፡ ከሚያመለክት ፡ ማስታወቂያ ፡ ጋራ ፡ ከንግድ ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ የተያያዙ ፡ የሆኑትን ፡ ለነጋዴው ፡ ገቢ ፡ የሚሆኑትንና ፡ ያሉበትንም ፡ ዕዳዎች ፡ ዝርዝር ፤

(፪) እነዚህን ፡ ጽሑፎች ፡ አንዱን ፡ ወይም ፡ ሌላውን ፡ ለማቅረብ ፡ ያልተቻለ ፡ ወይም ፡ ጕድለት ፡ ያለባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የዚህን ፡ ምክንያት ፡ ማስታወቂያው ፡ ማመልከት ፡ አለበት ።

## አንቀጽ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ መክሠር ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ መክሠር ፡ የሚሰጡ ፡ ፍርዶች ።

ቍ ፡ ፱፻፸፬ ። ባለሥልጣን ፡ ስለሆነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

(፩) በመክሠር ፡ ረገድ ፡ የሚቀርቡትን ፡ ክሶች ፡ ለመወሰን ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ የነጋዴው ፡ ሥራ ፡ በተቋቋመበት ፤ ወይም ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ንግዶች ፡ ያሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዋናው ፡ የንግዱ ፡ ሥራ ፡ ባለበት ፡ ቦታ ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

(፪) ይህም ፡ የንግዱ ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የኢንተርናሲዮናል ፡ ስምምነቶች ፡ አፈጻጸም ፡ ሳይነካ ፡ መክሠሩ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የተወሰነ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፤ መክሠሩ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሊታይ ፡ ይቻላል ።

ቍ ፡ ፱፻፸፭ ። ነገሩን ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

የነጋዴው ፡ መክሠር ፡ ነገር ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚታየው ፡

(ሀ) ባለዕዳ ፡ የሆነው ፡ ነጋዴ ፡ መክሠሩን ፡ ለማስታወቅ ፡ ማመልከቻ ፡ ሲያቀርብ ፤ ወይም ፡

(ለ) አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ከነጋዴው ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁ ፡ ሰዎች ፡ አቤቱታ ፡ ሲያቀርቡ ፤ ወይም ፡

(ሐ) ሕግ ፡ አስከባሪው ፡ ሲጠይቅ ፤ ወይም ፡

(መ) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ራሱ ፡ ሲፈቅድ ፡ ነው ።

BACK



**ቍ ፡ ፲፻፸፯ ። ስለ ፡ ቀዳሚ ፡ ምርመራ ።**

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ የታየው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የባለዕዳውን ፡ ሁኔታና ፡ ተግባር ፡ የሚመረምር ፡ አንድ ፡ ዳኛ ፡ መርጦ ፡ ማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ የተቀበለ ፡ ዳኛ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂ ፡ እንዲረዳው ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፫) በምርመራ ፡ የተገኘውን ፡ ሁሉ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ማስታወቅ ፡ ይገባዋል ።

**ቍ ፡ ፲፻፸፰ ። መክፈል ፡ የተቋረጠበትን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ መወሰን ።**

(፩) በመጀመሪያ ፡ ነገሩ ፡ በሚሰማበት ፡ ጊዜ ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፸፮ ፡ የተመለከተውን ፡ መግለጫ ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፤

(ሀ) የመክፈሉን ፡ መቋረጥ ፡ የተረዳው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መክፈል ፡ የተቋረጠበትን ፡ ቀን ፡ ይወስናል ።

(ለ) የመጠበቂያ ፡ ስምምነትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ውሳኔዎች ፡ ሳይነኩ ፤ መክሠሩን ፡ ይወስናል ።

(፪) መክፈሉ ፡ የተቋረጠበት ፡ ጊዜ ፡ ያልተወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በቍጥር ፡ ፲፻፸፭ ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ መክፈሉ ፡ የተቋረጠው ፡ የመክሠሩ ፡ ፍርድ ፡ በተሰጠበት ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይቈጠራል ።

**ቍ ፡ ፲፻፸፱ ። መክፈሉ ፡ የተቋረጠበትን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ማርዘም ።**

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፤

(ሀ) የከሠረው ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ጠባቂ ፡ ወይም ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ማናቸውም ፡ ወገን ፡ ሲጠይቅ ፤ ወይም ፡

(ለ) የሕግ ፡ አስከባሪው ፡ ሲጠይቅ ፤ ወይም ፡

(ሐ) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ራሱ ፡ ሲፈቅድ ፤

መክሠርን ፡ የሚያስታውቅ ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ በሚሰጥ ፡ ፍርድ ፤ ወይም ፡ በሚሰጡ ፡ ፍርዶች ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፸፯ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ የተወሰነውን ፡ የመክፈል ፡ መቋረጥን ፡ ጊዜ ፡ እልፍ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፪) ስለ ፡ ሆነም ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፹፯ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ የሚቀርበውን ፡ ማመልከቻ ፡ መቀበል ፡ አይቻልም ። እንዲሁም ፡ ይኸው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ መክፈል ፡ መቋረጥ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሊለወጥ ፡ አይቻልም ።

(፫) በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ስለ ፡ መክፈሉ ፡ መቋረጥ ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፤ መክሠርን ፡ ለማስታወቅ ፡ ከተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ በፊት ፤ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ የበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፱፻፷፱ ። ንግዱ ፡ ከተቋረጠ ፡ በኋላ ፡ ስለሚደረግ ፡ መክሠር ።**

(፩) ስሙ ፡ ከንግድ ፡ መዝገብ ፡ ከመሰረዙ ፡ አስቀድሞ ፡ ዕዳውን ፡ ከመክፈል ፡ ያቋረጠ ፡ ነጋዴ ፡ ሁሉ ፣ ስሙ ፡ ከንግድ ፡ መዝገብ ፡ በተሰረዘ ፡ በሚከተለው ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ መክሠሩ ፡ ሊነገር ፡ ይቻላል ።

(፪) ነጋዴው ፡ ያልተመዘገበ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፣ መክፈሉን ፡ ባቋረጠ ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፣ መክሠሩ ፡ ሊነገር ፡ ይቻላል ።

**ቍ ፡ ፱፻፸ ። ከሞት ፡ በኋላ ፡ ስለሚደረግ ፡ መክሠር ።**

(፩) አንድ ፡ ነጋዴ ፡ አከፋፈሉን ፡ በማቋረጥ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፣ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በሚከተለው ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ መክሠሩ ፡ ሊነገር ፡ ይቻላል ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱም ፣

(ሀ) በአንድ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፣ ወይም ፡

(ለ) በሕግ ፡ አስከባሪው ፡ አመልካችነት ፡ እንዲሁም ፣

(ሐ) በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ ነገሩን ፡ መመርመር ፡ ይችላል ።

(፫) ማንኛቸውም ፡ ወራሽ ፡ በውርስ ፡ የተላለፈለት ፡ ሀብት ፡ ከግል ፡ ሀብቱ ፡ ጋራ ፡ እንዳይደባለቅ ፡ ለማድረግ ፣ የሞተው ፡ ሰው ፡ መክሠር ፡ እንዲነገር ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፬) ነጋዴው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የሚፈረደው ፡ የመክሠር ፡ ፍርድ ፣ በፍትሐ፡ብሔር፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ አግኝተው ፡ የነበረውን ፡ የንብረት ፡ መለየት ፡ ጥቅም ፡ ውጤት ፡ ወዲያውኑ ፡ በደንብ ፡ ያስቀረዋል ።

**ቍ ፡ ፱፻፸፩ ። ስለ ፡ መክሠር ፡ ፍርድ ።**

መክሠርን ፡ ለማስታወቅ ፡ የሚሰጠው ፡ ፍርድ ፣ የኪሣራውን ፡ ሥራ ፡ መርማሪ ፡ አንድ ፡ ዳኛና ፣ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ የከሠረውን ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ መመረጥ ፡ ይኖርበታል ።

**ቍ ፡ ፱፻፸፪ ። ስለ ፡ ፍርድ ፡ አፈጻጸም ።**

ስለ ፡ መክሠር ፡ ረገድ ፡ የተሰጡ ፡ ፍርዶችና ፡ ትእዛዞች ፡ ለጊዜው ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፱፻፸፫ ። የፍርድ ፡ ማስታወቂያ ።**

(፩) በቍጥር ፡ ፱፻፷፯ ፣ ፱፻፷፱ ፡ እና ፡ ፱፻፸ ፡ መሠረት ፡ የተሰጠ ፡ ፍርድ ፣ ለዕዳ ፡ ከፋዩ ፣ ለከሠረ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ጠባቂና ፡ አቤቱታ ፡ ላቀረበው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ወይም ፡ ለወራሹ ፣ ቢዘገይ ፡ ፍርድ ፡ በተሰጠበት ፡ ቀን ፡ ማግስት ፡ ቅጂው ፡ ይተላለፋል ። ቅጂው ፡ የወገኖቹን ፡ ስም ፣ የፍርዱን ፡ ውሳኔና ፡ የተፈረደበትን ፡ ቀን ፡ የያዘ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(፪) በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፤ የፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ የፍርዱን ፡ ቅጂ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የውጭ ፡ በር ፡ ለጥፎ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ማቈየት ፡ አለበት ።

(፫) የፍርድ ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ የፍርዱን ፡ ቅጂ ፡ ለሕግ ፡ አስከባሪው ፡ ይልካል ።

(፬) የንግድ ፡ መዝገብ ፡ ኀላፊ ፡ የሆነው ፡ ሠራተኛ ፡ መዝገቡን ፡ ማስተካከል ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ የፍርዱን ፡ ቅጂ ፡ ሦስት ፡ ግልባጭ ፡ ይልክለታል ። እንደዚሁ ፡ ያለው ፡ መስተካከል ፡ በአገሩ ፡ ክፍል ፡ የንግድ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፤ ለጠቅላይ ፡ መዝገብ ፡ ክፍል ፡ መታወቅና ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ አንደኛ ፡ መጽሐፍ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ በንግድ ፡ ኦፊሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ መውጣት ፡ አለበት ።

(፭) ከዚህም ፡ በቀር ፡ የመክፈሉ ፡ መቋረጥ ፡ በተረጋገጠበት ፡ ቦታ ፡ ሕጋዊ ፡ ማስታወቂያዎችን ፡ ለመቀበል ፡ በተፈቀደለት ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ ቅጂው ፡ በማስታወቂያ ፡ ይወጣል ።

(፮) እንዲሁም ፡ ማስታወቂያው ፡ የዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ የንግድ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በሚገኙበት ፡ ቦታ ፡ መደረግ ፡ አለበት ።

ቍ ፣ ፱፻፹፬ ። ፍርድን ፡ ስለ ፡ መቃወም ።

(፩) በመክሠር ፡ ረገድ ፡ በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ መቃወሚያ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚቻለው ፡ ከተፈረደበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ነው ። በሚለጠፉ ፤ ማስታወቂያዎችን ፡ ለመቀበል ፡ በተፈቀደላቸው ፡ ጋዜጣዎች ፡ ወይም ፡ በንግድ ፡ ኦፊሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ ላለባቸው ፡ ፍርዶች ፡ ግን ፤ ይህ ፡ ጊዜ ፡ መቈጠር ፡ የሚጀመረው ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሥርዐት ፡ በመጨረሻው ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

(፪) የመክሠር ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈረድ ፡ የጠየቀው ፡ ሰው ፤ በተፈረደው ፡ በመክሠር ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ለማቅረብ ፡ አይችልም ።

(፫) ባለዕዳው ፡ የሚያቀርበው ፡ መቃወሚያ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ፍርድን ፡ የማገድ ፡ ውጤት ፡ አይኖረውም ።

ቍ ፣ ፱፻፹፭ ። በመቃወሚያው ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተሰጠ ፡ ፍርድ ።

(፩) መቃወሚያውን ፡ ውድቅ ፡ የሚያደርገውን ፡ ፍርድ ፡ ተቃዋሚው ፡ እንዲያውቀው ፡ ይደረጋል ።

(፪) የመክሠር ፡ ማስታወቂያን ፡ የሚሽረው ፡ ፍርድ ፤ የከሠረው ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡

ጠባቂ ፤ የመክሠርን ፡ ፍርድ ፡ የጠየቀው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፤ መቃወሚያ ፡ አላቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆን ፤ ባለዕዳው ፡ እንዲያውቁት ፡ ይደረጋል ። በዚህም ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ በቍጥር ፡ ፱፻፹፫ ፡ የተደነገጉት ፡ ሥርዐቶች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፱፻፹፮ ። ስለ ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ።

(፩) መክሠርን ፡ ለማስታወቅ ፡ በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፤ ፍርዱን ፡ እንዲያውቀው ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ነው ።

(፪) ይግባኙም ፡ በአጭር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ይፈረዳል ። ፍርዱም ፡ ወዲያውኑ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።

ቍ ፡ ፱፻፹፯ ። መቃወሚያ ፡ ወይም ፡ ይግባኝ ፡ ሊቀርብበት ፡ ስለማይቻል ፡ ፍርድ ።

(፩) መቃወሚያ ፡ ወይም ፡ ይግባኝ ፡ ሊቀርብባቸው ፡ የማይቻሉ ፡ ፍርዶች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤

(ሀ) የመክሠርን ፡ ሥራ ፡ መርማሪ ፡ ዳኛ ፡ ወይም ፡ ምትኩን ፡ ለመሾም ፤ ንብረት ፡ ጠባቂዎችን ፡ ለመሾም ፡ ወይም ፡ ለመሻር ፡ የተሰጠ ፡ ፍርድ ፤

(ለ) ነጻ ፡ ለመውጣት ፡ በሚደረጉ ፡ ጥያቄዎችና ፡ ለዕዳ ፡ ከፋዩና ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ ርዳታ ፡ ለማግኘት ፡ በሚደረጉ ፡ ጥያቄዎች ፡ ላይ ፡ የተሰጠ ፡ ፍርድ ፤

(ሐ) በንብረቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ ሸቀጦች ፡ እንዲሸጡ ፡ የሚፈቅድ ፡ ፍርድ ።

(መ) መርማሪ ፡ የሆነው ፡ ዳኛ ፤ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፤ በሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ በቀረበ ፡ አቤቱታ ፡ የተሰጠ ፡ ፍርድ ፤

(ሠ) የንግዱ ፡ ሥራ ፡ እንዲቀጥል ፡ የሚፈቅድ ፡ ፍርድ ፤

(፪) መርማሪ ፡ የሆነው ፡ ዳኛ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ (መ) በተመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ዳኝነት ፡ ውስጥ ፡ አይገባም ።

ቍ ፡ ፱፻፹፰ ። መክሠርን ፡ ለማስታወቅ ፤ የተሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ስለ ፡ ማንሣት ።

(፩) ይህ ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀንና ፡ በተቃዋሚነት ፡ ወይም ፡ በይግባኝ ፡ ላይ ፡ ውሳኔ ፡ በሚደረግበት ፡ ቀን ፡ መካከል ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በመክፈል ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ስምምነት ፡ በማድረግ ፡ የከሠረው ፡ ሰው ፡ መክፈልን ፡ ከማቋረጥ ፡ ሁኔታ ፡ የወጣ ፡ እንደ ፡ ሆን ፤ መክሠሩን ፡ ለመግለጽ ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ መነሣት ፡ አለበት ።

(፪) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ የመክሠሩን ፡ ሥራ ፡ የሚያስፈጽሙት ፡ ሰዎች ፡ የፈጸሟቸው ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑ ፡ ሥራዎች ፡ ያስገኙዋቸው ፡ ውጤቶች ፡ እንዳሉ ፡ ይቈያሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## የመክሠርን ፡ ሥራ ፡ የሚያስፈጽሙ ፡ ሰዎች ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

**ቍ ፡ ፲፻፳፱ ። ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣን ።**

የመክሠርን ፡ ፍርድ ፡ የፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጠቅላላውን ፡ የመክሠር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ይቈጣጠራል ። ከመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ሥልጣን ፡ በላይ ፡ በሆኑት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ። መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ በሚሰጣቸው ፡ ትእዛዞች ፡ ሁሉ ፡ ይግባኙን ፡ ያያል ።

**ቍ ፡ ፲፻፴ ። ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣን ።**

በፍርድ ፡ ቤት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፤ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሚታዩት ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ ከሚመለከቱት ፡ ክሶች ፡ በቀር ፤ የመክሠርን ፡ ፍርድ ፡ የፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመክሠር ፡ ጕዳይ ፡ የተነሣ ፡ የሚቀርቡትን ፡ ክሶች ፡ ሁሉ ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

### ክፍል ፡ ፪ ።

### የመክሠር ፡ መርማሪ ፡ ዳኛ ።

**ቍ ፡ ፲፻፴፩ ። ስለ ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ሥልጣን ።**

(፩) መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ የመክሠር ፡ ሥራዎችን ፡ ለመጠበቅና ፡ ለማፋጠን ፡ በተለይ ፡ የተሾመ ፡ ነው ።

(፪) ከመክሠር ፡ አሠራር ፡ በሚነሡት ፡ በዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ውስጥ ፡ በሆኑት ፡ ክርክሮች ፡ ሁሉ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ መግለጫ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ። የዚሁ ፡ መግለጫ፡መኖር፡በፍርድ፡ቤቱ፡ውሳኔዎች፡ውስጥ፡መጠቀስ ፡ አለበት ።

(፫) መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ተገቢ ፡ የሆኑትን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በመጠየቅ ፡ ወይም ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፤ በመክሠር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ንብረት ፡ ለመጠበቅ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ይፈጽማል ።

(፬) በሕግ ፡ የታዘዘ ፡ ሲሆን ፤ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ የገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ኮሚቴ ፡ ስብሰባ ፡ እንዲደረግ ፡ ጥሪ ፡ ያደርጋል ።

(፭) መርማሪው፡ ዳኛ፡ ራሱ ፡ እንዲሾም ፡ በሕግ ፡ ካልታዘዘ ፡ በቀር ፡ ርዳታቸው ፡ ለመክሠሩ ፡ አሠራር ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ሰዎች ፡ የከሠረው ፡ ሰው ፡ ንብ

ረት ፡ ጠባቂ ፡ እንዲሾማቸው ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ፡ ሊፈቅድለት ፡ ይችላል።

(፪) በከሳሽነት ፡ ወይም ፡ በተከሳሽነት ፡ የከሠረው ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ጠባቂ ፡ በፍ ርድ ፡ ቤት ፡ እንዲነጋገር ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ፡ ይፈቅድለታል ።

ቍ ፡ ፱፻፺፬ ። ስለ ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ትእዛዞች ።

(፩) የመርማሪው፡ዳኛ፡ትእዛዞች፡ ወዲያውኑ፡ በፍርድ፡ መዝገብ፡ ቤት ፡ ይቀመጣሉ ። መቀመጣቸውም ፡ በረከማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ ለባለጉዳዮቹ ፡ ይነገራቸዋል ።

(፪) መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ በሰጣቸው ፡ ትእዛዞች፡ ላይ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ መቃወሚያቸ ውን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማቅረብ ፡ ይችላሉ ። የረከማንዴው ፡ ደብዳቤ ፡ ከተላከ በት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በዐሥር ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ መቃወሚያው ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቀርባል ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ በመጀመሪያው ፡ ቀጠሮ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፱፻፺፭ ። መርማሪውን ፡ ዳኛ ፡ ስለ ፡ መተካት ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በራሱ ፡ አስተያየት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ መርማሪውን ፡ ዳኛ ፡ ከአባሎቹ ፡ ባንዱ ፡ መተካት ፡ ይችላል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## የከሠረው ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎች ።

ቍ ፡ ፱፻፺፮ ። ስለ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ መሾም ።

(፩) ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ከሚኖሩ ፡ ባንድ ፡ ሊስት ፡ ላይ ፡ ከተ ጻፉ ፡ ከተከበሩና ፡ ከታወቁ ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ ይመረጣሉ ። ይኸንንም ፡ ሊስት ፡ በየዓመቱ ፡ መጀመሪያ ፡ የንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ያዘጋጀዋል ።

(፪) የሚሾሙትም ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ልክ ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ ሦስት ፡ ነው ።

(፫) ብዙ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ የተሾሙ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ባንድነት ፡ ይሠራሉ ። መርማሪው ፡ ዳኛ፡ ግን፡ አስፈላጊ፡ መሆኑን ፡ እያየ ፡ ከመካከላቸው ፡ ለአንዱ ፡ ወይም ፡ ለብዙዎቹ ፡ ለብቻ ፡ የመሥራት ፡ መብትን ፡ መስጠት ፡ ይችላል ። እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ሥልጣን፡ የተቀበሉ ፡ ጠባቂዎች ፡ ብቻ ፡ አላፊ ዎች ፡ ናቸው ።

(፬) ለንብረት ፡ ጠባቂነት ፡ ለመሾም ፡ የማይችሉ ፡ ሰዎች ፤

(ሀ) ከስሮ ፡ ተብሎ ፡ ተፈርዶበት ፡ የነበረ ፡ ሰው ፤ ወይም ፡

(ለ) የሕዝባዊ ፡ መብቱን ፤ ለጊዜውም ፡ ቢሆን ፤ የሚከለክል ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፤ ወይም ፡

(ሐ) የባለዕዳው ፤ እስከ ፡ አራተኛ ፡ ደረጃ ፡ ድረስ ፤ የሥጋ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዘመድ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፤ ወይም ፡

(መ) ከኪሣራው ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ናቸው ።

(፭) ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ የባለዕዳውን ፡ ንብረት ፡ ለመግዛት ፡ አይችሉም ።

ቍ ፡ ፲፻፶፭ ። ስለ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ሥልጣን ።

(፩) ንብረት፡ ጠባቂው፡ የከሠረውን፡ ሰው፡ ንብረት ፡ በመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ጥበቃ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ ማስተዳደር ፡ አለበት ። ከሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጋራ ፡ ስላለው ፡ ጕዳይ ፡ በኅብረት ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ እንደራሴ ፡ ነው ።

(፪) ሥልጣኖቹ ፡ የማይተላለፉ ፡ ናቸው ፤ የሆነ ፡ ሆኖ ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ከፈቀደለት ፡ ለአንዳንድ ፡ ሥራ ፡ በተለየ ፡ ሥልጣኑን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ለማሳለፍ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፻፶፮ ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥ ።

(፩) በመርማሪው ፡ ዳኛ፡ ትእዛዝ ፡ የሚወሰኑት ፡ የዳኝነትና ፡ የአስተዳደር ፡ ወጪዎች ፡ ሁሉ ፡ ከተቀነሱ፡ በኋላ፤ ንብረት ፡ ጠባቂው ፡ የሚቀበላቸው ፡ ገንዘቦች ፡ ሁሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት፡ ባንክ፡ በከሠረው ፡ ንብረት ፡ ስም ፡ በሚከፈተው፡ ልዩ፡ ሒሳብ፡ ውስጥ ፡ ወዲያውኑ፡ ተቀማጭ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ። ይኸውም ፡ ገንዘብ ፤ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ፈርሞ ፡ በሚሰጠው ፡ የመክፈያ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለመውጣት ፡ አይችልም ።

(፪) ያሉም፡ እንደ፡ ሆነ፤ ለዚሁ ፡ ነገር ፡ በፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ በወንጀል ፡ ሕግ ፡ የተደነገጉት፡ ቅጣቶች፡ እንደ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩፡ የተመለከቱትን ፡ ትእዛዞች ፡ ያልፈጸመ ፡ የንብረት ፡ ጠባቂ ፡ መሻር ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ፲፻፶፯ ። ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ በሠሩት ፡ ሥራዎች ፡ አቤቱታን ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

ንብረት ፡ ጠባቂዎች፡ በሠሩት፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የከሠረው ፡ ሰውና ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ባለጕዳይ ፡ ለመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ። ዳኛውም ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ውሳኔ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፲፻፶፰ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎችን ፡ ስለ ፡ መሻር ።

(፩) መርማሪው፡ ዳኛ፡ በከሠረው፡ ሰው፡ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ኰሚቴ ፡ ስብሰባ ፡ በቀረቡለት ፡ አቤቱታዎች ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ አንዱ፡ ወይም ፡ ብዙዎቹ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ እንዲሻሩ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሐሳብ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

(፪) መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ለቀረቡለት ፡ አቤቱታዎች ፡ በአምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ውሳኔ ፡ ያልሰጠ፡ እንደ፡ ሆነ፤ አቤት፡ ባዮቹ፡ አቤቱታቸውን፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

(፫) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመርማሪውን፡ ዳኛ፡ መግለጫ ፤ የንብረት ፡ ጠባቂዎቹን ፡ ማስረጃና ፡ የሕግ ፡ አስከባሪውን ፡ ሐሳብ፡ በዝግ ፡ ችሎት ፡ ይሰማል ። ፍርዱ ፡ ግን፡ በአደባባይ ፡ ይነገራል ።

**ቍ ፡ ፱፻፺፱ ። ንብረት ፡ ጠባቂዎችን ፡ ስለ ፡ መተካት ።**

እንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ለመጨመር ፡ ወይም ፡ ለመተካት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስታውቆ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም፡ አስፈላጊውን፡ ይሾማል ።

**ቍ ፡ ፲፻ ። ስለ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ አላፊነት ።**

(፩) ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ሥራቸውን ፡ በሚያከናውኑበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ መንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ ይቈጠራሉ ። የተሰጣቸውን ፡ ተግባር ፡ በትጋት ፡ መፈጸምና ፡ ክርክርም ፡ የተነሣ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ የፈጸሙ ፡ መሆናቸውን ፡ ማስረዳት ፡ አለባቸው ።

(፪) የፈጸሙትን ፡ የአስተዳደር ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በየቀኑ ፡ የሚመዘግቡበት ፤ አስቀድሞ ፡ በመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ የተፈረመ፤ እንድ ፡ መዝገብ ፡ መያዝ ፡ አለባቸው ።

(፫) የኪሣራው ፡ ሥራ ፡ በሚከናወንበት ፡ ጊዜ፡ በተሻረው ፡ ጠባቂ ፡ ላይ ፡ የሚቀርበውን ፡ የአላፊነት ፡ ክስ ፡ ሁሉ ፡ አዲሱ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂ ፤ አስቀድሞ ፡ ከመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ፈቃድ ፡ ተቀብሎ ፡ ያከናውናል ።

(፬) የኪሣራው፡ ሥራ፡ በሚከናወንበትም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን፤ ሥራውን፡ የሚተው ፡ ንብረት ፡ ጠባቂ ፡ በቍጥር ፡ ፲፻ ፡ ፫ ፡ እንደ፡ ተመለከተው ፡ ስለሥራው ፡ አመራር ፡ መግለጫ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፲፻፩ ። የንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ የሥራ ፡ ዋጋ ።**

(፩) የንብረት ፡ ጠባቂዎችን ፡ ወጪዎችና ፡ የሥራ ፡ ዋጋዎች ፡ የሚወስን ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ነው ።

(፪) የሥራ ፡ ዋጋዎች ፤ በቍጥር ፡ ፲፻ ፡ ፪ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ የሥራ ፡ ማስተዳደሪያው ፡ መግለጫ ፡ ካልተሰጠ ፡ በቀር ፡ አይከፈሉም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ከተገኘ ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ለንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ከሚገባቸው ፡ ገንዘብ ፡ አስቀድመው ፡ እንዲከፈላቸው ፡ ለመፍቀድ ፡ ይችላል ።

(፫) የከሠረው ፡ ሰውና ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ ስለተወሰነው ፡ የሥራ ፡ ዋጋ፡ በስምንት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ መቃወሚያቸውን ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ በዝግ ፡ ችሎት ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

(፬) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ከተመለከቱት ፡ በቀር ፡ ለንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ሌላ ፡ ገንዘብ፡ ሊከፈላቸው ፡ አይቻልም። ያሉም ፡ እንደ፡ ሆነ፤ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቅጣቶች ፡ እንደ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ ይህን፡ ክልከላ ፡ በመጣስ ፡ የተከፈሉ ፡ ገንዘቦች ፡ ሁሉ ፡ ተመላሽ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

## የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ኮሚቴ ።

**ቍ ፡ ፲፻፪ ። ኮሚቴውን ፡ ስለ ፡ ማቋቋም ።**

(፩) በቍጥር፡ ፲፻፵፬ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹን፡ ሁኔታ ፡ የሚገልጽ ፡ ትእዛዝ ፡ በፍርድ፡ መዝገብ ፡ ከተቀመጠበት፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በሚከተሉት ፡ ዐሥር ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ የባለገንዘቦች ፡ ኮሚቴ ፡ መቋቋም ፡ አለበት ።

(፪) መርማሪው፡ ዳኛ ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ የገመተ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ኮሚቴው ፡ ለጊዜው ፤ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፤ እንዲቋቋም ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።

(፫) ከገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ አምስት ፡ አባሎች ፡ መርጦ ፡ መርማሪው፡ዳኛ፡ኮሚቴውን፡ያቋቁማል፤የኮሚቴውንም፡ፕሬዚዳንት፡ ይመርጣል ።

(፬) ከኮሚቴው ፡ ውስጥ ፡ እንዲተኩ ፡ የጠየቁትን ፡ አባሎች ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ በሌሎች ፡ አሎባች፡ ሊተካቸው ፡ ይችላል ። ዳኛው ፡ ባቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ መሠረት ፡ በሚሰጥ ፡ የፍርድ፡ቤት ፡ ውሳኔ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከሥራቸው ፡ ሊሻሩ ፡ አይችሉም ።

(፭) ማናቸውም ፡ ከባለዕዳው ፡ ጋራ ፡ እስከ ፡ አራት ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ ጭምር ፡ የሥጋ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ኮሚቴ ፡ አባል ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

**ቍ ፡ ፲፻፫ ። ስለ ፡ ኮሚቴው ፡ ሥራ ።**

(፩) ኮሚቴው ፡ ሐሳቡን ፡ እንዲሰጥ ፡ ሕጉ ፡ የሚያስገድድበት ፡ ሁኔታ ፡ ሳይነካ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወይም ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ የገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ኮሚቴው ፡ ሐሳቡን ፡ እንዲሰጥ ፡ ሊጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) የኮሚቴው ፡ ሐሳብ ፡ እንዲታወቅ ፡ በተጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ስብሰባ ፡ እንዲደረግ ፡ ለፕሬዚዳንቱ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ በታየው ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ፤ ፕሬዚዳንቱ፡ ኮሚቴውን ፡ ይሰበስባል ።

(፫) የኮሚቴው ፡ ውሳኔዎች ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ይሰጣሉ ።

(፬) ኮሚቴው ፡ ባለዕዳው ፡ ያቀረበውን ፡ ሒሳብና ፡ የሁኔታውን ፡ መግለጫ ፡ መመርመርና ፡ የንብረት ፡ ጠባቂዎቹን ፡ ሥራ ፡ በተለይ ፡ መጠባበቅ ፡ አለበት።

(፭) ኮሚቴው ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ የመክሠሩን ፡ አሠራር ፡ ሁኔታ ፤ ገቢ ፡ የሆኑትንና ፡ የተከፈሉትን ፡ ገንዘቦች ፡ ሒሳብ ፡ መግለጫ ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው።ንብረት ፡ ጠባቂዎቹም ፡ ለሚጀምሩት ፡ ወይም ፡ ለሚቀጥሉት ፡ ክሶች ፡ የኮሚቴውን ፡ ሐሳብ ፡ መቀበል ፡ አለባቸው ።

(፮) የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ኮሚቴ ፡ አባሎች ፡ ለሚያደርጉት ፡ ከባድ ፡ ጥፋት ፡ ብቻ ፡ አላፊዎች ፡ ናቸው ።

(፯) ስለ ፡ ሥራቸው ፡ ዋጋ ፡ አይቀበሉም ፤ ነገር፡ግን፡በመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ፊርማ ፡ ያደረጓቸው ፡ ወጪዎች ፡ እንዲመለሱላቸው ፡ መብት ፡ አላቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## የአጠባበቅ ፡ ሥራዎች ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### የአጠባበቅ ፡ ውሳኔዎች ።

**ቍ ፡ ሺ፱ ። የባለዕዳውን ፡ መዝገቦች ፡ ስለ ፡ መዝጋት ።**

(፩) አስፈላጊም ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ በቍጥር ፡ ሺ፲፩ ፡ የተነገረው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፤ ባለዕዳው ፡ ባለበት ፤ መዝገቦቹን ፡ ለመዝጋትና ፡ ሒሳቡን ፡ ለማቆም ፡ ባለዕዳውን ፡ ይጠሩታል ።

(፪) በዚሁ ፡ ጥሪ ፡ ባለዕዳው ፡ ያልቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በአርባ ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ እንዲቀርብና ፡ መዝገቦችንም ፡ እንዲያቀርብ ፡ ደረሰኝ ፡ ባለው ፡ ሬኮማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ ይጠራል ።

(፫) ለመቅረብ ፡ የማይችልበትን ፡ ምክንያቶች ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፤ መርማሪውም ፡ ዳኛ ፡ በቂ ፡ መሆናቸውን ፡ የተረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባለዕዳው ፡ ስለእርሱ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ለመወከል ፡ ይችላል ።

(፬) ራሱ ፡ ለመቅረብ ፡ ወይም ፡ ወኪል ፡ ለመላክ ፡ እንቢ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የሸሸ ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የማይገኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አ፤ ፈላጊውን ፡ ነገር ፡ እንዲያደርግ ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ለሕግ ፡ አስከባሪው ፡ ያስታውቃል ።

**ቍ ፡ ሺ፲ ። የባለዕዳውን ፡ መብቶች ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ።**

(፩) ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ሥራቸውን ፡ እንደ ፡ ጀመሩ፤ ለባለዕዳው ፡ በራሱ ፡ ባለዕዳዎች ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መብቶች ፡ ለመጠበቅ ፡ አስፈላጊውን ፡ ተግባር ፡ ማድረግ ፡ አለባቸው ።

(፪) ባለዕዳው ፡ ያላስመዘገበውን ፤ በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የመያዣ ፡ መብት ፤ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ማስመዝገብ ፡ አለባቸው ። ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ መሆናቸውን ፡ አስረድተው ፤ የመያዣውን ፡ መብት ፡ የሚያስመዘግቡት ፡ በንብረቱ ፡ ስም ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፲፩ ። የባለዕዳው ፡ በሆኑት ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ የመያዣ ፡ መብትን ፡ ስለ ፡ ማስመዝገብ ።**

(፩) ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ የባለዕዳው ፡ በሆኑትና ፡ ወደፊትም ፡ በሚያገኛቸው ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ በኅብረቱ ፡ ስም ፡ የመያዣ ፡ መብትን ፡ ማስመዝገብ ፡ አለባቸው ።

(፪) በስምምነት ፡ የመጨረሻውን ፡ ድርሻ ፡ ከከፈለ ፡ በኋላ ፡ ወይም ፡ ስምምነት፡

ያልተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሒሳቡ ፡ ማጣራት ፡ ሥራ ፡ በፍጹም ፡ ከተዘጋ ፡ በኋላ ፡ ባለዕዳው ፡ በሚያገኛቸው ፡ በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ የመያዣ ፡ መብቶች ፡ አይመዘገቡም ።

**ቍ ፡ ሺ፯ ። በንግዱ ፡ ላይ ፡ የመያዣ ፡ መብትን ፡ ስለ ፡ ማስመዝገብ ።**

(፩) በዚሁ ፡ ሕግ ፡ በሁለተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ቍጥር ፡ ፻፷፪ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) (ለ) በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑትን ፡ የመያዣ ፡ መብቶች ፡ በባለዕዳው ፡ ንግድ ፡ ወይም ፡ ንግዶች ፡ ላይ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ማስመዝገብ ፡ አለባቸው ።

(፪) መመዝገብ ፡ የሚገባው ፤

(ሀ) የባለዕዳው ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፤

(ለ) ባለዕዳው ፡ የከሠረ ፡ መሆኑ ፡ የተወሰነበት ፡ ፍርድ ፡ የተሰጠበት ፡ ቀን ፤

(ሐ) ባለዕዳው ፡ የከሠረ ፡ መሆኑን ፡ የወሰነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስም ፤

(መ) የንግዱ ፡ ዐይነትና ፡ አድራሻ ፤

(ሠ) መያዣ ፡ የተያዘባቸው ፡ የንግዱ ፡ ክፍሎች ፤

(ረ) ያለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መያዣ ፡ የሆነው ፡ ቅርንጫፍና ፡ ውክልና ፡ ነው ።

(፫) በዚሁ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ መያዣ ፡ ስለሚደረግ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ አንደኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ከቍጥር ፡ ፻፷፱ ፡ እስከ ፡ ፻፺፫ ፡ ያሉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፰ ። ለመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ የሚደረግ ፡ መግለጫ ።**

(፩) ሥራቸውን ፡ በጀመሩ ፡ በወሩ ፡ ውስጥ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ የባለዳዕውን ፡ ጉዳይ ፡ ሁኔታና ፡ ለዚሁም ፡ ሁኔታ ፡ መነሻ ፡ የሆኑትን ፡ ምክንያቶች ፡ ጭምር ፡ የሚያስረዳ ፡ መግለጫ ፡ ለመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ይልካሉ ።

(፪) መርማሪውም ፡ ዳኛ ፡ ሐሳቡን ፡ ጨምሮ ፡ ይህን ፡ መግለጫ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለሕግ ፡ አስከባሪው ፡ ያስተላልፋል ። መግለጫውም ፡ በታዘዘው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያልተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የዘገየበትን ፡ ምክንያቶች ፡ አስረድቶ ፡ ለሕግ ፡ አስከባሪው ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ማሸግ ።

**ቍ ፡ ሺ፱ ። እሽግን ፡ ስለ ፡ ማድረግ ።**

(፩) የባለዕዳውን ፡ መክሠር ፡ የፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መክሠሩን ፡ ለማስታወቅ ፡ በሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ እሽግ ፡ እንዲደረግ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ። እሽጉም ፡ የሚደረገው ፡ በማጋዜኖቹ ፤ በመደርደሪያዎቹ ፤ በሣጥኖቹ ፤ በቦርሳዎቹ ፤ በመዝገ

BACK



ቦቹ ፤ በሰነዶቹ ፤ በወረቀቶቹና ፡ የባለዕዳው ፡ በሆኑት ፡ የቤት ፡ ዕቃዎችና ፡ የሚ ንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ነው ።

(፪) ነገር ፡ ግን ፡ ባለዕዳው ፡ የጠፋ ፡ ወይም ፡ ገንዘቡን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከ ፊል ፡ ያሸሸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በፈቃዳቸው ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ አመልካችነት ፤ የመክሠር ፡ ፍርድ ፡ ከመስ ጠቱ ፡ በፊት ፡ በንኡስ ፡ ቊ ፡ (፩) በተዘረዘሩት ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ እሽግን ፡ ለማ ድረግ ፡ ይችላሉ ።

ቊ ፡ ሺ፲ ። ሊታሸግባቸው ፡ ስለማይቻሉ ፡ ዕቃዎች ።

(፩) በንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ጠያቂነት ፤ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተዘ ረዘሩት ፡ ዕቃዎች ፡ እሽግ ፡ እንዳይደረግባቸው ፤ ተደርጎባቸውም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንዲነሣላቸው ፤ ለመፍቀድ ፡ ይችላል ።

(ሀ) በሚሰጠው ፡ ዝርዝር ፡ ላይ ፡ በሚገኙት ፡ ለባለዕዳውና ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆኑት ፡ ልብሶችና ፡ ዕቃዎች ፤

(ለ) በሚበላሹ ፡ ወይም ፡ በሚያልቁ ፡ ዕቃዎች ፤

(ሐ) ሥራው ፡ እንዲቀጥል ፡ የተፈቀደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለንግዱ ፡ ወይም ፡ ለኢ ንዱስትሪው ፡ መካሄድ ፡ በሚያገለግሉት ፡ ዕቃዎች ።

(፪) የዕቃዎቹን ፡ ፕሮሴቬርባል ፡ የሚፈርመው ፡ ተገቢው ፡ ነለሥልጣን ፡ ባለበት ፤ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ በንኡስ ፡ ቊ ፡ (፩) የተመለከቱትን ፡ ዕቃዎች ፡ ዝርዝር ፡ ከነዋጋቸው ፡ ያሰናዳሉ ።

ቊ ፡ ሺ፲፩ ። ከእሽግ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚወጡ ፡ ዕቃዎች ።

(፩) በቊ ፡ ፩ሺ፱ ፡ ንኡስ ፡ ቊ ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ የሒሳብ ፡ ሰነዶችና ፡ መዝገቦች ፡ ታሽገው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተገቢው ፡ ባለሥልጣን ፡ እሽጉን ፡ አንሥቶ ፡ ሰነዶቹንና ፡ መዝገቦቹን ፡ ከዘጋቸው ፡ በኋላ ፡ ለንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ማስረከብ ፡ አለበት ። ይኸውም ፡ ባለሥልጣን ፡ መዝገቦቹና ፡ ሰነዶቹ ፡ የሚገኙበትን ፡ ሁኔታ ፡ በፕሮሴ ቬርባል ፡ ውስጥ ፡ በአጭሩ ፡ ያመለክታል ።

(፪) የመክፈያ ፡ ጊዜያቸው ፡ አጭር ፡ የሆኑትን ፤ እሽታ ፡ ማግኘት ፡ ወይም ፡ የአጠ ባበቅ ፡ ተግባር ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፤ በቦርሳው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ የንግድ ፡ ወረቀቶች ፡ ተገቢው ፡ ባለሥልጣን ፡ ከእሽጉ ፡ ውጭ ፡ አድርጓቸው ፡ ዝርዝራቸውን ፡ ከጻፈ ፡ በኋላ ፡ ገንዘቡ ፡ ገቢ ፡ እንዲደረግ ፡ ወይም ፡ አስፈላጊው ፡ እንዲፈጸም ፡ ለንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ይሰጣቸዋል ። የወረቀቶቹንም ፡ ሁኔታ ፡ የሚያሳይ ፡ መግለጫ ፡ ለመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ይተላለፋል ።

ቊ ፡ ሺ፲፪ ። ለከሠረው ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ተላከው ፡ ደብዳቤ ።

ለከሠረው ፡ ሰው ፡ የሚላኩት ፡ ደብዳቤዎች ፡ ለንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ይሰጣሉ ። የከሠረው ፡ ሰው ፡ ደብዳቤው ፡ ሲከፈት ፡ ለማየት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፲፫ ። እሽግን ፡ ስለ ፡ ማንሣት ።

ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ በአምስት፡ ቀን፡ ውስጥ ፡ የዕቃዎቹን ፡ ዝርዝር ፡ ለመመዝገብ ፡ እሽጉ ፡ እንዲነሣ ፡ ይጠይቃሉ ።

ክፍል ፡ ፫ ።

የዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ።

ቍ ፡ ሺ፲፬ ። የሒሳቡን፡ ሚዛን ፡ ስለ ፡ ማሰናዳትና ፡ ስለ ፡ መስጠት ።

የሒሳቡን፡ ሚዛን፡ ባለዕዳው፡ያልሰጠ፡ እንደ፡ሆነ፤ በሚገኙት፡ መዝገቦች፤ የሒብ፡ ሰነዶች ፤ ወረቀቶችና፡ መረጃዎች ፡ መሠረት ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሒሳቡን ፡ ሚዛን ፡ አሰናድተው ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ይሰጣሉ ።

ቍ ፡ ሺ፲፭ ። የባለዕዳውን ፡ ንብረቶች ፡ በዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ስለ ፡ ማስገባት ።

(፩) ባለዕዳው ፡ ባለበት ፡ ወይም ፡ ደረሰኝ ፡ ባለው ፡ ሬኮማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ በሚገባ ፡ ተጠርቶ ፡ ንብረቶቹ ፡ በዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ።

(፪) በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ በቍጥር ፡ ሺ፲ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) መሠረት ፡ እሽግ ፡ ሳይደረግባቸው ፡ ወይም ፡ ከእሽግ፡ ውጭ፡ ሆነው፡ በዝርዝር፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የገቡትና ፡ የተገመቱት ፡ ዕቃዎች ፡ እንደገና ፡ ይመረመራሉ ።

(፫) ይኸው ፡ የዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ በሁለት ፡ ዋና ፡ ይሠራል ። ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ ወዲያውኑ ፡ በፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ይቀመጣል ። ሁለተኛውም ፡ በንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ እጅ ፡ ይቀራል ።

(፬) ስለ ፡ ዕቃው ፡ ዝርዝር፡መዝገብ ፡ አጻጻፍና ፡ ስለ ፡ ዕቃዎቹ ፡ ግምት ፤ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፤ በመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ፈቃድ ፤ የሚገቡ ፡ መስለው ፡ የሚገምቷቸውን ፡ ሰዎች ፡ ርዳታ ፡ መጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ሺ፲፮ ፡ ከሞት ፡ በኋላ ፡ ስለሚደርስ ፡ መክሠር ፡ የዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ አሠራር ።

መክሠሩ ፡ ከሞት ፡ በኋላ ፡ የተገለጸና ፡ የዕቃውም ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ያልተሠራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የዕቃው ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ከመዘጋጀቱ ፡ በፊት ፡ ባለዕዳው ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ የዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ የሚዘጋጀው ፡ ወይም ፡ መዘጋጀቱን ፡ የሚቀጥለው ፡ ወራሾች ፡ ባሉበት ፡ ወይም ፡ በሚገባ ፡ ጥሪ ፡ ከተደረገላቸው ፡ በኋላ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፲፯ ፡ የሕግ ፡ አስከባሪው ፡ መብቶች ።

ሕግ ፡ አስከባሪው ፡ የዕቃው ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ሲደራጅ ፡ ለማየትና ፡ ለመገኘት ፡ ይችላል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ መክሠሩን ፡ የሚመለ

ከቱ ፡ ውሎችን ፤ ሰነዶችን ፤ መዝገቦችን ፡ ወይም ፡ ወረቀቶችን ፡ ሁሉ ፡ ለማየት ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ፲፻፴፰ ፡ የባለዕዳውን ፡ ንብረቶች ፡ ለንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ስለ ፡ ማስረከብ ።

የዕቃው ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ከተሰናዳ ፡ በኋላ ፡ የባለዕዳው ፡ ሸቀጦች ፤ ገንዘቦች፤ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ ሰነዶች ፤ መዝገቦች ፤ ወረቀቶችና ፡ ሰነዶች ፤ የሚንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችና ፡ ዕቃዎች ፡ ለንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ይሰጣሉ ። እነርሱም ፡ መረከባቸውን ፡ በዚሁ ፡ የዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ሥር ፡ ያመለክታሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

## መክሠርን ፡ የሚያስታውቅ ፡ ፍርድ ፡ የሚያስከትላቸው ፡ ውጤቶች ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### በባለዕዳው ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ውጤቶች ።

ቍ ፡ ፲፻፴፱ ። የከሠረውን ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ማሰር ።

የከሠረው ፡ ሰው ፤ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ሳይፈቅድለት ፡ በማናቸውም፡ ምክንያት፡ ከመኖሪያ ፡ ቦታው ፡ ለመራቅ ፡ አይችልም ። ይህን ፡ ቢተላለፍ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፹፫ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የከሠረውን ፡ ሰው ፡ ሊያስረው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፻፵ ። ለከሠረው ፡ ሰውና ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ ስለሚደረግ ፡ ርዳታ ።

ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ በሚያቀርቡት ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፤ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ለከሰረው ፡ ሰውና ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፤ ኪሣራ ፡ ላይ ፡ ከሚገኘው ፡ ንብረት ፡ ርዳታ ፡ እንዲደረግላቸው ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፻፵፩ ። ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ የከሠረውን ፡ ሰው ፡ ስለ፡ መቅጠራቸው ።

ሥራውን ፡ በቀና ፡ ለማከናወን ፤ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ባለዕዳውን ፤ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ በሚወስነው ፡ አኳኋን ፤ ቀጥረው ፡ ሊያሠሩት ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፲፻፵፪ ። በከሠረው ፡ ሰው ፡ ስለሚደርሱት ፡ ክልከላዎችና ፡ መብት ፡ ማጣት ።

በከሠረው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱት ፡ ክልከላዎችና ፡ መብት ፡ ማጣት ፡ ሊፈጸሙበት ፡ ይችላሉ ። ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ሕጋዊ ፡ ውሳኔዎች ፡ ሳይነኩ ፤ እነዚህ ፡ ክልከላዎች ፡ ወይም ፡ መብት ፡ ማጣት ፡ እንደገና ፡ መልሶ ፡ በመሰየም ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይቀሩም ።

ቍ ፡ ፲፻፵፫ ። የከሠረው ፡ ሰው ፡ በንብረቱ ፡ ለማዘዝ ፡ ስላለመቻሉ ።

የመክሠር ፡ ማስታወቂያው ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፤ የከሠረው ፡ ሰው ፡ የኪሣራው ፡ ሥራ ፡ ተጣርቶ ፡ ነጻ ፡ እስኪደረግ ፡ ድረስ ፡ በንብረቶቹ ፡

BACK



ላይ ፤ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ የሚያገኛቸው ፡ እንኳ ፡ ቢሆኑ ፤ የማስተዳደር ንና ፡ የማዘዝን ፡ መብት ፡ ያጣል ።

ቍ ፡ ሺ፳፬ ፡ ስለ፡ክስ ፡ አቀራረብ ።

የመክሠር ፡ ማስታወቂያው ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፤ ለመክሰስ ፡ ወይም ፡ ለመከሰስ ፡ የሚችሉት ፡ የንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። የከሠረው ፡ ሰው ፡ በክሱ ፡ ጣልቃ ፡ እንዲገባ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊፈቅድለት ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፳፭ ። ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ኅብረት ።

(፩) ገንዘባቸው ፡ በልዩ ፡ ቀዳሚነት ፡ መብት ፡ ወይም ፡ በመያዣ ፡ ያልተጠበቀ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ሁሉ ፡ የባለዕዳውን ፡ መክሠር ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በኅብረት ፡ ሁሉም ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ ከኪሣራው ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) ኅብረቱም ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተቈጥሮ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ወይም ፡ ባለዕዳ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ። እንደራሴውም ፡ ንብረት ፡ ጠባቂነት ፡ የተሾመው ፡ ሰው ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፳፮ ። ለየብቻ ፡ በግል ፡ የሚቀርቡትን ፡ ክሶች ፡ ስለ ፡ ማቋረጥ ።

ስለመክሠር ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፤ ከኪሣራው ፡ ላይ ፡ በኅብረት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ፡ የሆኑትን ፡ ሰዎች ፡ ለየብቻ ፡ ክስ ፡ ከማቅረብ ፡ ያግዳቸዋል ። የመክሠር ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ የባለዕዳውን ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ወይም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ለመያዝ ፡ የሚያደርገው ፡ የማስፈጸም ፡ ሥራ ፡ ይታገዳል ።

ቍ ፡ ሺ፳፯ ። የመክፈያ ፡ ጊዜያቸው ፡ ያልደረሰ ፡ ዕዳዎችን ፡ እንዲከፈሉ፡ስለ ፡ ማስገደድ ።

(፩) የመክሠር ፡ ማስታወቂያው ፡ ፍርድ ፤ የመክፈያ ፡ ጊዜያቸው ፡ ያልደረሱትን ፡ ለከሠረው ፡ ሰው ፡ የሚከፈሉ ፡ ዕዳዎች ፡ ሁሉ ፤ ወዲያውኑ ፡ ተከፋይ ፡ ያደርጋቸዋል ።

(፪) እነዚህ ፡ ዕዳዎች ፡ የመክፈሉ ፡ መቋረጥ ፡ ከተገለጸበት ፡ ቦታ ፡ ካለው ፡ ገንዘብ ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ ገንዘብ ፡ የተመለከቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ በተሰጠበት ፡ ቀን ፡ ሕጋዊ ፡ በሆነው ፡ ምንዛሪ ፡ በአገሩ ፡ ገንዘብ ፡ ይለወጣሉ ።

ቍ ፡ ሺ፳፰ ። ስለ ፡ ወለድ ፡ ሒሳብ ፡ መቋረጥ ።

የማይንቀሳቀስ ፡ ዋስትና ፡ ካላቸው ፡ ብድሮች ፡ በቀር ፤ ከከሠረው ፡ ሰው ፡ ከሚፈለጉት ፡ ብድሮች ፡ የሚታሰቡት ፡ ወለዶች ፡ ሁሉ ፤ የማስታወቂያው ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠበት ፡ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ በኅብረት፡ ላይ ፡ ከመቈጠር ፡ ይቋረጣሉ ። ዋስትና ፡ ያሏቸው ፡ የብድር ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ወለዶች ፤ ለዋስትናው ፡ ከተመደቡት ፡ ንብረቶች ፡ ከሚገኙት ፡ ገንዘቦች ፡ ላይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ ሊጠየቁ ፡ አይቻልም ።

**ቊ ፡ ሺ፷፱ ። የማስታወቂያው ፡ ፍርድ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ የተሠሩ ፡ ሥራዎች ፡ የማይጸኑ ፡ ስለመሆናቸው ።**

መክፈሉ ፡ ከተቋረጠበት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ባሉት ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀኖችና ፡ የማስታወቂያው ፡ ፍርድ ፡ በተሰጠበት ፡ ቀን ፡ መካከል ፤ ባለዕዳው ፡ ቀጥለው ፡ የተመለከቱትን ፡ ሥራዎች ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እነዚህ ፡ ሥራዎች ፡ የማያጸኑና ፡ በኅብረቱ ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ለመሆን ፡ የማይችሉ ፡ ይሆናሉ ።

(ሀ) በችሮታ ፡ የተደረጉ ፡ ስጦታዎች ፡ ሁሉ ፤

(ለ) የመክፈያ ፡ ጊዜያቸው ፡ ሳይደርስ ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፤ በማስተላለፍ ፤ በመሸጥ ፤ በማቻቻል ፤ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ የተደረገ ፡ የዕዳ ፡ አከፋፈል ፡ ሁሉ ፤

(ሐ) የመክፈያ ፡ ጊዜያቸው ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ሳይሆን ፡ በንግድ ፡ ሰነዶች፡ወይም ፡ በባንክ ፡ በኩል ፡ በማስተላለፍ ፡ የተደረገ ፡ የዕዳ ፡ አከፋፈል ፡ ሁሉ ፤

(መ) ዋስትናው ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ ለነበሩት ፡ ዕዳዎች ፤ በባለዕዳው ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ የተሰጡ ፡ ዋስትናዎች ፡ ሁሉ ።

**ቊ ፡ ሺ፸ ። የማስታወቂያው ፡ ፍርድ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት፡ ከተሠሩ ፡ ሥራዎች ፡ ውስጥ፡ በፈቃድ ፡ የሚሰረዙ ፡ ስለሚሆኑት ።**

አከፋፈሉ ፡ ከተቋረጠበት፡ ጊዜ፡ በኋላ ፤ የመክፈያ ፡ ጊዜያቸው ፡ ለደረሰ ፡ ዕዳዎች ፡ ባለዕዳው ፡ ያደረጋቸው ፡ ሌሎች ፡ አከፋፈሎችና ፡ በዋጋ ፡ ያደረጋቸው ፡ ውሎች ፡ በንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ጥያቄ ፡ ሊሰረዙ ፡ የሚችሉት ፤ ተከፋዮቹ ፡ ወይም ፡ ተዋዋዮቹ ፡ የአከፋፈሉን ፡ መቋረጥ ፡ ሁኔታ ፡ እያወቁ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቊ ፡ ሺ፸፩ ። የማስታወቂያው ፡ ፍርድ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ የተደረገው ፡ የመብት ፡ ማስመዝገብ ፡ በኅብረቱ ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ስላለመሆኑ ።**

(፩) ከንብረት ፡ ዋስትናዎች ፡ የሚገኙ ፡ በደንብ ፡ የተቋቋሙ ፡ መብቶች ፤ የመክሠር ፡ ማስታወቂያው ፡ ፍርድ ፡ እስከሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፤ ለመመዝገብ ፡ ይችላሉ ።

(፪) መክፈሉ ፡ ከተቋረጠ ፡ በኋላ ፤ ወይም ፡ መክፈሉ ፡ ከመቋረጡ ፡ በፊት ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ የተደረገው ፡ የመብት ፡ ማስመዝገብ ፡ ሁሉ ፡ በኅብረቱ ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ የማይችለው ፡ በማስመዝገቢያው ፡ ጊዜና ፡ ዋስትናው ፡ የተቋቋመበት ፡ ውል ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ መካከል ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ በላይ ፡ ያለፈ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፴፪ ። የመያዣ ፡ መብቱ ፡ በኀብረቱ ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፡ ከተባለው ፡ ሰው ፡ ቀጥሎ ፡ የመያዣ ፡ መብቱን ፡ ስለ ፡ አስመዘገበው ፡ ሰው ፡ ሁኔታ።**

የመያዣ ፡ መብቱ ፡ በኀብረቱ ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፡ ከተባለው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ቀጥሎ ፡ የመያዣ ፡ መብቱን ፡ ያስመዘገበ ፡ ሰው ፤ መያዣ ፡ የሆነው ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ የንግድ፡ መደብር፡ዋጋ ፡ ለገንዘብ፡ጠያቂዎቹ ፡ በሚከፋፈልበት፡ጊዜ፡መብቱ፡ሳይታወቅለት፡በቀረው፡ሰው ፡ ቦታና ፡ ስፍራ ፡ ተተክቶ ፡ ሊከፈለው ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በአዲሱ ፡ ተራ ፡ መሠረት ፡ ከሚያገኘውና ፡ ከእርሱ ፡ በፊት ፡ ለነበረው ፡ ሰው ፡ መብቱ ፡ ጸንቶለት ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ በድሮው ፡ ተራ ፡ መሠረት ፡ ያገኘው ፡ ከነበረው ፡ ገንዘብ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የገንዘብ ፡ ልዩነት ፡ ለኀብረቱ ፡ መመለስ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ሺ፴፫ ። አከፋፈሉ ፡ ከተቋረጠ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ተከፈሉ ፡ የንግድ ፡ ወረቀቶች ።**

(፩) አከፋፈሉ ፡ በተቋረጠበትና ፡ የማስታወቂያው ፡ ፍርድ ፡ በተሰጠበት ፡ ጊዜ፡ መካከል ፡ የሐዋላ ፡ ወረቀቶች ፡ ወይም ፡ ቼኮች ፡ ተከፍለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲመለስ ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ የንግዱን ፡ ወረቀት ፡ ገንዘብ ፡ በመጀመሪያ ፡ በተቀበለው ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) የተስፋ ፡ ሰነድ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ክሱ ፡ የሚቀርበው ፡ በሰነዱ ፡ ጀርባ ፡ በመጀመሪያ ፡ በፈረመው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ነው ።

(፫) ክሱ ፡ የቀረበበት ፡ ሰው ፡ ሰነዱ ፡ በተከፈለበት ፡ ጊዜ ፡ የአከፋፈሉን ፡ መቋረጥ ፡ ያወቀ ፡ መሆኑን ፤ በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) እና ፡ (፪) መሠረት ፡ ክስ ፡ አቅራቢው ፡ ማስረዳት ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ሺ፴፬ ። ስለ ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ።**

በቍጥር ፡ ሺ፳፱፡ ሺ፴ ፡ እና፡ ሺ፴፩ ፡ መሠረት ፡ የሚቀርቡ ፡ ክሶች ፡ ኪሣራ ፡ ማስታወቂያ ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ይርጋ ፡ ዘመን ፡ ይታገዳሉ ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## የባለዕዳውን ፡ ንብረቶች ፡ ስለ ፡ ማስተዳደር ።

**ቍ ፡ ሺ፴፭ ። ስለ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ጠቀላላ ፡ ተግባር ።**

(፩) ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፤ በመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ፈቃድ ፤ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የሚበላሹትን ፡ ወይም ፡ ወደፊት ፡ ዋጋቸው ፡ የሚረክሰውን ፡ ወይም ፡ ለማስቀመጥ፡ ብዙ ፡ ወጪ ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ዕቃዎች ፡ ይሸጣሉ ።

(፪) የብድር ፡ ገንዘቦችን ፡ ገቢ ፡ ያስደርጋሉ ፤ መርማሪውም ፡ ዳኛ ፡ የፈቀደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የንግዱን ፡ ሥራ ፡ ያካሂዳሉ ።

ቍ ፡ ሺ፹፯ ። የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ ስለ ፡ መሸጥ ።

(፩) መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ የከሠረውን ፡ ሰው ፡ ሐሳብ ፡ ሰምቶ ፡ ወይም ፡ በረኮማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ የከሠረውን ፡ ሰው ፡ በሚገባ ፡ ጠርቶ ፡ ሌሎች ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ እንዲሸጡ ፡ ለንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ሊፈቅድላቸው ፡ ይችላል ።

(፪) ዳኛው ፡ የሽያጩን ፡ ሁኔታዎች ፡ ይወስናል ።

ቍ ፡ ሺ፹፰ ። የንግድ ፡ መደብርን ፡ ስለ ፡ መሸጥ ።

የንግድ ፡ መደብር፡ (መድበል)፡ ሊሸጥ፡ የሚቻለው፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ፈቃድና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወሰነው ፡ የአሻሻጥ ፡ ሁናቴ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፹፱ ። ስለ ፡ ስምምነትና ፡ ግልግል ።

(፩) መርማሪው ፡ ዳኛ፡ የገንዘብ፡ ጠያቂዎቹን፡ ኮሚቴ ፡ ሐሳብ ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ የከሠረውን ፡ ሰው ፡ ሐሳብ ፡ ሰምቶ ፡ ወይም ፡ በሬኮማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ በሚገባ ፡ ጠርቶት ፡ ንብረቱን ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ስምምነትና ፡ ግልግል ፡ እንዲያደርጉ ፡ ለንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ሊፈቅድላቸው ፡ ይችላል ።

(፪) ስምምነት ፡ ወይም፡ ግልግል ፡ እንዲደረግበት ፡ የቀረበው ፡ ጉዳይ ፡ ዋጋው ፡ ያልተወሰነ፡ እንደ፡ ሆነ፣ ወይም፡ ከንብረት፡ ጠባቂዎቹ ፡ ሥልጣን ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስምምነቱ ፡ ወይም ፡ ግልግሉ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲጸድቅ ፡ ይቀርባል ።

(፫) የማጽደቁ ፡ ተግባር ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ የከሠረው ፡ ሰው ፡ ይጠራል። በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ስምምነቱንና ፡ ግልግሉን ፡ ለመቃወም ፡ ባለዕዳው ፡ ችሎታ ፡ አለው ።

ቍ ፡ ሺ፺ ። የንግድ ፡ ሥራን ፡ ስለ ፡ መቀጠል ።

(፩) ሕዝባዊ ፡ ጥቅም፡ ወይም፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ጥቅም ፡ በፍጹም ፡ የሚያስገድድ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ኰሚቴ ፡ ሐሳብና ፡ በመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ መግለጫ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የፈቀደላቸው፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ የንግዱን ፡ ወይም ፡ የኢንዱስትሪውን ፡ ሥራ ፡ ለመቀጠል ፡ ይችላሉ ።

(፪) የንግዱ ፡ ሥራ ፡ የቀጠለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ የንግዱ ፡ ሥራ ፡ መቀጠል ፡ ምክንያት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ከኅብረቱ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ይሆናሉ ። የመክሠሩም፡ ደንብ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ አይፈጸምባቸውም ። ገንዘባቸውም ፡ ከከሠረው ፡ ነጋዴ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ በኅብረቱ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ ሌሎች ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ አስቀድሞ ፡ ይከፈላቸዋል ።

(፫) የሚቀጥለውን ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ራሱ ፡ እንዳይሠራ ፡ ለማድረግ ፤ ንብረት ፡

ጠባቂው ፡ የንግዱን ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ ተቀባይ ፡ ለማድረግ ፡ እንዲችል ፡ መር ማሪው ፡ ዳኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሊሰጠው ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፻፺ ። የኪራይን ፡ ውል ፡ ስለ ፡ መቀጠል ።

(፩) ለባለዕዳው፡ ንግድ ፡ ወይም ፡ እንዱስትሪ ፡ የተመደቡትን ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች፤ እንዲሁም ፡ ከነዚሁ፡ ንብረቶች፡ ውስጥ፡ ለራሱና፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ መኖ ሪያ ፡ ሆነው ፡ የሚያገለግሉትን ፡ ቤቶች ፡ የሚመለከት ፡ የኪራይ ፡ ውል ፤ የነጋ ዴው ፡ መክሠር ፡ ብቻ ፡ እንዲፈርስ ፡ አያደርገውም ።

(፪) ንብረት፡ ጠባቂዎቹ፡ የኪራዩ፡ ውል ፡ እንዲሰረዝ ፡ ወይም ፡ እንዲቀጥል ፡ ለመ ምረጥ ፡ ይችላሉ ። ውሉ ፡ እንዲቀጥል ፡ ያደረጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የተከራዩን ፡ ግዴ ታዎች ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ። በሁለቱም ፡ አኳኋን ፡ ቢሆን ፤ በቍጥር ፡ ፻፺ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ የዕዳዎቹ፡ሁኔታ፡ዝርዝር፡በፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ከተቀመጠበት ፡ ቀን ፡ እንሥቶ ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ አሳባቸውን ፡ ለአከራዩ ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ።

(፫) ይኸውም ፡ ማስታወቅ ፡ ሊደረግ ፡ የሚቻለው ፡ በመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ፈቃ ድና ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ኮሚቴ ፡ አሳብ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፬) ከዚህ ፡ በላይ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፪) የተመለከተው ፡ የዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፤ ለአከራዩ ፡ የአጠባበቅ ፡ ሥራዎችንና ፡ ቦታዎችን ፡ መልሶ ፡ እጁ ፡ ለማድረግ ፡ ያለው ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ ለንግዱ ፡ ወይም ፡ ለኢንዱስትሪው ፡ ሥራ ፡ በሚያገለግሉ ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ዕቃዎች፡ ላይ፡ ፍርድ ፡ ለማስፈጸምና ፡ የኪራዩንም ፡ ውል ፡ ለማሰረዝ ፡ የሚቀርቡ ፡ ክሶች ፡ ሁሉ ፡ ታግደው ፡ ይቈያሉ ። አከራዩ ፡ ቦታዎቹን ፡ መልሶ ፡ እጁ ፡ ያደረገ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ የማስፈጸም ፡ ሥራ ፡ መታገድ ፡ ሁሉ ፡ በደንብ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

(፭) ንብረት ፡ ጠባቂው ፡ የኪራዩን ፡ ውል ፡ ለመቀጠል ፡ አሳቡን ፡ ለአከራዩ ፡ አስ ታውቆት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ማስታወቂያ ፡ በተደረገለት ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ አከራዩ ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ እንዲሰረዝ ፡ ጥያቄውን ፡ ካላቀረበ ፡ ውሉ ፡ ይቀጥላል ።

(፮) መክሠር ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ በደንብ ፡ ይሰረዛል ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ፡ እንዳልተጻፈ ፡ ይቈጠራል ።

(፯) በቍጥር ፡ ፻፺፩ ፡ እና ፡ ፻፺፪ ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ የዚህ ፡ ቍጥር ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፭ ።

## የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብቶችን ፡ ስለ ፡ መመርመር ።

### ክፍል ፡ ፩ ።

### ስለ ፡ ምርመራው ፡ አሠራር ።

**ቍ ፡ ፲፻፵፩ ። ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ማስረጃቻቸውን ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።**

(፩) የመክሠር ፡ ማስታወቂያ ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የሚጠይቁትን ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ከማመልከት ፡ ጋራ ፡ የመብቶቻቸውን ፡ ማረጋገጫ ፡ ሰነዶች ፡ ለንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ያቀርባሉ ።

(፪) ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ለተላኩላቸው ፡ ሰነዶች ፡ የደረሰኝ ፡ ወረቀት ፡ ይሰጣሉ ። እነዚህንም ፡ ሰነዶች ፡ የኪሣራው ፡ ሒሳብ ፡ በመጨረሻ ፡ ከተዘጋ ፡ በኋላ ፡ ይመልሳሉ ፤ ከዚህም ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ኀላፊዎች ፡ ናቸው ።

**ቍ ፡ ፲፻፵፪ ። ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ስለሚላኩ ፡ ማስታወቂያዎች ።**

(፩) በሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ ውስጥ ፡ የተጻፉ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የመክሠር ፡ ማስታወቂያው ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ሰነዶቻቸውን ፡ ያላቀረቡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህ ፡ ጊዜ ፡ ሲያልቅ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ሰነዶቻቸውን ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ያስጠነቅቋቸዋል ።

(፪) ይህ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ የሚፈጸመው ፡ ሕጋዊ ፡ ማስታወቂያን ፡ ለመቀበል ፡ ከተፈቀደላቸው ፡ ጋዜጣዎች ፡ ውስጥ ፡ በአንዱ ፡ በመጻፍና ፡ በንግድ ፡ ኦፊሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ በአጭሩ ፡ በመጻፍ ፡ ነው ። በንግድ ፡ ኦፊሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ የሚወጣው ፡ አጭር ፡ ጽሑፍ ፤ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ማስጠንቀቂያው ፡ የተጻፈበትን ፡ ሕጋዊ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለመቀበል ፡ የተፈቀደለትን ፡ ጋዜጣ ፡ ቍጥር ፡ ያመለክታል ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ደብዳቤ ፡ ይልኩላቸዋል ።

(፫) ማስጠንቀቂያው ፡ በንግድ ፡ ኦፊሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ በተጻፈ ፡ በ፲፭ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ሰነዶቹ ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፲፻፵፫ ። ዕዳዎችን ፡ ስለ ፡ መመርመር ።**

(፩) ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ዕዳዎችን ፡ የሚመረምሩት ፤ በከሠረው ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ወይም ፡ ደረሰኝ ፡ ባለው ፡ ሬኰማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ ከተጠራ ፡ በኋላ ፤ ተቃውሞም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ኮሚቴ ፡ ወይም ፡ በእንደራሴው ፡ ረዳትነት ፡ ነው ።

(፪) በተዘጋጀውም ፡ የዕዳዎች ፡ ዝርዝር ፤ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ይፈርምበታል ።

(፫) ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ዕዳ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፤ ክርክር ፡

እንዳሥተው፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ በረኮማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ ይህንኑ፡ ለገንዘብ፡ ጠያቂው ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ። ገንዘብ ፡ ጠያቂውም ፡ በጽሑፍ ፡ ወይም ፡ በቃል ፤ መልሱን ፡ በስምንት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

ቍ ፡ ሺ፴፱ ። የዕዳዎችን ፡ ዝርዝር ፡ በፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ማስቀመጥ ።

(፩) ምርመራው፡ ወዲያው፡ እንዳለቀ ፤ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ፡ የዕዳዎችን ፡ ዝርዝር፡ የተቀበሏቸውንና፡ የተቃወሟቸውን ፡ አስረጆች ፡ አመልክተው ፤ በፍርድ፡ ቤቱ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ያስቀምጣሉ ።

(፪) እንዲሁም ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ በሚንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ መብት፡ አለን ፡ የሚሉትን ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ዝርዝር ፡ ለመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ያቀርባሉ ።

ቍ ፡ ሺ፵ ። የማስቀመጥ ፡ ማስታወቂያ ።

(፩) የፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ የዕዳዎችን፡ ዝርዝር ፡ መቀመጥ ፤ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ፡ ጊዜ ፡ ሳይወስድ፡ በቍጥር ፡ ሺ፴፱ ፡ ንኡስ ፡ ቍ፡ (፪) በተመለከተው ፡ ዐይነት ፡ ያስታውቃል ።

(፪) ክርክር ፡ የተደረገበትን ፡ ዕዳ፤ ለሚመለከተው፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ በረኮማንዴ፡ ደብዳቤ ፡ ያስታውቀዋል ።

ቍ ፡ ሺ፵፩ ። ስለ ፡ አቤቱታዎች ።

(፩) በሒሳብ፡ ሚዛን፡ ውስጥ፡ የተጻፈ፡ ወይም፡ ሰነዱ፡ የተመረመረ ፡ ገንዘብ፡ ጠያቂ ፡ ሁሉ ፤ በንግድ ፡ ኦፊሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ በአጭሩ ፡ ጽሑፍ ፡ ማስታወቂያው ፡ ከተደረገበት ፡ ቀን ፡ በሚከተሉት ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ በወኪሉ ፡ ስለ ፡ ዝርዝሩ ፡ ጽሑፍ ፡ አቤቱታዎቹን ፡ ለፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ለማስታወቅ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) የከሠረውም ፡ ሰው ፡ እንደዚሁ ፡ ያለ ፡ መብት ፡ አለው ።

ቍ ፡ ሺ፵፪ ። ዕዳን ፡ ማስጻፍ ፡ ስለሚቆምበት ፡ የመጨረሻ ፡ ቀን ።

(፩) ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ ሲፈጸም ፤ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚቀርቡት ፡ አቤቱታዎች ፡ እንደ፡ተጠበቁ፡ሆነው ፤ መርማሪው፡ዳኛ፡ዕዳዎችን፡ማስጻፍን ፡ ያቆማል።

(፪) ይህን ፡ ውሳኔ ፡ በመፈጸም ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ክርክር ፡ ባልተደረገባቸው ፡ ዕዳዎች ፡ ዝርዝር ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂውን ፡ መቀበላቸውንና ፡ ያመኑለትንም ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ ያመለክታሉ ።

ቍ ፡ ሺ፵፫ ። ክርክር ፡ ከተነሣባቸው ፡ ዕዳዎች ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ፍርድ ።

ክርክር ፡ የተነሣባቸው ፡ ዕዳዎች ፤ በፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት፡ሹም ፡ አማካይነት፡ በረኮማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ ከአምስት ፡ ቀን ፡ አስቀድሞ ፡ ለሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ማስታ

ወቂያ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፤ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ባቀረበው ፡ መግለጫ ፡ ፍርድ ፡ ለመ ስጠት ፡ ለመጀመሪያው ፡ ችሎት ፡ ይላካሉ ።

ቍ ፡ ፲፻፺፱ ። ገንዘብ ፡ ጠያቂን ፡ ለጊዜው ፡ ስለ ፡ መቀበል ።

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚወስነው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፤ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ በመክሠሩ ፡ ሥርዐት ፡ ውስጥ ፡ ለጊዜው ፡ እንዲገባ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለመፍቀድ ፡ ይችላል ።

(፪) የፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ በረኮማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ በሦስት ፡ ቀን፡ውስጥ፡ ስለነርሱ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ለባለጉዳዮቹ ፡ ያስታውቃል ።

ቍ ፡ ፲፩፻ ። የመክሠርን ፡ ሥርዐት ፡ ስለ ፡ ማቋረጥ ፡ ወይም ፡ መቃወሚያን ፡ ስለ ፡ ማለፍ ።

(፩) አንድ ፡ ዕዳ ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጅ ፡ ክርክር ፡ ያነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ፡ቤቱ ፤ ሥል ጣን ፡ ባለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቃወሚያው ፡ እስኪወሰን ፡ ድረስ ፤ የመክሠሩ፡ ሥርዐት ፡ እንዲቋረጥ ፡ ወይም ፡ መቃወሚያው ፡ እንዲታለፍ ፡ ይወስናል ። እን ዲታለፍ ፡ የወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚያው ፡ ጊዜ ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፺፱ ፡ መሠረት ፡ ለጊዜው ፡ መብቱን ፡ እንዲቀበሉት ፡ ለመፍቀድ ፡ ይችላል ።

(፪) ዕዳው ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ የሚያስከትል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የመክሠሩን ፡ ጕዳይ ፡ የሚመለከተው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመክሠሩ ፡ ሥርዐት ፡ እንዲቋረጥ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ መቃወሚያው ፡ እንዲታለፍ ፡ የወሰነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ፍርድ ፡ እስኪሰጥበት ፡ ድረስ ፡ ለጊዜው ፡ መብቱን ፡ እንዲቀበሉት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊፈቅድ ፡ አይችልም ። ገንዘብ ፡ ጠያቂውም ፡ በሚሠሩት ፡ ሥራዎች ፡ ተሳታፊ ፡ ለመሆን ፡ አይችልም ።

ቍ ፡ ፲፩፻፩ ። በዋስትናቸው ፡ ላይ ፡ ክርክር ፡ ስለተነሣባቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ።

የንብረት ፡ ዋስትና ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፤ በዋስትናው ፡ ብቻ ፡ ክርክር ፡ ያለ በት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እንደ ፡ ተራ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ በመክሠሩ ፡ ሥርዐት ፡ ውስጥ ፡ እንዲገባ ፡ ይፈቀድለታል ።

ቍ ፡ ፲፩፻፪ ። በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ማስረጃቸውን ፡ ስላላቀረቡ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያ ቂዎች ።

(፩) ማስረጃቸውን ፡ በተወሰኑት ፡ ጊዜዎች ፡ ውስጥ ፡ ያላቀረቡት ፡ ገንዘብ፡ ጠያቂ ዎች ፤ በሚደረገው ፡ ክፍያ ፡ ውስጥ ፡ አይገቡም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የመጨረሻው ፡ ክፍያ ፡ እስኪደረግ ፡ ድረስ ፤ ለመቃወም ፡ የሚደረገውን ፡ ወጪ ፡ ችለው ፤ መቃ ወሚያ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

(፪) የነርሱ ፡ መቃወም ፤ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ያዘዛቸውን ፡ የክፍያዎች፡አፈጻጸም ፡ ሊያግደው ፡ አይችልም ።

(፫) ነገር ፡ ግን ፡ አዲስ ፡ ክፍያ ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለጊዜው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡

በሚወሰነው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ተካፋይ ፡ ሆነው ፤ በመቃወሚያውም ፡ ፍርድ ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፡ ድርሻቸው ፡ ተጠብቆ ፡ ይቀመጣል ።

ቍ ፡ ሺ፻፫ ። መብታቸው ፡ በኋላ ፡ ስለታወቀላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ።

መብታቸው ፡ በኋላ ፡ የታወቀላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ባዘዛቸው ፡ ክፍያዎች ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችሉም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ካል ተከፋፈለው ፡ ንብረት ፡ መጀመሪያ ፡ በሚያደርጉት ፡ ክፍያዎች ፡ ውስጥ ፡ በመጀ መሪያው ፡ ክፍያ ፡ ሊደርሳቸው ፡ ይገባ ፡ የነበረውን ፡ ድርሻ ፡ ለመውሰድ ፡ መብት፡ አላቸው ።

ቍ ፡ ሺ፻፬ ። ለምርመራው ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ።

የዕዳዎች ፡ ምርመራ ፡ ሥራ ፤ የኪሣራ ፡ ማስታወቂያው ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እጅግ ፡ ቢዘገይ ፡ በአምስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መፈጸም ፡ አለ በት ። ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ሁኔታዎች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፤ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተወሰነውን ፡ ጊዜ ፡ ለመለወጥ ፡ ይችላል ።

## ክፍል ፡ ፭ ።

## ስለ ፡ ጋራ ፡ ተገዳጆችና ፡ ስለ ፡ ዋሶች ።

ቍ ፡ ሺ፻፭ ። ሳይከፋፈል ፡ ያንድነት ፡ አላፊነት ፡ የተጻፈባቸውን ፡ ሰነዶች ፡ ይዘው ፡ ስለሚቀርቡ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ።

የከሠረው ፡ ሰውና ፡ መክፈላቸውን ፡ ያቋረጡ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፤ ሳይከፋፈል ፡ ባንድነት ፡ ተገዳጆች ፡ በመሆን ፡ በጀርባው ፡ የፈረሙበትን ፡ ወይም ፡ አላፊ ፡ የሆ ኑባቸውን ፡ ሰነዶች ፡ የያዘ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ በሰነዱ ፡ ላይ ፡ በተጻፈው ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ በንብረቶቹ ፡ ሁሉ ፡ ውስጥ ፡ ለመግባትና ፡ በማያደረጉትም ፡ ክፍያዎች፡ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ ገንዘቡን ፡ እስኪያገኝ ፡ ድረስ ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፻፮ ። ስለ ፡ ተከፈሉት ፡ ድርሻዎች ፡ በከሠሩ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ አቤቱታ ፡ ስለ ማቅረብ ።

በጋራ ፡ ተገዳጅ ፡ ሆነው ፡ ከከሠሩት ፡ ሰዎች ፤ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ በቍ ፡ ሺ፻፭ ፡ መሠረት ፡ በተከፈሉት ፡ ድርሻዎች ፡ ምክንያት ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚ ችለው ፤ ከከሠሩት ፡ ሰዎች ፡ ንብረት ፡ የተከፈሉት ፡ ድርሻዎች ፡ ድምር ፤ ከሚከፈ ለው ፡ ዋና ፡ ገንዘብና ፡ ከተጨማሪዎቹ ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አልፎ ፡ የተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ የሚሰጠው ፤ ሌሎቹ ፡ ተገዳጆች ፡ ዋስ ፡ ለሆኑላቸው ፡ የጋራ ፡ ተገዳጆችና ፡ ግዴታ ፡ በገቡበት፡ተራ፡ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፺፯ ። መክፈሉ ፡ ከመቋረጡ ፡ በፊት ፡ ከዕዳው ፡ ላይ ፡ ክፊሉን ፡ ስለተቀበለ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ።**

(፩) በከሠረው ፡ ሰውና ፡ በሌሎች ፡ የጋራ ፡ ተገዳጆች ፡ መካከል ፡ ሳይከፋፈል፡የአንድነት ፡ ኀላፊነት ፡ ያለባቸውን ፡ ሰነዶች ፡ የያዘ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ከሚጠይቀው ፡ ገንዘብ ፡ ክፊሉን ፤ መክፈሉ ፡ ከመቋረጡ ፡ በፊት ፡ የተቀበለ፡እንደ ፡ ሆነ፤ በኅብረቱ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ የሚታሰብለት ፡ ገንዘብ ፡ ከሚገባው ፡ ገንዘብ፡ ላይ ፡ በከፊል ፡ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ተቀንሶ ፡ ነው ። ለሚቀረውም ፡ ገንዘብ ፡ በጋራ ፡ ተገዳጆቹ ፡ ወይም ፡ በዋሶቹ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መብቶች ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ይቈያል ።

(፪) በከፊል ፡ የከፈለ ፡ የጋራ ፡ ተገዳጅ ፡ ወይም ፡ ዋስ ፤ ስለባለዕዳው ፡ በከፈለው፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ በዚሁ ፡ ኅብረት ፡ ውስጥ ፡ ይገባል ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

## ከንግድ ፡ መደብር ፡ ውስጥ ፡ ባልሆነ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የመያዣ ፡ ዋስትናዎች ፡ ያሏቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መብት ።

**ቍ ፡ ሺ፺፰ ። የንብረት ፡ መያዣ ፡ ስላላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡**

በደንብ ፡ የተቋቋመ ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ለማስታወሻ ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ በኅብረቱ ፡ ውስጥ ፡ ይጻፋሉ ። ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፤ በመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ፈቃድ ፤ ስለ ፡ ኅብረቱ ፡ ጥቅም ፡ በማለት ፡ ዕዳውን ፡ በመክፈል ፡ በመያዣ ፡ የተሰጠውን ፡ ነገር ፡ ለመውሰድ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፺፱ ። ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ መያዣውን ፡ ስለ ፡ መሸጡ ።**

በመያዣ ፡ የተሰጠውን ፡ ነገር ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ያልወሰዱት ፡ እንደ፡ሆነና፤ ገንዘብ ፡ ጠያቂውም ፡ ከሚገባው ፡ ገንዘብ፡ በሚበልጥ፡ዋጋ፡የሸጠው ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ ትርፉን ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ይወስዳሉ ። የሸጠበት ፡ ዋጋ ፡ ከሚገባው፡ገንዘብ ፡ ያነሰ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ቀሪ ፡ ለሆነው ፡ ገንዘብ ፡ ክፍያ ፤ መያዣ ፡ ያለው፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ እንደ ፡ ተራ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ሆኖ ፡ በኅብረቱ ፡ ውስጥ ፡ ይገባል።

**ቍ ፡ ሺ፻ ። ስለ ፡ አከራዩ ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ወሰን ።**

(፩) በቍጥር ፡ ፩ሺ፺፬ ፡ መሠረት ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ የፈረሰ፡እንደ፡ሆነ፤የአከፋፈሉን፡ መቋረጥ ፡ የሚያመለክተው፡ ፍርድ ፡ ከመሰጠቱ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ላለፈው ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ ኪራይ ፡ እና ፡ ሊያዘው ፡ ዓመት ፤ የኪራዩም ፡ አፈጻጸም ፡ ለሚመለከተው ፡ ሁሉና ፡ አጋጣሚ ፡ ለሚሆኑት ፡ የጉዳት ፡ ካሣዎች ፤ ለአከራዩ ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) የኪራዩ ፡ ውል ፡ ያልፈረሰ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለአከራዩ ፡ ያለፈው ፡ ኪራይ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከተከፈለውና ፤ ውሉ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ የተሰጡት ፡ ዋስትና ዎች፡ የጸኑለት፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ አከፋፈሉ ፡ ከተቋረጠ ፡ በኋላ ፡ የተሰጡት፡ ዋስትናዎች ፡ በቂ ፡ መሆናቸው ፡ የተገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በጊዜው ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ ጊዜው ፡ ያልደረሰው፡ ኪራይ፡ እንዲከፈለው ፡ ሊያስገድድ ፡ አይችልም።

<u>ቍ ፤ ሺ፹፩ ። በተከራየው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ የቤት ፡ ዕቃዎችን ፡ ስለ ፡ መውሰድ ።</u>

ከተከራየው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ የቤት ፡ ዕቃዎች ፡ የተወሰዱና ፡ የተሸጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በቍጥር ፡ ሺ፹ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) ውል ፡ በሚፈርስበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተመለከተውና ፡ ከዚህም፡ በቀር ፡ የተያዘው ፡ ዓመት ፡ ከሚያልቅበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ወደፊት ፡ ባለው ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ኪራይ ፡ ላይ ፡ አከራዩ፡ በልዩ፡ መብቱ ፡ ሊሠራበት ፡ ይችላል ።

<u>ቍ፤ ሺ፹፪። ንብረት፡ ጠባቂዎቹ፡ ስለሚያደርጉት፡ የውል፡ መቀጠል፡ ወይም፡ ማስተላለፍ።</u>

ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ለውሉ ፡ ማለቂያ ፡ ለቀረው ፡ ጊዜ ፡ የኪራዩን ፡ ውል ፡ ለመ ቀጠል ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ለማስተላለፍ ፡ የሚችሉት ፤ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ወይም ፡ እነርሱ ፡ ያስተላለፉላቸው ፡ ሰዎች ፡ በተከራየው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በቂ ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው፡ ዕቃዎች፡ የሚያስቀመጡ ፤ ከሕጉ ፡ ወይም ፡ ከውሉ ፡ የሚገኙትን ፡ ግዴታዎች ፡ ጊዜያቸው ፡ ሲደርስ ፡ የሚፈጽሙ ፡ እና ፡ ቤቶቹም ፡ የሚያገለግሉበ ትን ፡ ሁኔታ ፡ ሳይለውጡ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፤ ሺ፹፫ ። ተንቀሳቃሽ ፡ ዕቃዎችን ፡ ስለሚሸጠው ፡ ሰው ፡ ሁኔታ ።</u>

(፩) በቍጥር፡ ሺ፸፮፡ እስከ ፡ ሺ፸፰ ፡ የተመለከተው ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ፡ ሆኖ ፤ ተንቀሳቃሽ ፡ ዕቃዎችን ፡ ለሸጠው ፡ ሰው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የተሰጡት ፡ ዋስትናዎች ፡ በኪሣራው ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሆነው ፡ ሊቀርቡ ፡ አይችሉም ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍጥር፡ (፩) የተደነገገውን፡ የሚቃወም ፡ ስምምነት ፡ ሁሉ ፡ ፈራሽ፡ ይሆናል ።

<u>ቍ ፤ ሺ፹፬ ። በሚንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ የቀደምትነት ፡ መብት ፡ ያላቸውን ፡ ገን ዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ስለ ፡ መክፈል ።</u>

(፩) በቍጥር ፡ ሺ፺፬ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፪) የተመለከተው ፡ ዝርዝር ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፤ በዚህ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ ለተመለከቱት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ከመጀመሪያው፡ ገቢ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈላቸው ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ይፈቅዳል ።

(፪) ስለ ፡ ቀደምትነቱ ፡ ክርክር ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

## በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ የመያዣና ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ።

**ቊ ፡ ፲፩፻፳፫ ። ከሚንቀሳቀሱ ፡ ዕቃዎች ፡ ሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ተከፋፈለ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ የሽያጭ ፡ ዋጋ ።**

የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ የሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ ከሚንቀሳቀሱ ፡ ዕቃዎች ፡ የሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ በአንድነት ፡ ክፍያው ፡ የተደረገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ የሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ በሙሉ ፡ ዋጋቸውን ፡ ያልተቀበሉ ፡ የመያዣ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፤ በቍጥር ፡ ፲፩፻፳፩ ፡ እና ፡ በተከታዮቹ ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ መብታቸው ፡ ተቀባይነት ፡ አግኝቶ ፡ እንደ ፡ ሆን ፤ ባልተከፈላቸው ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ለኅብረቱ ፡ ከሚከፈለው ፡ ገንዘብ፡ውስጥ፡ ከተራ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ጋራ ፡ ተካፋይ ፡ ይሆናሉ ።

**ቊ ፡ ፲፩፻፳፬ ። ከማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ተከፈለ ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ዕቃዎች ፡ የሽያጭ ፡ ዋጋ ።**

የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ የሽያጭ ፡ ዋጋ፡ከመከፋፈሉ፡በፊት ፤ ከሚንቀሳቀሱ፡ ዕቃዎች ፡ የሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ፡ ጊዜ ፡ ክፍያዎች ፡ ተደርጎ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ በቍጥር ፡ ፲፩፻፳፬ ፡ የተመለከቱት ፡ ልዩነቶች ፡ ካላጋጠሙ ፡ በቀር ፤ በደንብ ፡ ተቀባይነት ፡ ያገኙ ፡ የመያዣና ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በጠቅላላ ፡ መብታቸው ፡ መጠን ፡ በክፍያው ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ይካፈላሉ ።

**ቊ ፡ ፲፩፻፳፭ ። ዋስትና ፡ ከሌለው ፡ ኅብረት ፡ ውስጥ ፡ የተቀበሉትን ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ መቀነስ ።**

(፩) የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ከተሸጡና ፤ መያዣና ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ባላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ተራ ፡ ከተወሰነ ፡ በኋላ ፤ ከነዚሁ ፡ መካከል ፡ ከማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ዋጋ ፡ ለጠቅላላው ፡ መብታቸው፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ የሚችሉት ፤ ከመያዣቸው ፡ የተነሣ ፡ ለማግኘት ፡ ከሚችሉት ፡ ገንዘብ ፡ ዋስትና ፡ ከሌለው ፡ ኅብረት ፡ ውስጥ ፡ ያገኙት ፡ ገንዘብ ፡ ተቀናሽ ፡ ሆኖ ፡ ነው ።

(፪) ተቀናሽ ፡ የሆነውም ፡ ገንዘብ ፡ መያዣ ፡ ባለው ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ አይቀርም ። ነገር ፡ ግን ፡ ዋስትና ፡ ለሌለው ፡ ኅብረት ፡ ተመላሽ ፡ ሆኖ ፡ ይቈያል ።

BACK



**ቍ ፡ ሺ፷፰ ። የመያዣ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በከፊል ፡ ለመቀበል ፡ ተራ ፡ ስለ፡ መጻፍ ።**

ከማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ የሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ በከፊል ፡ ለመከፈል ፡ ተራ ፡ የተጻፉ ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎችን ፡ የሚመለከት ፡ ጕዳይ ፡ ከዚህ ፡ እንደሚቀጥለው ፡ ይሠራል ፡—

(ሀ) ከማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ዋጋ ፡ ለመቀበል ፡ ተራ ፡ ከተጻፉ ፡ በኋላ ፡ በሚቀራቸው ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ዋስትና ፡ በሌለው ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ ይሆናሉ ።

(ለ) ባለፈው ፡ መከፋፈል ፡ ውስጥ ፡ ከዚሁ ፡ ድርሻ ፡ በላይ ፡ የተቀበሏቸው ፡ ገንዘቦች ፤ ለመቀበል ፡ ተራ ፡ ከተጻፉበት ፡ መያዣ ፡ ካለው ፡ ክፍያቸው ፡ ላይ ፡ ተይዘው ፤ ዋስትና ፡ ለሌለው ፡ ንብረት ፡ ተመላሽ ፡ ሆነው ፡ ይቈያሉ ።

## ክፍል ፡ ፰ ።

**በንግዱ ፡ መደብር ፡ ላይ ፡ መያዣ ፡ ያላቸው ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መብት ።**

**ቍ ፡ ሺ፷፱ ። ከሌሎች ፡ ከሚንቀሳቀሱ ፡ ዕቃዎች ፡ ሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ተከፋፈለው ፡ የንግድ ፡ መደብር ፡ ሽያጭ ፡ ዋጋ ።**

የንግዱ ፡ መደብር ፡ ሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ ከሌሎች ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቶች ፡ ሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ በፊት ፤ ወይም ፡ አብሮ ፡ ክፍያው ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ከመደብሩ፡ሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ በሙሉ ፡ ዋጋቸውን ፡ ያልተቀበሉ ፡ የመያዣ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፤ በቍጥር ፡ ሺ፵፩ ፡ እና ፡ በተከታዮቹ ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ መብታቸው ፡ ተቀባይነት ፡ አግኝቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባልተከፈላቸው ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ለኀብረቱ ፡ ከሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ ከተራ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ጋራ ፡ ተካፋይ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ሺ፸ ። ከንግዱ ፡ መደብር ፡ ሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ተከፋፈለው ፡ የሌሎች ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ዕቃዎች ፡ ሽያጭ ፡ ዋጋ ።**

የንግዱ ፡ መደብር ፡ ሽያጭ ፡ ዋጋ፡ከመከፋፈሉ ፡ በፊት ፡ የሌሎች ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቶች ፡ ሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ ተከፋፍሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መያዣ ፡ ያላቸውና ፤ መብታቸውም ፡ በደንብ ፡ ተቀባይነት ፡ ያገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፤ ከዚሁ ፡ ከሚከፋፈለው ፡ ገንዘብ ፤ በሙሉ ፡ በሚጠይቁት ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ተካፋይ ፡ ይሆናሉ ። ስለ ፡ ሆነም ፤ በቍጥር ፡ ሺ፷፯ ፡ የተደነገገው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፸፩ ። መያዣ ፡ ካልሆነው ፡ ንብረት ፡ የሽያጭ፡ዋጋ፡የተከፈለውን ፡ ስለ፡መቀነስ ።**

(፩) የንግዱ ፡ መደብር ፡ ከተሸጠና ፡ የሽያጩም ፡ ገንዘብ ፡ የሚከፋፈልበት ፡ አኳኋን ፡ ከተወሰነ ፡ በኋላ ፡ በንግድ ፡ መደብሩ ፡ ላይ ፡ ለሞላ ፡ ገንዘባቸው ፡ መያዣ፡

BACK



ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ገንዘባቸውን ፡ ከንግዱ ፡ መደብር ፡ ሽያጭ ፡ ላይ፡ የሚያገኙት ፤ መያዣ ፡ ካልነበረው ፡ ንብረት ፡ የሽያጭ ፡ ዋጋ ፡ የተከፈላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ተቀናሽ ፡ ሆኖ ፡ ነው ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) መሠረት ፡ የተቀነሰው ፡ ገንዘብ ፡ ከኪሣራው ፡ ላይ፡ በጎ ብረት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ለሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ጥቅም ፡ መያዣ ፡ ወዳልሆነው ፡ ንብ ረት ፡ ተመላሽ ፡ ይሆናል ።

<u>ቍ ፡ ሺ፸፪ ። በንግዱ ፡ መደብር ፡ ላይ ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች፡ በከፊል ፡ ለመቀበል ፡ ተራ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ።</u>

ከንግዱ፡መደብር፡ ሽያጭ፡ ዋጋ፡ ላይ፡የመያዣ፡መብት፡ኑሮዋቸው፡በከፊል፡ ብቻ፡ የተከፈሉ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ጕዳይ ፡ ከዚህ ፡ እንደሚቀጥለው ፡ ይሠራል ፤

(ሀ) ዋስትና፡ በሌለው፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ ያላቸው ፡ መብት ፡ የሚወሰነው ፡ ከን ግዱ ፡ መደብር ፡ ዋጋ ፡ ከተቀበሉት ፡ ገንዘብ ፡ በኋላ ፡ በሚቀራቸው ፡ ገንዘብ፡ መጠን ፡ ነው ።

(ለ) ባለፈው፡ መከፋፈል፡ ውስጥ ፡ ከዚሁ ፡ ድርሻ ፡ በላይ ፡ የተቀበሏቸው ፡ ገን ዘቦች ፤ ለመቀበል ፡ ተራ ፡ ከተጻፉበት ፡ መያዣ ፡ ካለው ፡ ክፍያቸው ፡ ላይ ፡ ተይዘው ፡ ዋስትና ፡ ለሌለው ፡ ንብረት ፡ ተመላሽ ፡ ሆነው ፡ ይቈያሉ ።

## ክፍል ፡ ፯ ።

## <u>በመፋለም ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ።</u>

<u>ቍ ፡ ሺ፸፫ ። የንግድ ፡ ወረቀቶችን ፡ በመፋለም ፡ ስለ ፡ መጠየቅ ።</u>

የመክሠር ፡ ማስታወቂያ ፡ ፍርድ ፡ በተሰጠበት ፡ ጊዜ ፤ በከሠረው ፡ ሰው ፡ ንብ ረት ፡ ውስጥ ፡ በዐይነት ፡ የሚገኙትን ፡ የንግድ ፡ ወረቀቶች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ያል ተከፈለባቸው ፡ ሰነዶች ፡ መልሶ ፡ ለመውሰድ ፡ የሚቻለው ፡ ባለሀብቱ ፡ እነዚህን፡ ወረቀቶች ፡ ወይም ፡ ሰነዶች ፡ ለባለዕዳው ፡ የሰጠው ፡ ወጋቸውን ፡ ተቀብሎ ፡ እን ዲያስቀምጥለት ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ። እንዲሁም ፤ ባለሀብቱ ፡ ለተ ወሰኑ ፡ አከፋፈሎች ፡ ባለዕዳው ፡ እንዲከፍልለት ፡ የሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲመለ ለስለት ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

<u>ቍ ፡ ሺ፸፬ ። በአደራ ፡ የተቀመጡ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎችን ፡ ወይም ፡ ላንድ ፡ ኮሚሲዮኔር ፡ የተሰጡትን ፡ ዕቃዎች ፡ ስለ ፡ መጠየቅ ።</u>

(፩) ለባለዕዳው፡ በአደራ፡ የተሰጡ ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ወይም ፡ በባለሀብቱ ፡ ስም፡ ለመሸጥ ፡ የተቀበላቸው ፡ ዕቃዎች ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ በዐይነት ፡ የሚገኙ ፡ ከሆነ ፡ ባለሀብቱ ፡ እንዲመለሱለት ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) የነዚሁ ፡ ዕቃዎች ፡ ዋጋ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዲመለስ ፡ ለመጠ

BACK



የቅ ፡ የሚቻለው ፤ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ ባለው ፡ ነገር ፡ ያልተከፈለ ፡ ወይም፡ በባለዕዳውና፡ በገዢው ፡ መካከል ፡ በተመላላሽ፡ ሒሳብ ፡ ያልተቻቻለ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፳፫ ። ከመክሠሩ ፡ በፊት ፡ ሽያጮቻቸው ፡ የፈረሰውን ፡ ዕቃዎች ፡ በመፋለም ፡ ስለ ፡ መጠየቅ ።

(፩) በፍርድ፡ ውሳኔ፡ ወይም፡ በውሉ፡ ቃል፡ መሠረት፡ የመክሠር፡ ማስታወቂያው ፡ ፍርድ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ ሽያጫቸው ፡ ፈራሽ ፡ የሆነውን ፡ ዕቃዎች ፡ በዐይነታቸው ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ካሉ ፡ በመፋለም ፡ ለመጠየቅ ፡ ይቻላል።

(፪) የሽያጩ፡ መፍረስ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ የታወቀው ፡ ወይም ፡ የተወሰነው ፡ የመክሠር፡ ማስታወቂያው፡ ፍርድ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ገንዘቡ ፡ ያልተከፈለው ፡ ሻጭ ፡ ያቀረበው ፡ የመፋለም ፡ ጥያቄ ፡ ወይም ፡ ክስ ፡ የመክሠሩ ፡ ማስታወቂያ ፡ ፍርድ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ ከሆነ ፡ የመፋለሙን ፡ ጥያቄ ፡ በከፊል ፡ ገንዘብ ፡ ሳይም ፡ ቢሆን ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፳፬ ። ባለሀብትነታቸው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የተሸጡ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ዕቃዎችን ፡ ስለ ፡ ማስመለስ ።

ዋጋቸው ፡ እስኪከፈል ፡ ድረስ ፡ ባለሀብትነታቸው ፡ ሳይተላለፍ ፡ ለከሠረው ፡ ሰው ፡ የተሸጡትን ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ በመፋለም ፡ መልሶ፡ለመውሰድ ፡ የሚቻለው ፡ የሽያጩ ፡ ቃል ፡ የመክሠር ፡ ማስታወቂያው ፡ ፍርድ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፪ሺ፫፻፳፯ ፡ መሠረት ፡ ተመዝግቦ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፳፭ ። ለባለዕዳው ፡ የተላኩትን ፡ ዕቃዎች ፡ በመፋለም ፡ ስለ ፡ መጠየቅ ።

(፩) ለባለዕዳው ፡ የተላኩ ፡ ዕቃዎች ፡ በራሱ ፡ መጋዘን ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ስለርሱ ፡ በሚሸጠው ፡ በኮሚሲዮኑ ፡ ማጋዘኖች ፡ ውስጥ ፡ ያልገቡ ፡ ከሆነ ፡ በመፋለም ፡ ለመጠየቅ ፡ ይቻላሉ ።

(፪) የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ላኪው ፡ በፈረመው ፡ ሰነድ ፡ መሠረት ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ላለው ፡ ሁለተኛ ፡ ገዢ ፡ ከመድረሳቸው ፡ በፊት ፡ ያለማታለል ፡ ዕቃዎቹ ፡ የተሸጡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመፋለሙን ፡ ጥያቄ ፡ ለመቀበል ፡ አይቻልም ።

ቍ ፡ ሺ፳፮ ። ስለ ፡ መያዝ ፡ መብት ።

ለባለዕዳው ፡ ያልተሰጡትን ፡ ወይም ፡ ለርሱ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ሆኖ ፡ ለሚሠራ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ገና ፡ ያልላኳቸውን ፡ ዕቃዎች ፡ ሻጩ ፡ ለመያዝ ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ፲፻፸፱ ። ዕቃዎች ፡ እንዲሰጡ ፡ ለማስገደድ ፡ ለንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ስለ ፡ አላቸው ፡ ሥልጣን ።

(፩) በቍጥር ፡ ፲፻፸፯ ፡ እና ፡ ፲፻፸፰ ፡ ስለ ፡ ተመለከቱት ፡ ጕዳዮች ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፤ በመርማሪው፡ ዳኛ፡ ፈቃድ ፤ የተስማሙበትን ፡ ዋጋ ፡ ለሻጩ ፡ በመክፈል ፡ ዕቃዎቹ ፡ እንዲሰጡዋቸው ፡ ለማስገደድ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

(፪) በዚህ ፡ ሥልጣናቸው ፡ ያልሠሩበት ፡ እንደ፡ሆነ፡ ሻጩ ፡ ከዕቃዎቹ፡ዋጋ ፡ የተቀበለውን፡ እና ፡ ከከሰረው ፡ ሰው፡ ለኪራይ ፡ ወይም ፡ ለመጫኛ፡ ለኮሚሲዮን ፡ ለአሹራንስ ፡ ወይም ፡ ለሌሎች፡ ወጪዎች ፡ አስቀድሞ ፡ የወሰዳቸውንና ፡ እነዚህንም ፡ ለመሳሰሉ ፡ ምክንያቶች ፡ የሚከፈሉትን ፡ ገንዘቦች ፡ ለኅብረቱ ፡ መልሶ ፡ እነዚህንም ፡ ወጪዎች ፡ ራሱ ፡ እንዲከፍል፡ ሻጩ ፡ ይገደዳል ። የሆነ፡ ሆኖ ፡ የውሉ ፡ አለመፈጸም ፡ ለሻጩ ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራዎችን፡ ሊያስገኙለት፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፲፻፹ ። የመፋለም፡ ጥያቄዎችን ፡ ስለ ፡ መቀበል ።

የመፋለም ፡ ጥያቄዎችን ፤ በመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ፈቃድ ፤ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ለመቀበል ፡ ይችላሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

ስለኪሣራው ፡ አሠራር ፡ የሚደረግ ፡ ዘዴ ።

ክፍል ፡ ፩ ።

ስምምነት ።

ቍ ፡ ፲፻፹፩ ። የስምምነት ፡ አሳብ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

(፩) በቍጥር ፡ ፲፻፵፯ ፡ የተመለከተው ፡ ቀን ፡ ካለቀበት ፡ እንሥቶ ፡ በማናቸውም፡ ጊዜ ፡ የከሠረው ፡ ነጋዴ ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ አንድ ፡ የስምምነት ፡ አሳብ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ። ይኸውም ፡ አሳብ ፡ የሚቀርበው ፡ በተለይ፡ለመርማሪው፡ ዳኛ ፡ ነው ።

(፪) በሚቀርበው ፡ አሳብ ፡ ውስጥ ፡ ዋስትና ፡ ለሌላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የሚሰጠው ፡ በሙቶ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የሚባለው ፡ ገንዘብና ፡ ባለዕዳው ፡ ለመክፈል ፡ እስከዚህ ፡ ቀን ፡ ይሁንልኝ ፡ ሲል ፡ የጠየቀው ፡ ጊዜ ፡ ይጠቀሳል ፡ እከፍላለሁ ፡ ላለው ፡ ገንዘብና ፡ ለሥን ፡ ሥርዐት ፡ ወጪና ፡ ለንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ኪሣራ ፡ ማረጋገጫ ፡ እንዲሆን፡ የሚሰጠውን ፡ ዋስትና ፡ መጥቀስ ፡ አለበት ።

(፫) ስለ ፡ ስምምነት ፡ የቀረበው ፡ አሳብ ፡ የሒሳብ ፡ ማጣራቱን ፡ ያግዳል ።

**ቍ ፡ ሺ፻፪ ። የቀረበውን ፡ ስምምነት ፡ ስለ ፡ መመርመርና ፡ የተባለውን ፡ አሳብ ፡ ለገንዘብ፡ ጠያቂዎች፡ ስለ፡ ማስታወቅ ።**

(፩) የስምምነቱ ፡ አሳብ ፡ የቀረበለት ፡ መርማሪ ፡ ዳኛ ፡ የንብረት፡ጠባቂዎችንና ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎችን ፡ ኮሚቴ ፡ ሐሳብ ፡ ይቀበላል ።

(፪) የቀረበው ፡ አሳብ ፡ የሚገባ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ የገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዳኛው ፤ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ እንዲያውቁት ፡ በፍጥነት ፡ እንዲተላለፍላቸው ፡ ያዛል ።

(፫) ይህ ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የሚላከው ፡ ማስታወቂያ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ በኩል ፡ ሆኖ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ በሚላከው ፡ በሬኮማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ ይፈጸማል ። ስለሆነም ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ፡ ብዛት ፤ ለያንዳንዱ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለመላክ ፡ የማይፈቀድ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ፡ ቤቱ ፤ የንብረት ፡ ጠባቂዎቹን ፡ እና ፡ የሕግ ፡ አስከባሪውን ፡ አሳብ ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፤ ለመርማሪው፡ ዳኛ ፡ ስለ ፡ ስምምነቱ ፡ የቀረበው፡ አሳብ ፡ የሕግ ፡ ማስታወቂያዎችን ፡ ለመቀበል ፡ በተፈቀደለት ፡ ጋዜጣና ፡ በንግድ ፡ ኦፊሲዬል ፡ ጋዜጣ ፡ እንዲወጣ ፡ ለማዘዝ ፡ ይፈቅድለታል ።

(፬) ማስታወቂያውም ፤ የከሠረው ፡ ነጋዴ ፡ ካቀረበው ፡ አሳብ ፡ በላይ ፡ ንብረት፡ ጠባቂዎቹና ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ኮሚቴ ፡ የሰጡትን ፡ አሳብ፡ያመለክታል ። በመክሠር ፡ አሠራር ፡ ሁኔታ ፤ በተፈጸሙት ፡ ሥርዐቶችና ፡ በተደረጉት ፡ ሥራ ዎች፡ ላይ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ያቀረቡት ፡ መግለጫ ፡ ከዚሁ ፡ ማስታወቂያ ፡ ጋራ ፡ ይያያዛል ።

(፭) ስለስምምነቱ፡ በተላለፈው ፡ ማስታወቂያ ፡ ውስጥ ፡ ከሓያ ፡ ቀን ፡ የማያንስ፡ ከ፴ ፡ ቀን ፡ የማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ይወሰናል ። በዚሁም ፡ ጊዜ፡ ውስጥ፡ በሐሳቡ፡ ያልተስማሙት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የከሠረው ፡ ሰው፡ ያቀረባቸውን ፡ አሳቦች ፡ ያለመቀበላቸውን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ሺ፻፫ ። ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ስለሚሰጡት ፡ ድምፅ ።**

(፩) የሚሰጠው ፡ ድምፅ ፡ በፕሮሴቬርባል ፡ ተጽፎ ፡ መርማሪው ፡ ዳኛና ፡ የፍ ርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ይፈርሙበታል ።

(፪) በውለታ ፡ ወይም ፡ ለጊዜው ፡ የተቀበሏቸው፡ ቢሆኑም ፤ መብታቸው ፡ በአገ ባብ ፡ የታወቀላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ሁሉ ፡ የድምፅ ፡ መስጠት ፡ መብት ፡ አላቸው ።

(፫) ልዩ ፡ ማረጋገጫዎች፡ ያሏቸው፡ ገንዘብ፡ ጠያቂዎች፤ የቀረበውን፡ የስምምነት፡ አሠራር ፡ በሚመለከተው ፡ ጕዳይ ፡ ስላላቸው ፡ መብት ፡ ድምፅ ፡ ለመስጠት ፡ የሚችሉት ፡ ማረጋገጫቸውን ፡ የለቀቁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ። ስምምነቱ ፡ ሳይ ደራጅ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሳያጸድቀው ፡ የቀረ ፤ ወይም ፡ የተሰረዘ ፡

ወይም ፡ የፈረሰ ፡ እንደ፡ሆነ፤ ማረጋገጫቸውን ፡ መልቀቃቸው ፡ ቀሪ፡ ይሆናል ።

(፬) የከሠረው ፡ ሰው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፤ እስከ ፡ አራት ፡ ቤት ፡ የሚቈጠሩ ፡ የሥጋ፡ ወይም ፡ የጋብቻ፡ ዘመዶች፡ እና፡እንዲሁም ፡ የመክሠሩ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተነገረበት ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ከነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ መብት ፡ የተላለፈላቸው ፡ ወይም ፡ የገዙ ፡ ሰዎች ፡ ድምፅ ፡ ለመስጠትና ፡ ከድምፅ ፡ ብልጫው፡ ቍጥር ፡ ውስጥ ፡ ለማግባት ፡ አይችሉም ።

(፭) የመክሠሩ፡ ማስታወቂያ፡ ፍርድ፡ ከወጣ፡ በኋላ ፡ የተደረጉት፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂነትን ፡ መብት ፡ ማስተላለፍ ፡ የድምፅ ፡ መስጠትን ፡ መብት ፡ አይሰጡም።

ቍ ፡ ሺ፸፬ ። ስምምነቱን ፡ ስለ ፡ ማጽደቅ ።

(፩) ስምምነቱ ፡ ውድቅ፡ እንዳይሆን፤ ከዕዳው ፡ ከሦስት ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ ባላቸው፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ድምፅ ፡ ብልጫ ፡ እንዲጸድቅ ፡ ያስፈልጋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፤ ድምፅ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ፡ ያልነበሩት ፡ ሰዎች ፡ በድምፅና ፡ በገንዘብ፡ ብልጫው ፡ አቈጣጠር ፡ ውስጥ ፡ አይገቡም ።

(፪) የከሠረው ፡ ሰው ፡ ያቀረበውን ፡ የስምምነት ፡ አሳብ ፡ አንቀበልም ፡ ሲሉ ፡ በቍጥር ፡ ሺ፸፪ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፫) በተመለከተው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያላስታወቁ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ስምምነቱን ፡ እንደ፡ ተቀበሉ ፡ ይቈጠራሉ ።

(፫) ይህ፡ የተነገረው፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ከሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ የተነሣ ፡ መብታቸውን ፡ የተቀበሏቸው ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ፡ቍጥር ፡ ወይም ፡ የሚጠይቁት፡ ገንዘብ፡ልክ፡ቢለዋወጥም፡የድምፅ ፡ ብልጫውን ፡ አቈጣጠር ፡ አይለውጠውም ።

(፬) የድምፅ ፡ መስጠትን ፡ ውጤት ፡ በቍጥር ፡ ሺ፸፫ ፡ ንኡስ ፡ (፩) በተመለከተው ፡ ፕሮሴቬርባል ፡ ላይ ፡ መርማሪው፡ ዳኛ ፡ ያረጋግጠዋል ።

ቍ ፡ ሺ፸፭ ። ስምምነቱን ፡ ስለ ፡ መቃወም ።

(፩) በስምምነቱ፡ውስጥ፡ለማግባት ፡ መብት ፡ የነበራቸው፡ወይም፡ከዚያ፡ወዲህ፡ መብታቸው ፡ የታወቀላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ሁሉ ፡ በስምምነቱ ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

(፪) ተቃዋሚነቱ ፡ ምክንያት ፡ ያለው ፡ መሆን ፡ አለበት ። መቃወሚያው ፡ ምክንያት ፡ ካልተሰጠበትና ፡ ድምፅ ፡ በተሰጠበት ፡ በስምንት ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ፡ ለባለዕዳውና ፡ ለንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ካልተላለፈላቸው ፡ ፈራሽ፡ ይሆናል ። ይኸውም፡መቃወሚያ፡በፍርድ፡ቤቱ፡መጀመሪያ፡ችሎት፡ለመቅረብ፡ጥሪ፡ይኖርበታል።

ቍ ፡ ሺ፸፮ ። ስምምነቱን ፡ ስለ ፡ ማጽደቅ ።

ማናቸውም ፡ ጥቅም፡ ያለው፡ ወገን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስምምነቱን ፡ እንዲያጸድቀው ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በቍጥር፡ ሺ፸፭ ፡ ከተወሰኑት ፡ ስምንት ፡ ቀኖች ፡ በፊት ፡ ለመወሰን ፡ አይችልም ።

(፪) በዚህ ፡ በተባለው፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መቃወሚያዎች ፡ ቀርበው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ፡ ቤቱ ፡ ስለነዚህ፡ መቃወሚያዎችና ፡ እንዲጸድቅ ፡ ስለ፡ ቀረበው ፡ ጥያቄ፡ ባንድ ፡ ፍርድ ፡ ይወስናል ።

(፫) ስለ፡ ስምምነቱ ፡ መጽደቅ ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚከተሉትን ፡ መመልከት ፡ አለበት ፡—

(ሀ) መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ስለ፡ መክሠሩ፡ አሠራርና፡ ስምምነቱ ፡ ሊፈቀድ ፡ የሚችል ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚያቀርበውን ፡ መግለጫ ፡ እና ፡

(ለ) ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ በቍጥር ፡ ሺ፷፪ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፫) መሠረት ፡ የሚያቀርቡትን ፡ መግለጫ ፡ እና ፡

(ሐ) ያለም ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ከከሠረው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በጋራ ፡ ተገዳጅ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ የሚያቀርቡትን ፡ ማስገንዘቢያ ።

(፬) መቃወሚያውንም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተቀበለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስምምነቱ ፡ ባለጉዳዮች ፡ በሆኑት ፡ ሰዎች ፡ በኩል ፡ ሁሉ ፡ ፈራሽ ፡ መሆኑን ፡ ይወስናል ።

## ቍ ፡ ሺ፷፯ ። ስምምነቱን ፡ ለማጽደቅ ፡ ስላለመቀበል ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስምምነቱን ፡ የማያጸድቀው ፡

(ሀ) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ደንቦች ፡ ያልተፈጸሙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡

(ለ) ስምምነቱን ፡ ማጽደቅ ፡ የሕዝብን ፡ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹን ፡ ጥቅም፡ የሚቃወም ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

## ቍ ፡ ሺ፷፰ ። የስምምነቱን ፡ አፈጻጸም ፡ ስለ፡ መጠባበቅ ።

(፩) ከስምምነቱ፡ መጽደቅ ፡ በኋላ ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎችና ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ኮሚቴ፡ ስለ፡ ስምምነቱ ፡ መጽደቅ ፡ በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ በተወሰኑት ፡ አደራረጎች ፡ መሠረት፡ የስምምነቱን ፡ መፈጸም ፡ ይጠባበቃሉ ።

(፪) የስምምነቱ ፡ ውለታዎች ፡ ከተፈጸሙ፡ በኋላ ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ኮሚቴ፡ ለንብረቱ ፡ የተሰጠው ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ እንዲነሣ ፡ ለመፍቀድ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

## ቍ ፡ ሺ፷፱ ። ስለ፡ ስምምነቱ ፡ ውጤቶች ።

(፩) የንብረት ፡ መያዣ፡ ካላቸውና ፡ መያዣቸውንም ፡ ካልለቀቁት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፤ እንዲሁም ፡ መብታቸውን ፡ ያገኙት ፡ የመክሠሩ ፡ አሠራር ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ከሆኑት ፡ መያዣ ፡ ከሌላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በቀር ፡ የስምምነቱ ፡ መጽደቅ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎችን ፡ ሁሉ ፡ ያስገድዳል ።

(፪) በቍጥር፡ ሺ፮፡ መሠረት፡ በከሠረው፡ ሰው ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ላይና፡ እንዲሁም፡ በቍጥር ፡ ሺ፯ ፡ መሠረት ፡ በንግዱ ፡ ላይ ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ያላቸውን ፡ በንብረቱ ፡ ስም ፡ የተመዘገበውን ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ የስምምነቱ ፡ መጽደቅ ፡ አይለውጠውም ። ስለዚሁም ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ፡ ስለ፡ስምምነቱ ፡

መጽደቅ ፡ የተሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ያስመዘግቡታል ።

(፫) ስምምነቱ፡ ቢኖርም ፡ ቅሉ ፤ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ስለሚጠይቁት ፡ ሙሉ ፡ ገንዘብ ፡ በባለዕዳው፡ የጋራ፡ ተገዳጆች ፡ ላይ፡ ያላቸውን፡ የክስ ፡ ማቅረብ ፡ መብት ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ይቈያሉ ።

ቍ ፡ ሺ፺ ። ስለ፡ መክሠሩ ፡ ውጤቶች ፡ መቅረት ።

(፩) ስለ፡ስምምነቱ፡ መጽደቅ ፡ የተሰጠው፡ ፍርድ ፡ የመጨረሻ ፡ ፍርድ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ወዲያው ፡ ስለ፡መብት ፡ እጦት ፡ በቍጥር ፡ ሺ፷፱ ፡ የተጻፈው ፡ ቃልና ፡ ለስምምነቱ ፡ አፈጻጸም፡ በቍጥር ፡ ሺ፹፰ ፡ የተደነገጉት ፡ ድንጋጌዎች፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ የመክሠሩ ፡ ውጤቶች ፡ ይቀራሉ ።

(፪) ንብረት፡ ጠባቂዎቹ ፤ በመርማሪው፡ ዳኛና፡ በገንዘብ፡ ጠያቂዎች፡ ኮሚቴ፡ፊት፤ ለባለዕዳው ፡ የመጨረሻውን ፡ ሒሳብ ፡ ያስረክባሉ ። በዚህም ፡ ሒሳብ ፡ ክርክር ፡ ከተደረገበት ፡ በኋላ ፡ ሒሳቡን ፡ ያቆማሉ ። ለባለዕዳው ፤ ንብረቶቹን ፤ መዝገቦቹን ፤ ወረቀቶቹንና ፡ ዕቃዎቹን ፡ በሙሉ ፡ ይመልሳሉ ። ባለዕዳውም ፡ ደረሰኝ ፡ ይሰጣቸዋል ። ባለዕዳው ፡ ሳይረከባቸው ፡ ቢቀር ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ የመጨረሻውን ፡ ሒሳብ ፡ ካሰናዱበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ለሁለት ፡ ዓመት ፡ ብቻ ፡ ኀላፊዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፫) ለዚህ ፡ ሁሉ፡ መርማሪው፡ ዳኛ ፡ አንድ ፡ ፕሮሴቨርባል ፡ ያዘጋጃል ። ክርክር ፡ በሚነሣበት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጥበታል ።

ቍ ፡ ሺ፺፩ ። ከጸደቀ ፡ በኋላ ፡ ስለ፡ ስምምነቱ ፡ መፍረስ ።

(፩) ከስምምነቱ ፡ መጽደቅ ፡ ወዲህ ፡ በተገለጸው ፡ ተንኰል ፡ ምክንያት ፡ ካልሆነና ፤ ተንኰሉም ፡ የተገኘውን ፡ ሀብት ፡ ከመደበቅ ፡ ወይም ፡ ዕዳውን ፡ ከማጋነን ፡ የተፈጠረ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ ስምምነቱ ፡ ከጸደቀ ፡ በኋላ ፡ እንዲፈርስ ፡ የሚቀርበው ፡ ማናቸውም ፡ ክስ ፡ አይሰማም ። ይኸንንም ፡ ክስ ፡ አንድ፡ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ራሱ ፡ ሊያቀርበው ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፤ ተንኰሉ ፡ በተገለጸ ፡ በአምስት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፪) የከሠረው ፡ በተንኰል ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ፍርድ ፡ የተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተደረገው ፡ ስምምነት ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ። ይኸውም ፡ የስምምነቱ ፡ መፍረስ ፡ ለተንኰሉ ፡ ግብረ ፡ አበሮች ፡ ከሆኑት ፡ በቀር ፤ ዋሶቹን ፡ ሁሉ ፡ በደንብ ፡ ነጻ ፡ ያወጣቸዋል ።

ቍ ፡ ሺ፺፪ ። ከስምምነቱ ፡ መጽደቅ ፡ በኋላ ፤ በተገለጸው ፡ ተንኰል ፡ ምክንያት ፡ ክስ ፡ በሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚደረጉ ፡ መጠባበቂያዎች ።

(፩) ከስምምነቱ ፡ መጽደቅ ፡ በኋላ ፤ ባለዕዳው ፡ በተንኰል ፡ መክሠር ፡ ተከሶ ፡

የተቀጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፤ አስፈላጊ ፡ መስለው ፡ የታዩትን ፡ የመ ጠባበቂያ ፡ ሥራዎች ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) እነዚሁ ፡ አስፈላጊ ፡ ሥራዎች ፤ የሚያስከስስ ፡ ነገር ፡ የለውም ፡ ከተባለበት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ የከሠረው ፡ ሰው ፡ በነጻ ፡ ከተለቀቀበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በደንብ ፡ ይቀራሉ ።

<u>ቍ ፡ ሺ፺፫ ። ስምምነቱን ፡ ስለ ፡ መሰረዝ ።</u>

(፩) ባለዕዳው ፡ የስምምነቱን ፡ ውሎታዎች ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያሉም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ዋሶች ፡ ባሉበት ፡ ወይም ፡ በሚገባ ፡ ከተጠሩ ፡ በኋላ ፡ ስምምነቱ ፡ እንዲፈርስ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማመልከት ፡ ይቻላል ።

(፪) ስምምነቱ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዲፈጸም ፡ ዋስ ፡ የሆኑትን ፡ ሰዎች፡ የስምምነቱ ፡ መፍረስ ፡ ነጻ ፡ አያወጣቸውም ።

<u>ቍ ፡ ሺ፺፬ ። ስምምነቱ ፡ ከተሰረዘ ፡ ወይም ፡ ከፈረሰ ፡ በኋላ ፡ የመክሠሩን ፡ አሠራር ፡ እንደገና ፡ ስለ ፡ መቀበል ።</u>

(፩) ስምምነቱ ፡ የተሰረዘ ፡ ወይም ፡ የፈረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስቀድሞ፡ በተጻፈው፡ የዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ መሠረት ፤ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ሳይዘገዩ ፤ አሽጎ ችም ፡ እንዳሉ ፡ ያሸገው፡ባለሥልጣን ፡ እየረዳቸው ፡ የተቈጠሩትን ፡ ባለዋጋ፡የሆ ኑትን ፡ ዕቃዎችና ፡ ወረቀቶችን ፡ ማረጋገጥ ፡ ይጀምራሉ ። አስፈላጊ ፡ ሲሆ ንም ፡ ተጨማሪ ፡ የዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብና ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ ያዘጋጃሉ ።

(፪) ወዲያውም ፡ በፍጥነት ፤ ስለዚሁ ፡ የተፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ ቅጅና ፤ አዲስ፡ ገን ዘብ ፡ ጠያቂዎችም ፡ እንዳሉ ፤ ገንዘብ ፡ የሚጠይቁባቸውን ፡ ሰነዶች ፤ በቍጥር፡ ሺ፺፫ ፡ በተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ መሠረት ፡ ለምርመራ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ በማሳሰብ ፡ ማስታወቂያ ፡ ያወጣሉ ።

<u>ቍ ፡ ሺ፺፭ ። የቀረቡትን ፡ አዲስ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብቶች ፡ ስለ ፡ መመርመር።</u>

(፩) በቍጥር ፡ ሺ፺፬ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የቀረቡትን ፡ የገንዘብ ፡ መጠ የቂያ ፡ ሰነዶች ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ይመረምራሉ ።

(፪) አስቀድሞ ፡ ተቀባይነት ፡ አግኝተው፡ ስለነበሩት፡ የገንዘብ፡ መጠየቂያ ፡ መብ ቶች፡ አዲስ ፡ ምርመራ ፡ አይደረግም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ የተከፈሉትን ፡ ያለመቀበል ፡ ወይም ፡ የመቀነስ ፡ መብት ፡ ሳይነካ ፡ ነው ።

<u>ቍ ፡ ሺ፺፮ ። ስምምነቱ ፡ ከጸደቀ ፡ በኋላ ፡ ባለዕዳው ፡ ስላደረጋቸው ፡ ውሎች ።</u>

ስምምነቱ ፡ በፍርድ ፡ ከመጽደቁ ፡ በኋላና ፡ ከስምምነቱ ፡ መሰረዝ ፡ ወይም ፡ መፍረስ ፡ በፊት ፡ ባለዕዳው ፡ ያደረጋቸው ፡ ውሎች ፤ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ተንኰል ፡ በማድረግ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ ፈራሽ ፡ አይሆኑም ።

**ቍ ፡ ሺ፺፯ ። ከስምምነቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ስላሉት ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መብት ።**

ከስምምነቱ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ባለዕዳውን ፡ ብቻ ፡ በሚ መለከት፡ ጉዳይ ፤ ሙሉ ፡ መብታቸውን ፡ እንደገና ፡ መልሰው ፡ ይይዛሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተመለከቱት ፡ መጠኖች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ ከኀብረቱ ፡ ውስጥ ፡ ለማግኘት ፡ አይችሉም ። ይኸውም ፤

(ሀ) እንዲከፈላቸው ፡ ከጠየቁት፡ ገንዘብ ፡ ምንም ፡ ድርሻ ፡ ያልወሰዱ ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ለሚጠይቁት ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፤

(ለ) ገንዘብ፡ ጠያቂዎች ፡ ከሚገባቸው ፡ ድርሻ፡ በከፊል ፡ ተቀብለው ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ በሚቀራቸው ፡ ድርሻ ፡ ልክ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ሺ፺፰ ። ከስምምነቱ ፡ በኋላ ፡ አዲስ ፡ ለሆኑት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ገንዘባቸው ፡ ባለመከፈሉ ፡ ምክንያት ፡ ሁለተኛ ፡ ስለሚደረግ ፡ የመክሠር ፡ ማስታወቅ ።**

ስምምነቱ ፡ ሳይሰረዝ ፡ ወይም ፡ ሳይፈርስ ፡ ከስምምነቱ ፡ በኋላ ፡ አዲስ ፡ የመ ጡት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ይከፈለን ፡ የሚሉት ፡ ገንዘብ ፡ ሳይከፈላቸው ፡ በመቅ ረቱ ፡ ምክንያት ፡ ሁለተኛ ፡ የኪሣራ ፡ ማስታወቂያ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሲሆን ፤ በፊ ተኛው፡ የኪሣራ፡ ማስታወቅ፡ ጊዜ፡ የነበሩት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በሁለተኛው፡ የኪሣራ ፡ ማስታወቅ ፡ ጊዜም፡ የዕዳ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ይሆናሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ጠያቂነታቸው ፡ የተነሣ ፡ አዲሶቹን ፡ ጠያቂዎች ፡ በሚመለከት ፡ ነገር ፡ ምንም፡ ብልጫ፡ አለን ፡ ለማለት፡ አይችሉም ፡ በቍጥር ፡ ሺ፺፯ ፡ የተወሰኑትም ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይፈጸሙባቸዋል ።

**ቍ ፡ ሺ፺፱ ። ንብረትን ፡ በመልቀቅ ፡ ስለሚደረግ ፡ ስምምነት ።**

(፩) የከሠረው፡ ሰው ፡ ያለውን ፡ ንብረት ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ በመልቀቅ ፡ ስምምነት ፡ ሊያግድ ፡ ይችላል ። ይህ ፡ የተባለው ፡ ስምምነት ፤ ልክ ፡ ለመደበ ኛው ፡ ስምምነት ፡ የሚሰጡትን ፡ ደንቦች ፡ በመከተል ፡ ይፈጸማል ። የሚሰጣ ቸውም ፡ ውጤቶች ፡ እንደነዚያው ፡ ያሉ ፡ ውጤቶች ፡ ናቸው ። የሚሰረዘውም ፡ የሚፈርሰውም ፡ መደበኛው ፡ ስምምነት ፡ በሚሰረዝባቸውና ፡ በሚፈርስባ ቸው፡ ምክንያቶች ፡ ነው ።

(፪) የተለቀቀውንም፡ ንብረት፡ የማጣራት፡ ሥራ ፡ በቍጥር፡ ሺ፶፩ ፡ እና፡ በተከታ ዮቹ ፡ በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማል ።

(፫) ያለውን ፡ ንብረት ፡ በመልቀቅ ፡ የሚደረገው ፡ ስምምነት ፤ በተለቀቀው፡ ንብ ረት ፡ ውስጥ ፡ ያልገቡትንና ፡ የከሠረው ፡ ሰው ፡ በኋላ ፡ የሚያገኛቸው፡ ንብረ ቶች ፡ እንዳይያዙ ፡ ያደርጋል ።

(፬) ስምምነቱ ፡ ቢኖርም ፡ ቅሉ ፤ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ከባለዕዳው ፡ በጋራ ፡ ተገ ዳጅ ፡ በሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ መብታቸውን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ይቈያሉ ።

BACK



**ቍ ፡ ሺ፻ ። በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ስለ ፡ መግባት ።**

ስምምነቱ ፡ የጸደቀበት ፡ ወይም ፡ የፈረሰበት ፡ ወይም ፡ የተሰረዘበት ፡ ፍርድ ፡ በቍጥር ፡ ፱፻፹፫ ፡ (፬) በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ የፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ መግባታቸውን ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ።

ክፍል ፡ ፪ ።

**በግዴታ ፡ የሚሆን ፡ የንብረት ፡ ማጣራት ።**

**ቍ ፡ ሺ፻፩ ። ስምምነቱን ፡ ያለመቀበል ፡ ስለሚያስከትላቸው ፡ ውጤቶች ።**

ስለ፡ስምምነቱ ፡ የቀረበው ፡ አሳብ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፹፬ ፡ የሚያስገድደውን ፡ ዕጥፍ ፡ የሆነውን ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ፡ ያላገኘ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ንብረቱ ፡ በግድ ፡ እስኪሸጥና ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹም ፡ የሽያጩን ፡ ድርሻ ፡ ጨርሰው ፡ እስኪከፋፈሉ ፡ ድረስ ፡ የመክሠሩ ፡ ሥራዎች ፡ ሳያቋርጡ ፡ ይቀጥላሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፻፪ ። ለከሠረው ፡ ሰው ፡ ስለሚደረገው ፡ ዕርዳታ ።**

ከሚከፋፈለው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ለከሠረው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ ርዳታ፡ ለመስጠት ፡ ይቻል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለማወቅ ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂ ዎቹን ፡ ኮሚቴ ፡ ያማክራል ። ኮሚቴው ፡ አሳቡን ፡ በመልካም ፡ የተቀበለው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ባቀረቡት ፡ አሳብ ፡ መሠ ረት ፡ የተፈቀደውን ፡ ርዳታ ፡ ልክ ፡ ይወስናል ።

**ቍ ፡ ሺ፻፫ ። ስለ፡ ንብረቱ፡ ማጣራት ፡ ሥራዎች ።**

(፩) ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፤ የባለዕዳውን ፡ የሚንቀሳቀሱትንና ፡ የማይንቀሳቀሱትን ፡ ንብረቶች ፡ ይሸጣሉ ። ባለዕዳውም ፡ ለነዚህ ፡ ሥራዎች ፡ መጠራት ፡ የለበትም ።

(፪) ከሽያጩም ፡ የተገኘው ፡ ገንዘብ ፡ በቍጥር ፡ ፱፻፺፯ ፡ በተመለከተው፡መሠረት፡ ይቀመጣል ።

(፫) ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ባለዕዳው ፡ ሳይጠራ ፤ በቍጥር ፡ ሺ፴፰ ፡ እንደተመለ ከተው ፡ ስለማንኛውም ፡ ዐይነት ፤ የባለዕዳውን ፡ መብቶች ፡ የሚመለከቱ ፡ ስም ምነቶችንና ፡ ግልግሎችን ፡ ለማድረግ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፻፬ ። የማይንቀሳቀሱትን ፡ ንብረቶች ፡ ስለ ፡ መሸጥ ።**

ግዴታ ፡ የሆነው ፡ ማጣራት ፡ ከመከፈቱ ፡ በፊት ፡ የተጀመረ ፡ የማይንቀሳቀሱ ትን ፡ ንብረቶች ፡ የማስለቀቅ ፡ ሥራ ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የመሸጥን ፡ ሥራ፡ለመ ሥራት ፡ የሚችሉት ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። እነርሱም ፡ በመርማ ሪው ፡ ዳኛ ፡ ፈቃድ ፡ በስምንት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ሥራውን ፡ ለመጀመር ፡ ይገደዳሉ ።

**ቍ ፡ ፲፻፮ ። የንግድ ፡ መደብርን ፡ ስለ ፡ መሸጥ ።**

የነጋዴው ፡ ንብረት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲጣራ ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ የንግድ ፡ መደብሩ ፡ እንዲያዝ ፡ የታዘዘ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ የንግድ ፡ መደብሩ ፡ እንዲሸጥ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ለማድረግ ፡ የሚችሉት ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። እነሱም ፡ በመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ፈቃድ ፤ በቍጥር ፡ ፲፩፻፮ ፡ የተመለከተው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፡ የንግዱን ፡ መደብር ፡ ለመሸጥ ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፲፻፯ ። በማጣራቱ ፡ ጊዜ ፡ ሥራውን ፡ ስለ ፡ መቀጠል ።**

(፩) ዋስትና ፡ የሌላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መክሠሩ ፡ በሚጠራበት ፡ ጊዜ ፡ ሥራውን ፡ እንዲቀጥሉ ፡ ለንብረት፡ጠባቂዎች፡ውክልናቸውን፡ሊሰጡ፡ይችላሉ ።

(፪) ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ኮሚቴ ፡ አሳሳቢነት ፤ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹን ፡ በሬኮማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ አሳባቸውን ፡ ይጠይቃቸዋል ። ከብዛታቸው ፡ የተነሣ ፡ ሊያንዳንዱ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለመላክ ፡ ያልቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፹፪ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፫) የተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ይፈጸማሉ ።

(፫) ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ድምፃቸውን ፡ ለፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ መስጠት ፡ እንዳለባቸው ፡ ይነገራቸዋል ።

(፬) ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹም ፡ የሥራው ፡ መቀጠል ፡ የሚቈይበትን ፡ ጊዜና ፡ የሥራውን ፡ ወሰን ፡ ይወስናሉ ። እንዲሁም ፡ ለወጪዎችና ፡ ኪሣራዎች ፡ መክፈያ የሚሆን ፡ በንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ እጅ ፡ የሚቈየውን ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ ይወስናሉ ። ውሳኔውም ፡ በቍጥርና ፡ በገንዘብ ፡ ሦስት ፡ ሩብ ፡ የሆነ ፡ አጠፌታ፡የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ያለው ፡ እንዲሆን ፡ ያስፈልገዋል ። ይህንንም ፡ የሚያጸድቀው፡ የመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፻፰ ። ያለውን ፡ ጠቅላላ ፡ ሀብት ፡ በአንደዜ ፡ ስለ ፡ መሸጥ ።**

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፤ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ የሚለውን ፡ ሰምቶ ፡ ያለውን ፡ ንብረት፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ እና ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ በቍርጥ ፡ ዋጋ ፡ ባንደዜ ፡ እንዲሸጡዋቸው ፡ ለንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ሊፈቀድላቸው ፡ ይችላል ።

(፪) የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ኮሚቴ ፡ ወይም ፡ ባለዕዳው ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ፡ ይህን ፡ ፈቃድ ፡ ለመስጠት ፡ ይቻላል ።

(፫) በሁለቱም ፡ ጊዜ ፡ ለሚቀርበው ፡ ጥያቄ ፤ በቍጥር ፡ ፲፻፯ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፬ ፡ በተደነገጉት ፡ ሁናቴዎች ፡ መሠረት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ አሳባቸውን ፡ ይጠየቃሉ ፤ የሰጡትም ፡ ድምፅ ፡ በቍ ፡ ፲፻፯ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ ፬ ፡ መሠረት ፡ በቍጥርም ፡ ሆነ ፡ በገንዘብ ፡ ከአራት ፡ ሦስት ፡ እጅ ፡ የሆነ ፡ አጠፌታ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ያለው ፡ እንዲሆን ፡ያስፈልገዋል ።

(፬) የውሉን ፡ ዕቅድ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲያጸድቀው ፡ ያስፈልጋል ።

(፭) ውሉም ፡ የጸደቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በንብረቱ ፡ በኩል ፡ ባለዕዳውን ፡ ነጻ ፡ ያደርገዋል ።

ቁ ፡ ሺ፻፹፫ ። ከሚጣራው ፡ ንብረት ፡ ስለሚበልጡ ፡ ግዴታዎች ።

የንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ ሥራዎች ፤ በመጣራት ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ ንብረት ፡ በላይ ፡ የሆኑት ፡ ግዴታዎች ፡ ያስከተሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በድምሩ ፡ መጋጠት ፤ ሥራዎቹን ፡ የፈቀዱት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ብቻ ፡ በንብረቱ ፡ ውስጥ ፡ ከሚደርሳቸው ፡ ድርሻ ፡ በላይ ፡ ለሆነው ፡ ገንዘብ ፡ ራሳቸው ፡ አላፊዎች ፡ ናቸው ። ይኸውም ፡ የሚሆነው ፡ በሰጡት ፡ ሥልጣን ፡ መጠን ፡ ነው ። በሚገባቸውም ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ለግዴታዎቹ ፡ ተካፋይ ፡ ይሆናሉ ።

ቁ ፡ ሺ፻፹፬ ። ስለ ፡ አከፋፈሉ ፡ ድርጅት ።

(፩) በቍጥር ፡ ሺ፹፯ ፡ የተመለከተው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ አንሥቶ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ በየሁለቱ ፡ ወር ፡ የኪሣራውን ፡ ሁኔታ ፡ የሚያስረዳ ፡ መግለጫና ፡ በቍጥር ፡ ፱፻፲፯ ፡ መሠረት ፡ የተቀመጠውን ፡ ገንዘብ ፡ ዝርዝር ፡ ለመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ያስረክባሉ ።

(፪) የነዚህንም ፡ ገንዘቦች ፡ አከፋፈል ፡ ድርጅት ፡ ለዳኛው ፡ ያቀርባሉ ።

(፫) ዳኛውም ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹን ፡ ኮሚቴ ፡ ካማከረ ፡ በኋላ ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ማሻሻል ፡ በክፍያው ፡ ድርጅት ፡ ላይ ፡ አስፍሮ ፡ የተሻሻለው ፡ ድርጅት ፡ በፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ እንዲቀመጥ ፡ ያዛል ። የድርጅቱንም ፡ መቀመጥ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ እንዲያውቁት ፡ ያደርጋል ።

(፬) ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹም ፡ ማስታወቂያው ፡ ከተሰጣቸው ፡ በዐሥር ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ስለድርጅቱ ፡ አስተያየታቸውን ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ። ይህ ፡ የተባለው ፡ ጊዜ ፡ ሲያልፍ ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ማስገንዘቢያዎቹን ፤ ተመልክቶ ፡ ክፍያውን ፡ የሚወስን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጣል ።

ቁ ፡ ሺ፻፹፭ ። ከማጣራቱ ፡ የተገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ ማከፋፈል ።

ከማጣራቱ ፡ ከተገኘው ፡ ገንዘብ ፤

(ሀ) ለመክሠሩ ፡ አሠራር ፡ የወጣው ፡ ኪሣራና ፡ የተደረገው ፡ ወጪ ፡ ገንዘብ ፤

(ለ) እንዳለም ፤ ለባለዕዳውና ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ የተደረገው ፡ ርዳታ ፤

(ሐ) ልዩ ፡ መብት ፡ ላላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የተከፈለው ፡ ገንዘብ ፤ ከተቀነሰ ፡ በኋላ ፡ የሚቀረውን ፡ ገንዘብ ፤ በቍጥር ፡ ሺ፸፩-ሺ፸፯ ፡ እና ፡ ሺ፸፰ ፡ የተመለከተው ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ሆኖ ፤ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ሁሉ ፡ በተረጋገጠላቸውና ፡ ተቀባይነት ፡ ባገኘው ፡ መብታቸው ፡ መጠን ፡ ይከፋፈሉታል ።

ቁ ፡ ሺ፻፹፮ ፡ ክርክር ፡ ያለባቸውን ፡ የገንዘብ ፡ መብቶች ፡ ድርሻ ፡ ጠብቆ ፡ ስለ ፡ ማቈየት ።

ተቀባይነት ፡ ስለ ፡ ማግኘታቸው ፡ ገና ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ ያልተሰጣቸው ፡ መብቶች ፡ ድርሻ ፡ ተጠብቆ ፡ ይቀመጣል ።

**ቍ ፡ ፲፻፲፪ ። ስለ ፡ አከፋፈሉ ፡ ሥርዐት።**

(፩) ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ በቍጥር ፡ ፱፻፺፯ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ በኪሣራው፡ስም ፡ ለመከፈሉ ፡ አሠራር ፡ ከተከፈተው ፡ ሒሳብ ፡ ላይ ፤ መብቱ ፡ ተቀባይነት፡ላገኘው ፡ ለያንዳንዱ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ለሚደርሰው ፡ ክፍያ ፡ በስሙ ፡ የተጻፈ ፡ ቼክ ፡ ይልኩለታል ።

(፪) የተከፈለው ፡ ገንዘብ ፤ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ባቀረበው ፡ ሰነድ ፡ ላይ፡ይጻፋል። ነገር ፡ ግን፡ ሰነዱን ፡ ለማቅረብ ፡ በማይቻልበት ፡ ጊዜ ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ የተቀመጠውን ፡ የዕዳ ፡ ሁኔታ ፡ የሚገልጸውን ፡ ፕሮሲቬርባል ፡ ተመልክቶ ፡ ክፍያውን ፡ ለመፍቀድ ፡ ይችላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

## የመክሠሩ ፡ ሥራ ፡ መዘጋት ።

**ቍ ፡ ፲፻፲፫ ። የመክሠሩ ፡ ሥራ ፡ ስለሚዘጋባቸው ፡ ምክንያቶች ።**

ስለ ፡ ስምምነቱ ፡ በቍጥር ፡ ፱፻፹፩ ፡ እስከ ፡ ፲፻፱ ፡ የተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፡ የመክሠሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የሚዘጋው ፤

(ሀ) ከማይነቃ ፡ ማጣራት ፡ የተገኘውን፡ ገንዘብ ፡ ጨርሶ ፡ በማከፋፈል ፤

(ለ) የሚበቃ ፡ ንብረት ፡ ባለመኖሩ ፤

(ሐ) ከንብረቱ ፡ የሚፈለግ ፡ ዕዳ ፡ ባለመኖሩ ፡ ነው ።

**ቍ ፡ ፲፻፲፬ ። የሚበቃ ፡ ንብረት ፡ ባለመኖሩ ፡ ስለሚሆን ፡ መዘጋት ።**

(፩) የመክሠሩ ፡ ሥራዎች ፤ የሚበቃ ፡ ንብረት ፡ ባለመኖሩ፡ ለመቀጠል፡ያልቻሉ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፤ መርማሪው፡ ዳኛ ፡ ያቀረበውን ፡ መግለጫ፡መሠረት፡ በማድረግ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሥልጣኑ ፡ የሥራዎቹን፡መዘጋት፡ ለመወሰን፡ይችላል ።

(፪) ይኸውም ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፤ ለያንዳንዱ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ በግል ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ ይመልስለታል ።

(፫) የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የከሠረው ፡ ሰው ፡ ንብረቶችን ፡ የማስተዳደርን ፤ በንብረቶቹ ፡ የማዘዝን ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ለቀቀ ፡ ይቈያል ። እንዲሁም ፡ አዲስ ፡ የገባባቸው ፡ ዕዳዎች ፡ በንብረቱ ፡ ላይ፡ መቃወሚያ፡ ሊሆኑ፡አይችሉም ። ንብረቱም፡ ከአዲሶቹ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ጋራ ፡ ተካፋይ ፡ መሆን ፡ የለበትም ።

**ቍ ፡ ፲፻፲፭ ። የሚበቃ ፡ ንብረት ፡ ባለመኖሩ ፡ ለተደረገው ፡ መዘጋት ፡ የተሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ስለማሻር ።**

(፩) ባለዕዳው ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፤ ለሥራዎቹ ፡ ወጪዎች ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ መኖሩን ፡

በማስረዳት ፤ ወይም ፡ ለወጪዎቹ ፡ በቂ ፡ የሚሆነውን ፡ ገንዘብ ፡ በንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ እጅ ፡ በማስቀመጥ ፡ ስለ፡ተደረገው ፡ መዘጋት፡ የተሰጠው፡ ፍርድ፡ እንዲሻር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

(፪) በማንኛዎቹም ፡ ሁኔታዎች ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፲፩ ፡ መሠረት ፡ ለተፈጸሙት ፡ የክስ ፡ ሥራዎች ፡ ወጪ ፡ የሆኑት ፡ ኪሣራዎች ፡ አስቀድሞ ፡ መከፈል ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፲፻፲፯ ። ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ላልጠየቁዋቸው ፡ ሰነዶች ፡ በንብረት ፡ ጠባቂዎቹ፡ ስላለባቸው ፡ አላፊነት ።**

ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ላልጠየቁዋቸው ፡ ሰነዶች ፡ የመክሠር ፡ ማስታወቂያው ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፲፻፲፰ ። ከንብረቱ ፡ የሚፈለግ ፡ ዕዳ ፡ ባለመኖሩ ፡ ስለሚደረግ ፡ መዘጋት ።**

(፩) በቍጥር ፡ ፲፻፺፩ ፡ የተመለከቱት ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ ሰነዶች ፡ ዝርዝር ፡ ጽሑፍ ፡ ለፍርድ ፡ የመዝገብ ፡ ቤት ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፤ ባለዕዳው ፡ ማስረጃቸውን ፡ ላቀረቡ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ሁሉ ፡ መክፈሉን ፡ ወይም ፡ ማስረጃ ፡ ላቀረቡት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ሁሉ ፡ በደንብ ፡ ለማደላደል ፡ አስፈላጊውን ፡ ገንዘብ ፤ እንዲሁም ፡ እስከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ስለ ፡ መክሠሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የወጡትን ፡ ወጪዎች ፡ የንብረት ፡ ጠባቂዎችንም ፡ ዋጋ ፡ ጭምር ፡ በንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ እጅ ፡ ማስቀመጡን ፡ ያስረዳ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ባለዕዳው ፡ ባቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፤ የመክሠሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በሚፈጸምበት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፤ የመክሠሩን ፡ መዘጋት ፡ ሊፈርድ ፡ ይችላል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔውን ፡ የሚሰጠው ፡ እነዚህ ፡ የተባሉትን፡ሁኔታዎች ፡ መፈጸም ፡ የሚያመለክተውን ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ያቀረበውን ፡ መግለጫ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

(፪) ፍርዱ ፤ ለባለዕዳው ፡ እንደገና ፡ መብቶቹን ፡ መልሶ ፡ በመስጠትና ፡ መብቶቹን ፡ ካሳጡት ፡ ውሳኔዎች ፡ ነጻ ፡ በማድረግ ፡ በመክሠሩ ፡ የተከፈተውን ፡ ሥነ ሥርዐት ፡ ጨርሶ ፡ ይዘጋል ።

**ቍ ፡ ፲፻፲፱ ። በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ስለ ፡ መመዝገብ ።**

ያለው ፡ ሀብት ፡ የማይበቃ፡ በመሆኑ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ ከንብረቱ ፡ ገንዘብ፡ የመጠየቅ ፡ መብት ፡ ባለመኖሩ ፡ ምክንያት ፤ ስለ ፡ መክሠር ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ እንዲዘጋ ፡ የተወሰነውን፡ፍርድ፡ በቍጥር ፡ ፻፷፫ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) መሠረት፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ማስገባት ፡ አለበት ።

BACK



## አንቀጽ ፡ ፫ ።

## የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ።

**ቍ ፡ ሺ፻፲፱ ። ስለ ፡ መጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ የሚቀርብ ፡ ጥያቄ ።**

ማናቸውም ፡ ዕዳውን ፡ መክፈል፡ አቋርጦ፡ ወይም ፡ ሊያቋርጥ ፡ ደርሶ ፡ የመክሠር ፡ ማስታወቂያ ፡ ያልተፈረደበት ፡ ነጋዴ ፤ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ ሥን ፡ ሥርዐት ፡ እንዲከፈትለት ፡ ፍርድ፡ ቤቱን ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ሺ፻፳ ። ስለ፡ ጥያቄው፡ አቀባበል፡ ሁኔታዎች ።**

(፩) ስለ ፡ መጠበቂያው ፡ ስምምነት ፡ የሚቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ተቀባይነት ፡ እንዲያገኝ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ በማስታወቂያ ፡ ጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ ለፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

(፪) በቍጥር ፡ ፱፻፹፫ ፡ ከተመለከቱት ፡ ዝርዝሮች ፡ ጋራ ፡ ባለዕዳው ፡ ዕዳዎቹን ፡ ከመክፈል ፡ ያቋረጠበትን ፡ ወይም ፡ ሊያቋርጥ ፡ ያሰበበትን ፡ ምክንያቶችና ፡ የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ የጠየቀበትንም ፡ ምክንያት ፡ የሚያመለክት ፡ መግለጫ ፡ ጨምሮ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

(፫) ከዚህም ፡ በቀር ፡ ባለዕዳው ፤

(ሀ) እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ ወይም ፤ የንግዱን ፡ ሥራ ፡ የጀመረው ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ይህን ፡ ሥራ ፡ ከጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ መጻፉን ፤

(ለ) በተመለከተው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ደንበኛ ፡ የሒሳብ ፡ አያያዝ ፡ መዝገብ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፤

(ሐ) በአለፉት ፡ አምስት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ የመክሠር ፡ ማስታወቂያ ፡ ፍርድ ፡ ያልወጣበት ፡ የመጠባበቂያ ፡ ስምምነትም ፡ ያልተደረገበት ፡ መሆኑን ፤

(መ) በራሱ ፡ ጥፋት ፡ በተንኰል ፡ በሕግ ፡ የተከለከለውን ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፰ ፡ እስከ ፡ ፯፻፳፰ ፡ የተመለከቱትን ፡ ወንጀሎች ፡ ሠርቶ ፡ በመገኘት ፡ ያልተቀጣ ፡ መሆኑን ፡ ማስረዳት ፡ አለበት።

**ቍ ፡ ሺ፻፳፩ ፡ በሚቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገለጹት ፡ አሳቦች ።**

(፩) የሚቀርበው ፡ ጥያቄ ፤ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ያሉትን ፡ አሳቦች ፡ የያዘ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

(ሀ) ዋስትና ፡ የሌላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ከሚጠይቋቸው ፡ ዕዳዎች ፡ ዋና ፡ ገንዘብ፡ላይ ፡ ስምምነቱ ፡ ከጸደቀበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ በአንድ ፡ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ቢያንስ ፡ ኀምሳ ፡ በመቶ ፤ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ የዐሥራ ፡ ስም

BACK



ንት ፡ ወር ፡ ሲሆን ፤ ሰባ ፡ አምስት ፡ በመቶ ፤ የተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ የሆን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መቶ ፡ በመቶ ፡ ለመክፈል ፡ ቃል ፡ መስጠትን ፤

(ለ) ከዚሀ ፡ በላይ ፡ በ(ሀ) የተሰጠውን ፡ ቃል ፡ ለመፈጸም ፡ የሚያረጋግጥ ፡ የዕቃ ፡ ወይም ፡ የሰው ፡ ዋሶች ፡ ለመስጠት ፡ ቃል ፡ መስጠትንና ፡ ለዋስትና ፡ የሚጠሩትን ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ዕቃዎች ፡ ዝርዝር ፡፡

(፪) ባለዕዳው ፡ የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ እንዲደረግለት ፡ ጥያቄውን ፡ ባቀረበበት ፡ ጊዜ ፡ ያለውን ፡ ንብረት ፡ ሁሉ ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ሁሉ ፡ በመልቀቅ ፡ መስማማትን ፡ ሊመርጥ ፡ የሚችለው ፤ የንብረቶቹ ፡ ግምት ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) ውስጥ ፡ በተመለከተው ፡ መጠን ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ የሚጠይቁትን ፡ ዕዳ ፡ ለመክፈል ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡፡

**ቍ ፡ ፲፻፷፪ ፡ ጥያቄውን ፡ ስላለመቀበል ፡፡**

በቍጥር ፡ ፲፻፷፩ ፡ ከተነገሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ አንዱ ፡ ሳይፈጸም ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፤ የሕግ ፡ አስከባሪውን ፡ ቃል ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ መጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ የቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ የማይቀበለው ፡ መሆኑን ፡ ያስታውቃል ፡፡

**ቍ ፡ ፲፻፷፫ ፡፡ ጥያቄውን ፡ ስላለመቀበል ፡ ተጨማሪ ፡ ምክንያቶች ፡፡**

(፩) ጥያቄው ፡ ተቀባይነት ፡ ሊያገኝ ፡ በሚችልበት ፡ ጊዜ ፡ ቢሆንም ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ባለዕዳው ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፷፩ ፡ መሠረት ፡ የሰጠውን ፡ ቃል ፡ ለመፈጸም ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ የገመተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፤ ጥያቄውን ፡ አልቀበልም ፡ ሊል ፡ ይችላል ፡፡

(፪) ባለዕዳው ፡ ሱቁን ፡ ዘግቶ ፡ ሸሽቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የራሱ ፡ ከሆነው ፡ ገንዘብ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ በተንኰል ፡ ደብቆ ፡ ወይም ፡ ቀንሶ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጥያቄውን ፡ አልቀበልም ፡ ማለት ፡ አለበት ፡፡

(፫) በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፷፪ ፡ የተመለከቱት ፡ ሁኔታዎች ፡ ባጋጠሙ ፡ ጊዜ ፤ ባለዕዳው ፡ ዕዳውን ፡ ለመክፈል ፡ ያቋረጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነጋዴው ፡ ከሥሮዋል ፡ ሲል ፡ በሥልጣኑ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ፡፡

**ቍ ፡ ፲፻፷፬ ፡፡ ስለ ፡ ክስ ፡ አቤቱታ ፡፡**

(፩) በቍጥር ፡ ፲፻፷፪ ፡ እና ፡ ፲፻፷፫ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) እና ፡ (፪) ፡ መሠረት ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈርስ ፡ አቤቱታ ፡ ሊቀርብ ፡ አይችልም ፡፡

(፪) በቍጥር ፡ ፲፻፷፫ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፫) የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ እንዲፈርስ ፡ ግን ፤ በቍጥር ፡ ፱፻፹፩ ፡ እስከ ፡ ፱፻፹፫ ፡ በተመለከቱት ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፤ አቤቱታ ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ፡፡

BACK



**ቍ ፡ ፲፻፹፩ ። የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትን ፡ ለመክፈት ፡ ስለሚሰጠው ፡ ፍርድ ።**

(፩) ፍርድ ፡ ቤቱ ፤ የቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ ተቀባይነት ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችልና ፡ የሚፈቀድ ፡ ሆኖ ፡ ያገኘው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ መጀመሩን ፡ ያስታውቃል ። በዚህም ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ማናቸውም ፡ አቤቱታ ፡ ሊቀርብ ፡ አይችልም ።

(፪) በዚሁ ፡ በተሰጠው ፡ ፍርድ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፤

(ሀ) አንድ ፡ ወኪል ፡ ዳኛና ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፸፱ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩)፣(፬) እና ፡ (፭) መሠረት ፡ አንድ ፡ መርማሪ ፡ ሰው ፡ ይመርጣል ።

(ለ) እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ ፍርዱ ፡ ከተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ በሠላሳ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ እንዲሰበሰቡ ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ጥሪ ፡ ያደርግላቸዋል ። እንዲሁም ፡ ፍርዱ ፡ በማስታወቂያ ፡ የሚወጣበትንና ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የሚነገርበትንም ፡ ቀን ፡ ይወስናል ።

(ሐ) ባለዕዳው ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹን ፡ ስም ፡ ዝርዝር ፡ ሞልቶ ፡ በቶሎ ፡ ለማቅረብ ፡ ያልቻለ ፡ መሆኑን ፡ በጥያቄው ፡ ውስጥ ፡ ባስረዳ ፡ ጊዜ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለተባለው ፡ ባለዕዳ ፡ ዝርዝሩን ፡ ለመሙላት ፡ ከስምንት ፡ ቀን ፡ ሊያልፍ ፡ የማይችል ፡ ጊዜ ፡ ይወስንለታል ።

(መ) ለሥነ ፡ ሥርዐቱ ፡ መፈጸሚያ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመዝገብ ፡ ቤት ፡ የሚያስቀምጥበትን ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ቢበዛ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ይወስንለታል ።

(፫) ባለዕዳው ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) (ሐ) እና ፡ (መ) የተሰጡትን ፡ ትእዛዞች ፡ ያልጠበቀ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በቍጥር ፡ ፲፻፹፫ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፫) የተመለከቱት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆኑበታል ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፪ ። ስለወኪሉ ፡ ዳኛ ፡ ትእዛዞች ።**

ወኪሉ ፡ ዳኛ ፡ በሰጣቸው ፡ ትእዛዞች ፡ ላይ ፡ ማናቸውም ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፸፪ ፡ መሠረት ፤ መቃወሚያ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፫ ። ስለ ፡ ምምነቱ ፡ ስለተመረጠው ፡ መርማሪ ።**

ለመጠበቂያው ፡ ስምምነት ፡ በተመረጠው ፡ መርማሪ ፡ ዳኛ ፡ ላይ ፤ ከቍጥር ፡ ፲፻፸፯ ፡ እስከ ፡ ፲፻፹ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፬ ። ፍርዱን ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።**

(፩) ስለ ፡ መጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ በመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ አማካይነት ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መግቢያ ፡ በር ፡ ላይ ፡ ይለጠፋል ፤ የዚህም ፡ ማስታወቂያ ፡ ቅጅ ፡ ሕጋዊ ፡ ማስታወቂያን ፡ ለመቀበል ፡ በተፈቀደለት ፡ ጋዜጣ ፡ ይወጣል ።

(፪) የፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤቱም ፡ ሹም ፡ በቍጥር ፡ ፱፻፺፫ ፡ (፩) በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ ፍርዱ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ እንዲገባ ፡ ያደርጋል ።

(፫) ወኪል ፡ የሆነው ፡ ዳኛና ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ ፈርመውበት ፡ በባለዕዳው ፡ መዝገቦች ፡ ከተጻፉት ፡ ጽሑፎች ፡ ቀጥሎ ፡ ፍርድ ፡ መሰጠቱን ፡ ምል ክት፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፤ የተባሉትን ፡ መዝገቦች ፡ ለባለዕዳው ፡ ይመልሱለታል ።

## ቍ ፡ ፲፻፹፱ ። ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ የሚሰጥ ፡ ማስታወቂያ ።

(፩) ወኪል፡ የሆነው ፡ ዳኛ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ የሚሰበሰቡበትን ፡ ቦታና ፡ ጊዜ ፡ ይወስናል ።

(፪) በቍጥር ፡ ፲፻፹፰ ፡ ንኡስ፡ ቍ ፡ (፪) (ለ) መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወሰነው ፡ ጊዜ፡ ውስጥ፡ የመዝገብ፡ ቤቱ፡ ሹም ፤ እንዳስፈላጊነቱ ፡ በሬኮማንዴ ፡ ደብዳቤ፡ ወይም ፡ በቴሌግራም፡ ለያንዳንዱ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ፡ ቀጥሎ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ የያዘ ፡ ማስታወቂያ ፡—

(ሀ) የባለዕዳውን ፤ ወኪል ፡ የሆነውን ፡ ዳኛና ፡ የመርማሪውን ፡ ስም ፤

(ለ) ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ጥሪ ፡ የተደረገበት ፡ ፍርድ ፡ የተሰጠበትን ፡ ቀንና ፡ የስብሰባውን ፡ ጊዜና ፡ ቦታ ፤

(ሐ) ባለዕዳው ፡ ያቀረባቸውን ፡ አሳቦች ፡ በአጭሩ ፡ ጨምሮ ፡ ይልካል ።

## ቍ ፡ ፲፻፺ ። ሥርዐቶቹ ፡ መፈጸማቸውን ፡ ስለሚያስረዱ ፡ ጽሑፎች ።

ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ የተላለፉትን ፡ መግለጫዎችና ፡ ማስታወቂያዎችን ፡ የሚ ያስረዱ ፡ ጽሑፎች ፡ ከዶሴው ፡ ጋራ ፡ ተያይዘው ፡ መቀመጥ ፡ አለባቸው ።

## ቍ ፡ ፲፻፺፩ ። ስለ ፡ መጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ የቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ ውጤቶች ።

(፩) ጥያቄው ፡ ከቀረበበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ስለ፡ስምምነቱ ፡ መጽደቅ፡የተሰጠው፡ ፍርድ ፡ የመጨረሻ ፡ እስከሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፤ ፍርዱ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በፊት ፡ መብቱን ፡ ያገኘ ፡ ማናቸውም ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ቢሆን ፡ የማስፈጸምን ፡ ሥር ዐት ፡ ለመጀመር ፡ ወይም ፡ ለመቀጠል ፤ በባለዕዳው ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ የቀዳ ሚነትን፡መብት፡ለማግኘት፡ወይም፡የመያዣን፡መብት ፡ ለማጸና ፡ አይችልም ።

(፪) እንዲሁም ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ መቈጠር ፤ የክስ ፡ መቀጠል ፡ መብት ፡ ማጣት ፤ ወይ.ም ፡ ከመብት ፡ መከልከል ፡ ሁሉ ፡ ይታገዳል ።

(፫) እንዳችም ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ፡ የሌላቸው ፡ ተራ ፡ የሆኑት ፡ ዕዳዎች፡ የመ ክፈያቸው ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ይቈጠራል ። እንዲሁም ፡ የሚሰጡት ፡ ወለድ ፡ አቈጣጠር ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ በኩል ፡ ብቻ ፡ የታገደ ፡ ይሆናል ።

(፬) በቀረጥ ፡ ስም ፡ ተከፋይ ፡ የሚሆኑት ፡ ገንዘቦች ፤ የቀዳሚነት ፡ መብት ፡ ባይኖራቸውም፡ እንኳ፤ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ የተመለከቱት ፡ ውሳኔዎች ፡ አይፈጸ ሙባቸውም ።

**ቁ ፡ ፲፻፴፪ ። የባለዕዳውን ፡ ንብረቶች ፡ ስለ ፡ ማስተዳደር ።**

የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፤ ባለዕዳው ፤ በመርማሪው ፡ ተጠባባቂነትና ፡ ወኪል ፡ በሆነው ፡ ዳኛ ፡ መሪነት፡የንብረቶቹን ፡ አስተዳዳሪነትና ፡ የሥራውን ፡ ማካሄድ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ይቈያል ። ዳኛውና ፡ መርማሪው ፡ ሰው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ መዝገቦቹንና ፡ ሒሳቡን ፡ ለማወቅ ፡ ይችላሉ ።

**ቁ ፡ ፲፻፴፫ ። ባለዕዳው ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ሥራዎች ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ስለ ፡ አለመሆናቸው ።**

(፩) የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡ ባለዕዳው፡ የሚያደርጋቸው ፡ ስጦታዎችና ፡ ሌሎች ፡ የችሮታ ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ የሚሰጣቸው ፡ ዋስትናዎች ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆኑባቸው ፡ አይችሉም ።

(፪) እንደዚሁም ፡ ወኪል ፡ የሆነው ፡ ዳኛ ፡ በጽሑፍ፡ ሳይፈቅድለት ፤ ፈቃዱንም ፡ ዳኛው ፡ ለመስጠት ፡ የሚችለው ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ጥቅም ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ሲሆን ፤ ባለዕዳው ፡ በሐዋላ ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ በተስፋ ፡ ሰነድ፡ቢሆንም፡እንኳ፡ ብድር ፡ የገባባቸው ፡ ውሎች ፤ ያደረጋቸውን ፡ ግልግሎች ፡ ወይም ፡ ስምምነቶች ፤ ለንግዱ ፡ ሥራ ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆን፡ ያደረገው ፡ የንብረት ፡ ማስተላለፍ፡ ወይም ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ እንዲጻፍበት ፡ መፍቀድ ፤ ወይም ፡ የሰጣቸው ፡ መያዣዎች ፡ ሁሉ ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ሊሆኑባቸው ፡ አይችሉም ።

**ቁ ፡ ፲፻፴፬ ። የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፤ ስለሚደረግ ፡ የመክሠር ፡ ማስታወቂያ ።**

ባለዕዳው ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፴፪ ፡ እና ፡ ፲፻፴፫ ፡ የተጻፉትን ፡ ድንጋጌዎች ፡ የተላለፈ ፡ እንደ፡ሆነ፤ ወይም፡ ከንብረቱ፡ አንዱን፡ ክፍል፡ የደበቀ፤ በተንኰል ፡ አንዳንድ ዶቹን ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ሳይቈጥር ፡ የተወ ፤ ዕዳውን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ያሳየ ፡ ወይም በጠቅላላው ፡ የተንኰል ፡ ሥራዎችን ፡ ሠርቶ ፡ የተገኘ ፡ ለመሆኑ ፡ የተረጋገጠ፡ እንደ፡ሆነ ፤ ወኪል፡ የሆነው ፡ ዳኛ ፡ የመርማሪውን ፡ ሐሳብ ፡ ሰምቶ ፡ ነገሩን ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ያስታውቅና ፤ በባለዕዳው ፡ ላይ ፡ የሚወሰኑት ፡ የወንጀል ፡ ቅጣቶች፡ እንደ፡ተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የባለዕዳውን ፡ መክሠር ፡ ያስታውቃል ።

**ቁ ፡ ፲፻፴፭ ። ስለ ፡ መርማሪው፡ ተግባሮች ።**

ለስምምነቱ ፡ የተመረጠው ፡ መርማሪ ፤ የባለዕዳውን ፡ የዕቃ ፡ ዝርዝር ፡ መዝገብ ፡ ያደራጃል ። የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹንና ፡ የባለዕዳዎቹን ፡ ዝርዝር ፡ ይመረም

ራል ። ስለ፡ንግዱ፡ ሁኔቴና ፡ ስለ፡ባለዕዳው፡ ፀመል ፤ ለስምምነት ፡ ስለ፡ቀረቡት ፡ አሳቦችና ፡ ለገንዘብ፡ ጠያቂዎች ፡ ስለ፡ቀረቡት ፡ ተያገሮች ፡ የሚያስረዳ ፡ መግለጫ ፡ ያዘጋጃል። መግለጫውም፡ ገንዘብ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ከመሰብሰባቸው ፡ በፊት ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከአምስት ፡ ቀን ፡ አስቀድሞ ፡ ለፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ይሰጣል ።

ቍ ፡ ፲፻፴፮ ። ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ስብሰባ ።

(፩) የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ሰብሳቢ ፤ ወኪል ፡ የሆነው ፡ ዳኛ ፡ ነው ።
(፪) ማናቸውም ፡ ገንዘብ፡ ጠያቂ ፡ በጥሪው ፡ ማስታወቂያ ፡ ላይ ፡ በጽሑፍ ፡ በማመልከት ፡ ብቻ ፡ ወክሶ ፡ በራሱ ፡ ፋንታ ፡ ወኪሉን፡ለመላክ ፡ ይችላል ።
(፫) ባለዕዳው ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነው ፡ ወኪሉ ፡ ራሱ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ። ልዩ ፡ ወኪልን ፡ እንዲልክ ፡ የሚፈቅደው ፤ ወኪል ፡ የሆነው ፡ ዳኛ ፡ ያረጋገጠው ፤ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ መሰናከል ፡ ሲኖር ፡ ነው ።
(፬) መርማሪው፡ ያቀረበው፡ መግለጫ፡ ከተነበበ ፡ በኋላ ፤ ባለዕዳው ፡ የመጨረሻ፡ ሐሳቦቹን ፡ ያቀርባል ።

ቍ ፡ ፲፻፴፯ ። ለስምምነቱ ፡ በቀረቡት ፡ አሳቦች ፡ ላይ ፡ ስለሚደረጉ ፡ ክርክሮች ።

(፩) ማናቸውም፡ገንዘብ፡ ጠያቂ፡ ስለ፡ስምምነቱ፡ የቀረቡትን ፡ አሳቦች ፡ የማይቀበልበትን ፡ ምክንያት ፡ ለመግለጽና ፡ እንድነት ፡ በሚቀርቡት ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብቶች ፡ ላይ ፡ ክርክርን ፡ ለማንሣት ፡ ይችላል ።
(፪) ባለዕዳውም ፡ በበኩሉ ፤ ምላሽ ፡ ለመስጠትና ፡ በሚቀርቡትም ፡ ዕዳዎች ፡ ላይ ፡ ክርክር ፡ ለማንሣት ፡ ይችላል ። የሚጠየቅባቸውን ፡ ማስረጃዎች ፡ ሁሉ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።
(፫) የነዚህ ፡ ክርክሮች ፡ ሁሉ ፡ አጭር ፡ ቃል ፡ በፕሮሴቨርባል ፡ ገብቶ ፡ አስረጂዎችም ፡ እንዳሉ ፡ መያያዝ ፡ አለባቸው ።

ቍ ፡ ፲፻፴፰ ። የስብሰባውን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ማስረዘም ።

በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሥራዎቹን ፡ ሁሉ ፡ ለመጨረስ ፡ ያልተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፤ ለሌሉትም ፡ ቢሆን ፤ ሌላ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሳይደረግ ፤ ስብሰባው ፡ ቀጥሎ ፡ ለሚገኘው ፡ የሥራ ፡ ቀን ፡ ይቀጠራል ። እንደዚሁም ፡ ሥራዎቹ ፡ እስኪያልቁ ፡ ድረስ ፡ ጊዜው ፡ እየተራዘመ ፡ ይሄዳል ።

ቍ ፡ ፲፻፴፱ ። ክርክር ፡ የተነሣባቸውን ፡ ዕዳዎች ፡ ለጊዜው ፡ ስለ ፡ መቀበል ።

(፩) ወኪል ፡ የሆነው ፡ ዳኛ ፡ ድምፅ ፡ ለመስጠትና ፡ ለድምፅ ፡ ብልጫ ፡ አቈጣጠር ፡ ብቻ ፡ ሲል ፡ ክርክር ፡ የተነሣባቸውን ፡ ዕዳዎች ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ ሊቀበላቸው ፡ ይችላል ። ይህ ፡ መፍቀድ ፡ ግን ፤ ስለነዚሁ ፡ ዕዳዎች ፡ ተገቢነት ፡ በመጨረሻ ፡ የሚሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ የማይነካ ፡ ነው ።

(፪) መብታቸውን ፡ ሳይቀበሏቸው ፡ የቀሩት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፤ መብታቸው ፡ ተቀባይነት ፡ አግኝቶ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫውን ፡ አቈጣጠር ፡ ይለውጠው ፡ ነበር ፡ በሚባልበት ፡ ጊዜ ፤ ስምምነቱ ፡ ለመጽደቅ ፡ በሚቀርብበት ፡ ችሎት ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላሉ ።

ቍ ፡ ፬፻፵፱ ። ስምምነቱን ፡ ለመቀበል ፡ ስለሚያስፈልገው ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ።

(፩) የመጠበቂያው ፡ ስምምነት ፡ ተቀባይነት ፡ እንዲያገኝ ፡ የቀዳሚነት ፡ መብት ፡ ወይም ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ ከሌላቸው ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብቶች ፡ ቢያንስ ፡ ከሦስት ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ ባላቸውና ፡ ድምፃቸውንም ፡ በሰጡት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ መደገፍ ፡ አለበት ።

(፪) በባለዕዳው ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ መያዣ ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ዋስትናቸውን ፡ ካልለቀቁ ፡ በድምፅ ፡ ብልጫው ፡ ሥራ ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ አይችሉም ። ይኸውም ፡ የመያዣ ፡ መብትን ፡ መልቀቅ ፡ በከፊል ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ዋስትና ፡ ካለው ፡ ተፈላጊው ፡ ጠቅላላ ፡ ገንዘብ ፡ አንድ ፡ ሦስተኛ ፡ ማነስ ፡ የለበትም ።

(፫) መያዣ ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፤ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) መሠረት ፡ መያዣውን ፡ በከፊል ፡ ሳይለቅ ፤ ድምፅ ፡ በመስጠቱ ፡ ተከፋይ ፡ ሆኖ ፤ በቍጥር ፡ ፬፻፵፮ ፡ መሠረት ፡ ስምምነቱን ፡ ተቀብሎ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ገንዘብ ፡ ጠያቂው ፡ ያለውን ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ በሙሉ ፡ እንደ ፡ ለቀቀ ፡ ይቈጠራል ።

(፬) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስምምነቱን ፡ በሚያጸድቅበት ፡ ጊዜ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፪) መሠረት ፡ በተሰጡት ፡ ድምፆች ፡ ምክንያት ፤ ወይም ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፫) መሠረት ፡ በተደረገው ፡ መቀበል ፡ ምክንያት ፤ የባለዕዳው ፡ ንብረት ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችለውን ፡ ብልጫ ፡ በግምት ፡ ውስጥ ፡ ያገባዋል ።

(፭) ስምምነቱ ፡ ያልተፈጸመ ፡ ወይም ፡ ያልጸደቀ ፡ ወይም ፡ የተሰረዘ ፡ ወይም ፡ የፈረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተደረገው ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ መልቀቅ ፤ በከፊልም ፡ ቢሆን ፤ ውጤቱ ፡ በደንብ ፡ ቀሪ ፡ ይሆናል ።

(፮) ለመጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ ስለሚሰጠው ፡ ድምፅ ፡ በቍጥር ፡ ፬፻፵፱ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፬) እና ፡ (፭) የተወሰኑት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፬፻፶ ። የተደረገውን ፡ ስምምነት ፡ ስለመቀበል ።

(፩) ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ስብሰባ ፡ በሚደረገው ፡ ፕሮሴቨርባል ፡ ላይ ፡ የድምፅ ፡ ሰጪዎቹን ፡ ስምና ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የሚጠይቁትን ፡ ጠቅላላ ፡ ዕዳ ፡ ጭምር ፤ ድምፃቸውንም ፡ የሰጡት ፡ ስምምነቱን ፡ በመደገፍ ፡ ወይም ፡ በመቃወም ፡ መሆኑ ፡ ተለይቶ ፡ ይጻፋል ። በፕሮሴቨርባሉም ፡ ወኪል ፡ የሆነው ፡ ዳኛ ፤ መርማሪው ፤ የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ ይፈርሙበታል ።

(፪) ፕሮሴቨርባሉ ፡ በተዘጋ ፡ በ፲ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ በቴሌግራም ፡ ወይም ፡ በደብዳቤ ፡

የሚላኩት ፡ የስምምነቶች ፡ አቀባበሎች ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ። እንዚሁንም ፡ ተጨማሪ ፡ ስምምነቶች ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ በፕሮሲቬርባሉ ፡ ኅዳግ ፡ ላይ ፡ ይጽፋቸዋል ።

ቍ ፡ ፲፻፶፪ ። ስምምነቱን ፡ ስለ ፡ አለመቀበል ።

የመጠበቂያውን ፡ ስምምነት ፡ ስለ ፡ መቀበል ፡ በቍጥር ፡ ፲፻፶ ፡ እና ፡ ፲፻፶፩ ፡ የተነገሩት ፡ ሁኔታዎች ፡ ያልተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወኪል ፡ የሆነው ፡ ዳኛ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያስታውቃል ፤ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ሰውዬው ፡ መክሠሩን ፡ በሥልጣኑ ፡ ያስታውቃል ።

ቍ ፡ ፲፻፶፫ ። ስምምነቱን ፡ ለማጽደቅ ፡ ስለሚደረገው ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

(፩) ከሓያ ፡ ቀን ፡ ለማለፍ ፡ በማይችል ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ስምምነቱ ፡ መጽደቅ ፡ በተወሰነው ፡ ቀን ፡ ባለጕዳዮቹ ፡ እፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርበው ፡ እንዲሰሙ ፡ ወኪል ፡ የሆነው ፡ ዳኛ ፤ ፕሮሲቬርባሉ ፡ ከመፈረሙ ፡ በፊት ፤ በፕሮሲቬርባሉ ፡ ውስጥ ፡ ጽፎ ፡ ባለጕዳዮቹን ፡ ይቀጥራቸዋል ።

(፪) የስምምነቱን ፡ መጽደቅ ፡ ለመስማት ፡ ለተወሰነው ፡ ችሎት ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ሲቀረው ፤ መርማሪው ፡ አሳቦቹን ፡ ከነምክንያቱ ፡ ለፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ያስረክባል ፤ ነገሩ ፡ በሚሰማበት ፡ ችሎት ፡ ወኪል ፡ የሆነው ፡ ዳኛ ፡ መግለጫውን ፡ ያቀርባል ።

(፫) ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹና ፡ ባለዕዳው ፡ በጕዳዩ ፡ ክርክራቸውን ፡ ለማቅረብ ፡ መብት ፡ አላቸው ።

ቍ ፡ ፲፻፶፬ ። ስለ ፡ ስምምነቱ ፡ መጽደቅ ፡ የሚሰጥ ፡ ፍርድ ።

(፩) ስምምነቱ፡ ተቀባይነት ፡ እንዲያገኝ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ሁኔታዎች ፡ መኖር ፡ እና ፡ የሥነ ፡ ሥርዐቱን ፡ መፈጸም ፡ ከመረመረ፡ በኋላ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፤

(ሀ) የንግዱ ፡ ድርጅት ፡ በያዘው ፡ ሥራና ፡ ባለው ፡ ችሎታ ፡ መሠረት ፤ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ስምምነቱ ፡ የሚጠቅማቸው ፡ መሆኑን ፡ መገመት ፡ እና ፡

(ለ) በሕግ ፡ ተፈላጊ ፡ የሆነው ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ድምፅ ፡ ብልጫ ፡ መገኘቱን ፡ ማረጋገጥ ፡ ስለዚሁም ፤ በኋላ ፡ የሚሰጡት ፡ የመጨረሻ ፡ ፍርዶች ፡ ሳይጓደሉ ፡ የተፈለገውን ፡ ድምፅ ፡ ብልጫ ፡ መገኘት ፡ ለማረጋገጥ ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተጠየቁትን ፡ ዕዳዎች ፡ ከፍተኛነትና ፡ መጠን ፡ ለጊዜውና ፡ በግምት ፡ መወሰን ፤

(ሐ) ስምምነቱ ፡ እንዲፈጸም ፡ ለማረጋገጥ ፡ የቀረቡት ፡ ዋስትናዎች ፡ በቂ ፡ መሆናቸውንና ፤ በቍ ፡ ፲፻፳፩ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፪) እንደተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ሲሆን ፤ ባለዕዳው ፡ ለገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ የለቀቀው ፡ ንብረት ፡ በቍጥር ፡

ሺ፻፶፩ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) በተወሰነው ፡ መጠን ፤ ከባለዕዳው ፡ የሚፈለገውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ በቂ ፡ መሆኑን ፤ መመርመር ፤

(መ) የባለዕዳውን ፡ መክሠር ፡ ያመጡትን ፡ ምክንያቶችና ፡ አሠራሩን ፡ በመገንዘብ ፡ ይኸው ፡ ባለዕዳ ፡ ስምምነቱ ፡ ሊደረግለት ፡ የሚገባው ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ መገመት ፡ አለበት ።

(፪) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያደረገው ፡ ምርመራ ፡ ውጤቶች ፡ ባለዕዳውን ፡ የሚረዱት ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ስምምነቱ ፡ እንዲጸድቅ ፡ ይፈርዳል ። እንዲህ ፡ ካልሆነ ፡ ግን ፡ ባለዕዳው ከሥሮዋል ፡ ሲል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሥልጣኑ ፡ ይፈርዳል ።

(፫) ስምምነቱ ፡ እንዲጸድቅ ፡ በሚሰጠው ፡ ፍርድ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፤

(ሀ) ለተገለጹት ፡ ዕዳዎች ፡ የሚደርሰው ፡ ድርሻ ፡ እንዲቀመጥ ፤

(ለ) ክርክር ፡ የተነሣባቸው ፡ ዕዳዎችን ፡ ለመክፈል ፡ የሚበቃ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲቀመጥ ፤

(ሐ) ወኪል ፡ የሆነው ፡ ዳኛ ፡ እንዲሾምበት ፡ ካላዘዘ ፡ በቀር ፤ ስምምነቱን ፡ በመፈጸም ፡ በየጊዜው ፡ ሊከፈል ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብና ፡ የአከፋፈሉንም ፡ ዐይነት ፡ ይወስናል ።

**ቍ ፡ ሺ፻፷፫ ። ንብረቶች ፡ በሚለቀቁበት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚደረጉት ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ።**

በቍጥር ፡ ሺ፻፶፩ ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፪) መሠረት ፡ ባለዕዳው ፡ ንብረቶቹን ፡ እንዲለቅ ፡ ስምምነቱ ፡ የሚወስን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ እንደ ፡ ተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለ ፡ ስምምነቱ ፡ መጽደቅ ፡ በሚሰጠው ፡ ፍርድ ፤

(ሀ) አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪዎችና ፤ የማጣራቱንም ፡ ሥራዎች ፡ እንዲጠባበቁ ፤ ሦስት ፡ ወይም ፡ አምስት ፡ አባሎች ፡ ያሉበት ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ኮሚቴ ፡ ይመርጣል ።

(ለ) የማጣራቱንም ፡ አደራረግ ፡ ይወስናል ።

**ቍ ፡ ሺ፻፷፬ ። በባለዕዳው ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ክልከላ ።**

(፩) በስምምነቱ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ ተሰጥቶ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ባጸደቀው ፡ ውሳኔ ፡ ውስጥ ፡ የገባ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ ባለዕዳው ፡ በስምምነቱ ፡ ውስጥ ፡ የተነገሩትን ፡ ግዴታዎች ፡ በሙሉ ፡ እስኪፈጽም ፡ ድረስ ፤ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶቹን ፡ እንዳይሸጥ ፡ እንዳይለውጥ ፡ ወይም ፡ እንዳያስዝ ፡ ወይም ፡ የመያዣ ፡ መብት ፡ እንዳይሰጥና ፡ በጠቅላላውም ፡ ለሥራው ፡ ዐይነት ፡ በሚያስፈልገው ፡ አኳኋን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከንብረቱ ፡ እንዳይቀንስ ፡ ይከለከላል ።

(፪) በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) የተመለከተውን ፡ ክልከላ ፡ በመጣስ ፡ የተሠራ ፡ ማናቸውም ፡ ሥራ ፡ የመጠበቂያው ፡ ስምምነት ፡ ከመጽደቁ ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ አንዳች ፡ ውጤት ፡ የለውም ፤

BACK



**ቍ ፡ ፲፻፵፯ ። ስለ ፡ ስምምነቱ ፡ መጽደቅ ፡ የሚሰጠው ፡ የፍርድ ፡ ማስታወቂያ ።**

የመጠበቂያውን ፡ ስምምነት ፡ በማጽደቅ ፡ ወይም ፡ አይሆንም ፡ በማለት ፡ የተሰጡት ፡ ፍርዶች ፡ በቍጥር ፡ ፱፻፶፫ ፡ ከተወሰኑት ፡ ደንቦች ፡ ተገቢ ፡ የሆኑትን ፡ በመከተል ፡ በማስታወቂያ ፡ መውጣት ፡ አለባቸው ።

**ቍ ፡ ፲፻፵፰ ። ስምምነቱ ፡ እንዳይጸድቅ ፡ ስለ፡መቃወም ።**

(፩) በነገሩ ፡ ያልተስማማው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ እና ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ባለጕዳይ ፡ የሆነ ፡ ማናቸውም፡ ሰው ፡ ፕሮሴቬርባሉ ፡ በተዘጋጀ ፡ በአምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ፡ ስምምነቱ ፡ እንዳይጸድቅ ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

(፪) የመቃወሚያውም ፡ ምክንያት ፡ ተገልጾ ፡ መቃወሚያውን ፡ ባለዕዳውና ፡ መርማሪው ፡ እንዲያውቁት ፡ መደረግ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፲፻፵፱ ። ስለ፡ ስምምነቱ ፡ መጽደቅ ፡ በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ስለ፡ማለት ።**

ስምምነቱን ፡ በማጽደቅ ፡ ወይም ፡ አይሆንም ፡ በማለት ፡ በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ ባለዕዳው ፡ ወይም ፡ በቍ ፡ ፲፻፵፰ ፡ መሠረት ፡ የተቃወሙት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ይግባኝ ፡ ሊሉ ፡ ይቻላሉ ። የይግባኙም ፡ ጊዜ ፡ የፍርዱ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከወጣበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ነው ። የይግባኙም ፡ ክስ ፡ ባለዕዳው ፤ መርማሪው ፤ በክርክሩ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ባለጕዳዮች ፡ ሁሉ ፡ እንዲያውቁት ፡ መደረግ ፡ አለበት ።

**ቍ ፡ ፲፻፶ ። የስምምነቱ ፡ መጽደቅ ፡ ውጤቶች ።**

(፩) በሚገባ፡ የጸደቀው፡ የመጠበቂያ፡ ስምምነት ፤ የጕዳዩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ከመክፈቱ፡ በፊት፡ የነበሩትን፡ ገንዘብ፡ ጠያቂዎች ፡ ሁሉ፡ አስገዳጅ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ለእነዚህ፡ ገንዘብ፡ ጠያቂዎች ፤ በባለዕዳው ፡ የጋራ ፡ ተገዳጆች ፤ በዋሶቹና ፡ ንብረቱን፡ ባስተላለፈላቸው፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ መብት ፡ በሙሉ ፡ እንደ፡ ተጠበቀ ፡ ይቈያል ።

(፪) እነዚህ ፡ የተዘረዘሩት፡ ሰዎች ፡ በስምምነቱ ፡ ላይ ፡ ማስገንዘቢያቸውን ፡ ለማቅረብ ፡ በክርክሩ ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ ይችላሉ ።

**ቍ ፡ ፲፻፶፩ ። ስለ ፡ ስምምነቱ ፡ አፈጻጸም ፡ የሚደረግ ፡ ተጠባባቂነት ።**

(፩) የመጠበቂያው ፡ ስምምነት ፡ ከጸደቀ ፡ በኋላ ፤ ስለ፡ ማጽደቁ ፡ በተሰጠው፡ፍርድ፡ ውስጥ ፡ በተመለከተው ፡ አሠራር ፡ መሠረት ፡ ስምምነቱ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ መርማሪው ፡ አፈጻጸሙን ፡ ይጠባበቃል ።

(፪) መርማሪው ፤ ገንዘብ ፡ ጠያቂውን ፡ ለመጕዳት ፡ ምክንያት ፡ የሚሆነውን ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ወኪል ፡ ለሆነው ፡ ዳኛ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ።

(፫) ማናቸውም ፡ ተቃራኒ ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፡ ከተመረጠበት ፡

BACK



ጊዜ ፡ እንሥቶ ፤ ሥራዎቹ ፡ እስከ ፡ ቀሩበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፤ ለመርማሪው ፡ የሚታሰብለትን ፡ ኪሣራና ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ወኪል ፡ የሆነው ፡ ዳኛ ፡ ይወስንለታል ።

ቍ ፡ ፲፻፶፪ ። የመጠበቂያ ፡ ስምምነትን ፡ ስለ ፡ መሰረዝና ፡ ስለ ፡ ማፍረስ ።

(፩) በንብረት ፡ ጠባቂው ፡ ቦታ ፡ የመርማሪው ፡ መተካት ፡ ብቻ ፡ የተጠበቀ፡ሆኖ ፤ ከቍ ፡ ፲፻፵፩ ፡ እና ፡ ፲፻፵፫ ፡ የተጻፉት ፡ ድንጋጌዎች ፤ የመጠበቂያ ፡ ስምምነትን፡ ለማፍረስና ፡ ለመሰረዝ ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

(፪) የመጠበቂያው ፡ ስምምነት ፤ በቍጥር ፡ ፲፻፳፩ ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፪) መሠረት ፡ ንብረቶችን ፡ ለመልቀቅ ፡ የሚወስን ፡ በሚሆንበት፡ጊዜ ፤ ከንብረቶቹ፡ መሸጥ ፡ የተገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ከዕዳው ፡ አምሳ ፡ በመቶውን ፡ 50% ለመክፈል ፡ የሚበቃ፡ ከሆነ ፡ ስምምነቱ ፡ አይፈርስም ።

ቍ ፡ ፲፻፶፫ ። ወደ፡ተሻለ ፡ ዕድል ፡ ስለ ፡ መመለስ ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ።

በመጠበቂያው ፡ ስምምነት ፡ ውስጥ ፤ ባለዕዳው ፡ ከስምምነቱ፡ ሰነድ ፡ ፈጽሞ ፡ ነጻ ፡ የሚሆነው ፤ ወደ ፡ ተሻለው ፡ ዕድል ፡ ተመልሶ ፡ ያልተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ገብቶበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የዚህ ፡ ውል ፡ ተፈጻሚነት፡ ለአምስት ፡ ዓመት ፡ በሚሆን ፡ ጊዜ ፡ ይወሰናል ፤ ያውም ፡ የባለዕዳው ፡ ንብረት ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከዕዳው ፡ በላይ ፡ ከመቶ ፡ ሐያ ፡ አምስት ፡ ጨምሮ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ።

## እንቀጽ ፡ ፬ ።

## ስለ ፡ ማኅበሮች ፡ መክሠርና ፡ የመጠበቂያ ፡ ስምምነቶች ፡ የሚጸኑ ፡

## ልዩ ፡ ውሳኔዎች ።

ቍ ፡ ፲፻፶፬ ። የጠቅላላ ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚነት ።

ከዚህ ፡ በፊት ፡ ባሉት ፡ እንቀጾች ፡ የተነገሩት ፡ ደንቦች ፡ ሳይነኩ ፡ ማኅበሮች ፡ በዚህ ፡ እንቀጽ ፡ ውሳኔዎች ፡ ይመራሉ ።

ቍ ፡ ፲፻፶፭ ። የመክሠር ፡ ማስታወቂያ ፡ ፍርድ ፡ ሊሰጥባቸው ፡ የሚችሉ ፡ ማኅበሮች ።

(፩) ከእሽሙር ፡ ማኅበሮች ፤ በቀር ፡ ማናቸውም ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ሁሉ ፡ የመክሠር ፡ ማስታወቂያ ፡ ፍርድ ፡ ሊሰጥባቸው ፡ ወይም ፡ የመጠበቂያ ፡ ስምምነት ፡ ለማግኘት ፡ ሊፈቀድላቸው ፡ የሚችሉ ፡ ናቸው ።

(፪) ሒሳቡን ፡ በማጣራት ፡ ያለ ፡ ማኅበር ፡ የመክሠር ፡ ማስታወቂያ ፡ ፍርድ ፡ ሊሰጥበት ፡ ይችላል ።

(፫) ማኅበሩ፡ በመሥራት፡ ላይ ፡ መኖሩ ፡ ከተረጋገጠ ፤ በሕግ ፡ ፈራሽነቱ፡ በተገለጸ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ እነዚህ ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

BACK



ቍ ፡ ሺ፪፻፶፮ ። የመከፈልን ፡ መቋረጥ ፡ ስለ ፡ ማስታወቅ ።

በቍጥር፡ ፱፻፸፪ ፡ መሠረት ፡ ያንድ ፡ ማኅበርን ፡ መክፈል ፡ ማቋረጥ ፡ የሚያስታውቀው ፤ ሕጋዊ፡ ከሆኑ ፡ እንደራሴዎች፡ አንዱ ፡ ነው ። ማኅበሩ ፡ ሒሳቡን ፡ በማጣራት ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ሆነ ፤ ይህን፡ ማስታወቂያ ፡ ማድረግ ፡ ግዴታ ፡ ያለበት ፡ ሒሳብ ፡ አጣሪው ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፪፻፶፯ ። ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ።

(፩) የሥራው፡ ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ባለበት ፡ ቦታ ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመክሠር፡ ረገድ ፡ የሚቀርበውን ፡ ክስና ፡ ሥርዐት ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

(፪) የኢንተርናሲዮናል፡ ስምምነቶች ፡ እንደ፡ተጠበቁ ፡ ሆነው ፤ የሥራው ፡ ዋና፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ እውጭ ፡ አገር ፡ በመሆኑ ፡ የመክሠሩን ፡ ጉዳይ ፡ የውጭ ፡ አገር፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ያየውም ፡ ቢሆን ፤ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመክሠሩን፡ ጉዳይ ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

ቍ ፡ ሺ፪፻፶፰ ። ሳይከፋፈል ፡ የአንድነትና ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ አላፊነት ፡ ያላቸው ፡ ማኅበረተኞች ፡ ስላሉበት ፡ ማኅበር ፡ መክሠር ።

(፩) የኅብረት፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሲሆን ፤ ማኅበረተኞች ፡ ሁሉ ፤ ሁለት ፡ ዐይነት ፡ ኀላፊነት ፡ ያለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ሲሆን፤ ያልተወሰነ ፡ ኀላፊነት ፡ ያለባቸው ፡ ማኅበረተኞች ፡ ሁሉ ፡ እነርሱን ፡ ለሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ በቍጥር፡ ሺ፪፻፶፮ ፡ የተመለከተውን ፡ ማስታወቂያ ፤ ማኅበሩ ፡ መክፈሉን ፡ ካቋረጠ ፡ በሐያ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፤ መስጠት ፡ አለባቸው ።

(፪) ሳይከፋፈል ፡ የአንድነትና ፡ ያልተወሰነ ፡ ኀላፊነት ፡ ያለባቸው ፡ ማኅበረተኞች ፡ ያሉበት ፡ ማኅበር ፡ መክሠር ፤ ወዲያውኑ ፡ የነዚህን፡ ማኅበረተኞች፡ መክሠር ፡ ያስከትላል ።

ቍ ፡ ሺ፪፻፶፱ ። ስለ፡ አላፊነት ፡ የሚደረግ ፡ ክስ ።

በቍጥር፡ ፫፻፴፮፡ እና፡ ፫፻፴፯፡ መሠረት፡ በመርማሪዎች፤ በዋና፡ ሥራ ፡ አስኪያጆችና፡ በሒሳብ፡ አጣሪዎች፡ ላይ ፡ በአላፊነት ፡ የሚቀርበውን ፡ ክስ ፤ በመርማሪው፡ ዳኛ ፡ ፈቃድ ፡ የገንዘብ፡ ጠያቂዎቹን ፡ ኮሚቴ ፡ ሐሳብ ፡ ሰምቶ ፡ ንብረት ፡ ጠባቂው ፡ ይፈጽመዋል ።

ቍ ፡ ሺ፪፻፷ ። የጋራ ፡ መክሠርን ፡ ስለ፡ማስታወቅ ።

(፩) የአክሲዮን፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ አላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ የከሠረ ፡ እንደ፡ሆነ፤ በዚህ ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ ተግባሮቹን ፡ በመሸፈን ፡ ለራሱ ፡

BACK



ጥቅም ፡ የንግድ ፡ ሥራዎችን ፡ ሠርቶ ፡ በማኅበሩም ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ የግል ፡ ገንዘቡ ፡ አድርጎ ፡ የተጠቀመ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፤ በማኅበሩ ፡ ላይ ፡ የተሰጠው ፡ የመክሠር ፡ ፍርድ ፡ በርሱም ፡ ላይ ፡ በጋራ ፡ እንዲጸናበት ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ፡፡

(፪) በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) የተመለከተው ፡ ውሳኔ ፤ ሁለት ፡ ዐይነት ፡ ኀላፊነት ፡ ያለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ በገቡት ፡ የተወሰነ ፡ ኀላፊነት ፡ ባለባቸው ፡ ማኅበረተኞች ፡ ላይ ፡ ይፈጸማል ፡፡

<u>ቍ ፡ ሺ፻፳፩ ፡፡ ሥራውን ፡ የተወ ፡ በአንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ አላፊ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ማኅበረተኛ ፡፡</u>

(፩) ማኅበሩ ፡ መክፈሉን ፡ ያቋረጠው ፤ ማኅበረተኛው ፡ ከመሰረዙ ፡ በፊት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ማኅበረተኛው ፡ ከንግድ ፡ መዝገብ ፡ ከተሰረዘበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ሳይከፋፈል ፡ የአንድነት ፡ አላፊነት ፡ ያለበት ፡ ማኅበረተኛ ፡ መክሠር ፡ እንዲገለጽ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይቻላል ፡፡

(፪) ሳይከፋፈል ፡ በአንድነት ፡ አላፊ ፡ የሆነው ፡ ማኅበረተኛ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ ያልተመዘገበ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ሥራውን ፡ ከተወ ፡ በኋላ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ መክሠሩ ፡ እንዲገለጽ ፡ ለመጠየቅ ፡ ይቻላል ፡፡

<u>ቍ ፡ ሺ፻፳፪ ፡፡ በማኅበሩ ፡ የውስጥ ፡ ደንብ ፡ ለመክፈል ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ መዋጮዎቹ ፡ እንዲገቡ ፡ ስለ ፡ መጠየቅ ፡፡</u>

በማናቸውም ፡ ማኅበር ፡ በማኅበሩ ፡ የውስጥ ፡ ደንብ ፡ ለመክፈያ ፡ ከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ቢሆንም ፡ እንኳን ፤ ንብረት ፡ ጠባቂው ፡ ያልገቡት ፡ መዋጮዎች ፡ እንዲገቡ ፡ ለማስገደድ ፡ ይችላል ፡፡

<u>ቍ ፡ ሺ፻፳፫ ፡፡ ሳይከፋፈል ፡ በአንድነት ፡ ኀላፊነት ፡ ስለ ፡ አለባቸው ፡ ማኅበረተኞች ፡ መክሠር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡፡</u>

(፩) የማኅበሩንና ፡ ሳይከፋፈል ፡ በአንድነት ፡ ኀላፊዎች ፡ የሆኑትን ፡ ማኅበረተኞች ፡ መክሠር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በአንድ ፡ ፍርድ ፡ ይገልጻል ፡፡ እንደ ፡ ደንቡም ፡ አንድ ፡ መርማሪ ፡ ዳኛና ፡ አንድ ፡ የንብረት ፡ ጠባቂ ፡ ይሾማል ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ የማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ከማኅበረተኞቹ ፡ ንብረት ፡ እንደ ፡ ተለየ ፡ ይቈያል ፡፡ የያንዳንዱም ፡ መክሠር ፡ ኀብረት ፡ በተለይ ፡ ይቋቋማል ፡፡

(፪) በማኅበሩ ፡ መክሠር ፡ ውስጥ ፡ የገንዘብ ፡ መጠየቂያ ፡ መብታቸውን ፡ ያቀረቡ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ በሚገባቸው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በየአንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ መክሠር ፡ ውስጥ ፡ መብታቸው ፡ እንዲታወቅላቸው ፡ እንዳቀረቡ ፡ ይቈጠራሉ ፡፡

(፫) መክፈል ፡ ከሚገባቸው ፡ በላይ ፡ ስለ ፡ ከፈሉት ፡ ገንዘብ ፡ የያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ መክሠር ፡ በሌላው ፡ ማኅበረተኛ ፡ መክሠር ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የተሰ

ጠው ፡ መብት ፡ ሳይነካ ፤ ከማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፤ ገንዘቡ ፡ በሙሉ ፡ እስኪከፈለው ፡ ድረስ ፤ በሚደረጉት ፡ ክፍያዎች ፡ ሁሉ ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ መብት ፡ አለው ።

(፪) ከማኅበረተኞቹ ፡ ላይ ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ በመብታቸው ፡ ሊሠሩበት ፡ የሚችሉት ፤ ባለዕዳ ፡ በሆናቸው ፡ ማኅበረተኛ ፡ መክሠር ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(፫) እያንዳንዱ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፤ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ተካፋይ ፡ የሆኑትን ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ መብት ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፱፻፷፬ ፡ የስምምነት ፡ ሐሳብ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ።

(፩) በመክሠር ፡ ላይ ፡ ላለው ፡ ማኅበር ፡ የስምምነቱን ፡ ጥያቄ ፡ የሚፈርሙት ፡ የማኅበሩ ፡ ሕጋዊ ፡ እንደራሴዎች ፡ ናቸው ።

(፪) የኅብረት ፡ የሽርክና ፤ ወይም ፡ ሁለት ፡ ዐይነት ፡ ኀላፊነት ፡ ያለበት ፡ የሽርክና ፡ ማኅበር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ የስምምነቱን ፡ ሐሳብና ፡ ሁኔታዎች ፡ ከማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ ፍጹም ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ያላቸው ፡ ማኅበረተኞች ፡ እንዲቀበሉት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

(፫) የአክሲዮን ፡ ማኅበር ፡ ወይም ፡ ኀላፊነቱ ፡ የተወሰነ ፡ የግል ፡ ማኅበር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ስምምነቱን ፡ የማጽደቁ ፡ ሥልጣን ፡ ለአስተዳዳሪዎቹ ፡ ካልተሰጠ ፡ በቀር ፤ ለስምምነቱ ፡ የቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ ድንገተኛው ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ እንዲያጸድቀው ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

ቍ ፡ ሺ፱፻፷፭ ። በአንድነት ፡ ሳይከፋፈል ፡ ኀላፊ ፡ የሆኑ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ስላሉበት ፡ ማኅበር ፡ የሚደረግ ፡ ስምምነት ።

(፩) በአንድነትና ፡ ሳይከፋፈል ፡ ያልተወሰነ ፡ ኀላፊነት ፡ ያለባቸው ፡ ማኅበረተኞች ፡ ያሉበት ፡ ማኅበር ፡ ስምምነት ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፤ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ ስምምነቱን ፡ ላንዱ ፡ ወይም ፡ ለብዙዎቹ ፡ ማኅበረተኞች ፡ ብቻ ፡ ሊፈቅዱላቸው ፡ ይችላሉ ።

(፪) እንዲሁም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ በጠቅላላው ፡ የማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ የግዴታ ፡ ማጣራት ፡ አሠራር ፡ ይፈጸምበታል ። ስምምነቱ ፡ የተፈቀደላቸውም ፡ ማኅበረተኞች ፡ የግል ፡ ንብረት ፡ ከማጣራቱ ፡ ውጭ ፡ ይሆናል ። ስምምነቱም ፡ የማኅበሩ ፡ ንብረት ፡ ባልሆነ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የድርሻ ፡ መክፈል ፡ ግዴታ ፡ ሊኖርበት ፡ አይችልም ።

(፫) የግል ፡ ስምምነት ፡ የተፈቀደለት ፡ ማኅበረተኛ ፡ ካንድነት ፡ አላፊነት ፡ ነጻ ፡ ይሆናል ።

BACK



## አንቀጽ ፡ ፰ ።

## አጭር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

**ቍ ፡ ፲፻፷፯ ። ስለ፡አፈጻጸሙ ፡ ሁኔታዎች ።**

(፩) የከሠረው ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ከሺ ፡ ብር ፡ የማይበልጥ ፡ ለመሆኑ ፡ ባለዕዳው፡ ያቀረበው ፡ የሒሳብ ፡ ሚዛን ፡ ወይም ፡ በኋላ ፡ የተገኙ ፡ መረጃዎች ፡ የገለጹ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ የሚከፋፈለው ፡ ድርሻ ፡ ከመቶ ፡ ዐሥር ፡ ለመብለጥ ፡ የማይችል ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደ፡ ሆነ ፤ ዳኛው ፡ በሥልጣኑ ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ በገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ጥያቄ ፡ የመክሠሩ ፡ አሠራር ፡ በአጭር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ እንዲቀጥል ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ።

(፪) የከሠረው ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ወይም ፡ የሚከፋፈለው ፡ ድርሻ ፡ በንኡስ ፡ ቍጥር ፡ (፩) ከተነገሩት ፡ ገንዘቦች ፡ የበለጠ ፡ መሆኑ ፡ ከመክሠሩ ፡ አሠራር ፡ ተገልጾ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የተፈጸሙት ፡ ሥራዎች ፡ እንደ ፡ ጸኑ ፡ ሆነው ፡ የመክሠሩ ፡ አሠራር ፡ በመደበኛው ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ እንዲቀጥል ፡ ዳኛው ፡ ያዛል ።

(፫) የመክሠር ፡ አሠራር ፡ መደበኛ ፡ ደንቦች ፡ ከአጭሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ጋራ ፡ በሚስማሙበት ፡ መጠን ፡ ተፈጻሚነታቸው ፡ ይቀጥላል ።

**ቍ ፡ ፲፻፷፰ ። ስለ ፡ አጭር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ አሠራር ፡ ልዩነት ።**

አጭር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በሚፈጸምበት ፡ ጊዜ ፡—

(፩) እሽግ ፡ አይደረግም ።

(፪) የባለገንዘቦች ፡ ኮሚቴ ፡ መምረጥ ፡ ግዴታ ፡ አይደለም ።

(፫) በፍርድ ፡ ቤት ፡ መቃወሚያ ፡ ካልቀረበ ፡ በቀር ፡ ክርክር ፡ በተነሣበት ፡ ዕዳ ፡ መቃወሚያ ፡ ላይ ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

(፬) መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ማንኛውንም ፡ ግልግል ፡ ለመፍቀድ ፡ ይችላል ።

(፭) ስለ፡ ገንዘቡም ፡ አንድ ፡ ክፍያ ፡ ብቻ ፡ ይደረጋል ።

(፮) የንብረት ፡ ጠባቂውን ፡ ሒሳብና ፡ የሚያገኛቸውን ፡ ገንዘቦች ፡ የሚመለከቱ ትን ፡ ክርክሮች ፡ መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ይወስናል ።

**ቍ ፡ ፲፻፷፱ ። ያሉትን ፡ ዕዳዎች ፡ ስለ ፡ መመርመር ።**

(፩) በሒሳብ ፡ ጽሑፎች ፤ ባለዕዳው ፡ በሰጠው ፡ መግለጫና ፡ ሊገኝ ፡ በሚቻለው ፡ መረጃ፡መሠረት፡ንብረት ፡ጠባቂው ፡ የገንዘብ ፡ ጠያቂዎቹን ፡ ዝርዝር ፡ ያሰናዳል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተባለው፡ ዝርዝር ፤ አስረጂ ፡ ከሆኑ ፡ ሰነዶች ፡ ጋራ ፡ ለመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ይተላለፋል ። መርማሪውም ፡ ዳኛ ፡ ያለውን ፡ ዕዳ ፡ ካረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ በትእዛዝ ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዲሆን ፡ ያደርጋል ። ማናቸውም ፡ ሰው ፡ እንዲያውቀው፡የዕዳው፡ዝርዝርና፡ትእዛዝ፡በፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ይቀመጣል ።

(፫) ዝርዝሩና ፡ ትእዛዙ ፡ እፍርድ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ በተቀመጠ ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡

ውስጥ ፤ ንብረት ፡ ጠባቂው ፣ በረኮማንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂ ፡ ስለ ፡ ዕዳው ፡ የተሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ያስታውቀዋል ።

(፬) ዝርዝሩና ፡ ትእዛዙ ፡ እፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ በተቀመጠ ፡ በዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ተቀባይነት ፡ ያላገኙት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ለመርማሪው ፡ ዳኛ ፡ አቤቱታ ፡ ማቅረብ ፡ ይችላሉ ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ተቀባይነት ፡ ያገኙት ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎችን ፡ የሚመለከቱ ፡ መቃወሚያዎች ፡ ሌሎች ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ ሊያቀርቡ ፡ ይችላሉ ።

(፭) መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ክርክሮቹ ፡ የሚሰሙበትን ፡ ቀን ፡ ይወስናል ። ክርክሮቹም ፡ በስምምነት ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ይጣጣራል ። እንዲህ ፡ ካልሆነ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

ቁ ፡ ፲፯፻፳፱ ። የመፋለም ፡ ጥያቄዎች ።

በመፋለም ፡ ጥያቄዎችና ፡ በባለዕዳው ፡ እጅ ፡ የሚገኙትን ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ዕቃዎች ፡ ስለ ፡ መመለስ ፡ በቍጥር ፡ ፲፯፻፳፰ ፡ የተደነገጉት ፡ ውሳኔዎች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆናሉ ።

ቁ ፡ ፲፯፻፴ ። ስለ ፡ ስምምነት ።

(፩) በገንዘብና ፡ እንዲሁም ፡ በቍጥር ፡ ብልጫ ፡ ያላቸውና ፡ ድምፅ ፡ ለመስጠትም ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠያቂዎች ፡ የተቀበሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የስምምነቱ ፡ ሐሳብ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ።

(፪) መርማሪው ፡ ዳኛ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) መሠረት ፡ ዕጥፍ ፡ የሆነው ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ መገኘቱን ፡ ከመረመረ ፡ በኋላና ፡ ስምምነቱም ፡ ተገቢ ፡ መሆኑን ፡ ከገመተ ፡ በኋላ ፤ ይህንኑም ፡ በትእዛዝ ፡ አጽድቆ ፡ ለአፈጻጸሙ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ትእዛዞች ፡ ይሰጣል ። ስምምነቱን ፡ በሚፈቅደው ፡ ወይም ፡ በሚሽረው ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ የይግባኝ ፡ ክስ ፡ እንዲቀርብ ፡ አይፈቀድም ።

# ስድስተኛ ፡ መጽሐፍ ።

## መሸጋገሪያ ፡ ሕግ ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ።

ቁ ፡ ፲፯፻፴፩ ። ስለ ፡ ይርጋ ።

(፩) ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የይርጋ ፡ ዘመናቸው ፡ ያለፉ ፡ ጕዳዮች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኝ ፡ በማንኛውም ፡ ምክንያት ፡ እንደገና ፡ ሊቀሰቀሱ ፡ አይቻልም ።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ሊፈጸሙ ፡ ለሚገባቸው ፡ ተግባሮች ፡ ወይም፡ፎር ማሊቴዎች ፡ የተወሰነ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ ሲኖርና ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ የሌላቸው ፡ ነገሮች ፡ ሲሆኑ ፤ የይርጋው ፡ ዘመን ፡ የሚቈጠረው ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከጸናበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

(፫) በዚህ ፡ ሕግ ፡ የይርጋ ፡ ዘመን ፡ የተራዘመ ፡ ሲሆን ፤ የሚፈረደው ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ ያለ ፈው ፡ ጊዜ ፡ ይቀነሳል ።

(፬) የይርጋው ፡ ዘመን ፡ እንዲያጥር ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ የተደነገገ ፡ ሲሆን ፤ በቀድ ሞው ፡ የይርጋ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ይፈረድና ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት፡ ያለፈው ፡ ጊዜ ፡ ይቀነሳል ።

ቍ ፡ ሺ፻፸፪ ። የተጠበቀ ፡ መብት ።

በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተገልጾ ፡ የተመለከተ ፡ ተቃራኒ ፡ ደንብ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ይህ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የተፈጸሙ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ ሕግ፡ ከወጣም ፡ በኋላ ፡ የጸኑ ፡ ይሆናሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታዎች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ተሻሽለው ፡ በወጡት ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማሉ ።

ቍ ፡ ሺ፻፸፫ ። በውጥን ፡ ስለሚገኙ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታዎች ።

በሕጉ ፡ ላይ ፡ ተገልጾ ፡ የተመለከተ ፡ ተቃራኒ ፡ ደንብ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፤ ይህ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፤ በውጥን ፡ ያሉት ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታዎች ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ሲጸና ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በተደነገጉት ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ነጋዴዎች ፤ ንግዶችና ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ።

ቍ ፡ ሺ፻፸፬ ። የንግድ ፡ መዝገብ ።

(፩) በቍጥር ፡ ፹፯ ፡ እስከ ፡ ፻፳፪ ፡ የተደነገጉት ፡ ሕጎች ፡ የሚጸኑት ፡ ወደፊት ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በሚወጣ ፡ ማስታወቂያ ፡ ከሚነገርበት ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ ነው ።

(፪) ይህ ፡ ሕግ ፡ በንግድ ፡ መዝገብ ፡ እንዲመዘገቡ ፡ የሚያዛቸው ፡ ነገሮች ፡ ይህ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ ሲሠራበት ፡ በቈየው ፡ ልምድ ፡ መሠረት ፡ መመ ዝገብ ፡ አለባቸው ።

(፫) ይህ ፡ ሕግ ፡ ሲጸና ፡ በቍጥር፡፻፫ ፡ እና ፡ ፻፯ ፡ መሠረት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ ዝርዝሮች ፡ የሚቀርቡበትን ፡ ፎርም ፡ በንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ለተመዘገቡ ፡ የን ግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ሁሉ ፡ የንግድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይሰጣል ።

**ቍ ፡ ሺ፻፸፮ ። በንግድ ፡ መደብር ፡ ላይ ፡ ስለሚሰጡ ፡ መያዣዎች ፡ መዝገብ ።**

(፩) በቍጥር ፡ ፻፸፬ ፡ የተደነገጉት ፡ ሕጎች ፡ የሚጸኑት ፡ ወደፊት ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በሚነገረው ፡ ቀንና ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

(፪) ይህ ፡ ሕግ ፡ የንግድ ፡ መያዣ ፡ እንዲመዘገብ ፡ ባስገደደ ፡ ጊዜ ፡ በዚሁ፡ሕግ፡ ላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ዝርዝሮች ፡ ንግዱ ፡ ተቋቁሞ ፡ በሚገኝበት ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ ይመዘገባሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፻፸፯ ። ኦፊሲዬል ፡ የንግድ ፡ ጋዜጣ ።**

(፩) ኦፊሲዬል ፡ የንግድ ፡ ጋዜጣ ፡ ወደፊት ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ፡በሚወጣ፡ማስ ታወቂያ ፡ በሚነገረው ፡ ቀን ፡ ይቋቋማል ።

(፪) በኦፊሲዬል ፡ የንግድ ፡ ጋዜጣ ፡ እንዲወጣ ፡ ይህ፡ሕግ፡በሚያስገድድበት፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የሕግ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለማውጣት ፡ መብት ፡ ባለው ፡ ጋዜጣ ፡ማስ ታወቂያው ፡ ይታተማል ።

(፫) በኦፊሲዬል ፡ የንግድ ፡ ጋዜጣና ፤ የሕግ ፡ ክፍል፡ማስታወቂያ፡ለማውጣት፡ መብት ፡ ባለው ፡ ጋዜጣ ፡ እንዲታተም ፡ ሕጉ ፡ በሚያስገድድበት ፡ ጊዜ፡ በእ ንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጋዜጣ ፡ የወጣው ፡ ማስታወቂያ ፡ በቂ ፡ ይሆናል ።

**ቍ ፡ ሺ፻፸፰ ። የንግድ ፡ ማኅበር ።**

ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የተቋቋሙት ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ይህ ፡ ሕግ፡ ከወጣም ፡ በኋላ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማያንስ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ድን ጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## የገንዘብ ፡ ሰነዶችና ፡ የባንክ ፡ ሥራዎች ።

**ቍ ፡ ሺ፻፸፱ ። መሠረቱ ።**

ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የወጡት ፡ የሚተላለፉ ፡ የገንዘብ ፡ ሰነዶች፡ ከዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ጋራ ፡ የሚስማሙ ፡ ባይሆኑም ፡ እንኳ ፤ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከወጣ ፡ በኋላም ፡ የጸኑ ፡ ይሆናሉ ።

**ቍ ፡ ሺ፻፹ ። ስለ ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ።**

በዚህ ፡ ሕግ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ እንቢታ ፡ ማስታወቂያ ፡ ለማቅረብ፡ የመዝገብ ፡ ሹም ፡ ( ሬጂስትራር ፡ ) ሳያገኝ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ በዚህ ፡ ሕግ ፡ በተደነገገው ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ምስክሮች ፡ ባሉበት ፡ የእንቢታ ፡ ማስታወቂያው ፡ ተግባር ፡ ይፈጸማል ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## ኪሣራ ።

**ቍ ፡ ፲፻፹ ። መሠረቱ ።**

(፩) ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የቀረቡ ፡ የኪሣራ ፡ ነገሮች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ይፈጸማሉ ።

(፪) ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የተሾሙ ፡ የመክሠር ፡ መርማሪ ፡ ዳኞችና ፡ የከሠረ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ጠባቂዎች ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ መመረጥ ፡ የማይችሉ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ሹመታቸው ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ ይቈያል ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፩ ። የኪሣራ ፡ ተግባሮች ።**

ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ የተጀመሩ ፡ የኪሣራ ፡ ክሶች ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከጸና ፡ በኋላ ፡ በዚሁ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ይቀጥላሉ ።

**ቍ ፡ ፲፻፹፪ ። የምስክር ፡ ወረቀቶች ።**

ይህ ፡ ሕግ ፡ ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ በቂ ፡ ንብረት ፡ ባለመኖሩ ፡ ምክንያት ፡ ስለ ተዘጉ ፡ የኪሣራ ፡ ጉዳዮች ፡ የተሰጡ ፡ የምስክር ፡ ወረቀቶች ፡ የጸኑ ፡ ይሆናሉ ።

ቍ ፡ ፲ ። ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) «በመመሥረታቸው» የሚለው ፡ በመመሥረቻቸው፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፸፩ ። «በንግዱ» ፡ የተባለው « በንግድ » ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፸፯ ። አርእስቱ «የውጭ» የተባለው ፡ «የወጪ ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፸፱ ። «በመሥራት» ፡ የተባለው ፡ «በመሠራት» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፻፳ ። (ረ) « መኖርና ፡ አለመኖሩን » የተባለው ፡ «መኖር ፡ አለመኖሩን » ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፻፹፭ ። (፫) (ባለሀብት) ፡ ከሚለው ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ « ወይም » ፡ ተጨምሮ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፻፴፪ ። «በቍጥር ፡ ፪፻፶፯ ፡ የተባለው ፡ «በቍጥር ፪ሺ፶፯» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፻፴፯ ። (፩) «ስለ ፡ ሰዎት» ፡ የተባለው ፡ «ሰዎች» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፻፴፰ ። (፩) «የሌላውም » ፡ የተባለው ፡ «የሌላውን» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፻፵ ። (፩) « ስም ፡ ምልክት» ፡ የተባለው ፡ «የስም ፡ ምልክት» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፻፵፪ ። «የሚፈጸሙ ፡ ናቸው» ፡ የሚለው ፡ «የሚፈጸም፡ ነው»፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፻፵፭ ። (፪) «ሒሳብ ፡ አጣሪ» ፡ የተባለው ፡ «ንብረት ፡ ጠባቂ» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፻፵፯ ። (፪) «ማፍረስ» ፡ የተባለው ፡ «መፍረስ» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፻፵፯ ። (፪) ፡ «ሒሳብ ፡ አጣሪው» ፡ የሚለው ፡ «ንብረት ፡ ጠባቂው» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፻፶፫ ። (፩) «ከከሦስት» ፡ የተባለው ፡ «ከሦስት» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፻፶፱ ። «መደብ» ፡ የተባለው ፡ «መደብር» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፻፷፪ ። (፩) «በስምነምት» ፡ የተባለው ፡ «በስምምነት» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ከቍ ፡ ፻፷፫ ። ቀጥሎ ፡ «ክፍል ፡ ፩» ፡ የተባለው ፡ «ክፍል ፡ ፫» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፻፷፯ ። (፩) «ማመልከቻና» ፡ የተባለው ፡ «ማመልከትና» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፻፸ ። (፬) «ከመተዘገቡበት» ፡ የተባለው ፡ «ከተመዘገቡበት» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ከቍ ፡ ፻፸፯ ። ቀጥሎ ፡ «ክፍል» ፡ የተባለው ፡ «ክፍል ፡ ፫ » ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፻፸፰ ። « ለመጕደል ፡ የሚያሠጋው» ፡ የተባለው ፡ «ለማጕደል ፡ የሚያሠጋው » ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፻፺፫ ። «በአምሰኛው» ፡ የተባለው ፡ «በአምስተኛው» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፪፻፪ ። (፩) «በዋስትና ፡ የተሰጠውን ፡ እንዲያስይዝ» ፡ የተባለው ፡ «ዋስትና ፡ እንዲሰጥ» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፪፻፭ ። የመጀመሪያው ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ንኡስ ፡ ቍጥር ፡ «፩» ሆኖ ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፪፻፲ ። (፩) «በቍ ፡ ፪፻፲» ፡ የተባለው ፡ «በቍ ፡ ፪፻፳» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ቍ ። ፪፻፴፪ ። (፩) «በቍጥር፡ ፪፻፴፪» ፡ የተባለው፡ «በቍጥር፡ ፪፻፴፩» ፡ ተብሎ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፪፻፶፯ ። (፪) «በሚያጠራበት » ፡ የተባለው ፡ «በሚጣራበት » ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፪፻፶፱ ። «በቍ ፡ ፪፻፶፱» ፡ የተባለው ፡ «በቍ ፡ ፪፻፶፰» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፪፻፸፭ ። «የወጣው» ፡ የሚለው «በወጣው» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፫፻፯ ። (፬) «ለማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ ያደረጉ» ፡ የተባለው ፡ « ለማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ ርዳታ ፡ ያደረጉ» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፫፻፲፭ ። (፪) ማኅበሩን ፡ እንዲፈርስ» ፡ የተባለው ፡ «ማኅበሩ ፡ እንዲፈርስ» ፡ ተብሎ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፫፻፲፪ ። (፪) «ንኡስ ፡ ቍ ፡ » የተባለው ፡ «በንኡስ ፡ ቍ ፡ »ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፫፻፲፫ ። (፩) «ዜማንታተው» ፡ የተባለው ፡ «ዜማንታቸው» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፫፻፲፯ ። (፫) «መክፈሉን» ፡ የተባለው ፡ «መክፈሉን» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፫፻፳፩ ። «፫፻፳፪ ፡ ፫፻፳፫» ፡ የሚለው ፡ «፫፻፳፪ ፡ ወይም ፡ ፫፻፳፫» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፬፻፲፪ ። እርእስቱ ፡ መጀመሪያ ፡ «፬፻፲» ፡ የተባለው ፡ ይሰረዝ ።
ቍ ፡ ፬፻፴፫ ። እርእስቱ ፡ «የማይጼታ ፡ ወረቀቶች» ፡ የሚለው ፡ «በማይጼታ ፡ ወረቀቶች» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፬፻፵፪ ። (፩) «በቍጥር ፫፻፺፱» ፡ የተባለው ፡ «በቍጥር ፡ ፬፻፴፱ ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ከቍጥር ፡ ፬፻፵፩ ፡ ቀጥሎ ፡ «ምዕራፍ ፡ ፳» ፡ የተባለው ፡ «ምዕራፍ ፡ ፳፩ » ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፬፻፵፯ ። (፪) «የኪሣና» ፡ የሚለው ፡ «የኪሣራና» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፬፻፶፩ ። (፫) «በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) « ፡ የተባለው» ፡ « በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፪)» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

በመጨረሻው ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ንኡስ፡ ቍ ፡ « (፫) የሆልዲንጉ ፡ ማኅበር » ፡ የተባለው ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ «(፬) ፡ የሆልዲንጉ ፡ ማኅበር» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ። እንዲሁም፡ «በንኡስ፡ ቍ፡ (፩)»የተባለው፡ «በንኡስ፡ ቍ፡ (፪)»፡ ተብሎ፡ይነበብ።
ቍ ፡ ፬፻፷፱ ። (ፕሮስቼክቱስ) ፡ የተባለው ፡ (ፕሮስፔክቱስ) ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፬፻፹፯ ። «ከቍጥር ፡ ፬፻፹፩ ፡ እስከ ፡ ፬፻፺» የተባለው « ከቍጥር ፡ ፬፻፹፯ ፡ እስከ ፡ ፬፻፺ » ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፭፻፸፱ ። (፩) «ለተመከተው» ፡ የተባለው ፡ «ለተመለከተው» ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፮፻፴፱ ። (፬) «እንዲመረመር» የሚለው ፡ «እንዲመረምር» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
ቍ ፡ ፮፻፶፪ ። (፪) «በንኡርስ» ፡ የተባለው ፡ «በንኡስ» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፲፻፵፭ ። (፪) «መንግሥት ፡ የሚያቋቋመው» ፡ የተባለው ፡ (መንግሥት ፡ የሚያቋቁመው) ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፲፻፹፯ ። በመጀመሪያው ፡ ኃይለ ፡ ቃል « (፩) » የሚለው ፡ ይሰረዝ ።

ቍ ፡ ፳፻፭ ። (፪) ፡ በቍጥር ፡ «፲፻፹፱» ፡ የተባለው ፡ «፲፻፺፪» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፳፻፳፭ ። (፩) (ሠ) (ቍጥር ፡ ፲፻፺፫) ፡ የተባለው ፡ (ቍጥር ፲፻፺፭) ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፴፻፸፯ ። (፩) «በሚሰማበት ፡ ጊዜ» ከሚለው ፡ ቀጥሎ» «ወይም ፡ ያለም ፡ እንደሆነ» የሚለው ፡ ተጨምሮ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፴፻፹ ። (፬) «በፍትሐ ፡ ብሔር» ፡ የሚለው ፡ «በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፴፻፹፩ ። «መመረጥ» የሚለው ፡ «መምረጥ» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፴፻፹፬ ። (፩) «በሚለጠፉ» ፡ የተባለው ፡ «በሚለጠፉና ፡ » ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፴፻፹፰ ። (፩) «ይህ» ፡ የሚለው ፡ ትሥርዝ ፡ «የመክሠር ፡ ማስታወቂያ» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፴፻፺፪ ። (፪) «ለፍርድ ፡ ቤት» ፡ የሚለው ፡ «ለፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፵፻ ። (፪) «አስቀድሞ» ፡ ከሚለው ፡ ቀጥሎ ፡ «በነጻ» ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ተጨምሮበት ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፵፻፪ ። (፩) «ለፍርድ ፡ መዝገብ ፡ የሚለው ፡ «በፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ቤት» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፵፻፭ ። (፪) እና ፡ በቍ ፡ ፵፻፯ ፡ (፩) «በኅብረቱ» ፡ የተባለው ፡ በንብረቱ ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፵፻፯ ። (፩) «በሁለተኛው» ፡ የተባለው ፡ «በአንደኛው» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
(ለ) «ሕጋዊ» የሚለው ፡ «ከሕግ» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።
(ረ) «ያለም ፡ እንደ ፡ ሆነ» ፡ ከሚለው ፡ ቀጥሎ « ከንግዱ ፡ መደብር ፡ ጋራ » ፡ የሚል ፡ ተጨምሮበት ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፵፻፱ ። (፪) «ገንዘቡን» ፡ የሚለው ፡ «ንብረቱን» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፵፻፳፫ ፡ ፵፻፴፩ (፪) ፡ ፵፻፴፪ ፡ ፵፻፴፬ (፪) ፡ ፵፻፵፭ ፡ ፵፻፵፯ (፩) ፡ ፵፻፵፫ ፡ ፵፻፵፬ ፡ ፵፻፳፭ ፡ ፵፻፳፯ ፡ ፵፻፳፬ ፡ ፵፻፷፬ ፡ ፵፻፸፬ ፡ ፵፻፺፯ ፡ ፵፻፲፬ (፫) ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ «ኅብረት» ፡ መሠረተ ፡ ቃሉ ፡ «ኅ» በ «ን» ፡ እየተለወጠ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፵፻፴፫ ። (፫) «በንኡስ ፡ ቍ (፩) ፡ እና ፡ (፪)» ፡ የሚለው ፡ «በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) ፡ ወይም ፡ (፪) » ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ፵፻፵፫ ። «በእንደራሴው ፡ ረዳትነት » የሚለው ፡ «እንደራሴው ፡ ባለበት » ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ሺ.፵፯ ። አርእስቱ ፡ «ማስጸፍ» ፡ የተባለው ፡ « ማጸፍ ፤ በንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) ፡ «ማስጸፍን »፡ የተባለው ፡ «ማጸፍን» ፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ሺ.፶፯ ። አርእስቱ ፡ «ስለ፡ ማቅረብ» ፡ የተባለው ፡ «ስላለማቅረብ»፡ ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ሺ.፷፫ ። (፩) በኪሣራው ፡ «ላይ»፡ የሚለው ፡ በከሣራው ፡ ንብረት ፡ «ላይ» ፡ ተብሎ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ሺ.፸፯ ። (፩) «በኮሚስዮኔሩ» ፡ የተባለው «በወኪሉ» ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ሺ.፺፯ ። የመጀመሪያው ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፩) ፡ ሆኖ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ሺ.፹፯ ። (፫) በመጀመሪያው ፡ መሥመር ፡ «ንኡስ ፡ ቍ ፡ (፬)» ፡ የተባለው ፡ ንኡስ ፡ ቍ፡ (፪) ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ሺ.፻፳፯ ። «ሺ.፻፩» የተባለው ፡ «ሺ.፩» ተብሎ ፡ ይነበብ ።

ቍ ፡ ሺ.፻፳፱ ። (፪) «ሺ.፻፷፩» ፡ የተባለው ፡ «ሺ.፻፳፩» ተብሎ ፡ ይነበብ ።